www.zeyeneta.com

ሁለቱ ኪዳናት

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ

ወደ ዕብራውያን የጻፈውን መልእክት

መሠረት በማድረግ

አዘጋጅ፡- ሙሪዬታ ኃየሱም በርሄ

አርታዒ፡- ዲያቆን ብርሃኑ አድማስ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

በሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ

ማኅበረ ቅዱሳን

ሕግና ሥርዓት
አሳታሚ አለበ

www.zeyeneta.com

©ማኅበረ ቅዱሳን

የመጀመሪያ እትም ፲፱፻፺፮ ዓ.ም
ሁለተኛ እትም ፳፻፪ ዓ.ም
ሦስተኛ እትም ፳፻፭ ዓ.ም
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
ALL RIGHTS RESERVED

ይህ መጽሐፍ
በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰንበት ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ
በማኅበረ ቅዱሳን
ኢዲቶሪያል ቦርድ ታርሞ ተስተካክሎ የተፈቀደ ነው::

አድራሻ:-

በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ
በሰ/ት/ቤቶች ማ/መምሪያ
ማኅበረ ቅዱሳን
ፖ.ሳ.ቁ 80078
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

Email:- lemat@eotc-mkidusan.org
Website;-www.eotc-mkidusan.org

የኮምፒውተር ጽሑፍና ቅንብር
የኅትመትና ኤሌክትሮኒክ ሚዲያ ምኅ ክፍል

ምስጋና

ይህ መጽሐፍ በመሪጌታ ኃየሎም በርሄ ሲዘጋጅ በተያቄና መልስ መልክ ነበር:: መጠኑም ከዚህ ያነሰ ነበር:: የማኅበሩ የኢዲቶርያል ቦርድ በሰጠው ማረሚያና ተጨማሪ ሃሳብ መሠረት መጽሐፉ ሰፋ ብሎ መዘጋጀት አስፈለገው::

ሁለተኛው ሥራ ብዙ ማንበብ፣ ማቀናበርና ነጥቦችን ለይቶ በየምዕራፉ ሚውጣትን ይጠይቅ ነበር:: ይህ ታላቅ ተልዕኮ የተሰጠው ዲያቆን ብርሃኑ አድማሴ ጊዜውን ሠውቶ አሁን በቀረበበት መልክ ሰላቀናበረው ከፍላችን ምሥጋናውን ያቀርባል::

በሌላም በኩል ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት በዋና ማጣቀሻነት የተጠቀም ንባቸውን መጻሕፍት በመላክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉልንን በአውሮፓና በአሜሪካ የሚገኙ የማኅበረ ቅዱሳን አባላትን ብጸዐ/ክ/እግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን::

የኅትመት ዝግጅት ማስተባበርያ ክፍል

www.zeyeneta.com

መግቢያ.....11

ምዕራፍ: አንድ

1. በሥጋዌ የተናገረን የባሕርይ ልጁ ከሁሉ ይበልጣል.....19

1.1እግዚአብሔር ከጥንት እስከ አሁን ተናገረን.....19

1.2 በልጁ ተናገረን.....25

1.3 የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ.....31

1.4 ሁሉን በሥልጣኑ ቃል ደገፈ.....35

1.5 ኃጢአታችንን በራሱ አነጻ.....39

1.6 በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ.....43

1.6.1 አቅጣጫ.....46

1.6.2 መንገል.....46

1.6.3 ክብረ ልዕልና.....47

1.6.4 ሥልጣን ቀኜ ተብሏል.....50

1.7 የአባትነትና የልጅነት ምሥጢር.....59

1.7.1 በፍጡራን መካከል.....60

1.7.2 በፈጣሪ በፍጡርና መካከል.....65

1.7.3 አባትነትና ልጅነት በፈጣሪ ዘንድ /በምሥጢረ ሥላሴ/.....66

1.7.4 በሹር.....69

1.8 በደስታ ዘያት ቀባህ.....79

1.8.1 የጸጎችና የቅብዐቶች ታሪክ.....80

1.8.2 የጸጎች እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘን.....81

1.8.3 የቅብዐቶች እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመመዘን.....83

1.8.4 ተቀባ ማለት ምን ማለት ነው.....91

ምዕራፍ ሁለት

2. ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለሙን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል.....93

2.1 አብልጠን እንጠንቀቅ.....93

2.2 ታስበው ዘንድ ሰው ምንድን ነው?.....97

ምዕራፍ ሦስት...

3. ክህነት.....108

3.1 የክህነት ትርጉም.....108

3.2 ክህነተ መልከ ጼዴቅ.....110

3.2.1 መልከ ጼዴቅ ማን ነው?.....110

3.2.2 የመልከ ጼዴቅ የዘር ሐረግ.....111

3.2.3 ሥርዓተ ሢመተ ክህነቱ ለመልከ ጼዴቅ.....113

3.2.4 ነገረ መልከ ጼዴቅ በዕብራውያን.....115

3.3 የብሉይ ኪዳን ክህነት /ክህነተ ሌዋውያን/.....119

3.3.1 ክህነቱ ምን ዓይነት ነበር?.....120

3.3.2 የብሉይ ኪዳን ክህነት ተቀባይ ምን መሆን ይጠበቅበታል?.....123

3.3.3 የብሉይ ኪዳን ካህናት አገልግሎት ምንድን ነው?..129

3.3.4 ሥርዓተ ሢመቱ/የአሿሿማቸው ሥርዓት/ ምን ይመስል ነበር?.....132

3.3.5 የሹመቱ ደረጃ.....134

3.3.6 የሊቀ ካህናቱ ልዩ አገልግሎት ምን ነበር?.....138

3.4 ክህነተ እግዚእ.....139

3.4.1 የጌታችንን ክህነት ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?....140

3.4.2 የጌታችን ክህነት በመልከ ጼዴቅ,ክህነት ስለምን ተመሰለ?.....143

www.zeyeneta.com

3.4.3 ጌታችን ስለ ምን ሊተ ካህናት ተባለ?.....144
3.4.4 የጌታችን ሊተ ካህናትነት ፍጹም ልዩ ነው.....149
3.4.5 በሙሉ ሌሎች ካህናት አያስፈልጉምን?.....151
3.5 ክህነተ ሐዋርያት/የሐዲስ ኪዳን ክህነት/.....152
3.5.1 ክህነቱ ምን ዓይነት ነው?.....152
3.5.2 ሥርዓተ ክህነትና አገልግሎት 159
ምዕራፍ አራት
4. ልደት.....160
4.1 ትርጉም 160
4.1.1 ሰንበት 160
4.1.2 ክብዓን.....166
4.1.3 መንግሥተ ሰማያት 174
4.2 የክብዓን መንገድ መሪ ሙሴ ለመንግሥተ ሰማያት መሪ ምሳሌ ነው 176
4.3 ወደ ዕረፍቱ እንደ ገባ ምን እናድርግ?.....18
4.4 እግዚአብሔር አዳምን ወደ ዕረፍቱ እንዲገባ ስለምን ፈቀደለት?.....186
4.5 የምዕራፉ የማጠቃለያ ጭብጥ 188
ምዕራፍ አምስት
5. አማላጅ.....190
5.1 ትርጉም 190
5.2 በምልጃ ወቅት የሚሳተፉ አካላት 191
5.3 ምልጃ ለምን ያስፈልጋል?.....192
5.4 አማላጅ ለምን ይግልጻል?.....198
5.5 ጌታችን አማላጅ አይደለም.....205
5.6 ምን ማለት ነው?.....209
ሀ. ጸሎትንና ምልጃን አቀራረብ 209
ለ. «የአዲስ ኪዳን መካከለኛ» ምን ማለት ነው.....210
ሐ. ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን ማለትስ ምን ማለት ነው 214
መ. «ስለኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» የሚለውስ?.....218
5.7 ማጠቃለያ.....222
ምዕራፍ ስድስት
6. መሠረት 225
6.1 መሠረት የተባለው ምንድን ነው?.....225
6.2 መሠረትነቱ ለማን ነው? 228
6.3 ደግመን እንመሥርት 232
6.3.1 በትምህርት 233
6.3.2 በምግባር 237
6.3.3 ቅዱሳንን በማገልገል 238
6.4 እነርሱን በንስሐ ማደስ የማይቻል ነው.....244
ምዕራፍ ሰባት
7. ሕግና ትእዛዝ 248
7.1 ሕግ 248
7.1.1 ሕገ ጠባይዊ 248
7.1.2 ሕገ ሥጋዊ 249
7.1.3 ሕገ መንፈሳዊ 251
7.1.4 ሕገ እግዚአብሔር.....253
7.1.5 አሪት 255
7.1.6 ወንጌል /ሕገ ወንጌል/ 257

www.zeyeneta.com

7.2 ትእዛዝ 258
7.2.1 ጊዜያዊ ትእዛዝ 259
7.2.2 በሳለማዊ ትእዛዝ 260
7.3 የተሻረችው ትእዛዝ 263
7.4 መጻሕፍት አልተሻሩም 262

ምዕራፍ ስምንት

8. ኪዳን 266
8.1 ትርጉም 266
8.2 የኪዳኑ ዓይነት 268
8.2.1 ብሉይ ኪዳን 268
8.2.2 አዲስ ኪዳን 21
8.2.3 እግዚአብሔር ለወዳጁ የገባው ኪዳን 2
8.3 እግዚአብሔር ሰውና ቃል ኪዳን 285
8.4 ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ኪዳን የጻፈበት ምክንያት 288

ምዕራፍ ዘጠኝ

9. መቅደስ የእግዚአብሔር መገለጫ 292
9.1 ትርጉም 292
9.2 አመሠራረት 295
9.3 የመቅደስ ሥራ እድገት 296
9.3.1 ደብረ ሲና 29
9.3.2 ደብተራ አሪት 298
9.3.3 የሰሎሞን ቤተ መቅደስ 299
9.3.4 ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም 303
9.3.5 በሰው እጅ ያልተተከለች ቅድስተ ቅዱሳን /መስቀል/ 30
9.3.6 የጊጋው ዙፋን/ ቤተ ክርስቲያን ቅድስት/ 309

ምዕራፍ አሥር

10. «መሥዋዕት» 318
10.1 መሥዋዕት በሕገ ልቡና 318
10.2 መሥዋዕት በሕገ ኦሪት 321
10.2.1 መሠረታዊ የመሥዋዕት ዓይነቶች 320
10.2.2 መሥዋዕተ አሪት ከአቀራረቡ አንጻር 324
10.2.3 በአሪቱ መሥዋት የተገኘው ጥቅም 327
10.2.4 መሥዋዕቱ ምንድን ነበር? 328
10.3 መሥዋዕተ ወንጌል 330
10.3.1 አዲሱ መሥዋዕት ለምን አስፈለገ? 330
10.3.2 የሐዲሱ መሥዋዕት መሥዋዕቱ ምን ዓይነት 332
10.4 መሥዋዕተ ምእመናን 340

ምዕራፍ አሥራ አንድ

11. እምነት 346
11.1 ትርጉም 347
11.2 እምነት ከመታመን አንጻር 347
11.2.ሀ የአጋንንት እምነት 347
11.2.ለ የክርስቲያኖች እምነት 348
11.3 ማጠቃለያ 356

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

12. ተስፋ ወንጌል መንግሥተ ሰማያት 358
12.1 ገነት 358
12.2 መንግሥተ ሰማያት 359
12.3 ለተስፋችን እንድንበቃ ምን እናድርግ? 363

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

13. ዋናዎቹን አስቡ 369

www.zeyeneta.com

ጠቅላይ ቤተክህነት



ይህ መጽሐፍ ወጣቶችን በትምህርተ ሃይማኖት፣ በፍቅረ እግዚ አብሔርና በቅንዓተ ቤተ ክርስቲያን ለመቅረጽ ለተጋው፣ የ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የወጣቶች ሐዋርያ፣ በቃሉም በኑሮውም አስተምሮ ብዙ አርቶዶክሳውያን መምህራን ወንጌልን ላፈራው ለጋሼ ግርማ ከበደ /1951 -1989 ዓ.ም/ ይሁን::

ማኅበረ ቅዱሳን

መግቢያ

ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ነው:: 2ኛጴጥ.1÷20:: በመሆኑም የቅዱሳት መጻሕፍቱ ዓላማ የእግዚአ ብሔር ዓላማ ነው:: የተጻፉትም የእግዚአብሔርን ድምፅ ለሚሰሙት ሁሉ ነው:: ይሁን እንጂ ከጊዜያት በኋላ ሰዎች ፍልስፍናቸውንም ሆነ ኑፋቄያቸውን ወደ ቤተ ክርስቲያን አሾለክው ማስገባት በጀመሩ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍትን ከዚህ አደጋ ለመጠበቅ ሠፍረው ቆጥረው አስረክበዋል፡ ለየመጻሕፍቱም የመጠሪያ አርእስት ሰጥተዋቸዋል::

ከእነዚህም መጻሕፍት ውስጥ አንዱ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ዕብራውያን ነው:: መልእክቱን የጻፈው ማን ነው? የተጻፈላቸው ሰዎች እነማን ናቸው? የመጽሐፉ ጭብጥ /ዐቢይ መልእክት/ ምንድን ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መስጠቱ መጽሐፉን በቀላሉ ለመረዳት ይጠቅማል:: ይልቁንም በጸሐፊው ማንነት ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ስለሚሰነዘሩ ይህንንና ቀደም ብለው የተነሡትን ጥያቄዎች በመጠኑ እንመለከታለን::

1. <u>የመጽሐፉ ሁኔታዎች</u>

ሀ/ <u>ጸሐፊው:-</u> ቅድስት አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ቅዱስ ጳውሎስ መሆኑን አምና ትቀበላለች:: በርግጥ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጸሐፊው ራሱን አልገለጠም፣ ከዚህም የተነሣ የተለያዩ አስተያየቶች ወይም ግምታዊ ንግግሮች ይደመጣሉ፣ ይሁን እንጂ በመጽሐፉ ውስጥ ስለ ጸሐፊው ማንነት የሚጠቁሙ መረጃዎችንና የቤተ ክርስቲያንን ትውፊት በበጎ ጎሊና ለሚቀበል ሰው ብዙም አዳጋች አይሆንም::

ጸሐፊው ቅዱስ ጳውሎስ ነውን? የሚለውን ጥያቄ ካነሡት

www.zeyeneta.com

ውስጥ ከ130–200 ዓ.ም የነበረው ሄረኔዎስ (Irenaeus) እና ከ170–236 ዓ.ም የነበረው ሒፖሊተስ (Hippolytus) ተጠቃሾች ናቸው። እኒህም ሆኑ ሌሎቹ ጸሐፊው ቅዱስ ጳውሎስ አይደለም ያሰኛቸው በሌሎች መልእክታቱ ላይ እንደ ገለጸው በዚህም ራሱን አለመግለጹ ነው።

በመጽሐፉ ስሙን ያልጠቀሰበት ዐቢይ ምክንያት ቢኖርም እርሱ እንደ ጻፈው የሚጠቁሙ መረጃዎች ግን አሉ። እነዚህም «ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደ ተፈታ ዕወቁ።» /ዕብ. 12÷23/ የሚለውና «ከኢጣልያ ያሉት ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።» የሚሉት ናቸው። ዕብ. 13÷24። እነዚህም ጸሐፊው ከጢሞቴዎስ ጋር ያለውን ቅርብ ግንኙነትና በጣልያን በአገልግሎት ላይ እያለ እንደ ጻፈው የሚያመለክቱ ናቸው። ይህ ጥያቄ በተነሣበት በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ መጽሐፉ «የበርናባስ ነው» የሚል አሳብ ያቀርብ የነበረው ጠርጡለስ (Tertulian ከ160–225 ዓ.ም) ነበር።

ይሁን እንጂ በሌላም በኩል አበው ትውፊት መሠረት በማድረግ ከ185–254 ዓ.ም የነበረው አርጌንስ (Origen) እና ከ150–215 ዓ.ም የነበረው ቀሌምንጦስ ዘእስክንድርያ (St.Clement of Alexandria) መጽሐፉ የቅዱስ ጳውሎስ እንደሆነ ገልጠዋል። በኋላም በአራተኛው ክፍለ ዘመን ከተነሡት ሊቃውንት ውስጥ ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ እና ቅዱስ አትናቴዎስ መጽሐፉን የቅዱስ ጳውሎስ እንደሆነ ጽፈዋል። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጸሐፊ የነበረው አውሳብዮስም በ340 ዓ.ም መጽሐፉን ከቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ዝርዝር ውስጥ አካትቶታል። በኋላም በ397 ዓ.ም ቅርጣግና (Chartage) ላይ የተካሄደው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤም መጽሐፉን የቅዱስ ጳውሎስ እንደሆነ ተቀብሎታል፡ በቀኖናም ደንግጉት አልፏል።

ቤተ ክርስቲያንም ከላይ የተጠቀሱትን ሊቃውንትና በቅርጣግና ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት የተወሰነውን ውሳኔ ተቀብላ ስለምትጠቀምበት መልእክቱ የቅዱስ ጳውሎስ ነው በማለት ተቀብላዋለች። «ወደ ዕብራውያን የተላከ የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት» በማለትም ትጠራዋለች። የቤተ ክርስቲያን ትውፊትም የሚያረጋግጠው ጸሐፊው ቅዱስ ጳውሎስ እንደሆነ ነው።

በመሠረቱ ቤተ ክርስቲያን የጽሑፉን ቅድስናና የቤተ ክርስቲያን ድምፅ መሆኑን መርምራ የምትቀበል በመሆኗ ስለ ጸሐፊው ያላት አሳብ ሁለተኛ ጉዳይ ነው። በመጀመሪያ ጽሑፉ የቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ አምነትና ክርስቲያናዊ ምግባር የጠበቀ መሆኑና ምእመናንን ለመንግሥተ እግዚአብሔር ማብቃቱ የሚታይ ሲሆን የጸሐፊውን ማንነት ማወቅና ማረጋገጥ ሁለተኛው ጉዳይ ነው። ይህ ሲባል የጸሐፊው መታወቅና አለ መታወቅ እያስፈልጋችም ለማለት አይደለም፣ ነገር ግን ጽሑፉ ቤተ ክርስቲያንን እስከ ጠቀመ ድረስ የቅዱስ ጳውሎስ ወይም የቅዱስ ጴጥሮስ መሆን እነርሱንም የማያጣላ እኛንም ከጽድቅ የማይከለክል ስለሆነ ጉንጭ አልፋ ክርክር አትከራከርበትም። ይልቁንም የእኛ ቤተ ክርስቲያን አበውና ሊቃውንት ይህን እንደ አብነት በመቁጠርና ክብርን በመጥላት በተሰጣቸው ጸጋ የጻፏቸው ጽሑፎች ላይ ስማቸውን ሳይገልጡ በትጎትና ክብርን በመሸሽ ያለፉት ብዙዎች ናቸው።

ለ/ የመጽሐፉ የአጻጻፍ ባሕርይ

የጽሑፉን ሙስጣዊ ባሕርይ ስንመለከት ከሌሎች የቅዱስ ጳውሎስ መልእክታት ለየት ያለ ባሕርይ እንዳለው እንመለከታለን። በቅርብ ጊዜ የተነሡ የነገረ መለኮት ሊቃውንት (theological scholars) ይህን ልዩ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ቅዱስ ጳውሎስ

www.zeyeneta.com

አልጻፈውም እስከ ግለት ደርሰዋል። ግን ጻፈው ለሚለው ጥያቄም «አጵሎስ» ይሆናል የሚል መልስ ይሰጣሉ። የዚህ አሳብ ጀማሪና በአደባባይም የለፈፈው ማርቲን ሉተር ነው። እነዚህ ሰዎች «አጵሎስ» ነው ለሚሉት አስረጂ አድርገው የሚያቀርቡት አጵሎስ የእስክንድርያ አይሁድ በመሆኑ ምሁረ አሪት ነው የሚል ነው። ከላይ እንደተገለጸው ግን አጵሎስ በኢጣልያ ናሮ ለማስተማሩ ምንም መረጃ የለም። በርግጥ አጵሎስ ቢታናሽ እስያ፣ በኤፌሶንና በቆሮንቶስ እንዳስተማረ ተዘግቧል። ያም ሆነ ይህ ለዚህ አሳብ ያበቃቸው ዋናው የጽሑፉ ባሕርይ ስለሆነ የአጻጻፉን ባሕርይ እንመለከታለን።

1ኛ. ጥልቅ የአሪት ዕውቀትን ይዟል፦ መጽሐፉን ስንመለከት ጸሐፊው ሕግንም፣ ነብያትንም መጻሕፍትንም (writtings) እጅግ ጠን ቅቆ የሚያውቅ እንደ ነበር መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንጻር አጵሎስን ከጳውሎስ ያንሣል ማለት አይቻልም፣ «በመጻሕፍት ዕውቀትም የበረታ ነበር።» /ሐዋ.18÷24/ ተብሎ ተመስክሮለታልና። ይሁን እንጂ ይህ ዕውቀት አለው በሚል ጸሐፊውን እርሱ ነው ማለት አይቻልም። መልእክቱ የአሪት ዕውቀት እያላቸው በሕጋቸው መዝሠዝን ላይተዉ፣ ያመኑ በመምሰል ከክርስትና እንደገና እምፈገፈጉ ያሉትን ዕብራውያንን ከክርስትና ትምህርት እንዳይወጡ ለማድረግ የተጻፈ ነው።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እጅግ የሚያከብሯቸውን አብርሃምን፣ ሙሴንና ዳዊትን እንዲሁም ሌሎቹን አበው እያነሣ የጊታችንን መገለጥ ይጠባበቁ እንደ ነበርና ጌታችንም የእነርሱ አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል። ከዚህ በኋላ ከሌዋውያን ከመልከ ጼዴቅ እንደሚበልጥ፣ መሥዋዕቱም አንድ ጊዜ ተርቦ ዘላለም የሚያድን መሆኑን፣ በአጠቃላይ አሪት የወንጌል መርገፍ ብሉይ ኪዳንም የአጼ ቅዳን ጥላ እንደሆኑ፣ የመጀመሪያዎቹ ሁሉ ሊመጣ ስላለው ምሉዕ እንጂ አማናዊው አዲሱ እንደሆነ የተገለጠበት መጽሐፍ

ነው።

2ኛ/ ከሌሎቹ መልእክታት በአቀራረብ መለየቱ፦ በሌሎቹ መልእክቶቹ ላይ አሐፊው እርሱ መሆኑን ገልጧል። በዚህ መጽሐፍ ላይ አልገለጠም። በዚህ ምክንያት ጭምር ነው የእርሱ ቢሆን ስሙን ይገልጥ ነበር የሚሉት። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ያደረገው ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ነው። ምክንያቱም በወቅቱ ከአሕዛብነት ወደ ክርስትና በተመለሱትና ከአይሁድነት ወደ ክርስትና በተመለሱት መካከል ሰፊ ልዩነት የነበረበት ወቅት ነው። በተለይም ከይሁዲነት ወደ ክርስትና የመጡት ከአሕዛብ የተመለሱትን ክርስቲያኖች ጥምቀት ያለ ግዝረት፣ ወንጌልም ያለ አሪት አይጠቅሙምና መገዘር አለባችሁ፣ ሥርዓተ አሪትንም ሳታጓድሉ መፈጸም አለባችሁ የሚሉበት ወቅት ነበር።

በዚህ ወቅት ክርክሮች እየተፋፋሙ ሲመጡ የአሕዛብ አስተማሪዎች የሚባሉት በርናባስና ጳውሎስ ከይሁዲነት ተመልሰው የሚያስቸግሩትን ተከራክሯቸው። ሰዎቹ ግን አንቀበልም ስላሉ ሽማግሌዎች ተመርጠው ወደ ኢየሩሳሌም ተላኩ። ሐዋ.15÷1። በዚህ ክርክር ምክንያት የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በ50 ዓ.ም ተካሄደ። በጉባኤው የተወሰነው «ለጣዖት ከተሠዋ፣ ከደምም፣ ከታነቀም፣ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና፣ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ።» ኦሚል ነበር። ሐዋ.15÷28-29።

በዚህ ወቅት ከይሁዲነት የተመለሱት ክርስቲያኖች የአባቶቻችንን ሥርዓትማ ፈጽመን እንዴት እንጥላለን? ይልቁንም የግዝረትንና የመሥዋዕትን ነገር ማለት ያፈገፍጉ ጀመር። ሌሎቹ ደግሞ ያለነዚህ ወንጌልና ጥምቀት አይረቡም በማለት ያስተምሩ

www.zeyeneta.com

ጀመር። በዚህን ጊዜ ቅዱስ ጳውሎስን ወደ ክርስትና ገብተው ካፈ
ፈጉት አይሁድም ሆነ ካላመኑት አይሁድ ተጨማሪ ጥላቻ ገጠመው።

እነዚህን ሰዎች ለማስረዳት መልእክት መጻፍ ነበረበት።
ጽሑፉን ሲልክ ግን «ከቅዱስ ጳውሎስ የተላከ» ቢለው ኑሮ ስንኪን
ሊሰሙትና አስቀምጠውትም ሰእኛ ሊተርፍ ቀርቶ ወደ ጉባኤም
ባላቀረቡት ነበር። ቅዱስ ጳውሎስ ስሙን ሳይገልጽ በጥበብ ስለ
ጻፈውም ብዙ ሰዎችን ጠቅሟል። በአጠቃላይ መልእክቱ የተጻፈው
በ60 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ ይገመታል። ይህም ቅዱስ ጳውሎስ
ሦስተኛውን ጉዞ ከአጠናቀቀ በኋላ በጦር ሆኖ የጻፈው ነው። በዚህ
ጉዞው ወቅት በኤፌሶን እያለ የመጀመሪያዪቱን መልእክቱን ለቆሮንቶስ
ሰዎች ጽፏል። ለጽሑፉም መነሻ የሆነው በእነርሱ ዘንድ ያለው እኔ
የክርስቶስ ነኝ፣ እኔ የኬፋ ነኝ፣ እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔ የአጵሎስ ነኝ
የሚለውን ክፍፍል በመስማት ነበር።

በዚህ ወቅት በኤፌሶን ያገኘውን አጵሎስን ወደ እነርሱ እንዲ
ሄድ ለምኖት እምቢ እንዳለው ጽፎአል። 1ኛቆሮ.16÷12። ይህ
የሚያመለክተው መልእክቱ በተጻፈበት ወቅት አጵሎስ ኢጣልያ
እንዳልነበረ የሚያስገምት ነው፡ ቅዱስ ጳውሎስ በዚያ ትቶት
ሄዷልና። ይልቁንም «ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደ ተፈታ ዕወቁ፥
ቶሎ ብሎም ቢመጣ ከእርሱ ጋር አያችኋለሁ።» ዕብ.13÷23
የሚለው ጸሐፊው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ መሆኑ ዐቢይ አስረጂ ነው።

ሐ. በዚህ በዕብራውያን መልእክት መነሻነት የተጻፈው ይህ
መጽሐፍ

መጀመሪያ ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ ስለተነሡት ችግሮች
ምክንያት የጻፈው መጽሐፍ ለቀድሞዎቹ ብቻ ሳይሆን አሁን
ላሉትም የማዕዘን ራስ ሳይሆን የማሠናከያ ድንጋይ ሆኖባቸዋል።
ቅዱስ ጳውሎስ ተፈጸሙ አለፉ ያላቸውን ሕገ ግዝረትን፣ ሕገ
መንጻትን፣ ሕገ መሥዋዕትንና የመሳሰሉትን ከቀዋሚያን ሕግጋተ

እግዚአብሔር መለየት ያቃታቸውና ስለ አምልኮተ እግዚአብሔር
ሥርዓት የሌላቸው ሰዎች ዘላለማዊውንና ሕያውን መሥዋዕት
ሊገነዘቡት ስላልቻሉ ይልቁንም እነ ሳጥናኤል በወደቁበት እንቅፋት
ሊላውንም ለማሰናከልና ለመጣል ስለሚሳደፉ ከምሥጢር ውትያኖስ
ከማይለካው የሊቃውንት ሰውተት የተፈለፈለና ለግንዛቤ ያህል
የተጻፈ ነው። የዕብራውያን መልእክት ዋናው ሥጉየ የወልደ እንለ
እመሕያው ክርስቶስን የባሕርይ ልዕልና ተገንዝበን በእርሱ
እንድናምን ነው። ስለዚህ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ
በሁለት ኪዳናት መሐል ያለውን ውሕደት እያሳየ የወንጌልን
መብለጥ የሚናገር መጽሐፍ ነው።

ከነብያት ከመላእክት ይበልጣል በሚል ጀምሮ፣ በክህነቱ፣
በመሥዋዕቱ፣ በሕጉ፣ በሚያወርሰን መካነ ዕረፍት፡ በኪዳኑ፣
በገባበት መቅደስ /መስቀል/፣... ይበልጣል፡ ስለዚህ ከሙሴ ፈቀቅ
ያሉት ከተቀጡ ወይንም ከቅጣት ካላመለጡ ከወልደ እግዚአብሔር
የምታፈገፍጉስ እንዴት ታመልጣላችሁ? ከአቤል እስከ ዘካርያስ ያሉ
አበው ተስፋቸውን /ገነትን/ እንኳን ሳያገኙ በእምነት ተመሰገኑ፣
እናንተ ግን ገነት በደሙ ተከፍታላችሁ ሳለ እንዴት ወደ አለማመን
ትመለሳላችሁ? እያለ በማነጻጸር የጻፈላቸው ናት።

ዳግመኛም የአሪቱ መሥዋዕት ሳይታጐል ዕለትን፣ ሠርቀ
ወርኃን፣ ሰንበትንና የዓመት በዓልን ተከትሎ የሚቀርብ በዚያውም
ላይ ፍጹም ድኅነተ ነፍስን የማያሰጥ ነበር። ይህ ግን /የክርስቶስ
መሥዋዕት ሆኖ መቅርብ/ አንድ ጊዜ ቀርቦ ሳለ ከአዳም መፈጠር
እስከ ዕለተ ምጽአት ያሉትን ያዳነና ማዳን የሚችል ነውና ደኅና
መሥዋዕት ነው እያለ ምሥጢረ ሥጋወደሙን፣ የባሕርይ ክህነቱንም
ከአሪቱ ጋር በማነጻጸር ዘርዘር አድርጉ ልቅርቧል። ከዚህ አንጻር
የዚህ መጽሐፍ አቀራረብ ቁጥር በቁጥር እያንዳንዱን ኃይለ ቃል

www.zeyeneta.com

በመተርጉም አይደለም:: በዚህ መንገድ «የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው» በሚል ርእስ በሊቃውንት ተተርጉሞ የተዘጋጀ መጽሐፍ ስላለ አዲስና ሌላ ተጨማሪ የትርጓሜ መጽሐፍ አያስፈልግም::

• የዚህ መጽሐፍ አጻጻፍ ግን ስለ አንድ ነገር የሚናገሩትንና በተለያዩ ምዕራፎች ላይ ያሉትን አሰባስቦ በአንዱ ምዕራፍ ሥር በመጨረስና በዚያ ዙሪያ ሰፋ ያለ ግንዛቤን በማቅረብ ነው:: ለአብነት ያህልም በዕብራውያን መልእክት ካሉት 13 ምዕራፎች ቢያንስ በስምንቱ ውስጥ ስለ ክህነት ተጽፏል:: በዚህ መጽሐፍ ግን «ክህነት» ራሱን የቻለ አንድ ምዕራፍ ሆኖ ምዕራፍ ሦስት ላይ ተጠናቅቋል:: ሌሎቹም በዚሁ መንገድ ተጽፈዋል:: ለየት ባለ መንገድ የተገለጸው ምዕራፍ አንድና በመጠኑ ምዕራፍ ሁለት ሲሆኑ በተለይ ምዕራፍ አንድ እያንዳንዱ ቁጥር ለብቻው ተተትኖ ተጽፎአል፤ ምክንያቱም የብዙ መናፍቃን መነሻና መሰናክያ ጥቅሶች በዚህ ሥር ስለሚገኙ ነው::

ይህ መጽሐፍ ለአንባብያን መጠነኛ ግንዛቤ ለማስጨበጥና ከመናፍቃን ትሰጣ ምአመናን እንዲጠበቁና ወደፊትም «የአንድምታ ትርጓሜ» እያሉ ቢያወጡ በዚሁ መንገድ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት አለመሆናቸውን ለማስገንዘብ የወጣ ነው:: ጥልቁን የቤተ ክርስቲያን ምሥጢር ደግሞ ከሊቃውንቱ በመጠየቅ እንደሚያጸብሩት እናምናለን::

አእምሮውን ለብዎውን ሰጥቶ ምሥጢሩን ይገልጥልን ጥበቡን ያሳድርብን ዘንድ ዕዝነ ልቡናችንን ይክፈትልን ዐይነ፣ ልቡናችንንም ያብራልን:: አሜን::

አርታዒው

ዲ.ብርሃኑ አድማስ

ምዕራፍ 1

በሥጋዌ የተናገረን የባሕርይ ልጁ ከሁሉ ይበልጣል::

«ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና፣ በብዙ ጉዳና ለአባቶቻችን በነብያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዘመናትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ተናገረን::»
ቁ.1–3

1.1. <u>እግዚአብሔር ከጥንት እስከ አሁን ተናገረን::</u>

<u>ጥንት:-</u> በዚህ መጽሐፍ ጥንት የተባለው ጌታችን ሰው ከመሆኑ በፊት የነበረው ጊዜ ነው:: በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በነብያት አድሮ በብዙ ዓይነትና በብዙ ጉዳና ተናግሮናል::

«እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን ነብያቱ አፍ የተናገረው፣ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና:: ሙሴም ለአባቶች ጌታ አምላክ እኔን እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤ በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ስሙት:: ያንንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ ተለይታ ትጠፋለች አለ:: ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ ከእርሱም በኋላ የተናገሩት ነብያት ሁሉ ደግሞ ስለዚህ ወራት ተናገሩ::» ይላል:: ሮሜ.3+21–24:: በብዙ ዓይነትና በብዙ ጉዳና ተናገረን ሲልም ቃል በቃል፣ በምሳሌ፣ በትንቢት፣ በምሥጢራዊ ምሳሌያትና ምሥጢራውያት ትንቢቶች መናገሩን ነው::

ቃል በቃል ተናገረ የሚባለው እግዚአብሔርም ሙሴን «እንግዲህ....አለው» የሚለውን ዓይነት ነው:: እንደ ምሳሌም አሥሩ ቃላትን በመስጠት ተናግሮናል:: በምሥጢራዊ ምሳሌ የሚባለው

www.zeyeneta.com

በመቅረዝ /በተቅዋመ ወርቅ/ /ዘጸ.25÷31/ በግዕጠንተ ወርቅ /ዘጸ.30÷1/ በአሮን በትር /ዘኍ.17÷1-11/ ይሄን በመሰለው የተናገረው ነው። በምሳሌ ተናገረ ስንልም በጓላ ዘመን ሰው ሆኖ የሚያድንበትን ግብር ገለጠልን ማለታችን ነው። ከሦስቱ ምሳሌዎች የመጨረሻውን እንኳን ብንመለከት እግዚአብሔር ሙሴን ከአሥራ ሁለቱ አለቆች /አበው/ አንዳንድ በትር ወስዶ ስማቸውንም በበትሩ ላይ ጽፎ በመገናኛው ድንኳን በምስክሩ ፊት እንዲያስቀምጥ ታዘዘ። ሙሴም አስቀመጠ። በነጋውም ከሌዊ ቤት የሆነ የአሮን በትር ሳይተክሏት ተተክላ፣ ውኃ ሳያጠጧት ለምልማ አብባ ለውዝም አፍርታ ተገኘች።

ምሳሌነቱ፦ በትር የእመቤታችን

- ሳይተክሏት ተተክላ፣ ውኃ ሳያጠጧት ለምልማ፣ አብባና አፍርታ መገኘቷ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን ያለ ሩካቤ ያለ ወንድ ዘር ድንግልናዋ ሳይለወጥ በመንፈስ ቅዱስ ግብር ጸንሳ ለመውለዷ ምሳሌ
- ፍሬ የጌታችን ምሳሌ /ሥጋየን ካልበላችሁ ደሜንም ካልጠጣችሁ የዘላለም ሕይወት የላችሁም ሲል በልተነው እንድንድን ፍሬ ሕይወት ሆኖ ተሰጥቶናልና።/

- ቀጥተኛ በሆነ ምሳሌ ደግሞ ለሙሴ በሐመልግል ወነበልባል /ዘጸ.3÷1-5/ ለጌዴዎን በጸምር /ማምጃ፣ ጻውጃ/ና በጠል /መሳ.6÷36/ ይሆን በመሰለው ሁሉ ነው።

በትንቢት ደግሞ

- «እነሆ÷ ድንግል ትጸንሳለች÷ ወንድ ልጅም ትወልዳለች÷ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» ኢሳ.7÷1። «ሕፃን

ተወልዶልናልና÷ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም ድንቅ መካር÷ ኃያል አምላክ÷ የዘላለም አባት÷ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።» ተብሏል። ኢሳ.9÷6። ቅዱስ ጳውሎስ ከጥንት እስካሁን ያለው በየጊዜው ያለማቋረጥ በየዘመኑ በነበሩ አባቶች በኩል መናገሩን ለመግለጽ ነው። ለአብነት ያህልም ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

<u>በአብርሃም፦</u>- በዘፍ.22÷1-19 እንደተገለጠው እግዚአብሔር አብርሃምን ሲፈትነው «የምትወደውን ወንድ ልጅህን ይስሐቅን ሠዋልኝ፤» አለው። አብርሃምም እንደታዘዘው ወደ ሞሪያ ተራራ ልጁን ወሰደ። ልጁንም ሊሠዋ ቢላዋ አነሣ። የእግዚአብሔርም መልአክ ጠርቶ «እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት፣ እግዚአብሔርን እንደምትፈራ አሁን አውቄአለሁ አለ። ከዚህም በኋላ አብርሃም በዕፀ ሳቤቅ የታሠረ በግ በዱር ውስጥ አየ። በልጁ ፋንታም ሠዋው። መልአኩም ሁለተኛ ጠርቶ እንዲህ አለው።

« እግዚአብሔር በራሴ ማልሁ ይላል፤ ይህን ነገር አድርገሃልና÷ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና÷ በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ... የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ።» ቁጥር 16-18 ይላል።

አብርሃም ልጁን መሥዋዕት አድርጉ ሊያቀርብ እንደሚችል እግዚአብሔር አያውቅምን? ስለምን ጠየቀው? የሚሉ ጥያቄዎችን ስናነሣ እግዚአብሔር በባሕርይው ፍጹም ዐዋቂ ነውና የአብርሃምን እምነት ስለማያውቅ አይደለም፤ በአብርሃም እኛን እየተናገረን እንጂ። የተናገረንም፦-

1ኛ. እምነታችንን እንደ አብርሃም በሥራ የምንገልጥ እንሆን ዘንድ፣

2ኛ. በይስሐቅ ፈንታ በጉ እንደ ,ተሠዋ በበደለኛው ሞት በሚገባው በአዳም ፈንታ ወልጁ እግዚአብሔር የመሥዋዕት በግ ሆኖ

www.zeyeneta.com

የሚቀርብ መሆኑን ለማጠየቅ ነው። «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።» ዮሐ.1÷29 እንዲል።

3ኛ. «በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ÷... የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ» የሚለውን ስንመለከት «ሁሉም» የሚባረኩበት ማን ነው? ለሚለው የጎሊና ጥያቄያችን እግዚአብሔር ትንቢት መናገሩ ይሰማናል።

<u>በይስሐቅ</u>፡- እግዚአብሔር አብርሃምን እንደ ባረከ እንዲሁ ይስሐቅንም ባርኮታል፣ በአብርሃም በኩል እንደ ተናገረን በይስሐቅም በኩል ተናግሮናል። «...ከአንተ ጋርም እሆናለሁ፣ እባርክሃለሁም፣ እነዚህን ምድሮች ሁሉ ለአንተም ለዘርህም እሰጣለሁና÷... የምድርም አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ።...» ዘፍ.26÷1–6።

<u>በያዕቆብ</u>፡–ያዕቆብ ብኩርናን ከዔሳው ስለገዛ/ዘፍ.25÷33/የዔሳውንም በረከት ስለተቀበለበት /ዘፍ.27÷1–42/ ዔሳው ያዕቆብን ለመግደል አሰበ። እናቱ ርብቃም ያዕቆብን መከረችውና ወደ አጐቱ ወደ ላባ ሄደ። በመንገድም መሸበትና አደረ። ድንጋይ ተንተርሶም ተኝቶ ሳለ ሕልምን አለመ። «እነሆም መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ÷ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ÷ እነሆም÷ የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡበት ይወርዱበት ነበር። እነሆም እግዚአብሔር በላይ ቆሞበት ነበር፣ እንዲህም አለ፡–...የምድርም አሕዛብ ሁሉ በእንተ በዘርህም ይባረካሉ።...የነገርሁህን ሁሉ እስካደርግልህ ድረስ አልተውህምና።» ዘፍ.28÷10–15።

– መሰላል የእመቤታችን ምሳሌ ነው። እግዚአብሔር በመሰላሉ ላይ ቆመ መባሉም በእመቤታችን በኩል በሥጋ መገለጡን ለመናገር ነው። ሕልሙን ያለመው ያዕቆብም የሰው ዘር ምሳሌ ነው። የሰው ዘር በሙሉ ጌታችንን ያየው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ከሁለተ አካል

አንድ አካል ከዙለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኖ በተገለጠ ጊዜ ነውና። «መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኪ የለም በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።» ዮሐ.1÷18። «የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል።» መዝ.83÷7 እንዲል።

በሙሴ ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ተነጋግሯል። ከዚህም በላይ በሙሴ አድሮ የሠራው ሥራ በኋላ ዘመን ተገልጦ ለሚሠራው ሥራ አብነት መሆኑን ነግሮናል። ይህም ይታወቅ ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛቆሮ.10÷1–13 የእስራኤል ዘሥጋን የጉዞ ታሪክ ከእኛ ከእስራኤል ዘነፍስ /ክርስቲያኖች/ ጋር በማነጻጸር አስተምሮበታል። ግብጽ የሲኦል፣ ፈርዖንና ሠራዊቱ÷ የዲያብሎስና የሠራዊቱ፣ እስራኤል የአዳምና የልጆቹ፣ ከነዓን÷ የገነት የመንግሥተ ሰማያት፣ ሙሴ የክርስቶስ ምሳሌዎች ናቸው። በሙሴ አድሮ እስራኤልን ከፈርዖንና ከሠራዊቱ አላቅቆ÷ ባሕር ከፍሎ ደመና ጋርዶ በሙሴ መሪነት ከግብፅ ነጻ ማውጣቱ በኋላ ዘመን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆኖ በመስቀል ተሰቅሎ በሞቱ ሞትን ሽሮ /1ኛቆሮ.15÷27/. አዳምንና ልጆቹን ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ አላቅቆ ባሕረ እሳትን ከፍሎ በጠለ ረድኤቱ ጋርዶ ገነትን ለማውረሱ ምሳሌ ነው። ይህንንም ራሱ ሙሴ «ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል።» ዘዳ.18÷15–16 ሲል ከራሱ ጋር አነጻጽሮ ተናግሮለታል። ሙሴ ተናገረው ስንልም እግዚአብሔር በሙሴ አድሮ ተናገረን ማለታችን ነው። ንግግሩ ለጊዜው ኢያሱ ቢሆንም ፍጻሜው ለጌታ ነውና።

<u>በዳዊት</u>፡– አምላካችን እግዚአብሔር እንደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ /ሐዋ.13÷22/ ብሎ በተናገረለት በቅዱስ ዳዊትም ተናግሮናል። በቅዱስ ዳዊት በኩል ያልተነገረ የሥጋዌ ምሥጢር አለ ለማለትም አይቻልም። በእርሱ አብዝቶ ተናግሮናል።

www.zeyeneta.com

«እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ አይጸጸትም÷ እንዲህ ብሎ÷ ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ» የሚል አለ። መዝ.131/132÷11። ቅዱስ ዳዊት ከአባቶቻችን ጋር ቃል ኪዳን ያደረገ ወደፊትም የሚያደርግ እግዚአብሔር፣ ሰው ሆኖ የሚገለጥ መሆኑን፣ በሥጋዌው የሚፈጽመውን፦ ሞቱን ትንሣኤውን ዕርገቱን ዳግመኛ የሚመጣ መሆኑን ለሰው የሚሰጠውን የሚመልስለትን ክብሩን ሁሉ ተገልጦለት ተናግሯል።

እንግዲህ ከላይ የዘረዘርናቸውን አበው እንደ ምሳሌ አነሣናቸው እንጂ በነቢያቱ ሁሉ እያደረ እግዚአብሔር ተናግሮናል። ንግግሮቹም እስካሁን በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግበው ያልተመዘገቡትም በትውፊት እየተላለፉ ብጉባኤ ቤት እየተነገሩ አሉ። ይኸውም በነቢዩ ኤርምያስ፦ «አባቶቻችሁ ከግብፅ ምድር ከመጡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በየዕለቱ እየማለድሁ ባሪያዎቼን ነብያትን ሁሉ ልኬባችሁ ነበር።» /ኤር.7÷25/ በማለቱ ይታወቃል። እግዚአብሔር በአበው በነብያት ተናገረን ስንል ግን ጸጋውን ሰጥቷቸው ሀብቱን አሳድሮባቸው ነና የሚመጣውን በእርግጠኝነት እንዲናገሩ አስችሏቸው እነርሱ የእርሱን ንግግር ተናገሩን ማለታችን ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔርን በቀጥታ እኛ ልንሰማው አንችልምና፣ እንኳን እኛ እግዚአብሔር አጽንቷቸው እንጂ ሰማይና ምድርም በፊቱ መቆም ባልተቻላቸው ቀልጠውም በጠፉ ነበር። አቅማችን ታናሽ መሆኑም በእስራኤል ዘሥጋ ታውቋል። እነርሱ እንኳን እግዚአብሔርን ከእግዚአብሔር ጋር የተነጋገረውን የሙሴን ገጽ ማየት ተስኗቸው ነበርና። ዘጸ.34÷29–35።

1.2. በልጁ ተናገረን

ሀ. ሁሉን መራሽ ባደረገው ሲል ምን ማለቱ ነው?

ወረሰ ተብሎ የተነገረለት ሥጋ ነው። ምክንያቱም ቅድመ ተዋሕዶ ሥጋ የመለኮትን ገንዘብ መለኮትም የሥጋን ገንዘብ አልተገናዘቡም /አልተቀባበሉም÷ አልተሰጣጡም÷ አልተወራረሱም/ ነበር፤ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ÷ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ÷ ቃልም እግዚአብሔር ነበር።» ዮሐ.1÷1 እንዲል። አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው ከሆነ በኋላ ግን ቃልና ሥጋ ተገናዝበዋል። አንዱ የሌላውን ውርሷል።

ቅድመ ተዋሕዶ	
ሥጋ	ቃል
⇒ ግዙፍ	⇒ ረቂቅ የማይታይ፣ የማይዳሰስ
⇒ ውሱን	⇒ ምሉዕ
⇒ ፍጡር	⇒ ሁሉን የፈጠረ
⇒ መዋቲ	⇒ የማይሞት፣ የማይለወጥ
⇒ /ረሀብ፣ ድካም፣ ጽምዕ/ የሚሰማው	⇒ ራሱን የቻለ፣ አካላዊ፣ መለኮት፣ በአብ በመንፈስ ቅዱስ ዕሪና /ትክክልነት/ የሚኖር
⇒ ጓለኛ /ዘመን የሚቆጠርለት/	⇒ የነበረ ያለ የሚኖር /ለዘመኑ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው/

ድኅረ ተዋሕዶ፦ «ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ÷ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን።» ዮሐ.1÷14 እንዲል ቃል በተዋሕዶ ሰው በሆነ ጊዜ የሥጋን ገንዘብ ሁሉ ለራሱ አደረገና ታየ፣ ተዳሰሰ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ ደከመውና አንቀላፋ፣ በላ፣ ጠጣ፣ ታመመ ሞተ ተቀበረ። «ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን

www.zeyeneta.com

በዓይናቸችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን።› 1ኛዮሐ.1÷1 እንዲል።

ቃል የሥጋ የሆነውን ሁሉ ገንዘብ እንዳደረገ ሥጋም የቃልን ገንዘብ ወርሷል። ፍጡር፣ ደካማ፣ የነበረ ሥጋ ፈጣሪ /አቻናፊ/ ሆነ፣ አምላክነትን ገንዘብ አድርጉ በየማነ አብ /በተደመ የቃል ክብርና ሥልጣን/ በዘባነ ኪሩብ ተቀምጠ ታየ። ሥራ.7÷56። ስለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጌታችን ሰውነቱን ካስረዳ በኋላ የቃል የሆነውን ሁሉ ወርሷል በማለት የሚበልጥ መሆኑን የገለጠው።

በአጭር ቃል ሥጋ በተዋሕዶተ መለኮት አምላክነትን፣ ገዥነትን፣ ፈጣሪነትን ወርሷል። «ለምንኽ÷ አሕዛብን ለርስትህ፣ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ አሰጥሃለሁ።» መዝ.2÷8። «ሁሉ በእርሱ ሆነ÷ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» ዮሐ.1÷3 እንዲል።

ለ. ዘመናትን በፈጠረበት ማለቱ?

ቅዱስ ጳውሎስ «ዘመናት» ያላቸው እነማንን ነው? የሚለውን ጥያቄ አስቀድሞ ማየቱ ለዐረፍተ ነገሩ ትርጉም ሰጭነት አስተዋጽኦ ይኖረዋል። ዘመን በራሱ ፍጡር ነው። ያልነበረውን ዓለም እግዚአብሔር ካለመኖር ወደ መኖር ሲያመጣው ያልነበረው ኑሮ ተጀምሯል፣ ዓለሙን ሲያሳልፈው ደግሞ የነበረው ኑሮ ይፈጸማል። ስለዚህ ጊዜ ወይም ዘመን እግዚአብሔር ለፈጠረው ፍጥረት መለኪያ ሆኖ እንዳገለገለ መረዳት ይቻላል። ከዚህ አንጻር «ዘመናትን በፈጠረበት» ማለት በመሥፈሪያው ወይም በመለኪያው ልኩን ወይም ሥፍሩን እንደ መናገር ያለ ነውና ልክን በመለኪያው ወይም ሥፍርን በመሥፈሪያው መናገር የሚለውን ለመረዳት በምሳሌ መመልከት ይቻላል።

አውሮፕላኑ 2000 ጫማ ላይ ይበር ነበር ማለት 2000 ጫማዎች ተነጥፈውለት ሳይሆን ጫማ መለኪያ ሆኖ የከፍታውን ልክ

በመለኪያው ሲናገር ነው። ስለዚህ ዘመናትን በፈጠረበት ሲል በዘመን የማይለካ የማይመዠር ፍጥረት የለም ለማለት ነው። ምክንያቱም ቢያንስ የፍጥረት ሁሉ ጥንት ወይም መነኛ አለው። ስለዚህ እርሱ ከተፈጠረው ሁሉ ያልፈጠረው እንደሌለ እንረዳለን። መልእክቱም ፍጡራንን ሁሉ በፈጠረበት በልጁ ህልው ሁኖ ተናገራን ለማለት ነው። «ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሯል፣ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው፣ ሁሉ በእርሱ ተጋጥሟል።» ቆላ.1÷17 እንዲል።

«ፈጠረበት» ሲልም አንጥረኛ ቀድሞ መደሻውን ሠርቶ የቀረውን ጓላ እንዲሠራ ወልድን ፈጥሮ የፈጠረበት አይደለም። ለምን ቢሉ፦

1. ዘመናትን /ሁሉን/ ፈጠረበት ማለቱ ለእርሱ ጥንትና ፍጻሜ እንደሌለው ሲያጠይቅ ሲያስረዳ ነው። ራሱን በራሱ ሊፈጥር የሚችል ፍጥረት የለምና።

2. «አንተ ልጄ ነህ÷ እኔ ዛሬ ወለድሁህ» መዝ.2÷7 እንዲል ወልድ ለአብ የባሕርይ ልጁ ነው እንጂ ፍጡሩ አይደለም። ምክንያቱም እኛ የምንወልደውን እንደማንፈጥረው፣ የምንፈጥረውንም እንደማንወልደው ሁሉ አብ ልጄ ነህ አለው እንጂ ፍጥረቴ ነህ አላለውም። ማቴ.3÷17፣ ማቴ.17÷5። በዚያውም ላይ መጽሐፍ «እግዚአብሔር በመጀመርያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» /ዘፍ.1÷1/ አለ እንጂ በመጀመርያ አብ ወልድን ፈጠረ አይልም። በቆላ.1÷16 ላይ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ «የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናትም ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት፣ ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋል።» ይላል። ቅዱስ ዮሐንስም «ሁሉ ;ነርሱ ሆነ÷ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» ዮሐ.1÷3 ብሏል።

«የሆነው ሁሉ» በእርሱ ከሆነ ካለ, እርሱም የሆነ ከሌለ «ራሱን

www.zeyeneta.com

በራሱ የሚፈጥር ነውን? ወልድን ፍጡር ነው ማለት አብንም ፍጡር ነው ማለት ነው። ሥግው ቃል ወልድ «እኔና አብ አንድ ነን» ብሏልና። ዮሐ.10÷30። ሰማይንና ምድርንም ከጥንት እርሱ እንደ መሠረታቸው በመዝ.101÷25–27 ላይ ያለውን ቅዱስ ጳውሎስ በዚሁ በዕብ.1÷10–12 ላይ አስቀምጦልናል። ጥንትን በፍጥረት እርሱ ከመ ሠረታት፣ እርሱ ጥንት የሌለው ፈጣሪ መሆኑን ማስተዋል ያሻል።

3. «ለይኩን»÷ ይሁን በሚል መፍጠሩን ለመናገር ነው። እግዚ አብሔር ፍጥረትን የፈጠረው በሦስት መንገድ ነው። በሀልዮ /በአሳብ/፣ በነቢብ/በቃል/ እና በገቢር /በሥራ/። ለምን ቢሉ በሀልዮና በነቢብ መፍጠሩ የሚሣነው የሌለ ሁሉን ቻይ መሆኑን፣ በገቢር መፍጠሩ ደግሞ ጥበበኛነቱን እናውቅ እንረዳ ዘንድ ነው። በሀልዮ የተፈጠሩት የዕለተ አሑድ ሰባት ፍጥረታት ናቸው። እነዚህም መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስ፣ እሳት፣ ጨለማ፣ ሰማያትና መላእክት ናቸው። ይኸንንም ሙሴ በዘፍ.1÷2 ላይ «በመጀመርያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። ምድርም ባዶ ነበረች÷ አንዳችም አልነበረባትም፣ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበረ፣ የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍሮ ነበር።» ሲል ምሥጢራዊ አድርጉ ገልጦታል። ምክንያቱም ሰማይ ብሉ ሰማያትን እንደ ገለጸ ምድር ብሉም አራቱን ባሕርያት /እሳት፣ ነፋስ፣ ውኃና መሬትን/ ገልጧል። ይልቁንም ምድር አንዳች አልነበረባትም በማለቱ ወደፊት በመሬት የሚኖሩ ግብር እምግብር የሚፈጠሩ ፍጥረታት መኖራቸውን ገልጿል። ታዲያ በዚህ ጥቅስ መሠረት የመላእክት መፈጠር በምን ይታወ ቃል? ቢሉ፦

1ኛ ምድርም አንዳች አልነበረባትም ብሉ የምድርን ባዶነት ተናግሮ ሰማያትን ግን አልነበረባቸውም አለማለቱ ፤

2ኛ. የመጀመርያ ፍጥረታትን በሀልዮ መፍጠሩ እግዚአብሔር

ሰሚ ፍጥረት አለመፍጠሩን ያጠይቃል። ሰሚ በሌለበት ደግሞ እግዚአብሔር ቀርቶ ሰው አይናገርምና። በእነዚህ ሰባት ፍጥረታትም ውስጥ መላእክት መኖራቸው የሚታወቀው ስምንተኛውን ፍጥረት «ብርሃንን» ለይኩን ብሉ በቃል መፍጠር በመጀመሩ ነው። ከብርሃን በፊት ሰሚ ምስክር መላእክት እንደተፈጠሩ ያጠይቃልና።

ወደ ዋናው ዓላማችን ስንመለስ ከዚህ ከብርሃን ጀምሮ እግዚ አብሔር ሌሎች አሥራ ሦስት ፍጥረታትን የፈጠረው በቃሉ ነው። ዘፍ.1÷3–25። እነዚህም ሰኞ አንድ ፍጥረት እርሱም ጠፈር ወይም ሰማይ፣ ማክሰኞ ሦስት ፍጥረት ከምድር፦ አዝርዕት /በማጭድ የሚታጨዱ/፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ /በእጅ የሚለቀሙ/፣ ዕፅዋት /በምሳር የሚቆረጡ/፣ ረቡዕ ሦስት ፍጥረት፦ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክ ብት፣ ኀሙስ ሦስት ፍጥረት ከውኃ የተገኙ በክንፍ የሚበሩ፣ በእግር የሚሽከረከሩ፣ በልባቸው የሚሳቡ፣ ዓርብ ሦስት ፍጥረት፦ ከየብስ የተገኙ በክንፍ የሚበሩ፣ በእግር የሚሽከረከሩ፣ በልባቸው የሚሳቡ ናቸው።

የዕለተ ዓርብ የመጨረሻው ፍጥረት በገቢር የተፈጠረው ሰው ነው። ከዚህ እንደምንረዳው እግዚአብሔር በስድስቱም ቀን ከፈጠራ ቸው ሃያ ሁለት ፍጥረታት ውስጥ አሥራ አራቱ በቃል ለይኩን ብሉ የፈጠራቸው ናቸው። በስድስቱም ቀን ውስጥ ቢቃል የተፈጠሩ ፍጥረታት አሉ። የሥላሴ ቃላቸው ደግሞ ወልድ ነው። ለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ «በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። ሁሉ በእርሱ ሆነ÷ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» /ዮሐ.1÷1–3/ ሲል የተናገረው። ስለ ዚህ ዓለማትን በፈጠረበት በልጹ ሲል ጥንት በሥነ ፍጥረት ለይኩን ብሉ በተናገረበት በአካላዊ ቃል ህልው ሆኖ ተናገረን ለማለት ነው።

www.zeyeneta.com

በልጁ ተናገረን ስንልም እንደ ነብያት በሕልም፣ በራእይ ወይም እንደ ሙሴ እንዲህ ብለህ ተናገር እያለው ሳይሆን በልጁ ህልው ሆኖ ተናገረን ማለት ነው። ህልውና ማለት የአካላት መደበላለት፣ ወይም መጠፋፋትና መዋዋጥ ሳይሆን በፍጹም የአካላት ምስትነት የአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ፣ የወልድም በአብ በመንፈስ ቅዱስ፣ የመንፈስ ቅዱስም በአብ በወልድ መኖር ነው።

«ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ... ይህ በመጀመርያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።» ዮሐ.1÷1–3 ማለቱ ወልድ በአብና በመንፈስ ቅዱስ ህልው ሆኖ ይኖር እንደነበር ያስረዳል።

«እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፣ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፣ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ።» ዮሐ.14÷10–11 ሲል ህልውናቸውን ተናግሯል። ይልቁንም በዮሐ. 3÷11 ላይ «እውነት እውነት አልሃለሁ፥ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን፣ ምስክርነታችንንም አትቀበሉትም።» ሲል የአብንና የመንፈስ ቅዱስን በእርሱ ህልዋን መሆን አስረዳን።

ስለዚህ «በልጁ ተናገረን» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ቃል «እግዚአብሔር ነበር» ተብሏልና የአብ የባሕርይ ልጁ ነው። ወልድ ራሱ እግዚአብሔር ነውና። አሪትንና ነብያትን ከነገሩን አበው እርሱ እንዲበልጥ ዕወቁ፣ ወልድ የሠራት ወንጌልም ከአሪት እንድት በልጥ ዕወቁ በማለት በአሪት የሚመኩ ዕብራውያንን አስተማረ።

በአሪትና በነቢያት እንደምናነበው አበው ነብያት የተናገሩት «እግዚአብሔር አንዲህ ይላል፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፣ በዚህ ቦታ እግዚአብሔርን አየሁት፣ እንዲህ ዓይነት ሕልም ወይም ራእይ አየሁ።» በማለት ነው። ጌታችን ግን የተናገረው «እንዲህ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ...» ማቴ.

5÷21–48፣ «ይሽንን... አድርጉ ይሽንን... አታድርጉ» በሚል ነው። «ኢየሱስም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፣ እንደ ጸሮቻቸው ሳይሆን እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና።» ማቴ.7÷28–29 እንዲል።

አበው ምሳሌውንና ትንቢቱን ተናገሩ፣ ሱባኤውንም ቆጠሩ። ጌታችን ግን ምሳሌው የተመሰለለት፣ ትንቢት የተነገረለት ሱባኤ የተቆጠረለት እርሱ መሆንን ነገረን።ማቴ.4÷14–17፣ ማቴ.12÷15–21፣ ማቴ.13÷34–35፣ማር.4÷34፣ማቴ.21÷1–13÷42፣ዮሐ.3÷15። የአበው የኑብያት ትንቢትና ምሳሌ መፈጸሙን በእርሱ መገለጥ ዐወቅን፣ በተአምራቱና በሥራው አመንን። በሞቱም ጠላታችንን ገድሎ ነጻ አወጣን። በትንሣኤውም የትንሣኤያችንን ተስፋ ነገረን። ከዚህ የምንረዳው የአበው ንግግርና የጌታችን ንግግር የሚለያየው ዐተናጋሪዎቹ ልዩነት መሆኑን ነው።

እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አግልክት ካላቸው÷ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ አናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን፡– ትሳደባለህ ትሉታላችሁን? እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፣ ባደርገው ግን÷ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንዳለሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ።» ዮሐ.10÷36–38 እንዲል። አበው ነብያት የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸው ናቸው፣ እርሱ ግን አካላዊ ቃል ነው። ይሁን እንጂ እነርሱም የተናገሩት ትንቢት ጌታችንም ያስተማረው ትምህርት አንድ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እነርሱ ከእርሱ ተልከው ተናግረዋልና።ማቴ.23÷34 ከእግዚአብሔርም የተላከ የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና። ዮሐ.1÷34።

1.3. የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ ሆኖ *(ዕብ.1÷3)* አሁንም ቅዱስ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው ስለ ጌታችንና

www.zeyeneta.com

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ታላቅነትና የባሕርይ አምላክነት ነው። ስለዚህም ነው የከብሩ መንጸባረቅ /ለአብ/ የጌትነቱ መታወቂያ፣ መገለጫ ሆነ፥ የሚለው። የሥላሴ ሦስትነት በጉላ፣ በተረዳ ነገር የታወቀውና የተረዳው በአካላዊ ቃል ሰው መሆን ነው። ለአብነትም ያህል በጥምቀቱ /ማቴ.3÷13-17/ በደብረ ታቦርም / ማቴ.17÷5/ የሥላሴ ልዩ ሦስነት ታይቷል። ይህ የእግዚአብሔር መልክእ መታየት፣ መገለጥ፣ የተፈጸመው መለኰታዊ ክብሩንም ያየነው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ነው። እርሱም ራሱ «እኔን ያየ አብን አይቷል።... እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁት ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው።... እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፥ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ።» /ዮሐ.14÷6-11/ ሲል የአብ የክብሩ መገለጫ የባሕርይው መታወቂያ መሆኑን አስረድቷል።

1.3.1 የባሕርዩ ምሳሌ

ይኸን ኃይለ ቃል ለመረዳት «ምሳሌ» የሚለውን ቃል ትርጉም መመርመር ያሻል።

ምሳሌ፦ ሀ/ የአብነት፣ የአስረጂ፣ የምስክር አቅራቢ /አገባብ/ ሆኖ ያገለግላል። «ለምሳሌ ያህል... » እንዲል። «የጋማ ከብቶችን በምግብነት የማይጠቀሙ ሀገሮች አሉ፥ ለምሳሌ ኢትዮጵያ» እንዲል።

ለ/ መርገፍ፦ አማናዊውን ነገር ለማስረዳት፣ በንጽጽር ለመግለጥ የምንጠቀምበት ቁስ፣ ፍጥረት፣...ነው። ሙሴ- የክርስቶስ ፈርያን- የዲያብሎስ፣ ግብፅ- የሲኦል፣ እስራኤል ዘሥጋ-በሲኦል የነበሩ ነፍሳት፣ ባሕረ ኤርትራ - የኃጢአት፥ የባሕረ ኃጢአት፣ ከነዓን- የገነት። ምሳሌዎች ናቸው። ሙሴ እስራኤልን ከፈርዖን አላቅቆ ከግብፅ እንዳወጣና ባሕረ ኤርትራን ከፋለሉ አሻግሮ ከነዓንን

እንዳወረሰ ጌታችንም የአዳም ልጆችን ከዲያብሎስ አላትቆ ከሲኦል አውጥቶ ባሕረ ኃጢአትን አድርቆ ወደ ገነት ለመመለሱ ምሳሌ ነበረ። «... እነዚህም ክፉ ነገር እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን።» እንዲል 1ኛቆሮ.10÷1-13 ::

ሐ/ አርአያ፦ ወደ ኋላ ለሚመጡት መንገድ ወይም ፈለግ አብነት /ተጠቃሽ/ ማለት ነው። በሥራው የተገለጠ አስረጂ/ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ መንገድ ነኝ» ዮሐ.14÷6 ማለቱም የሚሠራው ሁሉ ለእኛ ለማስተማር ስለሆነ ነበር። የጸመው፣ የጸለየው፣.... በፈቃዱ ስለ ሰው መከራን የተቀበለው ለእኛ አርአያ ለመሆን ስለነበር ነው። ሐዋርያትም የእርሱን ፈለግ ተከትለው ጸሙ፣ ጸለዩ፣ መከራን ተቀበሉ። በትምህርት በተአምራትም መሰሉት፥ በገድልም የሃይማኖታቸውን ጽናት አስመ ሠከሩ።

«እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።» /1ኛቆሮ.11÷1/ እንዲል እርሱን አብነት አድርገው በሃይማኖት ጸንተው፣ በምግባር ሰፍተው፣ በትሩፋት በልጥገው ፍሰጋውን ቢከተሉት ነፍሳቸውንም ለታመነ ፈጣሪ አሳልፈው ቢሰጡ በፍርድ እንዲመስሉት ወሰነላቸው። ማቴ.19÷21። አሕዛብም «አማልክት ሰዎችን መስለው ወርደዋል» አሏቸው። የሐዋ.14÷11። እነዚህ ቅዱሳንም ለእኛ አርአያዎች ናቸው። «እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን... በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ ከንቲአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለመታወም የጸናውን አስቡ።» ዕብ. 12÷1-3 ያለው ቅዱስ ጳውሎስ አርአያነታቸውን /ምሳሌነታቸውን/ እንድ ንከተል ነው።

ይልቁንም ደግሞ «የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ሞግዚ ትነታቸውን አስቡ፥ የኑሯቸውንም ፍጻሜ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው

www.zeyeneta.com

ምስሏቸው::» ዕብ.13÷7 በማለት ምሳሌነታቸውን እንድን ክብል በትእዛዝ ማጽናቱ ትርጉሙን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል::

ሠ/ በመልክ መስሉ በባሕርይ ተካክሉ መገኘት::

መልክ: ገጽ፣ ተክለ ቁመና፣ ስፋት፣ ቁመት... የሚለውን ሲያ መለክት ባሕርይ የሚባለው ደግሞ የራስ ገንዘብ የሆነ፣ ከሌላ ያልወረሱት ወይም ያልተቀበሉት ሌላውም ሊመስደው የማይቻለው /ከእግዚአብሔር በቀር/ ማለት ነው:: ባሕርይን ለእግዚአብሔር ተጽለን ስንናገር ግን እርሱ ከማንም ያልተቀበለው ከእርሱም ማንም ማን ሊመስደው የማይቻለው ገንዘቡ ማለታችን ነው:: ስለዚህ ቅዱስ ጳውሉስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርዩ ምሳሌ ያለው መግደል ማዳን፣ መስጠት መንሳት፣ .... የመሰለው ገንዘቡ ነውና ወልድ አብን በመልክ ይመስለዋል በባሕርይም ይተካከለዋል ሁሉ ነው::

ይኸንንም በ1ኛጢሞ.3÷16 ላይ በሚገባ ገልጦታል:: «እግዚ አብሔርንም የመሰለ ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው:: በሥጋ የተገለጠ /ከመገለጥ በፊት በእምላክነት ጸንቶ የኖረ ለማለት/፣ በመንፈስ የታመነ /ሰው በመሆኑ ዕሩቅ ብእሲ መስሏቸው ነበርና እምላክነቱን በመንፈስ ቅዱስ ዐወቅነው እንጂ በባሕርይ በጠባይዕ አላወቅነውም ለማለት/፣

– በአሕዛብ የተሰበከ

– በዓለም የታመነ

– በክብር ያረገ::» በማለት ገልጦታል::

ራሱም ጌታችን በባሕርይ የሚተካከለው መሆኑን ሲገልጽ «... አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል::» /ዮሐ.5÷21/ ብሏል:: በሌላም ቦታ «እኔና አብ አንድ ነን::» ብሏል:: /ዮሐ.10÷30/

በመልክ መምሰሉንም ሲናገር «እኔን ያየ አብን አይቷል::» /ዮሐ.14÷10/ ብሏል:: ለዚህም ነው ቅዱስ ዮሐንስ «አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን::» ያለው:: ዮሐ.1÷14::

1.4. ሁሉን በሥልጣኑ ቃል ደገፈ

ቅዱስ ጳውሉስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አብን በመልክ ይመስ ለዋል በባሕርይም ይተካከለዋል ማለቱን በአስረጂ ሲያቀርብ ሁሉንም በሥልጣኑ ቃል /በእምላክነቱ/ አደረገ ይላል:: ለምን ቢሉ:–

ሀ/ የጸመውና የጸለየው በሥልጣኑ ነው:: ጌታችንና መድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ ገብቶ ከቆመ ሳያርፍ ከዘረጋ ሳያጥፍ 40 መዓልትና 40 ሌሊት የጸመው በሥልጣኑ ነው:: በሥልጣኑ መሆኑም የሚታወቀው እንደ እርሱ ያለ ምግብና ውኃ ለ40 ቀን የጸመው ሙሴ የአወጣጡ ዓላማ እንዲጸም ፈልጉ ሳይሆን ወደ ተራራው እንዲወጣ በእግዚአብሔር ስለ ታዘዘ ነው:: የደብተራ አሪትን ምሥጢር ሲያሳየው ሰነበተ:: እግዚአብሔርም ካሳደረበት ጸጋ የተነሣ ፊቱ እንኳን እስኪያንጸባርቅ ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ቆየ:: ጌታችን ግን በፈቃዱ ጸመ÷ ጸለየ፣ ጥንተ ጠላታችን ዲያብ ሉስንም አሳፈረልን:: ዘጸ.34÷27–35፣ ማቴ.26÷36፣ ሉቃ. 22÷39–46፣ ዮሐ.17÷1–2:: «ነገር ግን አንተ እንደላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ:: » /ዮሐ.11÷42/ እንዲል::

ለ/ የለመነው በሥልጣኑ ነው:– ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው:: ሰው እንደ መሆኑ መጠን ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ አንቀላፍቷል፣... እንደ አምላክነቱም እንዲሁ ፍሬ ያጣባትን ዕፅ ረግሞ አድርቋታል፣ ባሕሩንም ገሥጿል፣ ሞግዱንና ነፋሱንም ፀጥ አድርጓል:: የመጣበትም ዋና ዓላማ የሰው

www.zeyeneta.com

ልጅትን ወደ ተደመ ነብራቸው ለመመለስ ነው። «ስለዚህ የዲ ያስብሉስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።» እን ዲል ዮሐ.3÷9።

የዲያብሉስ ሥራ የተባለው «ዕፀ በለስን ብትበላ አምላክ ትሆናለህ እንጂ አትሞትም።» የሚለው አዳም የተያዘበት ወጥመድ ነበር። ይህ ተንኰል የሚፈርሰው ሰው አምላክ ሲሆን ብቻ ነው። ሰው አምላክ መሆን የሚቻለው ደግሞ አምላክ ሰው ሲሆን ብቻ ነው። በዚህ ምክንያት አምላክ ሰው ሆነ፡ሰውም አምላክ ሆነ። የዲያብሉስ ሥራ ፈረሰ፣ ወጥመዱ ተሰበረ፡ እኛም ከአዳኙ ወጥመድ አመለጥን። መዝ.123÷7።

እንግዲህ የጌታችንን ሰው ሆኖ የተገለጠበትን ዓላማ ከተረዳን የጌታችን ልመና የዕሩቅ ብእሲ ልመና ሳይሆን ወልድ ዋሕድ ስለ አዳም ተገብቶ በሥልጣኑ ያቀረበው ልመና መሆኑን እንረዳለን። ይኸንንም ያደረገው ከሌላ በተቀበለው ሥልጣን ወይንም በተዋራ ጅነት አለመሆኑን መጠንቀቅ ይገባል። «አምላኬ አምላኬ÷ ስለ ምን ተውኸኝ?» /ማቴ.27÷46/ ያለው በሥልጣኑ ነው፣ ስለ መጀመሪያው አዳም ዳግማዊው አዳም ጸሎቱን ጸለየ ልመናውንም አቀረበ። «አዳም መልካሙንና ክፉውን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ» /ዘፍ.3÷22/ ብለህ የገባህልኝ ቃል ኪዳን ወዴት አለ÷ ጊዜውስ ይኸ አልነበረምን ለማለት ነው።

አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለክርስቶስ አምሳሉ ነውና። ሮሜ.5÷14። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በዮሐ.12÷27–30 እንደ ተጻፈ «አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ÷ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ። አባት ሆይ ስምህን አክብረው። ስለዚህም፡– አከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ። በዚያ ቆመው የነበሩትም ሕዝብ

በነሙ ጊዜ፡ ነጐድጓድ ነው አሉ፡ ሌሎች፡ መልአክ ተናገረው አሉ። ኢየሱስም መለሰ፡ እንዲህ ሲል፡ ይህ ድምፅ ስለ እናንተ ሙጥር እንጂ ስለ እኔ አይደለም።» ብሏል። ጌታችን በለመነ ጊዜ መልስ የመምጣቱ ምሥጢር በእቅራቢያው የነበሩ ሰዎች «ልመናን ያቀረበው ተወራጅ ቢሆን፣ ቢያንስ ነው እንጂ» ብለው እንዳይጠ ራጠሩ ነው። እነርሱንም ከድካማቸው ለማገገ መሆኑን መናገሩ እርሱ ያቀረበው ልመና በሥልጣኑ መሆኑን እንረዳ ዘንድ ነው።

ዳግመኛም ጌታችን በወንጌል «ወይስ ሰው አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያሥር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።» /ማቴ.12÷29/ እንዳለ ለአቅርቦተ ሰይጣን ሲል በሥልጣኑ ልመናውን አቅርቧል። በፈቃዱ በሥልጣኑ ያቀረበውም ልመና ኃይለኛውን ዲያቢሎስን አሥሮ ነፍሳትን የማረከበት መሣሪያው አድርጉታል ሲሉ ቅዱሳት መጻሕ ፍት ያስረዳሉ። «ወደ ላይ ዐረግህ÷ ምርኮን ማረክህ÷ ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ።» /መዝ.67÷18/ እንዲል። አንድም ጌታችን የጸለየው የለመነው ለአብነት ነው።

በእንጻሩ የሰው ልጆችን ልመናና ጸሎት ስንመለከት ግን በተዋራ ጅነት ነው፣ ማለትም እንድንጸልይ ታዝዘን፣ ብንጸልይና ብንለምን የምንጠቀም፣ ባንጸልይና ባንለምን ደግሞ የምንጐዳ ስለሆነ ነው። ማቴ.6÷7፣ ማቴ.7÷7፣ ማቴ.26÷41፣ ሉቃ.18÷1–14።

ሐ/ ትምህርቱና ተአምራቱ በሥልጣኑ ነው

ጌታችን ሲያስተምር እንደ ነብያት «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል...» እንደ ሐዋርያትም «የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት ዕወቁ፣ በእርሱም አምናችሁ ተጠመቁ...» በማለት አይደለም። ይልቁንም «እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ እኔ ግን እላችኋለሁ፣...» እያለ አስተማረ እንጂ፡ ሰዎችም የተገረሙት በዚህ

www.zeyeneta.com

ነበረ። «ኢየሱስም ይህን ነገር በፈጸሪስ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፡ እንደ ጻፎቻቸው ሳይሆን እንደ ባለሥልጣን ያስተምራቸው ነበረና።» /ማቴ.7:28/ ተብሎ እንደተጻፈ።

ተአምራቱም በሥልጣኑ ነው። እንደ ነብያቱ «አቤቱ አምላኬ ሆይ÷ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ ነፍሱን መልስ» /1ኛነገ.17÷21/ በሚል እንደ ሐዋርያትም «በእየሱስ አብሔር ስም÷ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ» ስም በማለት አይደለም። በሥልጣኑ በደረቅ ግንባር ላይ ሳይንን ፈጠረ። ዮሐ.9÷5–9። «ተነሥና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ» አለና ሽባውን ተረተረ። ዮሐ.5÷2–9። ውጡ ብሎ አጋንንትን አስወጣ። ማቴ.8÷22። «አልዓዘር÷ አልዓዘር» ብሎ ነፍሱን ከሲኦል ሥጋውን ከመቃብር ጠርቶ አዋሕዶ መልቱን አስነሣ። «እንደ እምነትህ ይደረግልህ፡ እንደ እምነትሽ ይደረግልሽ፡ አወዳለሁ ንጻ እያለ ከበሽተኞች ደዌን አራቀ። ዮሐ.11÷43፣ ማቴ.8÷1–18፣ ማቴ.9÷1፣ 18–25።

መ/ የሞተው በሥልጣኑ ነው

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ለአድኅኖተ አዳም ነው። ግርፋቱንና መከራውን የተቀበለው በፈቃዱ ነው። ይኸ ውም «ስለዚህ ይሁዳ ጭፍሮችንና ከካህናት አለቆች ከፈሪሳውያንም ሎሌዎችን ተቀብሎ በችቦና በፋና በጋሻ ጦርም ወደዚያ መጣ። ኢየ ሱስም የሚመጣበትን ሁሉ ዐውቆ ወጣና፡– ማንን ትፈልጋላችሁ? አላቸው። የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት። ኢየሱስ፡– እኔ ነኝ አላቸው።... እንግዲህ፡– እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ።» ዮሐ.18÷3–7 ተብሎ በመጻፉ አት ማቸውን ከገለጸ በኋላ በፈቃዱና በሥልጣኑ ለሕማምና ለሞት ተላልፎ እንደ ተሰጠ ያስረዳል።

ጌታችን ስለ ሞቱም አስቀድሞ «ነፍሴን ደግሞ አኖራታለሁና ስለዚህ አብ ይወደኛል። እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ» ሲል አስተምሯል። ዮሐ.10:17 18። ደግሞም ላኅጣት ሥልጣን አለኝ ማለቱ፡ ይልቁንም በፈቃዱ ስለ ሚቀበለው መከራና ሞቱ ስለመቀበሩና ስለ መነሣቱ ሲናገር ቅዱስ ጴጥሮስ «አይሁንብህ ጌታ ሆይ» በማለቱ ጌታችን «ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብም» ሲል መገሠጹ ማቴ.16÷21–23፡ ዳግመኛም ጊዜው ሳይደርስ አይሁድ እጃቸውን ሊጭኑበት አለመቻላቸው /ዮሐ.8÷20/ በሥልጣኑ እንዳደረገው ያጠ ይቃል።

ጊዜው በደረሰ ጊዜ ግን «ከዙሉት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል አለ።» ማቴ.26÷2። «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፡ እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጉች ይበተናሉ የሚል ተጽፏልና ከተነሣሁ በኋላ ግን ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው።» ማቴ.26÷31–32 በማለት በሥልጣኑ መቀበሉን አስረግ ጠልናል። በሥልጣኑም ከአብ ጋር ትክክል መሆኑን አስረድቶናል። በተጨማሪም «አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።... ከሰጠኝም ሁሉ አንድ ስንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው፡ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነ ሣዋለሁ።» በማለትም የእርሱንና የአባቱን በፈቃድና በሥልጣን አንድ መሆን አስረድቷል። ዮሐ.6÷37–40።

1.5. ኃጢአታችንን በራሱ አነጻ /ዕብ.1÷3/፡–

ቅዱስ ጳውሎስ ኃጢአታችንን በራሱ አነጻ ያለው ስለ ሦስት ነገር ነው።

www.zeyeneta.com

ሀ/ በተዋሕዶ የከበረ አምላክ መሆኑን ለማስረዳት

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ አይሁድ ዕሩቅ ብእሲ ወልደ ዮሴፍ ልንለው አንችልም። ምክንያቱም በዕሩቅ ብእሲ ደም ሰው ከኃጢአቱ አይነጻምና፣ ሰው በሰው ደም የሚነጻ ቢሆን ኑሮ ከጻድቁ ከአቤል ጀምሮ እስከ ዘመነ ሥጋዌ ድረስ የብዙ ነብያት ደም ፈሰሰ ነበርና በዚያ በዳንን ነበር። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ኃጢአታችንን ያነጻው በራሱ ነው ሲል የማንም ረዳትነት አያሻውም፣ እርሱ ራሱ በተዋሕዶ የከበረ ሁሉን ማድረግ የሚቻለው፣ ከተደረገውም ያለ እርሱ ምንም ምን ያልተደረገ፣ የሚሳነው የሌለ ነው ሲል ነው። አንዳንዶችም «ነቢይ ነው» የሚል አመለካከት ስለ ነበራቸው፣ «የዕሩቅ ብእሲ ሥጋ ቢበሉት ይመራል፣ ይተኩሳል እንጂ ኃጢአትን ዋጅቶ ከፍጻ አንጽቶ ሕይወትን አይሰጥም» ለማለት «ኃጢአታችንን በራሱ አነጻ» አለን።

ለ/ ከአሪት ሊቃነ ካህናት ልዩ መሆኑን ለማስረዳት

ዕብራውያን በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት አምነው ቢመለሱ እንኳን እነርሱ እንደሚያውቁት በቀደመው ዘመን እንደሚደረገው ሥርዓት «ኃጢአታችንን የሚያነጻ ሊቀ ካህን በክርስትናው መቼ አለ? ብለው እንዳይጨነቁ አስተድሞ ለማስረዳት የተናገረው ንግግር ነው። ምክንያቱም በአሪቱ የሚያነጻው ሊቀ ካህኑ፣ የሚያነጻበት የበግ፣ የፍየል፣ የላም ደም፣ የሚነጹት ደግሞ እነርሱ ነበሩ። ይኸም ከሚታጠብ ልብስ ጋር ይመሳሰላል። አጣቢው ሰው፣ ማጠቢያው /ማንጫው/ ላሙና እንዶድ፣ ታጣቢው /የሚነጻው/ ደግሞ ልብሱ ነበር።

በዚህ ሥርዓት አእምሯቸው የታነጸ ስለ ነበር ማን ያነጻናል? እንዳይሉ ጌታችን የፈጸመው አገልግሎት ከዚህ የተለየ መሆኑን፣ አንጭው ራሱ፣ ማንጫውም ክቡር ደሙ ሆኖ፣ ይኸ ለዘላለምም አንድ ጊዜ የቀረበ መሥዋዕት ስለሆነ አምነው ይመለሱ ዘንድ ኃጢአታችንን በራሱ አነጻ ሲል ጻፈላቸው። «ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቷልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል። ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቁጣው እንድናለን። ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ታረቅን።» እንዲል ሮሜ.5÷6–10።

ሐ/ መልአክ አለመሆኑን ለማስረዳት

/ይልቁንም ይበልጣል እንጂ/

ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል? የሚለው ጥያቄ ከተጠየቀበት ጊዜ አንሥቶ እስካሁን ድረስ የተለያዩ መልሶች ይሰጣሉ። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ለእርሱ ክብር ምስጋና ይግባውና «መልአክ» ነው የሚል ነው። ይህ መልስ ከዚያ ዘመን እስካሁን ዘልቆ ይገኛል። መነሻቸውም «በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል።» /ዳን.12÷1/ የሚለው ነው። በእርግጥ ቅዱስ ሚካኤል የመላእክት አለቃ ነው። «የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነ ጋገር፦ ጌታ ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብን ፍርድ ሊናገረው አልደፈረም።» ይሁዳ ቁ. 9 እንዲል።

ይልቁንም ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛተሰ.4÷16–17 ስለ ጌታችን ዳግም መምጣት በተናገረበት አንቀጹ «ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና...» ሲል የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ለንጉሥ ክርስቶስ ፊታውራሪ እንጂ የተገለጠው ጌታ ራሱ ቅዱስ ሚካኤል አለመሆኑን ገልጧል። ይልቁንም በሥጋ መገለጡ ቅዱሳን መላእክት እንዲያዩት ዕድል መስጠቱን «በሥጋ የተገለጠ...ለመላእክት የታየ» በማለት ገልጦ ታል። 1ኛጢሞ. 3÷16።

የተገለጠው ጌታ ሰው የሆነው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ በራ

www.zeyeneta.com

እ.1÷8 ላይ «አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ» ብሏል። መልአክ ነው ካልን ግን አልፋና ዖሜጋ ሊሆን አይችልም፣ መላእክት ጥንት ያላቸው ዘመን የሚቆጠርላቸው ፍጥረታት ናቸውና። ቅዱስ ዳዊት «መላእክቱ ሁሉ ስገዱለት» ያለውም ጌታችን መልአክ ስላልሆነ ነው። መዝ/96÷7።

መልአክ ነው ብለን ስናበቃ «ኃጢአታችንን» አነጻ ብለን ለመናገር አይቻለንም። ምክንያቱም መላእክት እንደ ሰው ልጆች ሥጋና ደም የላቸውምና። «መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ» መዝ.103÷4 እንዲል መላእክትም እዳምን ከኃጢአቱ ሊያነጹት ሊያድኑትም አይቻላቸውም፣ «ከእኔ በቀር ሌላ መድኃኒት የለም» እንዲል ሆሴ.13÷4 ቀድሞ የፈረደብን በኋላም አምላካዊ ፍርዱን ሊያነሣልን የሚቻለው እርሱ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ መልአክ አይደለም። «እርሱ ሰብሮናልና÷ እርሱም ይፈውሰናል፣ እርሱ መትቶናል÷ እርሱም ይጠግነናል።» ሆሴ.6÷1 «እኔ እግዚአብሔር ነኝ÷ ከእኔ ሌላ የሚያድን የለም።» ኢሳ.43÷11 እንዲል።

ቅዱስ ጳውሎስም «ኃጢአታችንን በራሱ አነጻ» ያለው ኃጢአትን ማንጻት የሚቻለው በተዋሕዶ ክብሩ፣ ማንንም ረዳት ይሆነው ዘንድ ሳይሻ፣ በገዛ ደሙ ቤተ ክርስቲያንን የዋጀ እርሱ የባሕርይ ጌታና አምላክ እንጂ መልአክ አይደለም ለማለት ጻፈልን። ሐዋ.20÷28። ይልቁንም ከመላእክት መብለጡን ሲገልጽ «ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ መጠን እንዲሁ ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል።» ዕብ.1÷4 ይላል። ምክንያቱም መላእክቱ «አገልጋዮቹ» ሲባሉ እርሱ ግን «የጌቶች ጌታ፣ የአማልክት አምላክ» መባልን ወርሷል።/መዝ.81÷1/ስለሆነም መላእክት የእርሱ አገልጋዮች ናቸው። ማቴ.4÷11። ለፈለገው አገልግሎትም ይልካቸዋል። «ነገር ግን እግዚ

አብሔር ኃይሉን የሚገልጽበትን ትጣቱን ሊያሳይ ቢወድ ትዕግሥቱን ካሳየ በኋላ ለማጥፋት የተዘጋጁትን ቁጣውን የሚገልጽበትን መልአክ ያመጣል። ዳግመኛም የጌትነቱን ብዛት ሊያሳይ ቢወድ አስቀድሞ መርጦ በወደዳቸው ለይቅርታ የተዘጋጁትን የይቅርታ መላእክትን ያመጣል።» ሮሜ.9÷22–23 እንዲል።

1.6 በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ /ዕብ.1÷4/

ይኽን ኃይለ ቃል ለመረዳት ቢያንስ ሁለት ነገሮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይጠቅማል።

1. የእግዚአብሔርን ባሕርይ፦

የእግዚአብሔርን ባሕርይ መመርመር የሚቻለው ፍጥረት የለም። እርሱ ራሱ ግን እንደ ወደደው መጠን የገለጠልን አለና በመጻሕፍት ከተጻፈው በመምህራን ከተነገረው በጥቂቱ እንጽፋለን። እግዚአብሔር በባሕርይው ምሉዕ ነው። ምልዓቱም በጉተራ እንደ ተቀመጠ እህል በዚህ ዓለምም እንደ መላ አየር /ነፋስ/ በመሠረት ላይ የተቀመጠ በጽንፍም የተወሰነ አይደለም። ሰው ጫማውን እንዲሸከም ዓለሙን የተሸከመ እንጂ ዓለሙ ሊሸከመው የማይቻለው ነው። የዓለማትም ዓለማቸው እግዚአብሔር ነው፣ ይዟቸው የሚኖር እርሱ ነውና።

በርባሮስ መሠረቱ፣ እርያም ቁመቱ፣ ከአድማስ እስከ አድማስ ስፋቱ የማይባል፣ በሰማይ በምድር በዕመቅ በአየር የመላ፣ የማይኖርበት ቦታ አለ ተብሎ የማይነገርለት ፍጹም አምላክ ነው። ስለዚህ እንደ ግዙፉን ፍጥረታት ለእግዚአብሔር ባሕርይ አቅጣጫ /ቀኝና ግራ፣ ፊትና ኋላ፣ ላይና ታች.../ ወርድ፣ስፋት ቁመት... የመሰሉት ሁሉ የሚስማሙት እንዳልሆነ ይልቁንም ሰም ለበስ ወርቅ /ምሥጢር/ እንዳላቸው መገንዘብ ያስፈልጋል።

2/ የቅዱሳት መጻሕፍት ብሂል፦ የቅዱሳት መጻሕፍት የአጻጻፍ

www.zeyeneta.com

ብሂል ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር ነው። በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት እንደ ተጻፉ በእርሱም አቅኝነት ሊተረጉሙ እንደሚገባ ተጽፏልና። 2ኛጴጥ.1÷20። ምክንያቱም የተጻፉት ለሰው ስለሆነ ምሥጢራዊውን ነገር ሁሉ ሰው በሚያውቀው ይገልጣሉ። ይልቁንም ከሰው ስሜትና ኅሊና የመረዳት አቅም በላይ ስለሆኑት ነገሮች ሰው በሚያውቀው ምሳሌ መጻፋቸው የመጻሕፍት ልማድ ነው። እግዚ አብሔር አዳምን ጠርቶ «ወዴት ነህ?» እያለ መጠየቁ እንደ ሰው አሳብ እግዚአብሔር አዳም ያለበትን ያላወቀ ሊያስመስለው ይችላል፤ ይኸ ግን ከመነገር በላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለጥ የተደረገ፣ ለሰውም ሊናገሩት የሚስማማ የአጻጻፍ ብሂል ነው። ወደ ርእሳችን ከመመለሳችን በፊትም ለምሳሌ ያህል የአንድን ቃል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሥጢር መመልከት የበለጠ ግልጽ ያደርግ ልናል።

<u>ቆመ</u> ምን ማለት ነው?

ሀ/ **በእግር ጸንቶ በመሠረት ላይ መቆም**:– በመሠረት ላይ በእግረ ሥጋ ወደ ላይ መቅናት /ቀጥ ማለት/ ነው። መቆም የግድ መሠረትን ይጠይቃል፤ እስከ ጽንፍም /ጣሪያም/ መድረስ አይቻ ልም። ይህ በእኛ ዘንድ የተለመደው ለሥጋዊ ለደማዊ ፍጥረት የታወቀው የተረዳው ትርጉም ነው። «እርሱም ዳሰሰኝ ቀጥ አድርጉም አቆመኝ።» ዳን.8÷18 እንዲል።

ለ/ <u>መግለጥ</u>:– ከላይ ከለመድነው ውጭ ቆመ የሚለው ቃል የማይወሰኑ፣ ቁኝና ግራ የሌላቸውን፣ የፈጣሪንም ሆነ የረቂቃን ፍጡ ራንን ወይም የመናፍስትን መገለጥ ያመለክታል። ለምሳሌ አብርሃም ቅድስት ሥላሴን በእንግድነት እንደ ተቀበለ በተጻፈበት የመጽሐፍ ክፍል ላይ «ዓይኑን አነሣና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ» /ዘፍ.18÷2/ ይላል፤ ተገለጡለት ለማለት ነው። ምክንያቱም እግዚ

አብሔር መንፈስ ነው። መሠረትና ጽንፍ የለበትም። ነገር ግን ለአብርሃም በሰው አምሳል ማየት እንዲቻለው ፈቀዱለት፤ በወደዱትም መጠን ማስተዋል በሚችለው መንገድ ተገለጡለት ማለት ነው። «እኔም ዳንኤል ራእዩን ባየሁ ጊዜ ማስተዋሉን ፈለግሁ፤ እነሆም የሰው ምስያ በፊቴ ቆሞ ነበር።» /ዳን.8 15/ ሲልም ተገለጠልኝ ማለቱ ነው። «የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው።» ሉቃ.1÷11 የሚለውም ይህንኑ ያስረግጥልናል።

ሐ/ <u>ግሣዴ</u>:– ከዚህም በላይ /ቆመ/ የሚለው ቃል /አማለደ/ የሚለውንም ትርጉም በቅዱሳት መጻሕፍት ይዞ እንመለከተዋለን። «አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር።» ዘፍ.18÷22 መባሉ እግዚአብሔር ውሱን አካል÷ ፊትና ጀርባ፣ ቀኝና ግራ አለው ለማለት አይደለም። ይልቁንም የእግዚአብሔርን ገጸ ምሕረት እየተለ ማመነ፣ ማር! ይቅር በል! በማለት እያማለደ ነበር ለማለት ነው።

«እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ» ሉቃ.1÷19 ሲልም የእግዚአብሔር ባለሟል ነኝ፣ ገጸ ምሕረቱን ደጅ ጠንቼ፣ ምሕረቱን ተቀብዬ ለደስታ ለብሥራት፣ ለምሕረት ለይቅርታ የምላክ የእግዚአብሔር ታማኙ ነኝ ማለቱ ነው።

«ዳግመኛም የጌትነቱን ብዛት ሊያሳይ ቢወድ÷ አስቀድሞ መርጠ በወደዳቸው ለይቅርታ የተዘጋጁ የይቅርታ መላእክትን ያመጣል።» /ሮሜ.9÷23/ ከተባለላቸው አንዱ እርሱ ነውና። ይልቁንም ቅዱስ ዳዊት ስለ ሙሴ አማላጅነት በተናገረበት አንቀጽ «የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ፣ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ።» በማለት «መቆም» ማማለድ መሆኑን በማያሳብል መንገድ ገልጾታል። መዝ.105÷23።

እንግዲህ ከላይ ያስቀመጥናቸውን ለግንዛቤ የሚረዱ ነገሮችንና ምሳሌውንም ከያዝን ወደ ኃይለ ቃላችን ትርጉም መመለስ

www.zeyeneta.com

እንችላለን::

„ቀኝ» የተባለ ምንድን ነው? በትዱሳት መጻሕፍት አገላለጽ ሰም ለበለ ወርቁስ /ምሥጢሩ/ ምንድን ነው? የሚለውን እንመለከታለን::

1.6.1 አቅጣጫ:- በትዱሳት መጻሕፍት ትምህርት መሠረት ዓለ ምን ለማወቅ የሚረዱ ስምንት አቅጣጫዎች አሉ:: አራቱ ዐበይት ሲ ሆኑ አራቱ ደግሞ ንዑሳን ናቸው:: ዐበይት አቅጣጫዎች ምሥራቅ፣ ምዕራብ፣ ሰሜንና ደቡብ ሲሆኑ መስዕ /ሰሜን ምሥራቅ/፣ አዜብ /ደቡብ ምዕራብ/፣ ሌብ/ደቡብ ምሥራቅ/ እና ባሕር /ሰሜን ምዕራብ/ ደግሞ ንዑሳን አቅጣጫዎች ናቸው:: አንድ ሰው በአንድ ጊዜ አራ ቱን አቅጣጫዎች በሰውነቱ ማመልከት ይቻለዋል::

በዚህም መሠረት ፊቱን ወደ ምሥራቅ ሲያደርግ ወደ ደቡብ የሚያመለክተው ግማሹን የሰውነቱን ክፍል ቀኜ ይለዋል:: ቀኝ እጄ፣ ቀኝ እግሬ፣ ቀኝ ዓይኔ፣..... እንዲል:: ሙሴም ግብፃዊውን ከመግደሉ በፊት «ወዲህና ወዲያም ተመለከተ» /ዘጸ.2÷12/ መባሉ ፊት ጀርባውን፣ ቀኝ ግራውን ለማለት ነው:: «ወደ ቀኝ ተመለከትሁ አየሁም÷ የሚያውቀኝም አጣሁ» /መዝ.141÷4/ ሲልም አቅጣጫን ያመለክታል:: ከዚህ በኋላ ግን ለእነዚህ ብልቶችም ቅጽል መጠሪያ ሆኖ እያገለገለ እንደሆነ መረዳት ይቻላል::

1.6.2. <u>ወንጌል</u>:- በትዱሳት መጻሕፍት ወንጌል ቀኝ ተብላለች፣ ጸድቃንን በቀኙ፣ ኃጥአንን በግራው ያቆማቸዋል እያለች እግዚአ ብሔር ለቅዱሳኑ ስላዘጋጀው ክብር የምትናገር ስለሆነ፣ ዳግመኛም እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሡት ሰዎች ሁሉ የጌታችንን አምላክነት የምትነግርና «በኋላዬ ሊከተለኝ የሚወድ መስቀሌን ተሸክሞ ይከተለኝ» የሚለውን ትምህርት በሰፊው አስረድታ ሰዎችን ወደ ተጋድሎ የምትመራ በኋላም ለክብር የምታበቃ ስለሆነ ቀኝ ትባላለች:: በመኃ.2÷7 ላይ መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን «ግራው ከራሴ

በታች ናት÷ ቀኙም ታቅፈኛለች::» ሲል ተናግሮላታልና::

ከላይ እንደተጠቀሰው የአንድ ሰው እጆች ቀኝ ግራ እንደሚባሉ ከአንድ እግዚአብሔር የተገኙትን አራትን ግራ ወንጌልን ቀኝ ብሏቸዋል:: ጠቢቡ ሰሎሞን በምሥጢራዊ መዝሙሩ አራትን ግራ ያላት አራት መሥዋዕት ብትሠዋም፣ ደም ብታፈስም፣ አንገሉቷ ፍጹም ሆኖ ሰውን ወደ ቀደመ ክብሩ ሊመልስ ያልቻለና ቀኝ ስለ ቀኝ፣ ዓይን ስለ ዓይን፣ በሬም ስለ በሬ ይሰጥ የምትል የበቀል ሕግን የያዘች ኃጣርን የምታመጣ በመሆኗ ነው:: ወንጌል ግን ሠሪዋም ካህኗም ራሱ ጌታችን ነውና፣ መሥዋዕቱ ራሱ ሆኖ፣ የባሕርይ ገንዘቡ በሆነ በራሱ ክህነት ራሱን ሠውቶ፣ ራሱ መሥዋዕቱን ተቀብሎ ወደ ቀደመ ክብሩ ሰውን መልሶታልና ዳግመኛም ቀኝ ጉንጭህን ቢመታህ ግራህን ስጠው፣ እጀ ጠባብህን ይወስድ ዘንድ ለሚወድ መጐናጸፊያህን ጨምርለት የምትል ፍጹም ሕግ÷ ቅዱሳ ንንም ለፍጹምነት ያበቃች ናትና ቀኙ ተባለች::

ለአሪት ግን መገኛዋ እግዚአብሔር ቢሆንም ሠሪዋ ሙሴ ነው:: እርሱም ሕዝቡ ሕገ አሪትን ፈጽመው መንግሥተ ሰማይት መግባት አልተቻላቸውምና ስለዚህ ሙሴ የሠራትን አሪት «ግራ» ሲላት ጌታ የሠራትን ግን «ቀኝ» አላት፣ ለክብር አብቅታናለች፣ ታበቃ ናለችምና::

1.6.3. ክብር ልዕልና:- እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚሰጠው ክብርና ባለሟልነት፣ ረድኤትና አጋ በትዱሳት መጻሕፍት ቀኝ እየተባለ ተገልጧል:: ግልጽ ለማድረግ በሦስት ከፍለን እንመለከተዋለን:: «የፀሐይ ክብር አንድ ነው፣ የጨረቃም ክብር ሌላ ነው፣ የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፣ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ይለያልና::» 1ኛቆሮ.15÷41::

ሀ/ የድንግል ማርያም ክብር ልዕልና ቀኝ ይባላል:- ቅድስት

www.zeyeneta.com

ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ሰው ሆኖ ይገለጥባት ዘንድ፣ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ መለኮታዊ አካል ይታይባት ዘንድ የበቃች አድርጉ ያዘጋጃት ዘላለማዊ ማደሪያው ናት። «መቅደስ ዘኢ ትትነሰት» የማትፈርስ መቅደስ እርሷ ናትና። /ውዳሴ ዘቀዳሚት ተመልከት።/

መጽሐፍ «እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም።» /ዮሐ.1÷18/ እንዲል ሊያየውም የሚቻለው ፍጥረት የለም። የሚቀርበው በሌለ ብርሃን ውስጥ ይኖራልና። ነገር ግን «የአግልክት አምላክ በጽዮን ይታያል» /መዝ.83÷7/ ተብሉ የተነገረው ትንቢት የተፈጸመላት እግዚአብሔርን የማየታችን ምክንያት እርሷ ናት። ይኸውም የሚመስለው በሌለ መንገድ ጸንሳ የሚመስለው በሌለ መንገድ ወለደችው። የሚሣነው የሌለ እርሱ በማይመረመር ግብር ተጸንሶ በመወለዱ እርሷንም ከፍጥረት ለይቶ መርጦ አክብሯታል።

ይህንንም ክብር ያገኘችው ከእኛ ከፍጡራን ሳይሆን ከራሱ ከፈጣሪ ነው። ይኸውም እርሱን ከመጽነሷ በፊት በሊቀ መላእክት በቅዱስ ገብርኤል «ጸጋን የተመላሽ ሆይ፥ ደስ ይበልሽ» በመባሏ ለእኛ ታውቋል። ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።» መዝ.44÷9 ሲል መናገሩ የንጉሠ ሰማያት ወምድር የጌታችንን እናቱ እርሱ በሰጣት ክብር ልዕልና ጸንታ ትኖራለች ለማለት ነው። ይኸን ክብር ልዕልና ከፍጥረት ወገን ያገኘው የለም። ወላዲተ አምላክ ከመባልም በላይ ክብር ልዕልና የለም።

ለ/ የቅዱሳን ክብር ልዕልና ቀኝ ይባላል፦ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የሚሰጠውን ክብር ይህ ነው ብሉ መናገር አይቻለንም። «የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርጠ

ግልናልና፥ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው።» /2ኛቆሮ.4÷18/ ተብሉ እንደ ተጻፈ ክብሩ አይታይምና። «እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመስል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።» /2ኛቆሮ.3÷18/ ሲል የቅዱሳን ክብርም ከእግዚአብሔር የተገኘ እንደሆነ ይገልጣል። ክብሩም ምን እንደሆነ እንደማይታወቅ «ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።» /1ኛዮሐ.3÷2/ ሲል ገልጦልናል። ክብሩ ከእግዚአብሔር ነው የሚመስሉትም እርሱን ነው። በተጋድሏቸውም ከክብር ወደ ክብር ያድጋሉ። ስለዚህ በመጨረሻ በፍርድ ጊዜ በተሰጣቸው ክብር ጸንተው እንደሚኖሩ ሲገልጽ «በጐችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራ ያቆማቸዋል» አለ። ማቴ.25÷33።

ቀኝ እጅ ኃያል፣ ፈጣን፣ ቅን እንደ ሆነ ሁሉ ጸድቃንም በሃይ ግናት በምግባር ኃያላን፣ ፈጣንና ቅኖች ስለሆኑ እርሱም በቀኙ /በክብር/ እንዲገለጹ ያደርጋቸዋል አለ። ኃጥኣንም እንደ ግራ እጅ ጠማሞች፣ ለበጌ ሥራም ደካሞችና ሰነፎች ናቸውና በግራ /በኃጣር/ ይገልጣቸዋል አለ። /መቆም ማለት መገለጥ ማለት እንደሆነ ማስታወስ ይገባል/ «ኃጣር» ውርደት፥ ሞት ማለት ነው። «በአለቆችም ላይ ኀጣርን አፈሰሰ፥ መንገድም በሌለበት በምድረ በዳ አሳታቸው» /መዝ.106÷40/ ተብሉ በምድረ በዳ ወድቀው ስለ ቀሩ ስለ እስራኤል ዘሥጋ እንደ ተጻፈ። በወንጌልም «መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና» /ዮሐ.5÷29/ ተብሏል።

www.zeyeneta.com

ሐ/ ለሰብአ ዓለም የሚሰጥ ክብር ረድኤት ቀኝ ተብሏል፦ እግዚአብሔር ለወዳጆቹ በማይታየውና በሚመጣው ዓለም ያልተገለጠ ክብር እንዳዘጋጀ ሁሉ በዚህ ዓለምም በረድኤት ያጸናቸዋል÷ ሞገስና ክብርም ይሰጣቸዋል። ይኸም የእግዚአብሔር ቀኝ ተብሎ በመጻሕፍት ተገልጧል። «በጠላቶቼ ቁጣ ላይ እጅቼን ትዘረጋለህ÷ ቀኝህም ታድነኛለች።» /መዝ.137÷7/ ማለቱ ረድኤትህ ክብርህ ታድነኛለች ሲል ነው። «በዚያ እጅህ ትመራኛለች ቀኝህም ትይዘኛለች።» /መዝ.138÷10/ «ቀኝህን ዘረጋህ÷ ምድርም ዋጠቻቸው።»÷ /ዘጸ.15÷12/ በማለት እስራኤል ዘሥጋ እነርሱን ማዳኑን፣ ጠላቶቻቸውንም ማጥፋቱን በመጥቀስ በረድኤት አለመለየቱን ገለጹ። ረድኤት ርዳታ ማለት ነው። «አንሣእኩ አዕይንትየ መንገለ አባር፣ እምአይቴ ይመጽእ ረድኤትየ። ረድኤትየሰ እምኀበ እግዚአብሔር ዘገብረ ሰማየ ወምድረ። ዓይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፣ ረዳቴ ከወዴት ይመጣ? ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።» መዝ.120÷1–2 እንዲል።

1.6.4. <u>ሥልጣን ቀኝ ተብሏል</u>፦ ሥልጣን የእግዚአብሔር የባሕርይ ገንዘቡ ነው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሰውን በአዲሲቱ ሰማያዊት መንግሥት በኢየሩሳሌም እስከሚያኖረው ድረስ በዚህ ምድርም በእርሱ ረድኤትነት እንዲያስተዳድሩን ሥልጣኑን የሰጣቸው ሰዎች አሉ። «ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለሥልጣኖች ይገዛ ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።» /ሮሜ.13÷1/ እንዲል። ስለዚህ ሥልጣን ለሰውም ለእግዚአብሔርም ይቀጸላልና አለው። ይህንንም በሁለት ከፍለን እንመለከተዋለን።

ሀ/ <u>ለሰዎች ሲቀጸል</u>፦ ሥልጣን ለሰዎች ተቀጽሎ «ቀኝ» ተብሎ በቅዱሳት መጻሕፍት ተገልጿል። ቅዱስ ዳዊት ስለ ራሱ መዋረድ

በተናገረበት አንተጽ ላይ «የቀባኸውንም ጣልኸው፣ የባርያህንም ኪዳን አፈረስህ... የጠላቶቹንም ቀኝ ከፍ ከፍ አደረግህ።» ይላል መዝ.88፡38 42። ጠላቶቼን በሥልጣን ከፍ ከፍ አደረግሃቸው ማለቱ ነው። በመዝ.143÷8 ላይም «ቀኛቸው የሐሰት ቀኝ ከሆነ÷ ከባዕድ ልጆች እጅ አስጥለኝ።» በማለት የጸለየው ሥልጣናቸው የሐሰት ሥልጣን ከሆነ፣ መማለጃን ተቀብለው ንጥኡን ጻድቅ፣ ጻድቁንም ንጥእ ከሚያደርጉ፣ ደህውን ከሚበድሉ ፍርድ ከሚያጓድሉ ሰዎች እጅ አስጥለኝ። ይኸን በማድረጋቸው በላያቸው ላይ ከምትመጣ መቅሰፍት ጠብቀኝ ሲል ነው። ቀኝ መባሏም እግዚአብሔር ሥልጣንን ለሰዎች የሰጠው በቅንነትና በእውነት በመፋጠን ሰዎችን አገልግለው እንዲከብሩበት ስለሆነ ነው።

ለ/ ለእግዚአብሔር፦ በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ሥልጣን ለእግዚአብሔር ስትነገር የባሕርይ ገንዘቡ ናት። ይህችውም በቅዱሳት መጻሕፍት «ቀኝ» እየተባለች በሚረዳን ቋንቋ ተጽፋለች። በቀኝ እጅ ብዙ ሥራን እንደምንሠራበት ሁሉ ፍጥረትን ሁሉ የእግዚአብሔር ሥልጣን ፈጥራለችና ነው። «ወደ መቅደሱም ተራራ አገባቸው፤ ቀኙ ወደ ፈጠረችው ወደዚች ተራራ።» መዝ.77÷54 እንዲል። ይልቁንም ቅድስት ሥላሴ እንዲት ሥልጣን እንዳለቻቸው ሲናገር በመዝ. 117÷16 ላይ «የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች። የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ፤ የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች።» ብሏል።

እስራኤል ዘሥጋም እግዚአብሔር በረድኤት እየመራ ካወጣቸውና ባሕረ ኤርትራን ከፍሎ ካሻገራቸው በኋላ ገሥግሶ ከኋላቸው ደርሶ ወደ ተከፈለው ባሕር የገባውን ፈርዖንና ሠራዊቱን ባጠፋላቸው ጊዜ ሥልጣን ዜሴ የእግዚአብሔር መሆኑንና በእርሱም እንደ ተደረገ ለመግለጽ «አቤቱ÷ ቀኝህ በኃይል ከበረ÷ አቤቱ÷

www.zeyeneta.com

ቀኘህ ጠላቱን አደቀቀ::» ዘጸ.15÷6 ሲሉ ዘምረዋል::

እንግዲህ ቀኝ ከብዙ በጥቂቱ ይሽን የመሰለ ትርጉም ካለው ቅዱስ ጳውሎስ «በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ» ሲል የጻፈው ምን ለማለት ነው? ዳግመኛም ቁጥር 12 ላይ መዝ.109÷1 ጠቅሶ «ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ፤ ከቶ ለማን ብሏል?» ማለቱ ስለ ምንድን ነው?

ሀ/ <u>በሰማያት</u>:- ማለቱ መጀመርያውን በክብሩ በልዕልናው ማለቱ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር በሰማይ ያለ በምድር የሌለ ተብሎ ቦታ የሚወሰንበት አይደለምና:: «እናንተስ እንዲህ ጸልዩ:- በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ...» /ማቴ.6÷9/ ማለቱ በልዑል መንበርህ በባሕርይ ልዕልናህ ጸንተህ የምትኖር በሉ ለማለት ነው::

ለ/ <u>ቀኝ</u>:- ሥልጣን፣ ዕሪና ማለት ነው:: ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋ ቢለብስም በሥልጣኑ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዕሩይ /ትክክል/ ነውና::

ሐ/ <u>ተቀመጠ</u>:- ይህን ማለቱ በመጽሐፍ «ወረገ» ተብሎ ነበርና «የት ደረሰ?» ለሚለው ጥያቄ እርሱ የተሠወረ ረቅቆ የጠፋ ሳይሆን አሁንም ቅድመ ተዋሕዶ በነበረው የባሕርይ ጌትነት፣ ሥልጣንና ክብር አለ ለማለት ነው:: «ተቀመጠ» የሚለው ቃል አስፈላጊነትም ቀድሞ በሥላሴ ዘንድ ያልነበረ ግዙፍነት፣ በአካላዊ ቃል ፍጹም ተዋሕዶ ሥጋ ብእሲ /የሰው ሥጋ/ ለዚህ መብቃቱን፣ በተዋሕዶ እምላክ ለመሆን መታደሉን ለመናገር ነው::

መ/ <u>ጠላቶች</u>:- እንዲህ የተባሉት ደግሞ አይሁድ፣ መናፍቃን /ተጠራጣሪዎች/ እና አጋንንት ናቸው:: ጌታችን በወንጌል «ሰዎች ሲተኙ ግን ጠላት መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድ ዘርቶ ሄደ::» ማቴ.13÷25 እንዲል::

አጋንንት ጥንት ጀምረው በንጹሐን ኑሮ ላይ የጉስቁልና

ምክንያቶችና አዳምን ከእግዚአብሔር የለዩ እስካሁንም ይህንኑ የሚያደርጉ ናቸው::

አይሁድም በትንሣኤው ማግሥት «ሰው ነው ሞቷል፤ ደቀ መዛሙርቱ ሰረቁት እንጂ አልተነሣም» እያሉ ቀድሞ ከፈጸሙት በላይ የመጀመሪያ ግብራቸውን በማጽናት ለክርስትና ራሳቸውን ጠላት አድርገዋል:: መናፍቃንም ከንጹሑ የሐዋርያት ትምህርት ኋላ ለኋላ እየተከተሉ ኑፋቄንና በተአምራት ማታለልን ዘርተዋልና ጠላቶች ተብለዋል:: እነዚህ ቀድሞም በነብያት እንደ ነበሩ ማስታወስ ያስፈልጋል:: ለአብነትም ከይሁዳ ወደ ቤቴል በተላከው የእግዚአብሔር ነቢይ ላይ ሐሰትን ዘርቶ ሞትን ያመጣበትን ሐሰተኛ ነቢይ ማስታወስ ይቻላል:: 1ኛነገ.13÷1-ፍጻሜ::

ሠ/ <u>እግር</u>:- እንዲህ የተባሉት ደግሞ ሥልጣን፣ ምእመናንና መላእክት ናቸው:: መላእክትንና ምእመናንን «እግር» ያላቸው ስለ ምንድን ነው? ቢሉ እግር የአካል አንድ ብልት እንደ ሆነ ሁሉ መላእክትና ምእመናንም የክርስቶስ አካሉ የምትሆን የቤተ ክርስቲያን ብልቶች ስለሆኑ ነው:: አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደሆኑ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው::» 1ኛቆሮ.12÷12 እንዲል:: እግርም በራሱ ሕይወት እንደሌለው የመላእክትም የምእመናንም ሕይወታቸው እግዚአብሔር ነው:: «እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤... እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ:: ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና» ዮሐ.15÷5 እንዲል:: ሰውን ተሸክሞ ወደ ልዩ ልዩ ቦታ የሚወስደው እግር እንደሆነው ሁሉ የሥላሴን መልእክት ይዘው የሚጓዙት መላእክትና ምእመናን ናቸውና::

ከላይ «ቀኝ»÷ ሥልጣን ነው እንዳልን፥ አሁንም «እግር» ማለት

www.zeyeneta.com

ሥልጣን ማለት ነው ብለናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ አንድን ነገር መግለጹ በትጉሳት መጻሕፍትም ግጻፉ እኛ ነገሩን እንድንረዳው የሚያግዘበት መንገድ ስለሆነ ነው። መንግሥተ ሰማያትን በብዙ ምሳሌ ማስረዳቱም የዚሁ አስረጂ ነው። ሥልጣን «ቀኝ»÷ «እግር» ከመባሉም አልፎ «ቀንድ» እንደተባለም በትጉሳት መጻሕፍት ሠፍሯል። «እውነቴና ምሕረቴ ከእርሱ ጋር ነው፣ በስሜ ም ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል፡» መዝ.88÷24 ተብሎ በእግዚአብሔር ስም የቅዱስ ዳዊት ሥልጣኑ ከፍ ከፍ እንደሚል ተገልጿል። ስለ ጌታችንም በመዝ.111÷9 ላይ «በተነ ለችግረኞችም ሰጠ፣ ጽድቁ ለዘላለም ዓለም ይኖራል፣ ቀንዱ /ሥልጣኑ/ በክብር ከፍ ከፍ ይላል።» ተብሎ ተጽፏልና።

በመሆኑም እግር ሥልጣን መባሉ በእግር እንዲረግጡበት እግዚአብሔርም የፈጠረውን ፍጥረት ሁሉ በእግሩ ርግጥ በእጁ ጭብጥ አድርጉ የሚገዛው በሥልጣኑ ነውና እግር ተባለ። ቅዱሳን መላእክትና ምእመናንም የሥልጣኑ መገለጫዎች ናቸውና እግር ተባሉ። ስለዚህ በትንቢት አስቀድሞ «ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ» ሲል፦

ሀ/ ለጌታችን ፦ በሞት ላይ የሠለጠነ ዲያብሎስን በሞትህ እስከምትገድልበት እስከ ዘመነ ሥጋዌ «በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን በሞት እንዲሽር፣ ይኸውም ዲያብሎስ ነው።» ዕብ.2÷14 «የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፣ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና። ነገር ግን፦ ሁሉ ተገዝቷል ሲል፣ ሁሉን ካስገዛለት /ከእግዚአብሔር/ በቀር መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን እንዴት ፈቀደለት?

– ለሞት ከራሱ በቀር ሁሉን ያስገዛለት እግዚአብሔር ነው። ስለዚህም የሰው ሁሉ ጠላት ተባለ። ለሞትም ሁሉ እንደተገዛለት

ቢቀር ከእግዚአብሔር ቀጥሎ ጌትነት ያለው በመሆን ይኖር ነበር። ይህ እንዳይሆን ግን «ሁሉ በሁሉ» ይሆን ዘንድ ሁሉ የተገዛለት ሞት ሁሉን ያስገዛለት ወልደ እግዚአብሔር በፈቃዱ በሞተ ጊዜ ሁሉን ገዛ። የእግዚአብሔር ሞት ግን ሞትን ራሱን ገደለውና ሥልጣኑን በሞት ሻረበት። ሞትን የእግዚአብሔር ሞት ባይገድለው ኖሮ ሞት ነፍሳትን ሁሉ እያጋዘ አምላክ የሆነ በመሰለን ነበር። ስለዚህ የእግዚአብሔር ሞት «ሞትን» የመግደል ሥልጣን ነበራትና ጠላት የተባለ በሞት ላይ የሠለጠነ ዲያብሎስ በእግዚአብሔር ሕይወት ሳይሆን በእግዚአብሔር ሞት ተገደለ። የእግዚአብሔር ሞት ምን ያህል ልዩ ኃይል እንዳለው ማስተዋል ይገባል። «ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ» ማለትም ሁሉን የገዛ ሞትን፣ ሁሉን ባስገዛለት በእግዚአብሔር ሞት ይገድለው ዘንድ ማለት ነው።

ለ/ ያልተፈጸመች ሞተ ሥጋ ተፈጽማ ነፍስና ሥጋ ተዋሕደው በአዲሲቱ መንግሥት ማስተዳደር እስከሚጀምርባት እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ፦

ቅዱሳት መጻሕፍት ኤልያስና ሄኖክን የመሰሉ ሰዎች ከሞት እንደ ተሠወሩ ይናገራሉ። ዕብ.11÷5፣ 2ኛነገ.2÷7–14። በሥጋ ልደትም አባትን ልጅ እየተካ አንዱ ሲሞት ሌላው እየመጣ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ሞተ ሥጋ እንደ ሠለጠነ ይኖራል። ለወልደ እግዚአብሔር ግን ያልተገዛ ስለሆነ አይደለም፣ ሁሉም ይሞቱ ዘንድ ስላላቸው ነው እንጂ። ሁሉንም አስገዝቶለታል ተብሎ ተጽፏልና። «ሁሉን ከእርሱ በታች ባስገዛ ጊዜ ያልተገዛለት ምንም አልተወምና። አሁን ግን ሁሉ እንደተገዛለት ገና አናይም።» /ዕብ. 2÷8/ በማለት ሞተ ሥጋን እያየን እንደሆነ ገልጿል።

በዕለተ ምጽአት ግን ሞተ ሥጋ ትፈጸማለች። «ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ።» ራዕ.20÷14። ቀዳማዊ ቃል

www.zeyeneta.com

ቀድሞ ዓለሙን ካለመኖር ወደ መኖር እንዳመጣው ያንጊዜ ደግሞ ከመኖር ወደ አለመኖር ያሳልፈዋል። «በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፡ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፣ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል።... ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።» /2ኛጴጥ.3÷10-13/ እንዲል ያን ጊዜ ለኃጥኡም ለጻድቁም የክርስቶስ ክብር ይገለጥለታል። ይኸውም አሁን ከሚታ ወቀው በላይ የሆነው የባሕርይ ጌትነቱ ነው። «ወዳጆች ሆይ÷ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፣ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።» /1ኛዮሐ.3÷2/ ሲል ክብሩ እንዳልተገለጠ ገልጿልና። ያን ጊዜ ግን ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል። ራእ.1÷7።

«ከአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይና በዚህ ዓለም ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሊመጣ ባለው ዓለም ደግሞ ከሚጠራው ስም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ሥፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው።» /ኤፌ.1÷21-23/ ተብሎ እንደ ተጻፈ የዓለማት ፈጣሪ ዓለሙን አሳልፎ በሁሉም ላይ ጌትነቱ ታውቆ ይኖራል። ስለዚህ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ ማለት ዓለሙን እንደመፍጠር ያለ ዓለሙን ማሳለፍ እስኪቻለው ድረስ በሥልጣን የተዋሐደው ሥጋ ከብሯል እስከዚህ ድረስ አለው። ከዚህ በኋላ ጌትነት ከዚህም በላይ አምላክነት የለም። ቅዱስ ጳውሎስ «ራስ» ያለው ከራስ በላይ አካል እንደሌለ ከእርሱም በላይ ባለሥልጣን የለም ለማለት ነው።

ሐ/ በሥጋዌ ተገልጠህ ዓለሙን ድል ነሥተህ ለምእመንም ዓለ ምን የምታሸንፍበት ኃይል ሰጥተህ ሐዋርያት ምእመናን መናፍቃንን በትምህርት አጋንንትን በኃይል በተአምራት አስኪያሳፍሯቸው

ድረስ፣ መናፍቃንን የሚያርዱበትን የሚያንተጠተጡበትን፣ አጋን ንትን የሚያስለቅቁበትን ኃይል መስጠት እስከሚቻልህ ድረስ በቀኝ /በዕሪና/ ያለህና የምትኖር ነህ ሲል ነው። ማቴ. 4÷1-12። እኔ ዓለ ምን አሸንፈዋለሁ። ዮሐ.16÷33። ዓለሙን ማሸነፍና ማሸነፍ የሚቻልበትን ግብር ማስተማር ኃይሉን መስጠት የሚቻለው አምላክ ብቻ ነውና። ይህን እስክታደርግ ድረስ በቀኝ የምትቀመጥ /በሥልጣን ሰሩይ/ የሆንክ ነህ ለማለት። «እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።» ሉቃ.24÷49 እንዲል።

መ/ መላእክት ጠላት የተባለ ዲያብሎስን እና የግብር ልጆ ቹን ከመንግሥተ ሰማያት በአፍአ /ውጭ/ በምትሆን በገሃነም እሳት እንዲ ጥሏቸው እስክታዝና እስኪፈጸም ድረስ በቀኝ የምትቀመጥ /በዕሪና ትክክል/ የሆንክ ነህ አለው። «የማይጠቅመውንም ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» ማቴ.25÷30 ብሎ ያዘዘ የሚያዝም እርሱ ነውና።

ስለዚህ «እስክግደርግልህ ድረስ» የሚለው ልዩ ምሥጢር ያለው መሆኑን መግንዘብ ያስፈልጋል። ይህንንም በሁለት መንገድ ማየት የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል።

1/ «እስክ» የሚለው ቃል ፍጻሜ የሌለው እስከ መሆኑንና በዚህ አግባብም የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ አምላክነት የሚያስረዳ ሆኖ መግባቱን ያሳያል። ምክንያቱም ሞትን ሳይገድል ዲያብሎስንም ሳይሽር «አምላክ» ነው ካልን ሞትን ሲገድልና ዲያብሎስን ሲሽር አምላክነቱ ይቀራል ማለት አይደለም፤ እንዲያውም ታወቀ+ተገለጠ+ ተረዳ ማለት እንጂ። ይኸም የሥነ ፍጥረትን ምሥጢር ይመስላል። እግዚአብሔር «በፈጠረው ፍጥረት እንዲታወቅ ሆነ» ማለት ከመፍጠሩ በፊት አምላክ አልነበረም ወይም ከፈጠረ በኋላ አምላክነቱ ቀርቷል

www.zeyeneta.com

አያስኝምና:: የተፈጠረውን ዓለም የሚያሳልፈው እርሱ ከሆነ «ቀድሞ አልፈጠረውም፣ ወደፊትም የአዲሲቱ ሰማይ አምላክ ሌላ ነው» አያስኝም:: በመሆኑም «እስከዚህ ድረስ» የሚለው የተባሉትን /ሞትን ለመግደል ዲያብሉስን ለመሻር/ ተገለጥህ እንጂ ከዚያም በፊት ከዚያም በኋላ አንተ በአንተነትህ /በአምላክነትህ/ ጸንተህ ትኖራለህ ለማለት ነው::

2/ «እስኩ–ድረስ» የሚለው ሐረግ በዚህ አገባብ የሚያመለክተው መጠነ ጊዜን ሳይሆን መጠነ ሥልጣንን ነው:: እስከ ዕለተ ምጽአት እስከ ዘመነ ሥጋዌ ድረስ ስንል ጊዜውን አይደለም፣ በተዋሕዶ ከብሮ አምላክ የሆነ ሥጋ ቀድሞ እግዚአብሔር የፈጠረውን ዓለም በተዋሕዶ መፍጠርን ወረሰ:: ወደፊትም ዓለምን ያሳልፋል:: በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ላይ ተቀምጦ በሦስትነት በአንድነት እስከ መመስገን ደረሰ፣ ሰው/ሥጋ/ አምላክ እስከ መሆን በቃ በማለት የጌትነቱ ፍጻሜ አምላክነት መሆኑን ለማስረዳት ነው:: «የዲያብሉስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ::» 1ኛዮሐ.3÷2 የዲያብሉስ የተንኮል ሥራ አዳምን «ዕፀ በለስ ብትበላ አምላክ ትሆናለህ» ማለቱ ነው:: ትለወጣለህ ሲለው ነው:: አዳም ግን ወደ አምላክነት አልተለወጠም÷ ሞተ እንጂ:: ታድያ ተንኮሉ እንዴት ፈረሰ? ስንል «ሰው አምላክ የሚሆነው ሊሆንም የሚቻለው እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ብቻ ነው:: ምክንያቱም ለአምላክ ሰው መሆን አይሳ ነውምና:: ሰው የሚሆነውም በውላጤ /በመለወጥ/ አይደለም፣ ቀድሞም ሰው የነበረ ያስመስላልና:: አምላክነቱ ሳይቀር ሰው መሆን ይቻለዋል:: ስለዚህም በተዋሕዶ ሰው ሆነ፣ ሰውም አምላክ ሆነ::

ሰው አምላክ በሆነ ጊዜ «አምላክ ትሆናለህ» ብሎ የተሳለቀ የዲያብሉስ ተንኮል ፈረሰ:: አዳምም ከወጥመዱ አመለጠ:: መዝ. 123÷7:: ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ጠላቶችህን ከእግርህ በታች እስካስገዛልህ ድረስ ሲል «አምላክ ትሆናለህ ብለው የተሳለቁብህ

አጋንንት አምላክ ሆነህ በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ተቀምጠህ በክብር በሰራና በሥልጣን ተገልጠህ እስኪያዩህ ድረስ» በማለት ለሰው የተደረገለትን መጠነ ሥልጣን መናገሩ ነው:: «ወተሰዓለ እም መላእክት፣ መዓርገ መላእክትን እንደ ጫማ ረገጠ::» ብሎ ነበርና ደረሰ÷ ታየ÷ ተገለጠ፣ በዘባነ ኪሩብ ለመገለጥ በቃ ሲል ወነበረ በየማነ አብ፣ በአብ ዕሪና ተቀመጠ አለ::

ቅዱስ ጳውሎስ በልዕልናው በግርማው ቀኝ ታየ ተገለጠ ካለ በኋላም ከመላእክት የሚበልጥ መሆኑን ለማስረዳት አስረጂ ይጠቅስ ጀመር:: «ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ መጠን እንዲሁ ከእነርሱ አብዝቶ ይበልጣል::» ዕብ.1÷4::

ቅዱስ ጳውሎስ እየተናገረ ያለው የጌታችንን ገናናነትና የባሕርይ አምላክነት ነው:: አስቀድሞ ሰው በመሆኑ ዕሩቱ ብእሲ እንዳይመስላቸው ንግግሩ ከነብያትና ከአበው እንደሚበልጥ አስረዳ፣ በሰማያት /በልዕልና/ ተቀምጧል:: በሰማያትም ሲባል ከመላእክት አንዱ ሆኖ አይደለም፣ ከመላእክት ይበልጣል:: ከመላእክት የሚበልጥ ስምንም ወርሷል በማለት ጽፏል::

አንዳንድ ሰዎች «በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል::» /ዳን.12÷1/ የሚለውን በመጥቀስ መልአክ ነው ለማለት ይቃጣቸዋል፣ የሚሉም አይጠፉም:: ቅዱስ ጳውሎስ ግን እያስረገጠ ይጠቅስላቸዋል:: በመላእክት «አንተ ልጄ ነህ÷ እኔ ዛሬ ወለድኩህ» ተብሎ የተነገረለት ማን ነው? ይላል:: ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ጥቅሱ የጌታችንን ከመላእክት መብለጥ ሊያስረዳ የፈለገው በእግዚአብሔር /በምሥጢረ ሥላሴ/ ባለው የአባትነትና የልጅነት ምሥጢር ነው::

1.7. የአባትነትና የልጅነት ምሥጢር

አባትነትና ልጅነትን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት ይልቁንም ቅዱስ

www.zeyeneta.com

ጳውሎስ ከላይ ያስቀመጠበትን ምሥጢር ለመመርመር በሦስት ከፍለን እንመለከተዋለን።

1.7.1. <u>በኖሙራን መካከል</u>፦ እግዚአብሔር ለፈጠረው ፍጥረት አስቀድሞ ሥርዓት ሠርቶለታል። ይኸውም በፍጥረቱ ታውቋል። «ከጠላ ፍጥረት አድርጎ የፈጠረው የለም።» ሲራ.39÷18 እንዲል። ከዚህም ውስጥ የፍጥረታት የመባዣና የመራቢያ መንገድ አንዱ አስረጂ ነው። ከፍጥረታትም መካከል የሰውን፣ የእንስሳትን፣ የአራዊትን ስንመለከት ወሲዱ ይባላል። እኛም በሰው መካከል ያለውን የአባትነትና የልጅነት ምሥጢር እንመለከታለን።

ሀ/ <u>የሥጋ አባት</u>፦ የሥጋ አባትነትና ልጅነት ምሥጢር መገለጫው ሥጋዊ ደማዊ ነው። ልጅ የሚገኘው ከወንድ አብራክ ዘር ተከፍሎ በእናት ማኅፀን ካለ ደም ጋር ተዋሕዶ በሠላሌ ሕፃናት በእግዚ አብሔር መግቦትና መለኮታዊ ጥበቃ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቆይቶ በመወለድ እንደ ሆነ የታወቀ የተረዳ ነው። ስለዚህ አባት የአብራኩን ክፋይ ልጄ ይለዋል፣ ልጁም አባቴ። የሥጋ አባትም ልጁን በሥጋውም በነፍሱም የተቻለውን ያህል እየመገበ፣ እያለበሰ፣ እያስተማረ በነገር ሁሉ ያሳድገዋል።

የሥጋ አባት በሥጋ የልጅነትን ጊዜ አሳልፏል፣ ከመጀመርያው ፍጥረት ከአዳም በቀር። ልጅም እግዚአብሔር ዕድሜ ከሰጠው ወደ አባትነት ያድጋል። ስለዚህ ልጅ ሁልጊዜም ልጅ እንደ ሆነ አይኖርም፣ አባት ብቻም ሆኖ የኖረ አባት /ወንድ/ የለም። ልጅነትም አባትነትም በጊዜና በሁኔታ የሚከሰቱ /የሚገለጡ/ ናቸውና። ስለዚህ አባትነትም ልጅነትም ብቸኛ ገንዘቡ የሆነ ምንም ሰው የለም። ልጆችም የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው። «እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፣ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው።» መዝ.126÷3 እንዲል። የተባረከም አባት እንዲሁ «እነሆ፥ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው እንዲህ ይባረካል፤... የልጆችህንም

ልጆች ታያለህ።» መዝ.27÷1–6 ይላልና።

ለ/ የጡት አባት፦ «የሰው ምጽዋቱ ከእርሱ ጋር እንደ ማኅተም ነው። የሰው ዋጋው እንደ ዓይን ብሌን ትጠበቅለታለች።» /ሲራ. 17÷21–22/ በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ተስፋውን ከእግዚ አብሔር አድርጎ ያልወለደውን ልጅ እንደ ወለደው አድርጎ የሚያሳድግ ሰው የጡት አባት ይባላል። ይኸን አባትነቱን የሚያገኘው ልጁን ካሳደገ ዘንድ ነው። ስለዚህ አባት ልጁን የሚያሳድገው ከጊዜ በኋላ ነውና። ልጅም የጡት ልጅ ይሁን እንጂ የሥጋ አባትም አለውና ልጅነቱ በማደጉ ነው፣ ራሱን ከቻለም በኋላ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ወደ አባትነት ያድጋል እንጂ በዚያው በልጅነት ተወስኖ አይቀርም።

ሐ/ የክርስትና አባት፦ ጌታችን በወንጌል በአንዱ ምግባር ሊሳው እንደማይጠቀም በአሥሩ ደናግል አንጻር አስተምሮናል። ማቴ.25÷1–13። በአንዱ እምነት ግን ሊሳው ይጠቀማል። በጌታው እምነት አገልጋዩ እንደ ተፈወሰ በእናቲቱም እምነት ልጆች እንደ ዳኑ ተጽፏልና። ማቴ.8÷5–13። ስለዚህም «ክርስትና» የክርስቲያኖች ልጆች ወንዶቹ አዳም ከተፈጠረ ወደ ገነት በገባበት በ40 ቀናቸው፣ ሴቶቹ ደግሞ ሔዋን ወደ ገነት በገባችበት በ80 ቀናቸው በጥምቀት ከሥላሴ ለመወለድ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገቡበት ቀን ነው። ኩፋ.4÷9።

የክርስትና አባትም በዚሁ ዕለት ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብቶ እንደ ስምዖን ሕፃኑን የሚታቀፍና /ሉቃ.2÷25–28/ በእርሱ እምነት ለልጁ «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ» /ሐዋ.8÷37/ ያለውን ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ የእምነት መገለጫ መሠረት አድርገው በተለያዩ የሃይማኖት ጉባኤያት ላይ ሊታውጁት ያረቀቁትን «ጸሎተ ሃይማኖት» የሚጸልይ ነው። ሥራውም

www.zeyeneta.com

«የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን?» /ዘፍ.4÷9/ ከሚለው ቃየናዊ እኩይ ምግባር ተለይቶ እግዚአብሔር ለሰው ባዘጋጀው የጥበቃ መንገድ ውስጥ እንደ አቅም መሳተፍ ነው:: ጥበቃ «በጉቼን፣ ጠቦቶቼን፣ ግልገሎቼን ጠብቅ» የተባለ የቅዱስ ጴጥሮስና የካህናት ብቻ አይደለምና::

ስለዚህ የክርስትና አባት የክርስትና ልጁን በጉውንና መጥፎውን፣ ሩቁንና ቅርቡን...እስከሚለይበት ዕድሜው ድረስ በሃይማኖት በምግባር እንዲኖር በክርስትና እንዲያድግ የሚያደርገው ነው:: በእርግጥ የክርስትና አባት ሊያደርገው የሚገባው የሥጋ ወላጆች፣ የነፍስ አባት የሆኑት ካህናትና መምህራን ከሚያደርጉት በተጨማሪ ነው እንጂ የሕፃናት የክርስትና ትምህርት ኃላፊነት በክርስትና አባት ላይ ብቻ የወደቀ አይደለም:: መጽሐፍ ከወላጆቻቸው ተምረው ስለ ተጠቀሙ ይገልጣልና:: «ግብዝነት የሌለበትን እምነትህን አስባለሁ፤ ይህም እምነት ቀድሞ በአያትህ በሉይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበረባቸው፣ በአንተም ደግሞ እንዳለ ተረድቻለሁ::» /2ኛጢሞ.1÷5/ እንዲል የክርስትና አባትነትና ልጅነት ግንኙነት ይህን ይመስላል:: በመሆኑም አባትነትና ልጅነት የተመሠረተው በጊዜና በሁኔታ ነው:: ዛሬ አባት ለሆነው የእርሱም አባት ነበረው:: ልጅም የሆነው ወደ ፊት አባት መሆን ይቻለዋል:: እግዚአብሔር ዕድሜውን እስከ ሰጠው ድረስ በእግዚአብሔር የጥበቃ ሥራ አልሳተፍም አይልምና:: ስለዚህ አባትነቱም ልጅነቱም የራሱ ብቻ የሆነለት ሰው የለም::

መ/ <u>የቀለም አባት</u>:- የቀለም አባት የሚባሉት ደገኛ መምህራን ናቸው:: ጌታችን በወንጌል «አምስት መክሊት የተቀበለው ሌላ አምስት መክሊት፣ ሁለትም የተቀበለው ሌላ ሁለት መክሊት አተረፋበት:: ጌታቸውም አመሰገናቸው ወደ ጌታህ ደስታ ግባም አለው» ተብሎ በምሳሌ የተነገረላቸው መምህራን ወንጌል ሊቃውንተ

ቤተ ክርስቲያን ናቸው:: የቀለም አባት ባለአምስቱ መክሊት አምስት እንዳተረፈው እርሱም ደቀ መዝሙሩን ራሱን አስመስሎ ሊያወጣ ነው:: ይኸውም ጳውሎስ ጢሞቴዎስንና ቲቶን፣ ቅዱስ ጴጥሮስም ቀሌምንጦስን እንዳወጡት ያለ ነው::

ስለዚህ እነዚህ በትምህርት ደቀ መዛሙርትን የሚወልዱ መምህራን አባቶች ሲባሉ ደቀ መዛሙርትም ልጆች ይባላሉ:: «በሃይማኖት ጎብረት እውነተኛ ልጄ ለሚሆን ለቲቶ፡» /ቲቶ.1÷4/ «በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነ ለጢሞቴዎስ...» /1ኛጢሞ.1÷2/ እንዲል:: ቅዱስ ጳውሎስ «አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም ጽናቴንም ስደቴንም፣ መከራዬንም ተከተልህ፤... አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር÷ ከማን እንደተማርኸው ታውቃለህና::» 2ኛጢሞ. 3÷10–15 ያለው ለዚህ ነው::

ስለዚህ የቀለም አባት መምህር ደቀ መዝሙር የነበረበት ጊዜ አለ፤ ደቀ መዝሙርም መምህር አባት ወደ መሆን ያድጋል ራሱንም አስመስሎ ይተካል:: መምህርነት የዘላለም ገንዘቡ የሆነ የለም፤ መምህርነት ገንዘቡ የእግዚአብሔር ናትና:: እናንተ ግን:- መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንድ ስለሆነ» ማቴ.23÷8 እንዲል:: ደቀ መዝሙርም ተግቶ እስከ ተማረ ድረስ መምህር መሆን ይቻለዋል:: «ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል» ሉቃ.6÷40 ተብሏልና::

ሠ/ <u>የሥልጣን አባት /የቆብ አባት/</u>:- የሥልጣን አባት የሚባሉት ጳጳሳት ናቸው:: በዲቁና በቅስና የሚሾሙ እነርሱ ናቸውና:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን በንፍሃተ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሾማቸው ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል:: ዮሐ.20÷22:: ከዚህም በኋላ ቅዱሳን ሐዋርያት እንደየሚገባቸው

www.zeyeneta.com

ዲያቆናትን ቀላውስትን በአንብሮተ እድ ይሾሙ ነበር። ሐዋ.6÷6፣ ሐዋ.13÷1-3። ለዚህ ደግ አገልግሎትም ተመርጠው የሚሾሙ ምግባራቸው ምን መምሰል እንዳለበት ተገልጧል። 1ኛጢሞ. 3÷1-13።

የማይገባው ሰውም እንዳይሾም ቅዱስ ጳውሎስ «በማንም ላይ ፈጥነህ እጆችህን አትጫን፣ በሌሎችም ኃጢአት አትተባበር፣ራስህን በንጽሕና ጠብቅ።» /1ኛጢሞ.5÷22/ ሲል ቅዱስ ጢሞቴዎስን መክሯል። አገልግሎቱም የእግዚአብሔር የሆነውን መንጋ መጠበቅ ነው። ሐዋ.20÷28፣ ዮሐ.21÷15-29። የቆብ አባትም የሚባለው «እኔ መንገድ እውነትና ሕይወት ነኝ» /ዮሐ.14÷6/ ያለውን የጌታ ትምህርት መሠረት አድርገው ወደ ተባሕትዎ የሚመጡ ደናግልን የሚያመነኩስ አባት ካህን ነው።

እነዚህም የአባትነትና የልጅነት ሁነቶች በሁኔታ የሚፈጠሩ በመሆናቸው ለአንድ ሰው በዘመኑ ብቸኛ ገንዘብ ሆነውለት የሚኖሩ አይደሉም። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በየጊዜያቸው ይፈጸማሉ እንጂ።

ረ/ <u>የንስሐ አባት</u>:- የንስሐ አባት ከላይ በሥልጣን እንደተመለከትነው ከደገኞች ሐዋርያት ጀምሮ በአንብሮተ እድ በንፍሐተ መንፈስ ቅዱስ የተሾሙ ካህናት እግዚአብሔር በጌቼን፣ ጠቦቶቼን ግልገሎቼን ጠብቅ ያለውን በግብር የሚፈጽሙ ሰውንም ከታሠረበት የኃጢአት ማሠሪያ የሚያላቅቁና ለመን ግሥተ እግዚአብሔር የሚያዘጋጁ ናቸው። «ኃጢአታቸውን ይቅር ያላች ኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፥ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው።» ዮሐ.20÷23።

«የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፡ በምድር የምታሥረው ሁሉ በሰማያት የታሠረ ይሆናል÷ በምድርም የምት

ፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።» ማቴ.16÷19፣ «እውነት እውነት አላችኋለሁ÷ በምድር የምታሥሩት ሁሉ በሰማያት የታሠረ ይሆናል÷ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።» ማቴ.18÷18 እንዲል። ስለዚህ የንስሐ አባትነትም ለተመረጡ ካህናት የሚሰጥና በጊዜ ከተሾሙ በኋላ የሚያገኙት ገንዘብ በመሆኑ፣ በዚ ያውም ላይ ከእግዚአብሔር የተቀበሉት ሹመት ስለሆነ የራሳቸው ገንዘብ እንዳልሆነ እንረዳለን።

ከላይ ያየናቸው በአባትነትና በልጅነት መካከል የምንረዳው ዓቢይ ቁም ነገር የአባትንም የልጅንም ፍጡርነት ነው። ስለዚህ ሁሉም በየጊዜያቸው ያልፋሉ÷ ከልጅነትም ወደ አባትነት በጊዜና በፈቃደ እግዚአብሔር ያድጋሉ። ስለዚህ አንዱን በመሆን ብቻ የተገኘ በዚ ያውም ጸንቶ የሚኖር ሰው የለም።

1.7.2. <u>በፈጣሪና በፍጡር መካከል</u> :- እግዚአብሔር ፈጣሪነቱ ለሁሉም ነው፣ ያልፈጠረው ፍጥረት የለምና። መግቦቱም ለሁሉ ነው፣ የፈጠረውን ፍጥረት በረድኤት የሚጠብቅም እርሱ ነው። መግቦቱም ግዕዛን ላላቸው ፍጥረታት ወይም ሥጋዊ ደማዊ ለሆኑት ብቻ አይደለም። ለተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ እንጂ «ዘይሠቅዮሙ ለአድባር እምውሃጥያቲሆሙ፣ እምፍሬ ተግባርከ ትፀግብ ምድር። ተራሮችን ውስጥ ውስጣቸውን የሚያጠጣቸው እርሱ ነው፣ ተግባር ከተባለ ደመና ፍሬ ዝናምን አስገኝተህ ምድርን ታረካታለህ።» መዝ.103÷13 እንዲል። «የእርሱ ወደ ሆነው መጣ÷ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን÷ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፣ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።» /ዮሐ.1÷11-13/ ተብሎ እንደ ተጻፈ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን

www.zeyeneta.com

የባሕርይ እምላክነት ለተቀበሉት ታምነውም ለሚጠመቁት ከአብራከ መንፈስ ቅዱስ ከሚገኘ ዮርዳኖስ የሚወለዱበትን ሥልጣን እግዚ አብሔር ሰጠ። «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።» ዮሐ.3÷5 ተብሎ ተጽፏልና።

ስለዚህ በስሙ አምነው የተጠመቁት ብቻ ልጆች ይባላሉ እንጂ ሰው የሆነ ሁሉ አይደለም። «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፣ ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ። ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ። ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ ባሪያ አይደለህም፣ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ» ገላ.4÷4-7 እንዲል። በዚህ የአባትነትና የልጅነት ግንኙነት ላይ አንድ የተለየ ነገር እናስተውላለን። ፈጣሪ በጸጋ መንፈስ ቅዱስ ወልዶናልና የጸጋ አባታችን ሲሆን ፍጡር የሆነ ሰው ደግሞ በጥምቀት ተወልዶ የእግዚአብሔር የጸጋ ልጅ ይሆናል። ስለዚህ የእግዚአብሔር አባትነት አምነው ለተጠመቁት ሁሉና ከላይ በፍጡራን መካከል አባትነት ላላቸው ሁሉ ነው። ልጆችም ወደው ፈቅደው አምነው በተጠመቁ ጊዜ ልጅነትን ያገኛሉ። ስለዚህ የእግዚአብሔርን አባትነት ለማግኘት አምኖ መጠመቅ ስለሚያስፈልግ በሁኔታ የተወሰነ መሆኑን መረዳት ይቻላል።

፲.7.3.<u>አባትነትና ልጅነት በፈጣሪ ዘንድ /በምሥጢረ ሥላሴ/</u>:- ይህ ከላይ በሁለቱም መንገድ ካየናቸው ምሥጢራት በተለየ ሁኔታ ፈጣሪ አባት፣ ፈጣሪም ልጅ ሆኖ የምናይበት መንገድ ነው። ሥላሴ ቢሥልጣን ዕሩያን /ትክክል/ ናቸው፣ ዓለሙን በመፍጠር ዳግመኛም በማዳኑ፣ የፈጠሩትንም በመመገብ፣ በአገዛዝ፣ በመመለክ፣... ይሁን በመሰለው ሁሉ አንድ ናቸው። በስም፣ በአካል፣ በግብር ግን ያለ

መቀላቀል፣ ያለ መጠፋፋት ፍጹም ሦስት ናቸው። የግብር ሦስትነታቸውም አብ ወላዲ አሥራዒ ነው፣ ወልድ ተወላዲ ነው፣ መንፈስ ቅዱስም ሠራዒ ነው።

አብ ይወልዳል ያሠርፃል አንጂ አይወለድም አይሠርጽምም። ወልድም ቢወለድ እንጂ አይወልድም፣ አይሠርጽም፣ አያሠረጽምም። መንፈስ ቅዱስም ቢሠርጽ እንጂ አይወልድም፣ አይወለድም፣ አያሠርጽም። ስለዚህ በግብር ፍጹም ሦስት ናቸው። አብም ወልድን ይወልደዋል ማለት ይፈጥረዋል ማለት አይደለም፣ እኛ የምንፈጥረውን እንደማንወልደው፣ የምንወልደውንም እንደ ማንፈጥረው። አብም አርሱ ልጄ ነው አለ እንጂ ፍጡሬ /ፍጥረቴ/ ነው አላለምና። ስለዚህ የአብ አባትነትና የወልድ ልጅነት ምሥጢር ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ ነው። አብ በአባትነት ብቻ ጸንቶ ይኖራል እንጂ ልጅ የነበረበት ጊዜ አልነበረም፣ ወልድም በልጅነት ጸንቶ ይኖራል እንጂ አባት ወደ መሆን አይለወጥም። መንፈስ ቅዱስም በሕይወትነት ጸንቶ ይኖራል እንጂ አባትም ልጅም ወደ መሆን የሚለወጥ አይደለም።

በአጭር ቃል አብ የወልድ የባሕርይ አባት ነው፣ አባትነትን ከማንም አልተቀበለውም፣ ማንም ከእርሱ ሊወ ስዳት አይችልም። ወልድም የአብ የባሕርይ ልጅ ነው፣ ልጅነትን ከማንም አልተቀበለውም ማንም ማን ከእርሱም ሊነጥቀው ሊወስድበት አይቻለውም። ለአብ ያለ ወልድ የባሕርይ ልጅ የለውም፣ ለወልድም ያለ አብ የባሕርይ አባት የለውም። የወልድ ከአብ መወለድም፣ የፀሐይ ብርሃን ከፀሐይ ከበብ ሳይቀዳደም እንደሚገኝ እንዲሁ የወጣ የተገኘ እንጂ በፍጡር ልማድ አይደለም። ከአብ ሲወለድ እናት አላስፈልገውም። መግለጫ ቋንቋ የሌለኝ ስለሆነ እንጂ የእርሱን መወለድ ልደት የእኛንም ልደት ማለት የሚገባ ሆኖ አይደለም።

www.zeyeneta.com

ለምሳሌ ለሰው በላ፣ ለእሳትም በላ ለእግዚአብሔርም በላ ተብሏል። ዘፍ.18÷1-10። ይሁን እንጅ የሰው አበላል፣ ከእሳት አባላል፣ የእግዚአብሔር አበላል ከእሳትና ከሰው እንዲለይ ሁሉ ልደቱም እንዲሁ ፍጹም ልዩ በአንደበት ከመነገር በጎሊና ከመታሰብ በላይ ነው። የእግዚአብሔር አብ ለወልድ አባትነቱና ለእኛ ያለው አባትነትም ፍጹም ልዩ እንደሆነ ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ ሱስ ከርስቶስ በዕለተ ትንሣኤው ገልጦታል። «እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁም ዐርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው አላት።» ዮሐ.20÷17 ተብሎ ተጽፏልና።

ቅዱስ ጳውሎስም ከመላእክት ይበልጣል ካለ በኋላ ለመብለጡ አስረጅነት የጠቀሰው የቅዱስ ዳዊት ትንቢት ይኸን በምሥጢረ ሥላሴ ዘንድ ያለውን የልጅነት ምሥጢር ከሥጋዌው ጋር በማዋሐድ ነው። ይኸውም፦-

–<u>አንተ ልጄ ነህ</u>– ተናጋሪው አብ ሰሚው ወልድ ሆኖ የተነገረ ነው። አብ ወልድን ቅድመ ዓለም አካል ዘእም አካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የወልድህ ልጄ ነህ አለው። «በመጀመሪያው ቃል ነበረ÷ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ÷ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።» ዮሐ.1÷፣ «አንቺም ቤተ ልሔም ኤፍራታ ሆይ፣ አንቺ በይሁዳ አእላፋት መካከል ትሆኚ ዘንድ ታናሽ ነሽ፣ ከአንቺ ግን አወጣጡ ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ በእሥራኤልም ላይ ገዥ የሚሆን ይወጣልኛል።» /ሚክ.5÷2/ በማለት ጥንት በሌለው ቀዳ ማዊነት /መጀመሪያነት/ እንደ ወለድኩህ ሁሉ እኔ ዛሬ ወለድኩህ ይላል።

ዛሬ የተባለች ድኅረ ዘመን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የተወለደባት ዕለት ናት። ዘመን የማይቆጠርለት መለኮት ዘመን የሚቆጠርለትን የአዳምን ሥጋ ነሥቶ በፍጹም ተዋሕዶ

መወለዱን ሲያጠይቅ ነው። «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ልጁን ላከ።» /ገላ.4÷4/ እንዲል ቀድሞ ከአብ ያለ እናት እንደተወለደ በኋላም ከእመቤታችን ያለ አባት ተወለደ። በዚህም የቀደመ ልደቱ ታወቀ ተረዳ። «ልደት ቀዳ ማዊ ተዐውቀ በደኃራዊ» እንዲል። ስለዚህ እንዲህ ተብሎ አስቀድሞ ትንቢት የተነገረለት ሱባኤ የተቆጠረለት አምላክ ወልደ አምላክ ነው እንጂ ዕሩቅ ብእሲ አይደለምና ከመላእክት ይበልጣል አለ።

ይልቁንም በ2ኛሳሙ.7÷14 ላይ እግዚአብሔር ለዳዊት ስለ ልጁ ስለ ሰሎሞን የተነገረው ፍጻሜው ለጌታችን መሆኑን አስረጂ አድርጉ አትርቦታል። «እግዚአብሔር ለዳዊት በእውነት ማለ አይጸጸትም፣ እንዲህ ብሎ ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀም ጣለሁ።» መዝ.131÷11 ስላለው በልማደ ሰው በሩካቤ በዘር የሚወ ለድና የሥጋ አባት የሚኖረው አይደለም ለማለት «እኔ አባት እሆንዋለሁ፣ እርሱም ልጅ ይሆንልኛል።» 2ኛሳሙ.7÷14 አለው። እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነው በፍጹም ተዋሕዶ ነውና የተጸነሰውም የተወለደውም በግብረ መንፈስ ቅዱስ ለኅሊና በሚረቅ ምሥጢር ነው። ስለዚህ ለቀደመ ልደቱ እናት እንዳላስፈለገው ለኋለኛ ልደቱም አባት አያስፈልገውም።

ይልቁንም ልደቱ የሚደነቅ እንጂ እግዚአብሔር ከገለጠልን አልፈን መናገር እንደማይቻለን ለማስረዳት «ደግሞም በኩርን ወደ ዓለም ሲያገባ፦-የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ለእግዚአብሔር ይስገዱ ይላል።» በማለት ቁጥር ስድስት ላይ ገልጿል። ለመሆኑ በኩር ማለት ምን ማለት ነው? ጌታችንስ ስለ ምን በኩር ተባለ?

1.7.4. <u>በኩር</u>:- በሁለት መንገድ እንመልከተዋለን፣ ምሥጢሩ ግን አንድ ነው። ይኸንንም እንደሚከተለው እናቀርባለን።

1.7.4.1. <u>ቀዳማዊ፣ አልቦ፣ ሥሙር</u> ማለት ነው። ከዚህ የተነሣ

www.zeyeneta.com

በኩር መባል የሚገባው ጌታችን ብቻ ነው። ቀዳሚ የሌለው ቀዳማዊ፣ ማንም ያልሾመው ሊሽረውም የሚቻለው የሌለ ሥልጣኑ የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አለቃ ሹም እርሱ ብቻ ነውና። «ሕፃን ተወልዶልናልና፣ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል። ስሙም ድንቅ መካር÷ ኃያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።» ኢሳ.9÷6 እንዲል።

1.7.4.2. <u>የመጀመሪያ ልጅ ማለት ነው፦</u> የመጀመሪያ ልጅ ማለት የእናቱን ማኅፀን ቀድሞ የፈታ ማለት ነው። ይሁን እንጅ የእናቱን ማኅፀን በመፍታቱ ብቻ የሚገኝ አይደለም። ምክንያቱም ብኩርና ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ጸጋ ነውና። ምሥጢራዊው ትርጉም ግላቅ፣ ከፍ ማድረግ፣ መሾም መሸለም እንደ ማለት ያለ ነው። «እርሱ፦ አባቴ አንተ ነህ÷ አምላኬ የመድኃኒቴም መጠጊያ ይላል። እኔም ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ÷ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል።» መዝ.88÷26–27 እንዲል። በዘፍ.25÷27–34 ላይም ዔሳው ብኩርናውን ለያዕቆብ እንደ ሸጠለት ተጽፏል። ብኩርና የእናትን ማኅፀን መፍታት ብቻ ቢሆን ኖሮ ያዕቆብና ዔሳው ወደ እናታቸው ማኅፀን ተመልሰው ያዕቆብ ቀድሞ ዔሳው ሊከተል አይችልምና ሸጠ ለት ባልተባለ ነበር። ስለዚህ ብኩርና ሹመት ከፍ ማድረግን ማክበርን እንጂ ሥጋዊውን ልማድ ብቻ የሚከተል እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ይስሐቅ ያዕቆብን «...አሕዛብ ይገዙልህ ሕዝብም ይሰገዱልህ፤ ለወንድሞችህ ጌታ ሁን፣ የእናትህም ልጆች ይሰገዱልህ የሚረግምህ እርሱ ርጉም ይሁን፣ የሚባርክህም ቡሩክ ይሁን።» /ዘፍ.27÷29/ ብሎ እንዳከበረው እንዳላቀው በመጻሕፍት ተጽፏልና። ስለዚህ ብኩርና ይህ ሀብትና ሹመት ለተሰጣቸው ሰዎች መጠሪያ ሆኖ እንዳገለገለ መገንዘብ ያስፈልጋል። ጌታ ራሱ የሚቀርበው በሌለ

ብርሃን የሚኖር /1ኛጢሞ.6÷16/፣ እኔ የኅለም ብርሃን ነኝ /ዮሐ.8÷12/፣ የዓለም ብርሃንነት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ እርሱ «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።» /ማቴ.5÷14/ እንዲል ሁሉ ብኩርናን /አለቅነትን፣ ሹመትን፣ ቀዳሚነትን/ ለሰው ሰጠቱን መገንዘብ ይገባል። እግዚአብሔርም በኩር ሁሉ የኔ ነው ማለቱ መምረጡ ማክበሩ መሆኑንን ልብ ማለት ይገባል። ለመሆኑ ጌታችንን ስለ ምን በኩር ተባለ?

ሀ/ <u>የአብ ተቀዳማ ተክታይ የሌለው አንድያ ልጁ ስለሆነ፦</u> አካላዊ ቃል የአብ ተቀዳሚ ተክታይ የሌለው የባሕርይ ልጁ ነው። በመልክ ይመስለዋል በባሕርይም ይተካከለዋልና፣ «እኔን ያየ አብን አየ፣ እኔና አብ አንድ ነን» እንዲል። ዮሐ.10÷30። ቀዳማዊ ልደቱንም በዚህና በዚህ ብሎ መመሰል አይቻልም፣ ሊቃውንትም በምናውቃቸው በፀሐይ፣ በእሳት፣ በባሕር መመሰላቸው ለእኛ ይረዳን ዘንድ ብቻ ነው። ለእርሱ ቀዳማዊ ልደት አብርሃም ከይስሐቅ እንደሚቀድም እንዲልቅም ይስሐቅም ከያዕቆብ እንዲቀድም እንዲልቅ አብ ወልድን የሚቀድመውም የሚልቀውም አይደለም። በዚህ ዓይነትም በልማደ ሰብእ ተወለደ አይባልም። «አወሳጠኩ ከጥንት የሆነ....» ሚክ.5÷2 እንዲል።

ጥንታዊ ቀዳማዊ አለቃ÷ በራሱ ፈቃድ ሁሉ የሚያደርግ ስለሆነ በኩር ይባላል። ቅዱስ ጳውሎስም «በኩርን ወደ ዓለም ሲያስገባ...» ያለው በኩርነቱን ለአብ ሰጥቶ ተናግሯልና የአብ ተቀዳሚ ተክታይ የሌለውን ለማለት ነው።

ለ/ <u>በኩረ ማርያም ስለሆነ፦</u> «የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም።» /ማቴ.1÷25/ እንዲል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእመቤታችን የበኩር ልጅ ነው። በኩረ ማርያም መባሉ ግን ሌሎች ሰዎች ለመላእክቶቹ በኩር ከሚባሉበት ፍጹም

www.zeyeneta.com

የተለየ እንደሆነ መረሳት የለበትም። ሊሎቹ ጽንሰታቸው በዘር በሩካቤ ነው። የሚወልዱትም በተፈትሖ ማኅፀን ነው። እርሱ ግን ያለ ወንድ ዘር፣ ያለ ሩካቤ በማኅረ መንፈስ ቅዱስ ተጸነሰ፣ ያለ ተፈትሖ ማኅፀንም በድንግልና ተወለደ።» «እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ጸንሳ ተገኘች። ማቴ.1÷18። ዳግመኛም «እነሆ ድንግል ትጸንሳለች÷ ወንድ ልጅም ትወልዳለች÷ ስሙንም /አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» ኢሳ.7÷14 ተብሏልና። እንበለ ዘር የተወለደም የሰውን ዘር በመናቅ በማቅለል አይደለም። ይልቁንም ስለ ሦስት ነገር ነው።

በጥንተ ተፈጥሮ ሔዋንን እግዚአብሔር ከአዳም የግራ ጎን አጥንት አስገኝቷት ነበርና ወንዶች ያለ ሴት እናንተ ሴቶችን አስገኝተናል፣ እናንተ ግን ወንዶችን፡- እኛ ወንዶች እንኳን መውለድ ቢቻላችሁም ያለ ወንድ መውለድ አይቻላችሁም እያሉ ይመኩ ነበርና ይኸንን ትምክህት ለማፍረቅ፣ እመቤታችን ያለ ወንድ ዘርዕ እርሱን አስገኝታ አስተካክላናለችና።

«እኔ አባት አሆነዋለሁ÷ እርሱም ልጅ ይሆንልኛል» /2ኛሳሙ.7÷14/ ተብሎ እንደ ተጻፈ ለጌታችን ከአብ በቀር አባት የሚያስፈልገው አይደለምና÷ አብም ያለ ወልድ ሌላ ልጅ አያስፈልገውም።

–ቀድሞ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ያለ እናት መወለዱን አሁን ደግሞ ከእመቤታችን ያለ አባት በመወለድ እንዲገልጥልን ስለ ወደደ ነው /ልደት ተዳግሞ ተወውቀ በደኃራዊ እንዲል/።

ስለዚህ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርቶስ የተወለደውን ልደት ብንም በምን የሚመስለውና የሚተካከለው የለም። ከእርሱ ልደት በፊትም በዚያም ጊዜ ከዚያም በኋላ እንበለ ዘርዕ ተጸንሶ የተወለደ ሊወለድም የሚቻለው የለምና። ልደቱን በምትመስል

ልደት የተደረሰም የሚከተልም የለምና በኩር ይባል ዘንድ ተገባው። እንዲህ የተደረገላት፣ እንበለ ዘርዕ፣ እንበለ ሩካቤ፣ እንበለ ሰስሎተ ድንግልና የጸነሰች፣ ያለ ተፈትሖ ማኅፀን፣ ያለ ምጥ፣ ያለ ርስሐት፣ በፍጹም ድንግልናም የወለደች በዚያውም ላይ አምላክን በመውለድ የከበረችና ወላዲተ አምላክ ለመባል ክፍጥረት ወገን ሁሉ የከበረች እንድትሆን ያደረገበት ልደቱ ፍጹም ልዩ ነው፣ በእንደበት ከመነገር በኅሊናም ከመታሰብ በላይ ነውና። እንኳን ከድንግል የተወለደበት ምሥጢር በዝማ ቤት የአገባቡም ምሥጢር ለሐዋርያት አልተገለጠም፣ እንዲያው ገብቶ ተመለከቱት እንጂ። ዮሐ.20÷26።

<u>ሐ/ በኩረ መኑታን ስለሆነ፡-</u> ሰው ሁሉ ይሞታል፣ ለሞትም ያልተገዛ፣ የማይገዛም ሰው የለም፣ «የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፣ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና። ነገር ግን ሁሉ ተገዝቷል ሲል፣ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው።» ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።» /1ኛቆሮ.15÷22–28/ በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ሁሉ ጌታችንም እንደ ሞተ አስረድቷል። ነገር ግን የእኛ ሞትና የጌታችን ሞት ልዩ እንደሆነ በዚሁ ጥቅስ ላይ ተብራርቷል።

1ኛ. ለሞት ሁሉን ያስገዛለት እግዚአብሔር እንደሆነ፣

2ኛ. ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ ራሱ እግዚአብሔር በወደደ ጊዜ በፈቃዱ እንደ ሞተ ገልጿል። ምክንያቱም የእኛ ሞት በፈቃዳችን በዕቅዳችን አይደለም፣ የእርሱ ግን በፈቃዱና በአሰባት ጊዜ የተፈጸመች ናትና፣ ይኸውም «ጊዜዬ ገና አልደረሰም» ዮሐ.2÷2 በማለቱ ታውቋል። ይልቁንም አስቀድሞ በነቢዩ በዳዊት «አንሰ ሰከብኩ ወኖምኩ፣ እኁ ተኛሁ አንቀላፋሁም» /መዝ.3÷5/ ብሎ በፈቃዱ መሞቱን ቀደም ብሎ አንዳናገረ ተጽፏል። በኋላም ቅድስት ነፍሱን

www.zeyeneta.com

ከቅድስት ሥጋው ራሱ እንደለያት «አባት ሆይ÷ ነፍሴን በእጅህ አደራ አሰጣለሁ አለ።» ሉቃ.23÷46 በማለት ገልጠልናል።

እኛ ግን መሞቻችንንም አናውቀውም «ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።» ማቴ.25÷12 እንደተባለው ነፍሳችንንም ከሥጋችን የመለየት ሥልጣን የለንም። «...እግዚአ ብሔር ግን÷ አንተ ሰነፍ÷ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዷት ይፈልጓታል፣ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው።» ሉቃ 12÷20 ተብሏል። ጌታችን ግን በሥልጣኑ እንደሚለያትም «ነፍሴን ላኖራትም ላነሣትም ሥልጣን አለኝ» ዮሐ.10÷18 ሲል አስቀድሞ አስተምሯል። ጌታችን ሞተ ሲባልም ነፍሱ ከሥጋው ተለየች ማለት እንጂ እንደ እኛ በድን ሆነ ማለት አይደለም፣ ምክንያቱም መለኮቱ ያልተለየው ሕያው ነውና። «እነ ንውም ወልብየ ንቅሕት፣ እኔ ተኝ ቻለሁ ልቤ ግን ነቅቷል» /መኃ.5÷2/ እንዲል ምውት በሰውነቱ ሕያው በመለኮቱ ነውና። «ቅዱስ ጴጥሮስም በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ።» 1ኛጴጥ.3÷19 ብሏልና።

ስለዚህ የጌታችንን ሞት የሚመስላት የሚተካከላትም የለም። በሥልጣኑ ሞቷልና ሥጋውም ከመለኮቱ ሕያው ነውና። ነፍሱንም ከሥጋው የለየ ራሱ በሥልጣኑ ነውና፣ ለሞቱ ተቀዳሚም ተከታይም የለውምና በኩረ ሙታን ይባላል። ይልቁንም ሞቱ በሞት ላይ ሠልጥና ዲያብሎስን አሸንፋለችና በማንና በሃ'ን እንመስላታለን፣ ከምንስ ጋር እናተካክላታለን። ዕብ.2÷14። «እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ÷ መጀመሪያ ከሙታንም በኩር ነው።» ቆላ.1÷19።

ሠ/ <u>በኩረ ትንሣኤ ስለሆነ</u>÷- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኩረ ሙታን እንደሆነ ሁሉ በኩረ ትንሣኤም ነው። ስለ ትንሣኤውም አስቀድሞ ነብያትን አናግሯል። «ሠዋትንሣእኩ እስመ እግዚአብሔር አንሥአኒ፣ ኢይፈርህ እምአዕላፈ አሕዛብ» ተነግሩ÷

እግዚአብሔር አንሥቶኛልና። የጠላቶቻችን /የአጥብቶ መቃብሮን/ ብዛት አልፈራም። መዝ.3÷5። «ይእዜ እትነሣእ ይቤ እግዚአብሔር÷ እሬሲ መድኃኒተ ወአግሀድ ዬቱ÷ ሦስት መነልት ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድራ እነሣለሁ ትንሣኤዬን አደርጋለሁ÷ ኃያሊንም በትንሣኤዬ እገልጣለሁ።» መዝ.11÷5፣ «እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶ ቹም ይበተኑ» መዝ.67÷1፣ «እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ።» /መዝ.77÷65/ ሲል አናግሯል። ራሱም በወንጌል «ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀን እሠራዋለሁ።» ዮሐ.2÷19፣ «ነፍሴን ላኖራትም ላነሣትም ሥልጣን አለኝ።» ዮሐ.10÷18።

ከላይ የቅዱሳት መጻሕፍትን አስረጂነት እንደተመለከትነው የጌታችን ትንሣኤ ልዩ ነው። ምክንያቱም የሌሎቹ ትንሣኤ አሥነሺ አስፈልጓቸዋል። የሰራንታዋን መበለት ልጅ ነቢዩ ኤልያስ /1ኛነገ.17÷12-24/፣ የሱናማዊቷን ልጅ ነቢዩ ኤልሳዕ /2ኛነገ.4÷32-37/፣ አልዓዛርን /ዮሐ.11÷43/፣ የመኩንኑን ልጅ / ማቴ.9÷18/፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ጣቢታን ቅዱስ ጴጥሮስ፣ አውጣኪስንም ቅዱስ ጳውሎስ /ሐዋ.9÷39፣ ሐዋ 20÷10/ እንዳሥነሷቸው ተጽፏልና። እነዚህ ሰዎች ሁለተኛ ሞት አለባቸው፣ እርሱ ግን የለበትም። በኋላም በትንሣኤ ዘጉባኤ ሁላችንም አሥነሺ ያስፈልገናል፣ «ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፣ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ።» 1ኛተሰ.4÷16፣ «እነሆ÷ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ ሁላችን አናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበተ ዓይን እንለወጣለን፣ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሁነው ይነሣሉ፣ እኛም እንለወጣለን።» 1ኛቆሮ.15÷52 እንዲል።

ስለዚህ የጌታችንን ትንሣኤ የሚመስል ትንሣኤ የሚነሣ፣ የተነ

www.zeyeneta.com

ሣም የለም። ምክንያቱም በሥልጣኑ እንደ ሞተ በሥልጣኑ መነሣቱ ዋናው ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢሆንም ሌሎች ተጨማሪ ከስተቶችም ነበሩ። በመጀመሪያ በመቃብር ውስጥ ቢያድርም በመለኮቱ ሕያው ስለሆነ። እንደ ሌሎቹ እርሱ መለወጥ /መበስበስ/ የለበትም፤ በሌላ በኩል በፍጹም ድንግልና ተጸንሶ በፍጹም ድንግልና እንደ ተወለደ የተነሣውም በገነባ መቃብር «መቃብር ከፈቱልኝ መግነዝ ፍቱልኝ» ሳይል ነው። በኋላም በተዘጋ ቤት ውስጥ ገብቷል። ዮሐ.20÷26።

ከመቃብሩ ላይ የተቀመጠውን ድንጋይ ከትንሣኤ በኋላ መልአኩ አንከባልሎታል። ይኸውም የጌታን በመቃብር አለመኖር አይተው ትንሣኤውን ያለ ጥርጣሬ እንዲቀበሉት ነው። ማር.16÷1–8 ፣ ማቴ.28÷1–3። በመሆኑም ከእርሱም በፊት ይሁን በዚያች የእርሱ የትንሣኤ ዕለት ከዚያም በኋላ የእርሱን ትንሣኤ በሚመስል የተነሣ የሚነሣም የለም፤ ለትንሣኤውም ከዚያ በፊት ቀዳሚ ከዚያም በኋላ ተከታይ የለውምና ጌታችን በኩረ ትንሣኤያችን ይባላል።

ሠ/ <u>በኩረ ምእመናን ስለሆነ ነው</u>፦- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ እንደሆነ ሁሉ ፍጹም ሰውም ነው። «ዳዕሙ ምኩር በኩሉ አምላኪነ ዘእንበለ ኃጢአት ባሕቲታ፣ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው።» ዕብ.4÷15 እንዲል። ይሁን እንጂ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር ያደረገው ሁሉ በሥልጣኑ ነው። ወንጌልም የምትሰጠው ምስክርነት ይህንኑ ብቻ ነው። አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ጌታችንን ቃል ከአብ ተቀብሎ አዳም ያስወሰዳቸውን ሰባት ሀብታት ገንዘብ አድርጓል፡ ስለዚህም ካህን፣ ንጉሥ፣ ሐዋርያ በኩረ ምእመናን መባል ተገባው ይላሉ። ኪ.ወ.ክ. መዝገበ ቃላት ገጽ 780 ተመልከት።

ይህ ግን ጌታችን የሚያስተምርበትንና ተአምራት ያደረገበትን ሥልጣን ያላወቁ አይሁድን ያስመስላቸዋል ማቴ.21÷23፡ «ሀብታም

ሲሆን እናንተ በእርሱ ድህነት ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።» /2ኛቆሮ.8÷9/ ተብሎ እንደተጻፈ ባዕለጸጋነቱም በእምላክነት ባሕርይ ጸንቶ ይኖር እንደ ነበር «እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም። ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ። በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ÷ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።» ፊል.2÷6–8 ሲል መዋረዱን /ትኅትናውን/ ጨምሮ ገልጧል።

ሰው በመሆኑም እንደ ደኸየ ሁሉንም ነገር እንደ ተወ «ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሣፈሪያ አላቸው ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም።» በማለት ስለ ራሱ ገልጦልናል። ማቴ.8÷20። ስለዚህ ጌታችን ከልዕልና ወደ ትኅትና ከባለጠግነት ወደ ድህነት የመጣ እንጂ ከትኅትና ወደ ልዕልና ከድህነትም ወደ ባለጠግነትም ሄደ ለማለት እንደማይቻል መገንዘብ ያስፈልጋል። በሰባቱ ሀብታት ማኅደርነት ወደ አምላክነት መሸጋገር የሚቻል ከሆነ ከእርሱ በፊት ዳዊት በንጉሥነት ተቀብቶ ሰባቱን ሀብታት ገንዘብ አድርጉ ነበር። ስለዚህ እርሱ ስለ ምን ወደ ቀደመ ክብራችን አልመለሰንም?

ሰባቱ ሀብታት የሚባሉት ይልቁንም ለዳዊት እንደተሰጡትና እንደፈጸማቸው እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን።

1. ሀብተ ክህነት፦- በሦያ አራቱ ጊዜያት አሥራ ሁለት አሥራ ሁለት ሆነው ተካፍለው እግዚአብሔርን ያገለግሉ ነበር። ከእነዚህም ኣዊን ገብቶ ስለ ተቆጠረ ሀብቱ አለው። 1ኛዜና.15÷1–37።
2. ሀብተ ኃይል፦- እንበላን ዘጡጫ ነፊርን በርግጫ መግደል

www.zeyeneta.com

ነው:: 1ኛሳሙ.17÷34::

3. ሀብተ መዊዕ:- በገናው ሳይቀር መርታት፣ ዜና ነገሩን ሲሰ ሙት መረበሽን ያመለክታል፣ የዳዊትም ዝናው ሲሰማ በዚህ በኩል መጣ ሲባል ጦሩ ሁሉ ይናድ ነበር:: 1ኛሳሙ.18÷30::
4. ሀብተ በገና:- በገና አዘጋጅቶ መደርደር÷ እግዚአብሔርን ማመስገን /1ኛሳሙ.18÷10/::
5. ሀብተ ፈውስ:- በሽተኛ የመፈወስ ሀብት ነው:: ቅዱስ ዳዊት በገና እየደረደረ ሳአልን ከሚያሰቃየው ርኩስ መንፈስ ያሳርፈው ነበር:: /1ኛሳሙ.16÷23/
6. ሀብተ ትንቢት:- ትንቢት የመናገር ሀብት ነው:: ቅዱስ ዳዊት 150ውን ዳዊት በአሥር አርዕስት አድርጉ ትንቢት ተናግሯል::
7. ሀብተ መንግሥት:- የገዥነት ሀብት ነው:: ይኸውም የገደለውን ማስገደል፣ የቀማውን ወንበዴ ማስመለስና መቅጣት የመሰለ ነው:: ዳዊትም ንጉሠ እስራኤል ነበር::

ታዲያ በሰባት ሀብታት አንድ ሰው በኩረ ምእመናን ከሆነ ዳዊት ለምን አልሆነም:: ጌታችን ሃብታትን የሚቀበል ሳይሆን የሚሰጥ ነው:: እንኳን ሀብታትን ዘላለማዊ ሕይወትን የሚሰጥ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በሥልጣን ዕኩይ ነው::

«አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው÷ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል::» ዮሐ.5÷21 እንዲል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ግን በኩረ ምእመናን ያሰኘው ይህ አይደለም:: እርሱ ከህሉቱ የባሕርይው ነው ከማንም አልተቀበለውም:: ከእርሱ ሥጋዌ በፊት፣ በእርሱ የሥጋዌ ዘመን፣ ከእርሱም በኋላ ራሱን ካህን፣ ራሱን መሥዋዕት፣ ራሱን መሥዋዕት ተቀባይ አድርጉ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር

ያስታረቀ ሊያስታርቅም የሚችል ሌላ ካህን የለንም:: ለዘላለም ካህን ነህ የተባለው ከህሉቱ የባሕርይው ስለሆነ ነው:: መዝ.109÷4፣ ዕብ. 9÷12፣ ሮሜ.5÷10፣ 2ኛቆሮ.5÷19::

የእርሱ መለኮታዊ ደም ከመፍሰሱ በፊትም ማንም ሰው ራሱን ከአዳም በደል /ከውርስ ኃጢአት/ ነጻ ማውጣት አልተቻለውም:: «ሁሉ ተሳስተዋል÷ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል::» /ሮሜ.3÷12/፣ «ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፣ በኃጢአትም ሞት፣ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ::» ሮሜ.5÷12 ተብሎ እንደ ተጻፈ:: ጌታችንም ይህን ኃጢአት አስወገደ:: «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወድ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው::» 1ኛጢሞ.1÷15::

ስለዚህ ጌታችን በፈቃዱ ሰው ሆነ:: የዲያብሎስንም ሥራ አፈረሰ:: 1ኛዮሐ.3÷8:: ልጆች ተብለን የምንጠራበትን ሥልጣንና ፍቅር ሰጠን:: ዮሐ.1÷12፣ 1ኛዮሐ.3÷1:: ለምእመናንንም የምግባር አብነት ለመሆን ጸሞ ሦስቱ አርእስተ ኃጣውእን ድል ነሣ:: ማቴ.4÷1–11:: እግር እስከ ማጠብም ራሱን ዝቅ አደረገ:: ዮሐ.13÷13::...ይህንና የመሰሏቸውን ሁሉ በማድረግ እንድንከተለው ጠራን:: ዮሐ.14÷6:: ቅዱስ ጳውሎስም እርሱን መምሰሉን ተረጐመው:: 1ኛቆሮ.11÷1:: እኒህን ሁሉ ግን በሥልጣኑ የሚያደርግ ከእርሱ በቀር ሌላ ባለመኖሩ በኩረ ምእመናን ተባለ::

1.8. ዐበይት ዘይት ቀባህ:-

በእንተዝ ቀብዐከ እግዚአብሔር አምላክከ
ቅብዐ ትፍሥሕት እምእለ ከማከ

ስለዚህም እግዚአብሔር አምላክነትህ ቅባህ

www.zeyeneta.com

የደስታ ቅባትም ከአንተ ዘንድ ነው። መዝ.44÷7።

1.8.1. <u>የጸጌችና የቅብዐቶች ታሪክ</u>፦ በኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚታወቀው እስከ አፄ ሱስንዮስ ድረስ ያለው የካቶሊኮች እንቅስቃሴ ከመውጣትና ከመግባት ያልበለጠ ነበር። በአፄ ሱስንዮስ ዘመን ግን በንጉሡ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነትን አግኝተው አዋጅ አሳውጀው የኢትዮጵያን ሃይማኖት ካቶሊክ ለማድረግ ተንቀሳቀሱ። እነ ጴጥሮስ ፓኤዝ በግእዝ እስከ መስበክ ደረሱ፣ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትና ምእመናንንም እንደ በግ በመታረድ፥ ሰማዕትነትም ተቀበሉ።

አፄ ሱስንዮስን ፈቅሰፍት እግዚአብሔር በደዌ በመታቸው ጊዜ ፈውስን ይሰጣቸው ዘንድ ወደ ገዳማቱ መባና መልእክተኛ ላኩ። በገዳማውያኑም ጸሎት እግዚአብሔር ገጸ ምሕረቱን አዞረ ላቸው። ንጉሡም አዋጁን በአዋጅ አሽረው የተዋሕዶ ሃይማኖት ብሔራዊት እንደሆነች እንድትጸና ልጃቸውም አቤቶ ፋሲል አፄ ተብሎ እንደነገሠ አሳወጁ። የሕዝቡን መጉዳት አይተዋልና ካቶሊኮች ቀርበው እንዲከራከሩና ለረታውም ሃይማኖቱ እንዲጸናለት አዘዙ። ክርክሩም በጎንደር ከተማ ሲደረግ የተዋሕዶ አፈ ጉባኤ ሆነው የቀረቡት አጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ሲሆኑ የካቶሊኮች ደግሞ አልፎንሱ ሜንዴዝ ነበረ። በክርክሩም ተዋሕዶዎች ረትተው ካቶሊኮች ከሀገር እንዲወጡ ታዘዙ።

በዚህ ጊዜ ነበር አልፎንሱ ሜንዴዝ ኤዎስጣቴዎስ ዘሳንኪ ጊዮርጊስ /ጎጃም/ እና ቁርንጭ መናፍቅ ተነስ ሃይማኖትን /ዘሸዋ/ ወስዶ በወደብ አካባቢ ታምሜያለሁ በማለት ለኤውስጣቴዎስ ቅብዐትን ለተክለ ሃይማኖት ጸጋን አስተምሯቸዋል። ይህንን በማድረጉም «በኢትዮጵያ ሁለት እሾህ ተክየባታለሁ» እንዳለ ይነገርለታል። እንደ አልፎንሱ ሜንዴዝ ንግርትም ሁለቱ እሾኾች እስካሁን ሕዝቡን ሲያቆስሉ የአንድነት ስሜትን ሲቀንሱ ለዘመናት ኖረዋል።

1.8.2. <u>የጸጌች እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሲመዘን</u>፦ ጸጋ ማለት ሀብት፣ መልካም ስጦታ፣ ዕድል ፈንታ፣ ትምህርት፣ ሥርየት፣ ይቅርታ፣ ብዕል፣ ክብር፣ሕዋስ፣ ሞገስ፣ የቸርነት ሥራ፣ ፈለዋጋ የሚሰጥና የሚደረግ፣ ማለት ነው። ኪ.ወ.ክ. ገጽ 743። የጸጋ እምነት ተከታዮች ሦስት ልደትን እንደሚያምኑ ይናገራሉ። ይኸ ንንም ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት፣ በማኅፀን መንፈስ ቅዱስን ተቀብቶ የጸጋ ልደት፣ በኋላም ከእመቤታችን በሥጋ የተወለደውን መወለድ በመዘርዘር ነው። ታድያ እግዚአብሔር ሰው የሆነው እንደዚህ ነውን ? ፈጽሞ። በቀላሉ ለመረዳት ይቻለን ዘንድ በመጠኑ ከምሥጢረ ሥላሴ እንመለከታለን።

ቅድስት ሥላሴ በክብር ዕሩያን ናቸውና አይበላለጡም፣ አብ ከወልድ ከመንፈስ ቅዱስ፣ ወልድም ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ፣ መንፈስ ቅዱስም ከአብ ከወልድ አይበልጥም አያንስምም። በአካላት ደግሞ ፍጹማን ናቸው። ይኸም ማለት ለአብ ፍጹም አካል፣ ለወልድም ፍጹም አካል፣ ለመንፈስ ቅዱስም ፍጹም አካል አላቸው። በከዊነ ህልውና ከመገናዘብ በቀር አካላት ያለመቀላቀል፣ ያለመጠፋፋት፣ በፍጹም ሦስትነት ጸንተው ይኖራሉ። በከዊነ ህልውና ግን በአብ ወልድም መንፈስ ቅዱስም ህልዋን ናቸው፣ በወልድም አብ መንፈስ ቅዱስ ህልዋን ናቸው፣ በመንፈስ ቅዱስም አብም ወልድም ህልዋን ናቸው።

በመሆኑም በአብ ልብነት ያስባሉ፣ በወልድ ቃልነት ይናገራሉ፣ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ሕያዋን ሆነው ይኖራሉ። «እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፣ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፣ ባይሆንስ ስለ ራሱ ስለ ሥራው እመኑኝ።» ዮሐ.14÷8–11። «እውነት

www.zeyeneta.com

እውነት እልሃለሁ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን ምስክራችንንም አትተቡለትም።» ዮሐ.3÷11 እንዲል።

ጸጉ ግን በእናቱ ማኅፀን እያለ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶ በጸጋ አምላክነትን አገኘ ይላሉ። ይህ ግን ፍጹም ስሕተት ነው። እንደ እነርሱ አባባል አብን ቀባዒ፣ ወልድን ተቀባዒ፣ መንፈስ ቅዱስን ቅብዕ አድርገው አብ ወልድን በመንፈስ ቅዱስ ቀብቶ እንዳከበረው ይናገራሉ። ይህ ግን አይሆንም፣ ምክንያቱም፦

1/ አብ ቀቢ ወልድ ደግሞ ተቀቢ ከሆኑ ጌታችንም የጸጋ አምላክ ነውና አብና ወልድ በሥልጣን እኩል /ፅፉያን/ ናቸው አያሰኝም። ቅዱሳት መጻሕፍት ደግሞ ወልድ በምንም በምን ከአብ እንደማያንስ ያስረዳሉ። «የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው።» ዮሐ.17÷10፣ «እኔና አብ አንድ ነን።» ዮሐ.10÷30 እንዲል። ይልቁንም ደግሞ «መጀመርያ ቃል ነበረ÷ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ÷ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።» ይላልና ራሱ ወልድ እግዚአብሔር ከሆነ እንዴት አብ ወልድን ሊያከብረው ይችላል? ከእግዚአብሔርነትስ በላይ ምን አምላክነት አለና እርሱ ይከብር ዘንድ ሻ? በጸጋስ አምላክ ከሆነ በአምላክነቱ ጸንቶ መኖር ይቻለዋልን? ጸጋ እንዲሰጥ ይሻላልና። በዚያውስ ላይ አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩ መመለስ ይቻለዋልን? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መስጠት አይቻልም።

2/መንፈስ ቅዱስ ትብ በመሆን ወልድን ተቀባው ካልን ምሥጢረ ሥላሴ ላይ የምናምነው የሦስት አካላት ትምህርት ይፈርስብናል። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ወልድን ተቀላትሏል÷ የራሱንም አካል አጥቷል ያሰኝብናል። መንፈስ ቅዱስ ቅብዕ ሆኖ ወልድን በማኅፀን እንዳልተቀባና በራሱ አካል ጸንቶ የሚኖር መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ጌታችን በ30 ዘመኑ በተጠመቀ

ጊዜ በርግብ አምሳል ተገልጦለታል። ዮሐ.1÷32 ፣ ማቴ.3÷16። ራሱ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት አስተምሯል። «ኃጢአትና ስድብ ሁሉ ለሰዎች ይሠረ ይላቸዋል፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሠረይለትም።» ማቴ.12÷31 በማለት ግልጥ አካላዊ ስለሆነ ነው። አካል የሌለው ዝርው ቢሆንማ ሥራ የሚሠራም፣ የሚሰደብም፣ ስለስድቡም ፍርድ ሊያመጣ የሚቻለው ባልሆነ ነበርና።

ይልቁንም «አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፣ እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።» /ዮሐ.14÷26/ በማለት አካላዊነቱን አስረግጧል። ስለዚህ ጌታችን በጸጋ /በሦስት ልደት/ ሰው የሆነ አይደለም። በጸጋ አምላክ ሰው ለድን አይችልምና። ለምሳሌ በጸጋ ሙሴም አምላክ ነበረ። ዘጸ.7÷1። ሌሎችም አምላክነት በጸጋ እንደተሰጣቸው መጻሕፍት ይናገራሉ። መዝ.81÷1።

1.8.3. <u>የቅብዐቶች አምነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ሲመዘን</u>፦ ቅብዐቶችም እንደ ጸጉ በማኅፀን ተቀብቶ ከብሯል በማለት የሚናገሩት ሦስት ልደታትን እናምናለን ሲሉ ነው። ከጸጉ ጋር ያላቸው ልዩነት ቅብዐቶች «ተቀብቶ የባሕርይ አምላክ ሆነ» ሲሉ ጸጉ ግን «ተቀብቶ የጸጋ ልጅ ሆነ» በማሊታቸው ነው። ቅብዐቶች «በማኅፀን ግርያም ተቀብቶ ከብረ÷ የባሕርይ አምላክ ሆነ» ይበሉ እንጂ በተለያዩ ዘመናት የሚነሡ መምህሮቻቸው የሚናገሩት ግን ይለያያል። ስለዚህ በየራሳቸው አመለካከት በሰድስት ከፍለን እንመለከተዋለን።

ሀ/ የመጀመሪያዎቹ /በእነ አፄ ፋሲል የነበሩት የእነዘኢየሱስ ትምህርት/፦

የእነዘህን ሰዎች አስተሳሰብ እንደሚከተለው እናቀርባለን።

www.zeyeneta.com

«ቃል በተዋሕዶ ዜገ /ተገዥ ሆነ/፣ ከሥጋ ሲዋሐድ የባሕርይ ክብሩን አጣ ለቀቀ፣ በተቀባ ጊዜ ግን ወደ ጥንተ ክብሩ ተመልሶ በሰውነቱም በአምላክነቱም በቅባት የባሕርይ ልጅ ሆነ» ይላሉ። ይኸም ማለት ሚጠትንና ውላጤን በአንድነት የሚያይ ነው። ምክንያቱም ቃል መጀመሪያ ገዥ ነበረ÷ ሲዋሐድ ተገዥ ሆነ ሲቀባ ተመልሶ ገዥ ሆነ የሚሉት ሚጠት ይባላል። ሥጋ ግን ቀድሞም ተገዥ ነበርና በቅብዐት ገዥ ሆነ ማለታቸው ውላጤ /መለወጥ/ ይባላል።

ይኽ ትምህርት ግን ፍጹም ስሕተት ነው። ምክንያቱም ቃል ሥጋን ሲዋሐድ የሥጋ ባሕርይ አሽንፎት ተገዥ ሆነ ካልን መጀመርያውንም የሚሣነው አለ ያሰኛልና አምላክ ነው ማለት አይቻልም። እግዚአብሔርም ከገዥነት ወደ ተገዥነት እንደገና ወደ ገዥነት የሚለዋወጥ አምላክ አይደለም። «እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» ሚል.3÷6 እንዲል። ዳግመኛም «ኢየሱስ ክርስቶስ ትላንትና ዛሬ እስከ ዘላለሙ ሕያው ነው» ይላል። ዕብ.13÷8 «ትላንት» ያለው ቀድሞ በቃልነት የነበረውን÷ «ዛሬ» ያለው ደግሞ ሥጋዊውን /በግነፀነ ማርያም ሰው መሆኑን/ «እስከ ዘላለምም» ያለው ከሥጋዊ በኋላ ያለውን ነው። በእነዚህ ሦስት ጊዜያትም እርሱ የሚለዋወጥ አይደለም። «ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ÷ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ÷ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ።» መዝ.101÷26 እንዲል።

ይልቁንም ደግሞ ቃል በተዋሕዶ ጊዜ ለሥጋ ተገዣ ማለታቸው ሥጋን ገዥ ከቃልም የሚበልጥ አምላክ ያደረጉት ያስመስላቸዋል። ይህ ግን አይደለም ቃል እግዚአብሔር ነውና። ዮሐ.1÷1። ያለ እግዚ አብሔርም አምላክ የለምና። «እቤቱ÷ በአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ ማን ነው?» ዘጸ.15÷11 እንዲል። እግዚአብሔር ፈጣሪ /ዘፍ.1÷1-31/ ሰውም ፍጡር ነውና /ዘፍ.2÷7/ ሥጋ ገዥ ቃልም

ተገዥ ሊሆኑ አይቻላቸውም። በዚያውም ላይ ከላይ በጸጉች እንደተመለከትነው ልብ ወልድን በመንፈስ ቅዱስ የሚያከብረው አይደለም።

ለ/ በአፄ ዮሐንስ አንደኛ የተነሡ

የእነ አካለ ክርስቶስ ትምህርት፦

እነዚህ ከመጀመሪያዎቹ የሚነቅፉት አላቸው። ይኸውም ቃል ሥጋን ሲዋሐድ ዜገ /ተገዥ ሆነ/ የሚለውን ከነቀፉ በኋላ መጽሐፍ «እስመ ተዋሕዶ አእተታ ለምንታዌ» የሚለውን ጠቅሰው በተዋሕዶ ሁለትነት ጠፍቶ አንድነት ቢገኝም ሥጋን ያከበረው የለም፣ የአምላክነት ክብርም አላገኘምና አብ መንፈስ ቅዱስን ቅብዐት አድርጎ ቃል የተዋሐደውን ሥጋ ቀብቶ አከበረለት። ሥጋም በተቀባ ጊዜ ክብር ተላለፈለት፣ተፈጥሮ ተገብሮ ጠፋለትና በቅባት የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ ሆነ ይላሉ። ይኸም ማለት መቀባትን ለሥጋ ብቻ ሰጥቶ ሥጋ ከበረ ማለት ነው። ይኸም ፍጹም ስሕተት ነው። ይህንንም በሦስት ፈርጅ ብንመለከተው የበለጠ ግልጽ ሊሆንልን ይችላል።

1/የፍጡር ሥጋ ተለውጠ አምላክ መሆን አይቻለውም። የፍጡር ሥጋ ተለውጠ በቅብዐት አምላክ ቢሆን ኑሮ ቀድሞ የተቀቡት እነ ዳዊት እነ ሰሎሞን አምላክ በሆኑ ነበር። ጥንቱን አባታችን አዳምንና ሔዋንን የሞት ሞት ያስቀጣቸው ፍጹም ጸብ ከሰ ማያውያን ጋርም ያጣላቸው «ፍጡር ወደ ፈጣሪነት ሊለወጥ ይችላል» ብለው ማመናቸው ነበር። ፍጡር ተለውጠ ፈጣሪ መሆን እንደማይቻለው ቢያምኑ ኑሮ እፀ በለስን አይበሉም ነበርና። ስለዚህ ይሄ ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ለእናታችን ለሔዋን ያስተማራት የመጀመርያው ኑፋቄ ነው ማለት ይቻላል።

ባሌላ መልኩም ፍጡር ተለውጠ ፈጣሪ መሆን ይችላል ማለት

www.zeyeneta.com

ፈጣሪም በኋላ ፈጣሪ ሆነ እንጂ ቀድሞ ፍጡር ነበር እንደማለት ያለ ነው። እግዚአብሔር ግን መቼም እግዚአብሔር ነው። እርሱ የማይለወጥ አምላክ ነውና። አንተ ግን ያው አንተ ነህ እንዲል።

2/ ቃልን ሰው ይሆን ዘንድ ምን አተጋው? ሥጋ በትብዐት ተለውጦ የባሕርይ ልጅ የባሕርይ አምላክ መሆን የሚቻለው ከሆነ ቃልን ወደ ማኅፀነ ማርያም መጥቶ እንዲያድር ለምን አስፈለገው? ቃል የአብ አካላዊ ቀዳማዊ የባሕርይ ልጅ ነው፤ አሁን ደግሞ ሥጋ ባትብዐት የባሕርይ ልጅ ሆነ ካልን ለአብ ሁለት ልጆች አሉት አያሰኝምን? እንዲህስ ከሆነ የተቆረሰው ሥጋ የፈሰሰው ደም የማን ነው? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ አይገኝላቸውም። በድቡሽት ላይ እንደ ተሠራ ቤት በፈራሽ ነገር ላይ ተመሥርተዋልና። ይልቁንም የተቆረሰው ቅዱስ ሥጋ የፈሰሰው ክቡር ደም በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሆነው የሥግው ቃል ክርስቶስ እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ያስረግጣል። አብም ልጁ አንድ ነው እርሱን ስሙት አለ እንጂ ሁለት ናቸው እነርሱን ስሙ አላለንም። ማቴ.3÷17፣ ማቴ.17÷4።

3/ ተዋሕዷቸውን ማጥፋት አይቻልምና፦ እነዚህ ሰዎች አስቀድመው ቃል በሥጋ አልዘገም /ተገኘ አልሆነም/ ተዋሕደዋል+ ሁለትነት ጠፍቶ አንድነት ጸንቷል ካሉ በኋላ ትብዐቱ ለሥጋ ብቻ ነው ይላሉ። በተዋሕዶ ሁለትነት ከጠፋ እንደ ምን አድርገው አንዱን ሥጋን ብቻ ተቀባ ማለት ቻሉ? አንድነት ካለ ሁለትነት ከጠፋ አንዱን ብቻ መቅባት ማክበር አይቻልም። አንዱን መቅባት ማክበር ከተቻለ ደግሞ ተዋሕደዋል ብሎ መናገር አይቻልም። ስለ ዚህ ይኸም ከመጀመሪያዎቹ በምሥጢር ያልራቀ ይልቁንም «ከድጡ ወደ ማጡ» እንደሚባለው የቃልን ማጠት እንነቅፋለን ሲሉ ለአብ ሁለተኛ ልጅ ያለው አስመሰሉት።

ሐ/በተዋሕዶና በትብዐት ባንድነት የአምላክነትን ክብር ከበረ

እነዚህ ደግሞ ሦስተኛዎቹ ሲሆኑ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን የነበሩት እነ አለቃ ጉሹ ናቸው። እነዚህ ወገኖች ደግሞ ከሁለቱም የሚያሻሽሉት ነገር ቢኖርም በምሥጢር ከውላጤ አልወጡም። እነ አለቃ ጉሹ የሚሉትም ቅባት ያለ ተዋሕዶ፤ ተዋሕዶም ያለ ቅባት ብቻ ብቻውን አያከብርም ይላሉ። የእነዚህ ሰዎች ንግግር በአጭሩ በተዋሕዶ ብቻ አምላክ አይደለም÷ ሊሆንም አይችልም ነው። ይህ ደግሞ በምሥጢር እንደ መጀመርያዎቹ /ቃል በተዋሕዶ ጊዜ ተገኘ ሆነ የሚለው/ ያለ ትምህርት ነው። ያለ ቅባት አይከብርም ብለዋጠ ልና።

ስለዚህ ከመቀባቱ በፊት አምላክነት ካልነበረውና ከተቀባ በኋላ አምላክ ወደ መሆን የሚያድግ ከሆነ ይህም ተለወጠ ማለት ነው። ለዚያውም ሁለት ጊዜ፤ መጀመርያ ቃል ሥጋን ሲዋሐድ አምላክ ነቱን ካጣ ተለውጧል ማለታቸው ነው። ከተዋሕዶ በኋላ በትብዐት የባሕርይ አምላክ ሆነ ማለታቸውም ለሁለተኛ ጊዜ ተለወጠ ማለታቸው ነው። ከላይ በተደጋጋሚ እንደ ተገለጠው እግዚአብሔር ሰው ወደ መሆን የሚለወጥ፣ ሰውም አምላክ ወደ መሆን የሚለወጥ ከሆነ ፍጡር ያልነበረ ፈጣሪ፣ ፈጣሪም የማይሆን ፍጡር የለም የሚሉ ያስመስላቸዋል። ይህ ደግሞ በዓለም ላይ ልዩ የክህደት ዓይነት እንደሆነ ያስገነዝበናል። እነዚህኞቹ ከቀደሙት ከሁለቱ የሚለያቸው ለየብቻቸው መክበር አይቻላቸውም ማለታቸው እንደሆነ ግን መዘንጋት የለበትም። ይህም ሥጋን ከፍጡርነት ባሕርይ ቃልንም ከፈጣሪነት ሥልጣን የሚያወጣ ነው።

መ/ ቃል ተቀብጿል፦ ይኸን ያሉት ደግሞ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ተቀብዐ ማለት አንቀጹ ለቃል ነው። ይኸውም «ዮም ወለድኩከ÷ ዛሬ ወለድኩህ» እንደሚል በሥጋ ርስት በሥጋ ሜሕርይ እንደ ሰሎሞን እንደ ይስሐቅ

www.zeyeneta.com

የዳዊት ለጅ፣ የአብርሃም ልጅ፣ የአዳም ለጅ፣ የማርያም ልጅ በተባለበት ሰውነቱ፣ በሰው ልጅነቱ ተዳማሪ አዳም ያስመስደውን ሀብት ከአብ ተቀበለ። ይኸውም በማዘር ተወለደ ካህን፣ ነቢይ፣ ንጉሥ መባልን ፍጹም ሀብቱን ፍጹም ሹመቱን የሚመለከት ነው። ቃል ይህን ከአብ ተቀብቶታል ባይ ናቸው።

ይኸም ፍጹም ስሕተት ነው። እኒህ ሰው ቅድመ ሱስንዮስ የነበረው የተዋሕዶ ብሂልም ይህ እንደነበር ይገልጣሉ። በመሠረቱ የቅብዐት ጠባይ የመጣው በ17ኛው ክፍለ ዘመን በፋሲል ንጉሠ ነገሥትነት ጊዜ ሲሆን ተዋሕዶ ከኤፌሶን ጉባኤ ጀምሮ ለተደመው የሐዋርያት እምነትና ትምህርት መጠሪያ እንደሆነ ከታሪክ መረዳት ይገባል። እንደ አለቃ ኪዳነ ወልድ አስተሳሰብ ቃል መንፈስ ቅዱስን በመቀባቱ መሲሕ፣ በኩር፣ ነቢይ ወሐዋርያ በኩረ ምእመናንም ሆነ ይላሉ። ኪ.ወ.ክ. ገጽ 384 እና 780። ይህ ደግሞ ፍጹም ከሀዲት ነው።

ወልድ ሰውነትን፣ ሐዋርያነትን ወደ ዓለም መምጣትን ወድዶ ፈቅዶ ያደረገው በገዛ ሥልጣኑ የፈጸመው እንጂ በቅባት መኖር በመቀባትም ገንዘብ ያደረገው አይደለም። «ነገር ግን የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ዝቅ አደረገ /ትጉት ሆነ/» ፊል.2÷9 እንዲል። ለደቀ መዛሙርቱም የነገራቸው ይኸንኑ ነው። ትኅትናው ሰው በመሆን ብቻ ያበቃ አይደለም። ራሱን ዝቅ አድርጉ የደቀ መዛሙርቱን እግር በማጠብ ሁሉ የተገለጠ ሆነ እንጂ። ዮሐ.13÷14። ይልቁንም በአብ ቀባጊነት በመንፈስ ቅዱስ ቅብዕነት ከሀብታት ወገን የሆነ አንድ ስንኳን ገንዘብ አደረገ ካልን «የቃልን» ከሃሌ ኩሉ መሆን /ሁሉን አድራጊነት/ አለማመን መሆኑን መገንዘብ ይገባል።

ምክንያቱም ያለ አብ ቀባጊነት እርሱ መሲሕነትን ገንዘብ ማድረግ ካልተቻለው እንደምን አድርጉ እግዚአብሔር ነው ማለት

ይቻላል? ይልቁንስ የሚሳነው የሌለ ሁሉን በራሱ ማድረግ የሚቻለው አምላክ ወልደ አምላክ ነውና የመንፈስ ቅዱስ ቅብዐትም ሆነ የአብ ቀባጊነት ለእርሱ አያስፈልጉትም። «ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም ያለ እርሱ የሆነ የለም።» ዮሐ.1÷3 ይላልና። ከማንም ሀብትን የሚቀበል ሳይሆን እርሱ እኛን ባዕለጠጉች ያደርገን ዘንድ ድህ ሆነ። «ሀብታም ሲሆን እናንተ በእርሱ ድህነት ባዕለጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድህ ሆነ።» 2ኛቆሮ.8÷8 ይላልና ሀብታሙ ድህ የሆነ እንጂ ድህው ሀብታም የሆነ አይደለም።

ሠ/ ሥጋ ቅድመ ተቀሐዶ ተቀባ፡- ይኸ አሳብ የነአቶ ዓለማየሁ ሞገስ አሳብ ነው። እርሳቸውም በዚህ ኃይለ ቃል ላይ የሚከተለውን ጉደን አድርገው ተናግረዋል። «ከአብ በመንፈስ ቅዱስ የከበረ የተቀባ ሥጋ ከመለኮት ጋር ከመዋሐዱ በፊት ከሆነ በጥንታውያን አርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ተቀባይነት አያጣም፣ አለው፣ መለኮትን ካየና ከጨመረ ግን የቅባቶችና የጸጎች አንጡራ ገንዘብ ሁኖ ኑሯል። ይኖራል።» ብለዋል። /አንድ አረኛ አንድ መንጋ፥ ገጽ 27/።

ይኸም ፍጹም ስሕተት ነው። ምክንያቱም የእርሳቸውም ሃሳብ ከውላጤ አልወጣምና። ሥጋ ቀድሞ ተቀባ ከተባለ ጌታችን የነሣው ሥጋ ከሰማይ የወረደ ወይም ከመሬትም የወጣ አይደለምና። ይልቁንም ከማርያም ነሥቶታልና እርሷን ቀብቶ አክብሮ አምላክ አድርጓታል እንደ ማለት ያለ ነው። ይህ ግን ሌላ አዲስ የክህደት ትምህርት ይመስላል። የሚገርመው እኒህ ሰው በዚሁ መጽሐፋቸው ስለ እመቤታችን በጻፉት ምዕራፍ ከጥንተ አብሶ ነጻ ነበረች ለሚለው የሁለት ወገን ጹሑፍ አቅርቤያለሁ በሚሉበት አንቀጽ መንፈስ ቅዱስ እመቤታችንን ከጥንተ አብሶ አነጻት አከበራት በማለት አሳብ አቅርበዋል። አስረጂም የሚሉትን አስቀምጠዋል። ይኸም አሳባቸው

www.zeyeneta.com

እርስ በርሱ እንደሚጋጭ ያመለክታል። በእንድ ወገን መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ሁኖ እርሷን እንዳንጻ ሲናገሩ በሌላ ወገን ደግሞ ቅብዐት ሆኖ ቅድመ ተዋሕዶ ሥጋን አከበረ ይላሉና።

በምንም መንገድ ይሁን ግን ጌታችን የሚዋሐደውን ሥጋ ራሱ ማክበር የማይቻለው ሆኖ ከተዋሕዶ በፊትም ቢሆን፣ በተዋሕዶ ጊዜም ቢሆን፣ ከተዋሕዶም በኋላ ቢሆን ሌላ ማክበሪያ ቅባት ሌላ አክባሪ ቀቢ አስፈለገው ከተባለ የእርሱ የቀደመ ሥልጣኑን አለ ማመን መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል።

ማጠቃለያ፦ በጸጋ ከበረ የሚሉትም ይሁኑ ተቀብቶ የባሕርይ አምላክ ሆነ የሚሉት ሁሉም አብን ቀባዒ፣ መንፈስ ቅዱስን ቅብዕ ወልድን ተቀባዒ በማድረግ ይስማማሉ። ነገር ግን ይህ ትምህርታቸው ፈጽሞ ትምህርተ መለኮት ሊሆን አይችልም። ምክንያቱም፦

1ኛ/ መንፈስ ቅዱስን ቅብዕ ነው ካልን ቅድስት ሥላሴን ክደናልና። በሥልጣን ዕሩይ ያይደለ የአብ የህብት ማሳደሪያው ምልክት አድርገነዋልና። እነ ሳኦል እነ ዳዊት የተቀቡት ዘይቱ በራሱ ሳይሆን ያከበራቸው እግዚአብሔር እነርሱን ለመምረጡና ህብቱንም በእነርሱ ለማሳደሩ ምልክት ነበረ። 1ኛሳሙ.10÷1፣ 1ኛሳሙ.16÷3። ይኸም ተቀብተው ህብተ እግዚአብሔር በሳኦልም በዳዊትም ከማደሩ በፊት ሳሙኤል እንዲልቃቸው፣ በኋላም ዘይቱ ከሁሉም ያነሰ ነገር ግን እግዚአብሔር ሃብቱን በእነርሱ በማሳደሩ ምልክት እንዳደረገው ሁሉ እነዚህም ሰዎች አብን እንደ ሳሙኤል መንፈስ ቅዱስን እንደ ዘይቱ ወልድንም እንደ ሳኦል እንደ ዳዊት አድርገው ማሰባቸው ፍጹም ከህደት ነው። መንፈስ ቅዱስን እንደ ዘይቱ ፈሳሺ ጠፊ እንዳደረጉት ወልድንም ህብቱን ከእግዚአብሔር ተቀብሎ እንደገና በተወሰደበት በሳኦል መስለውታልና ፍጹም ስሕተት ነው።

2ኛ/ የጸጋ የማደጉ ልጅ የወደቀ አዳምን ወደ ቀደመ ክብሩ ሊመልሰው አይችልም። አዳምን በጥንተ ተፈጥሮ የፈጠረው እግዚ

አብሔር ነው። ሕጉን ሲተላለፍም የፈረደበት እግዚአብሔር ነው። ዘፍ.2÷7፣ ዘፍ.3÷1-፱ጸሜ። ወደ ቀደመ ክብሩም ሊመልሰው የሚቻለው እግዚአብሔር ብቻ ነውና። «የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።» 1ኛዮሐ.3÷8 መባሉም ሰው የሆነው እርሱ አምላክ ወልደ አምላክ መሆኑን ያስረግጣል። ዮሐ.1÷1።

3. በትብዐት የባሕርይ አምላክ መሆን አይቻልም። ምክንያቱም «የባሕርይ» የሚባል ነገር መሠረት፣ ጥንት፣ መገኛ፣ የራስ የሆነ ከማንም የማይቀበሉት ነውና፣ ተቀብቶ ከበረ ካልን ቀድሞ የራሱ ያልሆነ ገንዘብን ተቀብሏልና የባሕርይ አምላክ ሆነ ማለት አይቻልንም። ቀድሞውኑ አምላክነት የባሕርይ ገንዘቡ ከሆነ ደግሞ መቀባት /ቅባትም ቀቢም/ አያስፈልግውም። ስለዚህ በደስታ ዘይት ቀባህ ሲል በትብዐትም ሆነ በጸጋ ከበረ ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

1.8.4. ተቀባ ማለት ምን ማለት ነው፦ «ቃልም እግዚአብሔር ነበር» እንዲል እርሱ ልዑለ ባሕርይ ነው። እርሱ የሌለው ከማንም ሊቀበለው የሚገባው ገንዘብ ምንም ምን የለም። የማንም ርዳታ አያሻውም። ስለዚህ ተቀባ ማለት ከበረ ማለት ሲሆን አክባሪውም ከባሪውም ራሱ ነው። በጥንተ ነገር ጥቅሱ ራሱ የሚለው እግዚአብሔር አምላክነትህ /መለኮትህ/ ቀባህ ነው። ይኸውም ከሚከተሉት ጥቅሶች ጋር አንድ ዓይነት ብሂል እንዳለው ያመለክታል።

ለምሳሌ «ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሣውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ባስነሣው ለምናምን ለእኛ ይቆጠርልን ዘንድ አለው።» ሮሜ.4÷25። አሁን ቅዱስ ጳውሎስ «<u>ከሙታን ባስነሣው</u>» ሲል ሌላ አሥነሽ ነበረው ለማለት አይደለም አምላክነቱን እንዲህ አለ እንጂ። ይኸ ባይሆን ኖሮ መጀመርያ «እኛን ለማጽደቅ የተነሣውን» ባላለም ነበርና።

www.zeyeneta.com

«ከርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደፊት እንዳይሞት ሞትም ወደፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና::» ሮሜ.6÷9 እንዲል::

ስለዚህ «አስነሣው» ተብሎ የተጻፈ ለአምላክነቱ እንደሆነ ሁሉ «ቀባህ» የተባለለትም «አምላክነቱን» ነው:: ይኸም ማለት የተዋሐድከውን ሥጋ በራስህ አከበርህ:: «እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኰነ ለቃል::» የቃል የሆነው /መፍጠር፣መመለክ፣ መሰገድ/ ፍጡር ለነበረ ለሥጋ ሆነ::» እንዲል:: አምላክነትህ ቀባህ ማለት ይኸ ነው:: የሥጋ የሆነው /መራብ፣ መጠማት፣ መድከም፣ መሞት..../ ለቃል ሆነ:: «ባለጠጋው በእርሱ ድህነት ባለጠጉች ትሆኑ ዘንድ ድህ ሆነ::» የተባለውም ይህ ነው:: እርሱን ድህ ያደረገው የሚያሳንሰው፣ ባለጠጋ የሚያደርገው ቀብቶ የሚያከብረው የለም:: እርሱ ሁሉን ማድረግ ይቻለዋልና::

ራስን በራስ ማክበር ለእግዚአብሔር የተለመደ ነገር ነው:: ፍጡርን ከመፍጠሩ በፊት ባሕርይውን ባሕርይው እንዳመሰገነችው ባሕርይውን ባሕርይው እንዳከበረችው ፍጡሩን ከፈጠረ በኋላ ሰው በሆነ ጊዜ ባሕርይው /አምላክነቱ/ የተዋሕዶውን ሥጋ አከበረች እንጂ በሌላ አክበባሪ የከበረ፣ የተቀባም አይደለም:: ቅዱስ ጳውሎስም የማንንም አክባሪነትና ባዕድ ክብርን እንዳልፈለገ ሲያጠይቅ በመዝ.101÷25–26 ቅዱስ ዳዊት የሰጠውን ምስክርነት በመጥቀስ አስረድቷል:: «ጌታ ሆይ÷ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፣ ሰማዮችም የእጅህ ሥራ ናቸው:: እነርሱ ይጠፋሉ÷ አንተ ግን ትኖራለህ፣ ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ÷ እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ÷ ይለወጡማል አንተ ግን ያው አንተ ነህ፣ ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም» ብሏል::

ምዕራፍ ሁለት

«ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል::»

2.1. አብልጠን እንጠንቀቅ

«ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምን አልባት እንዳንወሰድ÷ ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል:: በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ÷ መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ÷ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው÷ እንዴት እናመልጣለን? ይህ በጊታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና÷ የሰሙትም ለእኛ አጸኑት÷እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ተአምራትም÷ መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መሰከረለት::ዕብ2÷1–4::

ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው ምዕራፍ ላይ የጌታችንን ንግግር በንጽጽር አስቀምጦ ይልቁንም ደግሞ «የእግዚአብሔር ቃል መጣላቸው» የተባሉትን ነብያትንና የሚላላኩትን መላእክትን አንሥቶ ከእነርሱ እንደሚበልጥ አስረድቷል:: የእርሱን ከመላእክትም ከነብያትም መብለጥ ካመንን የእርሱ ንግግር ከሌሎቹ ይበልጣልና፣ ለእነዚያ ያልታዘዙት ከተቀጡ ለእርሱ የማንታዘዝማ የበለጠ ቅጣት ይጠብቀናልና እንጠንቀቅ ለማለት «ስለዚህ» ሲል ጀመረው::

ሀ) ለነብያት ያልታዘዙ ተቀጥተዋል

ከሊቀ ነቢያት ሙሴ እንኳን ብንጀምር ብዙ ሰዎች እንዳጉረመረሙበትና አንደ ተቃወሙት ተጽፏል፣ በዘኁ.12÷1–15 እንደምንመለከተው አሮንና እኅቱ ማርያም ሙሴን ተናገሩት:: እግዚአብሔርም እነርሱን ገሠጻቸው:: በተለይም ማርያምን በለምጽ

www.zeyeneta.com

መታት:: «እርሱም:– ቃሌን ስሙ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር+ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ+ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ:: ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም:: የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል በባሪያዬ በሙሴ ላይ ትናገሩ ዘንድ ስለምን አልፈራችሁም? አለ::» ዘኍ12+6–8 እንዲል:: ዳታንና አቤሮን ከእነርሱም ጋር የነበሩ 250 አለቆች የሙሴን ንግግር አትልለው በድፍረት ለግልገል ወደ ደብተራ አሪት ስለ ገቡ በእሳት ተቃጥለዋል:: ዘኍ.16+1–50:: እስራኤል ዘሥጋ የሙሴን ምክርና ንግግር አንሰማም በግለታቸው 40 ዘመን በበረሃ ተቀጥተዋል፤ ከኢያሱና ከካሌብም በቀር ርስታቸውን ከነዓንን ለማየት ሳይታደሉ ቀርተዋል:: 1ኛቆሮ.10+1–13::

ኢዮርብዓም እግዚአብሔር በላከው ነቢይ ላይ ዓመፀ፤ ንግግሩ ንም አቃለላት፣ ይይዘውም ዘንድ ወድዶ እጹን ባነሣት ጊዜ ደረቀች:: 1ኛነገ.13+4:: ንጉሡ ሶርያ ወልደ አዴር ሰማርያን በከበባት ወቅት በእስራኤል ጽኑ ራብ ሆኖ ነበር:: በራቡ ጽናት የተነሣ እናቶች የገዛ ልጆቻቸውን እስከ መብላት ደርሰው ነበር:: በዚህ ጊዜ ንጉሡ እስራኤል ተቆጥቶ ወደ.ነቢዩ ኤልሳዕ መልእክት ላከ:: ነቢዩም ነገ በዚህች ከተማ (በሰማርያ በር) አንድ መሥፈሪያ ዱቄት በአንድ ሰቅል ሁለት መሥፈሪያ ገብስ በአንድ ሰቅል ይሸመታል አለ:: መልእክተኛው ግን የነቢዩን ንግግር አትልሉ «እነሆ እግዚአብሔር በሰማይ መስኮቶች ቢያደርግ ይህ ነገር ይሆናልን?» ሲል በመናገሩ ነቢዩ «በዓይናችህ ታየዋለህ ከዚያም አትቀምስም» ሲል ተናገረው:: ነገሩ ተፈጸመ፤ አገልጋዩም በንጉሡ በር ተጠቅጥቆ ሞተ:: 2ኛነገ.6+24፤ 7+17::

ለ) የመላእክትን ንግግር ያቃለሉ ተቀጥተዋል::

የሎጥ ሚስት «ወደ ኋላ ዞረሽ እትይ» የተባለችውን የመልአኩን ንግግር ስለ አቀለለች የጨው ሐውልት ሆና ቀርታለች::

ዘፍ19+26:: ሊቀ ካህናት ዘካርያስም የቅዱስ ገብርኤልን ንግግር በእምነት ስላልተቀበለ ተገሥጿል:: ሉቃ.1+1–13:: የእግዚአብሔር ቃል «በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ሥፍራ ያገባህ ዘንድ+ እነሆ+ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ:: በፊቱ ተጠንቀቅ፣ ቃሉንም አድምጥ፤ ሸሚም በርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት::» ዘጸ.23+20 እንዲል በመልአኩ ፊት ኃጢአትን የሚሠሩትን ንግግሩንም የማያደምጡትን ይቀጣልና ተጠንቀቁ ይላል:: ቅዱስ ጳውሎስ ከላይ በተቀመጠው አንቀጽ ላይ የሚያስረዳው ይህንን ነው:: እነዚያ እግዚአብሔር የላካቸውን ነብያት በማ ቅለል፣ መላእክትን ባለማድመጥ ከተቀጡ ከተፈረደባቸው ይልቁንስ እኛማ የእነርሱን ፈጣሪና ጌታ ካቀለልነው እንደምን ቅጣታችን አይበልጥብንም? ስለዚህ ልንጠነቀቅ ይገባል ይላል::

የመላእክት ንግግር ጽኑ ከሆነ በጌታችን የተነገረች ወንጌል ማ እንዲት አትበልጥም? ስለ እርሱም ታላትነት ቀድሞ በነብያት ከተነገረው ትንቢት ይልቅ በሚሠራው ተአምራትና በባሕርይ አባቱ በአብ በባሕርይ ሕይወቱ በመንፈስ ቅዱስ በአደረባቸው በቅዱሳን ሐዋርያት ተመሰክረለት::

1. <u>በአብ</u>:– «የምወደው ልጄ እርሱ ነው፤ እርሱን ስሙት» ተብሉ ተመስክሮለታል:: ማቴ.3+17፣ ማቴ.17+4::

2. <u>በራሱ</u>:– ተአምራቱ ምስክሮቹ ናቸው፤ በደረቅ ግንባር ዓይን መፍጠሩ /ዮሐ.9+1–7/፤ የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን ሥጋውን ከመቃብር ነፍሱን ከሲኦል ጠርቶ አዋሕዶ ማስነሣቱ /ዮሐ.11+43/፤ በሠርግ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን መለወጡ /ዮሐ.2+7–9/፤... እንደ እምነትህ ይደረግልህ እንደ እምነትሽ ይደረግልሽ በማለት ለምጻምን ማንጻቱ፣ ዕውርን ማብራቱ፣ ጉባጣን ማቅናቱ... ለባሕርይ አምላክነቱ ምስክር ነውና::

www.zeyeneta.com

3. መንፈስ ቅዱስ በበነሶ ጎምሳ ያደረባቸውና ጸጋውን ያበዛላቸው ሐዋርያት የሰጡት ምስክርነት የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት ነው:: «በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና» ማቴ.16÷16 እንዲል:: «ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን:» /1ዮሐ.1÷1-2/:: ቀድሞ በነብያት እያደረ መንፈስ ቅዱስ ተናግሯልና::

እንዲህ ታላቅነቱ ከተመሰከረለት ያድነን ዘንድ ሰው ከሆነ ከጌታችን ትእዛዝ ብናፈገፍግ እንዴት ከቅጣት እናመልጣለን? የሠርግ ልብስ ሳይለብስ ስለመጣው ሰው «እጁንና እግሩን አሥራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፣ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ::» ማቴ.22÷13:: በአምስቱ የደናግል ስንፍና አንጸርም ደጅ ከተዘጋ በኋላ መጥተው ቢጮሁ «እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ አላውቃችሁም አለ::» ሲል ተናግሮናል:: በሰነፏና በሐሰተኛው አገልጋይ አንጻርም እንዲሁ:: ማቴ.25÷1-30::

ይልቁንም ስለ ዕለተ ምጽአት ሲናገር «በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል:: እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ::....» ማቴ.25÷41 ማለቱ ከፍርዱ ልናመልጥ አለመቻላችንን÷ ንግግሩንም ከአቀለልን ሥርየት የለሽ ኃጢአት መሥራታችንን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ማቴ.12÷31:: «የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፣ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ÷ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል? በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለውን እናውቃለንና፣ ደግሞም:- ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል:: በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ

የሚያስፈራ ነው::» /ዕብ.10÷28-31/ እንዳለ አብልጠን መጠንቀቅ ይጠበቅብናል::

ራሱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ ብእሲ መገለጡን አይተው እንደ ዕሩቅ ብእሲ ስላዩት በአምላክነቱ የሚደረገው ደኅኖ ተአምራት እንዲያደርግ በጠየቁት ጊዜ «ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፣ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም:: ዮናስ በዓሣ አንበሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደነበረ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል:: የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፣ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና፣ እነሆም÷ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ:: ንግሥተ ዓዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፣ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፣ እነሆም ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ::» ሲል አስተምሯል:: ማቴ.12÷39-42::

ስለዚህ ጌታችን ከሁሉም ስለሚበልጥ ከትእዛዙና ከትምህርቱ ከአምልኮቱም ፈቀቅ ባልን ጊዜ ከፍርዱ ልናመልጥ ስለማንችል አብልጠን መጠንቀቅ ይገባናል::

2.2. ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው?

ቅዱስ ጳውሎስ ከፍርዱ አናመልጥምና እንጠንቀቅ ካለ በኋላ በሚመጣው ዓለም የሚፈርድብን እናንተ ቸል ያላችሁት ሥጋን ተዋሕዶ የተገለጠው ነው:: በዚህ ክብር ይገለጥ ዘንድ፣ በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ይቀመጥ ዘንድ የተገባው መሆኑ የሚያስደንቅ አይደለም፣ ጌትነት የባሕርይ ገንዘቡ ነውና:: ነገር ግን የሚደንቀው የሰው ሥጋ በተዋሕዶ ቃል ለዚህ መብቃቱ ነው ለማለት የተናገረው ንግግር ነው:: ይኸውም የትኅትና ንግግር ነው:: ይህም ግልጽ እንዲ

www.zeyeneta.com

ሆንልን ለአብነት ያህል የጥቂቶቹን አበው ንግግር ከመጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ያስፈልጋል።

ሀ/ ሙሴ፦እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ሊያላቅቃቸው በፈቀደና ጊዜውም በደረሰ ጊዜ ሙሴን ጠርቶ አነጋገረው። «...አሁንም ና÷ ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብጽ ታወጣ ዘንድ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ። ሙሴም እግዚአብሔርን ወደ ፈርዖን የምሄድ÷ የእስራኤልንም ልጆች ከግብፅ የማወጣ እኔ ማን ነኝ? አለው።» ዘጸ.3÷9 ይላል። ሙሴ እኔ ማን ነኝ ያለው ታናሽ ነኝ አይገባኝም ለማለት ነው።

ለ/ ቅዱስ ዳዊት፦ ቅዱስ ዳዊት ከጠላቶቹ ሁሉ ባረፈ ጊዜ ለእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት አለመሥራቱን አሰበና አዘነ። «... በእውነት ወደ ቤቴ ድንኳን አልገባም፣ ወደ ምንጣፌም አልጋ አልወጣም፣ ለዓይኖቼም መኝታ ለሽፋሽፍቶቼም እንቅልፍ ለጉንጮቼም ሰረፍትን አልሰጥም÷ ለእግዚአብሔር ሥፍራ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያ እስካገኝ ድረስ ብሉ።» መዝ.131÷1–5 እንዲል። እግዚአብሔርም በእርሱ በሥጋ መገለጫውን÷ የዘላለም ማደሪያውን ለእርሱ ገለጸለት። ስለ ቤቱ ግን በነቢዩ በናታን አማካኝነት «... አሁንም ባሪያዬን ዳዊትን እንዲህ በለው ... በምድርም ላይ እንዳሉ እንደ ታላላቆች ስም ታላቅ ስም አደርግልሃለሁ። ለሕዝቤም ለእስራኤል ሥፍራ አደርግለታለሁ፥ እተክለውማለሁ። በሥፍራውም ይቀመጣል፥ ከዚያም በኋላ አይናወጥም።... ቤትህና መንግሥትህም በፊቴ ለዘላለም ይጠነክራል፣ ዙፋንህም ለዘላለም ይጸናል።...» የሚል የእግዚአብሔር በረከት ደረሰው። ንጉሡ ዳዊትም ገባ፣ በእግዚአብሔርም ፊት ተቀምጦ ጌታዬ እግዚአብሔር ሆይ÷ እስከዚህ ያደረስኸኝ እኔ ማን ነኝ? ቤቴስ ምንድር ነው? ...» አለ። 2ኛ ሳሙ.7÷1–22። ዳዊት እኔ ማን ነኝ ያለው የተደረገልኝ ነገር

የገባህልኝም ቃል ኪዳን ለእኔ የሚገባ አይደለም፥ አንተ ግን ለሁል ብትሆንም ለእኔ ለታናሹ አደረግህልኝ ለማለት ነው።

2.2.1. ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል። እንዴት?

2.2.1.1. <u>ዓለሙን ስለ መፍጠሩ፦</u> ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ምንድን ነው የቅዱስ ዳዊትን ንግግር የጠቀሰው ስንል ሊቃውንቱ «እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ዓለሙን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል» በማለት በአጭሩ ይመልሱታል። ምን ለማለት ነው? በመጠኑ እንመልከተው።

ሀ/ ዓለምን ለምን ፈጠረው? ለሰው በታወቀው በተረዳው ስለ ሦስት ነገር ዓለሙን ፈጥሯል።

- ስሙን ቀድሰው ክብሩን እንዲወርሱ የፈጠራቸው አሉ። ሰውና መላእክት
- ለምግበ ሥጋ የተፈጠሩ አሉ። ለሰውም ለእንስሳም /አንዱን አንዱ ይመገባልና/
- ለአንክሮ ለተዘከሮ /ባሕርይው የማይመረመር የሥራው ልኩ የማይታወቅ... መሆኑን አስተውለን እንድናመሰግን/

ለ/ ዓለምን ከምን አስገኘው?

- እም ኀበ አልቦ /ከምንም/ የተገኙ አሉ፣ እነዚህም ስምንቱ የዕለተ እሑድ ፍጥረታት ናቸው። መሬት፣ ውኃ፣ እሳት፣ ነፋስ፣ ጨለማ፣ ሰማያት፣ መላእክት፣ ብርሃን፣ እነዚህን ካለመኖር ወደ መኖር፣ ከኢምንት /ይህ ነው ከማይባል ካለመገኛ/ ወደምንት /ከስ ማቸው ወደሚጠሩበት አካላዊነት/ አመጣቸው። ሁሉን ማድረግ ይቻለዋልና።

- ግብር እም ግብር /ከተፈጠረው ፍጥረት ላይ በመውሰድ/ እነዚህ ከሰኞ እስከ ዓርቡ የተፈጠሩት አሥራ አራት ፍጥረታት

www.zeyeneta.com

ናቸው። ለእኒህም መሠረታቸው /መገኛቸው/ በዕለተ እሑድ ከቀዳ ማይ ሰዓተ ሌሊት እስከ አራተኛው ሰዓተ ሌሊት የተፈጠሩትና አሥ ራው ፍጥረታት ከሚባሉት መሬት፣ ውኃ፣ ነፋስና እሳት ናቸው። ለምሳሌ፦ ሰውን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋ /ከመሬት፣ ውኃ፣ ነፋስና እሳት/ ላይ ባሕርየ ነፍስን ጨምሮ ፈጠረው። እንስሳትን፣ አትክል ትን፣ ዕጽዋትን፣ አዝርዕትን በየወገናቸው የሚቆሸሩትን ሁሉ እን ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብትም ቀድመው ከተፈጠሩት ላይ የተፈጠሩ ናቸው።

ሐ/ እንዴት አድርጉ ፈጠራቸው?

– በአሳብ /በሀልዮ/ እኒህም ከብርሃን በቀር የዕለተ እሑድ ሰባቱ ፍጥረታት ናቸው። ምክንያቱም መላእክት እስከሚፈጠሩ ድረስ ሰሚ ፍጥረት የለምና። ሰሚ በሌለበት ስንኳን አምላክ ሰው አይናገርምና።

– በቃል /በንግግር/ «ይሁን» በማለት፦ ከዕለተ እሑድ ብርሃን እንሥቶ እስከ ዓርብ ሦስቱ ፍጥረታት በድምሩ አሥራ አራቱን

– በገቢር /በሥራ/፦ ሰውን «ከምድር አፈር አበጀው» ይላልና።

ስለዚህ ለሰው እግዚአብሔር በገለጠው፥ በታወቀውና በተረ ዳው መንገድ ስንመለከተው ዓለምን ያስገኘበትና የፈጠረበት ግብር ሁሉን ቻይ መሆኑንና ጥበበኛ መሆኑን፥ የፈጠረበት ዓላማም ጥበበ ኛነቱን ያስረዳል።

2.2.1.2. ዓለሙን ስለ ማዳኑ

ሀ/ ዓለሙን ለምን አዳነው?

– የበደለው አዳም ንስሐ ስለ ገባ

– እግዚአብሔርም ለሚመለሱት ንስሐን የሚቀበል ፍጹም መሐሪ ስለሆነ

– በደልና ክፋት ከአዳም ባሕርይ የተገኙ ስላልሆኑ

ለ/ ዓለምን ከምን አዳነው?

– ከሞት ከሰኑኑ

– ከፍዳ ከመርገም

– ከሲኦል ከገሃነም

– ከዲያብሎስ ወጥመድ ከኃጢአት

ሐ/ እንዴት አዳነው?

– ልዑል ቃል በተዋሕዶተ ሥጋ በትጎትና ሰው ሆኖ በመገለጥ

– ከኃጢአት በቀር ሰው የሆነውን ሁሉ በመሆን

– በሞቱ ሞትን ገድሎ ዲያብሎስን በመሻር

2.2.2. ዓለምን የማዳን ጥበብ ዓለምን ከመፍጠር ጥበብ እንዴት ይበልጣል?

ዓለምን ማዳን ዓለምን ከመፍጠር እንደሚበልጥ ለመጻፍ ሊታሰብ፣ የእግዚአብሔርን ዓለምን የመፍጠር ጥበብ፣ ዓለምን የማዳን ጥበብ፣ እግዚአብሔር እንደ ፈጸመው አድርጉ መጻፍና ማሳየት የሚቻል፣ ማንጸጸሩንም ቁልጭ አድርጉ ማቅረብ የሚቻል ስለሆነ አይደለም። ነገር ግን ለሰው እንደተሰጠው መጠን፣ እግዚአብሔርም እንደገለጠልን ሁኔታ፣ ለጎሊና በታወቀ በተረዳ ነገር መግለጽ በሚቻለው አቅም እንጽፋለን ለማለት ነው።

በዚህ ዓለም ከምናውቀው ብንነሣ የበሬ መዋጋትና የአህያ መራገጥ የሚያስደንቅ አይደለም፣ የተለመደ ነውና። የሰው መሞት አይደንቅም የሰው ማረግ ግን ይደነቃል፥ ያልተለመደ እንግዳ ነገር ነውና። የፈጣሪም በተለያየና ለሰው ጎሊና በሚረቅ መንገድ ፍጡራ ንን መፍጠሩ የሚያስደንቅ ሊሆን አይችልም። ካለበለዚያማ የፈጣሪ ሁሉን የማድረግ ቻይነት ወዴት አለ? ይህንንስ ማድረግ ካልቻለ

www.zeyeneta.com

ፈጣሪ ነው ማለት ይቻላልን? ስለዚህ እግዚአብሔር በአምላክነቱ ግብር ሰውን አድኖት ቢሆን፣ ሞትን ገድሉ ዲያብሉስንም ሽሮ ቢሆን ኖሮ አድኅኖቱ ባልተደነቀ ነበር፡ ለእርሱ ሁሉም ይቻለዋልና።

ሟች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ የሆነ ሰው ደግሞ መራቡ፣ መጠማቱ፣ መሞቱ የሚያስደንቅ አይደለም። ለእኛ የተለመደ የባሕርይ ገንዘባችን ነውና። ነገር ግን ሰውን የአምላክን ሥራ ሲሠራ ቢያዩት ያስደንቃል፣ የእርሱ ገንዘብ ያልሆነውን ገንዘቡ አድርጓልና። ሰው፣ በዘላለማዊው የእግዚአብሔር ዙፋን ሲገለጥ፣ በየማነ አብ በዘባነ ኪሩ ብም ሲቀመጥ ማየት ድንቅ ጥበብ ነው። በአንጻሩ ደግሞ የማይሞተውን፣ ሞትም የማይስማማውን እግዚአብሔርን ሲሞት ማየት በአንደበት ከመግለጽ በላይ የሆነ ድንቅ ነገር ነው። ይልቁንም እግዚአብሔር ሞትንና ሲኦልን አበጋዛቸውን ዲያብሉስንም፣ በሥልጣኑ ሳይሆን በሞቱ ድል መንሣቱ ሥራው የማይመረመር ሊነገር የማይቻል እንደሆነ ይነግረናል።

እግዚአብሔር በሞቱ ድል ለመንሣት ደግሞ መዋቲ /ሟች ፈራሽ በስባሽ/ የሆነ የአዳምን ሥጋ መዋሐድ ነበረበት። «ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ።» ዮሐ.1÷14 እንዳለ አካላዊ ቃል፣ አምላክ ወልደ አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ ሰውም በተዋሕዶተ ቃል አምላክ ሆነ። ስለዚህም ነገር «አዳምን ከፈጠረበት ጥበቡ ሰው ሆኖ አዳምን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል» በማለት ብፅ ትኅትናውን ተናገረን።

2.2.3. በውኑ ሰው አምላክ መሆን ይገባዋልን?

በዚህ ምድር ያሉ ነገሥታትና ገዥዎች እነርሱን ፈንቅሎ የእነርሱን ሥልጣን ለመውሰድ የተነሣውን ሰው ይሸልሙታልን? ስንኪን የእርሱ የዘሮቹም ስም አጠራራቸው እንዳይታወቅ አድርገው ያጠፏቸዋል። «ንጉሥ የገደለውን አንበሳ የሰበረውን የሚያነሣ የለም» እንዲባል፡ ስንኪን ሞታቸው ለቅሷቸውም አያምርም፡ ቀብራቸውም

በመልካም ቦታ አይሆንም። እንዲሁ አዳም የእግዚአብሔርን አምላክነትን ሽቶ ሰፀ በለስን በላ። በእግዚአብሔር አምላክነትም ላይ ዓመፀ። እግዚአብሔርም አዳምን ባጠፋው፡ እንዳልተፈጠረም ማድረግ በተገባው ነበረ፥ ማድረግም ይቻለዋልና። እግዚአብሔር ግን ፍቅሩ ፍጹም ስለሆነ ይልቁንም አዳም ያደረገውን ያላወቀ መስሎ እግረ ሰኰና ብእሲ /የሰው ኮቴ/ እያሰማ መጥቶ «አዳም፥ አዳም ወዴት ነህ» ሲል ጠራው?... ትእዛዙን ስላልፈጸመ ረገመው፡ ከገነትም አስወጣው።

ነገር ግን ንስሐውን ተቀበለ፥ «አዳም ከፋውንና ደጉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ።» አለ። /ዘፍ.3÷10–13/። ጊዜው ሲደርስም ያን በእርሱ ላይ የሣመፀውን፣ «መሬት ነህና ወደ መሬት ትመለሳለህ።» ብሎ የፈረደበትን የአዳምን /የሰውን/ ሥጋ ለተዋሕዶ አሰበው፡ አስቦም አልቀረ ነፍሱንም ሥጋውንም ነሥቶ በተዋሕዶ ሰው ሆነ፡ ሰውም አምላክ። ይህንንም ነቢዩ ዳዊት ሲያመለክት መሬት ትሆናል ብለህ ፈራሽ በስባሽ ያረግኸውን ሥጋ ለተዋሕዶ ታበቃው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? አምላክነትህን ሽቶ ያመፀ አዳምን ትጐበኘው ወደ ቀድሞ ክብሩም ትመልሰው ዘንድ ይልቁንም የሻውን አምላክነት ትሰጠው ዘንድ ሰው በውኑ ምንድን ነው?» አለ።

እግዚአብሔር ሰውን በማሰቡ /ለተዋሕዶ በመምጣቱ/ የተጠቀምነው ምንድን ነው?

<u>ሀ/ ሰው አምላክ ሆነ።</u>

እግዚአብሔር አዳምን አሰበው ስንል አምላክ ሰው ሆነ ማለታችን ነው። አምላክ ሰው በሆነ ጊዜም ሰው አምላክ ሆኗል። አካላዊ ቃል በተዋሕዶ ተዋሕዶ ረቂቁ ገዘፈ፣ ምሉዑም ተመሰነ፣ የሥጋንም ገንዘብ ገንዘቡ አደረገ። ሥጋም በተዋሕዶተ ቃል በተዋቅቦ ግዙፉ ረቂቅ፥ ውሱኑም ምሉዕ ሆነ፥ ሥጋ ከቃል መሳጠጠንን፣

www.zeyeneta.com

መመሰገንን፣ ኅለምን ማኅለፍን በአጠቃላይ ሥልጣን መለኰትን ገንዘብ አድርጉ በየማነ አብ በዘጠነ ኪሩብ ተገለጠ። በትዱላን መላእክትም ተመሰገን። ከላይ የተመለከትነውን ሐት አራቱ ወንጌላትም ሆኑ የቅዱሳን ሐዋርያት መልእክታት በሙሉ ያስረግጣሉ። «በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሥፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን።» ኤፌ.2÷7።

ለ/ አባ አባት ብለን የምንጠራበትን የልጅነት ሥልጣን አገኘን

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ የሚገልጠው ዐቢይ ምሥጢር ይህ ነው። ወልድ የአብ የባሕርይ ልጅ ነው፣ በሥጋ ደግሞ የማርያም ልጅ። «የአብርሃምን ዘር ይዟል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።» ዕብ.2÷16፤ «የአብርሃም ልጅ የዳዊት ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ» ማቴ.1÷1፤ «የአዳም ልጅ» ሉቃ.3÷38። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳም ልጅ ነው ካልን ወንድማችን ነው ማለታችን ነው። ሐዋርያው «እንግዲህ ልጆቹ በሥጋና በደም ስለሚካፈሉ...» ዕብ.2÷14 ያለው በሥጋ ወንድማችን መሆኑን ለመናገር ነው። እኛም እግዚአብሔር አብን አባታችን ብለን ለመጥራት የታደልንበት ዐቢዩ ምሥጢር አብ የወልድ አባት ነው እኛ ደግሞ የወልድ ወንድሞች ነን ስለዚህ በተዋሐደው ሥጋ በኩል አብን «አባታችን» ለማለት በቃን። ይህን ያገኘነው በምሥጢረ ሥጋዌ ነው። ጌታችን ሰው ባይሆን ኖሮ አምላካችን፣ ፈጣሪያችን እያልን እንደ ሌሎች ፍጡራን ርቀን በቀረን ነበር። «ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፣ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቀድ አልተወለዱም።» ዮሐ.1÷12፤

«ልጆችም ስለሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት ብሎ የሚጮህ

የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ ላከ።» /ገላ.4÷6/ እንዲል የልጅነትን ሥልጣን ያገኘነው፣ አባታችን ብለን መጥራት የቻልነው ሰው በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስለ ተዛመድን ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፣ ምንም እንኳ እኛ «እግዚእነ፣ አምላክነ፣ መድኃኒነ...» ብንለውም እርሱ እኛን ወንድሞቼ ሲል ለመጥራት አላፈረም።

«ስምህን /ስመ ሥላሴን፣ ስመ ወላዲነትህን/ ለወንድሞቼ /ለሐዋርያት፣ ለምእመናን/ እነግራቸዋለሁ። በማኅበርም /በአርድእት፣ በምእመን/ መካከል በዜማ አመሰግንሃለሁ፤» ደግሞም... «እኔ በእርሱ እታመናለሁ፤ ደግሞም፡– እነሆኝ እኔን እግዚአብሔር የሰጠኝንም ልጆች ሲል ወንድሞች ብሎ ሊጠራቸው አያፍርም።» ዕብ 2÷13–14፣ መዝ.21÷22፣ ኢሳ.8÷17 እንዲል።

በወንጌልም ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ለስብከተ ወንጌል ባሠ ማራበት እንቀጽ ላይ «በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፣ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል።» /ሉቃ.9÷26/ በማለት የዝምድናውን ነገር አጠንክሮ ታል። አፍርበታለሁ ያለ፣ ቢዛመደን እንጂ ባይዛመደን አይደለም። «በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፣ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።» ገላ.3÷27 እንዲል።

ሐ/ <u>ቋራኝነትን አራቀልን።</u>

ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ቀድሞ ከአዳም በደል ጀምሮ የሚወለዱትን ሁሉ ገና በእናታቸው ማኅፀን በዘርዕ ምክንያት ይቆራኟቸው ነበር። እርሱ ግን እንበለ ዘርዕ /ያለ ወንድ ዘር/ ተጸንሷልና ጽንትም /ጠማምነት+ የኃጢአት ዝንባሌ/ የለበትምና ሊቆራኘው አልቻለም። ሰይጣን በዘርዕ ያቆራኘውን በኋላ ኃጢአት ሲያሠራው

www.zeyeneta.com

ይኖርና በሞቱም ላይ አለቃ እርሱው ነበርና፡ የሚያስፈራ ጥቁር ገጹን /የሞት ጻዕር/ እያሳየ በድንጋጤ ይገድል ነበር። ከሞቱም በኋላ ሥጋን በመቃብር ነፍስንም በሲኦል እየተቆራኘ ይኖር ነበር።

ጌታችን ግን ያለ ዘር በመጸነስ የዲያብሎስን በግንባን መቆራኘት ቆረጠልን። ልጅነትንም ሰጥቶ ተዋሕዶን እንዳይኖር በተዋሕዶ ሥጋ ሰው ሆኖ ተገለጠልን። በኋላም ደግሞ «አባት ሆይ÷ ነፍሴን በእጅህ አደራ አሰጣለሁ።» /ሉቃ.23÷46/ በማለት በሞት ላይ የነበረውን ሥልጣን ሻረበት። የሞትም አስፈሪነት ጠፋና ለመናፈቅ በቃ። «ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፣ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፡» ፊል.1÷23 እንዲል። ነፍሳችንም በቁራኝነት ተይዛ በእግረ አጋንንት ከመጠቅጠቅ ዳነች።

ገነት በክቡር በደሙ ማኅተም ተከፍታልናለችና። በቀደመው ዘመን ሰይጣንንና ሞትን በመፍራት በድን የዳሰሰ፣ መቃብር ያፈለሰ ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ተብሎ ይለይ ነበር። አሁን ግን ይህ ቁራኝነት ስለ ቀረልን ሞትንም መፍራት ስለ ጠፋ አስከሬንን አጥበን፣ ገንዘን፣ ስመን የምንሸኝ በክብር ቀብረን የምንመለስ ሆነናል። ይልቁንም ከጌታችን በኋላ የቅዱሳን ነፍሳቸው የሚያርፉት በይባቤ መላእክት በመዐዛ ገነት የምትለይ ሆናለች፣ የዲያብሎስ ጽኑም (ጨለማ) ገጽ ሕሱም ራእይ ርቆልናል። «ክቡር ሞቱ ለጻድቅ በቅድመ እግዚአብሔር» እንዳለ። መዝ.115 /116/÷6 የጻድቃን ሞተ ሥጋቸው በእግዚአብሔር ዘንድ የተከበረ ሆኗል።

ሊቀ ዲያቆናት ወቀዳሚ ሰማዕት ቅዱስ እስጢፋኖስ ነፍሱ ከሥጋው ከመለየቱ በፊት የወልደ እግዚአብሔር ጌትነት እንደ ተገለጠለት /ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ/ ተብሎ የተጻፈውም የቁራኝነት መቅረት ማረጋገጫ ነው። ሐዋ.7÷56።

ስለዚህ እግዚአብሔር ዓለሙን ከፈጠረበት ጥበቡ ይልቅ ሰው ሆኖ ዓለሙን ያዳነበት ጥበቡ ይበልጣል ተባለ። ለፈጣሪ መፍጠር

የሚገድ ለእኛም የሚደንቅ አይደለም። ሊፈጥር አሰበ ሆነለት፣ ተረገረ ተፈጸመለት፣ ሠራ፣ አበጀ፣ አማረለትም። ሰውን ሲያድን ግን ለተዋሕዶተ ሥጋ ራሱን ዝቅ አደረገ፣ ሰውንም በልዑል መንበር አስተመጠ፣ ተሰቀለና ደሙን አፈሰሰ፣ የአዳምን ኃጢአት አደረቀ። ሞተ፣ ሞትንና ሲኦልን ገደለ፣ አበጋዛቸውን ዲያብሎስንም ሻረ። እንበለ ዘርዕ ተጸንሶ በዘር የሚቆራኙንን፣ በተዋሕዶ ሰው ሆኖ ተዋሕዶን የሚኖር ኃጢአትን ነቀለ አደረቀ። ቀድሞ በነሙሴ በነብያት የነገረንን ሥግው ሆኖ ነገረን÷ ሠርቶም እንሠራ ዘንድ አሳየን። ስለ መገለጡም መግለጫ ቃላት እስከሚታጣለት ድረስ ምግባሩን በትጎ ትና አስተማረን።

ስለዚህም ሊቃውንት ከሥነ ፍጥረት ምሥጢር የሥጋዌ ምሥጢር ይበልጣል አሉ። ምክንያቱም የተፈጠረውን ፍጥረት ከልበ ሥላሴ በቀር የሚያውቀው የለም። እንዲያው በወገን በወገን አድርገው መንፈስ ቅዱስ በገለጸላቸው መሠረት ቆጠሩ እንጂ። ይልቁንም አምላክ በሰውነቱ የሠራውን ለሰው የተደረገለትን በጉ ነገር መግለጥ አይቻለንም አሉ። ስንኪን ሰው መላእክትም በመደነቅ «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት፣ ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ፣ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።» ሉቃ.2÷14። ስለዚህ ለሰው የተደረገውን በጉ ፈቃድ መዘርዘር እንደማይቻል እንረዳለን።

ወደ ፊትም ከዚህ ዓለም መከራና ስቃይ ጋር የማይመዛዘን ደስታ ተዘጋ ጅቶልናልና። «ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ» ሮሜ.8÷18። በውኑ ይህ ሁሉ ይደረግለት ዘንድ ለአምላክነትም ይበቃ ዘንድ፣ ለምእመንም ቅድስና፣ ክብርና ርስት ይሰጥ ዘንድ ለሰው ይገባው ነበርን? በእውነት ያለ ሐሰት «ታስበው ዘንድ ሰው ምንድን ነው? ወይስ ትጐበኘው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?» ዕለት ዕለት ጸጋህ ይበዛልን ዘንድ እኛ ማን ነን?

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ሦስት

ክህነት

«ስለዚህ፡ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፡ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ::» ዕብ.3÷1 ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ በዕብራውያን መልእክቱ ያተኮረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉም የሚበልጥ መሆኑን ማስረዳት ነው:: ይህንንም የሚያስረዳው ደግሞ በንጽጽር ነው:: ከነብያት ስለ መብለጡ የእነርሱንና የእርሱን ንግግር በማነጻጸር አስረዳ:: ከዚያም በኋላ ደግሞ ከመላእክት መብለጡን አስረድቷል::

አሁን ደግሞ ከካህናት መብለጡን ለማስረዳት ያመጣል:: ከካህናት መብለጡን ያስረዳባቸው ዐበይት ቁም ነገሮችንም በተከታታይ ይገልጣቸዋል:: እኒህም 1ኛ. በክህነቱ 2ኛ. በመሥዋዕቱ 3ኛ መሥዋዕቱ በቀረበበት ድንኳን ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ሌሎችንም በአስረጅነት ያቀርባል:: አሁን በዚህ ርዕስ የምንመለከተው የክህነቱን መብለጥ ነው:: ሌሎቹን ወደ ፊት ራሳቸውን በማስቻል እንመለከታቸዋለን:: ቅዱስ ጳውሎስ በክህነት ለመብለጡ አስረጅ የደረጋቸውን ብቻ ዕብ.5÷1-10፣ዕብ.6÷20፣ 7÷1-28፣ 8÷1-3 በዚህ ርዕስ ሥር እናያቸዋለን::

1.1 የክህነት ትርጉም

<u>ክህነት:-</u> ተክህነ - አገለገለ፣ ተሾመ፣ ጲቄና፣ ቅስና ተቀበለ፣ ጸለየ፣ መንፈሳዊ ሥልጣን ተቀበለ ከሚለው ግሥ የተገኘ ሲሆን ትርጓሜውም ሹመት፣ አገልግሎት፣ በተቀበሉት ሥልጣን መሥራት ወይንም አገልግሎት መፈጸም ይሆናል:: በአጭሩ ዘይቤያዊ ትርጉሙ አገልግሎት ማለት ሲሆን በምሥጢር ሹመትን

መሠረተን ያመለክታል::

ሹመት የሚለው ቃል መመረጥን መለየትን የሚያመለክት ስለሆነ ክህነት መራጭና በሥርዓተ ሲመት የሚሾም ባለሥልጣን ያለበት የተለየ ሀብት መሆኑን ለመረዳት አያዳግትም:: ክህነት ሰው ለሆነ ሁሉ የሚያድሉት ወይም በተፈጥሮ እንደ ንጹሕ አየር ማንም የሚያገኘው ነገር አይደለም:: ክህነት መንፈሳዊ አገልግሎት ነው፣ ሰውንም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያቀርብ ከእግዚአብሔር የተገኘ ስጦታና ሥልጣን ነው::

አገልግሎት ነው ስንልም ከጸጋ መንፈስ ቅዱስ ወገን አንዱ ነው ማለታችን ነው:: ጸጋ ደግሞ ልዩ ልዩ ነው፣ ለተለያዩ ሰዎችም የተለያየ ጸጋ ይሰጣል፣ በመብት የሚጠየቅ አይደለም:: ጥቅሙ ለካህኑም ሆነ ለምእመኑ እኩል ነው፣ ክብሩ ግን ከኮከብ ኮከብ እንዲበልጥ ከሰውም ሰው እንዲለይ ከሌሎቹ የተለየ ማድረጉ የማይታበል ነው:: እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ብቸኛ ሀብት ነው ማለታችን እንዳልሆነ ግን ሊታወቅ ይገባል:: «የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፣ መንፈስ ግን አንድ ነው፣ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው» 1ኛቆሮ 12÷4፣ 1ኛጴጥ.1÷12::

የክህነት አጀማመሩን ስንመለከት ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ እንደሆነ እንገነዘባለን:: እግዚአብሔር አዳምን ነቢይ፣ ካህን፣ ንጉሥ አድርጐ ሾሞታልና:: ይህም ማለት ከተሰጡት ሰባት ሀብታት አንዱ ሀብተ ክህነት መሆኑን ያስረግጣል:: ከእርሱም በኋላ እስከ ሙሴ ያሉ አበው በበረከተ አበው እየተሾሙ /ዘፍ.48÷11-16፣ ዘጸ.7÷7/ ትንቢትንና ክህነትን ገንዘብ አድርገዋል:: ነብያት እንደ መሆናቸው ኃላፍያትንና መጻዕያትን እያዩ ተናግረ ዋል፣ ካህናትም እንደ መሆናቸው መሥዋዕት ሠውተዋል:: ዘፍ. 8÷20, ዘፍ.22÷13::

www.zeyeneta.com

ይሁን እንጂ ከሀጎቱ በተለያዩ ዘመናት ያሉትንና ራሳቸውን የቻለ ሥርዓት ኑሯቸው በቤተ ክርስቲያን የሚ ታወቁትን በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጡትን ካህናት አራት ዓይነት መልክ አስይዟቸው እንመለከታለን። ከዚህም አንጻር በየራሳቸው እንደሚከተለው እንመለ ከታቸዋለን።

3.2. ከህነተ መልከ ጼዴቅ

3.2.1. መልከ ጼዴቅ ማን ነው?፡-

ስለ መልከ ጼዴቅ ሲነሣ የጥያቄው መሠረት «አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም» /ዕብ7÷3/ የሚለው የቅዱስ ጳውሎስ ንግግር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ያለበትን ምክንያት ወደ ኋላ የምናመጣው ሆኖ ሰው አይደለም አለማለቱን ግን መገንዘብ ይገባል። የሰላም ንጉሥ የዘላለም ካህን የተባለ ከአብርሃም ጋር የተጨዋወተና ከአብርሃም አሥራትን የተቀበለ፣ ለአብርሃምም የሚበላውን የሚጠጣውን ያቀረበ ሰው ነውና። ዘፍ14÷21፣ዕብ.7÷9–10። ሰው አይደለም የሚል ማስረጃ ማቅረብ የሚቻለውም የለም።

ይሁን እንጂ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያናችን መጻሕፍት በብዙ መጻሕፍትና በሊቃውንቱ ከሚነገረው የመልከ ጼዴቅ የካም ዘርነት /ካማዊነት/ ሌላ ሴማዊም ነው ሲሉ ይገኛሉ። ለምሳሌ እንደ ስንክሳር ዘጳጉሜ 3 ቀን፣ ቀሌምንጦስና ገድለ አዳም ያሉት። ልዩነትን የሚያመለክት ግን አይደለም። ምክንያቱም ሰውን ከዚህ ወገን ብቻ ነው ብሎ መናገር አይቻልም። ለምሳሌ ያህል ጌታችን ከነገደ ይሁዳ ነው ተብሎ ይነገርለት እንጂ የዘር ሐረጉን በቅዱሳት መጻሕፍት ስንመለከት ግን ስንኳንስ ከእስራኤል ወገን ከሆኑት ከአሕ ዛብም ወገን ከሆኑት ከሞዓባያውያኑ ከነሩትና ከነረዓብ ዘር እንዳለው እንረዳለን።

ስለዚህ የሁሉም ሰው የዘር ሐረግ በዝርዝር ሊጻፍ

አይቻልም እንጂ ቢጻፍ አንድን ሰው ከአንድ ወገን ብቻ አድርጉ መናገር አይቻልም፣ ስለሆነም በሚያውቁት መንገድ ከሴም ወገን ነው ማለታቸው የሚያስነቅፍ አይደለም። እኛ ግን በጉላ በተረዳ ነገር በብዙ መጻሕፍትና በትርጓሜ መምህራን የሚታወቅበት የዘር ግንድ /ካማዊውን/ እናስቀምጣለን። ይህንን ጌታችንም አስቀድሞ በነብያት ዘክሮታልና ነው። ሕዝ.16÷1–10። ዘሩን መናገር ያሰፈለ ገው ቅዱስ ጳውሎስ ሰው መሆኑን አስረግጦ የተናገረበትን ምክንያት ለመግለጥ እንጂ የመልከ ጼዴቅ ካማዊነት የሚያጸድቅ ሴማዊነት የ ማያጸድቅ ነው ለማለት አይደለም።

3.2.2. የመልከ ጼዴቅ የዘር ሐረግ፡-

ለመጀመሪያ ጊዜ የአስራኤል እምብርት ወይም ዋና ከተማ ኢየሩሳሌምን ያቀናት ከካም ወገን የሆኑት የምስርና የናባ/ኑብያ/ ንጉሥ የነበረው ሴዱ ነው። ያቀናትም ብቻ ሳይሆን የቆረቆራትም እርሱ ነው። ስለዚህ በሴዱ ቤተ ሳይዳ ተብላለች። ሴዱ ሳሌምን ይወልዳል። ሳሌም ሚልኪንና መልከ ጼዴቅን ይወልዳል። በሳሌም ሳሌም ስትባል ኖራለች። በኋላ ግን መልከ ጼዴቅ ማለት ንጉሠ ጽድቅ ማለት ነውና እርሱ ንጉሠ ሳሌም ተብሎ ከተማዋን ኢየሩ ሳሌም አሰኝቷታል። የሰላም አየር፣ የሰላም ከተማ እንደ ማለት ነው።

አብርሃምን እግዚአብሔር ወደዚህች ከጠራው በኋላና አብርሃም አምስቱ ነገሥተ ኩሎዶጎሞርን ድል ነሥቶ በተመለሰ ጊዜ የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ በዘመኑ የሚፈጸም መሆኑንና አለመሆኑን ለማወቅ ፈቅዶ እግዚአብሔርን ጠይቆ ነበር። ዮሐ. 8÷56። እግዚአብሔር ግን ምሳሌውን መልከ ጼዴቅን ከተሰወረበት ቦታ ሄዶ እንዲመለከት ፈቀደለት፣ አስቀድሞ ለኖኅ ለልጁ ለሴምም÷ ከካም ወገን የተለየ የተባረከ ልጅ እንደሚወለድና አጽመ

www.zeyeneta.com

አዳምን ይጠብቅ ዘንድ ያለው መሆኑን ነግሮት ስለነበር፡ ሴም በታዘዘው መሠረት ከመርከቡ አውጥቶ ሲያስጠብቀው ኖኅ፡ ነበርና፡ በዚህ ጊዜ ግን ተገለጠ፡ ሕዝቡንም ሁሉ ዳኘ። ስለዚህም ነው ንጉሠ ሰላም÷ ንጉሠ ጽድቅ የተባለው።

ይህም ጊዜ ከአብርሃም አንሥቶ እስራኤል ግብጽ እስኪወርዱ ድረስ ያለው 215/ ሁለት መቶ አሥራ አምስት/ ዓመት ነው። ከዚህ በኋላ ግን እስራኤል ስለ መልከ ጼዴቅ ሊያውቁ አይችሉም። ተሰደው በግብፅ ለብዙ ዓመታት ኑረዋልና፡ ሲመለሱ እንኳን ከአርባ ዓመት በላይ እንደ ፈጀባቸው ተገልጿል።

ስለዚህም ነው እግዚአብሔር በተቆጣ ጊዜ ኢየሩሳሌምን የመጀመሪያ ስም የወጣልሽና አቆራቆርሽ ከአብርሃም በፊት በነበሩ የካም ልጅ የከነዓን ወገን ነው፡ እነርሱም ከመጀመሪያ ጣዖትን በምድር ላይ ሠርተው ማምለክ የጀመሩ ናቸው። ይህንም ያደረገውን ሰው በስም ጠርቶ እንዲህ ሲል የገሰጻት። « የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፡– የሰው ልጅ ሆይ÷ ለኢየሩሳሌም ርኵሰትዋን አስታውቃት÷ እንዲህም በል፡– ጌታ እግዚአብሔር ለኢ የሩሳሌም እንዲህ ይላል፡– ዘርሽና ትውልድሽ ከከነዓን ምድር ነው፡ አባትሽ / ጣዖት በማምለክ በግብር የወለደሽ ለማለት / አሞራዊ ነበረ፡ እናትሽም ኬጢያዊት ነበረች።...» ሕዝ.16÷1–14። ከዚህ ቀጥሎ ግብጽ ወርዳ በካማዊ ሥርዓትና አገዛዝ መኖሯን ጨምሮ ይገልጣል። ይህም መልከ ጼዴቅ ከካም ወገን መሆኑን የሚያስረዳ ነው።

በኋላ ዘመንም ማርቆስ ዮናናዊ የተባሉ በግብፅ በምንኩስና ጸንተው የሚኖሩ ሊቅ « መልከ ጼዴቅን ወልደ እግዚአብሔር ነው» የሚሉ መናፍቃን በዘመናቸው ተነሥተው በነበረበት ወቅት የመልከ ጼዴቅን ሰውነትና ሁኔታውን ለማስረዳት የመልስ ጽሑፍ ጽፈው አስረድተዋል። እርሳቸውም የጠቀሱት የዘር ሐረግ ከላይ የተቀመጠ

ውን መሆኑን በመጽሐፈ ፊልክስዩስ ገጽ 39 ላይ ተመዝግቧል። በዳዊትና በወንጌል ትርጓሜም የምንመለከተው ይህንኑ ነው።

3.2.3. ሥርዓተ ሢመተ ክህነቱ ለመልከ ጼዴቅ

ሀ) ክህነቱ፡ – መልከ ጼዴቅን ሙሴ አሮንን በሾመበት ሥርዓት ቅብዕ አፍልቶ፣ መሥዋዕት እንስሳ ሠውቶ፣ ልዩ ልዩ ጎብር ያሳቸውን አልባሳት አልብሶ የሾመው ሰው የለም። ይል ቁንም እግዚአ ብሔር መረጠው÷ በማይታወቅ ግብርም ሾመው እንጂ። መመረጡንና መሾሙንም እግዚአብሔር ለኖኅም ለሴምም ገለጠላቸው። ስለዚህም በታዘዘው መሠረት ሴም መልከ ጼዴቅን ይዞ ከወገኖቹ ማንም ሳያውቅ አጽሙ አዳምን ሊያስጠብቀው ወስዶታል። «ወእምዝ ይቤሉ ሴም ለመልከ ጼዴቅ አንተ ካህኑ ለዓለም፣ ካህኑ ለእግዚአብሔር ዘንረየከ እም ኩሉ ሰብእ ለተቃንዮ ቅድመ ሥጋሁ ለአቡነ አዳም። ሴም መልከ ጼዴቅን በአባታችን በአዳም አጽም/ሥጋ/ ፊት ታገለግለው ዘንድ ከሰው ሁሉ የመረጠህ የዓለም ካህን የእግዚአብሔር ካህን አንተ ነህ አለው።» እንዲል ቀሌምንጦስ።

ከዚህ የተነሣ አሮንና ልጆቹ በሙሴ እጅ፣ ሙሴም በመልአኩ እጅ /ሐዋ.6÷6/ እንደ ተሾሙ መልከ ጼዴቅ በእገሌ ተሾመ አይባልም። ይህ ሥርዓት ሳይፈጸምለት ከእግዚአብሔር ተሹሟልና። ቅዱስ ጳውሎስ « ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል። » ያለው ለዚህ ነው። «ለዘላለም» ማለቱም እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ለማለት ነው። ስለዚህ ክህነቱ ከሌዋውያን ክህነት ፍጹም ልዩ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ « እንግዲህ ሕዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን÷ እንደ አሮን ሹመት የማይቆጠር÷ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሣ ወደ ፊት ስለ ምን ያስፈ

www.zeyeneta.com

ልጋል?» ያለው:: ዕብ.7:11::

ለ) ሥርዓተ ክህነቱ መብሕትውናው

መልከ ጼዴቅ በሴም ብቻ ተጠርቶ አጭሙ እዳሙን ይዘው ወደ ጉልጉታ ከደረሱ በኋላ ሴም አስቀድሞ የእግዚአብሔር ካህን መሆኑን በእግዚአብሔርም ከሰው ሁሉ መመረጡን ከነገረው በኋላ ሥርዓትን ሠርቶበታል:: ሥርዓቱም በክህነቱ መፈጸም ስለሚገባውና በኑሮው ስለሚገልጠው ነው::

1. በክህነቱ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እንዲያመሰግን፣ የእንስሳ መሥዋዕት እንዳይሠዋ፣ ይልቁንም መሥዋዕቱ ከንጹሕ ስንዴና ወይን እንዲሆን በእጁም ደም እንዳያፈስ አዝዞታል::

2. በብሕትውናውም ቦታውን ፈጽሞ እንዳይለቅ፣ከመሬት በላይ ቤት ሠርቶ እንዳይኖር፣ ፀጉሩን እንዳይላጭ፣ ጥፍሩንም እንዳይ ቆርጥ፣ ሚስትም እንዳያገባ፣ ይህን የመሰለ ሥርዓት ሠርቶበታል:: «ወይእዜኒ አእኩቶ ለእግዚአብሔር አምላክከ ዘነረየከ ለክህነት ቅድሜሁ፡ ወኢትትፈለጥ እም ዝንቱ መካን እስከ ለዓለም:: ወኢ ታውስብ ብእሲተ፣ ወኢትላዒ ርእሰከ፣ ወኢትምትር ፅፍረከ፣ ወኢ ትከፀው ደመ፣ ወኢትሕንፅ ቤተ መልዕልተ መካን፣ ወኢትሠዕ መሥዋዕተ ዘእንስሳ፣ ወባሕቱ ይኩን መሥዋዕተከ ቅድመ እግዚ አብሔር ኀብስተ ስንደሌ ንጹሕ ወእምፍሬ ወይን ንጹሕ፣ ወናሁ መልአከ እግዚአብሔር ይሄሉ ምስሌከ እስከ ለዓለም» እንዲል ቀሌምንጦስ::

ስለዚህ በመልአከ እግዚአብሔር እየተረዳ እስከ አብርሃም ድረስ በፍጹም ብሕትውና ለማንም ሳይገለጥ ኑሯል:: ከአብርሃም በኋላ ግን የእርሱ ልጆች የሚኀበኙት ሲጣሉ የሚያስታርቃቸው ንጉሠ ሰላም እንደነበር ተገልጧል:: ለአብነትም ርብቃ ያዕቆብንና ዔሳውን እንደ ጸነሰች ከእርሱ በረከት ለመቀበል በሄደች ጊዜ የሚመጣው ተገልጠለት ታናሹ ያዕቆብ የታላቁ ጌታ እንደሆነ የሚያገለግለው

እግዚአብሔርም የእርሱ ልጅ እንደሚሆን እንደነገራት ከዚሁ በቀሌምንጦስ ተገልጧል:: ዘፍ.14፡18-21፣ ዮሐ.8:56::

3.2.4.. ነገረ መልከ ጼዴቅ በዕብራውያን

ሀ) ትውልዱ:-«አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም.. /ዕብ.7፡3/ ያለውን ብቻ በመጥቀስ አንዳንድ ሰዎች መልደ እግዚ አብሔር ነው ለማለት ይቃጣቸዋል:: ትልቁ ጥያቄ መሆን ያለበት « መልከ ጼዴቅ ሰው ነውን ወይስ ሊላ?» ነው፡ ከዚህ በኋላ የላይኛው ንግግር ግልጽ ይሆናልና:: ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ሰው በተሻለ ሁኔታ በዝርዝር እንደ ጻፈ ማስተዋል ይገባናል:: ስለ ማንነቱም ሲገልጽ «የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አሥራት የሰጠው ይህ ሰው እንዴት ትልቅ እንደ ነበረ አስቢ ተመልከቱ::» ቁ.4 በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የመልከ ጼዴቅን ሰው መሆን አረጋግጧል::

ሰው ከሆነ ደግሞ አባትና እናት የሉትም ሊባል አይችልም:: ታዲያ ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ምን የሉትም አለ? የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት የመልከ ጼዴቅ ዘሩ ከሌዋውያን አይደለም:: ባለመሆኑም ሙሴ አልጻፈለትም ለማለት ነው:: በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 6 ላይ «ትውልዱ ከእነርሱ የማይቆጠረው ግን ከአብርሃም አሥራትን አውጥቷል::» በማለት ትውልዱ ከአብርሃም ወገን የማይቆጠርለት መሆኑን በመግለጽ ራሱ ቅዱስ ጳውሎስ አረጋግጧል:: ቀሌምንጦስም ከእነርሱ ወገን ባለመሆኑ ሙሴ የመልከ ጼዴቅን ዘሩንና ጥንተ ነገሩን አልተናገረውም ሲል « ወኢዘከረ ሙሴ በውስተ አሪት ቀዳሚ መዋዕሊሁ ለመልከ ጼዴቅ» ብሏል::

ለ) ዕድሜ:-አንዳንድ ሰዎች ካሁኑ መልከ ጼዴቅን ወልደ እግዚ አብሔር ነው ለማለት ከሚያቀርቧቸው ማስረጃዎች አንዱ «ለዘመ ኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍጻሜ የለውም::»ቁ.3 የሚለው ነው:: መልከ ጼዴቅን «ሰው» ነው ብለን ጥንትም ፍጻሜም የለውም ማለት

www.zeyeneta.com

አይቻልም። ነገር ግን ጥንቱም ሆነ ፍጻሜው ለሌዋውያን የተገለጠ አይደለም ለማለት ነው። በዚህ መጽሐፍ ጥንቱን ወይም መነሻውን በዘር ሐረጉ ላይ ገልጸናል።

ሙሴ የጻፈው አብርሃም መልከ ጼዴቅን እንደተገናኘው እንጂ የተወለደበትን፣ የመጣበትን አይደለም፣ ፍጻሜውንም አላወቀምና እርሱም ሆነ ሌሎቹ አልገለጡም። ሰው እስከ ሆነ ድረስ ይሞታልና ለምድራዊ ሕይወቱ ፍጻሜ ይኖረዋል። ከአሁን በፊት ሞቷል ማለት ግን አይቻለንም። «በዚህስ የሚሞቱ ሰዎች አሥራትን ያስወጣሉ፤ በዚያ ግን የሚያስወጣ ቢሕይወት እንዲኖር የተመሰከረለት እርሱ ነው።» /ዕብ.7÷8/ ተብሉ ተጽፏልና። በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈው እነሄኖክና ኤልያስን የመሰሉ ነብያት ሞትን ሳያዩ በብሔረ ሕያዋን የተቀመጡ ብዙ ወዳጆች አሉት። ዕብ.11÷5፣ ዘፍ.5÷24፣ 2ኛነገ. 2÷11።

እነዚህ በመጽሐፍ ተጽፈው ለእኛ የተገለጡት ናቸው እንጂ በብሔረ ሕያዋን ያሉት የእግዚአብሔር ወዳጆች እነዚህ ብቻ እንዳልሆኑ መገንዘብ ይገባል። ይሁን እንጂ አይሞቱም አልተባ ለላቸውም፤ ለወልደ እግዚአብሔር ያልቀረ ከሰዎችም ለእናቱ ለድንግል ማርያም ያልቀረ ሞት ለእነርሱ ይቀርላቸዋል አልተባለም። « እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አለው እንጂ አይሞትም አላለውም።» /ዮሐ.21÷23/ እንዲል እስከ ዕለተ ምጽአት ሲኖር ይችላል ማለት ፍጹም አይሞትም ማለት እንዳይደለ የታወቀ የተረዳ ነገር ነውና።

ስለ እነ ኤልያስም ቢሆን « እነሆ÷ ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ሳይመጣ ነቢዩን ኤልያስን እልክላችኋለሁ። መጥቼም ምድርን በእርግማን እንዳልመታ እርሱ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች÷ የልጆችንም ልብ ወደ አባቶች ይመልሳል።» /ሚል.5÷6/ተብሉ ጌታ ለፍርድ ከመምጣቱ በፊት በእንጸረ ኤልያስ

በብሔረ ሕያዋን ያሉት ሁሉ መጥተው የሞት ጽዋ እንደሚቀበሉ ተገልጧል።

ሐ) <u>መልከ ጼዴቅን ማንሣት ስለ ምን አስፈለገ?</u>

ቅዱስ ጳውሎስ በዘርና በትውልድ የሚመኩትን እስራኤል ዘሥጋን የሚያስተምራቸው ስለ ጌታችን ታላቅነትና ፈጣሪነት ሲሆን ለማስታረቅም የእርሱ ከህነት ከሁሉም ትበልጣለች በማለት ነው። እስራኤል የአብርሃምንና የዳዊትን ታላቅነት የሙሴንም ነብይነት የሚያቃልልባቸውን ፈጽመው አይቀበሉም። ይልቁንም የአብርሃም፣ የዳዊትንና የሙሴን ነገር እያነሡ ቢነግሯቸው ያለ ጥርጥር ይቀበላሉ። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ የጌታችንን ታላቅነት በእነዚህ ሰዎች ኑሮ ትምህርትና ታላቅነት ለማስረዳት ነገሩን አምጥቶታል።

ሙሴ ስለ መልከ ጼዴቅና ስለ አብርሃም ግንኙነት ስለ አብርሃም አባትነት ጽፏል። ዘፍ.14÷18÷21። ዳዊትም መልከ ጼዴቅ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ መሆኑን ጠቅሷል። መዝ.109÷4። ቅዱስ ጳውሎስም መጀመሪያ ያስረዳው ከህነተ መልከ ጼዴቅ ከክህነተ ሌዋውያን የሚበልጥ መሆኑን ነው። ይህንንም በዘርፍ በዘርፉ እንደሚከተለው እንመለከተዋለን።

1.<u>በክህነት ይቀድማቸዋል</u>፦በዘፍ.14÷18–21እንደተጻፈው መልከ ጼዴቅ ከአብርሃም በፊት የነበረ ሰው ነው። ክህነቱም እንዲሁ። ምክንያቱም አብርሃምን የባረከው ካህን ስለሆነ ነውና። ዕብ.7÷1። እነርሱ ግን የአብርሃም ልጅ የይስሐቅ ልጅ ያዕቆብ ምድረ ግብፅ ተሰድዶ ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ በሙሴ መሪነት ወጥተው በአሮን አማካኝነት የተቀበሉት ነውና ቢያንስ ከአብርሃም አንሥቶ ያለው እንኳ ቢታሰብ ከ500 ዘመን በላይ ይቀድማቸዋል።

2.<u>ክህነቱ ዘላለማዊ ነው</u>፦ /ዕብ.7÷3/ መልከ ጼዴቅ ወደዚህ ዓለም በልደተ ሥጋ ከተገለጠ በኋላ እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜ መኖርን

www.zeyeneta.com

ከሰማቸው ሰዎች አንዱ ነውና አልሞተም። ስለዚህ እስከሚሞትባት ቀን ድረስ በክህነቱ ይኖራል። ከዚህም የተነሣ ክህነቱ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ አይደለም። የሌዋውያንን ክህነት ከተቀበሉት ከመጀመሪያዎቹ አምስት ሰዎች ግን በናዳብና በአብድዩ ወዲያው ሞት ተጀመረ። ሌሎቹም የሚሞቱ ስለሆኑ ክህነቱ ከልጅ ልጅ የሚተላለፍ ሆነ። « እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው። » ዕብ.7÷23 ተብሎ ተጽፎአልና።

3.<u>ሌዋውያንን አሥራት አስወጥቷል</u> :- ሌዋውያን አሥራትን ከሕዝቡ እንዲቀበሉ ሥርዓት አላቸው። ዘኁ.18÷21። መልከ ጼዴቅ ግን ከአብርሃም አሥራትን በተቀበለ ጊዜ አሥራት ማውጣት ከማይገባቸው ይልቁንም አሥራትን ይቀበሉ ዘንድ ካላቸው ከሌዋውያን ተቀብሏልና እንዲበልጥ ታወቀ ተረዳ። ዕብ.7÷6።

4. <u>ሌዋዊውያንን ባርኳል</u>:- ከሌዊ ወገን የሚሆኑ ካህናት ሕዝቡን ይባርኩ ነበር። «አሮንም እጆቹን ወደ ሕዝቡ ዘረጋ ባረካቸውም።» ዘሌ.9÷22 እንዲል። እነዚህን በረከትን ያድሉ ዘንድ ሀብተ ክህነት የተቀበሉ ሌዋውያንን ግን አስቀድሞ በአባታቸው በአብርሃም በኩል መልከ ጼዴቅ ባርኳቸዋል። ይህንንም ማድረጉ የሚልቅ በመሆኑ ነው ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ገልጦታል።« ትውልዱ ከእነርሱ የማይቆጠረው ግን ከአብርሃም አሥራትን አውጥቷል፣ የተስፋ ቃል የነበረውንም ባርኳል። ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው። » ዕብ.7÷6-7 እንዲል።

5.<u>መሥዋዕቱ የሚሞቱ እንስሳት አይደሉም</u> :- የሌዋውያን መሥዋዕት ከእንስሳት የሚዘጋጅና የሚቀርብ እንደሆነ እናውቃለን። ዕብ.10÷4። መልከ ጼዴቅ ግን በንጹሕ ስንዴና ወይን ያስታኩት ነበር፣ ይህንም መሥዋዕት አድርጉ ያቀርብ ነበር። «ወኢትሠሉ መሥዋዕት ዘእንስሳ፣ ወባሕቱ ይኩን መሥዋዕተከ

ቅድመ እግዚአብሔር ኀብስተ ሰንዳሌ ንጹሕ ወእምፍሬ ወይን ንጹሕ።» እንዳለ ቀሌምንጦስ። ይህም የእርሱ መሥዋዕት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአዲሱ ኪዳን የቆረሰውን ቅዱስ ሥጋውንና ያፈሰሰውን ክቡር ደሙን እንድንቀበልበት የሠራልን ሥርዓት ነው። /ሉቃ.22÷14-20፣ 1ቆሮ.11÷27/። ስለዚህ ከመሥዋዕተ ሌዋውያን መሥዋዕተ መልከ ጼዴቅ ይበልጣል።

ቅዱስ ጳውሎስ ሁሉንም በዚህ ምዕራፍ አጠቃልሎ እንዳስቀመጠው ከህነተ መልከ ጼዴቅ ከህነተ ሌዋውያንን ይበልጣል። የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክህነት ደግሞ ከመልከ ጼዴቅ ክህነት ይበልጣል። መልከ ጼዴቅ ለጌታችን አምሳል ነበርና።

ስለዚህ የቅዱስ ጳውሎስ ንግግር አባታችሁ አብርሃም አብርሃማዊ ካልሆነው ከመልከ ጼዴቅ የሚያንስ ከሆነ ይልቁንም ከመልከ ጼዴቅ አምላክ ከክርስቶስማ እንዴት አያንስም፣ የመልከ ጼዴቅ ክህነት ከእናንተ ከተሻለ ይልቁን የጌታማ እንዴታ፣ መሥዋዕታችሁ ከመልከ ጼዴቅ ካነሰ ይልቁን እንዴት ከጌታ ትበልጣላችሁ፣ ለመልከ ጼዴቅ አሥራት ካወጣችሁ ለጌታማ እንዴት አብዝታችሁ ማድረግ አይገባችሁ፣ በመልከ ጼዴቅ ከተባረካችሁ ይልቁንም መስጠትና መንሳት ለእርሱ ብቻ ከሚቻለው ከወልደ እግዚአብሔርማ እንዴት አብልጣችሁ መጠቀም ይገባችኋል ለማለት ተናገረው። ዓላማውም የጌታን ታላቅነትና የባሕርይ አምላክነት በመመስከር ልቆ ከሚልቁት እነርሱንም ያላቃቸው እርሱ መሆኑንና ይህ ሥልጣን እንዳለው ለማስታወቅ ነበር።

3.3. የብሉይ ኪዳን ክህነት /ክህነተ ሌዋውያን/ : -

ብሉይ ኪዳን ማለት የመጀመሪያ፣ የጥንት ወይም የቀደመ ውል ስምምነት ማለት ነው። የብሉይ ኪዳን ካህናት ስንል ደግሞ በዚያ

www.zeyeneta.com

ውል መሠረት አገልግሎት ለመፈጸም የተመረጡና አስፈላጊው ሥርዓት ተፈጽሞላቸው የተቀቡትን ሰዎች ማለታችን ነው። ከዘነቱ ደግሞ በውስጥ መሠረት የሚሰጠው የሚፈጸመው አገልግሎት ነው።

የመጀመሪያ ወይም የተድሞ ውል ወይም ስምምነት የምን ለሙም እግዚአብሔር እስራኤልን በሙሴ አማካኝነት እየመራ ነጻ ካወጣቸው በኋላ በዚያው በሙሴ አማካኝነት መገለጡን፣ የእርሱን አምላክነትና እርሱ ስለ አባቶቻቸው ስለ አብርሃም ስለ ይስሐቅ ስለ ያዕቆብ ሲል ሕጉን ቢጠብቁ ትእዛዙንም ቢፈጽሙ የሚያደርግላቸውን ይህ ባይሆን የሚያደርግባቸውን ገልጠ የተነጋገሩት የተገባቡት ውል ነው። ከቃለ እግዚአብሔር፡ ከወልደ እግዚአብሔር በሥጋ መገለጥ በፊት በመደረጉም ብሉይ «የተድሞ» የሚል ስም ተሰጥቶታል። ስለዚህ አገልግሎትና አገልጋዮች በመጠኑ እንመለከታለን።

3.3.1. ክህነቱ ምን ዓይነት ነበር?

ሀ/ ለአንድ ነገድ ብቻ የተሰጠ ነበር፡- የብሉይ ኪዳን ክህነት ለአንድ ነገድ ለሌዊ ብቻ የተሰጠ ነበር። ጥንቱን ስንመለከት እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ነጻ ለማውጣት በወደደ ጊዜ ኃይሉን የሚገልጥበት ሰው ያስፈልገው ነበር። በጊዜውም ሙሴ ዓላማውን ግብጻዊውን በመግደል፡ታማኝነቱንም የዮቶርን በጉች በመጠበቅ አስመስክሮ ስለ ነበረ ተመራ።እግዚአብሔርም በመልአኩ እጅ በቁጥ ቋጠው ሥር ሾመው። ዘጸ.3÷1፣ ሐዋ.7÷35።

ይሁን እንጂ ሙሴ አፈ ኮልታፋ ነኝ በማለቱ እግዚአብሔር ቢቆጣም ይራዳው ዘንድ የተመረጠው ወንድሙ አሮን ነበር። ዘጸ.4÷10–17። በኋላ መመረጡ ለልጆቹም ተፈቀደ። «በክህነትም ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ቅባቸው ቀድሳቸውም።» ዘጸ. 30÷30 እንዲል። ከዚህም በኋላ ክህነቱ የእነ አሮን ቤት ለሆነው ነገድ ተሰጠ። «እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡-

የሌዊን ነገድ አቅርበህ ያገለግሉት ዘንድ በካህኑ በአሮን ፊት አቁማቸው። የማደሪያውንም ሥራ ይሠሩ ዘንድ እርሱንና ማኅበሩን ሁሉ ለማገልገል የሚያስፈልገውን ነገር በመገናኛው ድንኳን ፊት ይጠብቁ።» ዘኁ.3÷5–7። ይልቁንም እሥራኤል በሰጢም በአመነዘሩበት ወቅት እግዚአብሔር ሕዝቡን በመቅሰፍት መትቶ 24,000 የሚሆኑ ሰዎች አልቀው ነበር።

በዚህ ወቅት መንፈሰ ዝሙት ልቡናውን ያዘነጋውና ሐፍረቱ የጠፋበት አንድ ጉልማሳ በቀን አንዲት ምድያማዊትን እንደ ምርኮ እየጐተተ አምጥቶ በድንኳኑ ውስጥ ይዞ ገባ። ሕዝቡ በሁኔታው በሚያለቅሱበት ወቅት በአምልኮተ እግዚአብሔር ልቡናው የተቃጠለው የአሮን የልጅ ልጅ ፊንሐስ ጦር ነጥቆ ሄደና ሁለቱንም በአንድ ጦር ወግቶ ገደላቸው። እግዚአብሔርም በቅንዓቱ ደስ አለው፡ መቅሰፍቱንም አራቀ፡ የክህነቱን ቃል ኪዳን ለቤቱ አጠናለት።

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- የካህኑ የአሮን ልጅ የአልዓዛር ልጅ ፊንሐስ በቅንዓቱ በመካከላቸው ቀንቷልና ቁጣዬን ከእሥራኤል ልጆች መለሰ፡ እኔም የእሥራኤልን ልጆች በቅንዓቴ አላጠፋሁም። ስለዚህ እነሆ የሰላሜን ቃል ኪዳን እሰጠዋለሁ። ለእርሱም ቀንቷልና፣ ለእሥራኤልም ልጆች አስተስርዮአልና ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ለዘላለም ክህነት ቃል ኪዳን ይሆንለታል።» /ዘኁ.25÷10–13/ ሲል በቃል ኪዳን አሳትሞታል።

ለ/ ምሉዕ አልነበረም፡- ክህነት ከእግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ የአገልግሎት ሹመት ነው። የክህነት ሥልጣንም በኃጢአት÷ በበደልና በመተላለፍ ላይ ነው። የብሉይ ኪዳን ክህነት ኃጢአትን የሚያስተሠርይ ቢሆንም ሊያስተሠርየው ያልቻለው የማይቻለውም ኃጢአት ነበር። ይህም ኃጢአት በዘር የሚተላለፍና ራሳቸው ካህናቱም ከዚህ ኃጢአት ያልነጹ ነበሩ። ኃጢአቱም ጥንተ አብሶ

www.zeyeneta.com

/የአዳም የመጀመርያው በደል/ የሚባለው ነው። «ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፣ እንደዚ ሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ።» ሮሜ.5÷12 እንዲል። ይህ ኃጢአት በአዳም ምክንያት ወደ ሰው ሁሉ ደረሰ፣ ኃጢአቱ ስለ ደረሰም ሞቱም ለሰው ሁሉ ደረሰ፣ ለሁሉም የደረሰው ደግሞ ከጊዜያችን በፊት ይህን ኃጢአት ሊያስተሠርይ የሚችል ሥልጣን ስላልተሰጠ ነበር። «ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ÷ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ።» ሮሜ.5÷14 እንዲል።

ስለዚህም ይህ ከህነት ጊዜያዊና አፍዐዊ የዕለት ተዕለት የሰው ልጆችን ሥጋዊ ነውርንና ኃጢአትን እንጂ ጥንተ አብሶን ለመደምሰስ የሚችል ምሉዕ አልነበረም። «እንግዲህ ሕዝቡ በሌዊ ከህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልና፣ በዚያ ከህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን÷ እንደ አሮን ሹመት የማይቆጠር፣ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሣ ወደፊት ስለ ምን ያስፈ ልጋል?» ዕብ.7÷11 ተብሉ እንደ ተጻፈ ሌላ ከህነትን ገንዘብ ያደረገ አዲስ ካህን እንደሚያስፈልግ እያመለከተ አለፈ።

ሐ/ ጊዜያዊ ነበር፦ ይህን ከህነት የሚቀበሉት ሰዎች ሟቾች ነበሩ። ስለዚህም ምንም እንኳን አገልግሎቱ መቀጠል ስለ ነበረበት አንዱ ሲሞት ሌላው እየተተካ እስከ ዘመነ ሥጋዌ ቢዘልቅም ከህነቱ በጊዜ የተወሰነ ነበር። አንድ ካህን «ካህን» ተብሉ የሚጠራው ከተሾመ በኋላ ነው። ይህም በታወቀ ጊዜ የሚሰጠው መሆኑን ያመለክታል። እስካልተሻረ ድረስ የሚያገለግል ቢሆንም እንኳ በሞቱ ከህነቱ አለፈ አይባልም፣ ሌላው በሕይወት ያለ ሊዋዊ ካህን መሆን ይቻለዋልና። ስለዚህ ከህነቱ ለሰዎች በጊዜ የተወሰነ ስለ ነበር ብዙ ሰዎች አስፈልገውታል። «እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው

ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው።» ዕብ.7÷23 እንዲል።

መ/ ፍጹም አልነበረም፦ ከህነቱ ፍጹም አልነበረም ስንል፦ ተሿሚዎቹ ላይ ፍጹምነት አለመኖሩን ለማመልከት ነው። በአንዱ በአዳም ምክንያት ሁሉም በኃጢአቱ ተይዘዋልና ፍጹማን አይደሉም። ስለዚህ ፍጹም ከህነት ሊሰጣቸው አይችልም። ለእነርሱም የሚያስፈልጋቸው አለና። «ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢ አት መብወንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው ተመርጦ ለእግዚአ ብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና፣ እርሱ ራሱም ደግሞ ድካምን ስለሚለብስ፣ ላልተማሩትና ለሚስቱት ሊራራላቸው ይችላል።» ዕብ.5÷1–2 እንዳለ ካህኑ ድካም ኃጢአት የሚስማማው ነው።

ስለዚህ ከጥንተ አብሶም በላይ ራሱ ኃጢአትን ሊሠራ ይችላል። ከዚህም የተነሣ ፍጹምነት ያለው ሰው ገንዘብ ሊያደርጋት የሚገባ ፍጹም ከህነትን ለመቀበል ፍጹም ሰውም አስፈለገን። «ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጉ ይሾማልና፣ ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነውን ልጅ ይሾማል።» ዕብ.7÷28 እንዲል።

3.3.2. የብሉይ ኪዳን ከህነት ተቀባይ ምን መሆን ይጠበቅበታል?

ከህነቱ ለአንድ ወገን /ነገድ/ የተሰጠ፣ ጊዜያዊ፣ ጉዶሉና ፍጹምነት የሌለው ቢሆንም እንኳ እንደ ፈለጉ የሚናኙት፣ በል ማድም የሚተላለፍ፣ ለማድ የለሾችም የሚገባ አልነበረም። ከተቀበሉት በኋላ እንኳ ያቀለሉት ፍጹም ቅጣት ተቀጥተዋል። ለአብነት ያህልም ልዩ ለሆነው አገልግሎት ያልታዘዙትን ናዳብንና አብድዩን /ዘሌ.10÷5/ እንዲሁም አፍኒንና ፊንሐስን ማስታወስ ይቻላል። 1ኛሳሙ.3÷1–4፣22። ስለዚህ የከህነቱ ተቀባይ የነበረ ሰው

www.zeyeneta.com

የሚጠበቅበት እንዳለ እንረዳለን::

ሀ/ <u>እግዚአብሔር የጠራው መሆን አለበት:-</u> «አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ከእሥራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ» ዘጸ.28+1 ተብሎ እንደ ተጻፈ ክህነት የሚቀበለው ሰው የተመረጠና የተጠራ መሆን ይጠበቅበታል::

እግዚአብሔርም ለዚህ አገልግሎት ነገደ ሌዊን እንደ መረጠ ወይም እንደ ጠራ ከላይ ተመልክተናል:: ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ «እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም::» /ዕብ.5+4/ በማለት ማንም ሊሰጠው እንደ ማይችል አስረግጧል:: አንዳንድ ሰዎች በማን አለብኝነትና በድፍረት /ከአገልግሎቱ ታላቅነት የተነሣ/ ለመሳተፍ ፈልገው ነበር:: ነገር ግን እግዚአብሔር አጠፋቸው፣ በጽኑ አቀጣጥም ቀጣቸው:: ዘኍ.16+1-50፣ 2ኛዜና.26+16-23::

ለ/ <u>ሙሉ የሰውነት አካላት ያሉት መሆን አለበት:-</u> እግዚአብሔር ለአገልግሎት መጀመሪያ የጠራው ሰው ሙሴ ነበረ:: ሙሴ አፈ ኩልታፋ መሆኑን እግዚአብሔር ያውቅ ነበር:: ሙሴ ግን አንደበቴ ኩልታፋ ነኝና አይገባኝም ብሎ ስለ ተከራከረ እግዚአብሔር ተቆጣ:: ዘጸ.4+15:: ስለዚህም ክህነቱን አንደበተ ርቱዕ ወደ ሆነው ወደ አሮን አሻገራት:: እርግጥ የክህነት አገልግሎት ሙሉ አካላት ለሌሉት የማይቻል ቢሆንም ይልቁንም የሙሴ እግዚአብሔርን መከራከር ለንዑሳን ጉደሉዎች ሁሉ ክህነትን ያስከለከለ ይመስላል:: ምክንያቱም ከሙሴ አንደበተ ኩልታፋነት አያንሱምና::

ሲከለክልም «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው:- ለአሮን እንዲህ ብለህ ንገረው:- ከዘርህ ከትውልዳቸው ነውር ያለበት ሰው ሁሉ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ

አይቅረብ:: ሰውር፣ ወይም አንካሳ፣ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፣ ወይም ትርፍ አካል ያለው ወይም እግሩ ሰባራ፣ ወይም እጁ ሰባራ፣ ወይም ጉባጣ፣ ወይም ድንክ፣ ወይም ዓይኑ መጭማጫ ወይም እከካም፣ ወይም ቋቁቻም፣ ወይም ጃንደረባ፣ ነውረኛ ሁሉ አይቅረብ::... ነገር ግን ነውረኛ ነውና መቅደሶቼን እንዳያረክስ ወደ መጋረጃው አይግባ፣ ወደ መሠዊያውም አይቅረብ:: የምቀድሳቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝ:: ሙሴም ይህን ለአሮን፣ ለልጆቹም፣ ለእሥራኤልም ልጆች ሁሉ ነገረ::» ዘሌ.21+16-24:: ስለዚህም ሙሉ አካል ያላቸው ነውር የሌለባቸው መሆን ይጠበቅባቸው ነበር::

ሐ/ <u>ርኅራኄ ያለው መሆን ይጠበቅበታል:-</u>

ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ.5+3 ላይ «እርሱም ራሱ ደግሞ ድካሙን ስለሚለብስ ስለ ተማሩትና ለሚስቱት ሊራራላቸው ይችላል» በማለት ለምን ርኅራኄ እንደሚያስፈልገው ገልጿል:: ራሱ ኃጢአት ማድረግ የሚስማማው ሰው ስለሆነ፣ ስለሚበድልም ለሚበድሉት ሊራራላቸው ይገባል:: ይልቁንም የካህን አስፈላጊነቱ ለሥርየተ ኃጢአት ነውና ርኅራኄ የሌለው ከሆነ የበደሉትን ከእግዚአብሔር ማስታረቅ አይቻለውም:: እነ ቆሬ፣ ዳታንና አቤሮን በበደሉ ጊዜ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያጠፋ ፈልጉ ሙሴንና አሮንን ፈቀቅ በሉ አላቸው:: እነርሱ ግን ርኅራኄን ገንዘብ አድርገዋልና በአንድ ሰው በደል ሕዝቡን እንዳያጠፋ ለመኑት፣ እግዚአብሔርም ሕዝቡን ከማጥፋት ታገሠ:: ዘኍ.16+20-22::

ይህም እግዚአብሔር ያጠፋውን ስለማያውቅ እነርሱ የሚነግሩት ሆኖ አይደለም፣ ይልቁንም የካህናትን ርኅራኄ ለመግለጥ የተደረገ ነው እንጂ:: በሌላም ጊዜ እሥራኤል እግዚአብሔርን ስለ በደሉ እነርሱን ሳጥፋ እንተንም በታላቅ ሕዝብ ላይ አለቃ ላድርግህ አለው:: ሙሴ ግን ሕዝቡን ከምታጠፋ፣ የእኔን ስም ከሕይወት መጽሐፍ ብትደመስስ ይሻለኛል በማለት ለመነ፣ እግዚአብሔርም

www.zeyeneta.com

የሙሴን ነፍስ እስከ መስጠት ድረስ ያለውን ርኅራኄ ተመልክቶ መቅሰፍቱን አቀለለ። ዘጸ.32+30–34። ስለዚህ ካህናቱ ርኅራኄ ከሌላቸው ተያይዞ መጥፋት ሊመጣ እንደሚችል መገንዘብ ይገባናል።

መ/ <u>መሸምድ አለበት</u>:– የብሉይ ኪዳን ክህነት ምንም እንኳን ለአንድ ነገድ የተሰጠ፣ ሰውየውም ሙሉ አካልና ርኅራኄ ያለው ቢ ሆንም ሥርዓተ ሚመት እስካልተፈጸመለት ድረስ ግን ካህን ሊሆን አይችልም።

እግዚአብሔር አሮንን ለሙሴ ረዳትነት ከጠራውና አሥራ ኤልም ከግብጽ ከወጡ በኋላ ሥርዓተ ደብተራ አሪት ሲሰጠው አንዱ ሥርዓት አገልጋዮቿ ካህናት መሾም አለባቸው የሚል ነው። «በክህነት ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ትባቸው ቀድሳቸውም።» ዘጸ.30+30 ተብሉ እንደ ተጻፈ በትብዐ ቅዱስ የሚከብሩ ነበሩ።«...ይህንም ሁሉ ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን ታስብባቸዋለህ፣ ትከናቸዋለህ፣ ትቀድሳቸውማለህ።» ዘጸ.28+41 እንዲል። ስንኪን ካህናቱ ነገሥታቱም ሳይቀቡ /ሥርዓተ ንግሥ/ ሳይፈጸምላቸው ለዙፋን አይበቁም ነበር።

ሠ/ <u>በንጽሕና በቅድስና ማገልገል አለበት</u>:– ክህነት የንጽሕና የቅድስና አገልግሎት ነው። ስንኪን ውሳጣዊ ቅድስና አፍዐዊ /ውጫዊ/ ቅድስናም በእጅጉ ያስፈልገዋል። ከላይ እንደተገለጸው እግዚአብሔር ሙሉ አካል የሌላቸውን ከአገልግሎቱ መከልከሉ ተልዕኮውን መፈጸም አይቻላቸውም በሚል ብቻ ሳይሆን ሌሎቹ የተቀበሉት /ሙሉ አካላት ያላቸው/ እንደ ተርታ ነገር እንዳ ያቀልሉትና ለውሳጣዊ ንጽሕናም የተጉ እንዲሆኑ ነው።

ይኸውም ይታወቅ ዘንድ አሥራኤል ከሞዓባውያን ጋር በማመንዘርና ለጣዖታቱም የተሠዋውን መሥዋዕት በመብላት እግዚ አብሔርን ባሳዘኑበት ወቅት፣ ዓይነ ልቡናው በመንፈሰ ዝሙት ጠፍ

ቶበት ሃፍረትና ፍርሃት አጥቶ ወደ ድንኳኑ ምድያማዊቷን ይዞ መጥቶ የተኛውን ሰው በቅንዓት መንፈሳዊ ቀንቶ ጦሩን ነጥቆ አንድ ላይ እንደ ተኝ ወግቶ የገደላቸውን ፊንሐስን እግዚአብሔር ክህነትን ለዘላለም አጽንቶለታል። ዘኍ.25+10–13። ለፊንሐስና ለቤቱ ክህነት ለዘላለም ሆኖ የተሰጠበት ዐቢይ ምሥጢር እግዚአብሔር ስለ ንጽሕና የሚቀናን ሰው ለዚህ አገልግሎት የመረጡ ምሥጢር በመሆኑ ነው።

ምክንያቱም ሌሎቹ ኃጣውእ /ኃጢአቶች/ የሚሠሩት አብዛኛውን ጊዜ በሦስተኛ አካል /በመጣሪያ/ ይሆናል። ዝሙትን የሚፈጽም ሰው ግን የሚበድለው በሰውነቱ ነው። «ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፣ ዝሙትን የሚ ሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።» 1ኛቆሮ.6+18 ተብሏልና። ዝሙት እግዚአብሔርን «ሰውን በመፍጠሩ ተጸጸተ» /ዘፍ.6÷6/ ተብሉ እስኪጻፍ ድረስ ያሳዘነ በደል ነው። አዳም በበደለ ጊዜ እንኳን እግዚአብሔር ተጸጸተ ተብሉ አልተጻፈም።

ለዚህም ነው በዘመነ ኖኅ ምድርና ነዋሪዎቿ በሙሉ በንፍር ውኃ በኋላም ሰዶምና ገሞራ በእሳት ዲን የተቀጡት፣ መንግሥተ እሥራኤል ከሁለት የተከፈለው፣ ሶምሶን ጸጋውን ያጣው በዝሙት ምክንያት ነው። ይልቁንም ካህኑ በንጽሕና ካላገለገለ ቅጣቱም የከበደ እንደሆነ በእነ አፍኒንና ፊንሐስ ታውቋል። ከእነርሱ አልፎ ሕዝቡ ይልቁንም የአምላክ እሥራኤል መገለጫው ታቦተ ጽዮን ሁሉ ለመ ማረክ በቅታለችና። 1ኛሳሙ.3+1–4፣ 22።

ረ/ ትእዛዘ እግዚአብሔርን /ሥርዓቱን/ ሳያቃልል ማገልገል አለበት:–

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔርን በአምላክነቱ ማወቅ ለተመ ረጡበት አገልግሎት ራስን ብቻ ዐዋቂ ኅአድርጉ እንደ መውሰድ

www.zeyeneta.com

የሚታይበት ጊዜ አለ። በእግዚአብሔር ቤት ግን ብቁ የምታደርገው በትጋትና የምትፈጸም የመታዘዝ አገልግሎት ናት እንጂ ሰውተትና መለማመድ አይደለም። ይልቁንም ደግሞ በእግዚ አብሔር ቤት የሚያገለግሉ ካህናት መታዘዛቸውን ቸል ብለው በሰ ውቀታቸው ተመሥርተው ሥርዓተ ቤቱን ሲያቃልሉበት እግዚአ ብሔር ብድራታቸውን እንደሚመልስ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ።

ለአብነትም ውሉደ አሮን ናዳብና አብዩድ መሥዋዕተ እግዚ አብሔርን ለመሠዋት የሚያስፈልገውን ፍሕም አፍመው ማቅረብን ቸል ባሉ ጊዜ በእሳት ተበልተው ሞተዋል። «የአሮንም ልጆች ናዳብና አብዩድ በየራሳቸው ጥናውን ወስደው እሳት አደረጉበት፣ በላዩም ዕጣን አኖሩበት፣ በእግዚአብሔርም ፊት እርሱ ያላዘዛቸውን ሌላ እሳት አቀረቡ። እሳትም ከእግዚአብሔር ፊት ወጥቶ በላቸው፣ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ።» ዘሌ.10÷1-2።

እግዚአብሔር ናዳብንና አብዩድን የቀጣቸው እነርሱ ያመጡት እሳት ዕጣን ማቅለጥ ስለማይችል፣ ወይም ገንዘብነቱ የእግዚአብሔር ካልሆነ ፍጥረት የተገኘ ሆኖ አይደለም። ትእዛዙን ስላልፈጸሙ ብቻ ነው፣ እግዚአብሔር በቀደሰው ይቀደሳልና፣ ቸል የሚሉትን ደግሞ ቸል ይላቸዋልና። ስለ ሞቱት ወንድሞቻቸው እንዳያለቅሱ ታዘዙ፣ እነርሱም የእግዚአብሔርን ቅባት ተቀብተዋልና፣ ስለዚህ እንደ ሙሴ ትእዛዝ ሳይወጡና ወንድሞቻቸውን ሳይቀብሩ ቀርተዋል። ዘሌ.10÷6-7። ፡ለዚህ ካህናቱ ለቤተ መቅደስ ሥርዓት ፈጽመው መታዘዝ ይገባቸዋል። ከተሰጧቸው ትእዛዛት መካከል ጥቂቶቹን ለመመልከት ያህል፦

- የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ ጠጥቶ አለመግባት /ዘሌ.10÷9/
- ወደ መገናኛው ድንኳን ከመግባት በፊት እጅና እግርን መታጠብ /ዘጸ.40÷32፣ ዘጸ.30÷17-21/፣
- ንዋያተ ቅድሳቱን በድንኳኑ ውስጥ በሚገባቸው ቦታ ማስቀመጥ /ዘጸ.40÷17-29/፣
- አዳዲስ ንዋያትን በተቀደሰው ዘይትና በጸሉት ማከበር /ዘጸ.40÷9-11/፣
- የከበሩ አልባሳትን /ልብሰ ተክህኖ/ በመልበስ ማገልገል /ዘሌ.8÷6-9/፣

ይህን የመሰሉትን መጠበቅና እንደ ሥርዓቱ መሥዋዕትን ማቅረብ ይጠበቅበታል።

3.3.3. የብሉይ ኪዳን ካህናት አገልግሎት ምንድን ነው?

«እንደገና በእሥራኤል ልጆች ላይ ቁጣ እንዳይሆንባቸው እናንተ መቅደሱንና መሠዊያውን ጠብቁ። እኔም እነሆ+ ሌዋውያን ወንድሞ ቻችሁን ከእሥራኤል ልጆች ራሳቸውን ወስጃለሁ+ የመገናኛውን ድን ኳን አገልግሎት ያደርጉ ዘንድ ለእግዚአብሔር የተሰጡ ለእናንተ ስጦታ ናቸው።» ዘኍ.18÷5-6 እንዲል ካህናቱ የመጀመሪያው አገልግሎታቸው ይህንኑ በቤተ መቅደስ የሚፈጸመውን አገልግሎት መወጣት ነው። አገልግሎቱም በየዕለቱ፣ በየሳምንቱና፣ በየዓመቱ የሚፈጸም እንደ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ።

በየዕለቱ የሚፈጸሙት ሦስት ናቸው። የቅድስቱን መብራት በቀዳማይ ሰዓተ ሌሊት አብርቶ በቀዳማይ ሰዓተ መዓልት ማጥፋት፣ ይኸውም እግዚአብሔር በብርሃን ብቻ የሚመለክ አምላክ መሆኑን ለማመልከት ነው። ዘጸ.25÷31-40። ሁለተኛው በየዕለቱ በተፈቀደው ቦታ ፍሕም አፍሞ የዕጣን መሥዋዕት ማቅረብ ሲሆን /ዘሌ. 16÷12-13/ ሦስተኛው ደግሞ በየዕለቱ የሚቀርቡ ሁለት ጠቦቶችን አንዱን ሧት ሁለተኛውን ቍርባ ማቅረብ ነበር። ዘጸ.29÷38።

www.zeyeneta.com

በየሳምንቱ የሚፈጸመው አገልግሎት ደግሞ አሥራ ሁለት ኅብስቶችን ጋግሮ ስድስት ስድስቱን በሁለት ተርታ አድርጉ በእግዚ አብሔር ፊት በገበታው ላይ ማስቀመጥ ነበር። ይህ ዘላለማዊ ሥርዓት ሆኖ ተሰጥቷቸዋል። ዘጸ.25÷23-30፣ ዘሌ.24÷5-9።

ሦስተኛውና የመጨረሻው የቤተ መቅደስ አገልግሎት ደግሞ በዓመት አንድ ጊዜ የሚፈጸም ሲሆን ይኸውም የሥርየተ ኃጢአት መሥዋዕትን ማቅረብ ነው። የሚፈጸምበትም ቀን የማስተሥርያ ቀን ሲባል ሥርዓቱም ለየት ያለ ነው። ሊቀ ካህናቱ የሚፈጽመው ከመሆኑ በላይ የመሳርጎ ልብሱን አውልቆ ሌላ ልብስ በመልበስ የሚ ፈጽመውና ኃጢአትንና በደልንም የሚሸከም ፍየል ወደ ምድረ በዳ የሚለቀበት ሥርዓት ነው። ዘሌ.16÷23፣ ዘጸ.30÷10። መሥዋዕቱ የሚቀርብበት ቦታም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ነበር።

ለ/ ሕግን ለሕዝቡ ማስተማር፦

ከመጀመሪያው ሰው ከሙሴ ጀምሮ እግዚአብሔር ያዘዘውን ለሕ ዝቡ መናገር ይጠበቅባቸዋል። ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ትእዛዝ ሁሉ እንዲፈጽሙ ሕጉንም እንዲጠብቁ ይነግራቸው ነበር። የሚበላውንና እንስሳ የማይበላውን፣ በዓል የሚያደርጉበትን ቀንና ወደ መኖኛው ድንኳን ሲመጡ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ይነግራ ቸው ያስተምራቸው ነበር። ዘጸ.14÷1፣ 27÷26። ከዚህም በኋላ ያሉ ካህናት ይህንኑ አገልግሎት ይፈጽሙ ነበር።2ኛዜና.15÷1-3።

አገልግሎቱን ቸል የሚሉትን ካህናት ደግሞ እግዚአብሔር ይወቅሳቸው ይቀጣቸውም ነበር። «ከሰባቱም ቀን በኋላ የእግዚአ ብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፦ የሰው ልጅ ሆይ፥ ለእሥ ራኤል ቤት ጠባቂ አድርጌሃለሁ፣ ስለዚህ የአፌን ቃል ስማ፣ ከእኔም ዘንድ አስጠንቅቃቸው። እኔ ኃጢአተኛውን፦ በእርግጥ ትሞታለህ ባልሁት ጊዜ፥ አንተም ባታስጠነቅቀው ነፍሱም እንድትድን ከክፉ

መንገድ ይመለስ ዘንድ ለኃጢአተኛው አስጠንቅቀህ ባትነግረው፣ ኃጢአተኛ በኃጢአት ይሞታል ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ።» ይላልና። ሕዝ.3÷18።

ሐ/ በአሮምና በቱሚም /በሰባኤ/

ፈቃደ እግዚአብሔርን መጠየቅ፦

ኡሪምና ቱሚም ከድንጋይ የሚቀረጹና በአንደኛው የሰድስቱ ነገደ እሥራኤል በሌላው ላይ ደግሞ የቀሩት የሰድስቱ ነገደ እሥራ ኤል ስም የተጻፈባቸው የመታሰቢያ ንዋያት ሲሆኑ አገልግሎት የሚፈጸምባቸውም ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሲፈለግ ጸሎቱን የሚያደርሰው ካህን በሚለብሰው ኤፉድ /ቀሚስ/ ላይ ባሉት የደረት ኪሶች በመክተት ነበር። ዘጸ.28÷30፣ ዘዳ.33÷8። በዚህ ሥርዓት መሠረት ኢያሱ በሙሴ እንዲተካ በዚሁ ሥርዓት እግዚአብሔር ተጠይቋል። ዘኍ.27÷18-23። ዳዊትም ፈቃደ እግዚአብሔርን እየጠ የቀ መልስ ከእግዚአብሔር ያገኝ እንደ ነበር ተጽፏል። 1ኛሳሙ.23÷6-12።

መ/ በግሌት እግዚአብሔርን ማመስገን፦

ግሌተ እግዚአብሔር አሁን እኛ አገር ባለው በያሬዳዊ ዜማ ባይሆንም እንኳ የተጀመረው ጥንት ነው። እስራኤል ከግብጽ እንደ ወጡ ሲያመሰግኑ እንመለከታለንና። ዘጸ.15÷1። ታቦተ ጽዮን ከምርኮ ከተመለሰች በኋላ የበለጠ ተጠናክሮ የሚሰጥ አገልግሎት እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። ይልቁንም ቅዱስ ዳዊት ብዙዎች ካህናትን ለተለያየ አገልግሎት መድቦ አገልግሎቱን ያስፈጽም ነበር። በዚህም መሠረት መለከት እየነፉ፣ በመሰንቆ፣ በበገናና በጸናጽል ይዘምሩ ነበር። 1ኛዜና.15÷6 ለአያንዳንዱም አገልግሎት ቅዱስ ዳዊት ሰዎችን መድቦ እንደነበር ተጽፏል። 1ኛዜና.15÷37 አገልግ

www.zeyeneta.com

ሉቱም ከዚህ በኋላ የካህናቱ አገልግሉት ሆኖ ቀጠለ። «ይህንንም ትእዛዝ እግዚአብሔር በነቢያቱ እጅ አዝዟልና እንደ ዳዊትና እንደ ንጉሡ ባለ ራእይ እንደ ጋድ፣ እንደ ነብዩም እንደ ናታን ትእዛዝ ጸናጽልና በገና መሰንቆም አስይዞ ሌዋውያንን በእግዚአብሔር ቤት አቆመ። ሌዋያንም የዳዊትን የዜማ እቃ ይዘው፣ ካህናቱም መለከቱን ይዘው ቆመው ነበር። ሕዝቅያስም የሚቃጠለውን መሥዋዕት በመሠዊያ ላይ ያሳርጉ ዘንድ አዘዘ፣ የሚቃጠለውም መሥዋዕት ማረግ በተጀመረ ጊዜ የእግዚአብሔር መዝሙር ደግሞ ተጀመረ፣ መለከቱም ተነፉ፣ የእሥራኤልም ንጉሥ ዳዊት የዜማ ዕቃ ተመታ። ጉባኤውም ሁሉ ሰገዱ፥ መዘምራኑም ዘመሩ፣ መለከተኞችም ነፉ፣ የሚቃጠለው መሥዋዕት እስኪፈጸም ድረስ ይህ ሁሉ ሆነ። ማቅረቡንም በፈጸሙ ጊዜ ንጉሡና ከእርሱ ጋር የነበሩ ሁሉ አጐነበሱ፣ ሰገዱም። ንጉሡም ሕዝቅያስና አለቆቹ ሌዋውያንን በዳዊትና በባለ ራእዩ በአሳፍ ቃል እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ዘንድ አዘዙ። በደስታም አመሰገኑ፣ አጐነበሱም ሰገዱም።» 2ኛዜና.29÷25–30።

ካህናቱን ይህን በመሰሉትና በአንዳንድ የሕዝቡ ማኅበራዊ ሕይወትም እየቀረቡ ያገለግሉ ነበር። ዘሌ.1÷2።

3.3.4. ሥርዓተ ሚሙቱ /የአሟሟታቸው ሥርዓት/ ምን ይመስል ነበር?

ከላይ ካሁኑ ምን መሆን ይጠበቅበታል በሚለው ርእስ ሥር መሾም እንደሚጠበቅበት ተመልክተናል። ታዲያ እንዴት ይሾሙ ነበር? በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን እንመለከታለን።

እግዚአብሔር በመጀመሪያ «በከህንትም ያገለግሉኝ ዘንድ አሮንንና ልጆቹን ቅባቸው ቀድሳቸውም።» ዘጸ.30÷30 ሲል አዘዘ። ቅብዐቱንም እንዴት እንደሚያዘጋጇው አስተምሮት ነበር። ዘጸ.30÷22–25። ከዚህ አገልግሉት ውጪም ማንም እንዳይጠቀምበት

ታዘዘ፡ ቅባቱ የተለየ የተቀደሰ ስለሆነ። «አንተም ለእሥራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ተናገር፡- ይህ ለልጅ ልጆችህ የተቀደሰ የቅብዐት ዘይት ይሁንልኝ። በሰው ሥጋ ላይ አይፍሰስ፣ እንደ እርሱም የተሠራ ሌላ ቅብዐት አታድርጉ ቅዱስ ነው፣ ለእናንተም ቅዱስ ይሁን። እንደ እርሱ ያለውን የሚያደርግ ሰው በሌላም ሰው ላይ የሚያፈሰሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።» ዘጸ.30÷31–32 እንዲል።

በዚህ ሥርዓትና ትእዛዝ መሠረት የሚቀቡት ዘይትም ሳይቀር የተለየ ሆነ። ሥርዓተ ሚመቱም እንደሚከተለው ነበር።

ሀ/ በመጀመርያ ገላቸውን መታጠብ አለባቸው።

ለ/ አስፈላጊ የሆኑትን አልባሳተ ከህነት ማልበስ /መጀመሪያ የለበሰው አሮን ብቻ ነበር። «ሙሴም አሮንንና ልጆቹን አቀረበ፣በውኃም አጠባቸው። ሸሚዝም አለበሰው፥ በመታጠቂያም አስታጠቀው፣ ቀሚስም አለበሰው፣ ኤፉድም ደረበለት፣ በብልሃትም በተጠለፈ ጽድ አስታጠቀውና በእርሱ ላይ አሠረው። የደረት ኪስ በእርሱ ላይ አደረገ፣ በደረቱ ኪስም ውስጥ ኡሪምንና ቱሪምን አኖረበት። እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው በራሱ ላይ መጠምጠሚያውን አደረገ፣ በመጠምጠሚያውም ላይ በፊቱ በኩል የተቀደሰውን አክሊል፣ ቅጠል የሚመስለውን የወርቅ ምልክት አደረገ።» ዘሌ.8÷6–9። ከዚህም በኋላ የአሮንን ልጆች አለበሳቸው። ዘሌ.8÷13።

ሐ/ ንዋያተ ቅድሳቱን ሁሉ በተቀደሰው ዘይቱ ማከበር። ዘሌ. 8÷10–13።

መ/ በኃጢአቱ መሥዋዕት፣ በሚቃጠለውም መሥዋዕት እጆቻቸውን መጫን፣ እንስሳቱንም ማረድ። እንደ ሥርዓቱም በቅደም ተከተል ማቅረብ። ከዚህ በኋላ ለሦስተኛ ጊዜ በሚቀርበው ለቅድስና በሚቀርበው የበግ መሥዋዕት ላይ፥ እጆቻቸውን ይጭናሉ። በጉም ይሠዋል። ከደሙም የቀኝ ጆሯቸው ጫፍ፣ የቀኝ እጅ አውራ

www.zeyeneta.com

ጣት፣ የቀኝ እግር አውራ ጣት በደሙ ይቀባሉ /እንዲነካቸው ይደረጋል።/ የዚህም በግ ስቡንና ላቱን፣ ቀኝ ወርቹንም፣ በእግዚ አብሔር ፊት ካለው የእንጀራ ሌማትም አንድ የቂጣ እንጉቻ፣ አንድ የዘይት እንጀራ አንድ ስስ ቂጣ ይወስዳል። እነዚህን ስድስቱን በእንድነት በተኟሚዎቹ ላይ ይወዘውዛል፣ ለእግዚአብሔርም የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጉ ያቀርባል። ዘሌ.8÷14–29።

ሠ/ ከዚህ በኋላ ተኟሚዎቹ የለበሷቸውን አልባሳት በተቀደሰው ዘይትና ከመሠዊያው ደም አምጥቶ ያፈሰባቸዋል÷ ይቀድሳቸውማል። ሰዎቹንም ይቀድሳል። ዘሌ.8÷30።

ረ/ ከዚህ በኋላ የተረፈውን ሥጋ ቀቅለው ይበላሉ፣ የተረፈውንም በእሳት ያቃጥላሉ። ዘሌ.8÷31።

ሰ/ በመጨረሻም እግዚአብሔር ይከናቸዋል፣ ከህጎታቸውም ለሰባት ተከታታይ ቀናት ስለሆነ ሰባቱ ቀናት እስኪፈጸሙ ድረስ በሌሊትም በመዓልትም በመገናኛው ድንኳን ይቀመጣሉ። ዘሌ.8÷33–36። ሥርዓተ ሢመቱ ከምሉዕ በክፍሉ ይህን ይመስላል። ሥርዓተ ሢመ ቱን በተመለከተ ተጨማሪ ማስረጃ ካስፈለገ በዘጸ.29÷1–37 ይመልከቱ።

3.3.5.<u>ያሹመቱ ደረጃ</u>

የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አገልግሎት ስንመለከተው ዘርፈ ብዙ ነው። አገልግሎቱ የሚፈጸምባቸው ቦታዎችም ይለዩ እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል። ለአብነትም ያህል መዝሙሩ የሚዘመርበት ቦታ፣ ዕለታዊና ሳምንታዊ መሥዋዕት የሚሠዋበት ቦታ እንዲሁም በዓመት አንድ ጊዜ የሚቀርበው መሥዋዕት የሚ ሠዋበት ቦታ ይለያያሉ። የቦታዎቹ መለያየት ደግሞ እግዚአብሔር ከሰጣቸው ቅድስና አንጻር መሆኑን እንመለከታለን። ከዚህም የተነሣ ወደ የቦታዎቹ የሚገቡት ሰዎች የተገባቸው ብቻ ነበሩ። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በሹመት የሚበላለጡ እንደ ነበር ለመረዳት

አያዳግትም፣ ከዚህ አንጻር በጊዜው የነበረውን በሦስት ከፍለን እንመለከተዋለን።

ሀ/ <u>መዘምር</u>:– እነዚህ ሰዎች መሥዋዕቱ ከሚቀርብበት ከመገናኛው ድንኳን በስተውጭ ሆነው በመሥዋዕቱ ጊዜ እግዚአ ብሔርን በመዝሙር የሚያመሰግኑ ናቸው። ምንም እንኳን እሥራ ኤል ከግብፅ በወጡ ጊዜ ሁሉም በአንድነት ቢዘምሩም በኋላ ግን ለሌዋውያን ብቻ የተሰጠ አገልግሎት እንደ ሆነ እንመለከታለን። 1ኛዜና.15÷6። አገልግሎቱን የሚፈጽሙትም በነብያቱና በቅዱስ ዳዊት ትእዛዝ መሠረት በቤተ መቅደስ የምስጋና አገልግሎት የተፈ ቀዱትን ንዋያት በመጠቀም ነበር፣ መለከት መንፋት ግን የካህናቱ ብቻ እንደነበር ይታያል። 2ኛዜና.29÷28–29።

ይህን አገልግሎት ለመፈጸም ከካህናቱ ውጭ የሆኑት ሰዎች ሌዋውያን ብቻ መሆናቸው ቤቱ አንድ ጊዜ ለዚህ አገልግሎት የተመረጠና የተቀባ በመሆኑ የሹመት ደረጃን ያመለክታል። 2ኛዜና 29÷25–30፣ 1ኛዜና.10÷1–ፍጻሜ።

ለ. <u>ካህናት</u>:– ካህናት ከላይ በሥርዓተ ሢመት ላይ እንደተ መለከትነው ሌዋውያን ቢሆኑም ማሟላት የሚጠበቅባቸውን አሟል ተው በሥርዓት የሚሾሙና የተፈቀደላቸውን አገልግሎት የሚፈጽ ሙት ናቸው። ለነዚህ ሰዎች የግድ ሥርዓተ ሢመት ያስፈልጋቸ ዋል። ይህ ሳይፈጸምላቸው ወደ መገናኛው ድንኳን መግባትም ሆነ አገልግሎት መፈጸም አይቻላቸውም። አገልግሎታቸውም ከላይ በተጠቀሰው መንገድ ሊቀ ካህናቱን በመርዳት ማገልገል ነበር። ዘሌ.10÷1፣ ዘሌ.9÷1–24።

ሐ/ <u>ሊቀ ካህናት</u>:– ሊቀ ካህናት የሚባለውን መዓርግ ስንመለከት እግዚአብሔር ከመጀመሪያዎቹ ካህናት ጀምሮ የለየው ሰው እንደ ነበር እንረዳለን። ከቅዱሳት መጻሕፍት እንደምንረዳው

www.zeyeneta.com

የመጀመሪያዎቹ ካህናት አሮንና ልጆቹ ናዳብ፣ አብዩድ፣ አልዓዛርና ኢታምር ነበሩ። እነዚህን አምስቱን የጠራ እግዚአብሔር ነው፣ የሾመ ደግሞ ሙሴ ነው። ሥርዓተ ሢመቱን ስንመለከት ለአሮን የተለየ ነገር እንዳለ እንመለከታለን። ይኸም አሮን አልባሳቱን የለበሰው ንዋያተ ቅድሳቱ ከመከበራቸው በፊት ሲሆን ልጆቹ ግን ንዋያቱ ከከበሩ በኋላ ነው።

ዳግመኛም ለቅድስና የተሠዋውን በግ ደም የቀኝ ጆሮዎቻቸውን ጫፍና፣ የቀኝ እጆቻቸውንና የቀኝ እግሮቻቸውን ሲያስነካ ለአሮን መጀመሪያ መደረጉን ይገልጣል። ስለ ልጆቹ ግን አሮንንና ልጆቹን ይላል እንጂ ግን ከግን እንደ ቀደመ አለመጻፉ የአሮንን ልዩ መሆን ያስረዳል። ይህም የሹመት ሁሉ መጀመሪያ ነበርና። ከዚህም በላይ አሮን የእነሙሴ ሁሉ ታላቅ፣ በኩር ነበር፣ ይኸም ከእግዚአብሔር ልዩ ሀብት አስገኝቶለታልና የመጀመሪያው ሊቀ ካህን እንዲሆን አድርጉታል። ዘሌ.8÷1–36፣ ዘሌ.21÷10 ፣ ዘኍ.35÷25።

አገልግሎቱን ከጀመሩም በኋላ በዓመት አንድ ጊዜ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የሚቀርበውን የሥርየት መሥዋዕት ያቀርብ የነበረው አሮን እንደነበር ተጽፏል። ዘሌ.16÷1–34። በሚፈጸመው አገልግሎት ሁሉ ልጆቹ ገብተው ይራዱ ነበር እንጂ መሥዋዕቱን በቀዳሚነት ያቀረበው አሮን ነበር። እግዚአብሔርም «ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው»... እየተባለ በተደጋጋሚ መጻፉም አሮን ከሌሎቹ ካህናት እንደ ተመረጠ ያጠይቃል። ዘሌ. 11÷1፣ ዘሌ.13÷1።

ከጊዜ በኋላ ግን የሌዋውያን ዘር እየበዛ በመጣ ቁጥር የካህናቱም ቁጥር እየበዛ መጥቷል። ከብዛታቸውም የተነሣ አገልግሎቱን ተካፍለው እንዲፈጽሙ ተደረገ። «በመጨረሻውም በዳዊት ትእዛዝ ከሃያ ዓመት ዕድሜ ጀምሮ ከዚያም በላይ ያሉት የሌዊ ልጆች ተቆጠሩ። ሥራቸውም የእግዚአብሔርን ቤት በየአደባባዩና በየጓዳው ውስጥ ለማገልገል፣ ቅዱሱንም ዕቃ ሁሉ ለማንጻት፣ የእግዚ

አብሔርንም ቤት አገልግሎት ለመሥራት ከአሮን ልጆች እጅ በታች ነበረ።» 1ኛዜና.23÷27–28 እንዲል አገልግሎቱን ሊዋውያን ሁሉ ይሳተፉበት እንጂ አለቅነቱ ግን ለአሮን ብቻ እንደ ተሰጠ እንመል ከታለን።

ይልቁንም የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ በእሳት ተበልተው ዘር ሳይተኩ ስለ ሞቱ አለቅነቱ በአልዓዛርና በኢታምር በኩል ወርዷል። «ዳዊትም ከአልዓዛር ልጆች ከሳዶቅ ጋር፣ ከኢታምርም ልጆች ከአቢሜሌክ ጋር ሆኖ እንደ አገልግሎታቸው ሥርዓት ከፍሉ መደባቸው። የአልዓዛርም ልጆች አለቆች በልጠው ተገኙ፣ እንዲሁም ተመደቡ፣ ከአልዓዛር ልጆች እንደ አባቶቻቸው ቤቶች አሥራ ለድስት፣ ከኢታምርም ልጆች እንደ አባቶቻቸው ቤቶች ስምንት አለቆች ነበሩ። ከአልዓዛርና ከኢታምርም ልጆች መካከል የመቅደሱና የእግዚአብሔር አለቆች ነበሩና እነዚህና እነዚያ እንዲህ በዕጣ ተመደቡ። ከሌዋውያንም ወገን የነበረው የናትናኤል ልጅ ጸሐፊው ሸማያ በንጉሡና በአለቆቹ ፊት፣ በካህኑ በሳዶቅና በአብያትርም ልጅ በአቢሜሌክ ፊት፣ በካህናቱና በሌዋውያኑ አባቶች ቤቶች አለቆች ፊት ጻፋቸው፣ አንዱንም የአባት ቤት ለአልዓዛር፣ አንዱንም ለኢታምር ጻፈ። 1ኛዜና.24÷1–6 እንዲል አለቅነቱ የአሮን ልጆች ለሆኑት ለሁለቱ ቤት እንደ ጸና እንመለከታለን።

በዚህ ዘመን ቅዱስ ዳዊት የቤተ መቅደሱን አገልግሎት፣ ጥቢቃውንና የአገሪቱንም አስተዳደር ሁሉ ልዩ ሥርዓት እንዳስያዘው መገንዘብ ያስፈልጋል። እያንዳንዱንም ነገር በሥርዓትና በመልካም አመራር እንዲተዳደር አድርጓል። ከላይ እንደተጠቀሰው ለቤተ መቅደሱ ዕቃ ዕቃ ቤተ አሮንን ሲደለድል ሃያ አራቱ አገልጋዮች ከታመቁ በኋላ አገልግሎታቸውንም በተራ እንዲፈጽሙ ዕጣ አጣጥ ሏቸዋል። 1ኛዜና.24÷7–9። ከዚህ በኋላ በሁለቱ ቤት ካሉ አለቆች

www.zeyeneta.com

ዋና /ሊቀ ካህን/ እንደ ነበራቸው ተጽፏል። «ከላዶትም ወገን የሆነ ዋነኛው ካህን አዛርያስ...» እንዲል 2ኛዜና.31÷10። በ2ኛነገ.12÷11 ላይና በ2ኛ ነገ.23÷4 ላይ በስሙ ሊቀ ካህናት ተብሎ ተጠርቷል።

ከዚህ አንጻር ሹመቱና ስሙ እየጐላ የመጣው ወደ ኋላ መሆኑን በእግዚአብሔር የተለየው ግን ቀድሞ ከአሮን ጀምሮ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን፣ ይኸውም ቅድስተ ቅዱሳንን ከተለዩ የተለየች ብሎ እንደመረጠው ከካህናትም ሊቀ ካህናት መምረጡ እንዳች ምሥጢር እንዳለው ያመለክተናል። ዘሁ.13÷22፣ ሐጌ.1÷1፣ ዘካ.3÷1 ተመልከት።

3.3.6. <u>የሊቀ ካህናቱ ልዩ አገልግሎት ምን ነበር?</u>

እግዚአብሔር መገለጫው የሚሆነውን የመገናኛውን ድንኳን በሰማይ እንዳለው አድርጉ እንዲሠራ ለሙሴ አዘዞታል፣ «በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ» ዘጸ.25÷40 በማለትም አስጠንቅቆታል። ሙሴም በታዘዘው መሠረት ተከሏታል። የተለየች የተመረጠች አድርጉ ሠርታታል፣ ከዚህችም ደግሞ ከተለዩ የተለየች ቅድስተ ቅዱሳንን እጅግ አልቋታል አክብሯታል። በውስጧም የሚቀመጡት እጅግ የከበሩ ንዋያት ነበሩ፣ ጽላቱና ማደሪያው ታቦቱ፣ የበቀለችው የአሮን በትር፣... የመሳሰሉት ነገሮች ይገኙበታል። ወደ እርሷም የገቡና በዚያ የተሠዋ መሥዋዕት ሁሉ ቅዱሰ ቅዱሳን ይሆናል። ዘሌ.10÷12ና17።

ስለዚህ ወደዚች ከተለዩ ወደ ተለየች ቦታ ዘወትር መግባትም የተከለከለ ነበር፣ «በእግዚአብሔር ፊት የቀረቡና የሞቱ ሁለቱ የአሮን ልጆች ከሞቱ በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ተናገረው፣ እግዚአብሔርም ሙሴን አለው እኔ በሥርየቱ መክደኛ ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመጋረጃው ውስጥ በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ሥርየቱ መክደኛ ወደ ተቀደሰው ሥፍራ

ሁልጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው።» ዘሌ.16÷1-2 እንዲል። ስለዚህ ወደዚህ የሚያስፈራ የእግዚአብሔር መገለጫ በዓመት አንድ ጊዜ ስለ ራሱ፣ ስለ ካህናቱና ስለ ሕዝቡ ኃጢአት የስርየት መሥዋዕት ለማቅረብ የሚገባው ሰው፡ ከሰው ከተለዩት ከካህናትም የተለየ መሆን ነበረበት፡ በጊዜው ይህን የሚያደርገው አሮን ነበር። ከዚህ በኋላም በልጅ ልጅ እየተተካ እንዲሄድ ታዝዟል። ዘሌ. 16÷32።

ይህን መሥዋዕት በሚያቀርብበትም ወቅት ልብሰ ተክህኖውን አውልቆ በትጎትና በመቅደሱ ውስጥ ገላውን ታጥቦ ነበር። ስለዚህ ዋናውና የመጀመሪያው የሊቀ ካህናቱ ሥራ በዓመት አንድ ጊዜ የሚቀርበውን የሥርየት ኃጢአት መሥዋዕት ስለ ራሱም፣ ስለ ካህናቱም፣ ስለ ሕዝቡም ማቅረብ ነበር። ዘሌ. 16÷23–34።

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን በሌዋውያኑ መብዛት ምክንያት አገልግሎቱ በዝቶ ነበር፣ ሕዝቡም ለእግዚአብሔር ቤት የሚያመጡት ስጦታ ብዙ ስለ ነበር ቤተ መዛግብት ሁሉ ተሠርቶ ነበር። ከዚህ የተነሣ ከዳዊት ዘመን ጀምሮ ለሁሉም የሥራ መደብ ተሰጥቷቸው ተራ ገብተው ያገለግሉ ነበር። በዚህ መሠረት ሊቀ ካህናቱ ቤተ መቅደሱን ማስተዳደርና በየዘርፉ የተመደቡ ካህናትን መቆጣጠር እንዲሁም በሽንጉዎች ላይ ሊቀ መንበር በመሆን ሕዝቡንና እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር። 2ኛነገ.12÷7፣ 1ኛ ሳሙ.3÷11–14፣ 2ኛ ነገ.22÷4፣ 2ኛዜና 31÷10–14፣ ማቴ.26÷56–65።

3.4. <u>ክህነተ አሮን</u>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነው። የነቢያት ሳኪ፣ በመላእክትም የሚመሰገን፣ ፍጥረትን ሁሉ በየወገኑ የፈጠረ ፍጹም አምላክ ነው።

www.zeyeneta.com

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ፣ የቅድስት ድንግል ንጽሕት ማርያምም የበኩር ልጅ፣ ብኩርና ገንዘቡ የሆነ፣ በተዋሕዶ የከበረ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው።

ሰው እንደ መሆኑም ከኃጢአት በቀር የሰውን ሥራ ሁሉ ሠርቷል። ከዚህም የተነሣ ፍጹም ካህን ሆኖ ፍጹም አገልግሎትን ሰጥቷል። ከሀገቱ የሰው ልጆች ከተቀበሉት ክህነት ጋር የሚነጻጸር አይደለም፣ ፍጹም የተለየ ነውና። ይህንንም እንደሚከተለው እናየዋለን።

3.4.1. የጌታችንን ክህነት ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው?

ሀ) የባሕርይው ስለሆነ፡- ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁሉንም ነገር ያደረገው በሥልጣኑ ነው። ሙታንን ያስነሣው፣ ድውያንን የፈወሰው፣ ያስተማረው፣ የሞተው፣ የተነሣው፣ ነገው... በሥልጣኑ እንደሆነ ቀደም ብለን ገልጠነዋል። የጌታችን የክህነት አገልግሎት ዋናው ራሱን መሥዋዕት አድርጉ ማቅረቡ ነው። ጌታችን ራሱን መሥዋዕት አድርጉ አቀረበ ስንል በመስቀል ላይ የፈጸመልንን አገልግሎት ነው። ይኸውም ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ነፍሱን ከሦ ዓለሙን የመቀደስና የማንጻት ሞትንና የሞትን አበጋዝ ዲያብሉስን በሞቱ ድል መንሣት ነው።

ይህ የጌታችን ሞት ነው ከእርሱ ለእኛ የተደረገልን የክህነት አገልግሎት። ሞቱ ደግሞ በሥልጣኑ እንደሆነ በምዕራፍ አንድ ላይ ተብራርቷል። በሥልጣኑ ፈጸመው ማለት ደግሞ ክህነቱ የባሕርይው መሆኑን ለመግለጥ ነው። ከማንም አልተቀበለውም፣ ማንም ከእርሱ ሊወስድበትም አይቻለውም። ይህም ማለት ባሕርየ መለኮቱ ባሕርየ ትስብእቱን በተዋሕዶ አከበረው፣ እንጂ ሌላ የሚሰጠው እርሱም የተቀበለበት የለም። ስለዚህ እርሱ እንደ መልከ ጼዴቅ በሥውር፣ እንደ አሮን በገሃድ የተሾመ አይደለም፣ እርሱ ሰጭ እንጂ ተቀባይ አይደለምና። ሁሉ በእርሱ ሆነ። ዮሐ.1÷3 እንዲል።

«እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም። ነገር ግን፡- አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ያለው እርሱ ነው።» ዕብ.5÷5 ሲል የቃልን በሥጋ መወለድ ሐዋርያው ተናግሯል። ይህም በእርሱ ፈቃድ ብቻ ሳይሆን በአባቱም ፈቃድ መሆኑን ለመናገር ነው።

ለ/ ዘላለማዊ ነው፡- ዘላለም የሚለው ቃል ለፍጡርና ለፈጣሪ ሲቀጸል አንድ ዓይነት ትርጉም የለውም። ለፍጡር ሲሆን የመጨረሻው ጽንፍ ፍጥረት በምድር ላይ እስካለ ድረስ የሚል ትርጉም ይኖረዋል። ለምሳሌ ያህል «እግዚአብሔርም አለው በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ፣ ለዘላለምም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይህን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ፣ ዓይኖቼና ልቤም በዘመን ሁሉ በዚያ ይሆናሉ።» 1ኛነገ.9÷3 ሲል ለዘላለም ያለው እስከ ዕለተ ምጽአት ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ «ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ አይቀርም» ማቴ.24÷2 እንደ ተባለ ቤተ መቅደሱ ብቻውን ሳይሆን ይህች ዓለም መሠረትና ድጓን ግሏን ግላንግሏን ይዛ ታልፋለች።

የመልከ ጼዴቅ ክህነትም ዘላለማዊነት እርሱ በሞተ ሥጋ እስኪለይ ድረስ ብቻ ነው። ዘላለም ለእግዚአብሔር ሲቀጸል ግን በዘመን የሚገደብ መነሻና መድረሻ ያለው አይደለም። ከዚህ የተነሣ የእርሱን ክህነት በዘመን የምንወስናት አይደለችም። በእርግጥ በእርሱ ክህነት ሰው የተጠቀመበት ጊዜ መነሻ አለው፣ ዓመተ ምሕረት እንዲሉ። የእርሱ ክህነት ዘላለማዊነቷ እርሱ ሽረትና ሞት የሌለበት አምላክ ስለሆነ ነው። ባሥጋ ሞተ የምንለው እንኳን ነፍሱ ከሥጋው ተለየች ለማለት እንጂ መለኮትና ትስብእት ተለያዩ ለማለት አይደለም።

ስለዚህ ለክህነቱ ተቀባይ ኢያስፈልገውም፣ የባሕርይ

www.zeyeneta.com

ከሰትንም ከእርሱ በተር ገንዘብ ሊያደርገው የሚቻለው የለምና። «እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው።» ዕብ.7÷24 ተብሉ ተጽፏልና።

ሐ/ ፍጹም ነው፦ የሌዋውያን ክህነት ፍጹም አይደለም፤ የመልከ ጼዴቅም ዘላለማዊ /በእንጻር/ እንጂ ፍጹም አልነበረም። ማንንም ወደ ግዜት መመለስ አላስቻላቸውምና፤ እነርሱም ራሳቸው በኢፃም የመጀመሪያ ኃጢአት ተይዘዋልና። «እርሱ ራሱ ደግሞ ድካምን ስለሚለብስ» /ዕብ.7÷28፣ ዕብ.5÷2/ ተብሉላቸዋልና ለእርሱ ግን ኃጢአት የለበትም ተብሏል። 1ኛዮሐ.3÷5። ከዚህ የተነሣ ክህነታቸው ፍጹም አይደለም። በመሆኑም ዕለት ዕለት ወደ ቤተ መቅደስ እየገቡ የሚሞት መሥዋዕት ማቅረብ ግድ ሆነባቸው። ዕብ.9÷6–7።

እርሱ ግን ክህነቱ ፍጹም መሥዋዕቱም ሕያው ስለሆነ ዕለት ዕለት መሥዋዕት ማቅረብ አላስፈለገውም። «እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም። ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና።» /ዕብ.7÷26/ እንዳለ አንድ ጊዜ ባቀረበው መሥዋዕት ለዘላለም አንጽቶን ሊኖር ይቻለዋልና። «እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና።» ቆላ. 1÷19–20 እንዲል። ስለዚህ የጌታችን ክህነቱ ፍጹም ነውና ከሌሎቹ ሁሉ የተለየ ነው።

3.4.2.የጌታችን ክህነት በመልከ ጼዴቅ ክህነት ስለ ምን ተመሰለ?

«የነገር ጥላ አለውና» /ዕብ.10÷1/ እንደ ተባለ ለሰው ሬቂቁን በግዙፉ፤ የሚይታየውን በማታየው መስሉ መናገርና ማስረዳት የተለመደ ነው። ይልቁንም እኛ የሰው ልጆች የማይመረመረውንና ከጎሊናት ሁሉ በላይ የሆነውን እግዚአብሔርን መረዳት የቻልነው በምሳሌ ነበር፤ በኋላም ሥጋው ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ አብዛኛውን ጊዜ በምሳሌ አስተምሮናል፤ በምሳሌ የተናገራቸውንም ተርጉሞልናል። ማቴ.13÷35።

ከዚህም አንጻር በመጀመሪያ መልከ ጼዴቅ የወለደ እግዚአብሔር ምሳሌው እንጂ ራሱ እንዳልሆነ እርግጠኛ መሆን ይገባል። ለጌታችን ምሳሌ ሆኖ የተረበም እርሱ ብቻ አይደለም። ዮናስ ለጌታችን ምሳሌ ሆኖ ተጠትሏል። ማቴ.16÷4። ሙሴ በምድረ በዳ የሰቀለው እባብ /ዮሐ.3÷14/፤ ሙሴ ውኃን ያፈለቀበት ዐለት /1ኛቆሮ.10÷1/፤ እነዚህን የመሰሉ ሌሎች ምሳሌዎችም አሉት። እነዚህ ሁሉ ግን ጌታችን ከሠራቸው ሥራዎች አንዱን ለማስረዳት ብቻ የሚቀርቡ እንጂ ስንኪንስ ጌታችንን ሊሆኑ ከተመሰሉለት ዐቢይ ነገር በሌላ የማይቀራረቡ እንደሆነ የታወቀ የተረዳ ነው። ስለዚህ የመልከ ጼዴቅ ምሳሌነትም ከላይ ከጠቀስናቸው ውስጥ የሚመደብና በእነኚያ ምሳሌዎች መተንተን ሊገለጥ የማይቻለውን የጌታን ክህነት ጉዳይ ለማስረዳት የተሻለ ስለሆነ ነው። ምሳሌነቱ እንዴት ነው?

– የመልከ ጼዴቅ አባትና እናት በዕብራውያን ዘንድ አይታወቅም፥ በሌዋውያን መጻሕፍት አልተጻፈምና ጌታም ለቀዳማዊ ልደቱ እናት ለድኃራዊ ልደቱ አባት የለውምና።

– መልከ ጼዴቅ በስንዴ በወይን ያስታኩት ነበር፤ ጌታም ቅዱስ ሥጋውን በስንዴ ክቡር ደሙን ቢወይን አድርጎ ሰጥቶናልና።

www.zeyeneta.com

ማቴ.26÷27·29።.

መልከ ጼዴቅ በዘሀ ጊዜ ተገኝ በዘሀ ጊዜም አለፈ አይባልም፣ ጌታም በዘሀ ጊዜ ተገኝ በዘሀ ጊዜም ያልፋል አይባልም። ዳን.7÷14፣ ዮሐ.12÷34። ለመንግሥቱ ሽረት ለዘመኑም ሕልፈት የለበትም።

– መልከ ጼዴቅ ከቤተ ሌዊ ሳይመለድ ከነገደ ካም ሆኖ ክህነትን ገንዘብ አድርጓል። ጌታም ከነገደ ሌዊ ሳይሆን ከነገደ ይሁዳ ተወልዶ ክህነትን ገንዘቡ አድርጓል። ዕብ.5÷6፣ 6÷20፣ 7÷21።

– መልከ ጼዴቅ ክህነቱን ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበለው ቢታመንም በሌዋውያን ሥርዓት ግን አልተሾመም። ይልቁንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሀብታትን የሚያድል እንጂ የሚቀበል ባለመሆኑ ሌላውን የሚቀባ እንጂ እርሱ በማንም የማይቀባ በመሆኑ ክህነቱን በሰው ሥርዓት ተቀብቶ ወይንም በእንብርቶ እድ /እጅን በመጫን/ በንፍሐተ መንፈስ ቅዱስ አልተቀበላትም። የባሕርይው ናትና። ይህ የመልከ ጼዴቅ ክህነት በሌዋዊ ሥርዓት አለመሆኑና ዘላለማዊ መሆኑ ለጌታችን የባሕርዩ ክህነት የተሻለ ቅርበት ስላለው ምሳሌው ለመሆን በቅቷል። የጌታችን ምሳሌ እንዲሆንም እርሱ ራሱ ያበቃው መሆኑን በወንጌል ገልጦታል። ዮሐ.8÷56።

3.4.3 ጌታችን ስለምን ሊቀ ካህናት ተባለ?

ከላይ በመልከ ጼዴቅ እንደተመሰለ አሁን ደግሞ በአሪት ሊቀ ካህናት ተመስሏል። ስለ ምን ? ስለ ጌታችን ክህነት የመልከ ጼዴቅ ምሳሌነት ያልገለጠው ነገር አለ። ይኸውም አገልግሎቱ ነው። ጌታችንም ሊቀ ካህናቱን ምሳሌ ያደረገው ከዚህ አገልግሎቱና ከአለቅነቱ አንጻር ነው። በዝርዝር እንመልከተው፦

ሀ. ሊቀ ካህናት ከሰው ተመርጦ ስለሰው ይሾማል

ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢአት መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው ተመርጠ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና፣» ዕብ.5÷1 እንዲል። ሊቀ ካህናት ሰው ነው፣ ከሰው ይመረጣልና የሚሾመውም ለሰው እንጂ ለራሱ ክብር አይደለም። ዘጸ.28÷1፣ዘሌ.8÷1። ሊቀ ካህናቱም /ዋናው ካህን/ እንዲሁ በእግዚአብሔር ዘንድ የታወቀ የተለየ ነው። «እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም፣» ዕብ. 5÷1፣ዘኍ.35÷25። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ፍጹም አምላክ ሲሆን ፍጹም ሰውም ነው። የአብርሃም ልጅ፣የዳዊት ልጅ ተብሏልና። ማቴ.1÷1። የድንግል ማርያምም የበኩር ልጅ ነውና። ማቴ.1÷25። ራሱም ራሱን «የሰው ልጅ ወልደ እጓለ እመሕያው» /ዕብ.7÷27/ እያለ ጠርቷል፣ መጻሕፍትም እንዲሁ። ዮሐ. 5÷28።

የሊቀ ካህናት ሹመቱ ስለ ሰው ነው፣ የሚያቀርበው መሥዋዕትም ሆነ የሚፈጽመው አገልግሎት ሰውን ከኃጢአት ለማንጻት፣ ከእግዚአብሔር በረከትን እንዲያገኝ ለማድረግ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ «ስለ ሰው ይሾማልና» ያለው ለዚህ ነው። ዕብ.8÷8። ጌታችንም ሰው የሆነውና ክህነትን ገንዘብ ያደረገው ስለ ሰው ነው። የሰውን ኃጢአት ለማራቅ ሰው ሆኗልና። «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪ ሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ ወድዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር አልላከውምና» ዮሐ.3÷16–17። «ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው።» 1ኛጢሞ.1÷15 እንዳለ። ስለዚህ ጌታችን ሰው ሆኖ ሰውን ሊያድን ስለ ሰው መሥዋዕትን ሊያቀርብ መጥቷልና ሊቀ ካህናት መባል

www.zeyeneta.com

ተገባው::

ለ/ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚቻለው ሊቀ ካህናት ብቻ ነው

ከመጀመሪያው ሊቀ ካህናት ከአሮን ጀምረን ስንመለከት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ለመግባት እርሱ እንጂ ልጆቹ አልተፈቀደላቸውም:: ይኸውም «እግዚአብሔር ሙሴን አለው:- እኔ በሥርየቱ መክደኛ ላይ በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመጋረጃው ውስጥ በታቦቱ ላይ ወዳለው ወደ ሥርየቱ መክደኛ ወደ ተቀደሰው ሥፍራ ሁልጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው::» ዘሌ.16÷2 በማለቱ ታውቋል:: ይህም የዘላለም ሥርዓት ይሆንላቸው ዘንድ ታዝዟል:: ዘሌ.16÷29::

ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ «ካህናት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ዘወትር በፊተኛይቱ ድንኳን ይገቡባታል፤ በሁለተኛው ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ ይገባባታል» /ዕብ.9÷7/ በማለት በማያሻማ መንገድ አስቀምጠልናል:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የገባባት ቅድስተ ቅዱሳን በሰው ያልተተከለች በፈቃደ እግዚአብሔር የሆነች ከእርሱም በፊት ከእርሱም በኋላ ማንም ያልጠገባትና የማይገባባት ናት:: ሊቀ ካህናት በዓመት አንድ ጊዜ ይገባል፤ እርሱ ግን አንድ ጊዜ ብቻ ገባ፤ ለዓለምና ለዘላለም መሥዋዕቱ ሕያው ሆኖ ይኖራል::

እነዚያ በየዓመቱ የሚገቡት ሟች ስለሆኑ መሥዋዕታቸውም ሙት ነውና ሌላ አዲስ ያስፈልጋቸዋል:: «ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ለሰው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ÷ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን÷ የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገባ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም::» ተብሎ

ተጽፏል:: ዕብ.9÷11-12::

ጌታችን የገባበት ድንኳን የተባለችው «ሰብዓዊ» ናት:: ድንኳን ያላት የዘላለም መሥዋዕት የሆነው የጌታ ትዱስ ሥጋ የተቆረሰው ከቡር ደሙ የፈሰሰው በመስቀሉ ላይ ስለሆነ ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ ወደዚች ድንኳን «አንድ ጊዜ ፈጽሞ በገዛ ደሙ ወደ ቅድስት ገባ» በማለት ራሱን መሥዋዕቱን አድርጉ የወጣበት መስቀል መሆን በግልጽ አስረድቷል::

ጌታችን መሥዋዕቱን ያቀረበው ሌላ ቦታ ላይ ነው ማለት የሚቻለው አሳቢ ፍጥረት የለም:: በሰው ያልተተከለች ያለበትም ምሥጢር አይሁድ መስቀሉን ጌታን ለመግደል የሰቀሉት እንጂ መሥዋዕተ እግዚአብሔር ይትረብበት ብለው ስላልሆነ ነው:: «ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች» ማለቱም በመስቀል ላይ ራሱን መሥዋዕት ሊያደርግ የሚችል ሰው የለም፤ ቢኖርም እንኳ፤ ሌላውን ቀርቶ ራሱንም ማዳን አይቻለውምና፤ ለፍጥረት ባልሆነች ብሏታል::

ጌታም ይህንን ነገር በወንጌል ገልጿል:: የዮሐንስ ወልደ ነጎድጓድ እናት በመንግሥትህ ጊዜ አንዱን በቀኝህ አንዱ በግራህ ይተመጡልኝ ብላ ለመነች:: ጌታም መንግሥቱና መገለጫው ድንኳኑ መስቀሉ እንደሆነ ሲገልጽላት «የምትለምኑትን አታውቁም:: እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ፣ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አሉ:: እንችላለን አሉት:: እርሱም:- ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም::» /ማቴ.20÷20-24/ በማለት መንግሥቱ የተባለ ሞቱ እንደሆነ ገልጿል:: ምክንያቱም ሰይጣንን ድል ነሥቶበታል፤ ነፍሳትን ማርኮ በታል፤ መገለጫ ዙፋኑም ድንኳኑ መስቀሉ ስለ ነበረ ቀኝና ግራ ለሽፍቶቹ መሆኑን ገልጦ አስተምሮናል::

www.zeyeneta.com

ይህንም አስተድሞ በነቢዩ በዳዊት አስነግሮታል። «ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፣ እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን።» መዝ.131÷7 በማለት መስቀል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ሕያው መሥዋዕት አድርጉ ሊያቀርብ የወጣበትና እግሮቹ የቆሙበት ከተለዩት ልዩ ናት ከምትባለው ቅድስተ ቅዱሳን የሚከብር መሆኑን አስረግጦ ተናግሮልናል። መስቀል የእግዚአብሔር ልዩ መቅደስ መሆኑ በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ ይብራራልና በዚያ ይመልከቱ።

በዚህ ርዕስ ግን ጌታ ወደዚህ ወደ ተለየች መቅደሱ /መስቀል/ እርሱ ብቻ አንድ ጊዜ ገብቷልና ሊቀ ካህናት ይባላል። ይልቁንም እርሱ በገባበት የገባም ወደ ፊትም የሚገባ የለምና ልዩ ሊቀ ካህናት መሆኑን ይስረዳል። «እንግዲህ ሕዝቡ በሊቂ ክህነት የተመሠረተ ተን ሕግ ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን÷ እንደ አሮን ሹመት የማይቆጠር÷እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሣ ወደፊት ስለምን ያስፈልጋል?» ዕብ.7÷11፤ «ቅዱስና ያለ÷ ተንኰል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰ ማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባ ናል።» ዕብ. 7÷20 ተብሎ የተጻፈው ለዚህ ነው።

ሐ/ ሊቀ ካህናት ሁሉ መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ይሾማልና፣ ዕብ.8÷3

የሊቀ ካህናት ዋናው አገልግሎት መባንና መሥዋዕትን ማቅረብ ነው። ይልቁንም በዓመት አንድ ጊዜ በቅድስተ ቅዱሳን የሚቀርበው መሥዋዕት የግድ ሊቀ ካህናት ይፈልጋል። ጌታችንም የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ የተባለለት /ዮሐ.1÷29/ ራሱን መሥዋዕት አድርጉ ያቀረበ ብቸኛ ሊቀ ካህን ነው። ራሱ መሥዋዕት በመሆኑም ሌላ የሚያቀርበው መሥዋዕት

አላስፈለገውም፡ ሁለቱም አንድ ጊዜ መሆን ይቻለዋልና። «... የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገሣ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም።» ዕብ.9÷12። «እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ። ዕብ.10÷12። እንዲል።

ስለዚህ እንጠብቀው የነበረውን ዓለምን ኃጢአት ማስተሥረይ የሚቻለውን እውነተኛ መሥዋዕት ራሱን በራሱ ለራሱ ያቀረበልን ነውና ሊቀ ካህን መባል ተገባው። «አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል።» የተባለው ለዚህ ነው። ዕብ.9÷26።

በአጭር ቃል ጌታችን ሊቀ ካህናት ሊባል የተገባው ፍጹም ሰው መሆኑን ለማጠየቅ በእውነተኛይቱ ሰው በማይገባበት ቅድስተ ቅዱሳን /መስቀል/ አንድ ጊዜ ብቻ ስለ ገባ፡ በእርሷም እውነተኛውን መሥዋዕቱን /ራሱን/ ስላቀረበና ኃጢአተ ዓለምን ስላራቀ ነው እንጂ ሌሎች ካህናት ከእርሱ በጎላ አያስፈልጉም ለማሰኘት አይደለም። ለመሆኑ የጌታችን ክህነት የብሉይ ኪዳን ካህናትና የሐዲስ ኪዳን ካህናት አስፈላጊነታቸው አንድ ዓይነትና እኩል ነውን? የጌታችንስ ሊቀ ካህናት መባል የሌሎቹን ያስቀራልን? እርሱ የሰጠውን አገልግሎት ሌሎቹ መስጠት ይችላሉን? በሚከተሉት ርእሶች በመጠኑ እንመለከታለን።

3.4.4 የጌታችን ሊቀ ካህናትነት ፍጹም ልዩ ነው

የኦሪት ሊቀ ካህናት ሊትነቱ በካህናቱና በሕዝቡ ላይ እንጂ ጥንተ አብሶን በማስተሥረይ እንዳልነበረ ክህነቱ ጊዜያዊና ሕጸጽ ያለበት /ምሉዕ ያልሆነ/ እንደ ሆነ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ይህም ማለት የጌታችን ክህነት አስፈላጊነት የበጉንና የፍየሉን ደም ለማቅረብ አልነበረም፡ ለእነርሱ ያልተቻለውን ኃጢአተ ዓለምን

www.zeyeneta.com

ለማስተስረይ እንጂ:: ይህ የአዲስ ኪዳን መሥዋዕትም ፍጹምና ሕያው የሆነ የወልደ እግዚአብሔር ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ስለሆነ ከዚህም በኋላ የበግና የፍየል ደም ማቅረብ ቀርቶልናል::

ይህ የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ሲቀር የብሉይ ኪዳን ክህነትም ቀርቷል:: ኪዳኑ አዲስ ሲሆን ካህናቱም አዲስ መሆን ይገባቸዋልና፣ ራሱ ጌታችንም አዲሱን የወይን ጠጅ በእሮጌ አቁማዳ የሚያስቀምጥ የለም:: አሮጌውን ልብስም በአዲስ እራፊ የሚጥፍ የለም» እንዳለ አዲሱን ፍጹሙንና ሕያውን መሥዋዕት ፍጹም ባልሆነ ክህነት ሊያቀርቡት ሊሠዉትም አይገባምና:: የዚህ መገናኛ ግን የጌታችን ክህነት ነው:: የእርሱ ግን ፍጹም ልዩ ነው:: ከብሉያቱ ጋር ምን ልዩነት እንዳለው ቀደም ብለን እያንዳንዳቸውን ተመልክተናል:: የሐዲስ ኪዳን ክህነትንም ወደፊት እንመለከታለን::

1.ጌታችን የክህነት አገልግሉት የፈጸመባት ቅድስተ ቅዱሳን «መስቀል» ናት፣ ከጌታችን በፊትም ከእርሱ በኋላም በመስቀል ላይ መሥዋዕትን ያቀረበ የለም::

2 የብሉይ ኪዳን ካህናት መሥዋዕተ እንስሳን የሐዲስ ኪዳን ካህናትም የጌታችንን ሥጋና ደም ያቅርቡ እንጂ ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው እንኳን ቢያቀርቡ ስንኳን የሌላውን የራሳቸውንም ኃጢአት ማስተሥረይ አይችሉም፣ ጌታችን ግን ራሱ ካህን፣ ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ ሆኖ ኃጢአተ ዓለምን አድርቋል::

3.የሌሎቹ ክህነት በየራሳቸው አይደለም:: ከእግዚአብሔር በጸጋ የተቀበሉት ነው የእርሱ ግን የባሕርይው ነው፣ ከማንም አልተቀበለውም፣ ማንም አይወስድበትም::

4.ሌሎች በየጊዜው በተሠራው ሥርዓት መሠረት አገልግሉት መፈጸም ይጠበቅባቸዋል፣ እርሱ ግን አንድ ጊዜ በፈጸመው አገልግሉት ወደፊት የሚመጡትን ብቻ ሳይሆን እርሱ ከመገለጡ

በፊት ለነበሩትና በሕይወተ ሥጋ ያልነበሩትን ሁሉ ከኃጢአታቸው አንጽቶ ወደ ርስታቸው ለመመለስ ተችሎታል::

እነዚህንና የመሰሉትን ስንመለከት የጌታችንን ክህነት ከፍጡር ክህነት ጋር ማመሳሰልና ማቀራረብ የማይገባ መሆኑን እንመለከታለን:: ለምሳሌ በሐዲስ ኪዳን የሥልጣኑ ደረጃ ከዲቁና እስከ ጵጵስና ድረስ ነው:: ይህን የሐዲስ ኪዳን ትልቁ የክህነት ማዕረግ /ጵጵስና/ ከጌታችን ክህነት ጋር ይበልጣል ያንሳል በሚል የሚወዳደር አይደለም:: የጌታችንን ሊቀ ካህናትነት የሚመስለው የለምና::

3.4.5 በውኑ ሌሎች ካህናት አያስፈልጉምን?

«ጌታችን ሊቀ ካህናት ስለሆነ ሌላ ካህን አያስፈልገንም» የሚለው አንዳንድ ሰዎች የሚያሰሙት ንግግር በራሱ የእግዚአ ብሔርን ሥራ በቀጥታ የሚቃወም ነው:: ለምን ቢሉ? ጌታችን ካህን ብቻ አይደለምና፣

ጌታችን የዓለም ብርሃን ነው:: ስለዚህ ሌላ ብርሃን ሰጭ አያስፈልግምን?

ጌታችን ሕይወት ነው፣ ስለዚህ ለሕይወተ ሥጋ የሚጠቅሙ ሁሉ ከእየር ጀምሮ አያስፈልጉምን?

ጌታችን መድኃኒት ነው፣ ስለዚህ ምንም ዓይነት መድኃኒተ ሥጋ አያስፈልግምን?

ጌታችን እውነት ነው፣ ስለዚህ እውነት የሆነ ሌላ ነገር ለእኛ አያስፈልግምን?

ጌታችን መንገድ ነው፣ ስለዚህ መንገድ አያስፈልግምን?

ጌታችን የሕይወት ውኃ ነው፣ ስለዚህ ውኃ አያስፈልግምን?

ጌታችን ንጉሥ ነው፣ ንጉሥ አያስፈልግምን?

ጌታችን እውነተኛ እረኛ ነው፣ ስለዚህ እውነተኛ እረኛ

www.zeyeneta.com

አያስፈልግምን?፡ የሚሉትን የሞኝ ይትበሃሉች ያመጣል።

ሌሉች ነብያት ከሌሉ የጌታችን ሊቀ ክህንነትስ በእነማን ላይ ነው? ጌታችን «እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ።» /ዮሐ.8÷12/ ብሎ ሲያበቃ «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።» ማቴ.5÷22 እንዳለ። «ፍርድ የእኔ የመልድ ነው፤» ዮሐ.5÷23፡ ካለ በኋላ እናንተም በዓለም ላይ ትፈርዳላችሁ እንዳለ «እኔ እውነተኛ እረኛ ነኝ» /ዮሐ.10÷11/ ካለ በኋላ «በጉቼን ጠብቅ፣ ጠቦቶቼን ጠብቅ፣ ግልገሉቼን አሠማራ» /ዮሐ.21÷15-19/ ሲል አረኝነትን ለሐዋርያት ሰጠ። እርሱ አምላክ ሆኖ ሳለ የጸጋ አምላክነትን ለትዳሳን የሰጠ እንጂ /ዘጸ.7÷1፣መዝ.81÷1/ የእኔ ገንዘብ የሆነ ሁሉ ለፍጡር አይገባም ብሎ የከለከለ አምላክ ያለን አይደለንም።

ይህን የእግዚአብሔር ልጆች መባልን ለእኛ ሰጥቶናል፣ ይህንንም ከላይ ተመልክተነዋል። ስለዚህ እግዚአብሔር ክህነትንም ለሐዋርያት ሰጥቷል። ክህነታቸው ከሌዋውያን ክህነት የተለየ ፍጹም ክህነት ነው። ይህንንም በሚከተለው ርእስ በስፋት እንመለከተዋለን።

3.5 ክህነተ ሐዋርያት /የሐዲስ ኪዳን ክህነት/

ሐዋርያት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ናቸው። እርሱ ጠራቸው፣ እርሱ ሾማቸው። ከዚህም በኋላ ደግሞ እነርሱ እየሾሙ ወደ ትውልድ ተላለፈ፣ ይሁን እንጂ ከብሉይ ኪዳን ክህነት ጋር በብዙ መንገድ ይለያል፣ ስለዚህ በዝርዝር እንመለከተዋለን።

3.5.1 ክህነቱ ምን ዓይነት ነው

ሀ. <u>በአንድ ተከፍሎ የለበትም</u>፡- የብሉይ ኪዳን ክህነት ለአንድ ነገድ ለሌዊ ብቻ የተሰጠ እንደ ነበር ተመልክተናል። በአዲስ ኪዳን ግን አምነው የተጠመቁ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። ዮሐ.1÷12። ለክህነት በሥጋ ልደት ከሚቆጠር ሌዋ

ዊነት ይወለዱ ዘንድ አይገደዱም፣ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ተወልደ ዋልና። ዮሐ.3÷1-10። ለዚህም ክህነት መሥራች የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት የጠራውና የመረጠው ከአሥራ ሁለቱም ነገደ እሥራኤል መሆኑ ክህነት ከልደተ ሥጋ የማትሰጥ መሆኑን ለማስረዳት ነው። ነገዳቸውም እንደሚከተለው ነው።

1. ቅዱስ ጴጥሮስ ከነገደ ስምዖን /በእናቱ ወገን/
2. ቅዱስ እንድርያስ ከነገደ ሮቤል /በአባቱ ወገን/
3. ቅዱስ ያዕቆብ ከነገደ ሌዊ /በአባቱ ወገን/
4. ቅዱስ ዮሐንስ ከነገደ ይሁዳ /በእናቱ ወገን/
5. ቅዱስ ፊልጶስ ከነገደ ዛብሎን
6. ቅዱስ በርቶሎሜዎስ ከነገደ ንፍታሌም
7. ቅዱስ ማቴዎስ ከነገደ ይሳኩር
8. ቅዱስ ቶማስ ከነገደ አሴር
9. ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ አልፍዮስ ከነገደ ጋድ
10. ቅዱስ ታዴዎስ ከነገደ ዮሴፍ
11. ቅዱስ ስምዖን ቀናዊ ከነገደ ብንያም
12. የአስቆሮቱ ይሁዳ ከነገደ ዳን ናቸው።

ጌታችን ሀብቱንና ጸጋውን የሚሰጣቸው ሰዎች ከቤተ እሥራኤልም ብቻ ሳይሆን ከቤተ አሕዛብ ሊሆኑ እንደሚችሉ «በልባችሁም፡- አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይመሰላችሁ፣ እላችኋለሁና፡ ከእዚህ ድንጋዮች /ከአሕዛብ/ ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር ይችላል።» /ማቴ.3÷9/ ሲል መጥምቁ ዮሐንስ አስረግጦልናል። ስለዚህ በሐዲስ ኪዳን ክህነትን ለማግኘት ከእግዚአብሔር ምርጫ በተጨማሪ ንጽሕናን መጠበቅ፣ትምህርትና ፍላጎት እንጂ የአንድ ነገድ አባል መሆን አያስፈልግም።

www.zeyeneta.com

ለ/ ፍጹምና ምሉዕ ነው

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የሰጠው ክህነት እንደ ሌዋውያን ነቀፌታ /ጉድለት/ አልነበረበትም። እነርሱን ከጥንተ አብሶ ካላቀቃቸው /ከፍጥረቱ ሁሉ ጋር/ በኋላ ንጹሐን አድርጓቸዋልና፡ የተሰጣቸውም ሥልጣን ፍጽምት ናት። ክህነተ ሌዋውያን ግን ፍጹም አይደለም ያሰኘው ከዘር ኃጢአት ያልተላቀቁና በክህነቱም የሚሰጠው አገልግሎት ልምላሜ ገነትን ዕረፍት ሠንሠላጥ ሰማያትን የሚያወርስ ስላልሆነ ነበር። የሐዋርያት ክህነት ግን በቦታ ሳይወሰን ኃጢአትን ማስተሥረይ የሚችል ነው።

«እውነት እላችኋለሁ÷በምድር የምታሥሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል÷በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» ማቴ.18÷18 እንዲል። ስለዚህ የሐዋርያት ሥልጣነ ክህነት ፍጹም ነው። እነርሱ የፈቱት የተፈታ፣ ያሠሩትም ደግሞ የታሠረ ነውና ከህነታቸው ፍጹም ሥርየተ ኃጢአትን የሚያሰጥ ነው። ካህናቱም በኃጢአት /በጥንተ አብሶ/ ያልታሠሩ ክህነቱም ሁሉንም ኃጢአት የሚያስተሠርይ ምሉዕ ፍጹም ነው። ካህናቱ ሰዎች እንደ መሆናቸው መጠን ኃጢአት የሚሠሩ ቢሆኑም ዕለት ዕለት የራሳቸውን እየተናዘዙ የሚነጹ ስለሆነና እነርሱ ፍጹማን ባይሆኑም ከኃጢአታቸው በንስሐ ይድኑበት ዘንድ የተሰጠው ሥልጣን ላይ ድካምና ሕጸጽን ሊያመጣ ስለማይችል ክህነቱ ፍጹምና ምሉዕ ነው።

የክህነተ ሐዋርያት የሥልጣን ፍጹምነት ኃጢአተ ምእመናንን ለማስተሥረይ ብቻ ሳይሆን የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እየፈተቱ ለምእመናን ለማቁረብም ነው። ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ሥጋውን ደሙን እንዴት መፈተት እንዳለባቸው በጸሎተ ኀሙስ ካስተማራቸው በኋላ /ማቴ.26÷20-29/፣ ለመጣ ደኅዋት ማርያም ሳይጸሰስ /ዮሐ.20÷17/ ለሐዋርያት መጸሰሱ ሥጋውን

ደሙን ለመፈተት ሥልጣን ለእነርሱ መስጠቱን ያጠይቃል። ሉቃ 24÷39፣ዮሐ.20÷20፣1ኛዮሐ.1÷1-2። ዘወትርም በቤተ ክርስቲያናችን የሚፈተተው የእርሱ ቅዱስ ሥጋ ክቡር ደም ነው፡ ኅብስቱ ተለውጦ አማናዊ ሥጋው፣ ወይኑም ተለውጦ አማናዊ ደሙን ይሆናልና። 1ኛቆሮ.11÷23-32።

ካህናት የማያምኑትን አስተምረውና አሳምነው የማጥመቅ ወዲያውም ደግሞ ወልደ እግዚአብሔር የማድረግ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው÷ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።» ማቴ.28÷19-20 እንዲል እያስተማሩ እያጠመቁ የቤተ ክርስቲያን አባል የማድረግ፣ በራሳቸው ፍልስፍና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን አትልለው በብልጣብልጥነት እንናራለን የሚሉትንም መክረው ዘክረው አልመለስ ካሏቸው ከመንጋው የመለየት ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። ማቴ.18÷15-17። ይህን የመሰሉትን ሁሉ የማድረግ ሥልጣን እንዳላቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። ሐዋ.5÷1-10። ስለዚህ የካህናተ ሐዲስ ሥልጣን ፍጹምና ምሉዕ ነው።

ሐ/ <u>ዘላለማዊ</u> ነው፡- የብሉይ ኪዳን ክህነትን ጊዜያዊ ነው ስንል በጊዜ መወሰኑን ብቻ ለማመልከት አይደለም። ይልቁንም የሚተካው አማናዊ ክህነት ከዚያ በኋላ እንደሚመጣ ለማመላከት ነው። ጊዜያዊ ነው ስንል ፍጹም የሆነው የት አለ? ያሰኛልና ነው። ያ የብሉይ ኪዳን ክህነት ለሐዲስ ኪዳን ክህነት እምሳል ጥላ፣መርገፍ ነበር። ይህ ግን የዚያ ፍጻሜና አማናዊ ነው። ከዚህ በኋላ ያሚመጣ ደኅኛ ክህነት የለምና ዘላለማዊ ነው እንላለን። ከዚህ ሌላ ክህነት እንደማይመጣ ሊያመለክትም «እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ

www.zeyeneta.com

ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ::» ማቴ.28÷20 በማለት አስረግ ጠልናል::

የብሉይ ወራሽ ሐዲስ፣የአሪትም ወራሽ ወንጌል እንደሆኑ ሁሉ የብሉይ ክህነትም የሐዲስ ኪዳን መጻረሻ ስለነበር ጊዜያዊ /መቆያ/ ሲባል የሐዲስ ክህነት ግን የዚያ ፍጻሜ ነውና ዘላለማዊ ክህነት ተብሏል:: አንድን ነገር ዘላለማዊ የሚያሰኘው ቅሉ ወራሽ የሌለው ሲሆን ነው:: የጊታችንም ክህነት የባሕርይው ነውና ማንም ሊወርሰው አይችልም:: እግዚአብሔር ሰጠ ሲባልም እንደ ባዕለጸጋ ካለው አንሥቶ የሚሰጥና የራሱም የማይጉድልበት ከዚህ የተነሣ የሐዲስ ኪዳን ነው:: ክህነት ወራሽ የላትምና ዘላለማዊ ክህነት ትባላላች::

መ/ ልዩ አገልግሎት ነው

አንዳንድ ሰዎች «ክህነት ሰው የሚመረጥለት ልዩ አገልግሎት አይደለም:: ሁላችንም ካህናት ነን» ይላሉ:: ለማስረጃም «በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ::» 1ኛጴጥ.2÷5::

«ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን÷መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ሳደረገ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን አሜን::» ራእ.1÷6 የሚሉትን ጥቅሶች በአስረጅነት ያቀርባሉ:: ይህ ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ መቃወም ነው:: ለሰው ሁሉ ያለ አድሉ ከእግዚአብሔር የሚሰጡ ነገሮች አሉ እነዚህም:-

1ኛ መሸበት ነው :- እግዚአብሔር በመግቦቱ የፈጠረውን ፍጡር ሁሉ ይመግባል:: እንስሳት፣ አራዊት፣ ሰማይ፣ ምድር፣ ሰው፣ መላእክት አይልም፣ ለሁሉም በጊዜው ምግባቸውን ይሰጣቸዋል:: ከሰውም አማኒ፣ከሃዲ፣ጻድቅና ኃጥእ የሚል ተከፍሎ አያደርግም::

2ኛ/ የማዳን ሥራው : ይህም አምነው ለመጡ ሁሉ የሚሰጥ ነው:: ትዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ ለግሪክ፣ ለእስራኤል፣ ለሮም ለኢትዮጵያ የሚል የለበትም::

3ኛ/ ነጻ ፈቃድ: ሰው ከእግዚአብሔር የተሰጠው ትልቁ ሀብት አእምሮ /ሰውተት/ ደኅንና ክፉውን ለይቶ የማወቅ ሀብት ነው:: በዚህ መሠረት ሰው አምኖ ወይቆ ፈቅዶ ነው እንጂ ተገድዶ አያጸድትም:: ይህን የመሰሉ ነገሮች ያለ አድሉ ተሰጥተውናል:: ከዚህ በኋላ ግን በአንድ መንፈስ የተለያየ ጸጋ ይሰጣል፣ ይኸውም ለማፋረስ ያይደለ ለማነጽ ነው:: «የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው፣ መንፈስ ግን አንድ ነው:: አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው፣ ጌታም አንድ ነው:: አሠራርም ልዩ ልዩ ነው÷በሁሉ የሚያደርግ እግዚአብሔር ግን አንድ ነው:» 1ቆሮ.12÷4 ይላልና::

ስለዚህ ከአገልግሎት ወገን የሆነውን ክህነትን ለእስራኤል እንደ ወረደው መና ለሁሉም ነው ማለት «አገልግሎትን መግቦት ነው» ማለት ይሆናልና ፍጹም ስሕተት ነው:: እነዚህን መሠረት አድርገው ሁላችንም ካህናት ነን ካሉ በራእ.5÷10 ላይ «የክርስቶስ ካህናት ብቻ ሳይሆን መንግሥትም ነን» ይላልና መንግሥት አያስፈልገንም ሊባል ነው:: ይህ ግን የሞኝ አሳብ ይሆንባቸዋልና አውነቱን መመርመር ያስፈልጋል::

በአሪት ለዚህ ለተለየ አገልግሎት እግዚአብሔር ለሊቀ ነቢያት ሙሴ አሮንንና ልጆቹን አትርብልኝ አለው:: ሌላ እንኳ ቢቀርብ ይገደል ነበር ያለው:: ይሁን እንጂ ሕዝቡን ደግሞ «አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ÷ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ:: እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ:: ለእስራኤል ልጆች የምትነግራቸው ቃል ይህ ነው::» ብሏቸዋል:: ዘጸ. 19÷5-6:: ሕ

www.zeyeneta.com

ዝቡን የካህናት መንግሥት ማለቱ ግን የሌዋውያንን ክህነት የሚያ ስቀር አይደለም። ጌታችንም በብሉይም በሐዲስም «የተቀደሰ ካህ ናት ትሆኑልኛላችሁ» ማለቱ በመንግሥቱ ከተገለጠ በኋላ ሁላችንም እንደ መላእክት አያመስገንን የምንኖር መሆናችንና ለዚያም የተዘጋ ጀን እንድንሆን ለመንገር ነው። «በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም።» ማቴ.22÷30 እንዲል።

አገልግሎቱ ልዩ መሆኑን ጌታችን በንግግርም በተግባርም ገልጠታል። በተግባር ጌታችን ወደ ተራራ ወጥቶ ሲጸልይ ከአደረ በኋላ በነጋው ጀምሮ ሐዋርያትን መምረጥና መጥራት ጀመረ። ይኸ ውም ይታወቅ ዘንድ የሚከተለው ከአምስት ገበያ ሕዝብ በላይ ሆኖ ሳለ አሥራ ሁለቱን እንደ ሕዝቡ አያሰናብታቸውም ነበር። ከዋለበት እየዋሉ ካደረበት እያደሩ ትምህርትና ተአምራት ሳይከፈልባቸው እንዲኖሩ አደረጋቸው እንጂ። እነርሱ ሊሄዱ በወደዱ ጊዜ እንኳን «ልትሄዱ ትወዳላችሁን?» በሚል ጥያቄያዊ ተግሣጽ እንዳይሄዱ አድርጓቸዋል። ዮሐ.6÷69።

በንግግር ደግሞ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣ ችሁኝም።...ልትሄዱና ልታፈሩ ፍሬአችሁም ሊኖር ሾምኳችሁ።» /ዮሐ.15÷16/ ብሏቸዋል። የመረጣችው የሾማቸው መሆኑን መናገሩ አገልግሎቱ ልዩ መሆኑን ያስገነዝበናል። ወደ አገልግሎትም ሲያሠማ ራቸው ሥልጣን እንደ ሰጣቸው በማቴ. 12÷1–15 ላይ ይገልጿል። ክትንሣኤው በኋላም «እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋር ነኝ» /ማቴ.28÷20/ ማለቱ ሥልጣኑ በእንብሮተ እድ የሚተላለፍ የተለየ መሆኑን የሚያመለክት እንጂ የሐዋርያትን አለመሞት አያመለክትም።

ከማረጉም በፊት በእንብሮተ እድ እስከ ጵጥርያርክነት ያለውን ሥልጣን ሾማቸው በተነሣ በነምላኛው በወረገ በአሥረኛው ቀንም መንፈስ ቅዱስን ልኮ በአእምሮ እንዲታደሱ በሰውተት እንዲ

ጉልምሱ፣ብዙ ቋንቋ እንዲናገሩ ምሥጢራትንም እንዲተረጕሙ አስቻላቸው ። ይህም አገልግሎቱ ልዩ በመሆኑ ነው። ሉቃ.24÷51፣ሐዋ2÷1–46።

ልዩ መሆኑ በሐዋርያትም አገልግሎት ጊዜ ተረጋግጧል። ለምሳሌ ያህል በይሁዳ ምትክ በጸሎትና በጾም በዕጣም ሌላ ሰው መመረጡ የዚህ አስረጂ ነው። ሐዋ.1÷22–26። ሰባቱ ዲያቆናትም በምርጫ፣በጸሎትና በእንብሮተ እድ መሾማቸው ይህን የሚያመለክት ነው። ሐዋ.6÷3–6። ከዚህም በኋላ በሰፊው በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ይገኛል።ሐዋ.14÷23፣ቲቶ1÷5፣1ጢሞ.4÷14፣ሐዋ.20÷28።

3.5.2 ሥርዓተ ክህነትና አገልግሎት

የአዲስ ኪዳን ካህናት ሥርዓተ ሢመታቸውና ለክህነቱ የሚያበቃቸው እንዲሁም አገልግሎታቸው በቤተ ክርስቲያናችን በስፋት የታወቀና የተረዳ የተጻፈበትም ነው። ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን የጸፉ ሁሉ የጸፉትና በሌሎችም መጻሕፍት በሰፊው የተገለጸ ስለሆነ እያንዳንዱን በዝርዝር ልንመለከተው አንችልም። ዐብዩ ነገር ሃይማኖታቸውን ጠንቅቀው ያወቁና የተረዱ ማስረዳትም የሚቻላቸው፣ አዲስ አማኝ ያልሆኑ፣ በንጽሕና በድንግልና የሚኖሩ ወይም ጋብቻቸውን ያልደገሙ፣ሙሉ አካላትና የጤንነት መንፈስ ያላቸው፣ ግብረ ገቦች፣ አብዝተው የወይን ጠጅ የማይጠጡ፣ ቄሞቶች፣ ትዕግሥተኞች፣ ሁለት ቃል የማይናገሩ፣ በዚህ ሁሉ ተፈትነው ነውር ነቀፋ የሌለባቸው ዲቁና ይሾማሉ። 1ኛጢ.ሞ.3÷8–18፤ ፍት መን.አን.7።

ከዚህ በኋላ ብሉያትንና ሐዲሳትን ቢያንስ አራቱን ወንጌላት ጠንቅቀው ሲያውቁና ዕድሜያቸው ከ30 በላይ ሲሆን ወደሚቀጥለው መዓርግ ይሸጋገራሉ። ሥርዓቱ ግን ሰፊና ጥልቅ ደረጃውም ብዙ ስለሆነ በዚህ እንፈጽማለን። አገልግሎታቸውም ከማስተማርና ከማሳመኑ በኋላ ምሥጢራትን መፈጸም ስለሆነ ሰባቱን ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ስንመለከት አገልግሎታቸውን የበለጠ እንረዳለን። ስለዚህ የሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናችንንና የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን መመልከት ያሻል።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ አራት

ዕረፍት

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው ዐቢይ ጉዳይ ዕረፍት የሚለውን ንይለ ቃል ነው። በቁጥር 14ና 15 ያለውንና ስለ ሊቀ ካህናት የተጻፈውን በምዕራፍ ሦስት ላይ የተመለከትነው ሲሆን ከላይ በምዕራፍ 3÷2–19 ያለውን ደግሞ ከዚህ ጋር በአንድነት እንመለከተዋለን።

4.1. ትርጉም

ዕረፍት፡– በቁሙ ማረፍ፣ ሞት፣ ወደ ዕረፍት ቦታ መግባት ማለት ነው። ይህ ዘይቤያዊ /ሰዋሰዋዊ/ ትርጉሙ ነው። ምሥጢራዊ ይዘቱን ስንመለከተው ግን በሦስት ወገን ከፍለን ልናስተምጠው እንችላለን።

4.1.1. ዕንቢት፡–

ዕረፍት የሚለው ቃል ማረፍ ነው ስንል ከማረፍ በፊት ሥራ እንደ ነበር ያመለክታል። ሥራ ከሌለ ዕረፍትን ልናውቀው አንችልም። ቅዱስ ጳውሎስ «ሕግ ባይኖር ኃጢአትም ባልነበረ» እንዳለ ሁሉ /ሮሜ.7÷7/ ሥራም ባይኖር ዕረፍት አይታወቅም ነበር። ሥራንም የጀመረ እግዚአብሔር ነው፤ የጀመረውም ፍጥረትን በመፍጠር ነው፤ እርሱ እንደ ጀመረም ሊገልጽ ሊቀ ነብያት ሙሴ «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ።» ዘፍ.1÷1 ሲል የሥራ መጀመሪያ የሆኑትን ፍጥረታትና የሥራ ጀማሪውን እግዚአብሔርን በመግለጽ እርሱም ጽሑፉን ይጀምራል። እግዚአብሔር ሥራን ከሠራ በኋላ ፍጥረትን ከመፍጠር ወረፈ። ስለዚህ የዕረፍት ጀማሪዋም እግዚአብሔር ነው። የመጀመሪያዪቱም ዕለተ ዕረፍት ሰንበት ተባለች፤ እግዚአብሔርም ቀደሳት አከበራት። ይህች ሰንበት አሁን «ቀዳሚት ሰንበት» እየተባለች ትጠራለች።

የመጀመሪያቱ ሰንበት፣ የመጀመሪያቱ ዕረፍት ማለት ነው። «ሰማይና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ። እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፏልና።» ዘፍ.2÷1–3 ተብሎ ተጽፏልና። ይህችን ሰንበት ጥንተ ሕግ፣ ጥንተ በዓላት፣ ጥንተ ዕረፍት ልንላት እንችላለን።

ለምን ቢሉ :–

ሀ/ ጥንተ ሕግ፡– እግዚአብሔር ሕግን በአዋጅ በጽሑፍ ለሕዝቡ የሰጠው በሙሴ ዘመን ነው። ፍጹም ሕግ መሰጠቱን ለማጠየቅ አሥር አድርጉ ሰጥቶታል፤ አሥር ፍጹም ቁጥር ነውና። በኋላም በዘመነ ሥጋዌው ፍጹም ነገርን በአሥር ቁጥር እየመሰለ አስተምሮበታል። ለአብነትም ለመላው የሰው ዘር ምሳሌ ሆነው የቀረቡትን አሥሩን ደናግል መመልከት ይቻላል። ማቴ.25÷1። እግዚአብሔር ለሊቀ ነቢያት ሙሴ ፍጹም ሕግን፡ አሠርቱ ቃላተ

www.zeyeneta.com

አራትን ሲሰጠው ሰንበት አንዷ ናት።

እርሷን ከሌሎቹ ለየት አድርጉ ተናግሮላታል። «የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ።» /ዘጸ.20፡8/ ማለቱ ቀድሞ መሰጠቷን ያመለክታል። መግደል መኖር እንደ ሆነ ቃየን ድርጊቱን ከመፈጸሙ በፊት በእግዚአብሔር ተነግሮታል። ዘፍ.4፡6-8። በሕግ ለሙሴ ሲሰጥ ግን መግደል መጥፎ መሆኑን «አስብ» ወይም አትግደል የሚለውን «አስታውስ» በሚል ሳይሆን «አትግደል» በሚል ብቻ ነው። ዘጸ.20፡13። ሌሎቹም እንዲሁ ነው የተሰጡት። ሰንበት ግን በተለየ መንገድ ስለ ተሰጠች ጥንተ ሕግ እንላታለን። ሙሴም አሠርቱ ቃላትን ከመቀበሉ በፊት ትእዛዘ እግዚአብሔርን ይቀበልና ያንገራቸው ሕጉንም ደጠብቁ ዘንድ ያስጠነቅቃቸው ነበር።

ደሽም ይታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር ሙሴን የሚከተለውን ተናግሮታል። «እግዚአብሔርም ሙሴን፣ በሕጌ ይሂዱ ወይም አይሂዱ እንደ ሆነ እኔ እንድፈትናቸው፣ እነሆ ከሰማይ እንጀራን አዘንብላችኋለሁ። ሕዝቡም ወጥተው ለዕለት ለዕለት የሚበቃቸውን ይልቀሙ። እንዲህም ይሆናል፡- በስድስተኛው ቀን ያመጡትን ያዘጋጁ ዕለት ዕለትም ከሚለቅሙት ይልቅ ሁለት እጥፍ ይሁን አለው።» ዘጸ.16+4-5። ይህ ንግግር በሙሴ አማካኝነት ትእዛዛትን ከመስጠቱ በፊት ሰንበትን ያከብሩ ዘንድ በስድስተኛው ቀን ማድረግ ያለባቸውን ነግሮታል። ቆይቶም ሲያስፈጽማቸው እንመለከታለን።

«እርሱም እግዚአብሔር የተናገረው ይህ ነው። ነገ ዕረፍት፣ ለእግዚአብሔርም የተቀደሰ ሰንበት ነው፣ የምትጋግሩትን ጋግሩ፣ የምትቀቅሉትንም ቀቅሉ፣ የተረፈውንም ሁሉ እንዲጠበቅ አኑሩ አላቸው። ሙሴም እንዳዘዘ ለነገ አኖሩት፣ አልሸተተም፣ ትልም አልሆነበትም። ሙሴም የእግዚአብሔር ሰንበት ዛሬ ነውና ብሉት። ዛሬ በሜዳ አታገኙትም ስድስት ቀን ልቀሙት ሰባተኛው ቀን ግን ሰንበት ነው፣ በእርሱ አይገኝም አለ። በሰባተኛውም ቀን እንዲህ

ሆነ፡ ከሕዝቡ አንዳንድ ሰዎች ሊለቅሙ ሄዱ ምንም አላገኙም።

እግዚአብሔርም ሙሴን፡ ትእዛዛቸንና ሕጎቼን ለመጠበቅ እስከ መቼ እንቢ ትላላችሁ፣ እግዚአብሔር ሰንበትን እንደ ሰጣችሁ እዩ። ስለዚህ በስድስተኛው ቀን የሁለት ቀን እንጀራ ሰጣችሁ። ሰው ሁሉ በሥፍራው ይቀመጥ በሰባተኛው ቀን ማንም ከሥፍራው አይሂድ አለው። ሕዝቡም በሰባተኛው ቀን ዐረፈ።» ዘጸ.16፡23-29። ይህ የተደረገው አሠርቱ ትእዛዛትን ከመቀበሉ በፊት ስለሆነ የሰንበትን ጥንተ ሕግነት ያረጋግጥልናል።

ጥንተ በዓላት፡- በዓል በዓመት፣ በወር፣ በሳምንት የሚከበር የደስታ የዕረፍት ቀን፣ ያለፈ ነገር የሚታሰብበት የሚዘከርበት ዕለት ነው። አከባበሩም የበዓሉን ምሥጢር እያሰበ የተለየ ልብስ በመልበስ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበት የሚዘምርበት ተግባረ ሥጋውን ትቶ ተግባረ ነፍሱን የሚፈጽምበት ዕለት ነው። ከዚህ አንጻር ሰንበትን ስንመለከት እግዚአብሔር ፍጥረትን ፈጥሮ ማረፉ የሚታሰብ ስባት+ እሥራኤልም ተግባረ ሥጋቸውን ትተው የሚሙሉባት ዕለት ስለሆነች የመጀመሪያዪቱ በዓል ናት ማለት እንችላለን።

ተግባረ ሥጋ የተከለከለባት መሆኑም ይታወቅ ዘንድ ሰው ብቻ ሳይሆን ለሰው የሚያገለግሉ ሁሉ «በዓል በማክበር ጸድቃን ባለ ማክበርም ኃጥኣን የማይባሉ» እንስሳትም መሬትም እንዲያርፉ ታዝዘዋል። «ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር አምላክህ ሰንበት ነው አንተም እንደምታርፍ ሎሌህና ገረድህ ያርፉ ዘንድ አንተ ወንድ ልጅህም ሴት ልጅህም ሎሌህም ገረድህም በሬህም አህያህም ከብትህም ሁሉ በደጆችህም ውስጥ ያለ እንግዳ በእርሱ ምንም ሥራ አትሥሩ።» /ዘጸ.5+14/ «ስድስት ዓመት ምድርህን ዝራ፣ ፍሬዋንም አግባ በሰባተኛው ዓመት ግን ተዋት አሳርፋትም።» /ዘጸ.23+10/ ተብሎ መጻፉ በዓል ተግባረ ሥጋን መሙው እንደ ሆነ ያስገነ

www.zeyeneta.com

ዝበናል::

ከዚህ በኋላ እስራኤል ከእግዚአብሔር እየታዘዙ ሌሎች በዓላትን አከብረዋል:: የቂጣ በዓል /ዘሌ.23÷5–8/፣ የመከር በዓል /ዘጸ.23÷16፣ ዘጸ.34÷22፣ ዘጎ.28÷26/፣ የዳስ በዓል /ዘሌ. 23÷39–43/፣ ቍሪም በዓል /በአስቴር ጊዜ ከሞት መዳናቸውን በማሰብ የሚያከብሩት/... የማስተሥረያ ቀን /ዘሌ.23÷26–32/ የመለከት መንፊያ ቀን /ዘሌ.23÷23–24/ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: ስለ ዚህ ለእነ ዚህ ሁሉ በዓላት ጥንታቸው ሰንበት ናት::

ሰንበተ ክርስቲያን:– ከላይ የተመለከትናት ሰንበት «ቀዳሚት ሰንበት»÷ «ሰንበተ አይሁድ» በመባል ትጠራለች:: ቀዳሚት መባሏ የመጀመሪያ ሰንበት መሆኗን ለማመልከት ሲሆን ሰንበተ አይሁድ መባሏ ደግሞ አይሁድ ከተፈቀደው በላይ እርሷን በማክበራ ቸውና በእርሷም ተወስነው በመቅረታቸው ነው:: እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረት «እግዚአብሔርም ይሁን አለ፣ ሆነም÷ መልካም እንደሆነም አየ» ተብሎ ተጽፎ በእምላካዊ ባሕርይው የሠራውን እንዳሳየን በኋላ ደግሞ አካላዊ ቃል ሰው ሆነና ሰውን የማዳን ሥራ ውን በዚህ ምድር ሠራ:: ያዕቆብን እስራኤል ብሎ እርሱ አምላክ እስራኤል እንደ ተባለ ሲመጣ ደግሞ እርሱ ክርስቶስ ተባለና እኛን ክርስቲያን አሰኘን:: ቀድሞ ፍጥረትን መፍጠር በመፈጸሙ ቀዳሚት ሰንበትን እንደ ሰጠን በኋላም የማዳን ሥራውን በመፈጸሙ ሌላ ሰንበትን ሰጣን፣ ሰንበተ ክርስቲያን::

ሰንበተ ክርስቲያን ማን ናት? ሰንበተ ክርስቲያን የምት ባለው ዕለት ዕለተ እሑድ ናት:: ይህችም ቀን ጌታችን ሰው ይሆን ዘንድ በማኅፀነ ማርያም ያደረባት ዕለት፣ የማዳን ሥራውን ፈጽሞ ሞትንና መቃብርን ድል ነሥቶ የተነሣባት ዕለት ናት:: መጀመሪያ ዓለሙን መፍጠር የጀመረባት ወደፊትም ዓለሙን በማ

ሳለና፡ ንብረተ ዓለም /የዓለም ኑሮን/ የሚፈጽምባት ዕለት ናት:: ከዚህ የተነሣ ቅዱስ ዮሐንስ ለይቶ «የጌታ ቀን» ይላታል:: ራእ. 1:8::

ሌሎች፡ የእግዚአብሔር ስላልሆኑ ሳይሆን ደገኛና የተለየ ሥራ የሠራባት ቀን ለማለት ነው:: ቅዱስ ዳዊትም አስቀድሞ «ባቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር፡ ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ባቲ፡ እግዚአብሔር - የሠራት ቀን ይህች ናት፡ ሐሴትን እናድርግ በእር ስዋም ደስ ይበለን::» /መዝ.117÷24/ በማለት እግዚአብሔር ታላላቅ ተግባራትን በመፈጸም ልዩ እንዳደረጋት ተናግሯል:: ስለዚህ የጌታችን ጽንሰቱን÷ ሥጋዌውን በኋላም ትንሣኤውን ለሐዋርያትም መንፈስ ቅዱስ ያደለበትን በማሰብ የምትከበር ታላቅ የቤተ ክርስቲያን በዓል ናት::

ትልቁና ብዙዎ ነገር የማዳን ሥራውን የፈጸመባት ስለሆነች ሰንበተ ክርስቲያን ተብላለች:: እግዚአብሔር የመረጣት የቀደሳት ቀን ናትና:: ስለዚህ ሰንበተ አይሁድ ለበዓላተ አይሁድ ጥንት እንደ ሆነቻቸው ሁሉ ሰንበተ ክርስቲያንም ለአዲስ ኪዳን በዓላት ጥንታቸው ናት:: ከዚህ በኋላ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ዘጠኙን ዓበይትና ዘጠኙን ንዑሳን /የጌታ በዓላትን/፣ ሠላሳ ሦስቱን የእመቤታችንን በዓላት፣ የቅዱሳን መላእክትን በዓላት፣ የጻድቃንና የሰማዕታት፣ የነብያትና የሐዋርያትን የልደት፣ የገድላት፣ የተአምራ ትና የዕረፍት በዓላትን የምናከብር ሆነናልና፣ ሰንበት አይሁድም ትሁን ሰንበተ ክርስቲያን በየጊዜያታቸው ጥንተ በዓላት ናቸው::

ሐ/ ጥንተ ዕረፍት:–

ሰንበት ጥንተ ዕረፍት ናት፣ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ዐር ፍባታልና:: የዕረፍት ጥንት ናት ማለታችንም ተከታይ እንዳላት ለማመልከት ነው:: ሰንበት ለሚመጡት የዕረፍት ትርጓሜያት

www.zeyeneta.com

ኣብነት ጥላ እንጂ ፍጻሜም አይደለችም። በሌላ በኩል ደግሞ ጥንት የሌለው ፍጻሜ አለመኖሩን መገንዘብ ያስፈልጋል። ሰንበትን የዕረፍት መጀመሪያችን ናት ብለን ከተገባረ ሥጋ ተቆጥበን ተግባረ ነፍስን ብቻ ካልሠራንባት ወደሚቀጥለው ዕረፍት ልንሸጋገር አንችልም። አምላካችን እግዚአብሔር እስራኤልን «ሰንበታቴን አትናቁ» እያለ የሚገሥጻቸው መካነ ዕረፍትን ያወርሳቸው ዘንድ አለውና ለዚያ ይበቁ ዘንድ ቀድሞ ሰንበትን ማክበር ይጠበቅባቸው ስለነበረ ነው።

«እንግዲህ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ እንዳለ+ እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን።» /ዕብ.4+3/ የሚለውን ጠቅሶ ቅዱስ ጳውሎስ የሚያስረዳው ዕረፍት የተባለ ቦታ እንዳለ ሲያመለክት ነው። ምክንያቱም ከዚሁ በመቀጠል «ስለ ሰባተኛው ቀን በአንድ ሥፍራ፦ እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ወረፈ ብሎአልና፣ በዚህ ሥፍራም ደግሞ፦ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም። እንግዲህ አንዳንዶች በዚያ እንዲገቡ ስለ ቀሩ+ ቀድሞም የምሥራች የተሰበከላቸው ባለመታዘዝ ጠንት ስላልገቡ፦ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ በፊት እንደ ተባለ+ ይህን ከሚያህል ዘመን በኋላ በዳዊት ሲናገር፣ ዛሬ ብሎ አንድ ቀን እንደገና ይቀጥራል።» በማለት ወደፊት የሚመጣ ነገር እንዳለ በአንጻረ ሰንበት ያመለክታል። ስለዚህ ወደፊት የሚጠበቅ ሌላ ዕረፍት እንዳለ ያመለክታልና ሰንበት ጥንተ ዕረፍት /የእረፍት መጀመሪያችን/ እንጂ ፍጻሜ ዕረፍት /የዕረፍት መፈጸሚያችን/ አይደለችም።

4.1.2. ክንዳን፦

ከላይ ሰንበት ጥንቅ ዕረፍት ናት፣ ምሳሌ በመሆን የምታገለግላቸው ዕረፍት እየተባሉ በቀኖቹ አንጻር የተጠሩ መካናት

«ቦታዎች/ አሉ። ከእነርሱ ውስጥ አንዷ ከነዓን ናት። ከነዓን ለአብርሃም የተሰፋ ምድር ሁና የተሰጠች ናት። ዘፍ.12+1–8፣ 15+7 በኋላ ግን ልጆቹ በረሀብ ምክንያት ተሰደው ወደ ግብፅ ወርደዋል። ዘፍ.42+1፣ 46+34 በግብፅም ብዙ ዓመት ኑረዋል። በዚያም የሴፍን የማያውቅ ሌላ ንጉሥ ተነሣ። ዘጸ.1+8 እርሱም እስራኤልን ያስጨንቃቸው' ጀመር።

«እርሱም ሕዝቡን፦ እነሆ የእስራኤል ልጆች ሕዝብ ከእኛ ይልቅ በዝተዋል በርትተውማል፣ እንዳይበዙ ሰልፍም በተነሣብን ጊዜ ጠላቶቻችንን አግዘው እንዳይወጉን ከምድሪቱም እንዳይወጡ፣ ኑ እንጠበብባቸው አለ። በብርቱ ሥራም ያስጨንቋቸው ዘንድ ግብር አስገባሪዎችን ሾመባቸው ለፈርዖንም ፊቶምንና ራምሴን ጽኑ ከተሞች አድርገው ሠሩ። ነገር ግን እንዳስጨነቋቸው መጠን እንዲሁ በዙ እጅግም ጸኑ። ከእስራኤልም ልጆች የተነሣ ተጸይፈዋቸው ነበር። ግብፃውያንም የእስራኤልን ልጆች በመከራ ገዟቸው። በጽኑ ሥራ በጭቃ በጡብም በእርሻም ሥራ ሁሉ፣ በመከራም በሚያሠሯቸው ሥራ ሁሉ ሕይወታቸውን ያስመርሯቸው ነበር።» ዘጸ.1+8–14 «ፈርዖንም የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ ወደ ወንዝ ጣሉት ሴትን ልጅ ሁሉ ግን በሕይወት አድኗት ብሎ ሕዝቡን ሁሉ አዘዘ።» ዘጸ.1+22 እንዲል እጅግ አስቃቂ የሆነ ኑሮን መኖር ተገደዱ።

«የእስራኤልም ልጆች ከባርነት የተነሣ አለቀሱ፣ ጮኹም፣ ስለ ባርነታቸውም ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ። እግዚአብሔርም የልቅሶአቸውን ድምፅ ሰማ፣ እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አሰበ። እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች አየ። እግዚአብሔርም በእነርሱ ያለውን ነገር ዐወቀ።» ዘጸ.2+23–25 እንዲል አሰባቸው። ሙሴንም ጠራውና ከግብፃውያን እጅ ሕዝቡን ሊያድን እንዳሰበ ከነዓንንም

www.zeyeneta.com

ሊያወርሳቸው እንደሆነ ነገረው። ዘጸ.3፡7 በእርግና በሙሴ አድሮም አሥር ታላላት ተአምራትን አሥራ ሦስኛ ሞተ በዙርን አሳይቶ አስለቀቃቸው። በኋላም ፈርዖንና ሠራዊቱን በባሕረ ኢርትራ አስጥሞ እነርሱን የሚታደጋቸው ጠላቶቻቸውን የሚበቀልላቸው መሆኑን አሳያቸው። ዘጸ.5÷1፣ 15÷1።

ከዚህም በኋላ እስራኤልን መና እየመ ረደላቸው ንዑሕ ውኃ ከወለት እያፈለቀላቸው ወደ ርስታቸውና ሰረ ፍት ወደሚያገኙበት ከነዓን ሊያስገባቸው መራቸው፡ እነርሱ ግን አላምን አሉ። የእግዚ አብሔርንም ሥራ ተጠራጠሩ። ትእዛዙን አልፈ ጽም ሕጉንም አልጠ ብቅ አሉት። በዚህ ምክንያት በምድረ በዳ ወድ ቀው ቀሩ። ርስታቸው ከነዓንንም ልጆቻቸው እንጂ ከኢያሱና ከካሌብ በቀር ወላጆች ሳይወርሷት ቀሩ። 1ኛቆሮ.10÷5 ልጆቻቸው ግን በኢያሱ መሪነት ወርሰዋታል። ኢያ.14÷1፣ 21÷45።

ሀ/የእስራኤል ሽማግሌዎች ከነዓንን ሳይወርሱ ስለምን ቀሩ?

«ወንድሞች ሆይ ይህን ታውቁ ዘንድ እወድዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ። ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፡ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፡ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፡ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተ ዋልና፣ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበረ። እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፣ በምድረ በዳ ወድቀዋልና።» 1ኛቆሮ. 10÷1–5 እንዲል ከነዓንን መውረስ ሳይቻላቸው ቀርተዋል። ለምን?

1ኛ/ በምቅት፡– «እነዚህም ክፉ ነገር እንደተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ምሳሌ ሆነልን።» 1ኛቆሮ.10÷6 የግብፅን ሽንኩር ትና ዱባ እንደገና ተመኙት፡ ሥጋውንም ተመኙ፡ የተመኙትን

ሰጣቸው ስለ ኃጢአታቸው ግን ቀሰፋቸው ብዙ ሰው በዚያ ከመቀበሩም የተነሣ በታውን የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ። ዘኍ.11÷4–35።

2ኛ/ ጣያት አምልኮ፡– «ሕዝቡም ሊበሉ ሊጠጡም ተቀመጡ ሊዘፍኑም ተነሡ» ተብሎ እንደተጻፈ ከእነርሱ አንዳንዶች እንዳደ ረጉት ጣያትን የምታመልኩ አትሁኑ።» 1ኛቆሮ.10÷7 ጣያትን በማምለካቸው ብዙ ሕዝብ ተቀሠፈ። ዘጸ.32÷1–35።

3ኛ/ በዝሙት፡– «ከእነርሱም አንዳንዶች እንደ ሴሰኑ በአንድ ቀንም ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደወደቁ አንሴስን።» 1ኛቆሮ. 10÷8፣ዘኍ.25÷1–9።

4ኛ/ እግዚአብሔርን በመፈታተናቸው፡– «ከእነርሱም አንዳ ንዳቹ ጌታን እንደተፈታተኑት በእባቦችም እንደጠፉ ጌታን አንፈ ታተን።» 1ኛቆሮ.10÷9። ዘኍ. 2÷4–9 «እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ እባቦችን ሰደደ ሕዝቡንም ነደፉ፡ ከእስራኤልም ብዙ ሰዎች ሞቱ።»

5ኛ/ በማንጉራጉራቸው፡– ከእነርሱም አንዳንዳቹ እንዳንጉራ ጉሩ በሚያጠፋውም እንደጠፉ አታንጉራጉሩ።» 1ኛቆሮ.10÷10 ዘኍ.14÷36።

በማንጎራጎራቸው በ40 ቀን ሊያወርሳቸው የነበረውን በአንድ ቀን ምትክ አንድ ዓመት ተፈረደባቸው። ልጆቻቸው 40 ዓመት በምድረ በዳ ተቅበዝብዘው እነርሱም በዚያው ረግፈው ቀሩ። ከ20 ዓመት በላይ ከሆኑት ኢያሱና ካሌብን ብቻ ምድረ ርስትን አውርሷቸዋል። «እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። የሚያጉረመርምብኝን ይህን ክፉ ሕዝብ እስከ መቼ እታገሠዋለሁ? በእኔ ላይ የሚያጉረመርሙትን የእስራኤልን ልጆች ማጉረምረም ሰማሁ። እንዲህ በላቸው፡– እኔ ሕያው ነኝና በፎሮዱ እንደ ተናገራችሁት እንዲሁ በእውነት አደርግባችኋለሁ+ ይላል

www.zeyeneta.com

እግዚአብሔር፣ በድኖቻችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ፣ የተቆጠራችሁ ሁሉ እንደ ቁጥራችሁ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነ ሁሉ÷ እናንተ ያጉረመረማችሁብኝ÷ ከዩፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በቀር በእርስዋ አስቀምጣችሁ ዘንድ እጄን ዘርግቼ ወደ ማልሁላችሁ ምድር በእውነት እናንተ አትገቡም። ምርኮኛ ይሆናሉ ያልችኋቸውን ልጆቻችሁን እነርሱን አገባቸዋለሁ፣ እናንተም የናቃችኋትን ምድር ያውቃሉ። እናንተ ግን በድኖቻችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ። ልጆቻችሁም በምድረ በዳ አርባ ዓመት ይትበዘበዛሉ፣ በድኖቻችሁም በምድረ በዳ እስኪጠፉ ድረስ ግልሙትናችሁን ይሸከማሉ። ምድሪቱን በሰለላችሁባት ቀን ቁጥር÷ አርባ ቀን፣ ስለ አንድ ቀንም አንድ ዓመት÷ ኃጢአታችሁን አርባ ዓመት ትሸከማላችሁ፣ ቁጣዬንም ታውቃላችሁ።» ዘኍ.14÷26–34 ተብሎ ተጽፏል።

ይህ የሚያመለክተው ባለመታዘዛቸው ጠንቅ እግዚአብሔር ዕረፍት አግኝተው እንዲኖሩባት ከፈቀደላቸው ከምድረ ርስት ሳይደርሱ በመንገድ መቅረታቸውን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ 3÷7–19 ላይ የሚተርከው ታሪክ ይህን የሚያመለክት ነው። ይልቁንም ቁ.16–19 «ሰምተው ያስመረሩት እነማን ነበሩ? በሙሴ ተመርተው ከግብፅ የወጡ ሁሉ አይደሉምን? አርባ ዓመ ትም የተቆጣባቸው እነማን ነበሩ? ሬሳቸው በምድረ በዳ የወደቀ÷ ኃጢአትን ያደረጉት እነርሱ አይደሉምን? ካልታዘዙትም በቀር ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ? ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን።» እያለ ከነዓንን ዕረፍቱ ይላታል።

ስለምን ከነዓንን ዕረፍት አላት? ስንል፣ እስራኤል በግብጽ በፈርዖንና በሠራዊቱ የተፈጸመባቸው ግፍና አሰቃቂ መከራ ለረጅም ዘመን ያለ ዕረፍትና ያለ ሰንበት ነበረ። ከመከራውም ጽናት የተነሣ

ጽኑ ነዘንን አዘነው ነበርና፡ ከዚህ አገዛዝ ይልቁንም ከፈርዖንና ከሠራዊቱ ከግብፅ ሕዝብም መላቀቅ ዕረፍት ነበር። እነርሱ ግን ከመከራው ቢላቀቁም ዕረፍት አግኝተው የድካማቸው ዋጋ ለእነርሱ በሚመ ዘንበት ባለንነን ገብተው መኖር አልተቻላቸውምና ወደ ዕረፍቱ አይገቡም በማለት ዕረፍቱ የሚገኝበትን ሁኔ በመጠቆም ተናገረ።

ለ/ ለምን ከግብፅ አወጣቸው?

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍጹም ዕውቀት ከሚደረገው ነገር ጋር በማነጻጸር ጥያቄ ያነሣሉ። እግዚአብሔር ምድረ ርስትን ካላወረሳቸው ስለምን አወጣቸው? የተቀጡት በበደላቸውስ ከሆነ መጀመሪያውኑ ስለምን አወጣቸው? የሚሉ ጥያቄዎችን ልናነሣ እንችላለን። እግዚአብሔር በባሕርያዊ ዕውቀቱ የነገር ሁሉ ፍጻሜውን ከመታሰቡና ከመጀመሩ በፊት ያውቀዋል። «ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ፡ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይኖር በመጽሐፍህ ተጻፉ።» መዝ.138÷16 እንዲል።

ይህ ፍጹም ዕውቀቱ ግን ፍርዱን አያዛባበትም። ወደፊት ይበድላሉና አሁን የሚለምኑትን እውነተኛ ልመና አልሰማም እል ልም። ወደፊትም ይመለሳሉና ስለ አሁኑ ኃጢአት ቅጣት ወይንም ተግሣጽ አያስፈልጋቸውም አይልም፣ ከሠራ በኋላ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው የሚከፍል እውነተኛ አምላክ ነውና። «ወይፈድዮ ለኩሉ በከመ ምግባሩ» እንዳለ ራእይ 22÷12። እግዚአብሔር ፍርዱ ምሕ ረቱን እንደማይከለክለው ዕውቀቱም ፍርዱን ያጎ ጊዜው እንዲፈርድ ወይም ባልተሠራ ሥራ ላይ እንዲፈርድ አያደርገውም። እግዚአ ብሔር በባሕርይው ፍጹም ነውና። «እኔ ፍጹም እንደ ሆንኩ እናንተም ፍጹማን ሁኑ።» ማቴ.5÷48 እንዲል።

ስለዚህ እግዚአብሔር አዳም የሚሳሳት መሆኑን እያወቀ ሳጥናኤልም እንደሚበድል እንደሚያጸጸት እያወቀ መፍጠሩ

www.zeyeneta.com

የፍርዱን ርቱዕነት ያጠይቃል። ምክንያቱም ፍርድ በሠሩት ላይ ተመሥርተው የሚፈርዱት መሆኑን ስንኳን እግዚአብሔር ሰውም ያውቀዋልና።

እስራኤልንም ያዳናቸው የወደፊቱን በማየት ሳይሆን በጊዜው የነበሩበትን ሁኔታዎች ተመልከቶ ነው። እነዚህም የሚከተሉት ሦስት ዋና ዋና ነገሮች ናቸው።

1ኛ/ እግዚአብሔርን ስላልረሱት፦ እስራኤል ለብዙ ዘመን በግብፅ ቢኖሩም በሕግ በአምልኮ እግዚአብሔርን ያስታውሱት ነበር። ስንኳን እነርሱ አንዳንድ ግብፃውያንም የእስራኤልን አምላክ እግዚአብሔርን ሀውቀውት እስከ መፍራት ደርሰው እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳል። «እንዲህም ሆነ፥ አዋላጆች እግዚአብሔርን ስለ ፈሩ ቤቶችን አደረገላቸው።» /ዘጸ.1÷21/ እንዲል እነዚህ አዋላጆች የእስራኤልን ወንዶች ልጆች ወንድ ወንዱን እንዲገድሉ የተሾሙ ግብፃውያን ነበሩና። ይህም እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ዘንድ ባይረሳ፥ በሕግ በአምልኮ ቢታሰብ እንጂ ይህ ባይሆን ኖሮ እነዚህ አዋላጆች እግዚአብሔርን ሊፈሩት ቀርቶ ሊያውቁት አይችሉም ነበር።

2ኛ/ እግዚአብሔርን ስለለመኑት፦ እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮ ሳይረሱ ልመናን የሚያቀርቡት ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ጸሎታቸው ይደርሳል። «እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም፥ ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።» /መዝ.33÷4/ እንዲል እስራኤልም በግብፃውያን ከተፈጸመባቸው ግፍ የተነሣ አምርረው አለቀሱ፥ በአባቶቻቸው አምላክም ተመክተው እንዲቻለውም አምነው ለመኑት። «የእስራኤልም ልጆች ከባርነት የተነሣ አለቀሱ፣ ጮኹም፣ ስለ ባርነታቸውም ጩኸታቸው ወደ እግዚአብሔር ወጣ።» ዘጸ.2÷23-24 ተብሉ እንደ ተጻፈ ባርነትም የእስራኤል ገንዘባቸው አይደለምና

ይልቁንም ኃለሙን የፈጠረ የኃለሙ ጌታ ከእነርሱ ይወለድ ዘንድ ተስፋን ሰንተው ነበር አንጂ። ዘፍ 49 10።

3ኛ/ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ስለማይረሳ፦

እግዚአብሔር አስቀድሞ ለአብርሃም ከነዓንን ሰጥቶታል። ለዘሩም ሊያወርስለት ቃል ኪዳን ገብቶለታል። «አብራምም ሚስቱን ሦራንና የወንድሙን ልጅ ሎጥን፣ ያገኙትን ከብት ሁሉና በካራን ያገኟቸውን ሰዎች ይዞ ወደ ከነዓን ምድር ለመሄድ ወጣ፥ ወደ ከነዓንም ምድር ገቡ። እግዚአብሔርም ለአብራም ተገለጠለትና፦ ይህችን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ አለው።» /ዘፍ 12÷4-7/ እንዲል።

እግዚአብሔር ትዕቢተኛውን ፈርዖንና ሠራዊቱን መቦሳቱ፥ እስራኤልም መርጫቸውና መለመናቸው ሀበይት ነገሮች ቢሆኑም «ምድራቱን ለዘርህ እሰጣለሁ» ሲል የገባለትን ቃል ኪዳን ግን ትልቅ ዋጋ ሰጥቶታል። ይልቁንም ለራሱ ለአብርሃም አስቀድሞ እንደሚሰደዱ፣ አገዛዝም እንደሚያጸኑባቸው አርሱ ግን ወዳጁን አብርሃምን ሲል እንደሚያወጣቸው ገልጦለት ነበረ። «ዐሐይም በገባች ጊዜ በአብራም ከባድ እንቅልፍ መጣበት፥ እነሆም÷ ድንጋጤና ታላቅ ጨለማ ወደቀበት፥ አብራምንም አለው፦ ዘርህ ለእርሱ ባልሆነች ምድር ስደተኞች እንዲሆኑ በእርግጥ ዕወቅ፥ ባሪያዎች አድርገውም አራት መቶ ዓመት ያስጨንቋቸዋል፥ ደግሞም በባርነት በሚገዟቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርዳለሁ፥ ከዚያም በኋላ በብዙ ከብት ይወጣሉ። አንተ ግን ወደ አባቶችህ በሰላም ትሄዳለህ በመልካም ሽምግልና ትቀበራለህ። በአራተኛው ትውልድ ግን ወደዚህ ይመለሳሉ። የአሞራውያን ኃጢአት ገና አልተፈጸመምና።» ኩፉ. 15÷12-15 ተብሉ እንደ ተጻፈ።

ስለዚህ እግዚአብሔር እስራኤልን ሊያወጣ ይህን ቃል ኪዳን

www.zeyeneta.com

በማሰብ እንደ ነበር ተጽፏል። «እግዚአብሔርም የልቅሷቸውን ድምፅ ሰማ፣ እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አሰበ። እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች አየ፣ እግዚአብሔርም በእነርሱ ያለውን ነገር ዐወቀ።» /ዘጸ.2÷24-25/ እንዲል እግዚአብሔር ሁልጊዜ የሰው ልጆችን የሚረዳው ስለ እነርሱ ብቻ አይደለም ስለ አባቶቻቸውም ቃል ኪዳን ጭምር እንጂ፣ ኖኅን ስለ ጽድቁ ብቻ አይደለም፣ ለአዳም ስለ ገባው ቃል ኪዳንም ጭምር አዳነው እንጂ። ስለዚህ ሁልጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ቃል ኪዳን ይታሰባል፣ ዋጋውም ታላቅ ነው።

4.1.3. መንግሥተ ሰማያት፦-

ዕረፍት ዕለተ ሰንበት ብቻ አይደለችም። መካን /ቦታ/ ጭምር እንደ ሆነች ይልቁንም ለመካናቱ ጥንታቸው እንደ ሆነች ተመልክተናል። እግዚአብሔር በአንጻረ ሰንበት ከነዓንን እንዳስታወቃቸው በአንጻረ ከነዓን ደግሞ መንግሥተ ሰማያት መካነ ዕረፍታችን እንደ ሆነች ሲያስረዳን ዕረፍት እያለ በመጥራት አስታውቆናል። «ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ ቢፈጸም፦- እንዲህ፦- ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ እንዳለ÷ እኛስ ያመንን ወዲ ዕረፍቱ እንገባለን። ስለ ሰባተኛው ቀን በአንድ ሥፍራ እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ ብሏልና፣ በዚህ ሥፍራም ደግሞ፦- ወደ ዕረፍቴ አይገቡም። እንግዲህ አንዳንዶች በዚያ እንዲገቡ ስለ ቀሩ፣ ቀድሞም የምሥራች የተሰበ ከላቸው ባለመታዘዝ ጠንቅ ስላልገቡ፦- ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባ ችሁን እልከኛ አታድርጉ፣ በፊት እንደ ተባለ÷ ይህን ከሚያህል ዘመን በኋላ በዳዊት ሲናገር፦- ዛሬ ብሎ አንድ ቀን እንደገና ይቀጥራል። ኢያሱ አሳርፏቸው ቢሆንስ፣ ኖሮ ከዚያ በኋላ ስለሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር።» /ዕብ.4÷3-8/ በማለት ቅዱስ ጳውሎስ በኢያሱ ከተገኘው ዕረ

ፍት የበለጠ ዕረፍት እንዳለ የሚመክረው ስለ መንግሥተ ሰማያት ነው።

ምክንያቱም ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ኢያሱ ከነዓንን ካወረሳቸው በኋላ ነው። ይህ ደግሞ ከከነዓን የምትበልጥ ሌላ መካነ ዕረፍት እንዳለች የሚያመለክት ነው። ይህችውም መንግሥተ ሰማያት ናት። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልዕክቱም እያስረዳው ያለው የመንግሥተ ሰማያትን ነገር ስለሆነ «እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ፣ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ።» ዕብ.4÷1 ሲል ጀመረው። ይህንንም ቅዱስ ዮሐንስ «ከሰማይም ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ አዎን ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ ሥራቸውም ይከተላቸዋልና ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።» /ራእ.14÷13/ ሲል መንግሥተ ሰማያት መካነ ዕረፍት መሆኗን አረጋግጧል።

ቅዱስ ጳውሎስም በዚሁ 4÷9-10 ላይ «እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል። ወደ ዕረፍቱ የገባ፣ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ እርሱ ደግሞ ከሥራው ዐርፏልና።» በማለት ሕዝበ እግዚአብሔር ለምንባል ለእኛ ለእስራኤል ዘነፍስ ባለ ግለፍ ጸንታ የምትኖር ዕረፍቱ መንግሥተ ሰማያት እንዳለችልን ታወቀ ተረዳ። ለምን ቢሉ እግዚአብሔር ዐረፈ ሲባል ሥራውን /መፍጠሩን/ ፈጽሞ ባለግለፍ ጸንቶ በሚኖር መንግሥቱ አለ ማለት እንደሆነ ሁሉ የእርሱ ሕዝብም ዕረፍታቸው ባለግለፍ ጸንታ የምትኖር መንግሥተ ሰማያት ናትና። ጌታችንም በወንጌል «ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ።» /ማቴ.5÷11/ በማለት የጨዋ ግሥተ ሰማያትን ታላቅነት ነግሮናል።

መንግሥተ ሰማያት ለሕዝበ እግዚአብሔር የተዘጋጀች የዕረፍት

www.zeyeneta.com

በታ ታላቅ ዋጋ ብትሆንም ግን ዕብራውያን እርሷንም ሆነ ፈጣሪ ዋን፣ ሠሪዋን፣ አሳዳሪዋን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ቸል ብለው ነበር:: ቅዱስ ጳውሎስም የዕረፍትን አስፈላጊነት በአንጻረ ሰንበት÷ ከነዓንን ዕረፍት አድርጉ የሰጠ ወልደ እግዚአብሔርን ከነዓንን ካወረሱት ከሙሴና ከኢያሱ ጋር እያነጻጸረና እያመሳሰለ የሙሴን ትምህርት ቸል ያሉ አስራኤል ዘሥጋ ዕረፍቱን ከነዓንን ካልወረሱ፣ የወልደ እግዚአብሔርን ትምህርት ቸል የምንል እኛ በእርሱ የማናምንም ከመንግሥተ ሰማያት ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ቀርቶልን ከሆነ፣ ምናልባት ከእናንተ ሃንም የማይበቃ መስሉ እንዳይታይ እንፍራ:: «ወኢንኀድግ ትእዛዘ ከመ ንባዕ ውስተ ዕረፍቱ፣ ወደ ዕረፍቱ እንግባ ዘንድ ትዕዛዙን አናፍርስ::» 4÷1 ይለዋል:: ለመ ሆኑ በአንጻረ ከነዓን መንግሥተ ሰማያት መነገሯና ሙሴ ከክርስቶስ ጋር በምሳሌነት እንዲነጻጸር ያደረገው ምንድን ነው?

4.2.የከነዓን መንገድ መሪ ሙሴ ለመንግሥተ ሰማያት መሪ ምሳሌ ነው:-

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሙሴና ጌታችን እያነጻጸረ በ3÷2 መጀመሩ ለከንቱ አይደለም:: ከላይ በታሪኩ እንደተመለከትነው ሙሴ እስራኤል ዘሥጋን ብዙ ዓመታት የመከራ ጽዋን ከጠጡባት ከግብፅ፣ እገዛዝ ካጸነባቸው ከፈርዖን አላቅቋቸዋል:: ይህ ለእስራ ኤል ዕረፍት ነበረ፣ ነገር ግን በመንገድ ቀሩ እንጂ ከነዓንን አልወረሱም:: ክርስቶስም አዳምንና ልጆቹን ነፍሳቸው የመከራ ጽዋን ከጠጣችበት ከሲኦል፣ ስመ ግብርናታቸውን ጽፎ አንዱን በሲኦል አንዱን በዮርዳኖስ ጥሎ ሥጋቸውን በመቃብር ነፍሳቸውን በሲኦል ተቆራኝቶ እገዛዝ አጽንቶባቸው ከሚኖር ከዲያብሎስ አላቅቋቸዋል:: ስለዚህ በጊዜው ግብፅ የሲኦል፣ ፈርዖን የዲያብሎስ፣ እስራኤል ዘሥጋ የሕዝበ እግዚአብሔር ምሳሌዎች እንደ ነበሩ ሁሉ ከግብፅ

የወጣ ሙሴም ከሲኦል ያወጣን የክርስቶስ ምሳሌ ነበር::

እስራኤልን ሙሴ ከግብጽ ቢያወጣቸውም በመንገድ ላይ ሳሉ ባልጠመናቸውና ባለመታዘዛቸው ምድረ ርስት ከነዓንን ሳይወርሷት በለፍዐ በምትሆን በምድረ በዳ ቀሩ:: አይሁድም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥንተ አብሶን በደሙ አርቆላቸው ሞተ በጥምቀት ልጅነት በሥጋወደሙም ሕይወት እንደሚገኝ ባለ ማመናቸው ለመንግሥተ ሰማያት አፍዐ በምትሆን በገሃነም ልመጣላቸው ምሳሌ ስለሆነ፡ ይህን በማስታወስ እያነጻጸረ ይጽፋል:: ዝንቱ ኩሉ ዘረከቦሙ ለእልክቱ ምሳሌ ተጽሕፈ ለእለምሮ መለተግሠጸ ዚአነ እለ በደኃሪ መዋዕል:: እነዚያ ያገኛቸው መከራ ኹሉ ዋኋላ ዘመን ለምንኖሣ ለእኛ ምሳሌ፣ ምክር፣ ዕዝናት ሊሆነን ተጻፈ::» 1ኛቆሮ.10÷11 የተባለው ለዚህ ነው::

ይሁን እንጂ ባለቤት ከቤቱ፣ ጌታም ከአገልጋዩ እንዲበልጥ ክርስቶስ ከሙሴ ይበልጣል አለ:: ዕብ.3÷3:: የጌታችንን ከሙሴ መብለጥ በንጽጽር እንመለከተዋለን::

የሙሴ ልደቱ በእናቱ ቤት ነበር:: ሦስት ወርም በእናቱ ቤት ተሸሽጎል፡ ከዚያም በኋላ ገና ወደ ባሕር እንደ ተጣለ የፈርዖን ልጅ አስወጥታ በእናቱ ሞግዚትነት አድጓል:: ዘጸ.2÷1-10:: ጌታችን ግን በከብቶች በረት ተወለደ፡ ከዚያም ወደ ግብጽና ኢትዮጵያ ተሰደደ ማቴ.2÷13፣ ዕን.3÷7:: ሙሴ እድገቱ በቤተ መንግሥት በንጉሡ በፈርዖን ዘንድ ነበረ:: ዘጸ.2÷10:: ጌታችን ግን በድኾች መንደር በናዝሬት ከተማ አደገ:: ለእናቱ እየተላላከ፣ እንደ አላዋቂም ከመምህራኑ አይሁድ እየተማረ አደገ:: ማቴ.2÷23፣ ሉቃ.2÷39-52::

ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት, ያወጣቸው ዘንድ በእግዚ አብሔር ተመረጠ፣ ተጠርጦ ተሾመ፡ ዘጸ.3÷1-2፣ ሐዋ.7÷35::

www.zeyeneta.com

ጌታችን ግን ሥልጣኑ የባሕርይ ገንዘቡ ነው። የሙሴም ኗሚ እግዚ አብሔር ጌታ ነው። «አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል።» ዮሐ.5÷22፣ «አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል።» ዮሐ.3÷34።

ሙሴ የጌታችንን ማንነት አስቀድሞ ሊገልጥ የተላከ የእርሱ መልእክተኛ ነው፣ «ሙሴ በሕግ ነብያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው።» ዮሐ.1÷46 እንዲል። ራሱ ጌታችንም «እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፣ የሚከሳችሁ አለ፣ እርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው። ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፣ እርሱ ስለ እኔ ጽፏልና።» ዮሐ.5÷45 ብሏል። ስለዚህ ሙሴ የእግዚአብሔር መልእክተኛ እንደ መሆኑ መጠን መና ሲያወርድላቸውም ውኃ ከዓለት ሲያፈልቅላቸውም ከእግዚአብሔር የተዘጋጀላቸውን አሳልፎ በመስጠት እንጂ ከእርሱ የተገኘ ገንዘቡን አልሰጣቸውም።

ባለቤቱ መጋቢያቸው ግን እግዚአብሔር ነው። «እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም።» /ዮሐ.6÷32/ ሲል በአባቱ ሕልው ሆኖ በእንዲት ሥልጣን መስጠቱን ተናግሯል። ይልቁንም በሙሴ የተሰጣቸው እንጀራ ርሃብ ሥጋን እንጂ ርሃበ ነፍስን አላስወገደምና፥ ዛሬ በልተውት ነገም ይራቡ ነበርና እውነተኛ እንጀራ አድርጉ የማያስርብ ምግብ ሥጋውን ደሙን የሰጠን መሆኑን ተናገረን። «እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።» ዮሐ.6÷51፣ «ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፣ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፣ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል።» ዮሐ.6÷58 እንዲል።

ስለ ጠጡት ውኃም ሲናገር ቅዱስ ጳውሎስ «ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ፣ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፥ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዐለት ጠጥተዋልና፣ ያም ዐለት ክርስቶስ ነበረ።» /1ኛቆሮ.10÷4/ በማለት ሙሴን አሳላፊ አድርጉ በረድኤት በጸጋ የሚመግባቸው ዐለት የተባለ ጌታችን እንደ ሆነ አስረግጧል። ስለዚህም ነው ጌታችን በወንጌል «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፣ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።» ዮሐ.6÷35 ሲል ከሙሴ ይልቅ መጋቢ ሥጋ ወነፍስ መሆኑን አስተማረን።

ሙሴ ፍጡር ነው፣ ሰው ነውና የእግዚአብሔር ቤቱ ነው። 1ኛቆሮ.3÷16። ጌታችን ግን ሙሴን ያዘጋጀ የቤቱ ባለቤት ነው። ዘፍ.2÷8፣ ዕብ.3÷3። ሙሴ በመልአኩ እጅ ተሾመ ሐዋ.7÷35። እሥራኤልን ከግብፅ አወጣቸው እንጂ እርሱ ከነዓንን አላያትም ሌሎቹንም አላወረሳቸውም። ጌታችን ግን የሰማያት ፈጣሪ /ዘፍ.1÷1/፣ በሕልውናውም አድሮባቸው የተደረገላቸውን አምነው ለተከተሉት ምእመናን ነፃት መንግሥተ ሰማያትን በማውረስ የታመነ ነው። «ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» ሉቃ.23÷43 እንዲል። ሙሴ እሥራኤልን ከግብፅ መርቶ በማውጣቱ፣ ከፈርዖንና ከሠራዊቱ በማላቀቁ ጌታችን ነፍሳትን ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ ለማላቀቁ ከሲኦልም ለማውጣቱ ምሳሌ ይሁን እንጂ ሙሴ ቤት፣ ጌታችን ግን የሙሴ /የቤቱ/ አዘጋጅ ባለቤት ነውና፣ ሙሴ ተላኪ፥ አላላፊ፥ መጋቢ፣ ጌታችን ግን ሙሴን የላከ በእርሱም አላላፊነት ሕዝቡን የመገበ ባዕለጸጋ ነውና እጅጉን ከሙሴ ይበልጣል።

ቅዱስ ጳውሎስ «የሃይማኖታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤» /ዕብ.3÷1/ ያለው እስራኤል መሪያቸውን ሙሴን፣ መልእክተኛውን ሙሴን ፥ሰምተውና ተከትለው ከመጡ

www.zeyeneta.com

፣ የሙሴ ላኪና አዘጋጅ አካላዊ ቃል ሰው ሆኖ ሐዋርያችን /መሪያችን ፈታውራሪያችን/ ሆኖ ሲመጣ አብዝተን ልንሰማውና ልንከተለው ይገባል፤ የሙሴ ጌታ ነውና ሲል አስተማረ። መብለጠ ንም በአጭሩ «ሙሴ ደግሞ በቤቱ ሁሉ የታመነ እንደ ሆነ፣ እርሱ ለሚመው የታመነ ነበረ። ቤትን የሚያዘጋጀው ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው መጠን እንዲሁ እርሱ ከሙሴ ይልቅ የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኖ ተቆጥሯልና። እያንዳንዱ ቤት በአንድ ሰው ተዘጋጅ ቷልና፣ሁሉን ያዘጋጀ ግን እግዚአብሔር ነው። ሙሴስ በኋላ ስለሚነገረው ነገር ምስክር ሊሆን በቤቱ ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበረ፤ ክርስቶስ ግን እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው፤ እኛም የምንደፍርበትን የምንመካበትንም ተስፋ እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ ቤቱ ነን» ዕብ.3÷2–6 ሲል አስቀምጦታል።

ይልቁንም ደግሞ ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ በማውጣቱ ከፈርዖንም በማላቀቁ ለእነርሱ ያስገኘው ዕረፍት የሥጋ ዕረፍት ብቻ ነው። ጌታችን ያስገኘው ዕረፍት ግን ከሲኦል ባርነት ለተላቀቁት የነፍስ ዕረፍት በዚህ ምድር ላይ ለምንኖር ለእኛ ለክርስቲያኖች ደግሞ የኀሊናና የመንፈስ ነጻነትን ያስገኘ ውላጣዊ ዕረፍት ነው። ይህንንም ዕረፍት የማግኘታችን ዜና ብሥራት የጌታችን ትንሣኤ ነው። ዕለተ ትንሣኤው የሆነችውን እሑድን ሰንበተ ክርስቲያን በማለት በኀሊናና በመንፈስ ነገረ እግዚአብሔርን ለማዘከር ብቻ እንጠቀምባታለን። «የጌታ ቀን» /ዮሐ.1÷8/ ተብላለችና። «ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፣ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።» /ዮሐ.4÷23–24/ እንዲል።

በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት ያስፈልጋል ሲል በክርስቶስ

ከሰይጣን ቁራኝነት በመላቀቅ የተገኘው እውነተኛ ዕረፍት የልብ፣ የኀሊና ዕረፍት.ለዚህ መንፈሳዊነት እንዳበቃን ለመናገር ነው። ስለዚህም ክርስቶስ በእጅጉ ከሙሴ ይበልጣል፤ የተነጻጸሩትም የሙሴን ታላትነት ለሚቀበሉና ጌታችንን «አምላክ ነው» ብለው ላልተቀበሉት ለዕብራውያን ለማስረዳት ለማሳመን እንጂ ቀድሞውኑ ለሚያምኑትማ ሙሴ ከክርስቶስ ጋር ይነጻጸር ዘንድ የሚገባ አይደለም። ፍጡሩን ከፈጣሪው ጋር ቀርቶ ሽክላን ከሠሪው ጋር የሚያነጻጽር የለምና።

4.3. ወደ ዕረፍቱ እንድንገባ ምን እናድርግ

ቅዱስ ጳውሎስ ታሪኩን ተረከ። ነገሮችን በማነጻጸር የጻፈው የተጻፈልን ሰዎች ማድረግ የሚገባንን እንድናደርግ ነው። በመሆኑም እኛ የክርስቶስን ታላትነትና የባሕርይ አምላክነት ከዐወቅን ከተ.ዳን በሙሴ ተመርተው ከወጡ በኋላ ለሙሴ ባለመታዘዝ ምድረ በዳ ከቀሩ ከእስራኤል ዘሥጋ መብለጥ አለብን። «ጽድቃችሁ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን ጽድት ካልበለጠ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።» ማቴ.5÷20 ተብለናልና። ወደ መንግሥቱ እንገባ ዘንድ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

ሀ/ ማመንና መታመን፦ ማመን÷ ይሆናል ይደረጋል ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ብሎ መቀበል ሲሆን መታመን ደግሞ ይሆናል፣ ይደረጋል ያሉትን ለማግኘት የሚፈጽሙት የእምነት መግለጫ ደገኛ ምግባር ነው። «በጠበል ከደዌ ሥጋ መፈወስ ይቻላል» ማለት ማመን ነው፤መጠመቅ ግን መታመን ነው። ለመፈወስ የፈጸሙት ተግባራዊ ምላሽ ነውና።

ስንኳን እስራኤል ዘነፍስ እስራኤል ዘሥጋም ዕረፍት የተባለች ከነዓንን ሳይወርሱ የቀሩት ባለማመን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እግዚአብሔር በእስራኤል ዘሥጋ ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብሎ የማለባቸው ባለማመናቸው ምክንያት እንደሆነ ገልጦልናል። «ሰምተው

www.zeyeneta.com

ያስመረሩት እነማን ነበሩ? ባመሲ ተመርተው ከግብጽ የወጡ ሁሉ አይደሉምን? አርባ ዓመትም የተቆጣባቸው እነማን ነበሩ? ሬሳቸው በምድረ በዳ የወደቀ፣ ኃጢአትን ያደረጉት እነርሱ አይደሉምን? ካልታዘዙትም በቀር ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ? ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን::»ዕብ. 3÷16–19:: ላለመታዘዛቸው ሁሉ ምንጩ አለማመናቸው አለመታመናቸውም እንደሆነ በግልጽ አስቀምጠልናል::

ማመን የነገር ሁሉ መሠረት ነው:: ሌላው ቀርቶ የዚህ ዓለም ሰው በታመመ ጊዜ ሐኪም ያዘዘለትን መድኃኒት የሚወስደው ሐኪሙን ካመነ ብቻ ነው:: ሐኪሙን ከበሽታዬ የሚፈውስ መድኃኒት አዝዞልኛል በማለት ካልተቀበለው መድኃኒቱን ሊወስደው አይችልም:: ማመኑ ሲቀድም መታመኑም ይከተላል:: ያለ እምነት መታመን የለም፣ መታመን የሌለው እምነትም ካለማመን አይሻልም::

እስራኤል የሙሴን ቃል ባለማመናቸው አልታዘዙትም /አልታመኑም/:: ስለዚህም ወደ ከነዓን አልገቡም፣ እነርሱ እንዲህ ከተቀጡ እኛ የሥግው ቃልን ትምህርት ሰምተን ካልታዘዘን እንደ ምን አይፈረድብን? ዘኍ.13÷25፣ 14÷30:: እነርሱ የሙሴን ቃል ባለማመናቸው ጠንቅ ከከነዓን ከተከለከሉ እኛማ የጌታን ቃል ሰምተን ቸል ካልነው ከመንግሥተ ሰማያት እንደ ምን አንከለከል? ለማለት ነው ቅዱስ ጳውሎስ ሰብራውያን በጌታችን ያምኑ ዘንድ የእነዚያን የአለማመን ውጤት እየገለጸ የሚያስረዳቸው::

ለ/ መታዘዝ:– ሕግ÷ ሐገገ፣ ገሠጸ፣ አታድርግ አለ÷ አታድርግ ያለበት፣ አንድ ድርጊት እንዳይደረግ የሚከለክል ሥርዓት ማለት ነው:: ሕግ የሚባለው አታድርግ የሚሉት የሥርዓት አንቀጾች ናቸው:: ለምሳሌ ያህልም አትስረቅ፣ አትግደል፣ አታመንዝር፣ በሐሰት አትመስክር... የመሰሉት:: እነዚህን በመጠበቅ ወይም አታድርግ

የተባለውን ባለማድረግ ብቻ ሰው ወደ ጽድት ወይም ወደ መካነ ፅድ ፍት ሊገባ አይችልም::

አታድርግ የተባለውን እንደ ጠበቀ ሁሉ አድርግ የተባለውንም መፈጸም ሲችል ነው እንጂ:: ሰው እንኳን የታዘዘውን ሳይፈጽም ጎሊናው እንዲያደርገው የነገረውን በጎ ነገርም ካልፈጸመው ኃጢአት ይሆንበታል:: «እንግዲህ በጎ ለማድረግ ዐውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው::» ያዕ.4÷17 እንዲል:: ስለዚህ አምላካችን እግዚአ ብሔር እኛን ትእዛዙን እንድንፈጽምለት ይፈልጋል:: ትእዛዙም ከባድ እንዳልሆነ ነግሮናል:: «እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ÷ ወደ እኔ ኑ፣ እኔም አሳርፋችኋለሁ:: ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፣ እኔ የዋህ በልቤም ትኁት ነኝና፣ ለነፍሳ ችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፥ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና::» ማቴ.11÷28–30 እንዲል::

ቅዱስ ጳውሎስም ይህን ቀሳል የሆነውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባለመፈጸማቸው ወደ ዕረፍቱ እንዳልገቡ በማስታወስ ዕብራውያንን ይመክራል:: «ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ የምሥራች ተሰብኮልናልና፣ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም::» /ዕብ.4÷3/:: እግዚአብሔር ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ያለባቸው አለመታዘዛቸው ነው:: እግዚአ ብሔር ለሙሴ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ከ12ቱ ነገድ አንድ አንድ ሰው ተመርጠው ምድረ ርስትን በ40 ቀን ሰልለው መጥተዋል:: ከዚህ በኋላ ሕዝበ እስራኤልን እንዲሄዱ አዘዛቸው:: ከመልእክተኞቹ አሥሩ ግን ፈርዖንና ሠራዊቱን ያሰጠመላቸውን እግዚአብሔርን ረስተው እምቢ ኤሉ÷ አጉረመረሙ÷ በሙሴና በአሮን በኢያሱና በካሌብም ላይ በጠላትነት ተነሡባቸው:: ስለዚህ እነርሱ ባለመታዘዝ ጠንቅ ሳይገቡ በበረሃ እንደ ቀሩ እኛም ባለመታዘዝ ከመንግሥተ ሰማያት

www.zeyeneta.com

በአፍአ እንዳንተር እንፍራ አላቸው። «...ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ።» ዕብ.4÷1።

ሐ/ አለመፍራት፦ ፍርሃት ያለማመን፣ የፍቅር ማጣትም ምልክት ነው። ስለዚህ ፍርሃትን ማራት የክርስቲያኖች ተግባር መሆን አለበት። ቅዱሳን መላእክትም የሰው ልጆችን ሲያበሥሩ አስቀድመው የሚናገሩት ፍርሃትን ስለ ማራት ነበረ። ሉቃ.1÷13፣ 30። እርግጥ የቅዱሳን ድንጋጤና ፍርሃት የተጎተና ነው። በማይ ገባው የሚፈራ ክርስቲያን ጽድቅን ሊፈጸም አይችልም። ኃጢአት ሞትን እንደሚያስከትል ሁሉ ሞተ ሥጋን መፍራትም ኃጢአትን እንድንሠራ ያደርገናል። ለዚህም ነው ጌታችን በወንጌል «ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፣ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።» /ማቴ 10÷28/ ሲል መፈራት የሚገባው እግዚአብሔር እንጂ ሞተ ሥጋ እንዳልሆነ ያስተማረው።

እስራኤል ዘሥጋ ርስታቸውን ሳይወርሱ ከቀሩባቸው ዐበይት ምክንያቶች አንዱ ፍርሃት ነበር። «ካሌብም ሕዝቡን በሙሴ ፊት ዝም አሰኘና፦ ማሸነፍ እንችላለንና እንውጣ÷ እንውረሰው አለ። ከእርሱ ጋር የወጡ ሰዎች ግን በኃይል ከእኛ ይበረታሉና በዚህ ሕዝብ ላይ መውጣት አንችልም አሉ።» ዘኍ.13÷31። ይህን ሲናገሯቸው ሕዝቡም ፈሩ÷ በሙሴና በአሮን ላይ አመፁ÷ በእግዚአብሔርም ፊት አጉረመረሙ። እግዚአብሔርም ተቆጣ። «እኔ ሕያው ነኝና በጆሮዬ እንደ ተናገራችሁት እንዲሁ በእውነት አደርግባችኋለሁ ይላል እግዚአብሔር፣ በድኖቻችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃሉ የተቆጠራችሁ ሁሉ÷ እንደ ቁጥራችሁ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ከዚያም በላይ የሆነ ሁሉ÷ እናንተ ያጉረመረማችሁብኝ÷ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በቀር በእርስዋ አስቀምጣችሁ ዘንድ

እጄን ዘርግቼ ወደ ማልሁላችሁ ምድር በእውነት አናንተ አትገቡም።» /ዘኍ.14÷28–30/ እንዲል። እግዚአብሔር ወደ ዕረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ኃይል አቅልለው ስለ ፈሩ ነው።

ፍርሃት ሁልጊዜም ኃጢአትን ያመነጫል፣ እንድንበድል ያደርገናል። ጴጥሮስ ጌታችን በተያዘበት ዕለት ጌታችንን «አላው ቀውም» ለማለት የበቃው ስለ ፈራ ነበር። ማቴ.26÷69–75። ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ገንዘብ ካደረገ በኋላና ፍርሃት በራቀለት ጊዜ የኃጢአት አለቆችና የመቅደስ አዛዥ ሰዱቃውያንም ስለ ጌታችን እንዳያስተምሩ ፍጹም ማስጠንቀቂያ ቢሰጧቸውም አልተቀበለውም። «መርተውም በኢየሱስ ስም ፈጽመው እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዟቸው። ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው፦ እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደሆነ ቍረጡ፣ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት አንችልም አሏቸው።» ሐዋ.4÷18–20 እንዲል።

ሐዋርያትም በሙሉ ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ፍሩሃን የነበሩ ጥቡአን /ደፋሮች/ ስለሆኑ ነው መንግሥተ ሰማያትን የሰበኳትና ይወርሷትም ዘንድ ተስፋ ያደረጓት። ስለዚህ እኛም እስራኤል ዘነፍስ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት እንድንገባ ሞትን መፍራት የለብንም፣ ያን ጊዜ ከኃጢአት በእርስዋም ከምትመጣ ዘላለማዊ ሞት እንጠበቃለንና። «ሞት ሆይ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ÷ ድል መንሣትህ የት አለ? የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው። ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።» 1ኛቆሮ. 15÷55–57።

www.zeyeneta.com

4.4. እግዚአብሔር አዳምን ወደ ዕረፍቱ /መንግሥተ ሰማያት/ እንዲገባ ስለ ምን ፈቀደለት?

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በአምሳሉና በአርአያው ከፈጠረው በኋላ ንጽሕናውን ቅድስናውን ገንዘብ አድርጉ ሰባት ዓመት በገነት ተቀምጧል። በኋላ ግን የማይገባውን አምላክነት ሽቶ በድሏል፡ እግዚአብሔርም እንደ ቃሉ ፈርዶበታል። ከገነትም አስወጥቶታል። ታዲያ ስለ ምን እንደገና በነፍሱ ወደ ገነት መለሰው? መንግሥተ ሰማያትንስ እንደሚያወርሰው ስለ ምን ተስፋ ሰጠው? የሚሉ ጥያቄዎችን ማንሣት አስፈላጊ ነው። በእርግጥ ይህን ምሥጢር ተናግሮ መጨረስ የማይቻል ቢሆንም ቀደም ብለን «ዓለ ሙን ስለ ምን አዳነው? ካልነው ውስጥ የተጠቀሱትን በመጠኑ እንገልጣለን።

ሀ/ አዳም ፍጹም ንስሐ ስለገባ፡– ፍጹም ንስሐ የሚባለው በፍጹም ልብ በጎሊና ሳያመጡ ሳያወርዱ እግዚአ ብሔርን በድያለሁ ብሎ መናዘዝና በቀኖና ራስን ማስገዛት ነው። ይህም ምግባራት ሠናያትን ገንዘብ አድርጉ መለመን ነው። እነዚህም ትኅትና /ባለፈው መአጸት/፣ የዋሕት /ከሚመጣው መጠበቅ/፣ ድኂን እም ኃጢአት /የቀደሙትን እንደገና ከመበደል መጠበቅ/ ናቸው። «መአ ልቡቱ ካልዕ ጎሊና ለአዳም ዘእንበለ ብካይ ላዕለ ኃጢአቱ» እንዲል መቅድመ ወንጌል። አዳም ስለ ኃጢአቱ ከማልቀስ፣ ከማዘን፣ ከመጸጸት በቀር ሌላ ግዳጅ አልነበረውም። ይህም ማለት አዳም በገነት የነበረ ክብሩን ጌትነቱን እያሰበ ይህን አጣሁት እያለ ሳይሆን ፈጣሪዉን አሳዘንኩት እያለ ያዝን ነበርና። መቅደመ ወንጌል የአዳም ንስሐ ፍጹም መሆኑን ሲናገር «ወገዓረ ብካዩ ለኃጢሠ ሥርየት» ኃጢአቱ እንዲሠረይለት፣ ኃጢአቱን ሊያስተሠርይለት ወደሚቻለው እየተጨነቀ በማልቀሱ ነው።» በማለት ገልጦታል።

ለ/ ክፋት ለአዳም የባሕርይ ገንዘቡ ስላልሆነ

ክፋት የባሕርይ ገንዘባችን አይደለም። ኃጢአትን ከራሱ ያመነጫት ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ ነው። አዳም በእርሱ ምክር ተታሎ ተሳሳተ እንጂ እንደ እርሱ ከሙስሐ አመንጭቶ አምላኩን አልበደለም። «ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፡ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።» 1ኛዮሐ.3÷8፡ «እናንተ ከአባ ታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፡ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበረ፡ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፣ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።» ዮሐ.8÷44 እንዲል የሐሰት አባት የኃጢአት ሁሉ ምንጭ ሰውንም ትዕቢትና ክፋት ያስተማረ ዲያብሎስ እንጂ ሰው አይደለም።

ይህን የባሕርይው ያልሆነን ክፋት ስለ ተዋሐደ ነበር አምላካችን በተዋሕዶ ኃጢአትን አስወገዶ እኛም እርሱን ተዋሕደነው እንድንኖር ሥጋውንና ደሙን መብል አድርጉ የሰጠን። «የዲያብሎስን ሥራ ያፈርስ ዘንድ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ።» 1ኛዮሐ.3÷9 እንዲል። አዙንም አዙን ግን እንዳንድ ሰዎች ሌሎቹን ሰዎች ሲፈጠሩ ከፍተው እንደ ተፈጠሩ ያለበለዚያም ክፋት የባሕርያቸውና በዘር የሚተላለፍ በሽታ እንዲያውም የቤታቸው ጣጣ አድርገው ሲመለከቱ ይሰማል። ይህ ፍጹም ከሀዲት ነው።

በእውነት ሰውን በክፋት ተፈጥሯል ማለት ፈጣሪውን መሳደብ ሲሆን ክፋትም ተዋሕዶት በዘር ይተላለፋል ማለት ክርስቶስ እኛን በመዋሐድ ያራቀልንን ቁራኝነት አላስለቀቀውም እንደ ማለት ያለ ነው። ክፋትንም የሰው የባሕርይ ገንዘብ አድርጉ ማሰብ፣ ሰውን እንደ ዲያብሎስ መቁጠርና የእግዚአብሔርንም ፍርድ የተዛባ ነው ከማለት ያደርሳል። ሁለቱም ከባሕርያቸው አመንጭተው በድለው ሳለ ሰውን ብቻ ለምን ለይቶ ፈጻነው ያሰኛልና። እግዚአብሔር ሰውን ያዳነው፣ ዛሬም እየበደልነው የማይጸየፈን ክፋትና

www.zeyeneta.com

በደል ተፈጥሯዊ ባሕርያችን ስላልሆነ ነው።

ሐ/ እግዚአብሔር ፍጹም መሐሪ ስለሆነ

ምንም እንኳ ሰው በደሉ የባሕርይው ባይሆንም፣ ፍጹም ንስሐ ቢገባም እንኳን «አምላክነትን መሻት»ን ያህል ታላቅ ኃጢአት አልነበረም። ንስሐውም ከዚያ በላይ ሊያደርገው የሚቻለው አለመኖሩ ነው እንጂ ኃጢአቱን ሊያመዝናት የበቃ ሆኖ አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር የአዳምን ንስሐ በተመለከተ ጊዜ አዘነለት፣ ሊያድነውም ፈቀደ። «ወፈቀደ ያድኅና እምትኃጹ በእንተ ፪ ገጸት በፀዱ በእንተ ንስሐሁ ወግኅረ ብካዩ ለኃጢአ ሥርየት ወረሲአቱ ገነተ ወፍግዓሁ ወተድላሁ፣ ወካልዕሰ በእንተ ዘተትኅተ ወእቱ ተትኅቶተ፣ ስለ ሁለት ነገር /በአዳም ንስሐ ስለ ታዩት/ ሊያድነው ወደደ። የመጀመሪያው ያጣት ገነትን ተድላውን ደስታውን ዘንግቶ ኃጢአቱን እንዲያስተሠርይለት እየተጨነቀ በግልቱ አላበጀውም ብሎ በመጸጸቱ፣ ሁለተኛውም በፍጹም ተዋርዶ ራሱን በማዋረዱ» ሲል መቅድመ ወንጌል አስተምጦልናል።

ይህም ለአዳም በደል ለመካሥ የሚበቃ ሆኖ አይደለም፣ የእግዚአብሔር መሐሪነት በንስሐ የሚገኝ መሆኑን ለመናገር ነው እንጂ። ስለዚህ እግዚአብሔር በፍጹም ምሕረቱ እንዳዳነን መገንዘብ ያስፈልጋል። «ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፣ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን።» ሮሜ. 5+10 እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ። እግዚአብሔር ገጸ ምሕረቱን የሚያዞረው ግን ለተነሣሕያን መሆኑን በውል መገንዘብ ያስፈልጋል።

4.5. የምዕራፉ የማጠቃለያ ጭብጥ

በዚህ ምዕራፍ ቅዱስ ጳውሎስ የዕረፍትን ነገር ተንትኖ የእስራኤል ዘሥጋን ጉዞ ለእኛ ለእስራኤል ዘነፍስ ምሳሌ አድርጉ ጌታችንን ከሙሴ ጋር እያነጻጸረ የጻፈበት ትልቁ ዓላማ ከፈርዖን ዲያብሎስ እንደሚከፉ ከግብፅም ገሃነም አሰቃቂ እንደ ሆነች ተገን

ዝበን፣ በሙሴ ፈጣሪ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከባሕረ ኤርትራ የሚጸና ባሕረ እሳት ተከፍሎልን መሻገራችንን ተገንዝበን፣ ከክነዓን የምትበልጥ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ በምናደርገው የነፍስ ጉዞ ጥምቀትን፣ ሥጋ ወደሙንና ንስሐን ባለማመንና ባለመታዘዝ እስራኤል ከወደቁባት ምድረ በዳ በተመሰለች ገሃነም እሳት እንዳ ንቀር ማስገንዘብ ነው።

እስራኤል ከግብጽ ወጥተዋል+ ከፈርዖንም ተላትቀዋል፣ ከነዓንን ግን አልወረሱም። እኛም ጥንተ አብሶ ተወግዶልን ከዲያብሎስ ቁራኝነት ተላቀናል፣ ነገር ግን መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የሚጠበቅብን ነገር አለ። ከሰረፍት በፊት ሥራ አለ። ከመንግሥተ ሰማያትም በፊት በምድራዊ ቆይታችን ሃይማኖት መያዝ ምግባር መሥራት ይጠበቅብናል። ያለ ሥራ ዕረፍት እንደ ሌለ ያለ እምነትና ምግባር መንግሥተ ሰማያትን መዋረት አይቻልም።

ይህንም ለመፈጸም የሃይማኖት ትምህርት መማር፣ እየሰ ሙም በምግባር መትጋት ያስፈልጋል። አልያ አሁን በመምህራን የሚሰጠውን ትምህርት፣ በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈልንን ምክር የማንሰማ፣ ሰምተንም የማንፈጽመው ከሆነ እረኛ በጉቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርሱም ኃጥኣንን ከጻድቃን ለይቶ በገሃነም ያስቀረናል። «እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ። የእግዚአብሔር ቃል /አካላዊ ቃል/ ሕያው ነውና፣ የሚሠራም፣ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል+ የልብን ስሜትና አሳብ ይመረምራል+ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፣ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።» እንዲል። ዕብ.4+11–13፣ ዕን.3.5+11–14።

ማስገንዘቢያ፡– ቁጥር 11ን በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ አካትተን እንመለከተዋለን።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ አምስት

አማላጅ

በዚህ ምዕራፍ ከቁ.1–6 ያለው ከህነትን የሚመለከት ስለሆነ በምዕራፍ ሦስት ላይ ታይቷል። ከቁጥር 11–14 ያለውን ደግሞ ምክር ስለሆነ በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ ላይ ብንመለከተው የበለጠ ግልጽነት ይኖረዋል። አሁን ራሱን አስችለን የምንመለከተው የአ ማላጅነትን ጉዳይ ሲሆን መነሻችንም በዚህ ምዕራፍ ከቁ.7–10 የተጠ ቀሱት ኃይለ ቃላት ናቸው። ምልጃን የተመለከተን ሁሉ በዚህ ምዕራፍ ሥር እንመለከታለን። ለአብነትም ዕብ.7÷25፣ ሮሜ.8÷34፣ 1ኛጢሞ.2÷5፣ ሮሜ.8÷26 1ኛዮሐ.2÷1 የመሰሉትን እንመለከታለን።

«እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ÷ እግዚ አብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤ ምንም ልጅ ቢሆን÷ ከተቀ በለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤ ከተፈጸመም በኋላ በእግዚአብሔር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ሊቀ ካህናት ተብሎ ስለ ተጠራ÷ ለሚታዘዙለት ሁሉ የዘላለም መዳን ምክንያት ሆነላቸው።» ዕብ. 5÷7–10። ይህን የመሰሉ ጥቅሶችን በማንሳት ሉተራውያን ጌታችንን አማላጅ ነው /ሉቱ ስብሐት/ በማለት ያስተምራሉ። ለመሆኑ ማማ ለድ ምንድን ነው? በምልጃ ውስጥ ስንት አካላት ይሳተፋሉ? ኢየሱስ ክርስቶስስ ሰው የሆነው ስለዚህ ነውን? የሚሉትንና መሰል ጥያቄዎችን በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት መግንዘብ ያስፈልጋል።

5.1. <u>ትርጉም</u>፦– ተንበለ፦–ለመነ አማለደ ከሚለው ግስ ተንባሊ፦–የሚለምን የሚጸልይ፣ ማላጅ፣ አማላጅ አቆላማጭ የሚል የግብር ስም ይወጣል። ስለዚህ አማላጅ ማለት በሁለት አካላት መካከል ገብቶ አንዱን ስለ ሌላው የሚለምን ማለት ነው። ከዚህ

አንጻር ጌታችንን በግብር ስም አማላጅ የሚሉት ሰዎች « ኢየሱስ ስለ ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚለምን የሚጸልይ ነው» ማለታቸው እንደሆነ እንገነዘባለን። የጸፉትም ይህንኑ ነው። እኛ ግን ክርስቶስ ንው ጎቤየ ሑሩ እምኔየ- ወደ እኔ ኑ÷ ከእኔ ሂዱ/ ብሎ የሚፈርድ፣ ቀድሞውንም የሚግለድ የሚለመን እንጂ የሚግልድ የሚለምን አይደለም ብለን እናምናለን፤ ቅዱሳት መጻሕፍትም ይህንኑ ያስረግጣሉ።

5.2. በምልጃ ወቅት የሚሳተፉ አካላት፦–

በምልጃ ውስጥ የተለያዩ እኔ ባይ አካላት እንዳሉ ለመረዳት የሚያዳግት አይደለም። ምክንያቱም ምልጃ አንዱ ስለ ሌላው የሚያቀርበው ልመና ነውና የሚለምን፣ የሚለመንለት፣ የሚለመን ሦስት አካላት ይሳተፉበታል።

ሀ/ <u>የሚለመነው /የሚግለደው/</u>፦– ይህ አካል የመፍረድ ሥልጣን ያለው የፈቀደውን ያደርግ ዘንድ የሚቻለው አካል ነው። በነገረ ድኅነት ለሚፈጸመው ምልጃ ይህ አካል እግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሁልጊዜም የሚለመን እንጂ የሚለምን አይደ ለም። ለሰውም ሁሉ እንደ ሥራው መክፈል የሚቻለው፣ የሁሉም ዋጋ በእርሱ ዘንድ ያለ፣ የሚተካከለው የሌለ፣ ባዕለ ጸጋ ጻኛ፣ እውነተኛ ፈራጅ አምላክ ነውና። «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፣ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።» ራዕ.22÷12፤ «እነሆ÷ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዙም በፊቱ ነው።» ኢሳ.40÷10፤ «ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል።» እንዲል። መዝ.49÷2።

ለ/ <u>የሚለምነው /የሚግልደው/</u>፦– ይህ ደግሞ ከተለማኙ ጋር በቅርብ የሚተዋወቅ፤ እውነቱን ለማስረዳት የበቃ፣ ይቅርታ ሊያሰጥ የታመነ፣ ይልቁንም ከተሟጋጁ ባለሟልነትን ያገኘ ነው። በቤተ

www.zeyeneta.com

ክርስቲያናችን ትምህርት ይህን ሥራ የሚሠሩት በባሕርይው ቅዱስ ከሆነው ከእግዚአብሔር በጸጋ የከበሩ ቅዱሳን ናቸው።

ቅዱሳን በሃይማኖት በምግባር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙና በፊቱም እውነትን የሚናገሩ ስለሆኑ የበደሉትን ይቅር እንዲል በለመኑት ጊዜ ከሰጣቸው ባለሚልነት የተነሳ ፈጥኖ ይቅር ይልላቸዋል። ለምሳሌ እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ተቆጥቶ ላጥፋቸው ባለ ጊዜ ሙሴ ስላቀረበው ልመና እግዚአብሔር ራርቶላቸዋል። «...እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ።» ዘጸ.32÷9–14፣ «እንዳያጠፋቸው ቁጣውን ይመልስ ዘንድ የተመረጠው ሙሴ በመቅሰፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ ያጠፋቸው ዘንድ ተናገረ።» መዝ.105÷23 እንዲል።

ሐ/ የሚለመንለት /ምልጃ የሚተርብለት/፦ ይህ ሦስተኛው አካል ሲሆን፣ መበደሉንና ኃጢአት ማድረጉን ዐውቆ በእግዚአብሔር ፊት በትኅት ሰብእና ልመናውን በማቅረብ ምልጃን የሚጠይቅ ምእመን ነው። ይኸም የተመሰገነውን መቶ አለቃ ይመስላል። «አንድ የመቶ አለቃም ነበረ፣ የሚወደውም ባሪያው ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር። ስለ ኢየሱስም በሰማ ጊዜ የአይሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ላከና መጥቶ ባሪያውን እንዲያድን ለመነው።» ሉቃ.7÷2–10። በእርግጥ ቅዱሳን ለምልጃ የሚማጠናቸውን ብቻ ሳይሆን በእነርሱ ላይ ለተነሡትም ሰዎች ይጸልዩላቸዋል እንጂ አይጸልዩባቸውም፣ ይቅርታ በማድረግ አምላካቸውን ይመስሉታልና። ሐዋ.7÷60።

ስለዚህ ምልጃ ስንል እነዚህን ሦስት አካላትና ትክክለኛ ተግባራቸውን ማስታወስና ማወቅ ይኖርብናል።

5.3. ምልጃ ለምን ያስፈልጋል?

ለመሆኑ ምልጃ ስለ ምን አስፈለገ? እግዚአብሔር ያለ ሦስተኛ ወገን ሲነግሩት ስለማይሰማ ነውን? ወይስ የእግዚአብሔር

ፍርድ በጠበቃው ችሎታ የሚለወጥ ስለሆነ? ምልጃስ በማጭበርበርና ሰነድ በመለወጥ ኃጥኡን ጻድቅ ማድረግ ነውን? ታዲያ ምንድን ነው ምልጃ? አንዳንድ ሰዎች እኛ እግዚአብሔርን በቀጥታ ማነጋገር እንችላለን እርሱም ይሰማናል፣ ስለዚህ ሦስተኛ ወገን አያስፈልገንም ይላሉ። በውኑ ምልጃ የሚሹት ወገኖች እግዚአብሔር አይሰማንም ብለው ይሆንን ወይስ ስለ ሌላ?

ሀ/ <u>ድኅነት ሥርዓት ስላለው፦</u>

እግዚአብሔር ሰው ሳይሆን ሰውን ለማዳን አይቻለውምን? የሚል ጥያቄ ብናነሣ «ስለማይቻለው ነው» የሚል ሰው ሊኖር አይችልም፣ እግዚአብሔርን «አምላክ» ነው ብሎ አስካመነ ድረስ። ታድያ ለምን ሰው ሆነ? ስንል እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ሥርዓት እንዳለው ወይም ፍርዱ ርቱዕ እንደ ሆነ እግዚአብሔርም የሠራውን ሥርዓት እንደሚጠብቅ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። «የኃለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፣ ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቷልና። ነገር ግን ሁሉ ተገዝቷል ሲል፥ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ ግልጥ ነው። ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።» 1ኛቆሮ.15÷28 እንዲል።

አምላካችን እግዚአብሔር ለሠራው ሥርዓት ራሱን በማስገዛት አሳይቶናል። ከዚህ የተነሣ ተጠምቆ የዕዳ ደብዳቤያችን ቢደመሰስም ለእኛም ጥምቀት እንደሚያስፈልገን ነግሮናል። ከእግዚአብሔር የምንወለድበት ሥርዓት አድርጉታልና። ዮሐ.3÷1–12። እንድንጸም፣ እንደንጸልይ፣ እንድንመጸውት... ሥርዓት ሠርቶልናል። ማቴ. 6÷1–34። ይህ ሁሉ ሥርዓት የተሠራው እርሱ በፈጸመው የቤዛነት ሥራ እግዚአብሔር እኛን ማዳን ስለማይችል አይደለም፣ የመዳናችን ሥርዓት ሆነው የተሰጡን ሁሉ የቢሮክራሲ ቅደም ተከተሎች ሳይሆኑ

www.zeyeneta.com

እርሱ ያደረገልንን የማመናችን ማረጋገጫዎች፣ ተገደን የምንጸድቅም የምንኾንንም ስላልሆነ ወድደን፣ ፈቅደንና መርጠን መሄዳችንን የምናስረግጥባቸው የመታመናችን ምስክሮች ናቸው። «ጥምቀት ልጅነት ያሰጣል» ብሎ የሚያስተምር አመነ የሚባለው «የተጠመቀ» ጊዜ ስለሆነ ነውና። ነገር ግን የማይጠመቅ ምእመን አይባልም።

ምልጃም ከእነዚህ የድነነት መንገድ ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ ነው። ለምሳሌ ያህል በዮሐ.2÷1–11 ስንመለከት እመቤታችን «ለጌታችን የወይን ጠጅ የላቸውም» ስትል የተናገረችው ጌታችን ግለቱን ስለማያውቅ አይደለም፣ የእርሱን ማወቅም እመቤታችን ስለ ማታውቅ አይደለም፣ የእርሱን አምላክነት እርሷ ታውቃለችና፣ ነገር ግን ጌታችን አስገድዶ የሚሰጥ አይደለም። ስለዚህ የሚለምን ወይም የሚጠይቅ ያስፈልግ ነበር። ባለ ሠርጉቹ ይህን ስላልተገነዘቡ አልጠየቁትም እንጂ ቢደረግላቸው የሚጠሉ ሆነው አልነበረም። እንኳን እነርሱ ደቀ መዛሙርቱም ገና አላመኑም ነበርና፣ ገባሬ ተአምራት መሆኑን የምታውቅ፣ ልመና ተቀባይ መሆኑንም የምታምን እመ ቤታችን ለመነችው ማለደችው፣ እርሱም ተለመናት÷ የፈቀደች ውንም ፈጸመላት።

ይህ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተዘጋጀ ሥርዓት ነው። ከዚህም በፊት እግዚአብሔር ሰው ይሆን ዘንድ በወደደ ጊዜ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ቅዱስ ገብርኤልን የላከው እርሷ ያለችበትን ቅዱስ ገብርኤል እንጂ እርሱ ስለማያውቅ ወይም መናገር የሚችለው መልአኩ እንጂ እርሱ ስለማይችል አይደለም፣ እግዚአብሔር የእርሱን ወደ እኛ መምጣት ፈቃድ ጠያቂ መልእክተኛ ካስፈለገው፣ ይልቁንም እኛ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስማ እንዴት አብልጠ ጠያቂ አያስፈልገንም፣ ይህንም ሥርዓተ መንገድ እርሱ አበጀው እንጂ እኛ አላመጣነውም። የኢዮብን ባልንጀሮች እግዚአብሔር አናግሯቸዋል፣ ቀድመው የተናገሩትንም ሰምቷል፣ እንዲጸኑ ሲፈልግ

ግን ወደ ኢዮብ የላካቸው ሥርዓተ ድኅነት ስለሆነ ነው። ኢዮ 42÷7–8 ጌታችን ድኅነት በሥርዓት የሚፈጸም የሃይማኖት ጉዞ መሆኑንና ለዚህም አብነታችን እርሱ እንደሆነ ሲናገር «እኔ መንገድ ነኝ» ብሏል። ዮሐ.14÷6። ስለዚህ ድኅነት ሥርዓት ያለው በሃይማኖት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርጉት ጉዞ ውስጥ አንዱ ምልጃ ነው።

ለ/ የእግዚአብሔርን ብዙኀ ምሕረት /የምሕረት ብዛት/ እንድናውቅ፦

እግዚአብሔርን ከበደለ በኋላ የሚጸጸት ሰው አለ፡ የማይጸጸትም አለ፣ እንደ በደለ አያውቅምና። እንደ በደለም አያውቅ ልቡናውን የሚያገዝፍ አለ። ሰው እንደበደለ በተሰማው በደሉም በቆረቆረው ጊዜ እግዚአብሔርን ይለምናል። ሲለምን ግን እግዚአብሔር እንዲምረው የሚያሳስበው ከእርሱ የተሻሉትን የሚበልጡትን እግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝባቸውን ሰዎች በማሳሰብ ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ምሕረት ተሰፍራ የምትለካ ስላልሆነች፣ ደጋጉቹን ባሰበ ጊዜ ብዙኀ ምሕረቱ ስለሚፈስስ ኃጥኣንም ይቅር ይባላሉና።

እነ ሙሴ እንዳዊት ስለ አስራኤል ሲለምኑ በደጋጉቹ በኩል አድርገው ነበር፣ ቅዱሳኑ በአካለ ሥጋ ባይኖሩ እንኳን ስለ ፣ነርሱ የሚደረገው ምሕረቱ በዘመን የማይገታ በመሆኑ ነው። «...ዘራችሁን እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛለሁ÷ ይህችንም የተናገርኋትን ምድር ሁሉ ለዘራችሁ እሰጣታለሁ÷ ለዘላለምም ይወርሷታል ብለህ በራስህ የማልህ ላቸውን ባሪያዎችህን አብርሃምንና ይስሐቅን አስራኤልንም አስብ። እግዚአብሔርም በሕዝቡ ላይ ሊያደርግ ስላሰበው ክፋት ራራ።» ዘጸ. 32÷13–14 ተብሉ እንደ ተጻፈው በዘመን የማይገታ የእግዚአብሔር ምሕረት በእስራኤልም ሸደል ሳይገደብ በዝቶ የተደ

www.zeyeneta.com

ረገው ሙሴ አብርሃምንና ይስሐቅን አስራኤል የተባለ ያዕቆብንም አንሥቶ ስለ ማለደው ነው።

ሙሴ የእግዚአብሔርን ብዝኀ ምሕረት በቅዱሳን ስም የሚ ሣለድ መሆኑን ስለ ዐወቀ አደረገው፡ እንጂ እኔ እበቃለሁ አላለም። ስለዚህ እግዚአብሔር ምልጃን የፈቀደው በዘመን የማይገታ ምሕረት ያለው መሆኑን ዐውቀን እንድንጠቀም ነው። «ለአባቶቻችን እንደ ተናገረ ለአብርሃምና ለዘሩ የዘላለም ምሕረቱን አስቦ እስራኤልን ብላቴናውን ረድኧል።» ሉቃ.1÷55 እንዳለች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እግዚአብሔር በቅዱሳኑ በኩል ዘላለማዊ ምሕረትን አድርጓል። ክብሩ፣ ገናንነቱ፣ ጌትነቱ የሚታወቀውም በእነርሱ ስም በማለድነው ጊዜ ነው።

ሐ/ የእግዚአብሔርን ባለሟሎች ለይተን እንድናውቅ በቃል ኪዳናቸውም እንድንጠቀም፡-

እግዚአብሔር በወዳጆቹ ሁልጊዜ ይደሰታል፣ ስለዚህም የሚታሰቡበትን ቃል ኪዳን ይገባላቸዋል። «ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ÷ ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ» መዝ.88÷3 እንዲል ከመረጣቸው ጋር ቃል ኪዳን አድርጓል፣ መሐላም ገብቷል። እግዚአብሔር ይህን ዐውቀን እንድንጠቀምበት ይፈልጋል። ክላይ እንደ ተመለከትነው የኢዮብን ባልንጀራዎች ወደ ኢዮብ የላካቸው እርሱ ለኢዮብ ያለውን ፍቅርና ጸሎቱን እንደሚሰማለት የገባለትንም ቃል ኪዳን ዐውቀው እንዲጠቀሙ ነው። ኢዮ.42÷7–8።

ሙሴ ለእስራኤል ለምኖ ምሕረትን ያስገኘው እግዚአብሔር ከነአብርሃም ጋር ያለውን ወዳጅነት የገባላቸውንም ቃል ኪዳን ስለ ሚያውቅ ነው። እግዚአብሔር ባለሟል ያደረጋቸውን ሰዎች ማወቅ ሲሳናቸውና በእነርሱም ላይ የዓመጻ ንግግር ሲናገሩ ይገሥ ጻቸዋል፣ አርንና ማርያም በሙሴ ላይ ባጉረመረሙ ጊዜ አርንን የተቆጣው

ማርያምንም በለምጽ የመታት የሙሴን ባለሟልነት ዐውቀው በጸሎቱ እንዲጠቀሙ ነው። ዘኍ.12÷1–15። ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስም የተገ ሠጸው ቅዱስ ገብርኤል የእግዚአብሔር ባለሟል መሆኑን በሥራ ስላላመነ ነው። ቅዱስ ገብርኤል «እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ» ማለቱ ንግግሬን አታቅልል የምነግርህን አምነህ ተጠቀም ሲለው ነውና። ሉቃ.1÷19።

እግዚአብሔር ከወዳጆቹ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያለ ምልጃ ሥርዓት መጠቀም አይቻልም። ሰሎሞን እግዚአብሔርን በድሉ ሳለ መንግሥቱ በእርሱ ዘመን ያልተከፈለው እግዚአብሔር ለአባቱ ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን እንዲያስብና እንዲምረው በአባቱ ስለ ማለደው ነው። «ነገር ግን ስለ ባሪያዬ ስለ ዳዊት ስለ መረጥኋት ስለ ኢየሩሳሌም አንድ ነገድ እሰጣለሁ እንጂ መንግሥቱን ሁሉ አልቀድድም።» 1ኛነገ. 11÷13 ሲል ምሕረትን ያደረገለት አስቀድሞ «...አሁንም የእስራኤል አምላክ አቤቱ አንተ በፊቴ እንደ ሄድህ ልጆችህ መንገዳቸውን ቢጠብቁ፣ በእስራኤል ዙፋን የሚቀመጥ ሰው በፊቴ አታጣም ብለህ ተስፋ የሰጠኸውን ለአባቴ ለዳዊት ጠብቅ።» 1ኛነገ.8÷25 ብሎ በዳዊት ስም ስለ ማለደው ነው።

መ/ ስለ ትኂትና፡-

ትኅትና ራስን ታናሽ አድርጉ መቁጠር ራስን በእግዚአ ብሔር ፊት መጣል ነው። የእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች ብዙ ጊዜ ራሳቸውን ሲመረምሩ ስንኳን በልዑል ባሕርይ በእግዚአብሔር ፊት በሰውም ፊት መቆም አይገባንም ይላሉ። «እግዚአብሔር ትዕቢ ተኞችን ይቃወማልና÷ ለትኍታን ግን ጸጋን ይሰጣል።» 1ኛጴጥ.5÷5 ተብሎ እንደ ተጻፈ። ስለዚህ ሁሉ ሮማዊው የመቶ አለቃ አብነ ታችን ነው። ራሱን በእግዚአብሔር ፊት፡ መቆም እንደማይገባው ቆጥሮ የአይሁድ ሽማግሌዎችን ልኳል። ጸኋላም «በቤቴ ጣራ በታች

www.zeyeneta.com

ልትገባ አይገባኝም» በማለቱ የበለጠ ተመሰገነ ተደነቀ እንጂ አልተዋረደም። ይልቁንም በእስራኤል እንኳን እንዲህ ያለ ታላቅ እምነት አላገኘሁም መባሉ እግዚአብሔር ስለ ወዳጆቹ የሚያደር ገውን ምሕረት አምኖ በትጎትና በመጠየቁ ነው። እግዚአብሔርም በትጎትና የሚተርበውን ጸሎት ይቀበላልና በትጉት ሰብእና ለቅዱሳን በገባው ቃል ኪዳን በኩል ብንለምነው የመንጠቀም እንጂ የምንጉዳ አይደለንም።

5.4. አማላጅ ለምን ይግልዳል?

በምልጃ ውስጥ ሦስት እኔ ባይ የተለያዩ አካላት እንዳሉ ተመልክተናል። ተማላጅ፣ አማላጅና የሚማለድለት። እነዚህ ሦስቱም የየራሳቸው ደረጃ አላቸው። ለምሳሌ በእምነት ስለምናደርገው ምልጃ ተማላጁ እግዚአብሔር ስንኳን የሚተካከለውና የሚመስለው ያየውም ፍጡር እንደ ሌለ ቅዱሳት መጻሕፍት ደጋግመው ደጋግ መው ገልጸውታል። ዮሐ.1÷18፣ ዘጸ.33÷20። «ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም÷ ከወልድም በቀር ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም።» /ማቴ.11÷27/ ተብሉም የተጻፈው ባሕርይው የማይመረመር ብዕሉም ዓይነትና ሥፍር የሌለው በመሆኑ ነው።

አማላጆቹ ደግሞ ፍጡራን ናቸውና ከተማላጁ ከእግዚአ ብሔር በማይነገር ወይም ልንገልጠው በማንችለው መጠን ያንሳሉ። እንኳን በፈጣሪና በፍጡር መካከል ያለው ልዩነት ሁለቱም ፍጡራን በሆኑት በፀሐይና በጨረቃ ወይም በፀሐይና በከዋክብት መካከል ያለው የብርሃን ልዩነት በእጅጉ የተራራቀ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም። ይሁን እንጂ ለሰው የፀሐይ ብርሃን ብቻ አያስፈል ገውም፣ ከፀሐይ ብርሃን በእጅጉ የሚያንስ ብርሃን ያላት ጨረቃም ጭምር እንጂ። ከጨረቃም የምናገኘው ጥቅም አለና። አማላጅም ፍጡር በመሆኑ ከፈጣሪ እጅግ ቢያንስም ከኃጥአን ግን በእጅጉ

ይበልጣልና በብዙው ይጠቅመናል። የእነርሱ ክብር ልዕልናም ከእኛ ጋር የማይነጻጸር ነው። ምክንያቱም ስለ ተጋድሏቸው እግዚአብሔር ጸጋውን አብዝቶላቸዋል። ሀብቱንም ሰጥቷቸዋልና። እርሱ አምላክ ሆኖ ሳለ እነርሱንም አማልክት ዘበጸጋ አድርጓቸዋልና። ዮሐ.10÷34፣ ዘጸ.7÷1፣ መዝ.81÷1። ስለዚህ ከእኛ በእጅጉ ይበልጣሉ። ታድያ ስለ ምን ያማልዳል?

ሀ/ ከእነርሱ የማይገኘውን ለማሰጠት፦

ቅዱሳን ሀብታቸው ጸጋቸው ከእግዚአብሔር የተገኘ ነው። ትንቢት ቢናገሩ ድውይም ቢፈውሱ፣ ሙታንም ቢያሰነሡ ከእግዚ አብሔር የተቀበሉትና በስሙም የሚፈጽሙት አገልግሎት ነው። ከተሰጣቸውም ጸጋ ለሰው ይሰጣሉ። ኤልያስ ኤልሳዕን «ከእንተ ሳልወሰድ አደርግልህ ዘንድ የምትሻውን ለምን አለው፤ ኤልሳዕም፦ መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ ይሆን ዘንድ እለምንሃለሁ አለ። እርሱም፦ አስቸጋሪ ነገር ለምነሃል፤ ነገር ግን ከአንተ ዘንድ በተወሰድሁ ጊዜ ብታየኝ ይሆንልሃል፤ አለዚያ ግን አይሆንልህም አለ።» 2ኛነገ.2÷9–10 የሚለው የኤልያስን ለጋሥነት ብቻ ሳይሆን የቅዱሳንን ሁሉ ለጋሥነት ያረጋግጣል።

ኤልሳዕም በአገልግሎት ደስ ላሰኘችው ሴት የምትፈልገውን ልጅ እንድትወልድ ይሁንልሽ አላት፤ ሆነላትም። 2ኛነገ.4÷8–17። ቅዱሳን የበደለውንም ሊገሥጹት ይቻላቸዋል። ቅዱስ ጴጥሮስ ሐናን ያንና ሰጲራን በገሠጻቸው ጊዜ እንደ ሞቱ ይታወቃል። ሥራ. 5÷1–11። ስለ መላእክትም «በመንገድ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋ ጀሁትም ሥፍራ ያገባህ ዘንድ÷ እነሆ÷ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድ ዳለሁ። በፊቱ ተጠንቀቅ÷ ቃሉንም አድምጥ፤ ስሜም በእርሱ ስለ ሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት።» ዘጸ.23÷20–21 እንዲል ይህ ኃይል አላቸው። የበራክዩ ልጅ የካህኑ

www.zeyeneta.com

ዘካርያስም መገሠጽ የዚሁ አስረጅ ነው። ዘካ.1÷7–። ሄሮድስም ራሱን ጣያት ባደረገ ጊዜ መልአከ እግዚአብሔር መትቶታል። «ለእግዚአብሔርም ክብር ስላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው በትልም ተበልቶ ሞተ።» ሐዋ.12÷23 ይላልና።

ቅዱሳን ይህን ያህል ክብርና ብርታት ይኑራቸው እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም የማይነጻጸሩና ከእርሱ የባሕርይ ፍጹምነት የተነሣ ለእነርሱ በተሰጠው ጸጋ ብቻ ሳይሆን ከእርሱም የሚገኘው እንዲደረግልን ይለምናሉ። ጸጋቸውም የተቆጠረ የታወቀ ነውና እግዚአብሔር በማይሠፈር ሀብቱ እንዲጉበኘን ይለምኑልናል። ለምሳሌ ያህል «ሕይወት» የእግዚአብሔር ብቻ ነው። ስለዚህም ሕይወትን ይሰጠን ዘንድ፣ ከሞትና ከኩነኔ ያድነን ዘንድ ይለምኑልናል። የእግዚአብሔር ስጦታ የባሕርይው ነውና ለስጦታውም መጉደል የለበትምና ከእነርሱ የሌለው ጸጋ ይሰጠን ዘንድ ያማልዱናል።

የአማላጅ የማማለዱ ምሥጢር ከተማላጃ ስለሚያንስና ከእርሱም የሚገኘውን ሀብት ይቅርታ ጸጋ ለማሰጠት ነው።

ለ/ ምሕረትና <u>ልመና ግብራቸው</u> ስለሆነ፡–

ቅዱሳን በዚህ በምድር ሳሉ ይቅር በማለት የተገለጡ ናቸው። ይቅርታቸውም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ምልጃን የጠየቃቸው ምእመን ፍጹም ምሕረት እንዲደረግለት ይለምኑለታል እንጂ በእነርሱ ይቅር ማለት ብቻ የሚመለሱ አይደሉም። ይኸም በኢዮብ፣ በሙሴ፣ በሳሙኤልና በይሁዳው ነቢይ ታውቋል። ኢዮ.42÷7–8 ዘኍ.12÷1–15፣ 1ኛሳሙ.15÷34፣16÷1፣ 1ኛነገ.13÷1–6። ቅዱሳን በምድር ብቻ ሳይሆን በሰማይም ያለ ማቋረጥ ይለምኑልናል፣ ይጸልዩልናል፣ያማልዱናል። «በዚያም ቦታ ሌላ ራዕይ አየሁ የጻድቃንን ማደሪያቸውን የቅዱሳንን ቦታቸውን አየሁ። ከዚያም ቦታ ዓይኖቼ ከመላእክት ጋር የሚኖሩበት ማደሪያቸውን ከቅዱሳንም ጋራ የሚኖሩበት ቦታቸውን አዩ። ስለ ሰውም

ልጆች ፈጽመው ይለምናሉ ይጸልያሉ።» ሄኖ.9÷21–23 እንዲል። ቅዱሳን ሥራቸው ከምስጋና ጋር ይቅርታንና ምሕረትን መለመን ነው። የሚለምኑትም ለኃጥኣንም ለጻድቃንም /በምድር ላይ ለሚኖሩ ደጋግ ሰዎች/ ነው።

ለማያምኑትም ይጸልያሉ። ሐዋ.7÷60። ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ የሰው ልጆች ሁሉ እንዲድኑ ከክብራት የፍጹምነት አሳብ የተነሣ በደል የባሕርይው የሆነውንና ስለ አጣው ክብር ከመጨነትና ከመናደድ በቀር በመበደሉ የማይጸጸተውን ሳጥናኤልን እንኪን እንዲ ምረው ለምናለታለች። ሌሎችም ቅዱሳን ተግተው የሚለምኑት ስለ ሰው ልጆች ነው። የቅዱሳን ልመና ሥራቸው ነው ስንልም የሚጠየቁበት ግዳጃቸው ነው ለማለት አይደለም፣ በዚህ ዓለም የሚኖር ሰው አየር ሳይተነፍስ መኖር እንደማያስበው ሁሉ ቅዱሳንም ስለ ሰው መጸለይንና መለመንን እንደሚተነፍሱት አየር ሕይወት አድርገውት ይኖራሉ ለማለት ነው።

አንዳንድ ሰዎች አማላጆቻችን አሁን በሕይወተ ሥጋ አለመኖራቸውን በእኛና በእነርሱ መካከል ያለውን ግንኙነት ሊያጸርጠው እንደሚችል ያስባሉ። በእምነት መተያየትና መገናኘት በዚህ ዓለም ካሉት የሥልጣኔ መገናኛዎች፣ ስልክ፣ ኢሜይልና ኢንተርኔት፣ ወይም የሬድዮና የቴሌቪዥን ዜና ከማየትና ከመስማት ጋር የማይነጻጸር ነው። በዚህ ዓለም ሰው የሠራቸው ዕቃዎች ድምፅን ወደ ሞገድ፣ ሞገድንም ወደ ድምፅ ለውጠው በተለያዩ ሀገሮች ያሉ ሰዎችን ማገናኘት ከቻሉ ፍጹም ዕውቀትና የሰማያዊው አምላክ ክብር በሚገለጠበት ልዩ ቦታ ከሚኖሩት ጋር በምድር የምንኖር ሰዎች በእምነት ልንገናኝ እንዴት አንችልም? እምነትንና በጉ ሥራንስ የቦታ ርቀትና በሥጋ አለመተዋወቅ የሚከለክላቸው ከሆነ የ«እምነት» መንፈሳዊነት እንዴት ሊሆን ይችላል? የኤሌክትሮ

www.zeyeneta.com

ማግኔት ሞገድ ያለ አስተላላፊ ነገር (electromagnetic wave can travel with out any media) መግዝ ይችላል የምንል እኛ በምድር ባለችው ቤተ ክርስቲያንና በሰማይ ባለችው ቤተ ክርስቲያንን መካከል ያለውን ርቀት የማይገድበው ግንኙነት ሳናምን በዓለም ምሉዕ በሆነ በእግዚአብሔር እናምናለን፣ ሕይወታችንም እርሱ ነው ማለት እንደ ምን ይቻለናል? በእኛ አድሮ የሚሠራው የእግዚአ ብሔር መንፈስ በእውኑ ከሞገድ ሊያንስ ይችላልን? የክርስቲያናችን ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከግዕፀነ ዮርዳኖስ ተወልዶ መንፈሳዊ መሆን ወዴት አለ? መንፈሳዊውን ነገር በሥጋዊ ፍልስፍና ዐይን የምንመለከተው ከሆነ እውነቱን ማስተዋል ይሳነናል።

ኤልሳዕ የሶርያ ንጉሥ የሚመክረውን ሁሉ ለእስራኤል ንጉሥ የሚገልጽለት ዘመናዊ መሣሪያ በመጠቀም ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ነበር። እርሱ አንድ ቦታ ተቀምጠ ተራራና ጋራ ሳይከለክለው ለመመልከት ያስችለዋልና። በዚሁም ተጨማሪ አስረጂ የሚሆነን የኢዮሣፍጥ ልጅ ኢቶራም በነገሠ ጊዜ የአክዓብን ልጅ አግብቶ ወንድሞቹን ገደለ+ በይሁዳ ተራራዎች ላይ መስገጃዎችን ሠራ+ በኢየሩሳሌምም የተቀመጡትን እንዲያመነዝሩ አደረጋቸው። 2ዜና.21÷1–11።

በዚህ ወቅት በአክዓብ ዘመን ከሀረገው ከኤልያስ መልእክት መጣበት። «ከነቢዩም ከኤልያስ እንዲህ የሚል ጽሕፈት መጣበት፦ የአባትህ የዳዊት አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ በአባትህ በኢዮሣፍጥ መንገድ በይሁዳም ንጉሥ በአሳ መንገድ አልሄድህምና+ በእስራኤል ነገሥታት መንገድ ሄደሃልና+ የአክዓብም ቤት እንዳደረገ ይሁዳንና በኢየሩሳሌም የሚኖሩትን እንዲያመነዝሩ አድርገሃልና+ ከአንተም የሚሻሉትን የአባትህን ቤት ወንድሞችህን ገድለሃልና+ እነሆ+ እግዚአብሔር ሕዝብህንና ልጆችህን ሚስቶችህንም ያለህንም

ሁሉ በታላቅ መቅሠፍት ይተሥፋል። አንተም ከደዌው ጽናት የተነሣ አንጀትህ በየዕለቱ እስኪወጣ ድረስ በክፉ የአንጀት ደዌ ትታመማለህ።» 2ኛዜና.21÷12–15።

ይህን ጽሑፍ ኤልያስ ለኢቶራም የላከለት ማን ነግሮት ነው? ኤልያስ በብሔረ ሕያዋን የሚኖር ሞተ ሥጋ ያላገኘው ነቢይ ነው። በዚያ እያለ በመሬት ያለውን ማወቅና የፈለገውን መመልከት መቻሉ ይልቁንም ከሞተ ሥጋ በኋላ ቅዱሳን ፍጹም ዕውቀት እንዳላቸው የሚያስረግጥልን ነው። 2ኛነገ.6÷8–13። ታድያ በእጸደ ሥጋ ይህን ያህል መመልከት ከቻሉ በእጸደ ነፍስማ እንዴት አብልጠው ኢይቻላቸውም። «ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደ ምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፣ ዛሬስ ከዕውቀት ከፍዬ አውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደታወቅሁ ዐውቃለሁ።» 1ኛቆሮ.13÷12 እንዲል።

የዛሬው ዕውቀት በሰማያት ከሚኖሩበት ሕይወት ካለው ዕውቀት እጅግ ያንሣልና። ሰማያዊ ኑሮንና ዕውቀትን ማላነስ የተሰጠንን ጸጋ አለማመን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ግን እንደሚበልጥ ያስረግጣሉ። «በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፣ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ+ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፣ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው።» ፊል.1÷24። ስለዚህ ቅዱሳን ሁሉን ያውቃሉ+ ለመንፈሳዊ ሥራም ድንበር አጥር የለበትም። ይህም የፍቅር አገልግሎት ስለሆነ ነው። ብዙ ውኃ ነበልባል አሳትን ሊያጠፋው ይችላል፣ ፍቅርን ግን ሊያጠፋት አይቻለውም፣ ፍቅር ረቂቅ የሆነ የእግዚአብሔር ገንዘብ፣ ግዙፍ አካል ያለው ሊያጠፋው ሊከለክለው የማይቻለው ነውና። «ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም፣ ፈሳሾችም አያስጥሟትም።» መኃ.8÷7 እንዲል።

www.zeyeneta.com

በፍቅር የሚደረገውን አገልግሎት ሊሸረውና ሊያጠፋው የሚቻለው ነገር የለም። «ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፣ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፣ ልሳናች ቢሆኑ ይቀራሉ፣ ዕውቀትም ቢሆን ይሻራል።» 1ኛቆሮ.13÷4። «የትዕዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልቡና ከበጎ ኅሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው።» 1ኛጢሞ.1÷5 እንዲል።

ሐ/ <u>ባለሟልነት ስላለው፡-</u>

አማላጅ ሁሉ የእግዚአብሔር ባለሟል ስለሆነ ይማልዳል። ባለሟሉቹ ለመሆናቸው የዘላለም መታሰቢያ ይሰጣቸዋል፣ እነርሱ በዚያ ይታሰባሉ? ስማቸው ይጠራል። እግዚአብሔርም መታሰቢያቸውን ይቀበላል፣ የማለላቸውን መሐላ፣ የገባላቸውንም ቃል ኪዳን ያስባል። «ነገር ግን በዚያን ጊዜ ያልተገረዘው ልባቸው ቢዋረድ÷ የኃጢአታቸውንም ቅጣት ቢቀበሉ÷ እኔ ለያዕቆብ የማልሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ፣ ደግሞም ለይስሐቅና ለአብርሃም የማልሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ፣ ምድሪቱንም አስባለሁ።» ዘሌ.26÷42-45 እንዲል እግዚአብሔር ቃል ኪዳናቸውን ያስባል።

እነርሱም በማዕዘናት ወይም በአትጣጫ በማይወሰን በእግዚአብሔር ፊት ይቆማሉ የተባሉ ገጸ ምሕረቱን የሚያሳያቸው ባለሟሉቹ ናቸው። «እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝና።» ሉቃ.1÷20 እንዲል። «ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፣ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና።» ማቴ.18÷10። ከባለሟልነታቸው የተነሣም በሰው ሕይወት ያለው ምሥጢር አይከፈልባቸውም። «እግዚአብሔርም አለ፡- እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሠውራለሁን? አብርሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናልና÷የምድር አሕዛብም ሁሉ በእርሱ ይባረካሉና።» ዘፍ.18÷18

በማለት እግዚአብሔር የአብርሃምን ባለሟልነት አረጋገጠ፣ አብርሃምም ባለሟልነቱን በአማላጅነት ተግባሩ ሲያረጋግጥ ወዲያውኑ ስለ ሰዶምና ገሞራ ለምኗል።

ቅዱስ ዮሐንስ በራእዩ ያያቸው በሰማዕትነት ያረፉ ሰዎች ነፍሳትም «ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም» እያሉ ንስሐንና ሃይማኖትን ላለመቀበል በጨከኑ ሰዎች ላይ የሚለምኑባቸው ባለሟልነት ስላላቸው ነው። ራእ.6÷9-11። ይልቁንም ሁልጊዜ ስለ እኛ እንደሚለምኑና እንደሚያማልዱ እግዚአብሔርም ልመናቸውን ሁሉ እንደሚቀበልላቸው «እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፣ ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አንጹ። ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ። ሌትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል÷ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።» ራዕ.7÷14-17፤ «ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፣ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቅ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው። የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።» ራዕ.8÷3-4 በማለት ባለሟልነታቸውን ከዚህም የተነሣ አማላጅነታቸውን እግዚአብሔርም ጸሎታቸውን መቀበሉን በማያሻማ መንገድ ገልጦልናል።

አማላጅ ለምን ይማልዳል የሚለው ጥያቄ በእነዚህ መልሶች ብቻ የሚወሰን አይደለም። እስካሁን ከአየናቸው ነጥቦች አንጻር በውኑ ጌታችን ቁጥሩ ከአማላጆች ጋር ነውን?

5.5. ጌታችን አማላጅ አይደለም፡-

አንዳንድ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ያሉ ደረቅ ምንባባትን መነሻ በማድረግ ጌታችንን አማላጅ ሲሉት ይደመጣሉ። ለእርሱ ክብር ምስጋና ይግባውና ስም አከራሩም ከፍ ከፍ ይበልና

www.zeyeneta.com

ጌታችን አማላጅ አይደለም። ጌታችን ለሰው ሲል ቢመራቡ ረሃብተኛ /ሉቱ ስብሐት/ እንደማይባል ሁሉ በፈጸመው የማስታረቅ ሥራም አማላጅ ተብሉ በግብር አይጠራበትም። ሰው እንዳይጠይቅ አይገደብምና ለምን? የሚል ጥያቄ ማንሳት እንችላለን። ከላይ በተጠቀሱት መሰረቶች መመዘን የሚቻል ቢሆንም በአጭር በአጭሩ እንደሚከ ተለው እንመለከታለን።

ሀ/ የሁሉ ነገር አስገኝ እርሱ ነውና፦

እርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጌታችን የሁሉ ባለቤት፣ የሁሉ አስገኝ እንደሆነ ታምናለች። ስለዚህም እርሱ ሽቶት የሚለምነው ነገር የለም። እርሱም የህብታት ሁሉ ሰጭ እንጂ የሚያስተ ወይም የሚቀበል አይደለም። «አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲያወጧቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።» ማቴ.10÷1፤ «አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰ ጣቸው እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል።» ዮሐ.5÷23 እንዲል ጌታ ሰጭ እንጂ የሚያሰጥም የሚቀበልም አይደለም፤ ሰው በመሆኑም እንኳን የተቀበለው የሚለምነውም ነገር የለም፤ ሁሉን ያደርግ ዘንድ የሚቻለው ባለሥልጣን ነውና። የአራት ቀን ሬሳ አልዓዛርን «ከመቃብር አፍ ውጣ» ብሎ በሥልጣኑ ያወጣው እርሱ ነው። ዮሐ.11÷38–44።

የሁሉ ፈጣሪም እርሱ ነው። «ሁሉ በእርሱ ሆነ÷ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።» ዮሐ.1÷3፣ ቆላ.1÷18። ታድያ ጌታችን የሁሉ ፈጣሪ የሁሉ አስገኝ ከሆነ፣ ሁሉን ለማድረግ ሥልጣን ያለው እርሱ ከሆነ፣ ሀብታትንም ሥልጣንንም የሚሰጥ እርሱ ከሆነ «ኮኖን» ምን ሊለምን ይችላል? ከእርሱ በላይስ የሚለመነው አካል ማን ነው? ከአብ ይለምናል እንዳንል «እውነት እውነት እላችኋለሁ÷

አብ ሲያደርግ ያየውን እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና።» ዮሐ.5÷19 ተብሉ እንደ ተጻፈ ወልድን ያግልዳል ማለት አብን ያግልዳል ማለት ነው። ምክንያቱም በባሕርይ አንድ ናቸው። «እኔና አብ አንድ ነን።» ዮሐ.10÷30 እንዲል።

ስለዚህ ጌታችን ተግላጅ እንጂ አማላጅ አይደለም። ለሌሎቹም ለምነው የሚያስምሩበትን÷ የሚያሥሩ የሚፈቱበትን ፍጹም ሥልጣን የሰጠ እርሱ ነው። «እውነት እላችኋለሁ÷ በምድር የምታሥሩት ሁሉ በሰማይ የታሠረ ይሆናል። በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ደግሞ እላችኋለሁ፦ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢስማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል። ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።» ማቴ.18÷18 ተብሉ ተጽፏልና።

ለ/ ምሕረትን የሚሰጥ እንጂ የሚለምን አይደለምና፦

ከላይ እንደ ተመለከትነው የሁሉ ነገር አስገኚም ሰጭም ራሱ ነው። ስለዚህ ምሕረትና ይቅርታ የባሕርይው ስለሆነ እርሱ ራሱ የሚሰጠን፣ ይቅር የሚለን፣ የሚያነጻን እንጂ ከሌላው የሚቀበለው ነገር የለም። እንደ ነብያት «በእግዚአብሔር ስም» እንደ ሐዋርያትም «በኢየሱስ ክርስቶስ ስም» ወይም በቅድስት ሥላሴ ስም አላለም፤ ሁሉንም በሥልጣኑ ያደረገው የትንትናና የምሕረት ምንጭ በመሆኑ ነው። «የዳዊት ልጅ ሆይ÷ ማረን» እያሉ የለመኑትን በምሕረቱ የጐበኘ እርሱ ነውና። ማቴ.9÷26። የመጻጉዕን /የበሽተኛውን/ ኃጢአቱን ያስተሠረየለት ይቅር ያለውና ከደዌውም ያዳነው እርሱ ነው። ዮሐ.5÷2።

ለምጻሙን ያነጻ፣ ጐባጣውን ያቀና... እርሱ ነው÷ ምሕረት

www.zeyeneta.com

ገንዘቡ ናትና። ስለዚህ ምሕረትን የሚሰጥ የሚያድል እንጂ የሚተበል አይደለም። ጌታም የዘግዊቷን ኃጢአቷን ይቅር ባለ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በልቡናቸው እንዲት ይህች ኃጢአተኛ ይህን ስታደርግ ዝም አለ በሚል በማማታቸው «ብዙ ዕዳ የተዉለት ትንሽ እዳ ከተዉለት ይልቅ የሚወድበት መውደዱ ይበልጣል።» ሲል በምሳሌ ከምሕረቱ ብዛት የተነሣ ዕዳዋን ኃጢአቷን ይቅር እንዳላት አስተምሯል። ስለዚህ ምሕረትን ከማን ሊተበል ጌታችን ያማልዳል?

ሐ/ መራጭ እንጂ ተመራጭ አይደለም፡-

«ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ» መዝ.88÷3 እንዲል እግዚአብሔር ለባለሟልነት የሚመርጣቸው÷ በመሐላ የሚያጸናላቸው÷ ቃል ኪዳን የሚገባላቸው ወዳጆች አሉት። ኤርምያስን ከአናቱ ማኅፀን፣ ዳዊትን ከበግ እረኝነት እየመረጠ እንደ ሾማቸው ሌሎቹንም ሁሉ ይመርጣቸዋል። ጌታችንም አማላጅ ባለሟሎቹን እርሱ የሚመርጥ እንጂ የሚመረጥ አይደለም። «... በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ÷ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ።» ሉቃ 6÷13፣ «እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ አልመረጣችሁኝም።» ዮሐ. 15÷16 እንዲል ጌታችን የሚመርጥ እንጂ የሚመረጥ አይደለም።

ስሙ የሚጠራበት ከተማ ኢየሩሳሌምን በሕገቡም ላይ እንዲ ነግሥ ዳዊትን የመረጠ እርሱ ነው። 2ኛዜና.6÷6። እግዚአብሔር ከባሕርይው ቅድስና የተነሣ ሰዎች የሚያቀርቡለትን ስጠታና ጸም ጸሎት መርጠ ይቀበላል። ኢሳ.58÷5፣ ዘፍ.4÷4። ቅዱስ ጳውሎስም በእግዚአብሔር የተመረጠ መሆኑ ተገልጿል። ሐዋ. 22÷14። ቅዱስ ጴጥሮስም በስብከቱ መመረጡን አስረግጧል። ሐዋ. 15÷7። ስለዚህ ጌታችን ለአገልግሎትም ለባለሟልነትም ሰዎችን የመረጠ፣ የሾመ፣ ኃይልንና ጸጋውንም የሰጠ እንጂ እርሱ የተመረጠ አይደለም። የእርሱ ክብሩም ሀብቱም የባሕርይው ነውና።

እነዚህን የመሰሉ ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንመረምር ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አለመሆኑን እንገነዘባለን። እርሱ ራሱ እግዚአብሔር ነውና። መዝ.46÷5፣ ሥራ.1÷19፣ ሮሜ.9÷5። ታድያ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈራጅ እንጂ አማላጅ ካልሆነ የእነዚህ ጥቅሶች ትርጓሜ ምን ማለት ነው ልንል እንችላለን፣ በሚቀጥለው ርእስ እንዳንድ ለምች ለዚሁ አላባቸው እንደ አስረጂ የሚያቀርቧቸውን እንዳንድ ጥቅሶች እንመለከታለን።

5.5. ምን ማለት ነው?

ሀ/ «ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ» ሲል ምን ለማለት ነው?

ጌታችን አማላጅ አይደለም ከተባለ «እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ÷ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰ ማለት።» /ዕብ.5÷7/ ምን ማለት ነው?

ይህ ጥቅስ በማያሻማ መንገድ የተገለጸ ነገረ ሥጋዌ ነው። ይኸውም ጌታችን ፍጹም አምላክ ቢሆንም ፍጹም ሰውና በሥጋው ወራት ከኃጢአት በቀር በሰው ያለውን ልማድ ሁሉ በሥጋዌ የፈጸመ ነው። ለአብ ነትም እንደ በላ እንደ ጠጣ፣ እንደ ተኛ፣ ለሞተ ሰው እንዳለቀሰ ተጽፏል። ማቴ.26÷20 ፣ ማቴ.14÷24-35፣ ዮሐ.11÷35። ጌታችን «እኔ መንገድ ነኝ» /ዮሐ.14÷6/ ብሎ እንዳስ ተማረን እርአያችን፣ ምሳሌያችንና መምህራችን በመሆኑም ጸሏል / ማቴ. 4÷1-10/፣ ጸልዮአልም /ሉቃ.22÷39-46/።

ጌታችን ሊቀ ካህናት ተብሎ ነበርና በሥጋው ወራት እንደ ካህናቱ አሪት የበግና የፍየል ደም ያቀረበ አይደለም። ይልቁንም ጸሎትን እንደ ላም፣ ልመናቅም እንደ በግ አድርጉ አቀረበ። እንድ

www.zeyeneta.com

ጊዜም ስለሆነ ያቀረበው ግዳጅ የሚፈጽም መሆኑን ሲያጠይቅ «በዐቢይ ገዳር መበለንብዕ፣ በፍጹም ኀዘንና በእንባ» አቀረበ አለ። «ከሞት ሊያድነው ወደሚችል» ሲልም ሰው ሁሉ በአንዱ አዳም እንደ ሞተና በጌታም ቤዛነት እንደ ዳነ ስለ ምእመናን በጌታችን መናገሩ ነው። የጌታችን የራሱ ሞትና ትንሣኤማ በሥልጣኑ እንደሆነ ምዕራፍ አንድ ላይ በሰፈው ስለ ተገለጸ ያንን መመልከት ያስፈልጋል። «እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰግለት» የሚለው «ወልድ» «በኩር» ሆኖ ላለ፣ አምላክነት ገንዘቡ ሆኖ ሳለ ፍጹም ሰው በመሆኑ ስለ አዳም ያቀረበው ቁርጥ ልመናው ተሰግለት፣ አምላክ ነኝ ልጸልይ አይገባኝም ሳይል ሰው በመሆኑ ታዝሏልና። ስለ መታዘዙም፣ እግዚአብሔርን ስለ መፍራቱም ቢል አንድ ነው፣ በአዳም ተገብቶ ነው እንጂ ጌታችን ከመ ከራ መስቀል በኋላ የሚያማልድ ሆኖ አይደለም። ሁሉን ነገር ያደረገው እኛ በብርቱ ጩኸት ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን በእግዚአብሔር ፊት እንድናቀርብ ለአብነት ነው። ምን ማድረግ እንደሚገባን መንገዱን ሲያሳየን ነው።

ለ/ «የአዲስ ኪዳን መካከለኛ» ምን ማለት ነው?

«የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ+ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል።» ዕብ.12+24፣ «አንድ እግዚአብሔር አለና+ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ+ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።» 1ኛጢሞ.2+5።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብቸኛም እውነተኛም የሰውና የእግዚአብሔር መካከለኛ ነው። ለምን?

1ኛ/ የነሣው ሥጋ የሰው ነውና

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የነሣው ሥጋና ነፍስ የሰው ነው። ይኸውም ትምክህታችን ከምትሆን ከቅድስት

ድንግል ማርያም ነው። ሉቃ.1÷26–45፣ ማቴ.1÷25፣ ማቴ.1÷1። ሥጋውን ከሰው ባይነሣው ኖሮ «ሰው» ሊባል አይችልም ነበር። የሰውና የእግዚአብሔር መካከለኛ ሊባልም አይገባውም ነበር። አምላክ የሆነ ሰው፣ ሰውም የሆነ አምላክ ከእርሱ በቀር የለምና «መካከለኛ» የተባለ ወልደ እግዚአብሔር የነሣው ሥጋ የሰው ስለሆነ ነው።

2ኛ/ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆኗልና።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ ከመንሣቱ በፊት በአካላዊ ቃልነቱና በመለኮታዊነቱ ነበረ። ሥጋም ውሱን ግዙፍ አካል የለው ባሕርይውም አዳግዊ፣ ሟች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ ነበረ። ከእመቤታችን ከተወለደ በኋላ ግን ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይም አንድ ባሕርይ ሆኗል። በመለኮት ብቻ እንዳይጠራ የሚዳሰስ፣ የሚጨበጥ፣ የሚበላ የሚጠጣ፣ የሚራብ የሚጠማ የሚደክም ሰው ሆኗል። «ሰው» ብቻ ነው እንዳንል ነፋሳትንና ማዕበላትን እንደ ነብያት «በእግዚአብሔር ስም»፣ እንደ ሐዋርያትም በቅድስት ሥላሴ ስም ሳይሆን በራሱ ጸጥ የሚያደርጋቸው፣ አጋንንትን በሥልጣኑ የሚያስወጣቸው በደረቅ ግንባር ላይ ዓይንን የፈጠረ፣ ውኃውን ወደ ወይን የለወጠ ነው። ስለዚህ ሰው ብቻ ነው፣ አምላክ ብቻ ነው ማለት አይቻልም።

ያልተዋሐዱ አካላትም ባሕርያትም በእርሱ አልታዩም። እርሱ አንድ ጊዜ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ነውና መካከለኛ መባል ተገባው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ይህን የእርሱን ሰውነትም አምላክነትም /አምላክ ወሰብእ/ /መካከለኛነት/ ለሚያምኑት ሥግው ቃል ክርስቶስ መሆኑን ለቅዱስ ጴጥሮስ ነግሮታል። ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ይሉታል? ብሎ ከጠየቀ በኋላ

www.zeyeneta.com

የሰዎችን አስተያየት ሰምቷል÷ ሐዋርያትንም ጠይቋል። ቅዱስ ጴጥ ሮስም ለሚጠይቀው ለወልደ ማርያም «አንተ ክርስቶስ የሕያው እግ ዚአብሔር ልጅ ነህ» ብሎ ሰውም አምላክም መሆኑን በተናገረ ጊዜ ጌታችን «... እኔም እልሃለሁ÷ አንተ ጴጥሮስ ነህ÷ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ÷ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም።» ሲል ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ይህ የወልደ እግዚአብሔር ሰው መሆንና «አንድ አካል አንድ ባሕርይ በመሆን» ሁለትነትን አጥፍቶ አንድነትን በማጽናት «መካከለኛ» የተባለበትን ምሥጢር አስተምሮናል። ማቴ.16÷14–20። እግዚአብሔር በአምላክነቱ በአዳም ላይ ርቱዕ ፍርድ ፈርዶበታል። ጌታችን በሥጋው ቃልነቱ በዚህ የአምላክነቱ ፍርድና በዓለም ጨዝት መካከል መካከለኛ በመሆን ራሱ መሥዋዕት፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ ራሱ መሥዋዕት አቅራቢ ሆኖ አስታረቀ። እንደሰውነቱ ዘመዳችንን፣ እንደ መለኮትነቱ ፈጣሪያችን በመሆኑ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያለ መካከለኛ ተባለ።

3ኛ/ የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ደሙን ከማፍሰሱ በፊት ስለ ሕዝብ የሚቀርበው መሥዋዕት በግ፣ ላም፣... መሆኑ ይታወቃል። ይህም ደግሞ የፍጡራን ሥጋና ደም ነበር። ጌታችን ግን ቀደም ሲል ይህን በበግና በፍየል ደም ኃጢአት አስተሥርዩ ብሎ የመሠረተውን ኪዳን ከእንስሳቱ በሚሻል ብቻ ሳይሆን ከደጉ ከአቤል ደምም የሚሻልን አምላካዊ ሥጋና ደም ለሥርየተ ኃጢአት ሰጠን፣ የቀደመውንም ኪዳን ሻረና አዲስ ኪዳንን መሠረተልን። «ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፦ እንካችሁ÷ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ

ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።» ማቴ.26÷26-28 እንዲል የአዲሱ ኪዳን መሥራች እርሱ ነው።

ከአቤል ደም ይሻላል ያሰኘው የአቤል ደም ጥንተ አብሶ ያልተለየው፣ የራሱንም ነፍስ ማንጻት የማይችል፣ «ወንድሜ ቃየን ገደለኝ» ብሎ የሚከስ የሚወቅስ ነው። የጌታችን ሥጋና ደም ግን ከኃጢአት የነጻ፣ ብዙዎችንም የሚያድን፣ እንደ አቤልም አይሁድ ገደሉኝ እያለ የሚከስ የሚወቅስ ሳይሆን አምነው የመጡትን ሁሉ የሚያድን ነው። ስለዚህም በእጅጉ ይበልጣል÷ የሚመስለውና የሚተ ካከለውም የለም። ጌታችን ሥጋውን ደሙን መሥዋዕት አድርጉ ካቀረበ በኋላ የሚቀርብ መሥዋዕት የለም። የሐዲስ ኪዳን ሐዋር ያትም የሚፈትቱት በሰለተ ዓርብ ጌታችን ያቀረበውን የእርሱን ሥጋና ደም እንጂ ቤተ ክርስቲያን ሌላ መሥዋዕት የላትም።

ስለዚህ ለብሉይ ኪዳን ካህናትና ለሐዲስ ኪዳን ካህናት አገልግሎትም ሆነ የሹመት ሥርዓት፣ ለክህነቱም የሥልጣን ልዩነት መካከለኛው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፣ ስለዚ ህም መካከለኛ መባል ተገባው። ጌታችን ስለ ራሱ ሲያስተምር ግንበኞች የናቁት የማዕዘን ድንጋይ በማለት የገለጠውን አውግስጢ ኖስ ዮተ ባለው የሰሜን አፍሪካ ሊቅ ሲተነትነው የማዕዘን ድንጋይ ሁለቱን ግንቦች /የግራና የቂኝ መሥመር/ የሚያገናኝ ከሁለቱም የሚቆጠር ድንጋይ ነው። የሁለቱም መሥመር ግንቦች አካል ሆኖ ይቆጠራል። ላንዱ መሥመር መጨረሻ ሲሆን ለሌላኛው መጀመርያ ይሆናል። የጌታም መካከለኛነት እንዲሁ ነው። ለብሉይና ለሐዲስ መካከለኛ ነው። የብሉይ ፈጻሚ የሐዲስ ጀማሪ ሆኖ ከሁለቱም ይቆጠራልና። እርሱ ባይወለድና መንገድ ባይሆን ኖሮ የብሉይን ቅዱሳን ከሐዲስ ኪዳን ቅዱሳን የሚያገናኝ አይኖርም ነበር ይላል።

www.zeyeneta.com

የብሉይ ኪዳን ካህናትና የሐዲስ ኪዳን ካህናት በሹመትም በአገልግሎትም እንደሚለያዩ ምሰራፍ ሦስትን ይመልከቱ::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተለያይተው የነበሩትን ሰውንና እግዚአብሔርን በመሸምገል ሳይሆን ራሱ በተለየ አካሉ ባለው የተወላዲነት ግብር ሥጋን ተዋሕዶ ሰው የሆነበት፣ ሰውም በተዋሕዶ ቃል እግዚአብሔር የሆነበት ፍጹምና እውነተኛ «የአዲስ ኪዳን» መካከለኛችን ነው:: የቤተ ክርስቲያን መሠረቷም «ወልደ ዋሕድ» ብሉ ቅዱስ ጴጥሮስ የመሰከረው ጌታችንም «ዐለት» ያለውና የመናፍቃን ትምህርት የማያናውጸው መሠረተ እምነት የሐዋርያትም ትምህርት ነው:: ስለዚህ በአጭር ቃል «መካከለኛ» ማለት «ወልደ ዋሕድ» ማለት እንጂ አማላጅ ማለት አይደለም::

ሐ/«ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን» ማለትስ ምን ማለት ነው?

«ጠበቃ» በራሱ ፈራጅ አይደለም፣ «ፈራጅም» ጠበቃ አይደለም፣ ምናልባት በዚህ ዓለም ሕይወት በአንዱ ሀገር በዳኝነት የሚሠራው በሌላ አገር ጠበቃ ሊሆን ይችል ይሆናል ይሁን እንጂ በአንድ ጊዜ ዳኛም ጠበቃም የሆነ የለም:: ያም ሆነ ይህ ዳኞችም፣ ጠበቆችም የአገር ሕገ መንግሥት በሚፈቅድላቸው መሠረት የሚሾሙና የሚያገለግሉ እንጂ በራሳቸውና በሥልጣናቸው ፍጹማን አይደሉም:: በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ይህ ሁሉ የለበትም::

ፍጹሙ ዳኛና ፈራጅ እርሱ ነው:: ሹመቱም የባሕርይው ነው:: ለምድራያውያንም ሥልጣንን የሰጣቸውና የሚሰጣቸው እርሱ ነው:: ሮሚ.13÷1–6:: ስለዚህ ጌታችንን ጠበቃ ማለት የሚገባ አይደለም:: ግእዛችን እንዲህ ይላል:: «ደቂቅየ ዘንተ እጽሕፍ ለክሙ ከመ ኢትአብሱ፡ ወእመኒ ቦ ዘአበሰ ጸራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ «ጻድቅ ውእቱ ይኅድግ ለነ ኃጣውኢነ:: ልጆቼ ሆይ÷ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ:: /1ኛዮሐ.1÷5–10/ ኃጢአትን የማያደርግ ካለም ክርስቶስ ከአብ ዘንድ የሚሰድልን ጸራቅሊጦስ

አለን:: ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ቸር የባሕርይ አምላክ ነው::» 1ኛዮሐ.2÷2 አለ እንጂ ስለ ጠበቃ የሚገልጽ የለውም::

አሁን በምንጠቀምበት የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ «ጠበቃ» ተብሎ መጻፉ ግን አማላጅ ነው አያሰኝም:: መልእክቱን ስንመረምረው የሚያስረዳው ሌላ ነውና:: 1ኛዮሐ.1÷5 እስከ 2÷6 ድረስ ያለው የሚናገረው ስለ ኃጢአትና ንስሐ ነው:: መልእክቱን የሚጀምረውም በዘመኑ የነበሩ የግኖስቲኮችን ባሕል /መዳን በዕውቀት ነው የሚሉ/ በማፍለስ ነው:: ምክንያቱም ግኖስቲኮች ንስሐን የሚቃወሙ ነበሩ:: የሚናገሩትም /የሚያስተምሩትም/:– 1ኛ– ከእግዚአብሔር ጋር የሚፈጠር ኅብረት ከኃጢአት መለየት ነው:: ስለዚህም የፈለግነውን ብናደርግ ኃጢአት በእኛ ዘንድ ሊኖር አይችልም:: 2ኛ– ኃጢአት የለብንም /የለምም/፤ ምክንያቱም አንድ ጊዜ ጌታን ተቀብለናልና በምንሠራው ሥራ በደለኞች አይደለንም፣ ኃጢአትን አንድ ጊዜ አጥፍቶልናል:: 3ኛ– ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያለው ሁሉ ኃጢአት አይሠራም የሚሉ ንስሐን የሚቃወሙ ትምህርቶች ስለ ነበሯቸው የቅዱስ ዮሐንስ መልእክት የሚያጠነጥነው ለእነዚህ መልስ በመስጠት ነው::

1ኛ/ «ከእግዚአብሔር ጋር አኖራለሁ» ብሎ የሚያምን ሁሉ እምነቱን በሥራ መግለጥ አለበት:: «ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም ብንመላለስ እንዋሻለን÷ እውነትንም አናደርግም፣ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን» በማለት ከክርስቶስ ጋር ያለን ኅብረት እምነታችንን በምግባር ስንገልጽ ነው በማለት መልሷል::

2ኛ/ ኃጢአት ተወግዷል ለሚለውም ትምህርታቸው እኛ በምንሠራው እንደምንበድል «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል:: ኃጢአት የለብንም፣ ብንል ራሳችንን እናስታለን÷

www.zeyeneta.com

እውነትም በእኛ ውስጥ የለም::» በማለት አስረግጦ መልሷል::

3ኛ/ ከዚህ አመለካከት የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያላቸው ኃጢአትን አይሠሩም፤ ሥራቸው ሁሉ የጽድቅ ነው ለሚሉት «ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም::» በማለት ንስሐን ይሰብክላቸዋል:: «በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው::» ይላልና::

በዚህ መንገድ ለጥያቄዎቻቸው መልስን በመስጠት የንስሐ ፋጻሜውና ኃጢአታችን በማስተሥረይ በእግዚአብሔር አብ ፊት እንድንቆም የሚያበቃን የልጁን ሥጋና ደም መቀበል ነው፤ ለማለት የተናገረው ነው:: ይህም ማለት ኃጢአትን ብንሠራ በምን ኃጢአታችን ያስተሠርይልናል ብላችሁ አትጨነቁ:: «ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: እርሱም የኃጢአታችን ማስተሥረያ ነው» /1ኛዮሐ. 2÷1–2/ በማለት «ጠበቃ» ተብሎ የተገለጸው ስንቀበለው ኃጢአታችን የሚያስተሠርየው ሥጋውና ደሙ እንደ ሆነ አስቀምጦታል:: «ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ::» በማለት ሥጋወ ደሙ ስለ ዓለም ኃጢአት የተሰጠ መድኃኒት መሆኑን አስቀምጧል:: ከዚህም በመቀጠል ከንስሐ በኋላ በምግባር እንድንኖር ያስተምረናል::

ግን ይከራከረዋል?

«ጠበቃ»+ ተከራካሪ አግላጅ ነው ካልን ጌታን የሚከራከረው ለመሆኑ ማን ነው?

በመጽሐፍ ቅዱስ መላእክትም ሰዎችም ከርኩሳት መናፍስት ጋር መከራከራቸው ተጽፏል:: ለአብነትም በይሁዳ ቁ. 9 ላይ የመላ እክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ስለ ሙሴ ሥጋ ከዲያብሎስ ጋር እንደ ተከራከረና በእግዚአብሔር ስም እንደ ገሠጸው ተጽፏል:: ቤሐ

ዮ.19+11 ላይም ስንመለከት ርኩሳን መናፍስት ደቂቀ አስቄዋን እንደ ተከራከሩና እንዳሸነፏቸው ተጽፏል:: ጌታችንስ የሚከራከረው ማንን ነው? ምክንያቱም ኢጋንንት ጌታችንን ቁመው ሊከራከሩ እንደማይችሉ ተመልክተናል፤ በማቴ.8+28 ላይ «... የእግዚአብሔር ልጅ+ ከአንተ ጋር ምን አለን?» እያሉ ገና በፋቁ እየጮሁ እንደ ወጡ ይልቁንም ጌትነቱን ወውቀው ለምነው እንደ ተቀበሉ ተጽፏል:: በማቴ.17+14 ላይም ለደቀ መዛሙርቱ ያስቸገረው ጋኔን በጌታችን በተገለጸ ጊዜ ፈጥኖ ወጣ እንጂ አልተከራከረም::

ታድያ ጌታችንን ሊከራከረው የሚችል ማን ነው? «ሁሉ በእርሱ ሆነ» ዮሐ.1+3 የተባለለት የሁሉ ፈጣሪ ነውና:: «ከሠሪው ጋር ለሚታገል ወዮለት! በምድር ሸክላዎች መካከል ያለ ሸክላ ነው:: ጭቃ ሠሪውን:– ምን ትሠራለህ? ወይስ ሥራህ:– እጅ የለውም ይላልን? አባትን:– ምን ወልደሃል? ወይም ሴትን:– ምን አማጥሽ? ለሚል ወዮ!» ኢሳ.45+9–10:: «እንግዲህ ስለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነትፋል? ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው? ትለኝ ይሆናል:: ነገር ግን+ አንተ ሰው ሆይ+ ለእግዚአብሔር የምትመልስ ማን ነህ? ሥራ ሠሪውን:– ስለ ምን እንዲህ አድርገህ ሠራሽኝ ይለዋልን? ወይም ሸክላ ሠሪ ከአንዱ ጭቃ ክፍል አንዱን ዕቃ ለክብር አንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ ሥልጣን የለውምን?» /ሮሜ.9+19–20/ እንዲል ፈጣሪን ሊከራከር የሚችል የለም::

በውኑ እርሱ ጠበቃ ሆኖ የሚከራከር ከሆነ በፍርዱ ዙፋንስ ላይ ማን ይቀመጣል? ስም አጠራሩ በቅዱሳኑ አንደበት ከፍ ከፍ ይበልና በክብሩ ዙፋን የሚቀመጠው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: «የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ+ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን

www.zeveneta.com

ይቀመጣል::» /ማቴ.25÷31/ ተብሎ ፈታሒ በጽድት ኑናኔ በር'ትሱ መሆኑ በግያሻግ መንገድ ተገልጧል::

ስለዚህ ጌታችን «ጠበቃ» አይደለም:: ዋናው ነገር ያለው በስሙ አምነን ተጠምቀን ንስሐ ገብተን የምንቀበለው ሥጋና ደሙ ከኃጢአታችን የሚያነጻን መሆኑን፣ የንስሐችን መፈጸሚያ÷ ፍጹም የኃጢአት ሥርየት ማግኛ መሆኑን በመናገር እንጂ «አማላጅ ነው» የሚያሰኝ ምንም ዓይነት ትርጉም የለውም::

መ/«ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው» የሚለውስ?

«የሚያጸድት እግዚአብሔር ነው÷ የሚኮንንስ ማን ነው? የሞተው÷ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው÷ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው÷ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው::» ሮሜ.8÷34:: «...እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል::» ዕብ.7÷24–25::

እነዚህ ጥቅሶች ጌታችንን «አማላጅ» ነው በማለት የሚያስተላልፉት መልእክት የለም:: የሰው ልጆች ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት አምነው ሲመጡ ወደ እግዚአብሔር ቀረቡ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሆኑ የሚባሉት በስመ ሥላሴ ተጠምቀው የወልደ እግዚአብሔርን ሥጋና ደም ሲቀበሉ ብቻ ነው:: ይህ የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ደግሞ እንደ አሪት መሥዋዕት በአንድ ቀን የሚያልቅ፣ ለእስራኤል እንደ ወረደውም መና በጊዜ መብዛት የሚለወጥ የሚበላሽ አይደለም:: ሁልጊዜ አዲስና ለዘላለሙ በሕይወት የሚኖር ነው:: «ሕያው» መባሉም ነፍስ ስለ ተዋሐደው ሳይሆን «መለኮት» ስለማይለየው

ነው:: ይህ ሕያው ሥጋውና ደሙ ሁልጊዜ ሰውን ወደ እግዚአብሔር ሲያቀርብ የሚኖር ከእግዚአብሔርም ጋር የመታረቂያው ብቸኛ መንገድ በመሆኑ እግለጸን /አስታረቀን/ ሲል ገልጠታል::

በዕብራውያን ላይ ያለውን ስንመለከተው ደግሞ የበለጠ መልዕክቱን ግልጽ ያደርገዋል:: «ሊያማልድ በሕይወት ይኖራል» የሚለው እንደ ጥሬ ንባቡ ከሆነ ጌታችን አሁንም በሕይወተ ሥጋ በዚህ ምድር መኖር አለበት፤ ጌታችን ግን እንደ ዐረገ «በየማነ አብ» በአብ ዕሪና እንደ ተቀመጠ በምዕራፍ አንድ ላይ ተመልክተናል:: ይህን የበለጠ ለመረዳት የሚከተሉትን ነጥቦች በድጋሚ እናስ ታውሳቸው::

ጌታችን በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ የሚለውን ዘግብራራት ስንገልጠው «አንድ ጊዜ ሰውም አምላክም አምላክ ወሰብእ ነው» ብለናል:: ይህም አንድ ጊዜ ግዙፍም ረቂቅም፣ ውሱንም ምሉዕም ነው ማለታችን ነው:: ሲገዝፍ ርቀቱ ያልቀረበት፣ ሲወሰንም ምልዑቱ ያልጐደለበት ማለት ነው:: እንደዚህም ሁሉ ጌታችን በተሰቀለበት ዕለት ሦስት ነገርን አንድ ጊዜ ሁኗል:: መሥዋዕት አቅራቢ ካህን፣ መሥዋዕት /ለዓለሙ አንድ ጊዜ የቀረበ/፣ ራሱ መሥዋዕት ተቀባይ:: ከዕርገቱም በኋላ ይህን ሦስት ነገር አንድ ጊዜ መሆኑን ከእርሱ የወሰደበት የለም:: ከእርሱ በኋላ ለቤተ ክርስቲያን ሌላ መሥዋዕት የላትም፣ ሌላም ሊቀ ካህናት ራሱን መሥዋዕት አድርጉ ያቀረበ የላትም፤ ልሁን ብሎ ቢመጣም አትቀበለውም፤ ከእርሱ የበለጠ የተሻለም የለም፤ አያስፈልጋትምና:: ሌላ ይቅር ባይ÷ ጸሎት ሰሚ÷ ጉዳይ ፈጻሚም አሥላክ ከእርሱ በቀር ሌላ የላትም:: እነዚህን ሁኔታዎች ግን የቤተ ክርስቲያን መምህራንና ሊቃውንት በተለያየ መንገድ ገልጸዋቸዋል::

በአንድ ጊዜ «የቆመ ካህን የቆመጠ ንጉሥ» የሆነ ጌታ

www.zeyeneta.com

ብቻ ነው። ቁሞ የተቀመጠ ተቀምጠም የቆመ የለምና።

ይኸውም «መሥዋዕት ተቀባይ» መሆኑን «የተቀመጠ ንጉሥ»÷ በአባቱ ቀኝ ተቀምጧል በማለት ገልጸውታል። «መሥዋዕት አቅራቢ» መሆኑን ደግሞ «የቆመ ካህን» ይሉታል÷ «እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ» ተብሏልና። «መሥዋዕት» መሆኑን ደግሞ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «ያማልዳል ያስታርቃል፣ ጠበቃችን» ነው በማለት እንደ ተገለጸ እንመለከታለን። ይህ የሚገልጸው ጌታችን በአንድ ጊዜ ሦስቱንም መሆኑን ነው። ምንም እንኳን ስለ መሥዋዕት ወደፊት በምዕራፍ 10 ላይ የበለጠ የምንመለከት ቢሆንም በዚህ ቦታ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ገለጠው ሕያው ሆኖ የሚኖርና ዕለት ዕለትም የሚሠዋ ነፍስንና ሥጋን የሚቀድስ ነው። ይኸውም አንድ ጊዜ በዕለተ ዓርብ በፈጸመው አገልግሎት ሁልጊዜ በሥጋውና በደሙ የሚያድነን÷ ስለሆነ ነው። ይኸውም ዛሬ የምንሠዋው መሥዋዕት /ሥጋወደሙ/ ከዕለተ ዓርቡ ጋር ኅብረት አንድነት ያለው፣ በምንም ያልተለየ ነፍስ የተለየው መለኰት የተዋሐደው በመሆኑ «ዘወትር ሲያማልድ በሕይወት ይኖራል» ተባለ።

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜም ሆነ በዚህ በዕብራውያን መልእክቱ በሌሎቹም ቢሆን በአጽንዖት የሚገልጠው ያለ ሥጋውና ደሙ የድኅነት መንገድ አለመኖሩን ነው። ሥጋውና ደሙ ሁልጊዜ ሕያው ሆኖ እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚያምኑት ሁሉ የሚፈተትና ብቸኛ መቅረቢያችን መሆኑን ለመግለጥ ስለ እኛ የተደረገውን ለማሳየት የተናገረው ነው። የግእዝ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ስንመለከት «ወይትዋቀስ በእንቲኣነ» ይላል፡ «ወቀሰ» አማለደ ማለት አይደለም። ወቀሰ÷ «ወቀሰ» /የኋለኛው ጠብቆ ይነበብ/ ተከራከረ፣ ፈረደ ማለት ነው። በ1938 ዓ.ም የታተመው አዲስ ኪዳንም «ስለ እኛ ይፈርዳል» ሲል ተርጉሞታል። ተከራከረ፣ ተዋቀሰ የሚለውን ትርጉም

እንኳ ቢይዝ ንግግሩ «ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚኣብሔር» ኢሳ.1÷18 የሚለውን ይመስላል። ይህም ማለት እግዚኣብሔርና ሰው ተቀምጠው የሚከራከሩ ሆነው አይደለም፤ ራሱን በሰው ወገን አስገብቶ ስለ እኛ ያለውን የንስሐን ጥሪ በመግለጽ መናገሩ እንጂ።

በቤተ ክርስቲያናችን እነዚህ «ያማልዳል÷ ያስታርቃል» የሚሉት ሥጋውንና ደሙን የተመለከተ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል። ሥጋውንና ደሙን የምንቀበለው በቅተን ነቅተን ሳይሆን የምና ስታውሰውን ኃጢኣት ተናዝዘን÷ ቀኖናችን ፈጽመን ቢሆንም የበቃን የነጻን አይደለንም። ይልቁንም ስለ ሥጋሀና ደምህ ይቅር በለን እያልን እየለመንን እንቀበለዋለን። በዚህ ጊዜም ከእግዚኣብሔር ጋር እንታረቃለን፤ ለማለት እንጂ በመስቀል ላይ ከፈጸመው የማስታረቅ ሥራ በኋላ ጌታችን የአማላጅነትን ሥራ ስለሚሠራ አይደለም። «አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢኣትን ሊሸር አንድ ጊዜ ተገልጧል። ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም ፍርድ እንደ ተመደበባቸው÷ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ÷ የብዙዎችን ኃጢኣት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢኣት ይታይላቸዋል።» ዕብ.9÷26–28።

በሮሜ 8÷31–35 ያለውን ሙሉውን አንቀጽ ስንመለከተው ሙሉ ቅዱስ ጳውሎስ በዘመኑ ለነበሩት መናፍቃን የሰጠው መልስ ሦሥቲረ ተዋሕዶን የሚገልጽ ነው። በዘመኑ ሥጋ መለኰትን ውጠታል፣ መለኰት ሥጋን «አርቆታል» የሚሉ መናፍቃን ስለ ነበሩ ያለ መጠፋፋት ያለ መቀላቀል በተዋሕዶ አንድ አካል መሆኑን ሊያጠይቅ እግዚኣብሔር ለገዛ ልጁ ሳይራራ ሰጥቶናል በሚል የተሰቀለው ወልደ እግዚኣብሔር መሆኑን÷ ወደፊትም የሚያጸድቀውም የሚኮንነውም እርሱ እንደ ሆነ መለኮታዊ ባሕርይውን÷ ተናግሯል። የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት አስረጂነቱ መለኰታዊና

www.zeyeneta.com

ሰብአዊ ባሕርይን በተዋሕዶ አንድ እንዳደረገ /አምላክም ሰውም መሆኑን/ ማስረዳት ነው።

5.7. ማጠቃለያ

ምልጃ ጥልትና ሰፊ ምሥጢር ያለው ትምህርት ነው። አፈጻጸሙም ብዙ ነው። ለምሳሌ ያህል ቅዱሳን ራሳቸው ይማል ዱልናል ይጸልዩልናል። እኛም ራሳችን ደግሞ እግዚአብሔርን እን ማልደዋለን። የምንማልደው ግን በትዱሳኑ ብቻ አይደለም፣ እን ማልደዋለን። ስለ ምሕረትህ፣ ስለ ቸርነትህ፣ ሰው ሆነህ ስለ መገለጥህ፣ ስለ ልዩ ምስትንትህ... ብለህ ማረን እንለዋለን። በዚሁ መንገድ ለዓለም መድኃኒት አድርገህ ስለ አቀረብከው ስለ ሥጋህና ደምህ ብለን እንለምነዋለን። ይህም ስለ ባሕርይ ቸርነትህ ማለታችን እርሱን «አማላጅ» ነው እንደማያሰኝ ሁሉ «ስለ ሥጋህና ደምህ» ብለን መለመናችን ወልደ እግዚአብሔርን አማላጅ አያሰኘውም።

«ሥጋውና ደሙ» ግን ፍጹም ድኅነትን የምናገኝበት ነው። ቅዱሳት መጻሕፍትም ይህንኑ ያስረግጣሉ። የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም የሥጋውንና ደሙን ፍጹም ሕይወትነትና ሥጋውን ደሙን በሚገባ ተቀብሎ ሲኖል የሚወርድ እንደ ሌለ ሲገልጡ «ከምሥጢራትም ሁሉ ምሥጢረ ቁርባን ይበልጣል።» ብለዋል። ሲያብራሩት እንደ ምሳሌ ምሥጢረ ጥምቀትን በመውሰድ ያነጻጽሩ ታል። በምሥጢረ ጥምቀት የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን። ወላጅ ደግሞ ልጁን ሊከደው ይችላል። ይሽንን በተመለከተም «በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።» ማቴ.10÷33 ብሏል።

ሥጋውን ከበላን ደሙን ከጠጣን ግን አይክደንም። ምክንያቱም «ራሱን ሊክድ አይችልምና» በማለት ይገልጡታል። ስለዚህ «ሥጋውና ደሙ» በሕይወት የሚኖር መድኃኒታችን ሕይወታችን ነው፤ ስለ በላነው ስለ ጠጣነው ሥጋህና ደምህም ብለን እንለምን

ዋለን÷ እግዚአብሔርም ይቅር ይለናል፡ የጌታችን ሥጋውና ደሙ አምነው ለሚመጡት ሁሉ ዘወትር ሲፈተት ይኖራል።

ጌታችን ዐርጓል። ሐዋ.1÷9። ዳግመኛም ለፍርድ ይመ ጣል። ሐዋ.1÷11። በዚያም ሥጋን ተዋሕዶ በመንበረ ልዕልናው ታይቷል። ሐዋ.7÷56። ከዚህ በኋላ ስንኳን ለጌታችን ለጻድቃን ለሰ ማዕታትም በሰማያት ስለ ሰው መከራ መቀበል የለባቸውም። በዚህ ምድር በሠሩት ሥራ ከድካማቸው አርፈው ቃል ኪዳናቸው /ልመ ናቸው/ ሲያስምረን ይኖራል እንጂ። ራዕ.14÷13። ስለዚህ የእነዚህ ጥቅሶች መልእክት አንድ ጊዜ በመስቀል ላይ በፈጸመው የማዳን ሥራ ሁልጊዜ ስንታረቅ የምንኖር መሆናችን ለመግለጥ ነው።

«አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን ለዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋልና።» ዕብ.10÷14፤ «የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል።» ዕብ.9÷28። «ያለ ኃጢአት ይታይላቸ ዋል» ሲልም መጀመሪያ ስለ ኃጢአት ሊሠዋ መገለጡን፤ ሁለተ ኛው ግን ለፍርድ የሚመጣ መሆኑን ለመግለጥ ነው። «ራሱን ባቀ ረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና» /ዕብ.7÷28/ እንዲል ጌታችን ራሱን ባቀረበ ጊዜ ሁሉንም «ተፈጸመ» በማለት ፈጽሞ ታል። ዮሐ.19÷30።

እንደ ጥሬ ንባቡ «ጌታን አማላጅ ነው» ካልን ሌላ አምላክ አለ ያሰኝብናል። ምክንያቱም በጥሬ ንባብ /ሮሜ.8÷27/ መንፈስ ቅዱስንም ይማልዳል ተብሏልና፤ በኢር.7÷25 ላይም «አባቶቻችሁ ከግብጽ ምድር ከወጡበት ቀን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ÷ በየዕለቱ እየማለድሁ ባሪያዎቼን ነብያትን ሁሉ ልኬባችሁ ነበር።» የሚል ጽሑፍ አለ። ከላይ ስለ ወልደ የተቀመጠውንም ጨምረን ስንመለከት አብንም፣ ወልድ ንም፣ መንፈስ ቅዱስንም አማላጅ ካልናቸው የሚማለደው ማን ነው?

www.zeyeneta.com

የሥላሴ አምላክነትስ ምኑ ላይ ነው? ስለዚህ ጌታችን አማላጅ አይደለም፣ ፍጹም የባሕርይ አምላክ ነው። «አይጮኽም ቃሉንም አያነሣም÷ ድምፁንም በሜዳ አያሰማም። የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም÷ የሚጤስንም ክር አያጠፋም፤ በእውነት ፍርድን ያወጣል። በምድርም ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም፤ አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ።» /ኢሳ. 42÷2–4/ እንዳለ ተማላጅ እንጂ አማላጅ አይደለም። «እነሆ÷ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ÷ ፊተኛውና ኋለኛው÷ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ራዕ.22÷12–13።

ምዕራፍ ስድስት

መሠረት

«ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠረትን ደግመን አንመሥርት÷ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት÷ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን፣ ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው።» ዕብ.6÷1–2 በሚለው መነሻነት በዚህ ምዕራፍ ቅዱስ ጳውሎስ መሠረት ያለው ምን እንደ ሆነና ደግመን መመሥረት የማንችለውን ነገር በማብራራት በዚህ ርዕስ ሥር እንመለከታለን።

6.1. «መሠረት» የተባለው ምንድን ነው?

በቅዱሳት መጻሕፍት «መሠረት» የተባለ «ወልድ ዋሕድ» የሚለው እምነት ነው። ይህንንም ከሰው ወገን ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስ በመጀመሪያ በመመስከሩ ጌታችን መሠረትነቱን በጊዜው አሳውቋል፤ ወንጌላዊውም ጽፎልናል። «ኢየሱስም...እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ÷ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ÷ አንተ ጴጥሮስ /ዐለት/ ነህ÷ በዚችም ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ÷ የገሃነም ደጆችም አይችሏትም።» ማቴ. 16÷15–18 ተብሎ እንደ ተጻፈ።

ይህን መሠረተ እምነት ጌታችን ሞሠረተ ቤተ ክርስቲያን አደረገው። ምእመን የሚመሠረተውና የሚታነጸው በዚህ ትምህርት

www.zeyeneta.com

ላይ ነውና። ትምህርቱ ሲለወጥ አምልኩ ይለወጣል፣ አምልኮት ከተለወጠ ደግሞ መሠረቱም ተስቷል /ተለቅቋል/ ማለት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መሠረት ቀደም ብሎ በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ ገልጾታል። «የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ። ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።» በማለት የንባቡን ትርጓሜ አስተምሯል። 1ኛቆሮ.3÷10–11።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑና ይልቁንም ሰው ሆኖ መገለጡ የቤተ ክርስቲያን መሠረት መሆኑን ነብያትም አስቀድመው በትንቢት «ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እነሆ÷ በጽዮን ድንጋይን ለመሠረት አስተምጣለሁ፣ የተፈተነውን÷ የከበረውን÷ መሠረቱ የጸናውን የማዕዘን ድንጋይ የሚያምን አያፍርም።» ኢሳ.28÷16፤ «ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፣ ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፣ ለዓይናችንም ድንቅ ናት።» መዝ.117÷22 በማለት ጽፈው ታል። አስራኤል ከግብጽ በሚወጡበት ጊዜ ውኃ ከወለት እየፈለቀላቸው ጠጥተዋል። ይሄም የጌታችን ምሳሌ ነበር። «...ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋልና፥ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበረ።» 1ኛቆሮ.10÷4 እንዲል።

በሌላ ሁኔታም ይህን ትምህርት ነብያትም ሐዋርያትም ማስተማራቸውንና ለቤተ ክርስቲያን መመሥረት ብቻ ሳይሆን መስፋትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገውን የእነርሱን ስብከት «መሠረት» በማለት ሲገልጡት «በሐዋርያትና በነብያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል÷ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።»

ኤፌ.2÷20 «በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡር ወደሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ÷ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ÷ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።» 1ኛጴጥ.2÷4–5 ብለዋል።

ጌታችንም በመዋዕለ ሥጋዌው የተራራው ላይ ስብከቱን ያጠናቀቀው በዚህ ትምህርት ነበረ። «ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዐለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል። ዝናብም ወረደ ጒርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው÷ በዐለትም ላይ ስለ ተመሠረተ /ወልድ ዋሕድ በሚለው የሃይማኖት ትምህርት የጸና ስለሆነ/ አልወደቀም።...» ማቴ.7÷24–28 በማለት በዚሁ ትምህርት ነበር።

ስለዚህ መሠረት የተባለው ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ ሦስት መልሶች አሉት እኒህም፦

1ኛ. «ወልድ ዋሕድ» የሚለው የቅዱስ ጴጥሮስ እምነት /ይኸውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።/

2ኛ. ስለ ወልድ ዋሕድ የነብያትም የሐዋርያትም ትምህርት

3ኛ. በእምነት ለሚኖረው ደግሞ ፈቃደ እግዚአብሔርን የሚያውቅበት ፈቃደ ካህን ምክረ ካህን ናቸው። በእነዚህ ሦስቱ ጸንቶ የሚኖር ሁሉ ጠላቱን ዲያብሎስን ድል ይነሣል፣ ማዕበሉ ዝናቡም ጒርፉም ነፋሱም ቢገፋት እንኳ ሊያናውጡት አይችሉም። ማቴ.16÷9፣ ማቴ.7÷25። ቤተ ክርስቲያንም ሌላ መሠረት የላትም፣ ሕንፃዋ ሁሉ በዚህ ላይ የታነጸ ነው። 1ኛቆሮ.3÷11። ከዚህም ሌላ የመንግሥተ ሰማያት በር የለም፣ ቁልፉን የተረከበው ቅዱስ ጴጥሮስ እምነቱ ከላይ የተገለጠው ነውና። ማቴ.18÷18። ከዚህም

www.zeyeneta.com

ውጭ በቤተ ክርስቲያን የተተከለ የሃይማኖት ትምህርት የለም፤ ይህንኑ የተተከለውን እናጠጣዋለን÷ እንንከባከበዋለን እንጂ:: 1ኛቆሮ. 3÷6–9::

6.2. መሠረትነቱ ለማን ነው?

ይህ ጥያቄ በምዕራፉ ርዕስ የተመለሰ ሊመስለን ይችላል፤ አዎን ተመልሷል፤ ይሁን እንጂ ይበልጥ መብራራት ስለሚገባው በንዑስ ርዕስነት ልናነሣው ተገደናል::

ሀ/ ለቤቲ ክርስቲያን:- እኛ አያንዳንዳችን «ክርስቲያን» የሚለውን ስም ያገኘነው ክክርስቶስ ነው:: ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን የምትባለው ክርስቲያኖች ሥርዓተ አምልኮታቸውን ለመፈጸም፤ ሥጋውን ደሙን ለመቀበል የሚሰባሰቡባት ሕንፃ ቤተ መቅደስ ብቻ አይደለችም:: ይልቁንም በክርስቶስ ክርስቲያን የተባሉ የክርስቲያኖች አንድነት÷ የምእመናን ክርስቶስ ጉባኤ ናት እንጂ:: ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአ ብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን? ማንም የእግዚአ ብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና÷ ያውም እናንተ ናችሁ::» 1ኛቆሮ.3÷16–17 በማለት ገልጦታል::

«የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና» የሚለው የቤተ መቅደሱን አንድነት ሲያመለክት ነው:: አንዱ ቤተ መቅደስ የእኛ የብዙዎች ስብስብ መሆኑን ያመለክታል:: ቤተ ክርስቲያንም የተባለው ይኸው የእኛ አንድነት ነው:: ቤተ ክርስቲያንም አንዲት ናት ነገር ግን በሁሉም ያለች ናት:: እግዚአብሔር አንድ ሆኖ የሌለበት ቦታ እንደ ሌለ ሁሉ የእርሱም ቤተ ክርስቲያን አንዲት ሆና በሁሉ ያለች ናት፤ መንፈሳዊትና ቅድስት ናትና:: «...እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና

ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለራሱ አንዲያቀርብ ፈለገ::» ኤፌ.5÷27 እንዲል::

ቤተ ክርስቲያን የታነፀችው በእዚህ መሠረት ላይ ነው:: የምትታነፀውም በዚሁ ላይ ነው:: «የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና::» 1ኛቆሮ.3÷9:: «በሐዋርያትና በነብያት መሠረት ላይ ታንፃችኋል÷ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክር ስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንፃ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚ አብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ::» ኤፌ.2÷20–22 እንዲል::

ለ/ ለምእመን:- አንድ አማኝ በግሉ «ወልድ ዋሕድ» ብሉ ካላመነ የቤተ ክርስቲያን አባል ሊሆን አይችልም:: ከግንዱ የተለየ ቅርንጫፍ በራሱ የሞተ ነውና:: የግንዱንም ፍሬ ካላፈራ ተቆርጦ ወደ እሳት ይጣል ዘንድ አለውና:: ዮሐ.15÷6:: አንድ ምእመን በእምነቱ ጸንቶ መኖር የሚቻለው ምግባርም ሠርቶ የሚጠቀመው በዚሁ መሠረት ላይ ሲታነፅ ብቻ ነው::

መሠረት አድርጉ ካልታነፅበት የእንቅፋት ድንጋይ አድርጉታልና ይወድቅበታል ይሰነካከልበታል እንጂ አይታነፅበትም አይጠቀምበትም:: «እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፤ ለማያምኑ ግን አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የፅ ንቅፋትም ድንጋይ የማሰናከያም ዐለት ሆነ፤ የማያምኑ ስለሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው::» 1ኛጴጥ.2÷7–8 እንዲል::

አንድ ምእመን ይህን እምነቱን ለማጽናት የሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ጠብቆ መገኘት አለበት:: አልያ በአምልኮቱ ሊጸና አይችልም:: የገላትያ ሸዎች በእምነት የተናወጡት ወደሌላ

www.zeyeneta.com

ትምህርት ሳያውቁት ገብተው ስለ ነበር ነው። «በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እንደነቃለሁ። እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፣ የሚያናውጧችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ አንዳንዶች አሉ እንጂ።» /ገላ.1+6/ ሲል ቅዱስ ጳውሎስ የገሠጻቸው ስለዚህ ነው። ጌታችንም ቃሌን ሰምቶ የሚሠራው ሰው ቢኖር ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ብልህ ሰውን ይመስላል እያለ ያስተማረው ምእመን ካመነና ከተማረም በኋላ ካሁኑ እያግከረ ከሰይጣን የሚመጣበትን ፈተና ሁሉ ድል መንሣት እንደሚቻለው ሲያስረዳ ነው።

ስለዚህ በትምህርቱም ብቻ ሳይሆን ዕለት ዕለት ፈቃደ እግዚአብሔርን በምክረ ካህን በፈቃደ ካህን ወውቀን ካልፈጸምን ከመ ሠረቱ ላይ አለን+ ጸንተናል ማለት አይቻለንም። በምክረ ካህን የማይኖር ንሴሐን አያውቃትም። በኑፋቄ ማዕበል ይናወጻል፣ ይወድቃል፣ የምግባር ጻሕጽም ለድቀት ለኃጢአት ያበቃዋል። ስለዚህ ምእመናን እያንዳንዳቸው በመሠረቱ ላይ መታነፃቸውን ወይም መሠረታቸውን አለመልቀቃቸውን መመርመር ይጠበቅባቸዋል። አልያ ግን በድቡሽቱ ላይ እንደ ተሠራው ቤት ስም አጠራራችን እስኪከሱ ድረስ አወዳደቃችን ይከፋልና በመሠረታችን ላይ እንታነፅ።

ሐ/ <u>ለመምህራን</u>

የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ምእመናን ለሚያስተምሩት ትምህርት መሠረቱ የጌታችንና የቃሉ ትምህርትና ተአምራት የእጁ ተአምራት ናቸው። ይህን ትምህርት ግን እንደ ጸጋቸው በተለያየ መንገድ ያስተላልፉታል። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ «የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጢ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ+ ሌላውም በላዩ ያንጻል።» 1ኛቆሮ.3+10 ያለው።

ይሁን እንጂ ፈርጃቸው ብዙ ነው፣ መንገዳቸውም ልዩ ልዩ ነው። «ለእያንዳንዳቸውም ጌታ እንደ ሰጣቸው ያገለግላሉ። እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር።» 1ኛቆሮ. 3+6 እንዲል።

ይሁን እንጂ አንድ በቤተ ክርስቲያን የሚያስተምር መምህር በወንበር በጉባኤ የተቀበለውን ጠንቅቆ ለደቀ መዝሙሩ ሳይበርዝ ሳይከልስ እንደሚያስተምር ሁሉ ኑፋቄንም እሹልከው የሚያስገቡ አይጠፉም። መምህራን ስለሚያንፁት ሕንፃ ስለሚሠሩትም ሥራ መጠንቀቅ ይጠበቅባቸዋል። «እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንፅ ይጠንቀቅ።» 1ኛቆሮ.3+11 እንዲል የሚያገለግሉት ለሰማያዊ ዋጋ ነውና። «የሚተክልና የሚያጠጣ አንድ ናቸው+ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።» 1ኛቆሮ.3+8 እንዲል ደመወዛችን ከእግዚአብሔር የሚከፈልና በእርሱ መለኮታዊ ባሕርይ የሚለካ ስለሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ለምን እናስተምራለን? የክርስቶስ ተከታይ ለማድረግ ወይስ የእኛ ተከታዮች እንዲሆኑ? ምን እናስተምራለን? ንጹሑን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ወይስ የግል አሳባችንን በመቀላቀል? ስለ ቤተ ክርስቲያን መስፋት በመጨነቅ? ወይስ ኑሯችንን ለማትናት ብቻ? የሚሉትን ጥያቄዎች ሰባክያነ ወንጌል መመርመር ያስፈልጋቸዋል። ካለበለዚያ ሕንፃቸው ከፈረሰባቸው ወይም ከተቃጠለባቸው በእግዚአብሔር ፊት ያሳፍራልና። «ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ+ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፣ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና+ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል። ማንም በእርሱ ላይ ያነፀው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፣ የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጐዳበታል።» 1ኛቆሮ.3+12–14

www.zeyeneta.com

እንዲል ስለ ደመወዙ ሲል በተመሠረተለት መሠረት ላይ እንደሚ ገባው ማነውንና አለማነውን መጠየቅ መመርመር ይገባዋል። አገልግሎቱ ሐዋርያት ለተሰየፉለት ሲታመኑበት ለደከሙለት ለሚደክሙለትም የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ነውን? ብሎ መጋደል ያስፈልጋል።

ካለበለዚያ ዋጋውን ሊያገኝ ቀርቶ ሥራውም ጸንቶ አይኖር ለትም። «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና።» ዕብ. 12÷29 ተብሎ ተጽፏልና።

6.3. ደግመኛ እንመሥርት

አስቀድመን መሠረታችን «ወልድ ዋሕድ» የምትል እምነት እንደ ሆነችና መሠረትነቷም ለመምህራን ትምህርት፣ ለእያንዳን ዳችን እምነትና በአጠቃላይም ለቤተ ክርስቲያን እንደ ሆነ ተመልክ ተናል። በመሆኑም «ደግሞ መመሥረት» ማለት የማዕዘኑን ራስ የጌታችንን ዐለትነት ከሁለት አካላት አንድ አካል ከሁለትም ባሕ ርያት አንድ ባሕርይ መሆኑን ክዶ፣ ነቅር፣ አጠይር ማመንም ማስተማርም ነው።

ዐለቱ ሲለወጥ ውኃውም ይለወጣል፣ ሕንፃውም ይናዳል ይፈርሳል፣ መሠረቱ ተነሥቷልና ያለ መሠረትም ቤት አይጸናምና። ማቴ.7÷25፣ 1ኛቆሮ.10÷4። ቅዱስ ጳውሎስ መሠረትን ደግመን እንመሥርት ያለው በእምነትም በምግባርም ነው። «መሠረትን ደግመን እንመሥርት÷ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሐና በእግዚአብሔር እምነት÷ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን ስለ ሙታንም ትንሣኤ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው።» ዕብ.6÷2።

ጥቅሱን መሠረት በማድረግ በሁለት ከፍለን እንመለከተ ዋለን። እምነት ሲለወጥ ምግባርም ይለወጣል፣ የምግባር ውድቀትም ቶሎ ንስሐ ካልገቡበት ለሃይማኖት ድቀት ያደርሳል። ትምህርት ሲለወጥ ሃይማኖቱም ይለወጣልና ሌላ ትምህርት እንግር አትበሉ።

6.3.1. በትምህርት፡-

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህች ምዕራፍ አጽንኦት የሰጠው ስለትም ህርት መለወጥ ነው። በጊዜው ዕብራውያን ትምህርቱ ከለመዱት ወግና ሥርዓት ስለ ተለየ ይጨነቁ ነበር፣ ቅዱስ ጳውሎስ ግን የሚያ ስረግጠው በጌታችን ለማመን የሚያስፈልገውን ትምህርተ ወንጌል ነበር። ምክንያቱም አሪትና ነብያት አምላል መርገፍ በመሆን ትን ቢት እየተናገሩ ሱባኤ እየቆጠሩ ቆዩ፣ አሁን ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ተተርጉመዋል፣ ትርጓሜውም ወንጌል ነውና ይህን መማር አለባችሁ። ትምህርቱ ከተለወጠ ሃይማኖቱም ይለወጣልና።

በትምህርት መለወጥም እምነት ይለወጣል። ስለዚህም አብ ነት አድርጉ የጠቀሳቸው አሉና እነዚህን አንድ በአንድ እንመለ ከታለን።

ሀ/ ጥምቀት፡- ምሥጢረ ሥጋዌን የማያምንና በዚህም ትም ህርት ያልጸና ሰው አይጠመቅም፣ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ በጥምቀት ከውኃና ከመንፈስ መወለድን ሊያምን አይችል ምና። ትምህርቱ ሲለወጥ እምነቱ ለመለወጡም አብነት የሚሆን ታሪክ ማቅረብ ይቻላል። የምጥመቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ደቀ መዛ ሙርት እና ወደ ጌታችን ይሄዱ የነበሩት አይሁድ ስለ ማጥመቅ የተ ከራከሩት በትምህርቱ መለወጥ ጭምር ነው፣ ዮሐንስ መንገድ ጠራ እንጂ ይመጣ ዘንድ የተነገረለት መሲሕ አይደለምና። እርሱ ግን ስለ ጌታችን ታላቅነት አስረግጦ መሰከረ፣ የላከውን ያውቃልና። ዮሐ.3÷25፣ 31–35።

ስለዚህ አንድ ሰው ሌላ ትምህርት ከተማረ ሌላ ጥምቀት ልጠ መቅ ማለቱ አይቀሬ ነው። ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ «ልጠመቅ» ሲል የጠ የቀው ትምህርተ ነብያት በትምህርተ ወንጌል ስለ ተተረጉ መለት ነው። ከዚህ የተነሣ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ሌላ ትምህርት አትማሩ የሚለን።

www.zeyeneta.com

ለ/ ከሰኑት:- ትምህርቱ ሲለወጥ እምነቱ ይለወጣል፣ እምነቱ ሲለወጥ የአምልኮት ሥርዓቱም ይለወጣል፣ ሹመቱም ከሰኑቱም ይለወ ጣል:: የመጀመሪያውን አትልሉ እንደ ገና በሌሎች ከሃድያን እን ብሮተ እድ ሐሰተኛ ሹመትን ይቀበላል:: ለዚሁም አስረጂ የሚሆነው በዘመናችን ያለ ሐዋርያው ትውፊት ራሳቸውን ከሶት አድርገው የሚኖሩት ናቸው::

ሐ/ <u>ትንሣኤ ሙታንና ፍርድ</u>

ከትምህርቱ መለወጥ የተነሣ የእነዚህ ሁለት ምሥጢራት ብቻ ሳይሆን ሌሎቹም ይካዳሉ:: የጌታችን የባሕርይ አምላክነት፣ <u>በክረ ሙታንና በክረ</u> ትንሣኤ መሆኑን ካላመንን ትንሣኤ ዘጉባኤን ልናምን አንችልም:: ከተንሣኤ በኋላ ያለውንም ፍርድ ቢሆን በእም ነት ልናስተውለው ያዳግተናል:: ምክንያቱም የትንሣኤ ዘጉባኤን ምሥጢርነትና ከዚህም በኋላ የሚገለጠውን የወልደ እግዚአብሔር እውነተኛ ፍርድ መቀበል የሚቻለን የእርሱን የባሕርይ አምላክነት ትምህርት ተምረን ስናምን ብቻ ነው::

እነዚህን የመሰሉ እምነቶችን ሊያስተዉ የሚችሉ ብዙ የሚያከራክሩ ነገሮች በዘመናቸው ነበሩ:: ለምሳሌ የግዝረት ክርክር ለመጀመሪያው የሐዋርያት ሲኖዶስ ዐቢይ ምክንያት ነበረ:: ሐዋ. 15÷1-29:: ግዝረትን ዋና ያደረገ ጥምቀትን ሊተበል አይችልም:: ስለዚህ በወንጌል ትምህርት ምክንያት ለሚፈጸሙ ምሥጢራት እንትፋት የሚሆኑ ነገሮችን የሚወልዱ አዳዲስ ትምህርቶች ሌላ መሠረቶች ናቸው:: ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ደግመን አንመ ሥርት ያለው ትምህርቱን ነው:: ትምህርቱ ሲለወጥ ሁሉም ነገር ይለወጣልና ደግመን ግለቱ በእኛው መጻሕፍት ለሌላ አምልኮት የሚጸርግ «ኢየሱስ» ኃኒ እያለ በሐሰት የሚገለጥ ርኩስ መንፈስን እንድናምን ስለሚያደርግ ነው::

በዚህ ዓይነት ስብከቶችና «መጽሐፍ ቅዱስ ይላል» በሚል

ፈሊጥ በአዲስ ትምህርት መነዳት የሚገባ አያደለም:: «በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዲት እንዳለፋችሁ አደንቃለሁ እርሱ ግን ሊላ ወንጌል አይደለም፡ የሚያናውጣችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ እንዳን ዶች አሉ እንጂ:: ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፡ የተረገመ ይሁን» ግንም ቢሆን ወንጌልን መነሻ በማድረግ ሊላ ትምህርት የሚያስተምር ከሆነ ልንተበለው የሚገባ አይደለም:: የመምህራንም ከብራቸው ትምህርታቸው ነው፡ ትምህርታቸው ከተለመጠ ከብራቸው ቀረ ማለት ነው:: ይኸውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡ መርጠ የሾማቸው የላካቸው እርሱ ነውና::

ከዚህ አገልግሎት በሌላ ትምህርት ምክንያት ከተለዩ ግን እግዚአብሔር ሲሾመው ከባሕርይው ከሀዲትን አፍልቆ የኩበለለ ዲያ ብሎስን ተከትለዋልና የመምህርነት ጸጋቸውን ያጡታል፣ ትምህርቱ ሲለወጥ እምነቱ ታማኙም ባለቤት ይለወጣልና፣ ስለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ «መሠረትን ደግመን አንመሥርት» የሚለው:: ከተገለጠው በቀር በወንጌል ስም ሊሠጥ የሚገባውሌላ ምንም ዓይ ነት ትምህርት የለምና::

አንዳንድ ሰዎች የሌሎቹን ትምህርት ብንሰማ ምን ችግር አለው? ቃሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ያለ ነው በማለት ራሳቸውን ያታል ላሉ:: ችግርማ አለው:: ይኸውም:-

1ኛ. <u>ለእውነት መታዘዝ ያቅተናል</u>::

«የግታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ+ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተስሉ ነበር፣ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው? ይህን ብቻ ከእናንተ እንድማር እወዳለሁ፣ በሕግ ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መስማት

www.zeyeneta.com

መንፈስን ተቀበላችሁን? እንንዲህ የማታስተውሉ ናችሁን? በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ ትፈጽማላችሁን? ....» ገላ.3+1–5/ በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የሚገሥጻቸው በሌላ ትምህርት እንደ ገና ሕግን /መሥዋዕተ እንስሳን በማቅረብ እንድናለን/ በመፈጸም እንጠቀማለን ወደ ማለት ስለ ተመለሱ ነው። ይህ ደግሞ ከሁሉም የሚበልጠውን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም /እውነታውን/ እንዲያቃልሉ አድርጓቸዋል።

2ኛ. ርኩስ መንፈስ ያድርብናል

የመናፍቃንን ትምህርት አሜን ብሎ መማር ተናጋሪውን መንፈስ መቀበል ነው። ጌታችን በወንጌል «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል» /ማቴ.10+42/ እንዳለ ከጌታ ደቀ መዛሙርት ቢማር ከጌታ መማር እንደሆነ ሁሉ ከመናፍቃን መስማት የላካቸውን ጌታ /ዲያብሉስን/ መስማት፣ ከእነርሱም መማር ከመንፈሳቸው መሳተፍ ነው። ጌታቸው ደግሞ ስንኳን በሰው አድሮ ራሱም ሳይፈራ ሳያፍር ጥቅስ እየጠቀሰ ጌታችንን ለመፈተን ተሰልፏል። ማቴ.4+1–12። ጌታን ለመፈተን ያሳፈረ እኛን በጥቅስ ለመፈተን የሚያዘገየው ምንድን ነው? አንጻንዶቻችን ደግሞ ጸሎታቸው ወደ እግዚአብሔር ነው እንላለን፣ አጋንንት እኮ ያምናሉ /ያዕ.2+13/ ሲለምኑትም የፈቀዱትን አድርጌ ሳቸዋል። ለዚህም በጌርጌሶን በመቃብር ይኖሩ የነበሩ አጋንንት ያደሩባቸው ሰዎች ጌታችንን ባዩት ጊዜ ለምነውታል። «ታወጣንስ እንደሆነህ ወደ አሪያ መንጋ ስደደን ብለው ለመኑት። ሂዱ አላቸው።» ማቴ.8+31 እንዲል ለምነው ተቀብለዋል።

የጌታችንንም ስሙን አሳምረው ጠርተውታል። «ኢየሱስ ሆይ፥ የእግዚአብሔር ልጅ ከእንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን መጣህን?» በማለት እውነቱን ተናግረዋል። ይህ ግን እነርሱን አማኞችና እውነተኞች አያሰኛቸውም፥ ሥራቸው ሌላ ነውና።

6.3.2. በምግባር

ቅዱስ ጳውሎስ ሰው ምግባረ ሃይማኖትን እንዳያቀልና መሠረቱ እምነቱ እንዳይናወጥ መሠረትን ደግመን አንመሥርት ሲል የመከረ ባትን ሁለተኛዋን አንቃጽ እንመለከታለን።

የእምነት መለወጥ ምግባርን እንዲለውጥ፣ የምግባር መለወጥ ሃይማኖትን ወደ መለወጥ ያደርሳል። ይህም «የሞተ ሥራ» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የገለጠው ነው። ለመሆኑ የሞተ ሥራ ምንድን ነው? የሞተ ሥራ በማለት የተጠራው ለሞት የሚያበቃው ሥራ ነው፣ እጠራሩ ፍጻሜውን በመግለጥ ስለሆነ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በሌላ ቦታ የሥጋ ሥራ ብሏቸዋል፣ ከመንግሥተ ሰማያት ለይተው ወደ ሁለተኛው ሞት የሚወስዱ ናቸውና። «የሥጋ ሥራም ከተገለጠ ነው። እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ትንኳት፣ ቁጣ፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ዘፋኝነት፣ ይህንም የሚመስል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።» ገላ.5+19–21 እንዲል።

እነዚህን ቦግድረግ የሸና ሰው ሃይማኖቱንም ይክዳል። ስለዚህ አንድ ሰው በግብትም ባለግብትም ሊጸድቅ ይችላል፣ ነገር ግን ንስሐ ቢገባ እግዚአብሔር ይምረዋል። ወደ ሃይማኖትና ምግባር ይመልሰዋል ለርስቱም የበቃ ይሆናል። «ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላዋጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም። ከእናንተም አንዳንዶች

www.zeyeneta.com

እንደ እነዚህ ነብራችሁ፣ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል+ ተቀድሳችኋል+ ጸድቃችኋል።» 1ኛቆሮ.6+9–11 እንዲል በንስሐ ከእነዚህ ሁሉ ልንላቀቅ፣ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለንና ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። 1ኛዮሐ.1+9 ስለዚህ ንስሐ ኃጢአትን ሁሉ የምታስተሠርይ የእግዚአብሔር በር ናት።

አንዳንድ ሰዎች ግን የንስሐን /የመናዘዝንና ቀኖና የመቀበልን/ ምሥጢር ረብህ የሌለው አድርገው ከማስተማራቸው የተነሣ ከእግዚአብሔር መንግሥት ይለያሉ። ትምህርታቸው ቀድሞ ምግባርን በኋላም የምግባርን እናት ሃይማኖትን ያስተዋቸዋልና።

ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ንስሐን የሚቃወም ትምህርት ከሞት የማያድን ነውና መሠረትን ደግመን አንመሥርት አለን። «... ይሆን ዕወቁ፣ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኩስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣያትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም። ከዚህ የተነሣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእነዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ።» ኤፌ.5+3–13 በማለት አንዳንዶች «ከንቱ ንግግር» በተባለ የውሸት ትምህርታቸው ብዙዎችን የኃጢአት አበጋዝ አድርገው ነብርና ከዚህ መጠበቅ እንደሚገባ ያስተምረናል።

በአሁኑም ጊዜ «እግዚአብሔር ፍጹም መሐሪ ነው» በሚል ፈሊጥ የሰውን ሁሉ ኃጢአት ዝም ብሉ ይቅር እንደሚል የሚያስተምሩና ሰውን ወደ ኃጢአት የሚጋብዙ መናፍቃውን ዐውቆ ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል። የእግዚአብሔር ምሕረት ለተነሣሕያን እንጂ ክህደ ልቡናቸውን አደንድነው በኃጢአት ለሚተጉት ሁሉ አይደለም፣ «እግዚአብሔር የሚያጠፉም እሳት ነው።» ዕብ.12+29።

6.3.3. <u>ቅዱሳንን በማገልገል፡-</u>

በዚህች ምድር ላይ ካሉት ታላላቅ ነገሮች ውስጥ አንዱ

መቀባበል ነው። የአንዱ መስጠት የሌላው መቀበል። ሰጪና ተቀባዩ ቢመሳሰሉም ቢለያዩም መስጠትና መቀበል ግን የሚቀር አይደለም፣ አንዱ ያለ ሌላው መኖር አይችልምና።

መሬት ዝናም ለዘር ጠል ለመከር ካላገኘች የዘሩበትን ማብቀል የተከለባትን ማጽደቅ አይቻላትምና ሰጠታ ያስፈልጋታል። መሬትም ይሆን ካልሰጠች ሰውም እንሰሳትም መኖር ያቅታቸዋል፣ ሌሎቹንም መመልከት ይቻላል፣ ዕዕዋት ንጹሕ አየር ለእኛ ይሰጡናል+ እኛም ለእነሱ የተቃጠለ አየር /ካርቦን ዳይኦክሳይድ/ እንሰጣቸዋለን።

ለሰማያዊ መንግሥት በምናደርገው መንፈሳዊ ጉዞም አንዱ ያለ ሌላው ሊጠቀም አይችልም። ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ መሥዋዕት ሆኖ መቅረብ ለእኛ እንጂ ለእርሱ ጥቅም አይደለም፣ ሁልጊዜ እኛ ከእርሱ እንቀበላለን እንጂ እርሱ ከእኛ የሚያገኘው ነገር የለም። የምናቀርበው ልመና፣ ጸሎትና መባዕ የሚጠቅመው እርሱን/ ሳይሆን እኛን ነው። ታድያ ጌታችን ለእኛ ጥቅምና ጽድቅ ካዘጋጀውና ሊቀበልልን ቃል ኪዳን ከገባቸው ምግባራት አንዱ ቅዱሳንን ማገልገል ነው። እግዚአብሔር በወደደ ሥጋ በሌሉ ቅዱሳን ስም በወደደ ሥጋ ያሉ ደጋግ ሰዎችን ማገልገል ደስ ያሰኘዋልና፣ ዋጋም ይከፍልበታል። «እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላችሁ እስካሁንም ስለምታገለግሏቸው+ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፃኛ አይደለምና።» ዕብ.6+10 ተብሎ ተጽፏልና።

በእውኑ ቅዱሳንን ማገልገል ማለት ምን ማለት ነው? ልዩ የሚያደርገውስ ነገር ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሊያስነሣብን ይችል ይሆናል። ቅዱሳንን ማገልገል ማለት እንግዳን መቀበል ማለት አይደለም። እንግዳ የሚቀበል ሰው ተሞገሰ ስጦታ አቀረቡ የመሰለውን፣ የሚወጣ የሚወርደውን፣ እሚሄ ከሆዲ፣ ጸድቅ ኃጥእ ሳይል

www.zeyeneta.com

ይቀበላል። እንዲህ ባለ እምነት /የሰው ልዩነት ሳያደርጉ መቀበል/ እንግዶችን የተቀበሉም መላእክትን ለመቀበል እንደ በቁ ተመስክሮ ላቸዋል። «እንግዶችን መቀበል አትርሱ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና።» ዕብ.13÷1-2 እንዲል። በዚህም መሠረት አብርሃም ቅድስት ሥላሴን ሎጥም ቅዱሳን መላእክትን ተቀብለዋል። ዘፍ.18÷1፣ ዘፍ.19።

አንድ ክርስቲያን ሕግን መጠበቅ ትእዛዛትንም መፈጸም ይኖርበታል። ሕግን መጠበቅ ማለት አታድርግ የተባለውን አለማድረግ ነው። ይህም አትስረቅ፣ አትግደል፣... እነዚህንና የመሰሏቸውን መጠበቅ፣ ከዚህም የሚበልጠው ደግሞ ትእዛዛትን መፈጸም ነው። ትእዛዛትን መፈጸም ሕግን እንድንጠብቅ ያደርጋልና። ከዚህም ዋናው ትእዛዝ «ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ» የሚል ነው። ይህ ምክረ ሃይማኖትን ሁሉ እንድንፈጽም ያደርጋልና። «የወንድማማች መዋደድ ይኑር።... ከእነርሱ ጋር እንደ ታሠረ ሆናችሁ እሥሮችን አስቡ፥ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳላችሁ ሆናችሁ አስቡ።» ዕብ.13÷1-3 በሚል ታዝዘናልና።

ይልቁንም ጌታ በወንጌል «ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፦ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሟችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ፥ ለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዷችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።» /ማቴ.5÷43-48/ ሲል ፍጹም ሕግን ሰጥቶናል። ይሁን እንጂ ይህ ትእዛዝን ከመፈጸም አልፎ ቅዱሳንን ማገልገል ሊሆን አይችልም።

ቅዱሳንን ማገልገል ከዚህ የተለየ መሆኑንም ቅዱስ ጳውሎስ ገልጦታል። ልዩ የሚያደርገውም የሁለት ነገሮች መገለጫ በመሆኑ ነው። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው።

ሀ/ <u>ለእግዚአብሔር ስም ያለንን ፍቅር እንገልጽበታለን።</u>

ብዙ ጊዜ በቅዱሳን ስም መጠራትን እግዚአብሔር ይፈቅዳል። እነ ሙሴ እነ ዳዊት የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ እያሉ በለመኑት ጊዜ ፈጥኖ ሰምቷቸዋል። ፈቃዳቸውንም ፈጽሟል። ስለዚህ ቅዱሳንን ማገልገል ማለት እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮ የሚያውቁትን በተልዕኮም የሚፋጠኑትን በስሙ መቀበል በቅዱሳን ስም የሚመጡትንም መቀበል ነው። «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል÷ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።» ማቴ.18÷5፤ «የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል÷ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።» ሉቃ 10÷16። «እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ ማናቸውን የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል÷ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።» ዮሐ.13÷20።

እንዲህ ተብሎ የተነገረላቸውን እንጂ ቸግሯቸው፣ ተርበው፣ ቀን ጥሏቸው የሚመጡትን መቀበል አይደለምና። እነዚያን መቀበል እንግዳ መቀበል ወይም ወንድምን በመውደድ ለሰው ሁሉ ማድረግ የሚገባንን በማድረግ የምንፈጽመው ነው። ቅዱሳንን ማገልገል ግን ራሱን እግዚአብሔርን መቀበል ለእግዚአብሔርም ስም ያለን አክብሮት የሚገለጥበት ልዩ አገልግሎት ነው። ስለዚህ ቅዱሳንን ማገልገል ማለት «ለእግዚአብሔር ስም ያለንን አክብሮት» የምንገልጥበት ወቢይ መንገድ ነው። የእግዚአብሔርን ስም «በአምልኮ» መጥራት ማለት ቅዱሳን የተባሉትን የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ወይም የቤተ ክርስቲያንን ልዑካን መቀበልና ለእነርሱ የሚገባውን

www.zeyeneta.com

ሁሉ ማድረግ ማለት ነው።

ኢትዮጵያውያን ምእመናን እስካሁን ድረስ ይህን አገልግሎት በመፈጸም እጅጉን የሚመሰገን ክርስቲያናዊ ሕይወት አላቸው። ይሁን እንጂ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው ሰጥተው በየበረሃው፣ በየገዳማቱና በየገጠሩ ያሉ መነኮሳትንና ካህናትን እንደሚገባን እንዳላደረግን ይሰማናል። ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ አገልግሎት ብዙ አስተምሯል። ጽፏልምና። አሕዛብን እየሰበከ በኢየሩሳሌም ያሉትን ቅዱሳን ያስብ ነበር፣ አደራም አድርጉ ተቀብሎት ነበር። ገላ.2÷10። በኢየሩሳሌምም ያሉት በተራቡ ጊዜ አዋጥተው ልከዋል። ሐዋ 11÷27-30። ለእርሱም ለተደረገው አገልግሎት በፊል.4÷16-20 ጽፎታል፡ «...በተሰሎንቄ እንኳ ሳለሁ+ አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ያስፈለገኝን ሰዳችሁልኝ ነበርና።... ነገር ግን ሁሉ አለኝ ይበዛል ኀማል፣ የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት የሚሆነውን ለእግዚአብሔርም፡ ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተሞልቼአለሁ።» እንዳለ ያዋጡትን በሰው በኩል የታሰበው ቦታ አድርሶ ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ጻፈው ያለ «የሰላምታና የደረሰኝ» ከእነርሱ መቀበል ይገባል።

ለ/ <u>ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ሥራ፡-</u>

ጌታችን በወንጌል ስለ መጨረሻው ፍርድ ባስተማረበት አንቀጽ ላይ ጻድቃን የሚመሰገኑበትን ኃጥአንም የሚወቀሱበትን የበጉ ሥራ ጉዳይ አመልክቷል። «ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል+ ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል። ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም።» /ማቴ.10÷40-42/ ሲል አስቀድሞ ከተናገረ በኋላ ይልቁንም እርሱ አድሮባቸው ለሚኖሩ ቅዱሳን መስጠት

ለእርሱ መስጠት እንደ ሆነ በማቴ.25÷34-46 ገልጦታል።

ጻድቃንን «ተርቤ አበላችሁኝ ...» ያላቸው ቅዱሳንን በማብላታቸው ሰ.ሆን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሳኦል ተብሎ የጌታን ደቀ መዛሙርት ሲያሳድድ «ሳኦል ሳኦል ለምን ታሳድደኛለህ? ብሎታል» በአካል ስላሳደደው ሳይሆን በጸጋ ያደረባቸውን ደቀ መዛሙርት ስላሳደደ ነው። ስለዚህም በእግዚአብሔር ሰዎች ላይ የሚደረግ ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ እንደተደረገ። ለእግዚአብሔር ሰዎች የሚደረግ ደግሞ ለርሱ እንደሚደረግ ይቆጠራል/። ኃጥኣንን ደግሞ «ብራብ አላበላችሁኝም... ያለው ለሰው አብልተው ስለማያውቁ ሳይሆን እርሱ አድሮባቸው የሚኖሩትን ቅዱሳንን ስላላገለገሉ ነው። በመጨረሻም በዚሁ ፍርድ «ኃጥኣን ወደ ዘላለም ቅጣት ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።» ተብሎ የተጻፈው ቅዱሳንን ማገልገል ለነኑት ለመንግሥተ ሰማያት የሚያበቃ ደግኛ ምግባር በመሆኑ ነው። «እግዚአብሔር+ ቅዱሳንን ስላገለገ ላችሁ አሁንም ስለምታገለግሏቸው+ ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።» /ዕብ.6÷10/ በማለት ፍቅረ እግዚአብሔርም ፍቅረ ቢጽም የሚፈጸምበት ሁለቱንም /አንድ አድርጉ/ ልዩ አገልግሎት መሆኑን ገልጦታል።

«ስለ እናንተ ግን+ ወዳጆች ሆይ+ ምንም እንኳ እንዲሁ ብንናገር+ አብልጦ የሚሻለውና ለመዳን የሚሆነው እንዲሆንላችሁ ተረድተናል» /ዕብ.6÷9/ በማለት ቅዱሳንን ማገልገል 1- አብልጦ የሚሻል 2- ለመዳን የሚሆን እንደ ሆነ አስረግጦልናል። ራሱም «አሁን ግን ቅዱሳንን ለማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ።» ሲል በአገልግሎቱ የሚገኝበትን ጥቅም እንድናውቅ አስገንዝቧል።

ቅዱስ ጳውሎስ «ደግመን መሠረትን አንመሥርት» እያለ የሚያስተምረውም ይህን የመሰለው አብልጦ የሚሻልና ለድኅነት

www.zeyeneta.com

ነፍስ የሚያበቃውን አገልግሎት የሚያስተው ሌላ ትምህርት እንዳን ማር ነው። በእምነታችንና በምግባራችን እንዳንጸና የሚያደርገን ሌላ ትምህርት ሁሉ ሌላ መሠረት ነው። «ልዩ ልዩ በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው።» ዕብ. 13÷9 «መንፈስ ግን በግልጥ፦ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያ ስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ ይላል።» 1ኛ.ጢሞ.4÷12 ተብሎ እንደ ተጻፈ ብዙዎች ከመንፈስ ቅዱስ ዕው ቀት ወደ አጋንንት ዕውቀት ሄደዋል። ሠራዊተ አጋንንት ወደ መሆን ራሳቸ ውንም እስከ ለወጡ ድረስ ወደ ንስሐና ወደ ቀደመው መሠረት መመለስ አይቻላቸውም። በሚቀጥለውም በጥቂቱ የምንመለከተው ስለ እነርሱ ይሆናል።

6.4. <u>እነርሱን በንስሐ ማደስ የማይቻል ነው</u>

«አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ሰማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን መልካ ሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን በኋላም የካዱትን እንደ ገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማ ይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱ ትማልና።» /ዕብ.6÷4-6/ እንዲል በጥምቀት ተወልደው በሜሮን ከብረው የቤተ ክርስቲያን ብርሃን ከበራላቸው በኋላ የካዱትን መመለስ ከባድ ነው።

«አንዳንዶች ጎሊናን ጥለው÷ መርከብ ያለ መሪ እንደሚጠፋ÷ በእምነት ነገር ጠፍተዋልና፤ ከእነዚያም÷ እንዳይሳደቡ ይማሩ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፈ የሰጠኋቸው÷ ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ናቸው።» 1ኛጢሞ.1÷19 እንዲል ብዙዎች የጠፉት በፍልስፍና ነውና እነዚህን መመለስ አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰድ

ባሉና። እንደ አብነትም ጌታ ካስተማራቸው መካከል አንዱ ከሆ ነው ከይሁዳ ጀምረን ብንመለከት የንስሐ ልቡናቸውን እንደተነጠቁ እንመለከታለን።

ሀ/ <u>ይሁዳ አስቆሮታዊ</u>፦ ይሁዳ ከበደለው በደል ተመልሶ ከጌታችን ደቀ መዛሙርት አንዱ ለመሆን በቃ። በአሥራት በኩራት ላይም ተሾመ። ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ለመሆን በቅቷልና። ስለዚህም ጌታችን ከዋለበት እየዋለ ካደረበት እያደረ ትምህርትና ተአምራት ሳይከፈልበት ኖሯል። ያልተማረው ትምህርት፣ ያላየው ምሥጢር ቢኖርም እንኳ ለድኅነቱ ከሚጠቅመው በላይ ያውቅ ነበር። ይሁን እንጂ በውስጡ ተንኮልና ሌብነት ስለነበረበት እጅግ ይጠበብ ነበር፤ ሥጋዊ ጥቅምም ጽድቅም እንዳይቀርበት።

ባለሽቱዋ ማርያም ጌታችንን ዋጋው እጅግ የከበረ ሽቱ እግሩን ቀብታ በጠጉርዋም በመዘመዘችው ጊዜ የይሁዳ ልብ በክፋት ተሞላ፤ «ይሁዳ፦ ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ስለምን ነው? አለ።» ዮሐ.12÷5 እንዲል። ይህን አሳብ ስንመለከተው ለድሆች የመጨነቅ የበጐነት አሳብ ይመስላል። ነገር ግን ሽፍጥና አመጽን የወለደ የሌብነት ጥንስስ ነበር። «ይህንም የተናገረ ሌባ ስለነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውስጡ ከሚገባው ይወስድ ስለነበረ ነው።» ዮሐ.12÷6 ተብሎ ተጽፏልና። ይህ ሰው ስለዚህ ገንዘብም ሲል ጌታችንን አሳልፎ ሰጠ።

ይሁዳ ጌታችን አሳልፎ የሰጠበት ምክንያት ሁለት ነው። የመጀመሪያው ያጣውን ገንዘብ ከአይሁድ ለመቀበል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጌታችን እንደልማዱ በተአምራት ያመልጣል የሚል ነበር። የሠራው ሳይታወቅበት ገንዘቡን ላለግጣት ነበር እንጂ ጌታችን ተሰቅሎ ይሞታል የሚል አሳብ አልነበረውም። ዮሐ.7÷30

www.zeyeneta.com

«በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደተፈረደበት አይቶ ተጸጸተ÷ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌች መልሶ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን እኛስ ምን ገደን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ።» ማቴ.27÷4-5 እንዲል።

ይሁዳ ይሆናል ብሎ ያሳሰበው በሆነበት አጠቀምበታለሁ ብሎ ያዘጋጀው ቀመር በወደቀበት ጊዜ ተጸጸተ፣ ጸጸቱ ግን የንስሐ አልነበረም፣ ይልቁንም የተያዘ ሌባ፣ «በዚህ ቀን መምጣት አልነበረብኝም» ብሎ የሚጸጸተው ዓይነት ነው፣ አሁንም ስለሌላ ቀመር ለመታነት ሄዷልና። «ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ» ማቴ.27÷6 በማለት ቅዱስ ማቴዎስ የሞቱ መንሥኤ መታነቁ መሆኑን ገልጦልናል። የሞተው ግን ከጌታ በኋላ ይልቁን በወረገብት ዕለት እንደሆነ ታሪክ ያስረዳል። ወዲያውኑ እንዳልሞተ አንጀቱ ተዘርግፎ እንደቆየ ይህም በብዙ ሰዎች ዘንድ እንደታወቀ ቅዱስ ሉቃስ ጽፎልናል። ሐዋ.1÷15-18።

ይሁዳ ዕውቀት አልቸገረውም፣ ከጌታ ተምሯልና፣ ምሥጢራትንም ተካፍሏል፣ በኋላ ግን በደለ፣ እንደ በደለም ራሱ ሀወቀ፣ ተጸጸተም ነገር ግን ንስሐ አልገባም። ይህን በማስታወስ ነው ቅዱስ ጳውሎስ ብርሃን የበራላቸውን /ልጅነት የተቀበሉትን/ ሰማያዊ ስጦታ የቀመሱትን /ኃይልና ተአምራት የተደረገላቸውን/ ኃላፊውና መጻኢው የተገለጠላቸውን በኋላም የካዱትን እንደ ገና ለንስሐ ማደስ አይቻልም የሚለው።

ለ/ አርዮስ፡- ሀብተ ውልድናን ስመ ክርስትናን ብቻ ሳይሆን ለደገኛው መዓርገ ክህነት ከበቃ በኋላ የወልደ እግዚአብሔርን አምላክነት አቅልሎ በራሱ ፍልስፍና በመመራት ፈጣሪን ፍጡር ለማለት የበቃ÷ ቢመከር ቢመከር አልሰማ ያለ፣ እንደ ይሁዳም አንጀቱ ተዘርግፎ የሞተ ሰው ነው። ይህ ሰው እሺ በሚልበት ጊዜ እንኳን ልቡናው የማይጸጸት ስለሆነ በታላቁ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ

/ኒቂያ-325/ እንኳን ተገዝቶ ያልሰማና ለንስሐ ያልበቃ ነው።

ከእርሱም በኋላ እነ መቅዶንዮስን እነ ንስጥሮስን ሌሎቹንም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የተመዘገቡ ሰዎችን መመልከት ይቻላል። እነዚህ ሁሉ ንስሐን ያመፁባት ሰዎች ናቸው። «ዕውቀት አለን» ብለው የሚመኩ ሁሉ «እሳሳታለሁ» ብለው መገመት ስለሚሳናቸው ወደ ንስሐ መመለስ አይቻላቸውም፣ የበቁ እየመሰላቸው በክህደት አበጋዝ ድል ይነሣሉ እንጂ። እኒህን የመሰሉ ሰዎች ሁሉ ወደ ጥንቱ መሠረት መመለስ አይቻላቸውም። ቆም ብለው ማስተዋል፣ ሌላውንም መጠየቅ፣ የተነገሩትንም መስማት ስለማይቻላቸው። ቆሞ የሚጠይቅ ራሱንም የሚመረምር ሞኝ ይመስላቸዋልና። «እግዚአ ብሔር እንዲህ ይላል፡- በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም የቀደመ ችውንም መንገድ ጠይቁ፣ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች ዕወቁ÷ በእርስዋም ላይ ሂዱ÷ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላ ችሁ እነርሱ ግን፡- አንሄድባትም አሉ።» /ኤር.6÷16/ ተብሎ የተጻፈው ተፈጽሞባቸዋልና።

የቤተ ክርስቲያን ወገን ነኝ የሚል ሁሉ ግን ተቀምጦ ማድመጥ፣ ቆሞ መጠየቅና ማስተዋል ይገባዋል። ምክር መስማትም ይጠቅማል። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ ትምህርቱን በቃልም በጽሑፍም ሲገልጽ አብሮ ምክሮቹን የሚጨምረው። በዚህ ምዕራፍም ላይ «በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድ ትመስሉ እንጂ ጸጥኞች እንጻትሆኑ÷ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንጻ ንጻችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን።» ዕብ. 6÷11-12 በማለት ይመክረናል። ከቁ.13-ፍጻሜም ምክር ነውና ከመጽሐፉ እንመልከት።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ሰባት

ሕግና ትእዛዝ

በዕብራውያን መልእክት ምዕራፍ ሰባት ላይ ስለ ክህነት ከመልከ ጼዴቅ ጋር በንጽጽርና በስፋት የተገለጠ ቢሆንም በምዕራፍ ሦስት ላይ የተጻፉ ስለሆነና ስለመሥዋዕት ያለው በምዕራፍ አሥር ላይ ስለሚገለጽ በዚህ ምዕራፍ ከቁጥር 15 እስከ 19 ያሉትን መነሻ በማድረግ ስለ ሕግና ትእዛዝ እንጽፋለን::

ሕግና ትእዛዝ የሚወራረሱበት ጊዜ ቢኖርም በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ግን «ሕግ» ተብሎ የተጠራውን በ«ትእዛዝ» መተካት የማንችልባቸው ሁኔታዎች እንዳሉ እናስተውላለን:: ከዚህም ባሻገር በሰዋስዋዊ ትርጉም የተለያየ ትርጉም እንዳላቸው አንዳንድ ሊቃ ውንት ይስማማሉ:: ከዚህ የተነሣ ሁለቱንም ለየብቻቸው አድርገን ለመመልከት እንገደዳለን::

7.1. <u>ሕግ:-</u> በቁሙ የተወሰነ የተጣፈ ሥርዓት፣ እውነተኛ ፍርድ፣ ያገር ልማድ፣ ለማድረግ የሚያዝ፣ ከማድረግ የሚከለክል፣ አታድርጉ አታድርጉ የሚል ግለት ነው:: /ኪ.ወ.ክ ገጽ 433/ ምንም እንኳ ዘይቤያዊ ትርጉሙ ይህ ቢሆንም ምሥጢራዊ ትርጉሙ ግን ብዙ ነው:: ሕግን በዚህ ብቻ ልንወስነው አንችልም:: ይልቁንም ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር ያሉትን መሠረት በማድረግ እንመለከተዋለን::

7.1.1. <u>ሕግ ጠባይዐዊ:-</u> ይህ ባሕርያዊ ሕግ፣ የተፈጠረው ፍጥረት ሁሉ በተፈጠረበት ግብር ጸንቶ መኖር የሚያስችለው በባሕ ርይው ዐውቆ የሚሠራው ነው:: ይኸም የመውለድና የመዋለድ ሥርዓት፣ በየጥቂቱ ማደግ፣ መራብ፣ መጠማት፣ ምግብ መሻት፣ መልበስ፣... ይኸን የመሰለው ነው:: «ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕ

ርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና:: እነርሱም ኅሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ::» ሮሜ.2÷13–15::

ሕግ ጠባይዐዊ ሕግ ተፈጥሯዊም ይባላል:: ቅዱስ ጳውሎ ስም በሌላ ቦታ ገልጦታል:: «ወንድ ጠጉሩን ቢያስረዝም ነውር እንዲሆንበት፥ ሴት ግን ጠጉርዋን ብታስረዝም ክብር እንዲሆንላት ተፈጥሮ እንኳን አያስተምራችሁምን? ጠጉርዋ መጐናጸፊያ ሊሆን ተሰጥቷልና::» 1ኛቆሮ.11÷14–15:: ስለዚህ እነዚህ ሕግጋት በመጻሕ ፍት ያልተጻፉ ነገር ግን እግዚአብሔር በየሰዉ ልቡና የጻፋቸው ናቸው:: እነዚህን ሕግጋት መታወቃቸው በሥነ ፍጥረት ታስቦ በማይ ደረስበት ምሥጢር የጻፈውን እግዚአብሔርን መታወቁ ነውና ሰው ለሚጠብቀውና ለሚተላለፈው ሁሉ መጠንቀቅና ማስተዋል ይገባዋል::

7.1.2. <u>ሕግ ሥጋዊ:-</u> በቅዱሳት መጻሕፍት ሕገ ሥጋ እየተ ባለ የተገለጠው ሁለት ነገር ነው::

1ኛ. <u>ሕገ መንግሥት:-</u> ይህ የሰው ልጅ በምድር ላይ እንዴት መተዳደር እንደሚገባው የሚያስረዳውና ከመጀመሪያው መስፍን እስራኤል ከሙሴ ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ በኋላም በነገሥ ታቱ በዐዋጅ መልክ እየወጣ ሕዝብ የሚጠቀምበት ነው:: ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር ስንመለከት ይልቁንም በአሪት ለእስራኤል ዘሥጋ አንደ መጻፉ መጠን በእግዚአብሔር ገላጭነት የተሠራ ነበር::

ይህም የቀማን የሚያስመልሱበት የበደለም የሚክሱበት ሕግ ነው:: ይህ ሕግ በሙጽሐፍ ቅዱስም እንደ ተሻሻለ እንመለከታለን፣ አሁንም አገሮች ለየራሳቸው አውጥተው «ሕገ መንግሥት» የሚለውን ስያሜ ሰጥተው ሲጠቀሙበት እንመለከታለን:: ይህን ሕግ ከጥንት ጀምሮ ስንመለከት ስለ ጋብቻ፣ ስለ እርሻ፣ ስለ እንስሳት

www.zeyeneta.com

እርባታ፣ ስለ ግብር... የሚናገር ነው። ለክርስቲያኖችም መለወጥ እንደሚገባው ጌታ በወንጌል «ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ÷ ክፉውን አትቃ ወሙ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፡... ለሚለምንህ ስጥ÷ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚ ወደው ፈቀቅ አትበል።» ማቴ.5÷38–42 በማለት የቅጣቱን ሕግ የምሕረት ሕግ እንዲሆን አድርጉታል። እርሱም ለሚገባው ለንጉሥ ግብርን ቀረጥን ከፍሏል። ማቴ.17÷24–27።

ሐዋርያትም በኋላ ይህን ሕግ መፈጸም እንዲገባ አስተም ረዋል። ሥልጣኑ ከእግዚአብሔር የተገኘ ነውና። «ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፣ ግብር ለሚገባው ግብርን÷ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን÷ መፈ ራት ለሚገባው መፈራትን÷ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።» /ሮሜ.13÷7/ እንዲል ይህ ሕግ ሥጋዊ በፍትሐ ነገሥት ከፍል ሁለት ላይ ተቀምጦ የምናገኘው ዓይነት ነው።

2ኛ. ሕገ ኃጢአት፡ ሕገ ኃጢአት ያልነው የበለጠ ግልጽ ለማ ድረግና ከሕገ መንግሥትም ለመለየት ነው። «አንሰ ሉቱ እትቀነይ በልብየኒ ወበ ኀሊናየ ለሕገ እግዚአብሔር መበነፍስትየኒ ለሕገ ኃጢ አት። እኔስ በልቡናዬም በኅሊናዬም ለእግዚአብሔር ሕግ እገዛለሁ። በሰውነቴ ግን ለሕገ ኃጢአት እገዛለሁ።» ሮሜ.7÷25 እንዲል።

ከዚህ አንጻር ሕገ ኃጢአት የምንለው ፈቃደ ሥጋን ነው። ሰውነታችንን ለሥጋዊ ነገር የሚጋብዝ ፈቃደ ነፍስንም የሚቃወም ነውና። ጌታችንም በሥጋ እስኪገለጥ ድረስ ሰው ሁሉ ሰውነቱን ለፈቃደ ነፍስ ብቻ ማስገዛት አልተቻለውም ነበር፤ ከታናሹ እስከ ታላቁ፣ ከሊቁ እስከ ደቂቁ ከኃጢአት አልተላቀቀም ነበርና። ጌታችን ሰው በሆነ ጊዜ ግን ይህ ተሻረ፤ ፈቃደ ሥጋን ድል የምና ደርግበትን ኃይል ከእርሱ አግኝተናልና። «በዓለም ሳላችሁ መከራ

አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዟችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።» ዮሐ.16÷33 እንዲል።

ቅዱስ ጳውሎስም ይህ ሕገ ኃጢአት መሻሩን ሲገልጥ የሚከተለውን ብሏል። «እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና። ከሥጋ የተነሣ ስለ ደከመ ለሕግ ያልተቻለውን÷ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጓልና1... በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙት አይችሉም።» ሮሜ.8÷1–8 ሲል በሰፊው አብራርቶታል። ገላ.5÷19 ላይም ተዘርዝረውልናል።

7.1.3. ሕገ መንፈሳዊ፡– ይህም ከሕግ ሥጋዊ አንጻር የሚ ታይ ስለሆነ በሁለት ከፍለን እንመለከተዋለን።

ሀ/ ሕገ ኒጸነት፡– የመንፈስን ሕግ የነጻነት ሕግ ነው የምን ለው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘነውና ፈቃደ ሥጋን ድል የምናደርግበት ስለሆነ ነው። «እናንተ ግን የእግዚአ ብሔር መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር÷ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም። የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ ወገን አይደለም።» ሮሜ.8÷9 እንዲል።

ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ መልእክቱ የመንፈስ ሕግ የሚባለው የአንዱን አንዱ መሸከሙ ነው በማለት እንደ አሪት ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ እንዳንል ይመክራል። «... ከእናንተ አያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።» ገላ.6÷2–3 እንዲል። ይህ የመንፈሳዊነት መመሪያ የሆነው ሕግ ሰውን ወደ ፍጹምነት እንደሚያመጣ «ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነጻ

www.zeyeneta.com

የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት÷ ሥራንም የሚ ሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው÷ በሥራው የተባረከ ይሆናል::» ያዕ.1÷23–25፤ «በነጻነት ሕግ ፍርድን ይቀበሉ ዘንድ እንዳላቸው ሰዎች እንዲህ ተናገሩ÷ እንዲህም አድርጉ::» ያዕ.2÷12 እንዲል::

ይህ በሥራ የመግለጥና ከባቴ አበሳ የመሆን ሕግ በክርስቶስ ያገኘነው ነውና የነጻነት ሕግ ተብሏል:: ቅዱስ ጳውሎስ የእምነት ሕግ በማለትም ጠርቶታል፤ አምነን የምንፈጽመው ነውና:: ሮሜ.3÷27::

ለ/ ፍትሕ መንፈሳዊ:- ይህ ሕግ በእኛ ቤተ ክርስቲያን ፍትሐ ነገሥት ክፍል አንድ ላይ የተጠቀሰና ባለ ሃያ ሁለት አንቀጽ ነው:: ይኸውም ቤተ ክርስቲያን ወደ ጸጥታ ወደብ ትመራ ዘንድ፣ አንዱ የሌላውን በመሥራት ተፋልሶ እንዳያጋጥም፣ በአንድ ክርስቶስ መሠ ረትነት ላይ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያንም አንዲት መሆኗ የሚገለ ጥበት ሥርዓተ አምልኮትን የሚያትት ሕግ ነው::

ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም ይባላል:: አሠራርን ወይም አፈጻጸምን የሚመለከት ነውና:: «ሥጋዬን ካልበላችሁ ደሜን ካልጠ ጣችሁ የዘላለም ሕይወት የላችሁም::» የሚለውን ጎብስቱ ወደ ሥጋው ወይኑም ወደ ደም የሚለወጥበትን ጸሎት፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት፣ እንቀበለው? ማን ምኑን ያቀብል?... የሚሉትን የሚሠራ ስለሆነ ሥርዓት ይባላል:: ሠሪዎቹም ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተሰ ጣቸው ሐዋርያትና በእነርሱም እግር የተተኩ ሊቃውንትና አበው ናቸው:: የተጀመረው ግን በሐዋርያት እንደሆነ በትጉሃት መጻሕፍት እንመለከታለን:: ሐዋ.15÷1–30::

ይህ ዓይነት የአበው /የጳጳሳት/ መሰባሰብና ሕግንና ሥርዓትን መስጠት እስከ ዕለተ ምጽአት የሚቀጥል ነው:: አስፈላጊነቱም በየጊ ዜው ለሚነሡ የቤተ ክርስቲያን ችግሮች መንፈሳዊ ሕግ ማውጣት ነው፤ ጉባኤውም «ቅዱስ ሲኖዶስ» በመባል ይታወቃል፤ በነገረ ቤተ

ክርስቲያን ዙሪያ የሚመክሩ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉባኤ ማለት ነው::

7.1.4. ሕገ እግዚአብሔር:- እንድንጠብቀው ወይንም እንድ ንፈጽመው ከእግዚአብሔር የተሰጠንን ሁሉ ሕገ እግዚአብሔር እንለዋለን:: በዚህ ጽሑፍ ግን በቁጥር ወስኖ የሰጠንን ብቻ እንመለ ከታለን:: እነዚህም አሠርቱ ቃላተ አሪትና ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ናቸው:: እነዚህ ሕግጋት እግዚአብሔር ሀበይት በመባል ይጠራሉ:: ጊዜያችን በሥጋዊው ተገልጦ በሚያስተምርበት ወቅት ቀድሞ በእን ጻረ ሙሴ የተሰጠውንና በፍጹም ቁጥር አሥር የሆነውን አሠርቱ ቃላትን ሕግ በማለት ጠርቷቸዋል:: «እኔ ሕግንና ነብያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም:: እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አን ዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፤ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ:: እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሡት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል::» ማቴ.5÷12–19 እን ዲል እነዚህ ሕግጋት /አሠርቱ ቃላተ አሪት/ የተሰጡበትም ሀበ ይት ዓላማዎች:-

1/ መጥፎውንና ክፉውን ለይተን እንድናውቅ፣

2/ ዓለሙ በእግዚአብሔር እጅ መሆኑን እንድናውቅ /ሮሜ. 3÷19/፣

3/ ኃጢአትን ለይተን እንድናውቅ /ሮሜ.3÷20/፣

4/ ክርስቶስን /አካላዊ ቃልን/ በመጣ ጊዜ ለመቀበል የሚያዘ ጋጅ መንገድ ስለሆነ /ገላ.3÷24/ ናቸው:: ስለ እነዚህ አራት ነገሮች ሕግ አሪትን ሰጥቶናል::ሕጉ በራሱ እንዲያጸድቅ ድሮውንም

www.zeyeneta.com

እንዳል ተቀበልነውም ማስተዋል ይኖርብናል። ሕግ ያስፈልገናልም ስንል ወልደ እግዚአብሔርን በማመን የሚገኘውን ጽድቅ ይተካል ማለታችን እንዳ ልሆነ መታወቅ አለበት። ደሙ ወልደ እግዚአብሔርን ሊተካ የሚችል ቀርቶ ሊወዳደረውም የሚችል የለምና።

ከዚህም በኋላ ጌታችን ሥጋዌውን አምነን በመንፈስ ውሉደ እግዚአብሔር ከተባልን ሥጋውንና ደሙንም ተቀብለን እርሱ አድሮ ብን ቤተ መቅደሶቹ ከተባልን በኋላ እንድንፈጽማቸው የተሰጡን ሕግ ጋት አሉ። ቅዱስ ጳውሎስ የሙሴን ሕግ የሥራ ሕግ እያለ ገልጦ ታል። ሮሜ.3÷27። የጽድቅ ፍጻሜ ባይሆኑም ተሠርተው /በሥራ/ ተገልጠው መታየት ያለባቸው ስለሆኑ። «በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደ ሉምና።» ሮሜ.3÷13 እንዲል። ጌታችን በሥጋው ተገልጦ የሰጠ ንን ሕግጋት ደግሞ የእምነት ሕግ ይላቸዋል። ሮሜ.3÷27።

የእምነት ሕግ እየተባሉ የተጠሩት ስድስቱ ቃላተ ወንጌል /ስድስቱ ቃላተ ምጽአት/ ናቸው። ምክንያቱም፦

1ኛ. ሠረው ራሱ ጌታችን በሥጋ ተገልጦ «እኔ» እያለ በመናገሩ «እርሱን እግዚአብሔር ነው» ብሎ የሚያምን የሚፈጽ ማቸው ስለሆነ፤

2ኛ. «ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ያደረጋችሁት ለእኔ ያደ ረጋችሁት ነው» ማለቱ ሥጋውን በበላን ደሙን በጠጣን ጊዜ አድሮብን የሚኖር በአንዱ አድሮ የሚሰጥ በሌላው አድሮ የሚቀበል መሆኑን ካላመንን እግዚአብሔርን «መቼ መጥተህ ተርበህ፣ ተጠ ምተህ...» እንድንለው ያደርጋልና።

3ኛ. ያለ ፍቅረ ቢጽ ፍቅረ እግዚአብሔር የማትፈጸም መሆኗን አምነን ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በነዳያን የምንገልጠው ስለሆነ፤

«ማንም፦እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ ወንድሙን የሚጠላ

ሰተኛ ነው። ያየውን ወንድሙን የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወድ እንዴት ይችላል? እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።» 1ኛዮሐ.4÷20-21 እንዲል።

በአጭር ቃል ሁለቱም የእግዚአብሔር ቃላት በመሆናቸውና መገኛቸውም እርሱ በመሆኑ ሲመሳሰሉ በሠሪዎቻቸው ይለያያሉ። የቀደመችው ሙሴ የኋለኛይቱ ሠራዔ ሕግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና። ከዚህም የተነሣ ኋለኛዋ የእምነት ሕግ ተብላለች። ይህም ማለት በማ መን ቢፈጽሟት የምታከብርና በፍርድ ቀን የምትጠየቀው ይህች ስለሆነች ነው። የማያምኑትና ሕግን ያልተቀበሉም በፍርድ የሚጠ የቁ አይደለም። «ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠ ፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደርጉ በሕግ ይፈረድባቸዋል።» ሮሜ.3÷12 እንደ ተባለ ያለ ሕግ ፍርድ አይደረግምና ሕጉ ተሰጥቶናል፤ ያስፈልጋልምና። እነዚህን ሕገ እግዚአብሔር ብለናቸዋል።

7.1.5. <u>አሪት</u>፦ በዚህ ርዕሰ ሥር ሁለት ንዑሳን ርዕሶችን እንመለከታለን።

ሀ/ <u>አምስቱ ብሔረ አሪት</u>፦ አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት በዕ ብራውያን ዘንድ ሕግ /ቶራ/ በመባል ይታወቃሉ። ጌታችን ወንድኃኒ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በመዋዕለ ሥጋዌው መጻሕፍቱን ሕግ ሲል እንደ ጠራቸው ተገልጿል። «እርሱም፦ ከእናንተ ጋር ሰሁ በሙሴ ሕግና በነብያት፣ በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።» ሉቃ.24÷44 እንዲል። ስለዚህ እነዚህ የሙሴ መጻሕፍት ሕግ ወይም የሕግ መጻሕፍት በመባል ይጠራሉ። በዕብራውያን የመጻሕፍት አከፋፈልም ሕግ በመባል የሚታወቁት እነዚሁ መጻሕፍት ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስም «በሕግና በነብያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር

www.zeyeneta.com

ጽድቅ...» ያለው መጻሕፍቱን ነው። ሮሜ.3:21።

ለ/ ሕገ አሪት፡ በዚህ ሥር የምንመለከታቸው ከአበው ጀምረው ለንጉሴ የተሰጡትንና እስከ ዘመነ ሥጋዌ እስራኤል ዘሥጋ የተጠቀሙባቸውን ሕግጋት ነው። እምላካችን እግዚአብሔር አሠርቱ ቃላት አሪትን መስጠቱ ለዓላማ እንደ ሆነ ከላይ የተመለከትነው ነው። አሥር ማድረጉም ሕግጋቱ ከዚያ ስለማይበልጡ ስለማያንሱም አይደለም፣ አሥር ቁጥር ፍጹም ስለሆነ ፍጹም ሕግን የመስጠቱ ምልክት ነው። ስለዚህ ከዚህ ውጭ የሆኑ በአሪት የተሰጡን ብዙ ሕግጋት አሉን። እነዚህም ከግዝረት ጀምሮ ስለሚበላውና ስለማይበላው እንስሳ፣ ስለ ካህናቱ፣ ስለ ቤተ መቅደሱና ስለ መሥዋዕቱ፣... ብዙ ሕግጋት ተሰጥተውን ነበር።

እነዚህ ሕግጋት በጊዜው ጠቅመዋል፡ በአዲስ ኪዳን ለሚተካው አምላል ጥላ መርገፍ በመሆን ካገለገሉ በኋላ ጊዜያቸውን ፈጽመው የተፈጸሙና አማናዊውን የተኩ አሉ፡ እንዳለም የዘለቁ ደግሞ አሉ። ዐቢዩ ጉዳይ ግን አብዛኛዎቹ አማናዊውን ተክተው ማለፋቸው ነው። በተለይ መሥዋዕተ አሪትንና ሥርዓቱን ስንመለከት ሙሉ ለሙሉ ተተክቷል። ጌታችን «ምሕረት እወዳለሁ መሥዋዕትን አይደለም የሚለውን አላነበባችሁምን።» እንዳለው በምሕረት የሚፈጸም ምሥጢረ ንስሐ ተተክቷል፤ አሁን በየጊዜው በግና ፍየል... የመሳሰሉትን ማቅረብ ቀርቶልናል። ይህን የመሰለው ሕግ የተ ባ ሕግ ተብሏል። ዕብ.7÷19።

«እንግዲህ ያልተገረዘ ሰው የሕግን ሥርዓት ቢጠብቅ አለ መገ ረዙ እንደ መገረዝ ሆኖ አይቆጠርለትምን? ከፍጥረቱም ያለተገ ረዘ ሕግን የሚፈጽም ሰው የሕግ መጽሐፍና መገረዝ ኅለህ ሕግን በም ትተላለፈው በእንተ ይፈርድብሃል።» ሮሜ.2÷25-27 እንዲል። ስለዚህ ሕገ አሪት ብለን የጠቀስናቸው ሕገ ግዝረት፣ ሕገ መሥዋዕ

ት፣ ሕገ በዓላት.... የመሳሰሉትና በአሪት የተጻፉትን ነው። እነዚህን የመሰሉ ዝርዝር ሕግጋት ላይ ያጠኑ አንዳንድ ተመራማሪዎች የሕ ጉቹን ዝርዝር ቁጥር እስከ 600 ያደርሱታል።

7.1.6. <u>ወንጌል /ሕገ ወንጌል/</u>፡-

ሀ/ <u>ወንጌል</u>፡- ሕግ ትባላለች። በክርስትና ሕይወታችን ማድረግ የሚገባንን የማይገባንንም ገልጻ የምታስተምርና ለነፃት ለመንግሥተ ሰማያት የምታበቃ፣ ቢጠበቋትም የምትጠብቅ ስለሆ ነች ሕግ ትባላለች። እንደ አብነት ከመጀመሪያው የጌታችን ስብከት ብንነሣ ከአንቀጸ ብፁዓን ጀምሮ ብርሃን እንድንሆን፣ ጨው እንድ ንሆን፣ በፈተና እንድንጸና፣ ከዚህም በኋላ ደግሞ ስንኪን መግደል እንዳንሳደብ፣ ስንኪን ማመንዘር አይተን እንዳንመኝ ... የምታስ ተምር ስለሆነ ወንጌል ሕግ ተብላለች።

ቅዱስ ጳውሎስም «በወንጌል አላፍርም።» /ሮሜ.1÷16/ ካለ በኋላ ይህች ወንጌል የሕይወታችን ሕግ እንደ ሆነች «ወንድሞች ሆይ+ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን?» ሮሜ.7÷1 በማለት በሕይወታችን ሁሉ የምንመራባት ሕግ ወንጌል እንደሆነች አስተምጠልናል።

ለ/ <u>ሕገ ትሩፋት</u>፡- በወንጌል ወይም በአዲስ ኪዳን የተጻፈ ውን ሁሉ ስንመለከት ፍጹምነትን የሚያመለክት ነው። ለምሳሌም በንጽጽር እንመልከት፡-

www.zeyeneta.com

አሪት	ወንጌል
አትግደል	ወንድሙን የሚቆጣ የሚሰድብ ሁሉ የሸንጉ የገሃነም ፍርድ የገባዋል:::
አታመንዝር	አይቶ የተመኘ አመነዘረ፣ ስለዚህ ያሰናከለህን አካል ቆርጠህ ጣል::
ሚስቱን የሚፈታ የፍቺን ደብዳቤ ይስጥ::	ስለ ዝሙት የፈታም የተፈታችውንም ያገባ ያመነዝራል::
ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ	ክፉውን አትቃወም፣ ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ግራህን አዙርለት::
ባልንጀራህን ውደድ፣ ጠላትህንም ጥላ::	ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ለሚያሳድዷችሁ፣ ጸልዩ ፍጹማን ሁኑ::
ከለለህ አሥራቱን በኩራቱን አውጣ::	ያለህን ሽጥና ተከተለኝ፣ ስለ እኔ ቤተሰቦቹን ያለተወ ለእኔ ሊሆን አይገባውም::

እኒህንና የመሰሏቸውን ልዩነቶች መመልከት ይቻላል:: ይህም ብቻ አይደለም «በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለ ምን ታያለህ- በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?» ማቴ.7÷7:: ስለዚህም አብዝተን እንድንሠራ የምታዝዘን ናትና ሕግ ትሩፋት ትባላለች:: «እንዲከለህም እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጐናጸፊያህን ደግሞ ተውለት ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሂድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ:: ለሚለምንህ ስጥ÷ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፈቀቅ አት በል::» ማቴ.5÷42 እንዲል:: ጌታችንም በወንጌል ያዘዘውን መፈጸም እንደሚገባን «ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል::...» ማቴ.7÷24-29 ሲል አስተምሮናል:: ስለዚህ ወንጌል ሕግ ትሩፋት ሕግ ፍጽምት ትባላለች::

7.2. ትእዛዝ:- እንደ ኪዳኑ ወልድ ከፍሌ መዝገበ ቃላት አገላለጽ ትእዛዝ የተባለው «አድርግ አድርግ» የሚለው ነው::

አንዳንድ ሊቃውንትም ይህን አላቱ ይሰማመባታል:: ይሁን እንጂ ሕግና ትእዛዝ ሊመራረሱ እንመለከታለን:: ለአብነትም «ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ ... (ዮሐ ፲፬-፲፭) የሚለውን ስንመለከት ሕግንም የሚያመለክት ነው:: «ጠብቁ» የሚለው «አታድርጉ»ንም የሚያመለክት ነውና:: «ከእናንተ እያንዳንዱ የእንዱን ሽከም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ::» (ገላ.፮÷፪) የሚለውን ስንመለከት ደግሞ ሕግ÷ ትእዛዝ ሆኖ እናኝ ዋለን:: «ፈጽሙ» ይላልና:: ስለዚህ ሕግና ትእዛዝ እየተወራረሱ የተጻፉ ናቸውና ፍጹም ልዩ ናቸው ማለት አይቻልም:: ይሁን እንጂ ሁል ጊዜ አንድ ሊሆኑ እንደማይችሉ ከላይ ለሕግ የተሰጠው ማብራሪያ ሊያስረዳን ይችላል::

ትእዛዝ በብሉያትም በሐዲሳትም እንደ ተጻፈው ጊዜያዊም ዘላለማዊም ሆኖ እንመለከተዋለን:: የበለጠ ግልጽ ለማድረግ እንደ ሚከተለው በሁለት ከፍለን እንመለከተዋለን::

7.2.1. <u>ጊዜያዊ ትእዛዝ:-</u> ይህ ትእዛዝ በጊዜ የተወሰነ፣ ከተወሰነለት ጊዜ በኋላ ትእዛዝነቱ የሚቀር ማለት ነው:: የሆነው ሆኖ ግን የሁሉም በጊዜ የተወሰኑት ትእዛዛት መጠነ ጊዜያቸው እኩል ነው ለማለት አንችልም:: እንደ አብነትም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመለከታለን:: «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ አማሌቅ በመንገድ እየተቃወመ ያደረገበትን እበቀላለሁ:: አሁንም ሂደህ አማሌቅን ምታ÷ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣ አትማራቸውም፣ ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ሕፃኑን በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል::» ሲል ሳሙኤል ለሳኦል የነገረው ትእዛዝ ለዚያ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ነበር:: 1ኛሳሙ.15÷3:: በጊዜውም የታዘዘውን ስላልፈጸመ «እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት÷ ማዳመጥም የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ

www.zeyeneta.com

ይበልጣል። 1ሳሙ.15÷22 በሚል ተገሥጸበታል። ይህም ትእዛዝ ነፍን የሚያረጋግጥልን ነው።

ለምሳሌ ለረጅም ጊዜ ከቆየው ትእዛዝ አንዱ ግዝረት ነው። ለአብርሃም የተሰጠ ትእዛዝ ነው። ዘፍ.17÷10። ከዚህ በኋላ ከእስራኤል የሚወለድ ወንድ ሁሉ ይገዘር ነበር። ግዝረት የእምነት አርአያነት የጥምቀት ምሳሌ ሆኖ እስከ ጌታችን መገለጥ ድረስ ቆይቷል። ግዝረቱ በተአምራት ይሁን እንጂ ሕግን ሊፈጸም የመጣ ጌታም በመሆኑ ተገዝሯል። ሉቃ.2÷21። በኋላ ግን የግዝረት ፍጻሜ ጥም ቀት በተሰጠች ጊዜ ትእዛዝነቱ /ተፈጻሚነቱ/ ቀረ። መገዘርም አለመ ገዘርም ለሥጋ ብቻ ሆኖ ቀርቷል፣ ሁለቱም አይጠቅሙምና። ገላ.5÷6። የመጀመሪያው የቅዱሳን ሐዋርያት ሲኖዶስም «ግዝረት» አስፈላጊ እንዳይደለ አስታወቀ። ሐዋ.15÷1-30። ይህም የሚያመለ ከተው ግዝረት ለረጅም ዘመን ሲፈጸም የኖረ ትእዛዝ መሆኑን ነው። ይሁን እንጂ በጥምቀት ፍጻሜውን ስላገኘ አሁን የማይጠመቅ እንጂ የማይገዘር አይጸድቅም አያሰኝም።

7.2.2. ዘላለማዊ ትእዛዝ፡- ይህ በጊዜ የማይወሰን በሁለቱም ጊዜያት ተፈጻሚነት ያለው ትእዛዝ ነው። «ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛዪቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ሁለተኛዪቱም ይህችን ትመስላለች+ እርስዋም ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት። አሪትና ነቢያት በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ጸኑ።» ማቴ.22÷40።

እነዚህ ትእዛዛት በቦታም በጊዜም የማይወሰኑ ናቸው። እነዚህ ትእዛዛት በሕይወተ ሥጋ ብቻ ሳይሆን በሕይወተ ነፍስም የማይቋረጡ+ እግዚአብሔርን በማምለክና አንዱ ሌላውን በማሰብ የሚፈጸሙ ትእዛዛት ናቸው። እኒህን የመሰሉ ስንፈጽማቸው የምንኖራቸውና በጊዜ ያልተወሰኑ ትእዛዛትን ዘላለማውያን እንላቸዋለን።

7.3. የተሻረችው ትእዛዝ፡-

ለዚህ ምዕራፍ መነሻ የሆነንን አንቀጽ ጠቅሰን አሳቡንና ትእዛዙን እናስቀምጣለን። «ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረ ገምና+ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች+ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቷል።» ዕብ.7÷19። ይህንና መሰል ጥቅሶችን በማንሣት አንዳንድ ሰዎች ተሽሯል፣ ቀርቷል፣ ወድቋል አይጠቅምም የሚሉት ነገር ይበዛል። ለመሆኑ የተሻረው ትእዛዝ ወይም ሕግ የቱ ነው? ቅዱስ ጳውሎስ ተሽራለች ያላትስ ማንን ነው።

ሀ/ ሕገ መሥዋዕት፡- ሙሉ ለሙሉ የተሻረችና የማትጠቅመው ትእዛዘ መሥዋዕት ሕገ መሥዋዕት ናት። በአሪቄ እንደ ነበረ ለኃጢአትም፣ ለደኅንነትም፣ ለበዓላትም፣ ለመሥዋዕትም የሚቀርቡትን እንስሳት እንድናቀርብ በሐዲስ አልታዘዝንም። የደም መረጨት፣ የስብ ማጨስ፣... ይህን የመሰለው ሁሉ ቀርቷል። ለምን ቢሉ አንድ ጊዜ ራሱን መሥዋዕት አድርጉ ካቀረበልን ከጌታችን ሥጋና ደም እየተሳተፍን የምንድን ኃጢአታችን የሚስተሠርይልን ሆኗልና። «እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለ ሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፣ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።» ዕብ.7÷25 እንዲል። ይህም አንድ ጊዜ በቀራንዮ ራሱን መሥዋዕት በማድረጉ ሁልጊዜ ከኃጢአት ሲያነጻን የሚኖር ስለሆነ ነው። «እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሥረያ አድርጎ አቆመው።» ሮሜ.3÷25 እንዲል።

ስለዚህ አማናዊውና ፍጹም መድኃኒት የሆነው ስለ መጣ ምሳሌው አስፈላጊ አይደለም። የእንስሳት መሥዋዕት ቢቀጥልማ የጌታችንን ሞት ለከንቱ ማድረግ ይሆንብናል። «የእግዚአብሔርን

www.zeyeneta.com

ጸጋ አልጥልም፣ ጽድቅስ በሕግ ብኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከ ንቱ ሞተ።» /ገላ.2÷21/ በማለት የተገለጠው ይኸው ሕገ መሥዋዕት ነውና። ቅዱስ ጳውሎስም ብዙ ጊዜ በሕግ እንደማይጸድቁ ያስተማ ረው የጌታችንን ቤዛነት አናምንም ለሚሉት ነው።ይህ በእርሱም ሕይ ወት የተፈጸመ ስለ ነበር ነው። «እኔ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቼ ነበርና።» /ገላ.2÷19/ ሲል የገለ ጸው በጌታችን ማመንን በመቃወም ሲያሳድድበት የኖረውን ሕይ ወት ነው። ያ በእርግጥም ሞት ነው።

ለ/ <u>የመንጻት ሕግ</u>፡- «እንደ ሙሴም ሕግ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ÷ በጌታ ሕግ፡- የእናቱን ማኅፀን የሚከፍት ወንድ ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ ይባላል ተብሎ እንደ ተጻፈ በጌታ ፊት ሊያቀ ርቡት÷ በጌታም ሕግ፡- ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች እንደ ተባለ÷ መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰ ዱት።» /ሉቃ.2÷22-24/ ተብሎ እንደ ተጻፈ የመንጻት ሕግ ነበራ ቸው። በዘጸ.13÷2፣ በዘሌ.12÷1 ላይ ተመልከቱ። ይህ ሕገ መሥ ዋዕት ተሽሯል፣ የሚቀርበው መሥዋዕትም ቀርቷል። ይህ ሲባል ግን እንዲት ሴት ከወለደች በኋላ ወደ ቤተ ክርስቲያን የምትገባበት ቀን፣ በግጻጇም ጊዜ ስንት ቀን እንደምትቆይ፣ በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የለም ማለት አይደለም። ያን ጊዜ የምትነጻበት ሕግና መሥዋዕት ነበራት፣ ያ ቀረላት ለማለት እንጂ እግዚአብሔርና ማደ ሪያውን ቤተ ክርስቲያንን ለማክበር የሚገባው ሥርዓት አልቀረም።

ሐ/ <u>ሕገ ምግብ</u>፡- በአሪት ስለ መብል ወይም ስለ አመጋ ገብ ሕግ ነበር። ከዚህም ውስጥ ሳይታጠቡ አለመብላት፣ ስብ አለመ ብላት፣ ጥሬ ሥጋ አለመብላት፣... የመሳሰሉት እነዚህ ሁሉ ምሳሌ ነት የነበራቸውና በጊዜያቸው ያገለገሉ ነበሩ። አሁን ግን ስለ አመጋ ገብ ሰው እንደ ፈቀደው ቀቅሉም፣ ጠብሰም፣ ጥሬውንም ሊበላ

ይችላል። ወደ ሆድ የሚገባ ሁሉ ወደ እዳሪ እንዲወድት የታወቀ ነው ተብሏልና። እኒህና የመሰሏቸው አማናዊ ትርጉማቸውን አስከ ያገኙ በምሳሌነት ጸንተው ኖረዋል።

ከላይ የተጠቀሱትን የሚመስሉ እንደ ግዝረት ያሉ የማይጠ ቅሙም የማጉይጉዱም ደግሞ አሉ። መገዘርን የሚቃወም የለም፡ ጥቅሙም ጉዳቱም ለሥጋ ነውና። ስለዚህ የተተኩት ይህን የመሰሉት ናቸው። ቅዱስ ጳውሎስ አጠንክሮ የተናገረለት ግን «ሕገ መሥዋዕ ትን» ነው። ይህም በጌታችን ከሚገኘው ጽድቅ የሚከለክል የሞተ መሥዋዕት ስለሆነ ነው። ይህንኑ የመሥዋዕት ጉዳይ በተገቢራራ መልኩ ምዕራፍ አሥር ላይ እንመለከተዋለን።

7.4. መጻሕፍት አልተሻሩም፡-

አንዳንድ ሰዎች «የተሻረች ትእዛዝ አለች» በሚለው ኃይለ ቃል ሰበብ ቃለ እግዚአብሔርን ሁሉ እንደ ተሻረ እንደማይጠቅም አድርገው ለማቅረብ ይዳዳቸዋል፣ መጻሕፍት ግን እንዳልተሻሩ ለግንዛቤ ያህል የሚከተሉትን እንመለከታለን።

<u>መጻሕፍተ አሪት</u>፡- ከላይ እንደ ተጠቀሰው የሕግና የትእዛዝን ልዩነት የማያውቁ የውልንና የውል ማስረጃንም ልዩነት ያልተገነዘቡ የሚመስሉ ሰዎች አሉ። አንድ ስምምነት ሲፈጸም ሰነድ ይዘጋጅ ለታል። ሲፈጸምና ጊዜው ሲያበቃ በውሉ መሠረት የሚፈጸመው ሥራ ያቆማል። ማስረጃው ግን ሊኖር ይችላል። አንዳንድ ሰዎች በዓ ለም በቀላሉ የሚረዱትን ነገር እየረሱ ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ልብ ወለድ የመሰለ ነገር ሲናገሩ ይደመጣል። ለመሆኑ ሕገ መሥዋዕትን የመሰሉ ሕግጋት መተካታቸው ኦሪት ዘሌዋውያንን ሊሽር ይችላልን? በመጻሕፍቱ የተጻፉ ሌሎች ትእዛዛትንስ? መመርመር ያለበት ጉዳይ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ሕገ መሥዋዕት መሻር በሰፊው ባስረ

www.zeyeneta.com

ዳበት በሮሜ መልእክቱ «ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ አይደለም።» /ሮሜ.9÷6/ በማለት ቃለ እግዚአብሔር ሊሻር እንደ ማይችል አስረግጧል። ጌታም ትምህርቱን አስፍቶ ማስተማር በጀመረበት ዕለት በተራራው ላይ ስብከቱ ያስቀመጠው ታላቅ ሐቅ ይህ ነው። «እኔ ሕግንና ነብያትን /መጻሕፍትን/ ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም። እውነት እላችኋለሁ÷ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ÷ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም÷ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።...» ማቴ. 5÷17–20፤ ሉቃ.16÷17፣ እንዲል። «ማንም በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው።» /ገላ.3÷11/ ያለውም በጌታችን ሳያምኑ፣ ሳይጠመቁና ሥጋውን ደሙን ሳይቀበሉ በሕገ መሥዋዕት፣ በሕገ ግዝረት ለሚመኩት ነው።

ላመኑት ደግሞ የእምነት ሕግ አላቸውና የእምነት ሕግ ወይም ሕገ ምግባር እንዳልተሻረ ይልቁንም እንደ ጸና ማስተዋል ይገባል። «የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።» ገላ.6÷3 ተብለናልና። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ በእምነት ሲል በሕገ መሥዋዕትና በሕገ ግዝረት ላይ ሆን ጌታችንን በማመንና በእርሱ ሥጋና ደም /ዘላለማዊ መሥዋዕት/ እንድናለን ለማለት እንጂ ከማመን በኋላ የሚፈጸመው ሕገ ምግባር ቀርቷል ለማለት አይደለም፤ 'ይልቁንም አብዝተን እንድንሠራ ሕገ ትሩፋት ወንጌልን ተቀበልን እንጂ። «ነገር ግን አንድ ሰው፦ አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ÷ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል። እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል። አንተ ከንቱ ሰው÷ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን? አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ

አልነበረምን? እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ÷ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን? መጽሐፍም፦ አብርሃም እግዚአብሔርን አመነ። ጽድቅም ሆኖ ተቆጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።» ያዕ.2÷18–26።

በዚህ ክፍል ሁለት ዐበይት ነገሮችን መገንዘብ ይቻላል። የመጀመሪያው ሕገ ምግባር እንዳልተሻረችና ከምግባር /ሥራ/ የተለየ እምነት የሞተ መሆኑን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ቅዱስ ያዕቆብ ለዚህ ማስረጃ አድርጉ ያቀረባቸው መጻሕፍተ አሪት መሆናቸውንና መጻሕፍተ አሪት አለመሻራቸውን ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ.9÷6 ላይ «ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ አይደለም» ሲል የመጻሕፍቱን አለመሻር በጽኑ ማጎተም ዘግቶታል። እነዚህን ለአብነት አቀረብን እንጂ ሌሎችም ያልተጠቀሱ አሉ። ስለ ኪዳን በሚቀጥለው ምዕራፍ፡ ስለ ቤተ መቅደስና ታቦት ደግሞ በምዕራፍ ዘጠኝ ላይ እንመለከታለን።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ስምንት

ኪዳን

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው እግዚአብሔር ለሰው ቸርነት ያደረገበትን ቃል ኪዳን፣ መሐላ፣ ውል ወይም ስምምነት ነው። እግዚአብሔር ከግለሰብ ጋር ያደረገው ውል ወይም ስምምነት አለ፣ ለሰው ዘር በሙላ የሚደረግም የቸርነቱ ስጦታ፣ መሐላና ውልም አለ። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ በዕብራውያን መልእክቱ በምዕራፍ ስምንት ላይ የገለጸው ስለ ብዙዎች ስለ ተደረገው ውል ወይም ከብዙዎች ጋር ስላደረገው ኪዳን ነው። ይህን መነሻ በማድረግ በዚህ ምዕራፍ ስለ ኪዳን እንመለከታለን።

8.1. <u>ትርጉም</u>

ኪዳን በቁሙ በተለያዩ ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል፣ ቁም ነገር፣ የፍትርና የአንድነት መሐላ፣ ሰላማዊ ሕግ፣ ሁለቱን ወገን አንድ የሚያደርግ፣ ስለ ረብና ስለ ጥቅም በተስፋ የቆመ የተጻፈ ሥርዓት፣ ቢያፈርሱት ጉዳትና ጠብ የሚያመጣ ጥቅም የሚያሳጣ ይሉታል። /ኪ.መ.ክ.+ ገጽ 529/

ኪዳን በአንድ ወገን ብቻ የሚፈጸም አይደለም፣ የሚፈጽም ሁለተኛ ወገን ያለው፣ ውሉ መሐላውና ምልክቱም በታወቀ በተረዳ ነገር የሚገለጽ ነው። በዚህ ጽሑፍ የምንመለከተው በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ግንኙነት ነው። በእርግጥ እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ያለ ቃል ኪዳን አልተወውም። «የጣ ሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ።» ሲል ከመፍጠሩ በፊት ቃል ገብቶለታል። ከፈጠረውም በኋላ «እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፣ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፣ ወንድና ሴት አድ

ርጉ ፈጠራቸው። እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሏት፥ ግዟትም፣ የባሕርን ዓሦችና የሰማይ ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዟቸው።» ዘፍ. 1÷26-28። ከጥቅሱ የምንረዳቸው ቁም ነገሮች አሉ። ለኪዳን ቢያንስ ሁለት አካላት ያስፈልጋሉ፣ውሉን የሚቀባበሉ ወይም ውል ሰጭና ውል ተቀባይ፣ ከዚህም በኋላ መሐላው/ኪዳኑ/ አለ፣ እንዲሁም ደግሞ የኪዳን ምልክት አለ። ለምሳሌ ያህልም በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል የነበረውን የመጀመሪያ ውል ላይ አራቱንም እንመለከታለን።

1. ውል ሰጭ (መሐላውን የማለ) ወይም ኪዳን የገባ - እግዚአብሔር
2. ውል ተቀባይ (የተማለለት) ባለ ቃል ኪዳን - አዳም
3. ውሉ (መሐላው) - ብትበላ ትሞታለህ ባትበላ በሕይወት ትኖራለህ ብሎ እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው ሕግና ትእዛዝ
4. ምልክት - ዕፀ በለስ

እነዚህን አካላት በሌሎቹም ውሎች ውስጥ ልንመለከት እንችላለን። በተጨማሪነት ለኖኅ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ስንመለከት መሐላው «እግዚአብሔርም ለኖኅና ለልጆቹ እንዲህ ብሎ ተናገረ፦ እኔም እነሆ ቃል ኪዳኔን ከእናንተና በኋላ ከሚመጣው ከዘራችሁ ጋር አቆማለሁ፣ ...ሥጋ ያለውም ሁሉ ጻግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም፣ ምድርንም ለማጥፋት ጻግመኛ የጥፋት ውኃ አይሆንም። እግዚአብሔርም አለ፦ በእኔና በእናንተ መካከል፥ ከእናንተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል፥ ለዘላለም የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው፣ ቀስቴን በደመና አድርጌአለሁ፥ የቃል ኪዳንም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል። በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ በደመናው ትታያለች፣ በእኔና

www.zeyeneta.com

በእናንተ መካከል÷ ሕያው ነፍስ ባለውም ሥጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ።» /ዘፍ.9÷8–15/ ሲሆን ምልክቱም ውሉን የተቀባበሉትም በግልጽ ተቀምጠዋል።

8.2. <u>የኪዳኑ ዓይነት</u>:–

እግዚአብሔር ከሰው ጋር በተለያየ መንገድ በተለያየ ጊዜና ቦታ እንደ አስፈላጊነቱ ቃል ኪዳን ገብቷል። በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውንም ሆነ አጠቃላይ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ይረዳን ዘንድ በሦስት መንገድ /ዓይነት/ በመከፈል የእግዚአብሔርንና የሰውን የቃል ኪዳን ግንኙነት እንመለከታለን።

8.2.1. <u>ብሉይ ኪዳን</u> :–

ብሉይ ያረጀ፣ ጥንታዊ፣ ቀዳማዊ፣ የድሮ፣ የቀድሞ፣ የፊት ማለት ስለሆነ ብሉይ ኪዳን:– ጥንታዊ ቀዳማዊ ውል፣ የሚል ትር ጉም ይኖረዋል። ይህ ውል እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤል ዘሥጋ የገባው ቃል ኪዳን ወይም ውል ነው። ይኸውም በባር ነት ቀንበር ተይዘው አገዛዝ ጸንቶባቸው በጭንቅ ከሚኖሩበት ከግ ብጽ አላቅቆ ከነዓንን ማውረስ ነበር፣ ለሙሴም የተነገረው ይህ ነበር። ዘጸ.3÷15–19።

የዚህም ኪዳን መገለጫ ምልክት ቀድማ ለሙሴ የታየችውና የማትቃጠለዋ ቁጥቋጦ (ዕፀ ጳጦስ) ነበረች። ዘጸ.3÷1። ከግብጽ ከወጡ በኋላ በመንገድ እያሉ እግዚአብሔር ይገለጥላቸው ነበር። የተጻፈ ሕግ ንም ሰጥቷቸዋል፣ ከዚህ በኋላ መገለጫውን ታቦተ ኪዳኑን የሚያስ ቀምጥበትን ድንኳን አሳይቶ እንዲሠራ አዘዘው፣ ሙሴም እንደታየው ሠራ። «በተራራው እንደ ተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ።» /ዕብ.8÷6/ እንዲል ኃጢአት የሚያስተሠርይበትንም ውል ወይም መሐላ ነገረው። ይኸውም ኪዳኑ የተመረቀበት ወይም ተግባራዊ የሆነበት የእንስሳት ደም ነበር። «ስለዚህም ፊተኛው ኪዳን

እንኳ ያለ ደም አልተመረቀም። ሙሴም ትእዛዛትን ሁሉ እንደ ሕጉ ለሕዝቡ ሁሉ ከተናገረ በኋላ÷ የጥጆችንና የፍየሎችን ደም ከውኃና ከቀይ የበግ ጠጉር ከሂሶጵም ጋር ይዞ:– እግዚአብሔር ያዘዘላችሁ የኪዳን ደም ይህ ነው ብሉ በመጽሐፉና በሕዝቡ ሁሉ ላይ ረጨው።» ዕብ.9÷18፣ዘጸ.24÷6–8።

ስለዚህ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን በደም እንዳጸናው እንመለከታለን። ሕዝቡ ግን ባለመጠበቅ ብዙ ጊዜ እንደ ተጉዱ እግዚአብሔርም ኪዳኑን ካልጠበቁ እንደማይጠብቃቸው ያስጠነቅቃቸው ነበር። «አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳ ኔንም ብትጠብቁ÷ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑልኛላችሁ እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደ ሰም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ።» ዘጸ.19÷5 እንዲል።

የብሉይ ኪዳን ግን ነቀፌታ እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ ተናግሯል፡ «ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ሥፍራ ባልተፈለገም ነበር።» ዕብ.8÷7 እንዲል። ነቀፌታ አለው ያሰኘው ምኑ ነው?

ሀ. <u>ውጫዊ /አፍአዊ/ ነበር</u>:– ይህ ኪዳን ለሰው ውጫዊ ነው የሚያሰኘው መሥዋዕቱ የእንስሳት ስለሆነና ደሙንም ይረጨታል እንጂ ስለማይበሉት ነበር። ሌላውንም ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን መሥዋዕት በማቃጠል የሚያቀርቡት እንጂ በሌላ ውሳጣዊ ነገር አይቀርብም ነበር። ዘሌ.9÷8–24። በዚህም የተነሣ የሰውን መሠረታዊ ኃጢአት /ጥንተ አብሶን/ ሊያስተሠርይ የሚችል ሰውንም ከሞትና ከኃጢአት የሚዋጅ አልነበረም። ዘጸ.19÷11።

ለ. <u>የሰውን ኀሊና ፍጹም ሊያደርግ ያጣውንም ነጻነት ሊመልስ</u> አልቻለም:– ሰው በገነት ጸንቶ በኖረበት ጊዜ መንፈሱ ያልተ ረበሸ ዕውቀቱና አሳቡ መንፈሳዊና ቢጹ ከእግዚአብሔርም ጋር

www.zeyeneta.com

ጎብረት ያለው ነበረ። የሰይጣንን ምክር ሰምቶ ዕፀ በለስን ከበላ በኋላ ግን ከፉው ሁሉ እየሠለጠነበት መጣ እንጂ አእምሮውን ለበጉ ነገር ለማዋል ወደ ቀደመው ነጻነት ሊመልሰው አልቻለም። አንድ ጊዜ ለኃጢአት ተሸንፏልና በባርነት ኖረ በኃጢአትም ሕግ ተገዛ። «ሰው ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና።» 2ኛጴጥ.2+19፤ «ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው።» ዮሐ.8+34 እንዲል ከዚህ ባርነት ነጻ ሊወጣ አልቻለም ነበር። «እንደዚህማ ባይሆን የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በኅሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን?» ዕብ.10+2፤ «እንደዚህም ስለ መብና መሥዋዕት ይቀርባሉ እነዚህንም እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ፥ ስለ ምግብና ስለ መጠጥም ስለ ልዩ ልዩ መታጠብም የሚሆን የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልክውን በኅሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም።» ዕብ.9+10 እንዲል።

ሐ. <u>ፍጹም ይቅርታን አላስገኘም</u>፦ ብሉይ ኪዳን ሰውን ከጥንተ አብሶ አላትቶ ፍጹም ይቅርታን ከእግዚአብሔር አላስገኘም። ለአገልግሎቱ የሚሾሙት ድካም ያለባቸው ናቸው። ዕብ.7+28። መሥዋዕቱም ምውት እንስሳ ነበርና። «ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና።» ዕብ.10+4 እንዲል። ሌላው ቀርቶ የእንስሳትን ደም የበላን ሰው እንኳ ይህ መሥዋዕት ራሱ መፈወስ አልተቻለውም። ዘሌ.17+10–13። «እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል።» ዕብ.9+22 እንዲል በዚያ ኪዳን የማይነጹ ነበሩ።

መ. <u>በፍርሃት የሚከበር ነበር</u>፦ ኪዳኑን የሚያከብሩት ስለሚፈሩ ብቻ ነበር። ባለመታዘዛቸው ምክንያት በየጊዜው መቅሰፍት ስለሚታዘዝባቸው በፍርሃት የሚያከብሩት እንጂ ውስጣቸውን ተዋሕዶት በፍቅርና የሚያገኙትንም አጋ በማሰብ አልነበረም። የሚታዘዙትም ትእዛዝ እንዲፈሩ የሚያደርግ ነበር። «እግዚአብሔርም ሙሴን አለው፦ ወደ ሕዝቡ ሂድ+ ዛሬና ነገም ቀድሳቸው+ ልብሳቸውንም ይጠቡ። በሦስተኛው ቀን ሕዝቡ ሁሉ ሲያዩ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ይወርዳልና ለሦስተኛው ቀን ይዘጋጁ። ወሰንም ለሕዝቡ በዙሪያው አድርግላቸው፦ ወደ ተራራው እንዳትወጡ ዳር ጫፉንም እንዳትነኩ ተጠንቀቁ። ተራራውንም የነካ ፈጽሞ ይሞታል። የማንም እጅ አይንካ ነገር ግን የሚነካው ሁሉ ይወገራል+ ወይም በፍላጻ ይወጋል እንስሳ ወይም ሰው ቢሆን አይድንም በላቸው።» /ዘጸ.19+10–13/ የሚለው የትእዛዙን አስፈሪነት ያመለክታል። «እንዲህም ሆነ በሦስተኛው ቀን በማለዳ ጊዜ ነጐድጓድና መብረቅ ከባድም ደመና እጅግም የበረታ የቀንደ መለከት ድምፅ በተራራው ላይ ሆነ፤ በሰፈሩም የነበሩት ሕዝብ ሁሉ ተንቀጠቀጡ።» /ዘጸ.19+16/ የሚለው ደግሞ የሕዝቡን ፍርሃት የሚያሳይ ነው።

ስንኳን እነርሱ ሙሴም እጅግ ይፈራና ይንቀጠቀጥ እንደ ነበር ተጽፎልናል። «ሙሴም፦ እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያስፈራ ነበር» ዕብ.12+21 እንዲል።

ሕጉንም በትምህርት ሰሙት እንጂ ውሳጣዊ ልቡናቸውን ይለውጥ ዘንድ ስላልተቻለው ደጋግመው እግዚአብሔርን ባድለዋል፤ ወደ ባዕድ አምልኮም ተሉ ዘወር ብለዋል። እግዚአብሔር ከንቱ እንዳወጣቸው ወዲያውኑ ጣዖት ማሠራታቸው ምን ያህል ከልቡ ናቸው ኪዳኑ እንደ ጠፋ የሚያረጋግጥልን ነው። ዘጸ.3+1–35።

8.2.2. ሐዲስ ኪዳን፦ ሐዲስ አዲስ ማለት ነው። አዲስ ኪዳንም+ አዲስ ውል አዲስ ስምምነት ማለት ነው። ለዚህም አስቀድሞ ትንቢት እየተነገረ ሱባኤ እየተቆጠረ እንደመጣ ቅዱሳት መጻሕፍት

www.zeyeneta.com

ያስረዳሉ። «እነሆ÷ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል÷ ይላል እግዚአብሔር። ከግብፅ አገር አወጣቸው በነድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደ ገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም፡ እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና÷ እኔም ቸል አልኋቸው÷ ይላል እግዚአብሔር።» ኤር. 31÷31–32 እንዲል።

የሐዲስ ኪዳን መሥራቿ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ኪዳኑ የጸናበትም ደም አምላካዊ ነው። «ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና፡– እንካችሁ÷ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመሰግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፡– ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።» ማቴ.26÷26–27 እንዲል።

የአዲሱ ኪዳን ደም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም መሆኑንና ስለ ኪዳኑም ደም አመሠራረት ወይም ስለ መሥዋዕተ ሐዲስ መነጋገር የብሉይን ኑቀፈታ የተባለውን ምንነትም ለማስታወስ ነው። ስለ ብሉይ ኪዳን ኑቀፈታ ስናነሣ ጌታችን ከሕግ ወገን ኑቀፈታውን ያራቀለት ወይም ያሻሻለው መኖሩን መመርመር ይገባል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በገጻመ ቆርንቶስ 40 መዓልትና 40 ሌሊት ጸሞ ከተመለሰ በኋላ ማስተማር የጀመረው የአዲሱን ኪዳን ሕግ በመስጠት ነበር። ይኸውም አንቀጸ ብፁዓን የሚባለው የትሩፋት ሕግ ነው። ከዚህ በመቀጠል በማቴ.5÷21–48 ያሉትን ስንመለከት የቀደመውን እያነሣ በአዲሲቱ ኪዳን ምን ያህል መሻሻል እንዳለባቸው ገልጿል። «ለቀደሙት አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።» የሚለውን የአሪት ሕግ በአዲሲቱ እያሻሻለ፣ መቆጣት፣ ወንድምን መሳደብ፣ በመንገድ ከወንድም ጋር አለመስማማት ሁሉ መግደል እንደ ሆኑ፤

ወይም የገደሉ የሚቀበሉትን ቅጣቶች የሚያመጡ እንደ ሆነ አስተምሯል። በመቀጠልም ሌሎች አምስት ትእዛዛትን ኑቀፈታቸውን በፍጹምነት አርቆላቸዋል።

ጌታችን በመጨረሻ ያዘዘው ግን ጠላቶቻችንን እንድንወድ ነበር። ይህም ወንጌል የፍቅር ሕግ መሆኗን የሚያስረዳ ነው። ስለዚህ «ፊተኛው ኑቀፈታ ባይኖረው ሌላ አዲስ ባላስፈለገም ነበር» ሲል አዲሱ ኪዳን ፍጹም ለመሆኑ ለውጥ የታየባቸው በሕግጋቱ፣ በመሥዋዕቱ፣ በክህነቱ እንደ ሆነ ማስተዋል ይገባል። ስለ እነዚህ ስለ እያንዳንዳቸው አንዳንድ ምዕራፍ ሆነው በዚህ መጽሐፍ የተቀመጡ ስለሆነ ያንን መመልከት ያስፈልጋል።

ቅዱስ ጳውሎስ የቀደመው ኪዳን ኑቀፈታ ባይኖረው ሌላ ኪዳን ባላስፈለገም ሲል፤ ስለ ቀደመው ኑቀፈታውን ገልጦ የአዲሱን ታላቅነት የገለጠው ስለ ምንድን ነው? ወይም ይህ ኪዳን ከዚያኛው በምን ይበልጣል?

ሀ/ ውሳጣዊ ነው፡– ውሳጣዊ ነው ሲባል በበደል የጐሰቆለውን ተፈጥሯችንን ወይም ባሕርያችንን ያደሰልን፣ ፍጹም ድኅነት ያገኘን በትን የነፍስን ቁስል ማከም የቻለ ለማለት ነው። «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ÷ ሁሉም አዲስ ሆኗል።» 2ኛቆሮ.5÷17 እንዲል።

ይህ ኪዳን ሁላችንንም በአዲስ ተፈጥሮ በጥንተ ተፈጥሮ እንደ ነበርን ያደረገን ልዩ ኪዳን ነው። ምክንያቱም ውሳጣዊ ሰውነታችንን ማደስ ተችሎታልና። «እነዚህን ሁሉ አስወግዱ፤ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ÷ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፍችሁታልና÷ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል ዕውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል።» /ቆላ.3÷9–10/ እንዲል ውሳጣውያን የነበሩ የዲያብሎስ ፍሬዎች የተነቀለበት

www.zeyeneta.com

ስለሆነ ከዚያኛው ይበልጣል። ጌታችንም በመዋዕለ ሥጋዌው የአድኅኖት ሥራውን ሲሠራ በመጀመሪያ ያደረገው ውሳጣውያን የሆኑትን ስስትን፣ ገንዘብ መውደድን፣ ትዕቢትን በጸም ድል ከነሣ በኋላ ነው ወደ ትምህርቱና ተአምራቱ የሄደው። ስለዚህ አዲሱ ኪዳን በዚህ /በውሳጣዊነቱ/ ከቀደመው እጅግ ይበልጣል።

ለ/ <u>ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር አዋሕዷል</u>፦ ይህ ኪዳን ውሳጣዊ ከመሆኑ የተነሣ ቅዱስ ጳውሎስ በተደጋጋሚ ሰውን ከእግዚአብሔር የሚለዩትን ኃጢአትንና ክፉ ምኞትን እንድንተው ይመክር ነበር። «ፊተኛ ኑሯችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥ በአእምሯችሁም መንፈስ ታደሱ፥ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።» ኤፌ.4÷22። ይኸም ሰው በጎሊናው ማዘዙን ነጻነቱን አግኝቶ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆኑን ያመለክታል። «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ ከሆኑ÷ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ <u>ከሞተ ሥጋ</u> ኅሊናችሁን ያነጻ ይሆን?» /ዕብ.9÷13–14/ እንዲል የኅሊናን ነጻነት አግኝተን ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት የፈጠርንበት እውነተኛ ኪዳን ነው።

እንደ ተጻፈውም ያኛው ሥጋን ብቻ ያነጻል አዲሱ ግን ውስጣችንን አንጽቶ ማኅደረ እግዚአብሔር ያደረገ ነው። «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም። ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።» 1ቆሮ.6÷19–20 እንዲል።

ሐ/ <u>በልብ ውስጥ ያደደቀ ነው</u>፦ «የበደላችሁትን በደል ሁሉ ከእናንተ ጣሉ አዲስ ልብና አዲስ መንፈስም ለእናንተ አድርጉ የእስራኤል ቤት ሆይ÷ ስለ ምን ትሞታላችሁ?» /ሕዝ.18÷31/ እንዲል እስራኤል ብዙ ጊዜ ቢነገራቸውም ቢማሩም ይሰሙታል፣ ለጊዜውም ይደነግጣሉ እንጂ በኋላ ወደ ባዕድ አምልኮ ይመለሳሉ። «ግልሙትናና የወይን ጠጅ ስካርም አእምሮን ያጠፋል። የግልሙትና መንፈስ ሕዝቤን አስቷቸዋልና÷ እነርሱም ከአምላካቸው ርቀው አመንዝረዋልና በትራቸውን ይጠይቃሉ÷ ዘንጋቸውም ይመልስላቸዋል። በተራሮችም ራስ ላይ ይሠዋሉ፣ ጥላውም መልካም ነውና ከኮምቦልና ከልብን ከአሆማም ዛፍ በታች በኮረብቶች ላይ ያጥናሉ፣ ስለዚህ ሴቶች ልጆቻችሁ ይገለሙታሉ÷ ሙሽሮቻችሁም ያመነዝራሉ።» ሆሴ.4÷11–13 ተብሎ እንደ ተጻፈ በየጊዜው እግዚአብሔርን በመርሳት ለአምልኮ ጣዖት የተጋለጡ ነበሩ። ይህም ያን ኪዳን አምልኮተ እግዚአብሔርን በማያስረሳ ኃይል በልቡናቸው ማተም ስላልቻለ ነበር።

አዲሱ ኪዳን ግን ኃይል ያለውና የሰውንም ውሳጣዊ ሰውነት ያነጻ በመሆኑ አምልኮት የሚፈጽሙትን ሰዎች ወደ ባዕድ አምልኮ አልሰደዳቸውም። በምግባር ሊደክሙ በፍልስፍናም ሊከሱ ይችላሉ፣ ጣዖታትን ቀርጸው የሚያመልኩ ግን አልሆኑም። ከነጻነት በኋላ ሕጉ እንዲሠርጽባቸው አድርጓል። በነቢዩ ኤርምያስም ያናገረው ይህንኑ ነው። «ሕጌን በልቡናቸው አኖረዋለሁ÷ በልባቸውም እጽፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑኛል። እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን÷ እያንዳንዱም ወንድሙን፦ እግዚአብሔርን ዕወቅ ብሎ አያስተምርም። ከታናሹም ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ያውቁኛልና÷ ይላል እግዚአብሔር።» ኤር.31÷34። ይህም የሐዲስ ኪዳን ሠሪ ጌታችን ከአሪት ሠሪ ከሙሴ እንደሚበልጥ ሁሉ ሕጉም

www.zeyeneta.com

ይበልጣል።

የአሪት ሕግ ርትዕ ሲሆን ወንጌል ግን ሕገ ትሩፋት ናት። ስለዚህም ፍጹም ሕግ በሚል የተሰጡት አሥርቱ ቃላት እንኪን በድንጋይ ጽላት ላይ ተጽፈው ነው የተሰጡት፡ ለሙሴም ከዚህ በላይ አይቻለውምና፡ ለጊዜ ግን ድንጋይን ሳይሆን ልብንም ለመጥረብና ለማስተካከል ይቻለዋል። ስለዚህ ሕጉ በሰው ልቡና አድሯል ሲባል እግዚአብሔር በሥጋ ፍጥረት አራት ባሕርያተ ሥጋና አምስተኛ ከምትሆን ባሕርየ ነፍስ ጋር እንደ አዋሐደ ያህል ሕጉ በሰዎች ልቡና አድሯል፡ አብሮ የተፈጠረ እስኪመስል ድረስ አድሮባቸው ይኖራል ለማለት ነው።

ሰዎች ሕጉን የሚያከብሩት እንደ እስራኤል ዘሥጋ በፍርሃትና በስጋት በመንቀጥቀጥም አይደለም። በዚያ ዘመን ሰዎች ወደ ደብረ ሲና ተራራ ሲቀርቡ ከተቀመጠው ድንበር ቢያልፉ እንደሚሞቱ ስለ ተነገራቸው እጅግ ይፈሩ ነበር። በሐዲስ ኪዳን ግን አካላዊ ቃልን አየነው፣ ዳሰስነው፣ አብረነው በላን ጠጣን፡ ሥጋውን በላነው ደሙንም ጠጣነው። ስለዚህ ተዋሕዶን የሚኖር በፍቅርና በመሉ ፈቃደኝነት የምናከብረው እንጂ በየጊዜው መቅሰፍት እያየን ያንን በመፍራት የምናከብረው አይደለንም። ይህም ኪዳኑ በእፍአ ሳይሆን በተፈጥሮ የተሰጠን ያህል ሆኖ በሰው ልቡና መጽደቁን የሚያስረግጥ ነው።

መ/ ፍጹም ይቅርታን ያስገኘ ነው፦ በአዲሱ ኪዳን የተገኘው ይቅርታ ፍጹም ነው። ከዚህ በኋላ ሌላ የኃጢአት ማስተሥረያ የሚያሻው አይደለም፡ በብሉይ ኪዳን ዘመን ብዙ መሥዋዕት የሚቀርብላቸው ኃጢአቶችም አሁን ያን ያህል ዋጋ የሚያስከፍሉ አይደሉም። የፈሰሰው የወልደ እግዚአብሔር ደም ሊያስተሠርየው የማይችለው ኃጢአት ዋጋ የማይመዝንለትም ነገር የለምና። ይህ ደም ለእኛ የተሰጠ ስጦታችን ነው፣ ያለ ዋጋም ተቀብለነዋልና

ይቅርታ ያስገኘ እንለዋለን። «ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።» ማቴ.26÷28 እንዲል።

8.2.3. እግዚአብሔር ለወዳጆቹ የገባው ኪዳን

እግዚአብሔር ወደ እርሱ ለሚመለሱትና በሕግ በአምልኮ ለሚፈልጉት ቅርብ ነው። ብዙ ሥራ ይሠራላቸዋል፡ ተጋድሏቸውንና ትጋታቸውን እየተመለከተም ደስ ስለሚሰኝ ቃል ኪዳን ይገባላቸዋል። ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ቃል ኪዳን ገብቷል። «ከመረጥኳቸው ጋር ቃል ኪዳንን አደረግሁ» መዝ.88÷3 እንዲል። በኋላም ቅዱሳን ሐዋርያትን፣ ጻድቃንና ሰማዕታትን የጠራቸው ለተጋድሉ ብቻ ሳይሆን ከተጋድሉም በኋላ የተሰፋ ቃል ሊሰጣቸው ኪዳንም ሊገባላቸው ነው። «የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው።» ዕብ.9÷15 እንዲል።

ሀ/ **ኪዳነ አዳም**፦ እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረውና በአርባ ቀኑ ወደ ገነት ካስገባው በኋላ ቃል ኪዳን ገብቶለታል። ይኸውም ዕፀ በለስን ባይበላ በሺህ በሺህ ዘመን እየታደሰ እንዲኖር ከበላ ግን እንደሚሞት አስጠነቀቀው። አዳምም እግዚአብሔር ያዘጋጀለትን በገነት መኖርንና ከዘመናት በኋላ የሚገኘውን ረቂቅ መታደስ ስለ ዘነጋ አትብላ የተባለውን ሕግና ትእዛዝ ተላልፎ በላ፣ ሞተም።

አዳምም እንደ ገና አዘነ አለቀሰ፣ ንስሐም ገባ፣ እግዚአብሔርም ንስሐውን ተቀበለ፣ ሊያድነውም ቃል ኪዳን ገባለት። «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ።» ገላ.4÷4/ የሚለው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ከመገለጡ በፊት ቃል ኪዳን እንደ ገባ

www.zeyeneta.com

የሚያረጋግጥልን ነው። ይህ ቃል ኪዳን ኖኅን ከምግባሩ በተጨማሪ እንደ ጠበቀው እንመለከታለን። እግዚአብሔር ምድርን በንፍር ውኃ በመታ ጊዜ ሰው የግድ መትረፍ ነበረበት፣ ካለበለዚያ ከሳይ የተመለከትነው ቃል ኪዳን ታበለ ያሰኛልና። ስለዚህ ኖኅ ከዳነባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ እግዚአብሔር ለአዳም የገባው ቃል ኪዳን ነው።

ይህ ሲባል ግን ኖኅ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅና ስለ ሰውም የሚያዝን መሆኑ ጽድቁም ያድነው ዘንድ የሚበቃው እንደ ነበረ ተመስክሮለታል። «የሰው ልጅ ሆይ፥ ምድር በግመፅ በእኔ ላይ ኃጢአት ስትሠራ፥ እኔም እጄን ስዘረጋባት የእንጀራዋንም በትር ስሰብር ራብን ስሰድድባት ሰውንና እንስሳውንም ከእርሷ ሳጠፋ፥ እነዚህ ሦስት ሰዎች፥ ኖኅና ዳንኤል ኢዮብም፥ ቢኖሩባት በጽድቃቸው የገዛ ነፍሳቸውን ብቻ ያድናሉ፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር።» /ሕዝ. 14፥12–14/ እንዲል እግዚአብሔር በእስራኤል ከፉ ኃጢአት ወቅት እንኳ ያልረሳው ጻድቅ ነው።

ለ/ <u>ኪዳኑ ኖኅ</u>፡– እግዚአብሔር እስራኤል ከምርኮ በኋላ እጅግ ከመበደላቸው የተነሣ ሲወቅሳቸው እግዚአብሔር ያስታወሰው የወዳጆቹን ጽድቅ ነው። እነርሱ ብቻ ይድናሉ ማለቱም ቃል ኪዳናቸውን ዐውቆ እንዲድን የሚለምን ሰው እስኪታጣ ድረስ መበደላቸውን ለመግለጽ ነው። ትልቁ ነገር ግን በዚያ በከፋ ኃጢአት ወቅት እንኳ እግዚአብሔር ስለ ጽድቃቸው ካስታወሳቸው ሰዎች አንዱ ኖኅ መሆኑ ነው።

ኖኅ በዘመኑ እግዚአብሔርን በሕግ በአምልኮ የሚፈልግ ሰው ስለ ነበረ እግዚአብሔር አልተለየውም፣ ምድርና ፍጥረታትም በንፍር ውኃ ሲቀጡ ለዘር የተመረጡትን ይዞ የቀረ ሰው እርሱ ነበር። ቅጣቱም ካለፈ በኋላ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቀረበ፣ እግዚአብሔርም ተቀበለለት፣ ቃል ኪዳንም ገባለት። «... ቃል ኪዳኔንም

ለእናንተ አቆማለሁ፥ ሥጋ ያለውም ሁሉ ዳግመኛ በጥፋት ውኃ አይጠፋም፥ ምድርንም ለማጥፋት ዳግመኛ የጥፋት ውኃ አይሆንም። እግዚአብሔርም አለ፡– በእኔና በእናንተ መካከል፥ ከእናንተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል፥ ለዘላለም የማደርገው የቃል ኪዳን ምልክት ይህ ነው፥ ቀስቴን በደመና አድርጌአለሁ፥ የቃል ኪዳኑም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል። በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቲቱ በደመናው ትታያለች፥ በእኔና በእናንተ መካከል፥ ሕያው ነፍስ ባለውም ሥጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ። ...ቀስቲቱ በደመናው ትታያለች።... በእኔና በምድር ላይ በሚኖር ሥጋ ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ያለውን የዘላለም ቃል ኪዳን ለማሰብ አያታለሁ።» /ዘፍ.9፥8–16/ እንዲል እስካሁን ድረስ እግዚአብሔር ለወዳጁ ለኖኅ የገባውን ኪዳን እያሰበ ጠብቆናል። በዘፍ.8፥22 ላይ ስንመለከትም ስለ ኖኅ «በምድርም ዘመን ሁሉ መዝራትና ማጨድ፥ ብርድና ሙቀት፥ በጋና ክረምት፥ ቀንና ሌሊት አያቋርጡም።» ሲል ቃል ኪዳን ገብቶለታል።

ሐ/ <u>ኪዳኑ አብርሃም</u>፡– እግዚአብሔር ከኖኅ ጋር እንዳደረገ ከአብርሃምም ጋር ቃል ኪዳን አድርጓል። አስቀድሞ «ታላቅ ሕዝብ አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፥ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።» ዘፍ.12፥2 ሲል የበረከት ቃል ኪዳን ገባለት በኋላም የኪዳኑን ምልክት ሰጠው። «እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፡– አንተ ደግሞ ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ፥ አንተ ከአንተም በኋላ ዘርህ በትውልዳቸው። በእኔና በአንተ መካከል፥ ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው

www.zeyeneta.com

ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ::» /ዘፍ.17÷9–10/ የሚለው ለበረከት የመለየቱ አብርሃም ኪዳኑን የመጠበቁ ምልክት ነው::

ከዚህም በኋላ እግዚአብሔር ልጁን እንዲያቀርብ አዘዘት በፈጸመ ጊዜ ኪዳኑን በመሐላ አጸናለት:: «የእግዚአብሔር መልአክም አብርሃምን ከሰማይ ሁለተኛ ጊዜ ጠራው÷ እንዲህም አለው:– እግዚአብሔር:– በራሴ ማልሁ ይላል፤ ይህን ነገር አድርገሃልና÷ አንድ ልጅህንም አልከለከልህምና በእውነት በረከትን እባርክሃለሁ÷ ዘርህንም እንደ ሰማይ ከዋክብትና በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ አበዛዋለሁ፤... ዘርህም የጠላቶችን ደጅ ይወርሳል፤ የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ÷ ቃሌን ሰምተሃልና::» /ዘፍ.22÷16–18/ ሲል ቃል ኪዳን ተጋብቷል:: ለይስሐቅ /ዘፍ.26÷1–5/ እንዲሁም ከያዕቆብ ጋር ቃሉን ሳይለወጥ የአባቶቹን ቃል ኪዳን ገብቶለታል:: ዘፍ.28÷10–15::

እግዚአብሔርም ለአነርሱ የገባውን ቃል ኪዳን አስቦ አስራ ኤልን ከግብፅ አውጥቷቸዋል፤ ከመከራቸውም ሁሉ አድኗቸዋል:: «እግዚአብሔርም የልቅሶቸውን ድምፅ ሰማ÷ እግዚአብሔርም ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን አሰበ::» ዘጸ.2÷24 እንዲል::

መ/ ኪዳነ ዳዊት:– እግዚአብሔር ከቀደሙት አበው ጋር እንዳደረገው በሥራው ደስ ካሰኘው ከቅዱስ ዳዊትም ጋር ቃል ኪዳን አድርጓል:: ለእግዚአብሔር ማደሪያ ቤተ መቅደስ ለመሥራት ያሰበ ሰው ነውና:: አስቦም አልቀረ ሱባኤ ገብቶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠይቋል፤ እግዚአብሔርም መልሶለታል:: በናታን በኩል

ቶችህንም ሁሉ ከፊትህ አጠፋሁ፤ በምድርም ላይ እንዳሉ እ ታላላቆቹ ስም ታላቅ ስም አደርግልሃለሁ:: ለሕዝቤም ለእስራ ሥፍራ እደርግለታለሁ÷ እተክለውማለሁ፤ በሥፍራውም ይቀመጣ ከዚያም በኋላ አይናወጥም፤ እንደ ቀድሞው ዘመንና በሕዝቤ በእ ኤል ላይ ፈራጆች እንዳስነሣሁበት ጊዜ ግፈኞች ተመለ አያስጨንቁትም ከጠላቶችህም አሳርፍሃለሁ:: እግዚአብሔ ደግሞ:– ቤት እሠራልሃለሁ ብሎ ይነግርሃል:: ዕድሜህም በተፈጸ ጊዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ÷ ከወገብህ የሚወጣውን ዘር ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ÷ መንግሥቱንም አጸናለሁ:: እርሱ ለስ ቤት ይሠራል፤ የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ:: እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤ ከፉ ነገርም ቢያደር ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች መቀመጫ እገሥጸዋለ ከፊቴም ከጣልሁት ከሳኦል እንዳራቅሁ ምሕረቴን ከእርሱ አላርቅ፱ ቤትህና መንግሥትህም በፊቴ ለዘላለም ይጠነክራል÷ ዙፋንህ ለዘላለም ይጸናል::» /2ኛሳሙ.7÷8–16/ የሚል ጽኑ ቃል ኪ ገብቶለታል::

«ከመርጥሁት ጋር ቃል ኪዳንን አደረግሁ÷ ለባሪያዬ ለዳዊት ማልሁ:– ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ÷ ዙፋንህንም ለል ልጅ እመሠርታለሁ::» መዝ.88÷3–4 ሲልም አጽንቶለታል::

እግዚአብሔርም ሰሎሞን በተቆጣ ጊዜ ለዳዊት የገባለት ቃል ኪዳን አስቦ መንግሥቱን በእርሱ ዘመን ሳይከፍልበት ቀረ «እግዚአብሔርም ሰሎሞንን አለው:– ይህን ሠርተሃልና÷ ያዘዝሁህን

www.zeyeneta.com

አንድ ነገድ አሰጣለሁ እንጂ መንግሥቱን ሁሉ አልቀድድም::» 1ኛነገ.11+11-13 እንዲል::

ሠ/ ኪዳነ ምሕረት:- «እነዚህም ሁሉ በእምነታቸው ተመሰከረላቸው ሳሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም+ ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና::» /ዕብ.11+39-40/ ተብሎ እንደ ተጻፈ ቃል ኪዳን የተገባላቸው ሁሉ ጊዜያዊውን ተጠፋ አገኙ እንጂ ፍጹሙን አላገኙትም::

ለናኅ በተገባው ቃል ኪዳን መሠረት ምድር በንፍር ውኃ ዳግመኛ አልጠፋችም፣ ይህ ከጊዜው ጊዜ ጀምሮ የምንመለከተው ነው:: አብርሃም ዘሮቹ በዝተዋል ከነዓንንም ወርሰዋል፣ ይህም ጊዜያዊ ነበር:: ዐይነተኛዋን ርስት ግን ሊያገኙ አልቻሉም:: የዳዊትም ቢሆን መንግሥቱ ለጊዜው ፈጽሞ ባይጠፋም ፍጹም ግዛት ግን አላገኘም:: ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ለእነርሱ የተገባው ቃል ኪዳን ፍጹም ሆኖ የሚሰጥበት ሌላ የቃል ኪዳን ፍጻሜ እንደሚያስፈልግ ነው:: ይህ የቃል ኪዳን ፍጻሜ ነው «ኪዳነ ምሕረት» እየተባለ የሚጠራው:: «እስመ ትቤ ለዓለም ኢሐንጽ ምሕረተ፣ በሰማይ ጸንአ ጽድቅከ:: ምሕረትን ለዘላለም አደርጋለሁ ብለሃልና ቸርነትህ እንደ ሰማይ ጸንቶ ይኖራል::» መዝ.88+2-3 ሲል አስቀድሞ አናግሯልና::

ይህም የምሕረት ኪዳን /የቃል ኪዳኑ ፍጻሜ/ በእመቤታችን በኩል ተገለጠ:: አስቀድመው ነብያቱ ሁሉ ለአበው የተሰጠውን ፍጹም ተስፋ መገለጫ ይመረምሩት ነበረ:: «ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነብያት ስለዚህ መጻን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፣ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ+ ስለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አስቀድሞ እየመሰከረ+ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር::

ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን የሰበኩላችሁ ሰዎች አሁን ባወሩላችሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፣ ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ::» 1ኛጴጥ.1+10-12 እንዲል መላእክቱ ሁሉ እጅግ የናፈቁት ጉዳይ ነበረ:: ነብያትም ስለ ሁኔታው ሲመረምሩ የተመለከቱትን ጻፉ::

ነቢዩ ኢሳይያስ:- «ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፣ እነሆ+ ድንግል ትፀንሳለች+ ወንድ ልጅም ትወልዳለች+ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች::» ኢሳ.7+14::

ነቢዩ ሕዝቅኤል:- «ወደ ምሥራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ፣ ተዘግቶም ነበር:: እግዚአብሔርም:- ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል::» ሕዝ.44+1-2::

ቅዱስ ዳዊት:- «እነሆ+ በኤፍራታ ሰማነው+ በዱር ውስጥም አገኘነው:: ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን፣ እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን::» መዝ.131+6::

«እግዚአብሔር ጽዮንን መርጧታልና+ ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዷታልና+ እንዲህ ብሎ:- ይህች ዘለላለም ማረፊያዬ ናት፣ መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ:: አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ+ ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ:: ካህናቶቿንም ደኅንነትን አለብሳቸዋለሁ+ ቅዱሳንዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል::» መዝ.131+13-17::

ይህን ነብያቱ በትንቢት እየመረመሩት መንፈስ ቅዱስም እየገለጠላቸው እየጸፉት ቆዩ፣ መላእክቱም ሊያዩት ይመኙ ነበር ተብሎ እንደ ተጻፈ እጅግ ሲናፍቁት ቆዩ፣ የማያዩትን አምላክ ለማየት የሚችሉት በዚህ መንገድ ብቻ ስለ ነበረ ነው:: ለዚህም ነው

www.zeyeneta.com

ቅዱስ ጳውሎስ 1ኛጢሞ.3÷16 ላይ «ለግዚአብሔርን የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፡ በሥጋ የተገለጠ÷ በመንፈስ የጸደቀ÷ ለመላእክት የታየ÷ ለአሕዛብ የተሰበከ÷ በዓለም የታመነ÷ በክብር ያረገ::» ሲል ለመላእክት የመታየቱ ምሥጢር በዚሁ በምሥጢረ ሥጋዌ በኩል መሆኑን የገለጠልን::

አምላካችን እግዚአብሔር ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ በመገለጡ የዲያብሎስ የተንኮል ወጥመድ ተሰበረ በት፡ ሰው ከሞት ከኩነኔ አመለጠ፡ ሥጋውን ብልተን ደሙንም ጠጥ ተን ከእርሱ ጋር ተዋሕደን የምንኖር ሆነናል:: ስለዚህ ፍጹሙን ምሕ ረት በዚህ በኩል አግኝተናልና ኪዳነ ምሕረት ተባለ::

ኪዳነ ምሕረት የቅድስት ድንግል ማርያም መጠሪያ ነው:: ምክንያቱም:-

1. የፍጹሙ ኪዳን ምልክት እርሷ ናትና /ኢሳ.7÷14/::
2. ኪዳኑን በደሙ ያጸናልን ልጇ ነውና፡ ሥጋውንና ደሙንም ከእርሷ የነሣው ነውና::
3. ለእርሷም ፍጹም ምሕረትን የሚያስገኝ ቃል ኪዳን ገብቶላታልና::

ሔዋን ምክረ ከይሲን ሰምታ ሞትና ኩነኔን የሚያመጣ መብልን ብትበላም ቅድስት ድንግል ማርያም ብሥራትንና ምስጋናን ከሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል ተቀብላ መብልዐ ሕይወትን ወልዳ የሕይወት ምግብን አብልታናለችና የደኅንነታችን ምክንያት የሕ ይወታችንም ትምክህት እርሷ ስለሆነች ፍጹም ቃል ኪዳንም ተቀብላ ለችና ኪዳነ ምሕረት እንላታለን::

ከእመቤታችንም በኋላ ላሉ ጻድቃንና ሰማዕታት ተጋድ ሏቸውን በፈጸሙ ጊዜ የሞት አስፈሪነቱ ቀርቶ ሥልጣኑ ስለተሻረበት፣ በጽሉም ገጹ ነፍስ ከሥጋ መለየቱ ስለ ቀረ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰማዕቱ ሊቀ ዲያቆን አስጢፋኖስ

እንደ ተገለጠለት ተገልጦ ያነጋግራቸዋል፡ ፍጹም ቃል ኪዳንም ይገባላቸዋል:: ይህም ቃል ኪዳን የምሕረትና የይቅርታ ወደ ገነትም የሚመልስ ቃል ኪዳን ነው::

8.3. እግዚአብሔር፣ ሰውና ቃል ኪዳን

እግዚአብሔርና ሰው የማይቋረጥ ግንኙነት ያላቸው በቃል ኪዳን ነው:: እግዚአብሔር ለሰው ሁልጊዜ ቃል ኪዳን ይገባል፡ ኪዳ ኑንም ይፈጽማል፡ ሰው ግን ቃል ኪዳኑን አይጠብቅም:: አሁን አሁንስ ይባስ ብሎ «ቃል ኪዳን የለም፡ አስፈላጊም አይደለም::» የሚሉ ሰዎችንም እየተመለከትን ነው::

እግዚአብሔር ዓለሙን እንኳን የሚያስተዳድረው በኪዳን ነው:: ለምሳሌ ያህል መግቡቱን ብንመለከት፡ እግዚአብሔር የፈጠ ረውን ፍጥረት ሁሉ ይመግባል ያለ አርሱም መጋቢነት ዓለም ጸንታ መኖር አይቻላትም:: ይሁን እንጂ በዚህ ዓመት ያለው ሰው፣ እንስሳ፣ አራዊት፣ የመሬት ይዘት፣ ሌሎች ፍጥረታት በሚል ዝርዝር ለዓመት ለሁለት ዓመት... እያለ ዕቅድ እያወጣ፣ እየወጣ እየወረደ እንደማይፈጽመው የታወቀ ነው:: አንድ ጊዜ በተናገረው ቃል ሁሉም በየጊዜው ሲፈጸም እንዲኖር ማድረግ ስለማይሳነው ነው::

ሰው አክሰጂን ተጠቅሞ ካርቦን ዳይ አክሳይድ ሲሰጥ አትክልት ደግሞ ካርቦን ዳይ አክሳይድ ተጠቅመው አክሰጂን መስጠ ታቸው በሥነ ፍጥረት ሕግ የተደረገ ነው እንጂ ሰውና አትክልት ተዋውለው እኛ ይህን እናድርግ እናንተም ለእኛ ይህን አድርጉ በሚል የተደረገ አይደለም:: ይህ እግዚአብሔር እንዲሆን ባዘጋጀው ኪዳን የመኖራችን ምልክት ነው:: እንዲህ ለሥነ ፍጥረት መግቡቱን በኪዳን /አንድ ጊዜ በሠራው ሥርዓት/ እንዳጸናው ሁሉ ከዚህም በኋላ ለሰው የተለያዩ ኪዳናትን ገብቷል:: አዳም የመጀመሪያውን ባለመብላት ሊሰጠው የተገባለትን ተስፋ ስላልጠበቀ፡ አጣ ወደ

www.zeyeneta.com

ምድርም ወጣ።

እግዚአብሔር ግን ሰው ቃል ኪዳኑን ባለመጠበቁ የሚታክ ተው አምላክ አይደለም። በየጊዜው ከአባቶቻችን ጋር ቃል ኪዳን ገብቷል፣ ይልቁንም ከላይ እንደ ተመለከትነው ለእቢው ለእያንዳ ንዳቸው ከገባው ቃል ኪዳን በተጨማሪ በሙሴ አማካኝነት ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ኪዳንን ሰጠ። ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበት መሥዋዕት አቅርበው አፍአዊና ጊዜያዊ ሥርየተ ኃጢአት የሚያገ ኙበት፣ ሱባኤ ገብተው የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚረዱበት ኪዳን ሰጣቸው – ብሉይ ኪዳንን። በዚህ ኪዳንም ሳይወሰን ፍጹሙን ኪዳን ለመመሥረት ራሱ መጣ። ኪዳኑንም መሠረተ፣ እስከ ዕለተ ምጽአ ትም ድረስ አምነው የሚጠመቁና ሥጋውን ደሙን የሚቀበሉ እንዲ ድኑ እርሱ እንድ ጊዜ ኪዳኑን መሠረተ፥ አንድ ጊዜም ስለ ሰው ሞተ አንድ ጊዜም መሥዋዕት አቀረበ፣ በዚህ አንድ ጊዜ በተፈጸመ አገልግሎትም ሁልጊዜ የምንጠቀም ሆንን።

በኪዳኑ አዳም፣ በኪዳኑ ኖኅ፣ በኪዳኑ አብርሃም ላይ ብሉይ ኪዳንን እንደ ሰጠ በዚያውም ላይ ለነዳዊት ተጨማሪ ኪዳን እንደ ገባ፣ በፍጹሙ ኪዳን ላይ ታንፀው በተጋድሏቸው ደስ ላሰኙት ለጻድ ቃን ለሰማዕታትም የምሕረት ቃል ኪዳንን ገባላቸው። ስለ እነርሱ ተጋድሎና መከራ የሌሉቹ ድካም እንዲሸፈን ፈቀደ። እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኳችሁ። ሌሎች ደከሙ እናን ተም በድካማቸው ገባችሁ። እንዳለ ጌታ ዮሐ.4+38 ስለ ሙሴ እው ነተኛነት የእስራኤልን በደል ይቅር እንዳለ ስለ እነርሱም /ሐዋ ርያት፣ ጻድቃንና ሰማዕታት/ የእኛን በደል ይቅር ሊል ቃል ገባ።

ሰው ግን ቃል ኪዳን ይቀበላል እንጂ አይጠብቅም፣ ስለዚህም ተጠቃሚ አይሆንም። ለአብነትም እግዚአብሔር ለዳዊት ቃል ኪዳን ገባለት፣ ዳዊትም ልልኛ ለሰሎሞን ነገረ፣ ሰሎሞን ግን እንደ ኪዳኑ ቃል መጓዝ ተሳነው፣ አባቱ የነገረውን ነገር ብቻ ሳይሆን ሁለት ጊዜ

ተገልጦ ያነጋገረውን የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ረሳ። ስለዚህ እግዚአብሔር ለዳዊት የገባውን ቃል ኪዳን አስቦ በዘመኑ ይቅር ቢያደርግም በኋላ በሮብዓም ጊዜ ግን መንግሥቱ ተከፈለ። ያም ሆኖ ለሮብዓም ምንም የሚገባው አልነበረም። እግዚአብሔር ግን አሁንም ስለ ዳዊት ሲል በሁለቱ ነገድና በዋናዋ በኢየሩሳሌም ላይ እንዲ ነግሥ ፈተደለት። ይህ ስለ ቃል ኪዳኑ የተደረገ ነው።

ከዚያም በፊት የነበሩ አስራኤል ዘሥጋ ከዚያም በኋላ ያሉ እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑት ቃል ኪዳኑን እንደ ውሸት በመቁጠር በማናናትና በመተው ነበር። የነብያትም መጻሕፍት በሙሉ የሚያ ስረዱት ይህንኑ ነው፣ እግዚአብሔር እስራኤልን የሚወቅሰው እስከ መቼ ኪዳኔን ትንቃላችሁ? እስከ መቼስ ትተጪታላችሁ፣ አሁንስ ይህን አድርግባችኋለሁ ሲል እንደ ተናገረ በየመጻሕፍቱ የምንመለ ከተው ሐቅ ነው።

ስለዚህ ዓለም ጸንታ ያለችው ፍጥረት በመግቦት የሚኖረው በቃል ኪዳን ነው። ያለ ቃል ኪዳን መኖር የሚቻለው ፍጥረት የለም። ኖኅን የማያውቅ ብዙ ሰው ሊኖር ይችላል፣ እግዚአብሔር ግን ለኖኅ የገባውን ቃል ኪዳን፣ የምድርን የመዘራትና የዘሩትን የማጨድ፣ የብርድና የሙቀት፣ የበጋና የክረምት፣ የቀንና የሌሊት መፈራረቅ አያስታጉልም። አንድ ጊዜ እግዚአብሔር የገባውን ቃል ኪዳን ሁልጊዜም ይፈጽማልና። ዘፍ.8+22፣ 9+8–16።

ሰው ግን ሁልጊዜ ቃል ኪዳንን ይንቃል። «እነርሱ ግን እንደ አዳም ቃል ኪዳንን ተላልፈዋል በዚያም ላይ ወንጅለውኛል።» ሆሴ.6+7 እንዲል። እንግዲህ እግዚአብሔር እንዲጠብቀን እኛም ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ እንታመንለት። «የሰው ስንኳ ቢሆን እርግጠ ኛውን ኪዳን ማንም አይንትም ወይም አይጨምርበትም» ተብሎ ተጽፎልናልና። ገላ.3+15።

www.zeyeneta.com

8.4. ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ኪዳን የጻፈበት ምክንያት፦

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ የሚያስተላልፈው ዐቢይ ምሥጢር የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት /ታላቅነት/ ነው። ያረ ጻበት ዘዴ ግን ንጽጽራዊ ነው። ከነብያት፣ ከመላእክት ይበልጣል አለ። ከዚህ በመቀጠልም ከሌዋውያን ሊቃነ ካህናት ብቻ ሳይሆን የእነርሱ አባት ለሚሆን ለአብርሃም ከገበረለት ከመልከ ጼዴቅም ይበልጣል አለ። እነ ሙሴ እነ ኢያሱ ለእስራኤል ካስገኙት ዕረፍት በክርስቶስ የሚገኘው ዕረፍት ይበልጣል፣ ከክነዓንም መንግሥተ ሰማ ያት ትበልጣለች፣ ሙሴ መሪዋ ፈታውራሪዋ ከሆነችው ሕገ አሪት ጌታ የሠራት ሕገ ወንጌል ትበልጣለች፣ እያለ በማነጻጸር ካመጣ በኋላ አሁንም በዚህ ምዕራፍ እንደ ተመለከትነው. እነ ሙሴ ከተቀበሉት ኪዳን /ብሉይ/ ጌታ የመሠረታት ሐዲሲቱ ኪዳን ትበልጣለች፣ ለአበው የተሰጠው ተስፋ የተፈጸመው በእርሱ ኪዳን ነው፣ በዚህም በአዲሲቱ ኪዳን ለወዳጆቹ የሚገባው ቃል ኪዳን ለአበው እንደገባው የተስፋ አይደለም፣ በኪዳኑ የሚያምኑና የቃል ኪዳ ኑን ትእዛዝ የሚጠብቁ ሁሉ የሚከብሩበት የሚጠቀሙበት ነው እንጂ፣ ለማለት አምጥቶታል።

በአጭሩ ስለ ምን ኪዳንን ማንሣትና ማነጻጸር አስፈለገው ስንል የዕብራውያንን የብሉይ ኪዳን እምነትና አስተሳሰብ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1. <u>ስለ ዕብራውያን የተሳሳተ አስተሳሰብ፦</u> ዕብራውያን «መሲሕ» ይመጣል» ተብሎ ለአበው ስለተገባው ቃል ኪዳን የነበራ ቸው አስተሳሰብ የተሳሳተ ነበር። በተለይም ጌታችን በሥጋዊ በተገ ለጠበት ዘመን እነርሱ በሮማውያን ቅኝ ግዛት ሥር በመሆና ቸው የጌታችንን መምጣት የሚጠባበቁት በሥጋዊ ገዥ ልግድ ነገሥ ከሮ ማውያን ቅኝ ግዛት እንዲያላቅቃቸው ነው። ይህ ሥጋዊ አስተ ሳሰብ መሲሕ ክርስቶስ ከዲያብሎስ አገዛዝ፣ ከሰይጣን ቁራኝነት፣ ከሞትና

ከኩነኔ ሊያድነን መጣ የሚለውን እንዳይቀበሉ አድርጓቸዋል። ስለ መጀመሪያው ኪዳን የነበራቸው የተሳሳተ አስተሳሰብ በክርስቶስ እንዳያምኑ ካደረጋቸው፣ ያ ኪዳን ያልተፈጸመ መስሏቸው ሲጠባበቁ ከመኖር ተመልሰው የሚበልጥ አዲስ ኪዳን መቆሙን ወውቀው በእርሱ አምነው እንዲጠቀሙ ነው።

2. <u>የአዲሱን ኪዳን ፍጹምነት እንዲያውቁ፦</u> ዕብራውያን የተነገረው ተስፋ በክርስቶስ መፈጸሙን እንኳ ቢያምኑ በአሪት የበደለ ሰው ኃጢአቱ በለምጽ ይታወቃል፣ በእንስሳት መሥዋዕትም ኃጢአቱ ይሠረይለታል። እነዚህ ሰዎች ግን በለምጽ አለመሞታቸውን አይተው የሠሩት ኃጢአት ጽድቅ፣ አለማመናቸውም እምነት መስ ላቸው በዚያው አለማመን እንዳይጸኑ፣ ዳግመኛም ለኃጢአት ሥር የት በግና ፍየል አለማቅረባቸው ኪዳኑ የማያድን መስሎ እንዳይታ ያቸው ነው።

ምክንያቱም አዲስ ኪዳን እንደ ብሉይ ኪዳን ዕለት ዕለት የእንስሳትን ደም የምትሻ ጉደሉ አይደለችም። ጉደሉም ያሰኛት የእንስሳው ደም ከመታረዱ በፊት ሰውዬው ለሠራው ኃጢአት የሚቀርብ እንጂ ከሚመጣው የሚጠብቅ አልነበረም፣ በዚያውም ላይ የማያስተሠርየው ኃጢአት እንዳለ የታወቀ ነው - ጥንተ አብሶ። የክርስቶስ ደም ግን አንድ ጊዜ በቀረበው ሁልጊዜ የምንድን ሆነና ልና ይህን ወውቀው እንዲመለሱ ነው።

3. <u>የምሕረት ኪዳን መመሥረቱን እንዲያውቁ፦</u> ከዚያ በፊት የነበረውን ኪዳን የምሕረት ኪዳን ነበረ ለማለት አያስደ ፍርም። ስለ እያንዳንዱ ኃጢአት ማስተሥረያ የሚሆን መሥዋዕትን ይጠይቅ ነበር። ማቅረብ ያልቻለም ሥርየተ ኃጢአት አግኝቷል የሚባልበት መንገድ አልነበረም። አዲሱ ኪዳን ግን ስለ ኃጢአቱ ንስሐ ከመግባትና መንፈሳዊ ቅጣት /ቀኖና/ ከመቀበል በቀር ስለ

www.zeyeneta.com

ኃጢአት የሚከፈል ነገር ኖለም። በእውነትና በሥርዓት ተጸጽተው ለመጡ ሁሉ አንድ ጊዜ የቀረበውን ሥጋና ደምን በመቀበል ሥር የት ተገኘ። ይህም እግዚአብሔር አስቀድሞ «ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትን አይደለም።» ሲል ያናገረውን የፈጸመበት የምሕረትና የይቅርታ ኪዳን መሆኑን የሚያስረግጥልን ነው። «ከመሥዋዕት ይልቅ ምሕረትን፣ ከሚቃጠልም መሥዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወድዳለሁና።» ሆሴ.6÷6 እንዲል።

ጌታችንም በመዋዕለ ሥጋዌው ያስተማረው ይህንኑ ነው። ፈሪሳውያን ሐዋርያትን እሸት በመመገባቸው ሰንበትን ሽረዋል ሲሉ በከሰሱበት ወቅት፣ ዳዊት በተራበ ጊዜ ያልተፈቀደለትን እንዳደረገ አላነበባችሁምን? ካህናተ ኦሪትስ በሰንበት መሥዋዕት እንዲሠዉ ኃጢአትም እንዳይሆንባቸው አላስተዋላችሁምን? ነገር ግን ከመቅደስ የሚበልጥ ከዚህ አለ። ምሕረትን እወድዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደ ሆነ ብታውቁ ኃጢአት የሌለባቸውን ባልኩነናችሁ ነበር? ማቴ.12÷1–8 ሲል አስተምሯል።

አሁንም በዕብራውያን የነበረው በእኛ እንዳለ እናስታውሳለን። እግዚአብሔር ምሕረትን ይቅርታን ከመውደዱ የተነሣ ይቅርታ የሚ ወዱትን ሁሉ ይቅር አለ። ዘማዊቷ ማርያምን በአንዲት ብልቃጥ ሽቱ ይቅር አልልሽም አላለም፣ በቀኙ የተሰቀለውንም ሽፍታ በጨነ ቀህ ጊዜ አንዲት ቃል በመናገርህ ያን ሁሉ ኃጢአትህን ይቅር አል ልህም አላለውም። የመጣው ለምሕረት ነው÷ ኪዳኑም የምሕረት ነው። ለጻድቃን ለሰማዕታትም የገባው ቃል ኪዳን የምሕረት እንጂ የመሥዋዕት አይደለም። ሰዎች ግን አዲስ ኪዳን የሚለው ስላልገባን የመከሰሻ ምክንያት የሌለባቸውን ለምሕረት ኪዳን የተቀበሉ ሐዋር ያትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን ስንከሳቸው እንሰማለን። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ያነሣበት ምሥጢር ኪዳኑ ኪዳነ ምሕረት እንጂ ኪዳነ መሥዋዕት አይደለም፣ የሚበልጥ ኪዳን ተሰጥቶናልና ብንመለስ

ዛናምን መቼም እንድናለን ለማለት አመጣው። «ሰንወቅ ዕናውቅም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል፤ ጌታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደ መጪረሻ ዝናብ ይመ ጣል።» ሆሴ.6÷3።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ ዘጠኝ

መቅደስ የእግዚአብሔር መገለጫ

በዚህ ምዕራፍ መነሻነት ስለ መቅደስ ሁለንተናዊ ገጽታና በም.4÷16 ላይ የጸጋው ዙፋን ስለ ተባለች ቤተ ክርስቲያንና «በእጅ ያልተሠራች» ስለ ተባለችው ቅድስተ ቅዱሳን እንመለከታለን::

9.1. ትርጉም:- መቅደስ የሚለው ስም ቀደሰ-አመለገነ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጓሜውም ማመስገኛ፣ መሥዋዕትና ኂሩት ማቅረቢያ፣ የአምልኮት ቤት፣ ሦስት ክፍል ያለው ቤት ማለት ነው:: ለብሉይ ቤተ መቅደስ ኡላም፣ ሀይከልና ጻቤር የሚባሉ ሦስት ክፍሎች ነበሩት:: ለሐዲሱ ደግሞ ቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስትና መቅደስ የሚባሉ ሦስት ክፍሎች አሉት:: እነዚህ ሦስት ክፍሎች ከፍ ብለው አራት ዝቅ ብለው ሁለት ያልሆኑበት በሰ ማያዊው ቤተ መቅደስ እምሳል በጥንቃቄ የተሠሩ ስለሆኑ ነው:: «በተራራው እንደ ተገለጸልህ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ ብሎት ነበርና::» ዕብ.8÷5 እንዲል::

ከላይ የተመለከትነው የቤተ መቅደስን ዘይቤያዊ ትርጉም ነው:: ምሥጢራዊ ትርጉሙ ደግሞ «የሰማይ ደጅ»÷ የእግዚአብሔር መገለጫ ማለት ነው::

የሰማይ ደጅ:- «ያዕቆብም ከእንቅልፉ ተነሥቶ:- በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ሥፍራ ነው፤ እኔ አላወቅሁም ነበር አለ:: ፈራ÷ እንዲህም አለ:- ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራ፤ ይህ ሥፍራ የእግዚ አብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም ይህም የሰማይ ደጅ ነው::» ዘፍ.28÷16-17 ተብሎ እንደ ተጻፈ:: እግዚአብሔር በቦታ የሚወሰን አምላክ አይደለም:: የሰማይም ደጅ በምድር ላይ ያለ አንድ ቦታ የሚሆን ሆኖ አይደለም:: በልዕልናው /በሰማይ/ ጸንቶ የሚኖር እግዚ

አብሔር ለምድራውያን የሚገለጥበት ቦታ ወይም ሰማያውያንና ምድራውያን የሚገናኙበት ቦታ ነው ለማለት ነው::

ምክንያቱም ከላይ እግዚአብሔር ተቀምጦ /በክብር ተገልጦ/፣ ከታች ሰው፣ በመካከል መላእክት መውጣት መውረዳቸው ሰውና እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆኑ ሰማይና ምድር የሚገናኙበትም የጋራ ዋልታ፣ ዛቢያ ወይም ዓምድ ቤተ መቅደስ ነው:: አንዳንድ ሊቃው ንትም ይልቁንም የሦስት መካናት መገናኛ ይሉታል:: ከምድር በታች /በወጸደ ሥጋ የተለዩ/ ያሉትም፣ በምድር ያሉትም በሰማይ ያሉትም መገናኛቸው ቤተ መቅደስ ነው ይላሉ:: በደብረ ታቦር የሙሴ /ከወጸደ ሥጋ የተለዩ/፣ የኤልያስ/ ከብሔረ ሕያዋን/፣ የሦስቱ ሐዋርያት /ከዚህች ምድር/ መገናኘታቸው ይህንኑ ምሥጢር የሚያስረግጥ ሆኖ እናገኘዋለን:: የእነዚህ መገናኛ ዓምድ ሆኗልና::

ለሰማይም ደጇ ስንል የተዘጋ በር ሲከፍት ማጀት የጐረሰው ጓዳ የመሰለው እንዲታይ ቤተ መቅደስም የማይታየው እግዚአብሔር ይገለጥባታል፣ ምሥጢረ ሰማይ ይነገርባታልና የሰማይ ደጅ ተብላ ለች:: «ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ እነሆም÷ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም÷ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ:- በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ::» /ማቴ. 3÷16-17/ የሚ ለውም የሰማይ መከፈት ማለት የእግዚአብሔር መገለጥ ነው የሚለ ውን ያስረግጥልናል:: ነቢዩ ኢሳይያስም እግዚአብሔር ተገለጠልኝ ብሎ በተናገረበት አንቀጽ «የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር::» ኢሳ.6÷1 ማለቱ መቅደስ የእግዚአብሔር መገለጫ ልዩ ቦታ መሆኑን ያረጋግጥልናል::

ከዚህ አንጻር በምድር ላይ እንደ ቤተ መቅደስ የሚያስፈራ ቦታ የለም:: የሚያስፈራውም ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር መገለጫ

www.zeyeneta.com

ስለሆነ ነው። ያዕቆብ «ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራ! ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው።» ዘፍ.18÷16 እንዳለ። በሌላም ቦታ በጓላ ዘመን መቅደስን የእግዚአብሔር ቤት እያሉ ጠርተውታልና። 2ኛዜና.36÷18 የእግዚአብሔር ቤት መባሉ በዚህ ቦታ የሚሄዱት እግዚአብሔርን ፈልገው ብቻ ስለሆነ ነው። «እግዚአብሔርንም የፈለገ ሁሉ ከሠፈር ውጭ ወዳለው መደ መገናኛው ድንኳን ይወጣ ነበር።» ዘጸ.33÷7 እንዲል።

ስለዚህ ቤተ መቅደስ የእግዚአብሔር መገለጫ፣ የሰማይና የምድር የጋራ ዛቢያ ነው ወይንም ምድር /መሠረት/ ሰማይን /ጣሪያ/ ዓምዱ ቤተ መቅደስ ነው። ያለ ዓምድ ቤት እንዳይቆም ያለ ቤተ መቅደስም ሰማይና ምድር አንድነት የላቸውምና እንደ ቤተ መቅደስ በምድር ላይ የሚያስፈራ ክብር ያለውም ቦታ የለም። ከእግዚአብሔር በላይ ንጉሥ አለመኖሩን ለሚያምን እንደ ቤተ መቅደስ የሚፈራውና የሚያከብረው ቤተ መንግሥት አይኖርም። እንደ እግዚአብሔር ኃያልና ፈራጅ ንጉሥ፣ እንደ ቤተ መቅደስም የከበረ ቦታ፣ እንደ ካህንም ባለ ሥልጣን ፈጽሞ የለምና፣ ቤተ መቅደሱን እናክብረው እንፍራው። «ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ» ተብለን ታዘናልና። ሮሜ.13÷6።

ቤተ መቅደሱን በማይፈሩና በድፍረት በሚያጐሰቁሉ ሰዎች ላይ እግዚአብሔር ያዝናል። ሕዝ.8÷5–18። ቤተ መቅደሱን በማርከስ ላቸው እግዚአብሔርን በመዘንጋታቸው «ስለዚህ እኔ ደግሞ በመዓት እሠራለሁ፣ ዓይኔ አይራራም፣ እኔም አላዝንም ወደ ጆሮዬም በታላቅ ድምፅ ቢጮኹ አልሰማቸውም አለኝ።» እንዲል ሕዝ.8÷18፤ «ደግሞም የካህናቱ አለቆች ሁሉ ሕዝቡም እንደ አሕዛብ ያለ ርኩሰት ሁሉ መተላለፍን አበዙ፣ በኢየሩሳሌምም የቀደሰውን የእግዚአብሔርን ቤት አረከሱ። የአባቶቻቸውም አምላክ እግዚአብሔር ለሕዝቡና ለማደሪያው ስላዘነ ማለዳ ተነሥቶ በመልእክተኞቹ እጅ ወደ እነርሱ

ዞልነ ነበር እነርሱ ግን የእግዚአብሔር ቁጣ በሕዝቡ ላይ እስኪ ጠባ ድረስ ፈጽሞም እስኪማይድንላቸው ድረስ በእግዚአብሔር መልእክተኞች ይሳለቁ ቃሉንም ያቃልሉ በነቢያቱም ላይ ያፌዙ ነበር። ስለዚህም የከለዳውያንን ንጉሥ አመጣባቸው። እርሱም ጕልማሶቻቸውን በቤተ መቅደሱ ውስጥ በሠይፍ ገደላቸው... በእርሱም ያስ አፍ የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል እንዲፈጸም÷ ምድሪቱ ሰንበትን በማድረግዋ እስክትፈርፍ ድረስ በተፈታችበትም ዘመን ሁሉ÷ ሰባ መት እስኪፈጸም ድረስ÷ ሰንበትን አገኘች።» /2ኛዜና 36÷14–21/ እንዲል ስንኳን ሰዎቹን ቤተ መቅደሱን እስኪያፈርስ ድረስ እግዚአብሔርን ያስቆጣል።

9.2. አመሠራረት፦ ቤተ መቅደስን ለመሥራት በመጀ መሪያ ያሰበው ያዕቆብ ነው። «ያዕቆብም እንዲህ ብሎ ስእለት ተሳለ፦ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን÷ በምሄድባትም በዚች መንገድ ቢጠብቀኝ÷ የምበላውንም እንጀራ የምለብሰውንም ልብስ ቢሰጠኝ÷ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ብመለስ÷ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆንልኛል፣ ለሐውልት /ትክል ድንጋይ/ የተከልሁት፣ ይህም ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ይሆናል፣ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ።» ዘፍ.28÷20–22 እንዲል። ይሁን እንጂ ከቤተ ምሥዋዕ ያለፈ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ብሎ በጠራው መልክ ባለ ሦስት ክፍል የሠሩ መሆናቸውን የሚጠቁም ማስረጃ ብዙም የለም።

እስራኤል ከግብፅ ከወጡ በኋላ ግን እግዚአብሔር የቤቱን ስም «መቅደስ» ብሎ በመጥራት ሥሩልኝ አለ። «በመካከላቸውም አድር ዘንድ መቅደስ ይሥሩልኝ። እኔ እንደማሳይህ ሁሉ÷ እንደ ማደሪያው ምሳሌ እንደ ዕቃውም ሁሉ ምሳሌ÷ እንዲሁ ሥሩት።» ዘጸ.25÷9። የቤተ መቅደስ አመሠራረት ከእግዚአብሔር እንጂ ከሰው

www.zeyeneta.com

አይደለም። መቅደስም የሚል ስም ያወጣለት ራሱ እግዚአብሔር ነው። ይልቁንም ደግሞ ሦስት ክፍሎች ያሉት መሆኑን ለሙሴ ካሳየው በኋላ አሠራሩንም በግልጽ በተብራራ መንገድ ነግሮታል።

ሦስት ክፍሎች ያሉትና ቅርጹ ወይም አከፋፈሉ ራሳቸውን ችለው የቤት ቅርጽ በመያዝና አንዱ በአንዱ ውስጥ ሆኖ መሠራት እንዳለበት ያመለከተው እግዚአብሔር ነው። ዘጸ. 26+1–37። ከዚህም እግዚአብሔር ካሳየውና ከነገረው ውጭ በሌላ መንገድ እንዳ ይሠራ እግዚአብሔር ሙሴን አስጠንቅቆት ነበር። «በተራራ ላይ እንዳሳየሁህ ምሳሌ እንድትሠራ ተጠንቀቅ።» ዘጸ.25+40 እንዲል። ስለዚህ የቤተ መቅደስ መሥራቿም ቀያሽ መሐንዲሷም እግዚአ ብሔር ነው።

አሁን አሁን አንዳንድ ሰዎች በሰዎች ፍላጐት የመጣ ሥልጣ ኔም የወለደው አድርገው በመቁጠር ስንፈልግ የሚኖር ሳንፈልግ የሚቀር አድርገው ይቆጥሩታል፡ መኖሩን የማይቀመሙትም አሁን በተማሩትና በሠለጠኑበት የምሕንድስና ሞያ መሠራቱን እንጂ ያድ ርበታል ብለው በሚያስቡት በእግዚአብሔርን ፈቃድ የተዘጋጀ ሥርዓ ቱንም የጠበቀ ሆኖ መዘጋጀቱን ይዘነጉታል፡ ይህም በእውነቱ ሊስ ተዋል የሚገባው ምሥጢር ነው። እግዚአብሔር ሙሴን ስለ ምን አስጠነቀቀው? የቤተ መቅደስ ሦስት ክፍል መሆን ለምን አስፈለገ? እግዚአብሔር ስለ ሳንቃዎቹና በውስጡ ስለሚኖሩት ንዋያትስ ምን አናገረው? የሚሉት ጥያቄዎች ሊስተዋሉ ይገባል።

9.3. የመቅደስ ሥራ እድገት

ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ እግዚአብሔርን በመሥ ዋዕት ለማግኘት አስቀድመው መሠዊያ ይሠሩ እንደ ነበር ታሪክ ያስረዳል። አብርሃምም ልጆቹም ይህን ሠርተዋል። ያዕቆብ ደግሞ «የእግዚአብሔርን ቤት እሠራለሁ» ሲል ተሳለ፣ እነ ኤልያስም አስቀድመው የፈረሰ መሠዊያዎችን በመሥራት እግዚአብሔርን ደስ

አሰኙት። 1ኛነገ.18+30። በዚህ መንገድ ተጀምሮ የኖረው እግዚ አብሔርን የማገልገል መንገድ እያደገና እየተሰወጠ መጥቷል። የተለወጠው ግን ቤተ መቅደሱ የሚሠራበት ቁስ እንጂ ሌላው አይደለም። ከተራራ ወደ ደብተራ አሪት፣ ከደብተራ አሪትም ወደ ሰሎሞን መቅደስ፣ ከሰሎሞን ቤተ መቅደስም ወደ አዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን እየተሸጋገረ አሁን ላለንበት ዘመን በቅቷል። ይህንንም በዝርዝር እንደሚከተለው እንመለከታለን።

9.3.1. ደብረ ሲና፡- ከላይ በትርጉም ቤተ መቅደስ የእግዚ አብሔር መገለጫ ነው እንዳልን እግዚአብሔር ለሙሴ ዘመጀመሪያ የተገለጠለት በሲና ተራራ ላይ ነው። ዘጸ.3+1። እግዚአብሔር ለሙሴ መገለጡ ብቻ ሳይሆን ደብረ ሲና ሕግጋትና ትእዛዛት የተሰጡበት፣ ሥርዓት የተሠራባት ተራራ ነበረች። ሙሴን ለሁለተኛ ጊዜ ሲጠራውና ወደ ተራራው ራስ ከመውጣቱ በፊት ሥርዓቱን ነግሮታል፣ ሙሴም ለሕዝቡ።

ሥርዓቱም ሕዝቡ ወደ ደብረ ሲና ከመውጣታቸው ሦስት ቀን በፊት ጀምረው ራሳቸውን እንዲቀድሱ፣ መኝታ እንዲለዩ፣ ልብ ሳቸውን እንዲያጥቡ የሚል ነው። ከወጡ በኋላ ደግሞ ተራራውን ከሕዝቡ ወገን ፈጽመው እንዳይነኩት ታዝዘዋል፣ ሙሴና አሮን ወደ ተራራው ወጥተዋል፣ በመጨረሻም ሙሴ ብቻ እግዚብሔርን ያነጋ ገረበት የጨለማ ቦታ አለ፣ ይህም ተራራው ሦስት ክፍል እንደ ተደረገበት ያመለክታል፣ ሕዝቡ ያለበት፣ አሮን ያለበትና፣ ሙሴ ያለበት። አቀማመጡንም ስናስተውል፣ የቅኔ ማኅሌት፣ ቅድስትና መቅደስን ሥዕል ይዘ እንመለከተዋለን። ለዚህም ነው ቅዱስ ዳዊት «ጌታ በመቅደሱ በሲና በመካከላቸው ነው።» መዝ.67+17 ሲል ሲናን መቅደሱ ያላት። በድጋሚም «ወደ መቅደሱም ተራራ አገባቸው+ ቀኙ ወደ ፈጠረቺው ወደዚህች ተራራ» /መዝ.77+54/

www.zeyeneta.com

ሲል ተራራው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ መሆኑን ተናግሯል።

አስተድሞ ሄኖክ እግዚአብሔር በሚወደው ቦታ የዕጣን መሥዋዕትን ሠውቷል። «ለእግዚአብሔር በዚህ ዓለም አራት ቦታዎች አሉትና፥ እርሱም እግዚአብሔር በሚቀበለው ዕጣን በሠርክ አስተድሞም በተትር ጊዜ መቅደስን አጠኑ። እርሱ፣ እነዚህም፣ የኤዶም ገነትና የሥራቱ ደብር /ደብር ቅዱስ/፥ ይህ ዛሬ አንተ ያለህበትም ደብረ ሲና ናቸው።» ኩፋ.5÷32 ላይ ደብረ ሲናና የተጠቀሱት ሁለት ቦታዎች የተራራ መቅደሶች እንደ ሆኑ ተቀምጧል። ያልተገለጸው አራተኛው ጊዜው ሲደርስ በሰው የሚሠራው ነው።

በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርት መሠረት ደብረ ታቦር ቤተ መቅደስ ነው፣ «ክብርህን አሳየኝ» /ዘጸ.33+17/ ሲል የለመነ ሙሴ በተገባለት ቃል ኪዳን መሠረት ሙታንን ወክሎ የተገኘበት፣ ኤልያስ ሕያዋንን ወክሎ፣ ሐዋርያትም ሰብአ ዓለምን በመወከል የተገኙበት ይልቁንም የአምላካችን የእግዚአብሔር መለኮታዊ ክብር የተገለጠበት ቤተ መቅደስ ነው። ማቴ.17+1–6።

ቅዱስ ዮሐንስም በራእዩ በሰማይ የተገለጠለትን ቤተ መቅደስ ተራራው ሲል ይጠራዋል፣ ስለዚህ ተራራ ከቦታ ሁሉ ከፍ ያለ ነው። ይልቁንም ደብረ ሲናንና ደብረ ታቦርን የመሰሉ ከተራሮችም ከፍ ያሉ ተራሮች በመሆናቸው ከተለዩት የተለዩ የእግዚአብሔር መገለጫዎች ለመሆናቸው አስረጂ ነው። ራእ.21+10–11።

9.3.2. <u>ደብተራ አሪት</u>:– ደብተራ የምሥዋዕ የሠረገላ ተድባብ፣ የመንበረ ታቦት አጉበር፣ በስተላይ እንደ ድባብ እንደ ጃንጥላ+ እንደ ባጥና እንደ ጣራ ሹኖ የተሠራ። ድንኳን፣ መላጃን በጺፍቴራ አምሳል የተሠራ+ እንደ ብራና የሚወጠርና የሚገተር፣ ቤተ መቅደስ። /ኪ.ወ.ክ.+ ገጽ 337።/

ደብተራ አሪት ሊቀ ነቢያት ሙሴ የሠራት መቅደስ ናት።

ከተደመቸው ከሲና ተራራ አንጻር ሰንመለከት ባለ ሦስት ክፍል እንድትሆን እግዚአብሔር ለሙሴ አሳየው፣ አሠራሩንም ነገረው። ዘጸ.25+40፣ ዘጸ.20 እስከ ፍጻሜው። ስለዚህም የክፍሎቹና የአገልግሎቱ ሁናቴ በሰፊው ተዘርዝሮ የታወቀበት ስለሆነ ለውጥ እንዳለው መግንዘብ አያሻንትም። ይልቁንም የምሥዋዑ አሠራር፣ የመሥዋዕቱ ሥርዓት፣ የመሥዋዕት አቅራቢዎቹ፣ የካህናቱ በእግዚአብሔር መመረጥና መሾም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚቻለው ሊቀ ካህናቱ ብቻ ሲሆን እርሱም የተፈቀደለት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ መሆኑን ስንመለከት የቤተ መቅደሱን እድገትና ክብር እንመለከታለን። በደብተራ አሪት ጊዜ ብዙ አዲስ ሥርዓቶችን እናስተውላለን። የካህናቱን አልባሳት፣ ሥርዓተ መሥዋዕትን፣ ሥርዓተ ማዕጠንትን፣ በቅድስተ ቅዱሳኑ የሚተመጡ ንዋያተ ቅድሳትን፣ የካህናቱን መታጠብ... ይህን የመሰሉትን ሁሉ እንመለከታለን። ዘጸ.25+1–27፣ 21።

ደብተራ አሪት የተሠራችው በድንኳን ከመሆኑ በቀር በኋላ ዘመን ከተሠሩት ቤተ መቅደሶች በሥርዓትም በክብርም የምታንስ አልነበረችም፣ እግዚአብሔርም በዚህ እየተገለጠ ሕዝቡን ይባርክ ከሙሴም ጋር ይነጋገር ነበረ። «ሙሴም ወደ ድንኳኑ በሄደ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ይነሡ ነበር፣ እያንዳንዱም በድንኳኑ ደጃፍ ይቆም ነበር። ሙሴም ወደ ድንኳኑ እስኪገባ ድረስ ይመለከቱት ነበር። ሙሴም ወደ ድንኳኑ በገባ ጊዜ የደመና ዓምድ ይወርድ ነበር+ በድንኳኑም ደጃፍ ይቆም ነበር፣ እግዚአብሔርም ሙሴን ይናገረው ነበር። ሕዝቡም ሁሉ የደመናው ዓምድ በድንኳኑ ደጃፍ ሲቆም ያየው ነበር፣ ሕዝቡም ሁሉ ተነሥቶ እያንዳንዱ በድንኳኑ ደጃፍ ይሰግድ ነበር።» ዘጸ.33+8–11 እንዲል።

9.3.3. <u>የሰሎሞን ቤተ መቅደስ</u>:– እግዚአብሔር ለረጅም ዘመን በድንኳን ሲመለክ ከኖሮ በኋላ ቅዱስ ዳዊት ለእግዚአብሔር

www.zeyeneta.com

ቤት ይሠራለት ዘንድ አሰበ። «...ንጉሡ ነቢዩ ናታንን፦ እኔ ከዝግባ በተሠራ ቤት ተቀምጫለሁ፥ የእግዚአብሔር ታቦት ግን በመጋረጆች ውስጥ እንደ ተቀመጠ አይ አለው።» 2ኛሳሙ.7÷2 እንዲል። ይህንን የዳዊትን አሳብ ተቀብሎ በሰሎሞን እንዲፈጸም ቃል ኪዳን ገብቶ ለታል። «እግዚአብሔርም ዳግም፦ ቤት እሠራልሃለሁ ብሎ ይነግርሃል። ዕድሜህም በተፈጸመ ጊዜ ከአባቶችህም ጋር ባንቀላፋህ ጊዜ ከወገብህ የሚወጣውን ዘርህን ከአንተ በኋላ አስነሣለሁ፥ መንግሥቱንም አጸናለሁ። እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፤ የመንግሥቱንም ዙፋን ለዘላለም አጸናለሁ።» /2ኛሳሙ.7÷12-13/ ሲል እግዚአብሔር የቤቱን መሠራት አጸደቀው፤ ሥምረቱ መሆኑንም ገለጸ።

በዚህ ፈቃደ እግዚአብሔር መሠረትነት እንደ ቃል ኪዳኑም በዳዊት ፋንታ የነገሠው ልጁ ሰሎሞን ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስን ሠራ። 1ኛነገ.5÷1፣8÷66። ቤቱን ሠርቶ ከፈጸመ በኋላ ቤቱን በድግስ አስመረቀ፤ ለእግዚአብሔርም ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ሥምረቱን ገለጸለት። «ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቤት የንጉሡን ቤትና ሰሎሞን የወደደውን የልቡን አሳብ ሁሉ ሠርቶ በፈጸመ ጊዜ፥ እግዚአብሔርም በገባዖን ለሰሎሞን እንደ ተገለጠለት ዳግመኛ ተገለጠለት። እግዚአብሔርም አለው፦ በፊቴ የጸለይኸውን ጸሎትህንና ልመናህን ሰምቻለሁ፤ ለዘላለምም ስሜ በዚያ ያድር ዘንድ ይሸን የሠራኸውን ቤት ቀድሻለሁ ዓይኖቼና ልቤም በዘመኑ ሁሉ በዚያ ይሆናሉ።» /1ኛነገ.9÷14/ ሲል ምን ያህል እንደ ተደሰተበት ገልጧል።

በእውነቱ ባሕርይው ቸርና ሰው ከድካሙ የሚያቀርበውን ሁሉ ተቀባይ ስለሆነ እንጂ የፍጥረት ሥራ ፈጣሪን የሚያስደንቅ ሆኖ አይደለም። ይልቁንም ሰሎሞንም ሕዝቡም ወደ እግዚአብሔር መመለሳቸውንና ለአምላካቸው ያላቸውንም ፍቅር የሚገልጡበት

በመሆኑ እግዚአብሔር እጅጉን ይደሰትበታል። ይህ ቤተ መቅደስ በፍርሃትና በአክብሮት እግዚአብሔርን የምናመልክበት ቦታ ነው። ይልቁንም በብቃታችን ወደ መቅደሱ መግባት እንዳልተቻለን ማስታወስ ይገባል። «እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ፤ አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ አሰግዳለሁ።» መዝ.5÷7 እንዲል። በዚህም ቦታ ከመገኘት በቀር ሕይወት የለም። «እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት፣ እርስዋንም እሻለሁ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፣ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን አይ ዘንድ፣ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ።» እንዲል።

በዚህ በሰሎሞን ቤተ መቅደስ ሦስቱን ክፍሎች እያንዳንዳቸውን እንመለከታለን።

ሀ/ <u>ቅኔ ማኅሌት</u>፦ ይህ በዕብራይስጡ «ኡላም» የሚሉት ነው። ይህ ክፍል አይሁድ በዘመናቸው መዘምራኑ መለከት እየነፉ ከበሮ እየመቱ የሚያገለግሉበት ነበር። በሙሴ የድንኳን ሥራ ይህ ክፍል እንደ ተጠቀሰ እንመለከታለን። መጀመሪያ የቅድስቱንና የቅድስተ ቅዱሳኑን አሠራር ከገለጸ በኋላ በመጨረሻ ስለዚህ ክፍል ገልጿል። «ከማደሪያውም በላይ ለድንኳን የሚሆኑ መጋረጆች ከፍየል ጠጉር አድርግ፣ አሥራ አንድ መጋረጆች ታደርጋለህ።» /ዘጸ.26÷7/ በማለት የተለየ ክፍል እንዲሠራ አዝዞታል። በዚህ ክፍል ልዩ ንዋያተ መሥዋዕት እንዲቀመጡበት ታዟል። በአሁኑ የቤተ ክርስቲያን አሠራር ይህ ክፍል ንዋያተ ማኅሌት የሚቀመጡበትና ማኅሌተ እግዚአብሔር የሚቆምበት ቦታ ነው። ንዑስ ክርስቲያንም «ፃዑ» ተብለው ወደ መካነ ቀኖናቸው እስኪሄዱ ድረስ በዚህ ክፍል ሆነው ያስቀድሳሉ። ክፍሉ ለሰቀልያ በመጋረጃ ለክብ ግን በግንብ ይለያል።

ለ/ ቅድስት፦ በዕብራይስጥ «ሀይክል» የሚሉት ነው። በእሪተ መቅደስ «የተቀደሰው ቦታ» እየተባለ እንደሚጠራ እንመለከታለን።

www.zeyeneta.com

ይህም ከውስጠኛው ቅድስተ ቅዱሳን ከሚባለው ለመለየት ነው። 1ኛነገ.6+16–18።

በሙሴ ዘመን በዚህ ክፍል ውስጥ መቅረዙ፣ ጠረጴዛው፣ ገበታው፣ ጎብስቱ ይቀመጥበት ነበር። በዚያ ዘመን በየዕለቱና በየሳምንቱ የሚቀርቡት ይሠውበት ነበር። «የመጀመሪያይቱ ድንኳን ተዘጋጅታ ነበርና+ በእርስዋም ቅድስት በምትባለው ውስጥ መቅረዙና ጠረጴዛው የመሥዋዕቱም ኅብስት ነበረበት።» ዕብ. 9+2–3፤ «...ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ ካህናት አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ዘወትር በፊተኛይቱ ድንኳን ይገቡባታል።» ቁ.6 እንዲል። አሁን በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ይህ ክፍል ሥጋውን ደሙን ለመቀበል የተዘጋጁ ምእመናን የሚያስቀድሱበት ክፍል ነው።

ሐ/ <u>ቅድስተ ቅዱሳን</u>፦ በዕብራይስጡ «ዳቤር» ይሉታል። ከተለዩ የተለያች ወይም ከተቀደሱት የተቀደሰች ማለት ነው። «ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን የምትባለው ድንኳን ነበረች+ በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ። ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት፣ በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር፣ የኪዳኑም ጽላት ነበሩ+ በላይዋም ማስተሥሪያውን የሚጋርዱ የክብር ኪሩቤል ነበሩ፤» ዕብ. 9+3–5።

ቅድስተ ቅዱሳን ፍጹም ልዩና የእግዚአብሔር መገለጫ ከመሆኑ የተነሣ ሊቀ ካህናቱ እንኳን የተፈቀደለት በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንዲገባ ነበር። «በሁለተኛይቱ ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ ይገባባታል+ እርሱም ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ ስሕተት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም።» /ዕብ.9+7/ የሚለውን ይዘው አንዳንድ ሰዎች እነዚህን እንደማያስፈልጉ አስመስለው ሲናገሩ ይደመጣል። ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ንዋያተ ቅድሳቱ ሥርዓትና ጌጥ

በዝርዝር በየስልቱ በየፊርጁ ዛሬ እንናገር ዘንድ ጊዜው አይደለም ያለው የጹሑፉ ትኩረት የጌታችንን የባሕርይ አምላክነት ማሳወቅና ዕብራውያንን ማሳመን ስለሆነ ነው። በዚያውም ላይ ሰዕብራውያን እነዚህ እንግዳ ነገሮች አይደሉም።

9.3.4. <u>ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም</u>፦

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድስተ ቅዱሳን ትባላለች። በዘይቤያዊ ትርጉሙ ቅድስተ ቅዱሳን ከተለዩ የተለያች ማለት ነው። ቅድስት ድንግል ከተለዩት ከቅዱሳን ሁሉ የተለየች ናትና።

እያየነው ካለነው ከቤተ መቅደስ ትምህርት አንጻር ደግሞ ቅድስተ ቅዱሳን ከተለዩ የተለያችና ልዩ ምሥጢራትን የያዘች ናት። ልዩ የሚያደርጋት ምንድን ነው?

ሀ/ ሊቀ ካህናት ብቻውን አንድ ጊዜ ብቻ ያሚገባባት መሆኗ፦ «በሁለተኛይቱ ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት አንድ ጊዜ ይገባባታል።» ዕብ.9+7 እንዲል። ድንግል ማርያምም ነቢዩ ሕዝ ቅኤል /ሕዝ.44+1/ እንደተናገረው ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ በማኅፀንዋ ያደረ፣ እንደ ትንቢቱም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና የተወለደ፣ ተዘግታ የምትኖር ደጅ የተባለላት እርሷ ናት። ኢሳ.7+14።

በአሪት ቅድስተ ቅዱሳን ሊቀ ካህናቱ ብቻ እንዲገባ የተፈቀደለት እርሱ ከሌሎቹ ካህናት በክብር ስለሚበልጥ ነበረ። ሌሎቹ ካህናት ቢገቡባት ኖሮ ሊቀ ካህናቱ ከእነርሱ ልዩነት አይኖረውም ነበረ። አሁንም ጌታችን ባደረበት ማኅፀን ያደረበት የለም፣ በክብር የሚተካከለው የለምና። እመቤታችንም ሌሎችን ልጆች ወልዳለች ማለት እርሱን ዝቅ ማድረግና እንደሌሎቹ «በዘር በሩካቤ የተወለደ እሩት ብእሲ» ብሎ መሳደብ ነው።

www.zeyeneta.com

ለ/ <u>ለሙሴ ንዋያት ይገኙባታልና</u>

ከላይ እንደተገለጸው በቅድስት ቅዱሳን ውስጥ አራቱ የወርቅ ንዋያትና አምስተኛ የበቀለችው የአሮን በትር ይገኙባታል። ስለ እነዚህ ዝርዝር አውንም መናገር ባይቻልም በትንሹ እንመ ልከታቸው።

1/ <u>ማዕጠንተ ወርቅ፡-</u> የዕጣን መሥዋዕት መሠዊያ ነው። አሠራሩንም ሙሴ ከእግዚአብሔር እንደ ታዘዘው አድርጉ ሠርቶ ታል። ዘጸ.30÷6–10፣ ዘጸ.37÷25–29። ዛሬ ይህ ንዋይ ጽንሐሕ በመባል ይታወቃል። ይህ የወርቅ ማዕጠንት ሦስት ዘንጉች በዙሪያው፣ አንድ በመካከል ያለው ሆኖ ሁሉም ከላይ ይገናኛሉ። ሁለት አቅርንት /ቀንዶች አሉት/። አገልግሎቱም ፍሕም ተጨምሮበት ዕጣን የሚሠዋበት ነበረ።

ማዕጠንት የእመቤታችን ምሳሌ+ በወርቅ መለበጡ የንጽሕ ናዋ የቅድስናዋ፣ ዕጣን የትስብእት፣ ፍሕም የመለኩት፣ የወርቅ ዘንግ/መካከለኛው/ የመንፈስ ቅዱስ /ሥጋንና ነፍስን ከእመቤታችን የከፈለ ያዋሐደ መንፈስ ቅዱስ ነውና/፣ አቅርንት የሥልጣነ እግዚ አብሔር ምሳሌዎች ናቸው።

በማዕጠንቱ ብዙ ሁነቶች ይፈጸማሉ። ለምሳሌም የዘንጉ መውጣትና መውረድ ይህ የጌታችን መምጣት፣ ማረግ፣ ዳግመኛ መምጣትና ዓለሙን አሳልፎ መኖርን፣ መዓዛ ዕጣን ደግሞ መዓዛ ወንጌል፣ በአጠቃላይ ጌታችን በምድር ላይ የፈጸመውን አገልግሎት የምንማርበት ምሥጢር ያለው ነው። ማዕጠንቱ የማጎፀነ ማርያም ምሳሌም ነው። በማዕጠንቱ ፍሕሙና ዕጣኑ እንዲዋሐዱ በማጎፀነ ማርያምም መለኮትና ትስብእት ተዋሕዶዋልና።

2/ <u>መሰበ ወርቅ፡-</u> የወርቅ መሰብ ሲሆን በውስጡም መና ይቀመጥበት ነበር። መሰበ ወርቅ የእመቤታችን፣ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፣ ሙና ለዓለሙ ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ አድርጉ

ሥጋውንና ደሙን የሰጠ የወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።

3/ በትረ አሮን፡- ሳይተከሏት ተተክላ፣ ውኃ ሳያጠጧት ጸድቃ ለምልማ የተገኘች ለውዝ ገውዝ ያፈራችው ከአሮን የተገኘች የሌዊ በትር ናት። ዘኍ.17÷1–10። ይህችውም ያለ ወንድ ዘር በግብረ መንፈስ ቅዱስ የሕይወትን ፍሬ ጸንሳና ወልዳ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ያስገኘችልን የእመቤታችን ምሳሌ ናት።

4/ ጽላት፡- በሙሴ የተቀረጹ ቃላተ እግዚአብሔር በራሱ በባለቤቱ የተጻፉበት የቃል ኪዳኑ ማኅተም ነው። ዘጸ.34÷1–9፣ 28። ይህም አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር በተለየ አካሉ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷም ነፍስን ነሥቶ ሰው ይሆን ዘንድ ምክንያት ለሆነችው ለድንግል ማርያም ምሳሌ ነበር።

5/ <u>ታቦት፡-</u>የጽላቱ ማደሪያ ነው።አሠራሩን ዝርዝር ምሥጢሩን በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ መመልከት ይቻላል። ጽላቱ ቃላተ እግዚአብሔር የሚያድርበት ታቦቱም ለአካላዊ ቃል በኩነት ማደሪያ ለሆነችው ለድንግል ማርያም ምሳሌ ነው። ወርቁም የንጽሕናዋ የቅድስናዋ ምሳሌ ነው።

እነዚህ አምስቱ ንዋያት ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚሰጡት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ብቻ እንደሆነው ሁሉ አካላዊ ቃልም አራት ባሕርያተ ሥጋ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስን ነሥቶ ሰው የሆነው ከአ ማናዊት ቅድስተ ቅዱሳን ከእመቤታችን ነው። ስለዚህም እግዚአ ብሔር ሊገለገል ሳይሆን ሊያገለግል ያደረባት መቅደስ ይልቁንም ልዩ ሊቀ ካህናት የገባባት ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ማርያም ናት።

የአምስቱ ንዋያት ቅድስናቸውና ክብራቸው በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ መኖራቸው ነው፤ቅድሽናቸውንም የሚያገኙት በሚቀድሳቸውም

www.zeyeneta.com

ሊቀ ካህናት የሚቀደሱት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ነው::እመቤታችን ቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕተ ንጹሐንም አምስቱ ብሒረ ጸድቃንን /ቅዱሳን መላእክትን፣ ቅዱሳን ነብያትን፣ ቅዱሳን ሐዋርያትን፣ ቅዱሳን ጻድቃንንና ቅዱሳን ሰማዕታትን/ ያከበረ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የገባባት እነርሱም በቅድስና ጸንተው የሚኖሩባት ቅድስተ ቅዱሳናቸው ናት:: ስለዚህ ከተለዩ የተለየችው ከተቀደሱትም የተቀደሰችው አማናዊት ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ናት::

ሐ/ <u>የእግዚአብሔር መገኛ ናትና</u>

እግዚአብሔር በባሕርይው ምሉዕ ከመሆኑ የተነሣ በሰማይ በምድር በእመት፣ በአየር፣ በሚታየውም በማይታየውም አለ:: ይህ ሕልውናው ግን ባሕርይው ምሉዕ፣ ሰፋሕ ረቂቅ ከመሆኑ የተነሣ ነው:: ይሁን እንጂ ለፍጡሩ ይልቁንም ለሰው በተለየ ሁኔታ የሚገለጥበት የእግዚአብሔር መገኛው መገለጫው ይባላል:: «እግዚ አብሔርንም የፈለገ ሁሉ ከሠፈር ውጭ ወዳለው ወደ መገናኛው ድንኳን ይወጣ ነበር::» /ዘጸ.33÷8/ የሚለው ቃል እግዚአብሔር ልዩ መገለጫ እንዳለው ያመለክታል::

ይህም ቦታ በሙሴ የመገናኛው ድንኳን ይባል ነበር፣ ሰውና እግዚአብሔር ይገናኙበት ነበርና:: ዘጸ.33÷7:: በኋላም ቤተ መቅደስ ተብሏል:: ይሁን እንጂ በዚህ ቦታ እግዚአብሔር ለሰው የሚገለጠው በረድኤት፣ በጸጋ፣ በምሳሌ ነው:: በቅድስት ድንግል ማርያም ግን በባሕርይው የማይታየው እግዚአብሔር እንዲታይ በኩነተ ሥጋ የተገለጠባትና፣ ራሱ ለአገልግሎት ሲመጣ የገባባት እውነተኛ የእግዚ አብሔር ድንኳን እርሷ ናት::

ቅድስት ድንግል ማርያም እንደ ሙሴ ድንኳን የእግዚአ ብሔር ድምፅ የተሰማባት፣ ሰውም በፍርሃትና በርቀት የሚሰግድባት ሳይሆን አምላክ ሰው የሆነባት ሰውም አምላክ የሆነባት ልዩ ድንኳን ናት:: እግዚአብሔርን ሊያየው የሚቻለው ፍጡር የለም:: ዮሐ.

1÷18፣ 1ኛዮሐ.4÷12:: ነገር ግን በድንግል ማርያም በኩል አየነው:: «ወያስተርኢ አምላክ አግልክት በጽዮን የአግልክት /የቅዱሳን/ አምላክ እግዚአብሔር በጽዮን /በአማናዊት ጽዮን በእመቤታችን/ ይታያል /በኩነት ይገለጣል/::» መዝ.83÷7፣ ተብሎ እንደ ተነገረ የሚያየው የለም ብሎ ያስተማረ ቅዱስ ዮሐንስም አየነው ሰማነው ሲል አስተማረ:: 1ኛዮሐ.1÷1::

ስለዚህ እመቤታችን እንደ ሙሴ ድንኳን በረድኤት፣ እንደ ቤተ ክርስቲያን በጸጋ ሳይሆን በኩነት የተገለጠባት፣ ለመገልገልም ሳይሆን አገልግሎት ሊሰጥ የተገለጠባት ቤተ መቅደስ ናት፣ ከላይ እንደተመለከትነው ሰው እግዚአብሔርን ሲፈልግ ወደ መገኛው ድንኳን ይመጣ ነበር፣ በድንግል ማርያም ግን እግዚአብሔር ሰውን ለመፈለግና ወደ ቀደመ ክብሩ ለመመለስ የገባባት የማትፈርሰው መቅደሱ ናት:: ሌሎቹ ሁሉ «ድንጋይ በድንጋይ ላይ ከቶ ሳይፈርስ አይቀርም» እንደ ተባለ በዕለተ ምጽአት ያልፋሉ፣ እርሷ ግን ይህ ጎልፈት የለባትምና ቅዱስ ኤፍሬም የማትፈርሰው መቅደስ ብሏ ታል:: /ውዳሴ ማርያም ዘቀዳሚት/::

ድንግል ማርያም ለመላእክትም ለሰውም ፈጣሪያቸውን እንዲያዩ ያበቃች ልዩ የእግዚአብሔር መቅደስ ናት::

በአጠቃላይ ከላይ እንደተመለከትነው በተዋሕዶተ ሥጋ አካላዊ ቃል ሊቀ ካህናት ተብሎ በአምስቱ ንዋያተ ቅድሳት አንጻር አራት ባሕርያተ ሥጋ አምስተኛ ባሕርየ ነፍስን ገንዘብ አድርጉ ፍጹም መሥዋዕት ሆኖ የተገለጠባት ሰውና እግዚአብሔርንም <u>ዐተ</u>ዋሕዶ ያገናኘባት አማናዊቱ ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን ማርያም ናት:: ሌሎቹም ምሳሌዎቿ ናቸው::

9.3.5. <u>በሰው እጅ ያልተተከለች ቅድስተ ቅዱሳን /መስቀል/</u>

«ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፣ በሰማያት በግርማው

www.zeyeneta.com

ቡፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፡ እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ነው፡ እርስዋም በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት።» ዕብ.8÷1-2።

መስቀል ጌታችን ሊቀ ካህናት ሆኖ፣ ራሱን መሥዋዕት አድርጉ ያቀረበባት ከተለዩ የተለየች ቅድስተ ቅዱሳን ናት። እግዚ አብሔር አገልግሎት የተቀበለባት ብቻ ሳይሆን አገልግሎት የፈጸ መባት፣ መሥዋዕት ሆኖ የተሠዋባት ዓት። የመስቀል አምስቱ ንዋያት አምስቱ ችንካሮች ናቸው። መሥዋዕተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በአምስቱ ችንካሮች ሥጋውን ቆርሶልናል ደሙንም አፍስሶ ልናልና።

ጌታችን መድኃኒታችን በገዛ ደሙ የገባባት ብቸኛ መቅደስ /ቅድስተ ቅዱሳን/ የተባለ መስቀል ነው። ከዚህ ውጭ የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም የቀረበበት መቅደስ የለምና። «ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች» የተባለችውም ማንም ፍጡር ስለ ሰው ራሱን መሥዋዕት አድርጉ ማቅረብ ስለማይችል ነው። ዳግመኛም መስቀል በአይሁድ የተዘጋጀው በእነርሱ ጎሊና ዕሩት ብእሲ የመሰላቸውን ጌታ ሰቅሎ ለመግደል እንጂ ወደ እግዚአብሔር ፍጹም መሥዋዕት የሚያቀ ርብበት ልዩ መቅደስ እንሥራ በሚል አይደለም። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ «በሰው እጅ ያልተተከለች» ሲል ገልጿታል። «ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ፥ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት /መስቀል/ በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም።» ዕብ.9÷11-12 እንዲል።

በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት ለቅድስት ሥላሴ የአምልኮት ስግደት ከሰገድን በኋላ የጸጋ ስግደትን የምናስከትለው ለእመቤታችን ከዚያም ለመስቀል ነው። እመቤታችንና መስቀል

የተለዩ የእግዚአ ብሔር መቅደሶች አካላዊ ቃል በተዋሕዶተ ሥጋ የተገለጠባቸው መሥዋዕት ሆኖ የቀረበባቸውም፣ ያቀረበባቸውም፡ የተቀበለባቸውም ናቸውና። «ወንሰግድ ውስተ መካን ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ፣ እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን።» /መዝ.131÷7/ ተብሎ የተነገረላቸው አካላዊ ቃል በተዋሕዶተ ሥጋ የተወሰነባት ድንግል ማርያምና መሥዋዕት ሆኖ የቀረበበትን መስቀልን ነው።

ይህች ለፍጥረት ያልሆነች በሰው እጅ ያልተሠራች ቅድስተ ቅዱሳን ያላት መስቀል እንደ ሆነች ሲያስረግጥ «ሊቀ ካህናት በየዓ መቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፣ እንዲህ ቢሆንስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር። አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራ ሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጧል።» /ዕብ. 9÷26/ በማለት «መግባት» ያለው መከራ መቀበልንና መሞትን እንደሆነ ግልጽ አድርጉ አስቀምጦልናል።

9.3.6. <u>የጸጋው ዙፋን /ቤተ ክርስቲያን ቅድስት/</u>

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ራሱን መሥዋዕት አድርጉ ካቀረበልን ለእኛ የሕይወት እንጀራ ሆኖ ከተሰጠን በኋላ መሥዋዕት መሠዋት ቀርቶልናል፣ ይሁን እንጂ አንድ ጊዜ ከተሠዋው ፍጹሙ መሥዋዕት ሁልጊዜ የምንሳተፍበት ሥርዓት ተሠርቶልናል፣ ይህን ሥርዓት የምንፈጽምባት የጌታችንን ሥጋና ደም የምንቀበልባትን «ቤት» ቤተ ክርስቲያን ዘክርስቶስ «የጸጋው ዙፋን» ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ጠርቷታል። «እንግዲህ ምሕ ረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።» ዕብ.4÷16 እንዲል።

ስለ ምን የጸጋው ዙፋን አላት?

የጸጋው ዙፋን ያላት ዙፋን ያሚዘረጋው በንጉሡ ቤተ

www.zeyeneta.com

መንግሥት ብቻ ነው። ዙፋን የሚኖረው ንጉሥ ሲኖር ነው። ዙፋኑ የሚቀመጥበት ቤተ መንግሥቱም የንጉሡ የፍርድ አደባባይ ነው። በዚህ ቦታ ፍርድን ከንጉሡ የሚሹ ደጅ ይጠኑበታል፡ ንጉሥም ነገራቸውን እየሰማ ፍርድ ይሰጥበታል። የንጉሡ መገለጫ የሆነው ይህ ቦታም ንጉሡ የዋጀው ነውና እጅግ የተከበረ ነው።

ቤተ ክርስቲያንም ንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ክርስቶስ የሚገለጥባት፣ እርሱም የሚሠየምባት /የሚፈተትባት/፣ ለተነሣሕ ያንም መብል ሆኖ የሚሰጥባት፣ ፍጹም ይቅርታን ሥርየተ ኃጢአትን የሚያሰጡ ባለሙሉ ሥልጣን ካህናት የሚገኙባት፣ ምእመናንም ምሕረትን ከእግዚአብሔር የሚያገኙባት የምሕረት አደባባይ ናት። ይህችውም እግዚአብሔር አስቀድሞ ለያዕቆብ የገለጠለት የሰማይ ደጅ ንጉሠ ሰማያት የሚታይባት የእግዚአብሔር ቤት ናት። በገርገር እንመልከታቸው።

ታቦት /ዙፋን እግዚአብሔር/፡- ታቦት ማደሪያ ማለት ነው። ይኸም የእግዚአብሔር መገለጫ ዙፋን መሆኑን ያመለክታል። የሐዲስ ኪዳን ታቦት ከብሉይ ኪዳን ታቦት የሚለይበት መንገድ አለው። በሐዲስ ኪዳን ታቦት የሚባለው የብሉይን ታቦትና ጽላት አንድ አድርጉ የያዘ ይመስላል፣ በብሉይ ጽላት ላይ የተጻፉት ቃላትም አልተጻፉበትም። ምክንያቱም በፍትሐ ነገሥት በአንቀጽ ቀጻግዊ እንደተገለጸው ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችል ጸሕልና ጽዋ የሚያስቀምጥ እንዲሆን ተወስኗል። በላዩም አልፋ ወዖ፣ ቤጣ፣ የውጣ የሚባሉ አስማተ አምላክ /የአምላክ ስሞች/ በአራቱ ማዕዘን ይቀረጽበታል። በመካከል ሥነ ስቅለት ይቀረጽበታል፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግዚአብሔር ታቦተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ተብሎ ይጻፍበታል። ኪሩቤል መንበረ ጸባዖትን እንደ ተሸከሙ ይሣልበታል። ከዚያም የቅዱሱ ስም ይቀረጽበታል። እስከ 15ኛው ምእተ ዓመት ከላይ ቅድስት ሥላሴን፣ ዝቅ ብሎ

እመቤታችን ወደ ላይ አንገድን በማትና፣ ከታች ደግሞ ቅዱሱን ወደ እመቤታችን አትንተው ይተረጹ ነበር። ሁሉም ምሥጢራት ያላቸው ናቸውና ዝርዝሩን በፍትሐ ነገሥት ተመልከት።

ከላይ እንደ ተገለጸው ታቦቱ ጸሕል ጽዋ እንዲያስቀምጥ ሆኖ የሚሠራው መሠዊያ ሆኖ ስለሚያገለግል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ. 13÷10 ላይ «መሠዊያ አለን» ያለው ታቦቱን እንደ ሆነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ተርጉሞታል። «ታቦት ነበረን» አላለምና፣ አለን ያለው በዘመነ ሐዲስ በመሆኑ መሠዊያ በሐዲስ ኪዳን ለመኖሩ ያስረዳል ብሏል። ታቦቱ የሚቀመጥበት ደግሞ በአዲስ ኪዳን መንበረ ታቦት ይባላል። መንበረ ታቦቱም በቅዳሴ ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትንና መባርህትን ከታቦቱና ከሥዕለ እግዝእትነ ማርያም በተጨማሪ እንዲ ያስተምር ሆኖ የሚሠራ ባለ አራት ማዕዘን ጠረጴዛ የሚመስል ሲሆን በእኛ ሀገር በላይ አጉበር ያለውና በአራቱም ማዕዘናት ተከፋች መሳከው ያሉት ነው። ከዚህ አንጻር የታቦቱ አገልግሎት ለመሠዊያ ነው። «መሠዊያ አለን» እንዳለ ቅዱስ ጳውሎስ ያለ መሠዊያ የምትኖር ቤተ ክርስቲያን የለችም።

የፕሮቴስታንት አማኞች መሠዊያውም ቤተ መቅደሱም የሏቸውም። ስለዚህም መሥዋዕቱም የለም። የሚያቀርቡትም ምክንያት የብሉይ ኪዳን የሆነው የበግ ደም ሲቀር መሠዊያም አብሮ ቀርቷል የሚል ነው። ይህ ግን የሐዲስ ኪዳን አገልግሎትን ከብሉይ ማነስ እንጂ ማከበር አይደለም፤ ይልቁንም ለዚያ ፍጹም ሥርየተ ኃጢአትን ለማያሰጠው ይህን ያህል ክብር ከተገባው ለፍጹሙ መሥዋዕትማ የበለጠ ይገባዋል። «ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለ ተሻረው ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ+ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ+ ቆመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ

www.zeyeneta.com

በክብር አይሆንም? የኩነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ÷ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና። ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጠው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን አጥቷልና። ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ÷ ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኗልና።» እንዲል 2ኛቆሮ.3÷7-11።

የምሥራችም የምሰራብም አብያተ ክርስቲያናት መሠዊያ አላቸው። ሁሉም እጅግ ያከብሩታል። ያለ መሠዊያም መሥዋዕት የለምና። በሐዲስ ኪዳን ስንኳን ብሉይን ለተቀበሉት ለአሕዛብም መ ሠዊያ እንደሚያስፈልጋቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉና አበቃለት ሊባል አይችልም። «በዚያ ቀን በግብፅ ምድር መካከል ለእግዚአብሔር መሠዊያ÷ በዳርቻዋም ለእግዚአብሔር ዓምድ ይሆ ናል፣ ይህም ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር በግብፅ ምድር ምልክ ትና ምስክር ይሆናል። በዚያም ቀን እግዚአብሔር በግብፅ የታወቀ ይሆናል÷ ግብፃውያንም እግዚአብሔርን ያውቃሉ በመሥዋዕትና በቁርባን ያመልካሉ÷ ለእግዚአብሔርም ስእለት ይሳላሉ ይፈጽሙት ማል።» /ኢሳ.19÷19-21/ የሚለውን ጥቅስ ስንመለከት ተፈጻሚነቱ በየትኛው ዘመን /ኪዳን/ ነው? በብሉይ ወይስ በሐዲስ? የሚል ጥያቄ ልናነሣ እንችላለን።

ተፈጻሚነቱ በሐዲስ ኪዳን ነው። በብሉይ ዘመን ግብጻውያን ስንኳን ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠርተው መሥዋዕት ሊያቀርቡ ቀርቶ እግዚአብሔርን እንኳ በውል አያውቁትም። ሙሴ ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ይሠው ዘንድ ሕዝቡን ልቀቅ ባለው ጊዜ ፈርዖን «ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በምድረ በዳ ትሠዉ ዘንድ እለቅቃችኋለሁ፣ ነገር ግን ርቃችሁ አትሂዱ ጸልዩልኝ አለ።» /ዘጸ.8÷25-29/ ተብሎ መጻፉ ግብፃውያን በጊዜው እግዚአብሔርን እንደማያመልኩ የሚያስረዳ ነውና። ስለዚህ ግብፃውያን እግዚአ

ብሔርን ዐውቀው ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ያቀረቡትና ያገለገሉት በሐዲስ ኪዳን እንደ ሆነ የታወቀ የተረዳ ነው። ይህም መሠዊያ በሐዲስ ኪዳን እንዳለ የሚያስረግጥ ነው።

ይልቁንም ደግሞ ብሉይ ኪዳን ካለፈች በኋላ በተጻፈው በዮሐንስ ራእይ ላይ «እምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ።» ራእ.6÷9 ተብሎ መጻፉ መሠዊያ በእግዚአብሔር ፊት የከበረ መሆኑን ያመለክታል። የቅዱሳን ጸሎትን መላእክት የሚያሳርጉት በመሠዊያው እንደ ሆነ ተጽፏልና። «ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሠዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው በወርቁ መሠዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው።...» ራእ.8÷3 እንዲል።

በዚህ መሠዊያችን ላይ ቤተ ክርስቲያን የምትሠዋው መሥዋዕት የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም ነው። የምንቀበለውም ንስሐ ገብተን በሚቻለን ሁሉ ተናጽተን ተዘጋጅተን ነው። በድፍረት የሚፈጸም እንደ ምግብ ሥጋም ለማን ኛውም ሰው የተፈቀደ ነገር አይደለምና። «ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም እጸ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን÷ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለ ማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና÷ ይጠጣልምና።» 1ኛቆሮ.11÷27 እንዲል።

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ይህ ሕያው መሥዋዕት «እነ ንውም ወልብየ ንቅሕት፤ እኔ ተኝቻለሁ ልቤ ግን ነቅቷል» መኃ.5÷2 እንዲል ነፍስ የተለየዉ መለኮት የተዋሐደው ሥጋውና ደሙ የሚፈተትበት ዙፋን እግዚአብሔር ታቦቱ ነው።

www.zeyeneta.com

በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ያለው መሠዊያ እግሮች ያሉት የእኛን ታቦት የሚያህል መጠን ያለው ጠረጴዛ የመሰለ ነገር ነው። በእኛ ግን ታቦቱ የሚቀመጥበት መንበረ ታቦት አለን፣ አጉበር ያለው በመሆኑ ደግሞ ክብሩን ሳቅ ያደርገዋል።

ስለዚህ ታቦታችን በሰማያዊው ቤተ መቅደስ ውስጥ ያለው የዙፋኑ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። ራእ.5÷6–14። ያለ እርሱ ሥጋ ውንና ደሙን ቤተ ክርስቲያን አትፈትትምና። ለቀደመው መሥዋዕት ለምውቱ ይህ ሁሉ የሚያስፈልገው ከሆነ ለሕያው መሥዋዕት የበለጠ ስለምን አያስፈልገውም። ያንን «ወበልዑ መሥዋዕተ ምውተ፤ የሞተ መሥዋዕትን በሉ።» መዝ.105÷28 ይለዋልና። ይህ ግን መሥዋዕቱ ሕያው ነው።

ሰሎሞን «ተኝቻለሁ» ያለው እንቅልፍ የነፍስ ከሥጋ መለየ ትን የሚያመለክት በመሆኑ ሲሆን «ልቤ ንቁ ነው» ማለቱ ደግሞ በመለኮቱ ሕያው መሆኑን ሲያስረዳ ነው። ከዚህ ውጭ ለፍጡር ተኝቶም ነቅቶም አንድ ጊዜ የሚቻለው አይደለም። እግዚአብሔር ግን አንድ ጊዜ ሙትም ሕያውም ነበረ። ሞተ /ነፍሱ ከሥጋው ተለየች/÷ ሕያው ነው /መለኮት አልተለየውምና/። ስለዚህም ለሁላችን ሕይወት ሆነን፣ ከሞትም በኋላ ሕይወተ ነፍስን አደለን። ዮሐ.6÷57።

ለ/ <u>ልዑካኑ</u>፦– ቤተ ክርስቲያን የጸጋው ዙፋን የመንበሩ ድንኳን ናት ስንል፣ በዙፋኑ ፊት ሠራዊተ ንጉሥ፣ ፈቃድ ፈጻሚዎቹ ልዑካኑ እንዳሉ እንመለከታለን። ራእ.5÷1–14። እነዚህ ልዑካን እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑ በተልዕኮም ደስ የሚያሰኙት ናቸው። «መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሃያ አራቱ ሊቃናት በበጉ ፊት ወደቁ÷ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ። በሰማይና በምድር

ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ፦– በረከትና ክብር ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው÷ ለበጉም ይሁን፡ ሲሉ ሰማሁ። አራቱም እንስሶች አሜን አሉ÷ ሊቃናቱም ወድቀው ሰገዱ።» /ራእ.5÷8–14/ እንዲል አምልኳቸውን በግብር የሚገልጡ ልዑካን ያሉባት ናት። ምድራዊውን ቁስ ተጠቅመን የምንሠራት ቤተ ክርስቲያን ሰማያዊት ናት፡ ሥርዓቷ ሁሉ ሰማያዊ ነውና። ቅዱስ ያሬድ እንደ ተመለከተው ቤተ ክርስቲያንን የሰማይ ደጅ የሚያሰኟትን ሁሉ ይዛለች። ንጉሡ እግዚአብሔር፣ መሰላሏ /ማዕከለ ፈጣሪ ወፍጡራን/ እመቤታችን፣ ቅዱሳን መላእክት፣ የሰው ልጆች /ምእመናን/ ይገኙባታል። በማቴ.17÷1–4 እንደተገለጸውም ጌታችን ባለበት ሙታን ሥጋ የተባሉት አዝማደ ሙሴ፣ ሕያዋን አዝማደ ኤልያስ፣ ሐዋርያትና ሊቃውንት ይገኙባታል። በቤተ ክርስቲያናችን የቅዱሳን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያርጋል። /ራእ.8÷1–5/ ልዑካኑ ጎሩያነ እግዚአብሔር ናቸውና። «አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው፣ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው፣ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።» ሮሜ.8÷30 እንዲል።

ሐ/ <u>የምሕረት አደባባይ</u>፦– የንጉሥ መገለጫ በሆነው ዙፋን ፊት አደባባይ አለ። ለአብነትም የጲላጦስን የፍርድ አደባባይ ማስታወስ ይቻላል። በእግዚአብሔር ቤት ፊት ያለችው አደባባይ ግን የምሕረት አደባባይ ናት። «አውደ ምሕረት» ተብላ ትጠራለችና። በዚህች አደባባይ ምሕረት ይቅርታ ዕርቅ ይፈጽምባታል እንጂ የይገባኛል ፍርድ አይፈረድባትም። የሚነገረው ቀለም የሚለጠው ትምህርት ሰዎች መሐርያን ተነሣሕያን እንዲሆኑ ነው። ምእመናን በራሳቸው በደል ይቅርታ ጠይቀው የደበሉትን ክሰው የቀሙትን መልሰው ንስሐ ገብተው የሚመለሱባት የበደሉትን ይቅር

www.zeyeneta.com

ብለው በተሳትፎ ፍጹም ሥርየተ ኃጢአት የሚያገኙበትን ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ፍጹም ዕርቅ ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቁባ ታል።

በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተዋጀች ናት። «ብዙ ደሙ የፈሰችን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።» ሐዋ.20+28 እንዲል ቤተ ክርስቲያን ቅድስትና ፍጹምት ናት፤ «በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ እድፈት ወይም የፈት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና እለአሙር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነች ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲ ያቀርብ ፈለገ።» ኤፌ.5+27 እንዲል ቤተ ክርስቲያን ክብርት በክርስቶስ ናት።

የእርሱ የሆኑቸውም ሁሉ የእርሱ የሆነው ጌታ ባለቤት ናትና የሚገው ሁሉ ንጽሕ ቤት ናት። ይልቁንም «ምልዕተ ጸጋ» ድንግል ማርያም እንዳለች ያዕቆብ በራእይ አይቷልና በቤተ ክርስቲያን የማይጎ ደፍ ጸጋ እግዚአብሔር የለም። ሀብተ መንፈስ ቅዱስ የተሰጣቸውና ቃጋድሏቸውን የፈጸሙ የቅዱሳን ሐዋርያትና የቅዱሳን መላእክት፣ የሁሉም እመቤታቸው ማርያም፣ የሁሉ ጌታ እግዚአብሔር የሚገ ኝባት ናትና፣ አጋንንትን ያሰለቀቀው ልብሳቸው ሙት የሚያስነሣው በትራቸው በአጠቃላይ ቤተጋድሉ ወቅት በእነርሱ ምክንያት የተቀደሱት ንዋያታቸውን የያዘች ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ ጸጋ እግዚአብሔር ናት።

እርሷንም የናቀ በሙሰሚ የሚፈተተውን ሥጋውን ደሙን የና ቀና ያቀለለ ነው። እርሱም ትጣት የማይቀርለት ነው። «የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ምስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም

እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያዋረደ እንዴት ይልቅ የሚብስ ትጣት የሚገባው ይመስላችኋል?» ዕብ.10+28–29 እንዲል።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ አሥር

«መሥዋዕት»

መሥዋዕት፡– ማለት መንፈሳዊ አምኃ፥ ሕርድ፥ ቁርባን፥ የእንስሳት፣ የአዝርዕትና የአትክልት፣ የስንዴ፣ የወይን፣ የዘይት፣ የዕጣን የመሰለው ሁሉ ፍጡር ለፈጣሪው ከጸሎትና ከምስጋና ጋር የሚያቀርበው፣ የሚያቃጥለው። /ኪ.ወ.ክ.፥ ገጽ 664።/

ከእንስሳት ከአዕዋፍ ደሙ ለመረጨት፣ ሥጋው ስቡ ለመቃጠል የሚቀርበው መሥዋዕት ይባላል፤ ከአትክልት ከአዝርዕት ወይኑ ለመረጨት፣ እህሉ ለመቃጠል ቁርባን፣ ዕጣኑም ለመዓዛ መሥዋዕት ይሆናል። መሥዋዕት የተጀመረው ከበደል በኋላ አዳም ከገነት በወጣ በማግሥቱ እንደ ሆነ ይታወቃል።

መሥዋዕት ለመሠዋት አራት አካላት ወይም ነገሮች ያስፈልጋሉ። እነዚህም፡–

1. መሥዋዕት የሚቀርብለት ምሕረት የሚጠየቅለት፣
2. መገናኛና መታረቂያ መሥዋዕት፣
3. አስታራቂ፥ መሥዋዕት አቅራቢ፣
4. መሥዋዕትን ተቀብሎ ይቅር የሚል ዋጋ የሚከፍል፣ እነዚህን ነጥቦች መሠረታዊ አድርገን ይዘን ከሕገ ልቡና እስከ ሕገ ወንጌል ድረስ ያሉትን የመሥዋዕት ዓይነቶችና ያስገኙትን ጥቅም እንመለከታለን። ቅዱስ ጳውሎስም በምዕራፍ አሥር ሙሉ ለሙሉ እና በምዕራፍ ዘጠኝ በከፊል እንዲሁም በሌሎቹ ስለ መሥዋዕት የጠቀሳቸውን ለመረዳት፣ ስለ ጌታችን አማናዊ ሥጋና ደም በማነጻጸር ፍጹም መሆኑን ያስተማረበትን እንመለከታለን።

10.1. መሥዋዕት በሕገ ልቡና፡–

ሕገ ልቡና የሚባለው ከአዳም እስከ ሙሴ ድረስ ያለው ጊዜ

ነው። በዚህ ወቅት አበው የተጻፈ ሕግ ሳይኖር ሕግን በልቡናቸው ሥሉሳቸው እግዚአብሔርን በእምነት ያገለግሉበት ጊዜ ነው። ይል ቁንም ደግሞ አዳም፣ አቤል፣ ሴት፣ ከዚያም ለልጅ ልጅ እየተላለፈ እስከ ኖኅ ደረሰ። ኖኅም ለልጆቹ ሕገ መሥዋዕትን አስተማረ፥ ከዚያም ለአብርሃም ደረሰ፣ አብርሃም ለይስሐቅ፣ ይስሐቅም ለያዕቆብ፣ ያዕቆብም ለልጆቹ እያለ እስከ ሙሴ ሳይለወጥ በመድረሱ ሕግ አሰኝቶታል።

የመጀመሪያው መሥዋዕት አቅራቢም አባታችን አዳም ነው፤ መሥዋዕቱንም /ከሰማን፣ ቀንዓት፣ ሉባንጃ ስንቡል ከሚባል ሽቱ/ በኅ መዓዛ አድርጉ በጠዋት ለእግዚአብሔር አትርቧል። ኩፋ.5÷1።

ከአዳም በኋላም ልጁ አቤል መሥዋዕት ሠውቷል፤ እግዚአ ብሔርም መሥዋዕቱን ተቀብሎለታል። ከዚህም በኋላ ብዙ ደጋግ አበው መሥዋዕት አቅርበዋል። በሕገ ልቡና እጅግ የተወደደና የሠመረ መሥዋዕት ካቀረቡት ውስጥ ስምንቱ አበው የማይዘነጉ ናቸው። እነርሱም አዳም፣ አቤል፣ ሄኖክ፣ ኖኅ፣ መልከ ጼዴቅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ናቸው። መሥዋዕት አቅራቢዎቹ እነርሱ ሲሆኑ መሥዋዕቱ ደግሞ የሚታጠን ዕጣንና የተለያዩ ሽቱዎች እንዲሁም ከንጹሐን እንስሳት ወገን የሆነ የእንስሳ መሥዋዕትን ሠውተዋል።

የመልከ ጼዴቅ ግን ጎብስተ ሰንዳሌና ወይን እንደ ነበር ፣ ቀሌምንጦስ ተገልጧል። /ከህነተ መልከ ጼዴቅ ላይ ተመልከት - ምዕራፍ ሦስት/። ዘፍ.4÷4፣ ዘፍ.8÷20፣ ኩፋ.5÷32፣ ዘፍ.22÷ 13–14፣ ዘፍ.26÷25፣ ዘፍ.33÷20፣ ዘፍ.35÷1–2። መሥዋዕቱን የተ ቀበለላቸው በፊቱ መሥዋዕትን ያቀረቡለት አምላካቸው እግዚአብሔር ነው።

በመሥዋዕቱ ያገኙትም ጥቅም «ተስፋ» ነበር። በኋላ ዘመን

www.zeyeneta.com

ሰው ሆኖ ሰውን ወደ ተደመ ፍጹም ክብሩ እንደሚመለስ ነገራቸው። ለጊዜውም በረከተ ሥጋን ሰጥቷቸዋል፣ ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን አድርጓል። ለአብነትም ምድርን በድጋሚ በማየ አይኅ ላያጠፋት ለኖኅ ቃል ኪዳን ገብቶለታል። ዘፍ.8+20። ለአበው የሚባርካቸው የተባረከ የሚረግማቸውም የተረገመ እንዲሆን ተነግ ሮላቸዋል። ይህም ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ባገኙት በረከት የሚባርኩትም የተባረከ የሚረግሙትም የተረገመ ይሆን ነበር። ዘፍ.26+3–4፣ ዘፍ.27+1–40 ለአብነት መመልከት ይቻላል። ተስፋውንም ቅዱስ ጳውሎስ «የዘሙኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአ ብሔር ልጁን ላከ።» ገላ.4+4 ሲል ገልጠታል።

10.2. <u>መሥዋዕት በሕገ አሪት</u>:– ሕገ አሪት እግዚአብሔር እሥራኤልን በሙሴ መሪነት ከግብጽ ባርነት ካወጣቸውና ከተገለጠላቸው በኋላ በደብረ ሲና ተራራ የተሰጠች ሕግ ናት። ከዚህም የተነሣ የመሥዋዕቱ ዓይነት፣ የሚሠዋበት ጊዜ፣ መሥዋዕት አቅራቢው ሁሉ ከእግዚአብሔር የተመረጡና በሕግ የተወሰኑ ነበሩ።

10.2.1. <u>መሠረታዊ የመሥዋዕት ዓይነቶች</u>:– በአሪት የመሥዋዕቱ ዓይነትም ሆነ አቀራረቡ በስፋትና በጥልቀት ተዘርዝሮ የተነገረና እንደ ሥርዓቱም ሲፈጸም እንደ ነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ። በዚህ ርዕስ ሥር ጠቅለል ጠቅለል እያደረግን በተለያዩ ዘርፎች እንመለከታለን።

መሠረታዊ የመሥዋዕት ዓይነቶች አሉ ከማለታችን አንጻር መሥዋዕቶችን ሁሉ በማጠቃለል በምስት ንዑስ ዘርፎች ከፍለን እንመለከታለን።

1. <u>ጊዜን መሠረት አድርገው የሚቀርቡ መሥዋዕቶች</u>:–እነዚህ የመሥዋዕት ዓይነቶች መደበኛ ናቸው። ምክንያቱም፣ በየጊዜያቸው ሳይታጐሉ የሚቀርቡ መሥዋዕቶች ስለሆኑ። እነዚህም የሚከተሉት

ናቸው፡

ሀ. <u>የዕለት መሥዋዕት</u>:– በየዕለቱ የሚቀርቡ ሁለት ጠቦቶች ሲሆኑ አንዱ በጠዋት ሁለተኛውም በሠርክ የሚቀርብ ነው። ዘጸ. 29+38።

ለ. <u>የሰንበት መሥዋዕት</u>:– በዕለት ከሚቀርበው በተጨማሪ 12 ኅብስቶች ተዘጋጅተው የእህል ቁርባን ሁነው የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። ዘሌ.24+5–9። ከመሥዋዕቱም ከዘወትሩ በተጨማሪ ሁለት ነውር የሌለባቸው የበግ ጠቦቶችና ሌሎች ተጨማሪ ቁርባኖች ይቀርቡ ነበር። ዘኍ.28+9–10።

ሐ. <u>የሠርቀ ወርኃ /የመባቻ/</u>:– ይህም በዘወትር ከሚቀርበው ሌላ ሁለት ወይፈኖች አንድ አውራ በግ፣ ሰባት የአንድ ዓመት የበግ ጠቦቶች አንድ ፍየል የኃጢአት መሥዋዕት ከአስፈላጊው የእህል ቁርባን ጋር የሚቀርብበት ነው። ዘኍ.28+11–15።

መ. <u>የዓመት በዓላት</u>:– እስራኤል በተለያዩ ወራት የሚከናወኑ የዓመት በዓላት አሏቸው። ከእነዚህም ውስጥ ከግብፅ በመጠበት በአቢብ ወር /ይህም በእኛ መጋቢት ነው/ በአሥራ አራተኛው ቀን በሚያከብሩት የፋሲካ ወር የቂጣ በዓል የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። ዘኍ.28+16፣ ዘጸ.23+14፣ ዘጸ.34+18። ሁለተኛ ደግሞ ከግብፅ በመጡበት ሰባተኛ ወር የሆነው የመስከረም ወር ነው። በዚህ ወር የመጀመሪያው ቀን የመለከት ድምፅ የሚነፋበት የተቀደሰ ጉባኤ ቀን ነው።

እስከ 11ኛው ምእተ ዓመት ድረስ ይህ ቀን የዓመት መጀመሪያ ነበር። በኋላ ግን ከ1073–1085 የሮማ ፓፓ የነበረው ጎርጎርዮስ ሰባተኛ የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ከልደት ጋር እንዲያያዝ ወደ ጥር አዙሮታል። የምዕራቡ ዓለም በሙሉ ይህን ሲከተል ኢትዮጵያ ብቻ ጥንቱን ላትለቅ ጠብቃው ትገኛለች።

www.zeyeneta.com

በዚህ ወር አሥረኛው የማስተሥረያ ቀናቸው ነው። ይህም ሊቀ ካህናቱ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ስለ ሕዝቡና ስለ ራሱ የሥርየት መሥዋዕት የሚያቀርብበት ነው። ከ15ኛው ቀን ጀምሮ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ዳስ ሠርተው በዚያ ይቀመጣሉ። በዓሉም የዳስ በዓል ይባላል፤ ልዩ የመሥዋዕት አቀራረብም አለው። ዘሌ.23+23–44። በዚህ የዳስ በዓል በሰባቱም ቀናት መሥዋዕት ይቀርባል። በመጀመሪያው ቀን አሥራ ሦስት ወይፈኖች፣ አሥራ አራት የአንድ ዓመት የበግ ጠቦቶች፣ ሁለት አውራ በጉች፣ ከእህሉ ቁርባን ጋር ይቀርባሉ። ከዚህ በኋላ እስከ ሰባተኛው ቀን ድረስ ትላንት ከተሠዋው በዕለቱ አንድ ከወይፈኖቹ በመቀነስ ሲሠዋ ጠቦቶቹና አውራ በጉቹ ግን በሰባቱም ቀናት ተመሳሳይ ነበሩ። ዘኍ.29+1–38። ስምንተኛውንም ቀን የተቀደሰ በዓል አድርገው ያከብራሉ።

ሦስተኛው በዓላቸው የመከር በዓል ነው። ለዚህም ራሱን የቻለ የመሥዋዕት ሥርዓት አለው፤ የሚገባውን በማቅረብ ይሠዋሉ። ዘጸ.23+16፣ ዘሌ.23+9–21።

2. <u>በትብዐት ምክንያት የሚቀርብ መሥዋዕት</u>

ይህ የመሥዋዕት ዓይነት ሰዎችንም ሆኑ ዕቃዎችን ለእግዚአብሔር የተለዩ ለአገልግሎትም የበቁ ለማድረግ ትብዐ ቅዱስ ተቀብተው በጸሉት በሚከብሩበት ወቅት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። ይኸውም በሚከተሉት ምክንያቶች የሚቀርብ ነው።

ሀ.ሰዎች ሲካኑ /ክህነት ሲቀበሉ/ ዘሌ.8ና 9፣ ዘኍ.8+1–ፍጻሜ።

ለ. ሲነግሡ፤ 1ኛሳሙ.11+14፣ 16+1–23።

ሐ. ንዋያተ ቅድሳትንና የእግዚአብሔርን ድንኳን ወይም አዲሱን ቤት ለማክበር ከትብዓት በኋላ የሚቀርብ መሥዋዕት፤ ዘኍ. 7+1–ፍጻሜ፣ 1ኛ ነገ.8+62–66።

3.<u>የሰዎችን ሕይወት መሠረት አድርጎ የሚቀርብ መሥዋዕት</u>

ይህ የመሥዋዕት ዓይነት ደግሞ የተለያዩ የሕይወት ገጠመኞች አሏቸው፤ በዚህ ኑሯቸውም ለእግዚአብሔር እንዲያቀርቡት የሚጠየቅ መሥዋዕት ነው። መሥዋዕቶቹ እንደ ምክንያቶቹ ስለሚለያዩ እንደሚከተለው እንዘረዝራቸዋለን።

ሀ. <u>የመንጻት መሥዋዕት</u>፡– ይህ ሴቶች ወንድ በወለዱ በ40 ቀናቸው ሴት በወለዱ በ80 ቀናቸው የሚያቀርቡት፤ ዘሌ.12+1–8።

– ሴቶች ከግዳጅ በሚነጹበት፣ ከለምጽ ከደዌ በሚነጹበት ወቅትና በመሳሰሉት የሚቀርብ ነው። ዘሌ.14 በሙሉ፣ ዘሌ. 15+16–33።

ለ. <u>የኃጢአት መሥዋዕት</u>፡– አንድ ሰው ትእዛዝ ተላልፎ በድሉ ኃጢአቱ ተሰምቶት በግሉ የሚያቀርበው መሥዋዕት፣ አልያም ሕዝቡ ወይም አንድ ባለሥልጣን ኃጢአት በመሥራቱ ምክንያት የሚያቀርበው ነው። ዘሌ.4+1–35።

ሐ. <u>የቅንዓት መሥዋዕት</u>፡– ባል ሚስቱን በሌላ ወንድ በጠረጠረና በቀና ጊዜ ለካህኑ ተናግሮ «መራራ ውኃ»ን /ማየ ዘለፋ/ ካጠጣት በኋላ የሚያቀርበው መሥዋዕት ነው። ዘኍ.5+11–28።

መ. <u>የቅድስና መሥዋዕት</u>፡– ሰው ራሱን ለእግዚአብሔር የተለየ ለማድረግ የናዝራዊነት ስእለት በሚሳልበት ወቅት የሚያቀርበው መሥዋዕት ነው። ዘኍ.6+1–21።

ሠ. <u>የበደል መሥዋዕት</u>፡– አንድ ሰው ሳያውቅ ኃጢአትን ቢሠራ ወይም እንዳይነካ የተከለከለውን ቢነካና ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሠራው ኃጢአት ቢታወቀው በእርሱ ላይ በደል ይሆንበታል፤ በዚህም በታወቀው ጊዜ የሚያቀርበው መሥዋዕት የበደል መሥዋዕት ይባላል። ዘሌ.5+1–19።

ረ. <u>የስእለት መሥዋዕት</u>፡– አንድ ሰው የተለየ ነገር እንዲፈጸምለት በመሻት ጸሎቱ ከኩፍ እንዲሆንለት የሚያቀርበው መሥዋዕት ነው። ይህ መሥዋዕት ሕጸጽ የሌለበት መሆን አለበት። ዘሌ.

www.zeyeneta.com

22÷23::

ሰ. የፈቃድ መሥዋዕት:- አንድ ሰው በበዓላት ጊዜ ወይም በፈለ ገው ዕለት ከሚጠበትበት ሌላ ወድዶ ፈቅዶ የሚሰጠው ሲሆን የሚቀርበው መሥዋዕት ላይ ጉድለት ቢኖርበትም እንዲቀርብ የተፈቀደ የመሥዋዕት ዓይነት ነው:: ዘሌ.22÷23::

ሸ. የምሲጋና መሥዋዕት:- ይህን መሥዋዕት ለየት የሚያደርገው ከመሥዋዕቱ ጋር ለሚቀርበው የእህል ቁርባን ጎብስቱ እርሾ ያለው መሆኑና እንደ ስእለትና ፈቃድ መሥዋዕት አድሮ የማ ይበላ መሆኑ ነው:: በአንድ ቀን ማለት አለበት:: ዘሌ.11÷18::

ከዚህ በተጨማሪ የዕርት ወይም የሰላም መሥዋዕት በማለት የሚከፍሏቸው አሉ፣ ይህም ሰዎች ከተበላደሉ በኋላ የቀማው መልሶ የበደለው ከም ከፈጸመ በኋላ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው መሥዋዕት ነው:: በዚህ ጽሑፍ ግን ይህንን የበደለ መሥዋዕት በሚለው ጽንሰ ሐሳብ ተጠቃልሏል:: ምክንያቱም ይህ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት በደል ሆኖ ይቆጠርበታልና:: ዘሌ.6÷1–7::

10.2.2. <u>መሥዋዕተ ኦሪት ከአቀራረቡ አንጻር</u>:-

ከላይ የተዘረዘሩት የመሥዋዕት ዓይነቶች መሥዋዕቱ በምን ምክንያት እንደሚቀርብ የሚያስረዱ ናቸው:: ሰው በተለያየ ምክንያት እንደ ትእዛዙ መሥዋዕቱን ከሰጠ በኋላ ካህኑ እንዲት ያቀርበዋል የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: «የሚቃጠል መሥዋዕ ትና የእህል ቁርባን የኃጢአትና የበደል መሥዋዕት፥ የቅድስናና የደኅንነት መሥዋዕት ሕግ ይህ ነው::» ዘሌ.7÷37 እንዲል::

አቀራረባቸውን ሙሴ በሕግ ከእግዚአብሔር እንደ ተቀበለው የሠራላቸው የመሥዋዕት የአቀራረብ ሥርዓቶች የሚከተሉት ናቸው:: ለንዋያተ ቅድሳት ክብርም ይሁን ለክህነት፣ የፈቃድም ይሁን የስእለት፣ የቅድስናም ይሁን የበደል በእነዚህ ስድስት መን

ገዶች ብቻ መሥዋዕት ሆኖ ይቀርባል::

1. <u>የሚቃጠል መሥዋዕት</u>:- እንጨቱ በመሠዊያው ላይ ተረ ብርቦ ሲነድ ያድራል፣ በመሠዊያው ላይ የሚነድደው እሳት ለዘወ ትር አይጠፋም::

– ካህኑ የበፍታ ቀሚስና ሱሪ ለብሶ ሥጋውን በመሠዊያው ላይ በመረብረብ የሚያቃጥለው ነው::

– መሥዋዕቱ እንደ ተቃጠለ አመዱን ከመሠዊያው ያፈሰ ሰዋል፣ ከዚህ በኋላ ልብሱን ቀይሮ ከሠፈሩ ውጭ ወደ ሆነ ሩትና ንጹሕ ሥፍራ ወስዶ አመዱን ያፈስላል::

– ለሚቃጠለው መሥዋዕት የቀረበው የእንስሳ ቆዳ ለካህኑ ይሆናል:: ከዚህ በተረፈ የተጋገረው የእህል ቁርባን፣ በመቀቀያ ወይም በምጣድ የበሰለው ሁሉ፣ በዘይት የተለወሰው ወይም የደረ ቀው የእህል ቁርባን ሁሉ ለሁሉም ካህናት ይሆናል:: ዘሌ. 6÷8–12፣ 7÷8–9::

– የሚቃጠለው የእንስሳ ቁጥር ግን እንደሚቀርብበት ዕለ ትና ምክንያት ይለያያል::

2. <u>የእህል ቁርባን</u>:- የእህሉ መጠን ከላይ እንደተገለጸው በዕ ለቶቹና በሚቀርብበት ምክንያት የተለያየ ነው:: አቀራረቡም ለእግዚ አብሔር የሚቃጠለው መልካም ዱቄት ከዘይት የተለወሰና ዕጣን ያለው ሆኖ ይቀርባል፣ እርሾ አይገባበትም:: ይህን ያቃጥላል፣ የተረፈውንም ከአሮን ወገን ወንዶቹ ሁሉ ይበሉታል:: ለዘወትር በሚቀርበው መሥዋዕት ላይ የኢፍ መሥፈሪያ አንድ አሥረኛ ሲሆን ግማሹ ለሚት ግማሹ ለማታ ነው፤ ይህም ሙሉ በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕት ነው:: ዘሌ.6÷14–23::

3. <u>የኃጢአት መሥዋዕት</u>:- ለዚህ የሚቀርበው መሥዋዕት የሚታረደው የሚቃጠለው መሥዋዕት በታረደበት ቦታ ነው:: የሚ

www.zeyeneta.com

ሠዋው ካህን ይበላለታል። የሚበላው ግን በእደ ባባዩ በተቀደሰው ሥፍራ ላይ ነው። ከክህነት ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ ይበላዋል። ለግሰ ተሥረያ ይሆን ዘንድ ከደሙ ጋር ወደ መገናኛው ድንኳን የሚገባው ሥጋ ግን ይቃጠላል እንጂ አይበላም። ደሙ የነካው ልብስ ሁሉ የሚታጠበው በዚያው በተቀደሰው ሥፍራ ብቻ ነው። የሚቀቀልበትም ዕቃ ሸክላ ከሆነ ይሰበራል ናስም ከሆነ ተፈግፍጎ ይታጠባል። ዘሌ.6÷24-30።

4. የበደል መሥዋዕት፡- አቀራረቡ እንደ ኃጢአት መሥዋዕት ነው፣ ሥርዓቱም አንድ ነው። ነገር ግን ደሙን መሠዊያው ላይ መርጨት አለበት። የሚሠዋው ካህን ወደ ተቀደሰ ሥፍራ አምጥቶ ላቸው ከካህናት ወገን የሆኑ ወንዶች ሁሉ ይበሉታል። የሚሠዋው ካህን ግን የሚበላው መሆኑ አልተገለጠም። ዘሌ.7÷1-2።

5. የደኅንነት መሥዋዕት፡- የስእለት፣ የፈቃድ፣ የምስጋና መሥዋዕቶች ሁሉ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ። በጣም ለየት የሚያደርገው ለምስጋና በሚቀርበው የደኅንነት መሥዋዕት እርሾ ያለበት ኅብስት ማቅረብ የሚቻል በመሆኑ ነው።

– የደኅንነት መሥዋዕት አያድርም፣ በተሠዋበት ቀን ብቻ የሚበላ ነው። የቁርባኑን ግን የስእለትና የፈቃድ ከሆነ አንድ ቀን አሳድሮ መብላት ይቻል ነበር። እስከ ሦስተኛ ቀን የቆየው ግን ይቃጠላል እንጂ አይበላም። ዘሌ.7÷11-18።

– በዚህ መሥዋዕት ፍርምባው ይወዘወዛል፣ በኋላም ሰቡን ካቃጠሉ በኋላ ለአሮንና ለልጆቹ ይሆናል።

– ቀኝ ወርቹ ለማንሣት ቁርባን ለካህኑ ይሠጣል። ዘሌ.7÷28-39።

6. የቅድስና መሥዋዕት፡- ይህ ሰዎች ክህነትን ለተቀበሉ ጊዜ ከኃጢአት መሥዋዕትና ከሚቃጠለው መሥዋዕት በኋላ በሦስተኛ

ኛነት የሚቀርብ ሲሆን ክህነትን የሚቀበሉት ሰዎች ከደሙ የተነ ጅሯቸውን ጫፍ የቀኝ እጅና እና የቀኝ እግር አውራ ጣት የሚቀቡለት ነው። የሚወዘወዘው ፍርምባ ለሠዋው ካህን ከመሆን በቀር ሌላው የሚቃጠል ነው። ዘሌ.8÷22-30።

10.2.3 <u>በአሪቲ መሥዋዕት የተገኘው ጥቅም፡-</u>

መሥዋዕት ያለ ጥቅም አይሠዋም። ከዚህ አንጻር የብሉይ ኪዳን መሥዋዕት ያስገኘው ጥቅም ምንድን ነው? የሚለውን መመልከት ያስፈልጋል።

ሀ. <u>ሥርየተ ኃጢአት፡-</u> የመሥዋዕት ትልቁ ጥቅሙ ሥርየተ ኃጢአትን ለማግኘት ነው። ይሁን እንጂ መሥዋዕቱ የእንስሳት፣ የአዕዋፍ፣ የእትክልትና የአዝርዕት ስለ ነበር መሥዋዕት ሆኖ ለሚቀርብለት የሰው ልጅ ፍጹምና ምሉዕ የሆነ ሥርየተ ኃጢአትን አላስገኘም። በራሱ ትንሣኤ የሌለው እንስሳ ለሌለው ሊሰጥ አልቻለምና «እንደ ሕጉም ከጥቂቶቹ በቀር ነገር ሁሉ በደም ይነጻል» እንዲል ይልቁንም ነፍሳትን ከሲኦል ወደ ገነት ማሻገር አልተቻለውም፣ የአዳምን ኃጢአት ሊያስተሠርይ አይችልምና። «እንግዲህ በሰማያት ያሉትን የሚመስለው ነገር በዚህ ሊነጻ እንጂ በሰማያት ያሉት ራሳቸው ከእርሱ ይልቅ በሚበልጥ መሥዋዕት ሊነጹ የግድ ነበረ።» ዕብ.9÷23 ተብሎ እንደ ተጻፈው። ምንም ይህ ታላቅ ጉድለት ይኑርበት እንጂ ጊዜያዊ ኃጢአትን እንደ ሕገ መሥዋዕቱ ሲቀርብ ያነጻ ነበረ። ዘሌ.17÷11።

ለ. <u>ተስፋ፡-</u> «እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ÷ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፣ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት÷ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንደ ሆኑ ታመኑ። እንዲህ የሚሉት ለእነርሱ የሚሆነውን አገር እንዲፈልጉ ያመለክታሉና።» /ዕብ.11÷13-14/ እንዲል አበው ሁሉ ደኖሩት በተስፋ ነው። ከዚህ

www.zeyeneta.com

አንጻር መሥዋዕታቸውም ተስፋቸውን እንዲመለከቱት በተሻለ መሥ
ዋዕት የሚቤዣቸው እንዳለ አሳይቷቸዋል፤ ምሳሌና ጥላነቱንም ው
ቀውታል::

ምክንያቱም ደም እንዳይበሉ የተከለከሉት የእንስሳው ነፍሱ
ደሙ በመሆኑ ነው:: ይህም ምውት /የሞተ/ መሥዋዕት እንደሚበሉ
ያመለክታል፤ ይሁን እንጂ ሥጋው የተጠበሰ ወይም የተቀቀለ መሆኑ
ወደፊት የሚመጣው አምላካችን እሳት /መለኮት/ በተዋሐደው ሥጋ
እንደሚያድን የሚያሳይ ተስፋ ነበር::

10.2.4.<u>መሥዋዕቱ ምንድን ነበር?</u>:-ይህን ጥያቄ የምንመለከተው
መሥዋዕቱ የምን እንስሳ ወይም ከምን ይዘጋጃል ከሚለው አንጻር
ሳይሆን በሚቀርብበት ሰዓት የነበረውን ብርታት ወይም ድካም ለማ
መላከት ነው:: ከዚህ አንጻር መሥዋዕቱ:-

ሀ. <u>የሞተ ነበር</u>:- «ወበልዑ መሥዋዕተ ምውተ» ሙት መሥ
ዋዕትን በሉ::» /መዝ.105÷28/ ተብሉ እንደ ተጻፈ ምውት ነበር::
ምክንያቱም የእንስሳው ነፍስ በደሙ የሚያድር ስለነበር የረጋ ደሙን
ለብቻው ስለ ነፍሳቸው ቤዛ በመሠዊያ ላይ አቅርበው ሥጋውን
አቃጥለው የተረፈውን ይበሉ ነበርና:: «የሥጋ ሕይወት በደሙ
ውስጥ ነውና ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሠርያና በመሠዊያው
ላይ ለነፍሳችሁ ማስተሥረያ ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት::»
ዘሌ.17÷11 እንዲል:: ከዚህም የተነሣ እንደ ሕጉ እንደ ክህነቱ
ድካም ያለበትና እንኳን ሌላውን ሕይወት የሚሰጥ ለራሱም የሞተ
ስለሆነ ሌላ ሕያው መሥዋዕት እንደሚያስፈልግ እያመለከተ አለፈ::

ለ. <u>ሰውን አያቀርብም ነበር</u>:- ከላይ በመሥዋዕት አቀራረብ
እንደተመለከትነው ለእግዚአብሔር መሥዋዕቱ ከቀረበ በኋላ ካህኑ
ካለበለዚያም የካህናት ወገን የሆኑ ወንዶችን ወይም አሮናውያን
ወንዶች ብቻ እንዲበሉት መፈቀዱ እግዚአብሔር ያቀረባቸው እነዚ
ህን ብቻ እንደሆነ ያመለክታል:: ሌሎቹን ወደ እግዚአብሔር

የሚያቀርብ አልነበረም::

ሌላው ቀርቶ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባው ካህን አንድ
ብቻ መሆኑ ለእርሱም በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ መፈቀዱ ካህኑና ሕጉ
ብቻ ሳይሆን የመሥዋዕቱንም ድካም የሚያሳይ፣ ሕዝቡንም ወደ
እግዚአብሔር በፍቅር የሚያቀርብ አለመሆኑን የሚያስረዳ ነው:

ሐ. <u>ሽክም ነበር</u>:- መሥዋዕቱን ስንመለከት በየእለቱ የሚቀ
ርብ መሥዋዕት ነበር፣ በየሰንበቱ እንዲሁም ደግሞ በየዓመት በዓላቱ
የሚቀርብ ነበር:: ከእነዚህ ውጭ ግለሰብም ሆነ ሕዝቡ ስለሚያጠፉት
አያንዳንዱ በደል ሁሉ የሚቀርብ መሥዋዕት እንዳለ ከላይ ተመል
ክተናል:: ይህ ሁሉ ግን ለሕዝቡ ጊዜያዊ በደልንና ኃጢአትን ከማ
ስተሥረይ አልፎ ነፍስን ንጹሕ ሊያደርግና ወደ ጥንተ አብሶን
አጥፍቶ የጥል ግድግዳን አፍርሶ ተደመ ከብር ሊመልስ አልቻለም::

ለአብነት ያህልም የዳስ በዓል በሚባለው በሰባተኛው ወር
በሚከበረው ብቻ በየዕለቱ፣ በሰንበት፣ በፈቃዳቸውና በስእለታቸው
ከሚቀርቡት በተጨማሪ 73 ወይፈኖች፣ 136 አውራ በጉችና ጠቦ
ቶች፣ 10 አውራ ፍየሎችን ያቀርቡ ነበር:: ይህ እንግዲህ በአንዱ
በዓል ብቻ ነው:: በዓመት ውስጥ ለመሥዋዕት የሚቀርበውን ነገር
ስንገምተው ምን ያህል ሽክም እንደ ነበር መገንዘብ ይቻላል:: ከዚህና
«ዓይን ስለ ዓይን» ከሚሉት መሰል ሕጎቿ ጋር የአሪት መሥዋዕት
አቀራረብ ከባድ እንደ ነበረ ማስተዋል ይቻላል:: ለዚህም ይመስላል
ጌታ ወንጌልን ቀላል ሽክም፣ ልዝብ ቀንበር ያላት:: ማቴ.11÷30::
ይህን ሁሉ ደም አፍስሳ አሪት አንድን ሰው ማዳን ከቶ አልተቻ
ላትም:: ዘጎ.29::

መ. <u>የሚደጋገም ነበር</u>:- ስለ ኃጢአት ሥርየት በዓመት
አንድ ጊዜ የሚሠዋው መሥዋዕት ለነበሩትም ለተወለዱትም በየዓ
መቱ የሚደጋገም ነበር:: ይህም መሥዋዕቱ የጐሰቆለውን ባሕርይ

www.zeyeneta.com

የማያድስ፣ ጎሊናን ከሞተ ሥራ /ከኃጢአት/ የማያነጻ፣ ውስጣዊ የሆነውን የተሰበረውን ልብና አእምሮ መጠገን ያልተቻለው የማይ ቻለውም እንደ ሆነ ያስገነዝባል። «ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው። እንደዚህም መባና መሥዋዕት ይቀርባሉ፣ እነዚህም እስከ መታደስ ዘመን ድረስ የተደረጉ ስለ ምግብና መጠጥም ስለ ልዩ ልዩ መታጠ ብም የሚሆኑ የሥጋ ሥርዓቶች ብቻ ናቸውና የሚያመልከውን በኅ ሊና ፍጹም ሊያደርጉት አይችሉም።» ዕብ.9+10 እንዲል።

10.3. <u>መሥዋዕተ ወንጌል</u>፦-

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዲሲቱን ኪዳን ወንጌልን ከሠራ በኋላ በደሙ አጽንቷታል። ዮሐንስ መጥምቅ «እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚይስተሠርይ የእግዚአብሔር በግ» በማለት እንደገለጠው አንድ ጊዜ ተሠውቶ ሁልጊዜ የሚመገቡት መሥዋዕት ሆነ። /ዮሐ.1+29/ የብሉይ መሥዋዕት ዘወትር የሚሠውት ዘወትር የሚመገቡት ግን ሕይወት ዘለዓለም የሌለው ነበር። ይህ ግን የተ ሠዋው አንድ ጊዜ የምንመገበው ግን ለዘወትር፣ ለሚመገቡትም ሕይ ወት ዘለዓለም የሚያስገኝ /ዮሐ.6+56/ ሆነ።

ስለዚህም ጌታ «...የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም።» ዕብ.9+12 ተብሎለታል። ስንኳን ሐዲሲቱ የመጀመ ሪያይቱም ያለ ደም አልተመረቀችምና። ይህን የጌታችን ሥጋና ደም የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕታችን ወይም መሥዋዕተ ወንጌል እንለዋለን።

10.3.1. <u>አዲሱ መሥዋዕት ለምን አስፈለገ</u>?፦-

ሀ. <u>በቀደመው ፍጹም ሥርየት ስላልተገኘ</u>፦- «ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምላል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና+ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀ

ርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም። እንደዚህማ ባይሆን የሚያመ ልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በኀሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን? ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፣ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነው።» /ዕብ. 10+1-4/ እንዲል የቀደመው መሥዋዕት ኃጢአትን ሊያስወግድ እንዳልተቻለው እንመለከታለን። ይህም ቀድሞ የታወቀ በመሆኑ ትንቢት ተነግሮ ነበር። «ሥጋክ አንጽሕ ሊተ መሥዋዕተ ዘበእንተ ኃጢአት ኢሠ መርኩ።» መዝ.39+6፤ ትርጓሜውም «ከኃጢአት ምክንያት የሚ ሠዋውን መሥዋዕት አልወደድኩም፣ ሥጋህን ንጹሕ መሥዋዕት አድርግልኝ» ማለት ነው። ስለዚህ አስፈልጓል።

ለ. <u>እርሱ እግዚአብሔር ያስፈልገን ስለነበር</u>፦- ከላይ እንደተ መለከትነው የአሪቱ መሥዋዕት ድካም ነበረበት። ቀደም ብለን በምዕራፍ ሦስት ላይም እንዳየነው ደግሞ አገልግሎቱ /ክህነቱ/ ደካማ ነበር። ስለዚህ ሕጉም፣ ክህነቱም፣ ነብያትም፣ መላእክትም፣ መሥዋዕተ አሪትም አዳምን ሊያድኑት ስላልቻሉ፣ እንዲሞት የፈረደበት እርሱ እንደሆነ የሞት ፍርዱን አንሥቶ ሊያድነውም የሚቻለው እርሱ ነውና እግዚአብሔር የሚሠራልን ሥርዓት የሚከፍልልን አዲስ መሥዋዕት ያስፈልገን ነበር። «አኮ በመልአክ ወአኮ በተንብል አላ ለሊሁ ይመጽእ ወያድኅኖሙ፣ በመልአክተኛ አይደለም በእግላጅም አይደለም፣ እርሱ ራሱ ያድናቸውማል።» /ኢሳ.63+8/ እንደ ተባለ እርሱ ራሱ ያስፈልገን ስለነበረ ነው።

በሐዲስ ኪዳን የቀረበልን መሥዋዕትም የጌታችን ሥጋና ደም እንደ ሆነ ቅዱስ ጳውሎስ ግልጽ አድርጉ አስቀምጠልናል፤ በመዝ.39+6-8 ላይ ያለውን ሲተረጉም «በዚህ ላይ መሥዋዕትንና መባን በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕትንም ስለ ኃጢአት የሚሠዋ

www.zeyeneta.com

መሥዋዕትን አልወደድህም፡ በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ፡ እነዚህም እንደ ሕግ የሚቀርቡት ናቸው÷ ተጥሎ እነሆ÷ አምላኬ ሆይ÷ ፈቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ፡ ብሏል። ሁለተኛውን ሊያቆም ፈተኛውን ይሽራል። በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ በማቅረብ ፈጽሞ ተቀድሰናል።» /ዕብ.10÷6–10/ ሲል የተደመውን መሥዋዕት የተካው አዲሱ መሥዋዕት የጌታችን ሥጋና ደም መሆኑን አስረግጦልናል።

10.3.2.ያሐዲሱ መሥዋዕት ምን ዓይነት ነው?:–

ሀ. ሕያው ነው:– አነ ንውም ወልብየ ንቅሕት፡ እኔ ተኝቻለሁ /በሥጋ መሞቱን ሲናገር/ ልቤ ግን ነቅታለች /በመለ ኮት ሕያው መሆኑን/ ሲናገር ነው። ተደጋግሞ እንደ ተገለጠው በአሪት የነበሩ ብዙ ሥርዓቶች ለሐዲሱ ምሳሌዎች ናቸው። የአሪት መሥዋዕት ደሙ አይበላም ነፍሱ ስለምታድርበት፣ ያልተጠበሰ ወይም ያልተቀቀለ እሳት ያልነካውም አይበላም፣ በድንም ፈጽሞ የተከለከለ ነበር። እነዚህ ሦስቱ በአንድነት ስለ ጌታችን ሥጋና ደም እምመ ለኩቱ ያለፉ ጥላዎች ናቸው። «ደሙን /የእንስሳውን ነፍስ/ አትብሉ» መባላቸው የጌታ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው መሆኑ፣ እሳት ያልነካውን አለመብላታቸውም መለኮት የተዋሐደው መሆኑን የሚያመለክት ነበር፡ «በድን አትብሉ» መባላቸውም ሥጋውና ደሙ፣ ነፍስ የተለየው፣ መለኮት የተዋሐደው ሕያው እንጂ ሙት አለመሆኑን ለማጠየቅ ነው። ይህን ሁሉ ምሥጢር አጠቃልሎ መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞን «እኔ ተኝቻለሁ÷ ልቤ ግን ንቁ ናት» ሲል አመሥጥሮ ተናግሯል።

ሕያው ከመሆኑም የተነሣ ለእኛ ሕይወት ይሆነናል። «ስለ ዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው:– እውነት እውነት እላችኋለሁ÷ የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም

ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።» ዮሐ.6÷53፤ «እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ።» ዮሐ.14÷6 እንዲል። ቅዱስ ጳውሎስም «ከአቤልም ደም ይልቅ ወደሚናገር ወደ መረጨት ደም ደርሳችኋል» ዕብ.12÷24 ብሏል። ይህም የፍጡሩ የአቤል ደም ከመሰከረች /በተአምራት/ ይልቁንም የፈጣሪዋ ምን ያህል ሕያው እንደ ሆነ የሚያስረግጥ ነው።

ለ. <u>ፍጹም የኃጢአት ማስተሥርያ ነው።</u>

ጌታችን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሰውን ከማጻኑ በፊት ኃጢአት በዓለም ላይ ነግሦ ነበረ፤ የደጋጉቹም ጽድቅና በጎ ሥራ የውርስ ኃጢአታቸውን ደምስሶ ወደ ገነት ሊያሻግራቸው አልቻለም ነበር። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ የነቢዩን የዳዊትን ትንቢት መዝ.13÷1–3፣ መዝ.52÷2–4፣ መዝ.5÷9 እና መዝ.139÷3 ላይ የተጻፉትን በማስታወስ «ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ...» በማለት ሁሉም ከኃጢአት በታች እንደ ነበሩ አስታውሷል። ሮሜ.3÷9–18።

በዚህ ዐቢይ ኃጢአት ምክንያት ነብያት ሁሉ ይህን ኃጢአት የሚያስወግደው መሲሕ እንደ ሆነ በትንቢት እየተመለከቱ በዘመናቸው ሊያዩት እየተመኙ አለፉ። «እውነት እላችኋለሁ÷ ብዙዎች ነብያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም÷ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም።» ማቴ.13÷17 እንዲል። በዘመነ ሥጋዌ የተገኘው ነቢዩ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ግን አይቷል፤ «በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ:– እነሆ÷ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።» ዮሐ.1÷29 እንዲል።

በቅዱስ ዮሐንስ እንደ ተመሰከረው ጌታችን ከአዳም ጀምሮ ለነበሩት ሰዎች እስከ ዕለተ ምጽአት ለሚነሡትም ኃጢአተ ዓለምን አንድ ጊዜ የሚያስወግድ እጅነተኛ መሥዋዕት ስለሆነ «የእግዚአ

www.zeyeneta.com

ብሔር በግ» ተባለ። መንፈሳዊው ቅዱስ ዮሐንስ አንድ ጊዜ በተ ሠዋው በጊታችን ሥጋና ደም ሁልጊዜ ፍጹም ሥርየተ ኃጢአት የምናገኝ መሆናችንን አስተምሯል። «የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።» 1ዮሐ.1+7፤ «...እርሱም የኃጢ አታችን ማስተሥረያ ነው+ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም+ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።» 1ዮሐ.2+2 ብሏል። ሥጋውና ደሙ ሰዎችን ፍጹማን ማድረግ የቻለ ፍጹም መሥዋዕት ነው። «አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጓ ቸዋልና።» ዕብ.10+14 እንዲል። የአሪቱ የበግና የኮርማዎች ደም ከአመድ ጋር ተረጭቶ ውጫዊውን ነገር የሚያነጻ ነበረ፣ የጌታችን ግን ፍጹም ነውና ኅሊናችንን የሚያነጻ ሆነ። «የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማ ንጻት የሚቀድሱ ከሆኑ+ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ ሕያ ውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ ኅሊናችሁን ያነጻ ይሆን?» ዕብ.9+13-14 ተብሎ ተጽፏልና።

ሐ. <u>ፍጹም አንድነትን ያስገኘ ነው</u>።

የብሉይ ኪዳን ሕግ በፍርሃት ይከበር ነበር። ሕግ የሻረም ከሕዝቡ ተለይቶ እስኪጠፋ ወይም ተወግሮ እስከ መገደል ይደርስ ነበር። ወደ እግዚአብሔር መገለጫም የሚቀርበው ካህን አንድ ብቻ ሲሆን ለእርሱም የተፈቀደለት የሥርየተ ኃጢአት መሥዋዕት ለማ ቅረብ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ነበር። መሥዋዕቱም የሚፈቀደው ለሌዋውያን ካህናትና ከእነርሱ ወገኖች ለሆኑ ወንዶች ብቻ መሆኑ ሰውና እግዚአብሔር በተስፋው ዘመን ምን ያህል እንደ ተራራቁ የሚያመለክት ነው።

በሐዲስ ኪዳን ግን ጎና ጌታችን እንደ ተወለደ እርት ተመጠ ነ። አምላክ በተዋሐዶ ሰው ሲሆን ሰውም በተዋሐዶ አምላክ ሆኗ

ልና፣ እረኞችና መላእክት አንድ ላይ ዘመሩ። ከዚህም በኋላ ጌታችን በትምህርትና በተአምራት ሰዎችን ከድንቁርናና ከኃጢአት ማሠሪያ ሲፈታ ቆይቶ እርት የሚታተመው በመሥዋዕት ስለሆነ በመስቀል ላይ ስለ እኛ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ በዚህም ጥልን ገደለ። «እርሱ ሰላማችን ነውና፣ ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛትን ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ፣ ይህም ከሁለታቸው አንድን አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ+ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው።» ኤፌ.2+14-16 እንዲል።

በዚህ ፍጹም መሥዋዕትም ሥርየትን አግኝን። «ደምም ሳይፈስ ሥርየት የለም።» /ዕብ.9+22/ የተባለው በዚህ ተደመደመ። ሰውና እግዚአብሔርም ፍጹም አንድነት የሚያገኝበት ያመነ የተጠ መቀ ሁሉ በዘር በጸታ እና በዕድሜ ተከፍሎ ሳይኖር የምን በላው ሕያው መሥዋዕት ሥጋውና ደሙ ተሰጥተናልና።

ይልቁንም ሁላችን እንበላው ዘንድ እግዚአብሔር ሁሉንም ይጠራል። «እነሆ በደጅ ቆሜ እንኳኳለሁ፣ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ+ ወደ እርሱ እገባለሁ፣ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ፣ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።» ራእ.3+20 ተብሎ እንደ ተጻፈ። ከእግዚአብሔር ጋር ስለሚፈጥርልን ፍጹም አንድነትም ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው «ሥጋዬን የማበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖረለሁ።» ዮሐ 6+56 ብሎናል።

መ. <u>አማናዊ ነው።</u> የምንተበለው ሥጋና ደም /የምንቆር በው ቁርባን/ አማናዊ የክርስቶስ ሥጋና ደም ነው። «ሲበሉም ኢየ ሱስ እንጀራን እንሥቶ ባረከ ቆርሶም ፈደተ መዛሙርቱ ሰጠና፦ እንካችሁ+ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስገኖም

www.zeyeneta.com

ሰጣቸው እንዲህም አለ፡– ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤ ስለ ብዙዎች ለኃጢ
አት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።» ማቴ.
26+26–27። ጌታችን ሥጋውንና ደሙን የሰጠው በመስቀል
ከመሰቀሉ በፊት ነው። ጌታችን «የሥጋዬ ምሳሌ ነው» «የደሜ
ምሳሌ ነው» አላለንም፤ ሥጋዬ ነው ደሜ ነው አለን እንጂ።

አንዳንድ ሰዎች «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።»
/1ኛቆሮ.11+24/ የሚለውን ጥቅስ መነሻ በማድረግ መታሰቢያ ነው
ይላሉ። ለመሆኑ ይህ አባባ ወደ ዓለም የገባው መቼ ነው? ምክንያ
ቱስ ምንድን ነው?

ታሪክ፡– በታሪክ እንደሚታወቀው 11ኛውና 12ኛው ክፍለ
ዘመን የፍልስፍና የዕውቀት ዘመን (Scholastic era)፣ የምክንያት
ዘመን (Age of Reason) ይባላል። በዚህ ዘመን ነበር እነዚህ የፍልስፍና
ሰዎች ለሮም ቤተ ክርስቲያን መምህራን «ጎብስቱን ሥጋው፣ ወይኑን
ደም ትላላችሁ፤ እንዴት እንደሚለወጥ አስረዱን?» የሚል ጥያቄ አነ
ሡ። ቤተ ክርስቲያኒቱም ለእነርሱ የመለሰች መስሏት በእምነት
የሚፈጸመውን ምሥጢር በፍልስፍና መለሰች። ምሥጢርነቱንም
ዘነጋችው። መልሷም በውላጤ ሲሆን ቃሉም "Transubstantiation"
የሚል ነው። "change of state" መለወጥ ማለት ነው። ይህም እንደ
ቃና ውኃ እንደ ሉጥ ሚስት ዓይነት ነው። ይህንን ዓይነት ለውጥ
ፈላስፎች «ፍጹም ለውጥ» "chemical change" ይሉታል። ይህም
አንድ አካል የመጀመሪያ አካልና ባሕርይውን ለውጠ ሌላ አካልና
ሌላ ባሕርይ ሲኖረው እንደ ማለት ነው።

ይህ መልስ ያላረካቸው ፈላስፎችም በ16ኛው ክፍለ ዘመን
የመከራከሪያ ዋና አጀንዳቸው ሆነ። እናድላለን ብለው የተነሡ እነ
ሉተርም ምክንያታውያን (Rationalists) ስለነበሩ ተቃራኒውን መናገር
ጀመሩ። በዓይናችን ፣ ው ሥጋና ደም ወደ መሆን አልተለወጠ

ም ና ምሳሌው (its symbol) እንጂ ራሱ አይደለም በማለት ማስተማር
ቀጠሉ። መንፈሳዊ እውነታም የለውም አሉ።

በእውነቱ ግን ጌታ የተናገረውን ሰው መዘንጋት የለበትም።
«ይህ ሥጋዬ ነው፣... ይህ ደሜ ነው።» ሉቃ.22+19–20። «እኔ
የበጎች በር ነኝ።» ዮሐ.10+7 ብሏል። ታድያ እርሱ ከጣውላ ወይም
ከብረት ካለበለዚያም ከመስተዋት የተሠራ «መዝጊያ» ነኝ ማለቱ
ነውን? እኒህ ዓይነት ነገሮች ናቸው ምሥጢራት የሚባሉት።
እንዴት ውላጤው እንደሚፈጸም በጎሊና ከመታሰብ በላይ ነው፤
ከትጸሊያችን በኋላ የምንተበለው አማናዊ ሥጋ ወደሙን ነው። ቅዱስ
ጳውሎስ በ1ኛቆሮ.11+25 «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።
ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ
ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።» የሚለውን ቤተ
ክርስቲያን በእጅጉ ትፈጽመዋለች። ሊቃውንቱ ውላጤ ዘእንበለ
ውላጤ ይሉታል። መለወጥ ሳይኖር ማለት ነው። መለወጡ
ጎብስትነቱን ወይንነቱን ለቅቆ ሳይሆን በጎብስቱ በወይኑ አማናዊ
ሥጋና ደም ሆኖ ነው።

በየዕለቱ በትጸሊ ጊዜ ሥጋውና ደሙን ካህኑ በሚፈትትበት
ሰዓት «ነአምን...» ከሚለው ጀምሮ ሕዝቡ በሙሉ «ንዜኑ ሞተከ
እግዚኦ ወትንሣኤከ ትድስተ፣ ነአምን ዕርገተከ ወፅጌሙ ምጽአተከ
ንሴብሐከ ወንትአመነከ ንስእለከ ወናስተብቍዐከ፣ አ እግዚእነ ወአም
ላክነ፣ አቤቱ ሞተ ብኩርናህንና ልዩ ትንሣኤህን እንናገራለን፣ በክብር
እንጸረግህ፣ ጸግሙኛም እንድትመጣ እናምናለን። አቤቱ፥ ጌታችን
አምላካችን ሆይ፥ እናመሰግንሃለን፣ እንታመንብሃለን፣ እንለምንሃለን፣
እንግልድሃለንም» እያሉች በሚገባ የጌታን ሞትና ትንሣኤ ዕርገቱንና
ጸጋም ምጽአቱን ታስባለች።

ቅዱስ ጳውሎስም ሞቱን ትንሣኤውን አስቡት አለ እንጂ

www.zeyeneta.com

ሥጋውና ደሙ አይደለም አላለም። ይልቁንም ሳይገባው የሚቀበለው ዕዳ አለበት ብሏል። «ስለዚህ ሳይገባው ይህን አንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና።» 1ኛቆሮ.11÷26–30።

«የጌታን ሥጋ ስለማይለይ» ማለቱ በዓይነ ሥጋ ሲመለከቱት ጎብስትና ወይን ለሚመስላቸው ሰዎች አማናዊነቱን ሲናገር ነው። ጌታችን «ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው» /ዮሐ.6÷55/ ብሎ አማናዊ ያለው በጸሎተ ኀሙስ «ይህ ሥጋዬ ነው፤ ይህ ደሜ ነው....» ማቴ.26÷26–28 ያለውን ነው።

ሠ. <u>አንድ ጊዜ የቀረበ ነው</u>:– መሥዋዕተ አሪት የሚደጋገም እንደ ነበር ተመልክተናል። «ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ፥ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን፥ የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገባ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም።» /ዕብ. 9÷11–12/ እንዲል ጌታችን የራሱን ሥጋና ደም መሥዋዕት አድርጉ ያቀረበልን በመስቀል ላይ ነው።

በዚህ አንድ ጊዜ ባቀረበው መሥዋዕት ሁልጊዜ የምንማር የምንታረቅ ሆነናል። «እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና።» ዕብ.7÷27። ቤተ ክርስቲያን አሁን ቅዱስ ቁርባንን ለምእመናን የምታቀብለው ራሱ ጌታችን በጸሎተ ኀሙስ በሠራው ሥርዓት መሠረት ነው። ማቴ.26÷26። ያለ ሥጋ

ወደሙም ሕይወት ስለማይኖረን አምነን ሥጋውን ልንበላ ደሙንም ልንጠጣ ስንሄድ ቤተ ክርስቲያን እንደሚገባን ሆነን መሄዳችን ታረጋግጣለች። ይህም ከዕለተ ዓርቡ መሥዋዕት መሳተፍ ይባላል እንጂ አዲስ መሥዋዕት መሠዋት አይደለም። ከተሰቀለ በኋላ አርባ ቀን እንደሚቆይ እያወቀ ከተሰቀልኩ በኋላ ሳይል አስቀድሞ ሊሐዋርያት ሥጋውንና ደሙን መስጠቱ እንዴት ከሥጋውና ደሙ እንደምንሳተፍ አዲስ ሥርዓት መሥራቱ ነው።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲሞት ከተባበሩት አይሁድ መካከል አንዱ በኋላም ደቀ መዛሙርቱን ሲያሳድድ የነበረው ሳውል /ቅዱስ ጳውሎስ/ ከተመለሰ በኋላ አሕዛብን ስለ ሥጋ ወደሙ አማናዊነት ያስተማረው በጊዜው ምእመናን ይሳተፉ ስለነበረ ነው። «ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት፤ ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና።» /1ኛቆሮ.11÷27–30/ ያለው ቅዱስ ጳውሎስ በዘመኑ የነበሩ ምእመናን እንዴት አንድ ጊዜ ከተሠዋው ሥጋና ደም መሳተፍ እንዳለባቸው ሲያስጠነቅቅ ነው።

ይህ ሁል ጊዜ የሚፈተት ሥጋና ደም አንድ ጊዜ የቀረበ የአንድ የእግዚአብሔር ሥጋና ደም ነው። ይህንንም ሲገለጽ ቅዱስ ጳውሎስ «ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።» ዕብ.7÷25 ብሏል። «ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራል» የተባለው አንድ ጊዜ በቀራንዮ ተሠውቶ ሳለ በመለኮት ሕያው ሆኖ በየጊዜው በወልደ እግዚአብሔር አምነው የሚመጡትን ሁሉ ሕይወት እያሰጠ ሲያስታርቅ የሚኖር በመሆኑ

www.zeyeneta.com

ነው ::

አንድ ጊዜ ብቻ መሠዋቱንም «ሊተ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአት ሊያስወግድ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሟል፣ እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል። አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋልና።» ሲል ዘግቶታል። ዕብ.10+11–14።

10.4 <u>መሠዋዕተ ምእመናን</u>:– ከላይ እንደተገለጸው ለድኅነታችን የሚሆን መሥዋዕት አንድ ጊዜ የቀረበ ነው። በፊት በዕለተ ሰንበትና በወር መባቻ በበዓላት የሚቀርቡትን መሥዋዕት ያስቀረ ነው፣ እነዚህ ለዚህ ለፍጹሙ መሥዋዕት አምላል መርገፍ እንጂ ጸንተው ሊኖሩ የሚገባቸው አልነበሩም። ይህን አታድርጉ እያሉ አይሁድን የሚወተውቱ አንዳንድ በጊዜው የነበሩ ምእመናን ቅዱስ ጳውሎስ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፣ እነዚህ ሊመጣ ያሉት ነገሮች ጥላ /ምሳሌዎች/ ናቸውና፥ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።» ሲል አስተምሯቸዋል። ቆላ.2+16–17።

እነዚህ መሥዋዕተ እንስሳት እንዲቀሩላቸው መደረጉ በክርስቶስ አማናዊ መሥዋዕት ስለ ተፈጸሙ ነው። «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና» /1ኛቆሮ.5+7/ እንዳለ በእርሱም ደም ጸድቀ ናልና። ሮሜ.5+9፣ 1ኛጴጥ.1+18–19።

ከዚህ በኋላ ግን በክርስቶስ ላመኑ ምእመናን የሚጠበቅባቸው መሥዋዕት መንፈሳዊ ነው። «እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕት ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ

መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።» /1ኛጴጥ.2+5/ እንደ ተባለ ይህ ውም በኩር መቀደስ ነው። «በኑሯችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ» ተብለናልና። 1ኛጴጥ.1+16። ከዚህ አንጻር ምእምናን ሊያቀርቧቸው የሚገባቸውን መሥዋዕት እንደሚከተለው እንገልጻለን።

ሀ. <u>መንፈሳዊ አገልግሎት</u>:– «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ + ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው።» ሮሜ.12+1 እንዲል። ቅዱስ ጳውሎስ ለአገልግሎት የሚፋጠን ሰውነቱን «ቅዱስ» /የሚቻለውን ያህል በንጽሕና ተጠብቆ/ አድርጉ ቢቀርብ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ፍጹም መንፈሳዊ መሥዋዕት ማቅረቡ ነው። «እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፣ ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።» ሮሜ.6+12–14 በሚል ታዝዘናልና።

ለ. <u>መባ /እምኃ/</u>:– ምእመናን አሥራቱን ለቤተ ክርስቲያን በሚገባው መንገድ መስጠት ወይም መፈጸም መንፈሳዊ ግዴታቸው ነው። ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በነጻ በፈቃዳቸው የሚሰጡት ስጦታ በፍቅርና በእምነት ሲሰጡት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ መሥዋዕት ይሆንላቸዋል። «የመዓዛ ሽታና የተወደደ መሥዋዕት የሚሆነውን ለእግዚአብሔርም ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ ተሞልቻለሁ። አምላኬም እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል።» /ፊል.4+18/ ሲል ቅዱስ ጳውሎስ በእግዚአብሔር መወደድ ብቻ

www.zeyeneta.com

ሳይሆን የሚገኘውንም በረከት በመጪመር ገልጦታል::

ይህ ስጦታ ለችግረኞችም ይልቁንም አበላ አጠጣ በክር ኩበት አገር ተርቢ ተጠምቼ፣ አበድሬ ተከብሬ በናርኩበት አገር ተዋርጀ እንዴት አድርጌ እለምናለሁ ለሚሉትና በቤታቸው ተደብቀው ችግር ለጸናባቸው ሲሆን እጅግ የተወደደ መሆኑን ምርጥ ዕቃ ቅዱስ ጳውሎስ ገልጦታል:: «ነገር ግን መልካም ማድረግን ሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፡ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና::» /ዕብ.13÷16/ እንግዲህ «የሚሰጥ በልግሥና ይስጥ::» ሮሜ.12÷8::

ሐ. <u>ምስጋና</u>:- እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔር ነሣ፣ ከእግዚአብሔር መልካሙን ብቻ እንቀበላለን ክፉውንስ ለምን አንቀበልም? እንዳለው እንደ ኢዮብ፣ በጠገቡም፣ በተራቡም፣ በእዘኑም፣ በተደሰቱም ጊዜ እግዚአብሔርን ማመስገን ንጹሕ መሥዋዕት ነው:: «እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት÷ ማለት ለስሙ የሚመስክሩ የከንፈሮችን ፍሬ÷ በእርሱ እናቅርብለት::» ዕብ. 13÷15 ተብለናልና::

ልበ አምላክ ቅዱስ ዳዊትም «የፍሪዳውን ሥጋ እበላለሁን? የፍየሉንስ ደም እጠጣለሁን? ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ሠዋ÷ ለልዑልም ስእለትህን ስጥ፡» ብሏል:: መዝ.49÷16 ነቢዩ ሆሴዕም «እሥራኤል ሆይ÷ ቢኃጢአትህ ወድቀሃልና ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ተመለስ:: ከእናንተ ጋር ቃልን ውሰዱ÷ ወደ እግዚአብሔርም ተመልሳችሁ ኃጢአትን ሁሉ አስወግዱ፣ በቸርነትም ተቀበለን÷ በወይፈንም ፋንታ የከንፈራችንን ፍሬ እንሰጣለን አሦር አያድነንም፣ በፈረስ ላይ አንቀመጥም፣ ድህ አደጉም በእንተ ዘንድ ምሕረትን ያገኛልና ከእንግዲህ ወዲህ ለእጆቻችን ሥራ ለአምላኮቻችን ናችሁ አንላቸውም ብለው::» ሆሴ.14÷1-3 በማለት ዋናው ለእግዚአብሔር

የምናቀርበው የከንፈር ፍሬ መሆኑን ተናግሯል::

መ. <u>ምሕረትና ጸሎት</u>:- ጌታችን በወንጌል «ምሕረትን እወ ድዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም::» ተብሎ በሆሴዕ የተነገረውን ሆሴ.6÷6 በመጥቀስ ያስተማረው እርሱም ስለማረን እንጂ ስለ መሥዋዕታችን ሰው የሆነ አይደለምና ነው:: ስለዚህ እርሱ በምሕረት እንደታረቀን እኛም ሌሎቹን ልንምር ይቅር ልንል ካልቻልን መንፈሳዊ መሥዋዕትን አለማቅረባችን ሌላውንም ጸሎታችንንም ከንቱ ማድረጋችን ነው:: ማቴ.9÷13፣ ማቴ.12÷6 «እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ÷ በዚያም ወንድምህ አንዳች በእንተ ላይ እንዳለው ብታስብ÷ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ÷ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ÷ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ::» ማቴ.5÷23 ሲል ጌታ ማስተማሩ መባን ትቶ መሄድ እንዲገባ ያደረገ ምሕረት ከመባው የበለጠ ትልቅ መሥዋዕት ስለሆነ ነው:: ከዚህ በኋላ የምናቀርበውንም መባና ጸሎት እግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጉ ይቀበልልናል:: እንደዚህ ዓይነት በዕ ጣንና በመባዕ ከምሕረት /ይቅር ማለት/ በኋላ የሚቀርብንም ጸሎት መሥዋዕት ስለሆነ ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ፊት ያሳር ጉታል:: ራእ.8÷3-5::

ሠ. <u>መሥዋዕትነት</u>:- ሰው ከዚህም በላይ እግዚአብሔርን በንጹሕ ኅሊናና በፍጹም ልብ ሲያገለግል ስንኳን የርሱ የሆነውን የዚህን ዓለም ገንዘብ ራሱንም ለእግዚአብሔር ለማቅረብ አይፈራም:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእርሱ ያደረገውን በማሰብ ይጸናልና:: «እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁሉ ሁኑ÷ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ::» /ኤፌ.5÷1-2/ የተባለውን

www.zeyeneta.com

በግሰብ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍጹም ፍቅር መሥዋዕት በመሆን ይገልጡታል። «ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል።» 1ዮሐ. 4÷18 እንዲል።

ስለዚህ ሰዎች በራሳቸው ላይ ወስነው ስለ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን «እውነትን እየመሰከሩና ጽድቅ እየሠሩ» የሚቀበሉት መከራ ራሱ መሥዋዕትነት ይባላል። ይህም /ክርስቲያኖች ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መሥዋዕት አድርጉ ማቅረብ/ የታዘዘ ነው። ቅዱስ ጴጥሮስ «በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኀዘንን ቢታገሥ ምስጋና ይገባዋልና። ኃጢአት አድርጋችሁ ስትጐሰሙ ብትታገሡ+ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ ስትጐሰሙ ብትታገሡ+ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምስጋና ይገባዋል። የተጠራችሁ ለዚህ ነውና፣ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሏልና።» /1ኛጴጥ.2÷19–21/ ሲል በመልእክቱ ያስተላለፈው በመሥዋዕትነትም ጌታችንን እንድንከተለው ነው።

ቅዱስ ጳውሎስም «እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ+ በመከራውም እንድካፈል+ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆን ልኝ+ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ።» /ፊል.3÷11/ በማለት ክርስቶስን መምሰል ራስን መሥዋዕት እስከ ማድረግ ድረስ እንደ ሆነ ገልጠልናል። በዕብ.11÷1–40 የተጠቀሰው የቅዱሳን ታሪክም በእምነት ድል መንሣታቸውን ተከትሉ የሚተርከው የተቀበሉትን መከራ ወይም መሥዋዕትነት ነው።

የመሥዋዕትነት መንገዱ ብዙ ነው። በቀጥታ በዓለም ከሚያስተምሩበት ገበታና ጉባኤ እየተያዙ፣ በመጋዝ የተተረተሩት፣ በሰይፍ የተቀሉት፣ በእሳት እንደ ሰም የቀለጡት፣ ለአናብስት የተጣሉትና.... በዚህ ዓይነት መንገድ መከራ እየታገሡ ስላ ሕዝቡ

አየጸለዩ ያለፉት ሁሉ ሰማዕታት ይባላሉ። ዓለሙን ንቀው የላመ የጣመ ላለመብላት፣ የሞቀ የደመቀ ላለመልበስ ገዳም ገብተው፣ ዳዋ ጥሰው፣ ጤዛ ልሰው፣ ድንጋይ ተንተርሰው፣ የቀን ሐሩሩን የሌሊት ቁሩን፣ ድምፀ አራዊትን ግርማ ሌሊትን ታግሠው ከአጋንንት ጋር ተዋግተው ዓለሙን ድል የሚነሡት ደግሞ ጻድቃን ይባላሉ።

ሌሎች መከራዎችንም በመታገሥ ራሳቸውን መሥዋዕት የሚያደርጉ በገዳም በበረሃ በዓለም በከተማ ያሉ ብዙዎች ናቸው። «ከእኔ ይቅል አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፣ መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፣ ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል÷ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።» /ማቴ.10÷37–39/ የሚለውን አምላካዊ ቃል መሠረት አድርጎ ከሁሉም የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ የሚያስቀድም ሁሉ መሥዋዕትነትን ከፈለ ሊባል ይችላል። መሥዋዕትነት ሁሉ ክብር አለው። ከብሩም እንደ መከራው ይለያያል። «ከኮከብ ክብር የኮከብ ክብር ይበልጣል።» 1ኛቆሮ.15÷41 ተብሏልና።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ አሥራ አንድ

እምነት

11.1. <u>ትርጉም:</u> –

እምነት በዓይነ ሥጋ ከመታየት፣ በልብ ከመታሰብ፣ በጆሮም ከመሰማት ወይንም በስሜት ሕዋሳት ከመመርመር በላይ የሆነውን፣ በቦታ ርቀትም በአካል ርቀትም /ረቂቅነትም/ ያለውን ይሆናል ይደረጋል ብሎ መቀበል፣ ማለት ነው። ከዚህም የተሻለ የቃላት ትርጓሜ መስጠት ይቻል ይሆናል። ፈላስፎችም በእነርሱ ፍልስ ፍናና ዕውቀት መሠረት የማይፈጸምን ነገር መቀበል የሚያዳ ግታቸው «እምነት» ምን እንደ ሆነ ስላልተገነዘቡ ብቻ ሳይሆን «ከሰው ዕውቀት በላይ የሆነ ነገር የለም።» የሚል እምነት ስላላቸው ነው።

እነርሱ በፍልስፍና እግዚአብሔርን ሊያውቁት የሚችሉት ሽክላ ሠሪውን ካወቀ በኋላ ነው። በምርምርና በፍልስፍና የሚገኝ ነገርም ሳይንስ /ጥበብ ሥጋዊ/ ይባላል እንጂ እምነት አይባልም። በሥጋ መንገድ ማረጋገጫ (proof) ያለውም ነገር ቴረም (theorem) ይሉታል እንጂ ከዚህ በላይ ስምም ክብርም የለውም። ይሁን እንጂ ፈላስፎች ይህን እንኳ ለማረጋገጥ ለመነሻነት እንደ «እምነት» የሚቀበሏቸው አሳቦች አሏቸው፣ እነዚህን ዓረፍተ ነገሮች መነሻና ቅቡል አሳቦች (Accepted assumptions) በእነርሱ አጠራር አግዚየምስ (Axioms) ይሏቸዋል፣ ያለ እነዚህም ማስረገጥ (prove) ማድረግ አይችሉም፣ ይህም ያለ እምነት መሥራት የሚችል ፍጡር እንደሌለ የሚያመ ለክት ነው።

ከቅዱሳት መጻሕፍት አንጻር እምነት ብዙ ዓይነት አገላለጽና አፈጻጸም ይኖረዋል። ይሁን እንጂ ዓለም ፈጣሪ፣ ሠራዒና መጋቢ፣

መነሻና መድረሻ፣ የተጀመረበትና የሚፈጸምበት አለው ብሎ መግን ዳግመኛም ለሚሠሩት ሥራ ሁሉ ዋጋ ከፋይ መኖሩን አውቆና አምኖ መሥራት በሁሉም ሰው ዘንድ ታምኖ ሊኖር የሚገባው ነው። ይህም «እስራኤል ሆይ፥ ስማ፥ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።» /ዘዳ.6÷4/ የሚለውን በማስታወስ ይህን አንድ አምላክ የማወቅ ግዴታ ነው። ይህን አንድ አምላክ እንደሚገባ ማወቅና ማመንም አንድ ነው። ኤፌ.4÷4። እምነት የሚገለጽበት ሥራ የመታመኛ መንገዱ ግን ብዙ ነው።

11.2. <u>እምነት ከመታመን አንጻር:–</u>

ፍጡር በፈጣሪው ካለው መታመን አንጻር የአንዱ እምነት ከሌላው ይለያል። ይህንም ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት አድርገን እንመለከተዋለን።

ሀ. የአጋንንት እምነት:– «እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፣ መልካም ታደርጋለህ፣ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።» ያዕ.2÷19 እንደሚል አጋንንት በአንድ እግዚ አብሔር ያምናሉ። በኋላም አካላዊ ቃል ከትድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ መወለዱን ያውቃሉ፣ እርሱ ወልደ እግዚአብሔር እንደ ሆነም መስክረዋል። «ኢየሱስ ሆይ፥ የእግዚ አብሔር ልጅ ከእንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን መጣህን?» ማቴ.8÷28 በማለት ተናግረዋልና።

ከዚህም ንግግራቸው ሁለት ነገሮችን እንረዳለን። የመጀመሪያው የወልደ እግዚአብሔርን ማንነት ማወቅና ማመን ሲሆን ሁለተኛው የሚፈርድባቸውንና የሚፈረድበትን ጊዜ ዐውቀው አየበደሉ መኖር። ምክንያቱም «ጊዜው ሳይደርስ» ብለዋልና። ከዚህ ቀጠል አድርገው ቢለምኑት እንደ ግይነሣቸው ዐውቀውና አምነው ለመኑት። «ታወጣንስ እንደ ሆነ ወደ እሪያው መንጋ ስደደን፣

www.zeyeneta.com

ብለው ለመኑት::» /ማቴ.8÷31/ እንዲል እንዲህ በጸሎት በልመና ማመናቸው ብቻ የሚደንቅ አይደለም:: ሰውም ቃለ እግዚአብሔርን መሠረት አድርጉ መኖር እንዳለበት ስለሚያውቁና ስለሚያምኑ መጽሐፍ ቅዱስ ለሚይዙ ሰዎችም ጥቅስ እየጠቀሱ ወደ እነርሱ መንግሥት ሰዎችን ሳይቀር ይስባሉ:: ስንኪን ለዕሩቅ ብእሲ ለጌታችንም ጥቅስ በመጥቀስ ፈተናን አትርበዋል:: ማቴ.4÷1-12::

ይህ ሁሉ የሚያመለክተን ለኢጋንንት እምነት አላቸው፡ ሰውቀት አላቸው፡ ነገር ግን ንስሐን አይቀበሉም፡ ጥፋታቸውንም አይሰሙም፡ የሚናገሩበት አፋቸው እንጂ የሚሰሙበት ጆሯቸው የእግዚአብሔርን ቃል አይቀበልምና::

ጌታችን ይህ እንደሚደረግ ዐውቆ በማቴ.13÷24-30 በምሳሌ ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሯል:: በንጹሑ ዘር ቢቃለ እግዚአብሔር ላይ እንክርዳዱን ዘርቶ ሰዎችን ከመንግሥተ እግዚአብሔር ለመለየት የሚጠቀምበት መሣሪያው እምነት መሆኑን የነገረን ከኢጋንንት እምነት እንድንጠበቅ ነው::

ለ. <u>የክርስቲያኖች እምነት:-</u>

የክርስቲያኖች እምነት በሚል ያነሣው ያለ ምክንያት አይደለም:: የክርስቲያኖች እምነት ከቀደሙት አበው ይለያል:: አበው አንድ እግዚአብሔር ብለው የሚያምኑ ቢሆኑም በገጽም አንድ ይሉ ነበር:: ክርስቲያኖች ግን «ወእንዘ ታጠምቅዎሙ በሉ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡ ስታጠምቋቸውም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በሉ» /ማቴ.28÷18/ ከሚለው የጌታችን ትእዛዝ እንደምንመለከተው አንድ እግዚአብሔር በስም በአካላት በግብር ሦስት የሚሉ ስለሆነ ከቀደሙት ይለያሉ:: ከዚህ አንጻር የሚለይ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የእነርሱ አምላክ ሊባል የማያፍርባቸው ወዳጆቹ ብዙ ናቸው:: ይሁን እንጂ በሰዎች ውስጥ ያለው መታመን ስለሚለያይ ሰው የሚሠራው የሃይማኖት ሥራም ይለያያል:::

ጌታችን በወንጌል «እንዲህ ያለ ታላላት እምነት በእስራኤል ስንኪን አላገኘሁም» /ማቴ.8÷10/ ሲል ማመስገኑ በመታመናችን መጠን እምነታችን እንደሚወሰን ለማጠየቅ ነው:: ስለዚህ የክርስቲያኖች እምነት:-

1. <u>በሥራ የሚገለጥ ነው:-</u> ማመናቸውን በመታመን ይገል ጹታል:: ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ከተሰበከና በልቡናው አምን ሆኗል ተደርጓል ብሉ ካመነ በኋላ «እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?» ማለቱ አምኖ አለመቅረቱን የሚያስረዳ ነው:: ወዲያውኑ ታምኖ ተጠምቋልና:: ክርስቲያኖች ሁሉ አምነው የሚቀሩ አይደሉም ታምነው በሥራ ይፈጽሙታል እንጂ:: በጥንተ ተፈጥሮም ሆነ በኋላ በሐዲስ ተፈጥሮ የተፈጠርነው በሃይማኖት መልካም ሥራ ለመሥራት ነውና:: «እንመላለስበት ዘንድ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን::» /ኤፌ.2÷10/ እንዲል እምነትም ከሥራ ከተለየ የሞተ ነው:: ያዕ.2÷20::

2. <u>ተስፋ ያለው ነው:-</u>

ያለ ተስፋ መኖርም አይቻልም፣ ማመንም አይቻልም:: ይሁን እንጂ ተስፋ ማለት እርግጠኛ የሚሆን ነገር ግን ጊዜው ያልደረሰለትና የሚጠበቅ ማለት እንጂ ላይሆን የሚችል በጥርጣሬ (Probability) ያለ ማለት አይደለም:: በተስፋ እግዚአብሔርን አምነው ደስ ያሰኙትን እግዚአብሔር አይረሳቸውም:: ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ላይ በሰፊው የዘረዘረው:: «ሃይማኖትስ ተይቅት ይእቲ ሕዘይሲፈዋ:: ህለው እለተአመኑ ተሰፈዎሙ ንዋየ ዘኢያስተርኢ:: ሃይማኖትስ ተስፋ ለሚያደርጋት ሰው ዋጋ በማ ሰጠት የተረጻች ናት፣ ቀድሞም የማይታየውን የማያልፍ መንግሥተ ሰማያትን ገንዘብ በማድረግ ጸንተው የሚኖሩ ነበሩ::» /ዕብ.11÷1/

www.zeyeneta.com

በሃለት ቀድሞ አምነው በተስፋ የጸኑትንና ስለ መንግሥተ ሰማያ ትም መነሪ የተተበለትን ቅዱሳን ይዘረዝራል።

❖ የአቤል እምነት፡- የእግዚአብሔርን ንጽሐ ጠባይስ በፍጹም በማመን የነበረና የሚሰጠውን መልስ ተስፋ በማድረግ መታመኑን ንጹሕ በግ በማቅረብ ስለ ገለጠ እግዚአብሔርም መሥዋዕቱን በሙቀበል መስክረለት። «ሞቶም ሳለ እስካሁን በመሥዋዕቱ ይናገራል።» ያለለት ለዚህ ነው።

❖ ሄኖክ፡- የደጉን የአቤልን መሞት አይቶ «ደግ መሆን ይገድላል» የሚል የሞኝ ብሂል ሳይናገርና ሞት በአቤል ብቻ በታወቀበት ተስፋውን ሰንቆ በሕግ በአምልኮት እግዚአብሔርን መፈለጉ ታላቅ እምነት ነው። እግዚአብሔርም ወደ ብሔረ ሕያዋን በመውሰድ እምነቱን መስክረለት። እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው ግን ሳይወሰድ መሆኑ ሊስተዋል ይገባል።

❖ አብርሃም፡- ሊቀበለው ያለውን ሥፍራ ከነሳንን አያውቀውም፣ ግን አልተጠራጠረም፣ እምኖና ተስፋ አድርጉ ሄደ። ሁለተኛም እርሱ ዘር ከቆረጠ ሚስቱም ደሟ ከደረቀ በኋላ ወንድ ልጅ ትወልዳላችሁ ሲለው እግዚአብሔርን ያለ ማመንታት ተቀበለ፣ ተስፋ አድርጉም በእምነት የሣራን ማኅፀን የራሱንም ሥጋ ተመለከተ። ሮሜ.4÷17-22። ሦስተኛም ተስፋ የተነገረለትን ልጁን ይስሐቅን መሥዋዕት አድርገህ አትርብ ሲባል አብርሃም «ከሞት እንኳን ሊያስነሣው ይቻለዋል» ብሎ ተስፋው ሳይፈጸም እንደማይቀር አመነ፥ ተስፋም አደረገ።

❖ ሣራም፡- ደሟ ደርቋል፥ ልምላሜዩ ጠፍቷል ሳትል በእምነት ዘርን ለመጽነስ ኃ.የ.ነን አገኘች። ቁ.11-12።

❖ የሙሴም ከእርሱም በኋላ ያሉት አበው እምነት የተመሰከረው በተስፋ ሩቁን በመመልከት ነው። «ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት መሆኑን

አስቧልና... ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቷልና።» ቁ.23-22 እንዲል። ይህን ተስፋቸውን ነበር ቅዱስ ጳውሎስ በቁ.13-16 የገለጸው። «እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ+ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና ዳሩ ግን ከሩት ሆነው እዩትና ተሳለሙት+ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ። እንዲህ የሚሉት ለእነርሱ የሚሆነውን አገር እንዲፈልጉ ያመለክታሉና። ያን የወጡበትን አገር አስበው ቢሆኑ ሊመለሱ ጊዜ በሆነላቸው ነበር፣ አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ ነገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም+ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና።» በማለት ገልጦታል።

አበውን ያስደነቀው ጌታ ግና በሥጋ ሳይገለጥ ነፍሳትም ወደ ግኔት ሳይመለሱ በተስፋ አምነው ሥራ መሥራታቸው ነው። ታድያ ግና በሕገ ልቡናና በሕገ ኦሪት ተስፋቸው የላቀ ሆኖ በእምነት ሥራ መሥራት ከቻሉ እኛ ክርስቲያኖች ራሱ በአካል አስተምሮን ተስፋውንም «ሥፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና... እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።» /ዮሐ.14÷1-4/ በማለት ነግሮን ሳለ ተስፋውን ተቀብለን የማናምን ከሆንን ምን ብልጫ አለን። «የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና» /ዕብ.10÷23/ እንዲል እጅጉን በማመን መታመን የሚጠበቅብን ክርስቲያኖች ነን። «የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ይጎባችኋል።» ዕብ.10÷36 በማለት ጽፎልናልና። ስለዚህ የክርስቲያኖች እምነት ተስፋ ያለው «እንደሚሆን እርግጠኞች በመሆንና ጊዜን በመጠበቅ የሚኖሩት የተስፋ ሕይወት» ነው።

ሐ. <u>የፍትር ሕይወት ነው</u>፡- የክርስቲያኖች እምነት መንጌል መቀበል ነው። መንጌል ደግሞ ከኦሪት ጥበልጣለች፣ ይህንንም ቅዱስ

www.zeyeneta.com

ጳውሎስ በሁለት ምሳሌ አትርቦታል።

1ኛ. በይስሐቅ በረከት፡– «ይስሐቅ ሊመጣ ስላለው ነገር ያዕቆብና ዔሳውን በእምነት ባረካቸው።» ዕብ.11÷20 ይላል። ይመጣ ዘንድ ያለው ነገር ምንድን ነው? ይስሐቅስ እንዴት ዐወቀው? በሮሜ.9÷10–13 ላይም «... ይህ ብቻ አይደለም÷ ነገር ግን ርብቃ ደግሞ ከአንዱ ከአባታችን ከይስሐቅ በጸነሰች ጊዜ÷ ልጆቹ ገና ሳይወለዱ÷ በጎ ወይም ክፉ ምንም ሳያደርጉ÷ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ÷ ለእርስዋ፡–ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት።ያዕቆብን ወደድሁ ዔሳውን ግን ጠላሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።» ሲል ታሪኩን በተሻለ መንገድ አትርቦታል። ሌላውንም በዕብ.12÷16 ላይ « ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ።» በማለት ገልጠታል። እነዚህን ታሪኮች በዘፍ.25÷21–34 እና በዘፍ.27÷27–29 እናገኛቸዋለን፣ ይሁን እንጂ ታሪኩን በአጭሩ አስቀምጠን ወደ ምሥጢሩ እንሂዳለን።

ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረው ገና ሳይወለዱ እግዚአብሔር ያዕቆብን መርጧል። ይህም አድልዎ አይደለም። እግዚአብሔር የነገርን ፍጻሜውን ከመጀመሩ በፊት፣ የዓለምን ኑሮና ፍጻሜ ከዓለም መፈጠር በፊት የሚያውቅ በመሆኑ፣ ከመወለዳቸው በፊት ያዕቆብ ምን ዓይነት ሰው እንደ ሆነ ዔሳውም ምን እንደሚሆን ያውቅ ነበር። «ዓለም ሳይፈጠር እንኳ አስቀድሞ ታወቀ።» 1ኛጴጥ.1÷21 እንዲል። ርብቃ ግን ጽንሱ በማኅፀኗ ይንዋወጥባት ስለነበረ በጊዜው «መከነ ራዕይ» ወደሚባለው ስትሄድ ቦታው መልከ ጼዴቅ የሚኖርበት ስለነበረ እግዚአብሔር በአፈ መልከ ጼዴቅ ታላቁ ለታናሹ እንደሚገዛ ነግሯት ነበረ።

እግዚአብሔር «ያዕቆብን ወደድሁ» ማለቱም ሕገ ነፍስን

/ብኩርና ምሳሌዋ ነበረችና/ ስለ መምረጡ÷ «ዔሳውን ጠላሁ» ማለቱም የዔሳውን ለሕገ ሥጋ ማድላት ማወቁን ለመናገር ነው። ዔሳው ከአደገ በኋላ አደን ሳይቀናው በተመለሰ ጊዜ ብኩርናውን ለያዕቆብ ሸጠ። ከዚህም በኋላ ዔሳው ለቤተሰቦቹ የማይታዘዝ ያዕቆብ ግን የሚታዘዝ ፈቃዳቸውንም የሚፈጽም ነበር። አባታቸው አርጅቶ እመርቃለሁ ባለ ጊዜም ርብቃ ለያዕቆብ ምክር መምከሯ ታዛዥ በመሆኑና እግዚአብሔርም የመረጠው እንደ ሆነ ስለምታውቅ ነው። ያዕቆብም በእናቱ ምክር መሠረት በመጠቀሙ ሥራው ሠመረለት አባቱም ፍጹም በረከትን ሰጠው።

ይህች ቀን በዘመነ አበው ትውፊት አባት ከመሞቱ በፊት ልጆቹን የሚባርክባት የተለየች ዕለት ናት። ከዚህ በኋላ ያዕቆብን ዔሳው እንዳይገድለው ጠሩ፣ ከብዙ ዘመንም በኋላ በእናትና አባታቸው ምክር መሠረት ዔሳው ያዕቆብን በአንድ ቀን ተዘርተን «በአንድ ቀን የታጨድን ነን።» በማለት ብኩርናውን መልሰልኝ ሳይል ታርቋል። ከታረቀ በኋላ ግን ልጆቹ ቀድሞ አላግባብ ሸጥከ አሁን ደግሞ የማይሆን ዕርቅ ታረቅህ ብለው በመቆጣት ሰይፍ አንሥተው አባታቸውን መንገድ መሪ አድርገው ያዕቆብን ለመዋጋት ሄዱ። የአካባቢው ሰዎችም ያዕቆብን ይወዱ ነበርና ወንድሙ ጦር አሰልፎ መምጣቱን በነገሩት ጊዜ ሁለት መቶ ቤተሰቦቹን ይዞ አራት በር ባላት ቤት ሃምሳ ሃምሳውን በእያንዳንዱ ገጽ አሠልፎ ጠበቀው። ይሁዳ ባለበት በር በኩል ዔሳው ልቡ ለቀስት ተመችቶ ታየው። ይሁዳም የአባትን ታላቅ ወንድም መግደል አባትን መግደል ነው በማለት አነጣጥሮ ለአባቱ ሰጠው፣ ያዕቆብም ዔሳውን ገደለ፣ ጦሩም ተበተነ። ከዚህ በኋላ የዔሳውን ዘሮች ሲያስገብሯቸው ኖረዋል። ታሪካቸውም እንዲህ ይደመደማል። ኩፋ.26+47–48። አስቀድሞ የተመለከተው ታድያ ምንድን ነው? ከታሪኩስ ጀርባ ያለው ምሥጢር?

www.zeyeneta.com

ዘመጀመሪያ ያዕቆብ የኢሳውን ብኩርና መግዛቱ በእስራኤል ተስፋ አነሳሳብ የመግባታቸው ምሳሌ ነው። ኤሳው የእስራኤል ያሰ ቡብም የአሕዛብ ምሳሌዎች ናቸው። በኋላም ያዕቆብ ፍጹሙን በረከት ከአባቱ መቀበሉ፣ ለሕገ ነፍስ የሚያደላ በመሆኑ ወልደ እግዚአብሔር ከእርሱ ልጆች ሰው ይሆን ዘንድ አስቀድሞ እግዚ አብሔር ግብሩን ዘሙቆ የመረጠው ስለሆነ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ያዕቆብ የጌታ፡ ከያዕቆብ ጋር ያሉት የምእመናን፣ ዔሳው የዲ ያብሎስ፣ ከዔሳው ጋር ያሉ የአጋንንት+ ማኅፈድ የመስቀል፣ ቀስት የሥልጣን እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። በድጋሚም ያዕቆብ የታላቁ ሊቅ የቂርሎስ፣ ከእርሱ ጋር ያሉ ሁለት መቶ ሰዎች የሁለት መቶው ኢዲስ ቆጸላት፣ ዔሳው የንስጥሮስ ምሳሌዎች ናቸው።

ዳግመኛም ታላቁ ለታናሹ ይገዛል የሚለው ከያዕቆብ ቤት ከይሁዳ ወገን የሚመለደው ጌታ ንጉሠ ሰማያት ወምድር ስለሆነ ሁሉንም የሚገዛ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ታሪክ በምሥጢር ያመጣው የወንጌልን በረከት የተቀበለው ያዕቆብ ከዔሳው የበለጠው በተቀበለው በረከት በወንጌል ነው። ይህም የወንጌልን ታላቅነት አስቀድሞ ይስሐቅ በውቆታል ለማለት አምጥቶታል።

2ኛ. በያዕቆብ በረከት፡- «ያዕቆብ ሲሞት በእምነት የዮሴፍን ልጆች እያንዳንዳቸውን ባረካቸው።» ዕብ.11+21። ታሪኩ ዘፍ.48+15 ላይ ተገልጿል። ያዕቆብ እጆቹን አመሳቅሎ የባረካቸው ወንጌል ተገ ልጦለት አስቀድሞ አይቶ በሚበልጠው የመስቀል በረከት ሲባር ካቸው ነው።

እነዚህን ሁለት ግስረጃዎች ከዚሁ ምዕራፍ አስረጅ አድርገን የጠቀስነው አሪት ከመሠራቷ በፊት፣ ከአሪት በኋላ የምትሠራ ወንጌል ለአበው የተገለጸችላቸው ወንጌል ታላቅ ስለሆነች መሆኑን ለማስረዳት ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ጻፈው ነው።

የወንጌል ታላቅነት ምን ላይ ነው? የሚለውን ስናነሣ የፍቅር ሕግ ስለሆነች ነው። «ወዓዲ እንተ ትኄይስ ፍናተ እሜ ሀረክሙ፣ የምትበልጠውን መንገድ አሳያችኋለሁ 1ኛቆሮ.12+31 ላይ እና 1ኛ ቆሮ.13ን በሙሉ ስለ ፍቅር የጻፈው ፍቅር የምትበልጥ በመሆኗ ነው። ጌታችን ስለ ሰው ፍቅር ሰው ሆነ፣ ሞታችንንም ሞቶ ሕይወትን ሰጠን፣ የሠራልንም የእምነት ሕግ የፍቅር ሕግ ናት። «ጠላታችሁን ውደዱ፣ የሚረግሟችሁን መርቁ፣ ስለሚያ ሳድዷችሁ ጸልዩ፣ ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታው ግራህን ስጥ፣ ከእንተ ለሚበደር አትከልክል፣ መጐናጸፊያህን ለሚወስድ ቀሚስህን ጨምር ለት» ትላለችና።

ስለዚህ የክርስቲያኖች እምነት የፍቅር ሕይወት ነው እንጂ በቃል ብቻ የሚነገር በጾሮም የሚሰማ ብቻ አይደለም። «ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም» 1ኛዮሐ.4+7 ይላልና ፍቅራ ቸውም በሥራ የሚገለጥ ነው። «ልጆች ሆይ+ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት አንዋደድ።» 1ኛዮሐ.3+18 በሚል ታዝዘዋልና።

ቅዱስ ጳውሎስም በ1ኛቆሮ.12+31 «የሚበልጠው መንገድ ፍቅር ነው» ብሎ በም.13 ላይ የፍቅርን ታላቅነት አስረድቶ የደመደመው «ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።» 1ኛቆሮ.13+13 በሚል ነው። ወንጌል እምነት፣ ተስፋና ፍቅር ናትና። የምትፈጸ መው የምትተገበረው በፍቅር ስለሆነ ፍቅርም ከሌለ ሌሎቹ ስለ ማይኖሩ ፍቅር ይበልጣል አለው። እምነት የማናየውን ነገር የሚያስረግጥ ነው /ዕብ.11+1/ ያላየናትን ርስት መንግሥተ ሰማያት ወርሰን ያላየነውን ክብሩን አይተን ያመንነውን አግኝተን እንፈጽ ማለን፣ ተስፋ እናገኘዋ ለን፣ እንደርስበታለን ብሎ ማሰብ ነው። ተስፋችንም መንግሥተ ሰ ማያት ናት። እርሷንም ወርሰን

www.zeyeneta.com

ተስፋችን ይፈጸማል። ፍቅር ግን እግዚአብሔር ነው። እርሱ ግን ዘላለም ይኖራል። ስለዚህም ፍቅር ትበልጣለች አለ።

11.3. <u>ማጠቃለያ</u>

በዚህ ምዕራፍ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ ከአዳም እንሥቶ እስከ እርሱ ዘመን ማለት እስከ ብሉይ ኪዳን ፍጻሜ ያሉትን በማን ሣት ዕብራውያንን የሚወቅሰው ያለ ምክንያት አይደለም። እነዚህ ምሳሌውን አይተው ትንቢቱን ሰምተው ነፍሳት ከሲኦል ሳይወጡ በእምነታቸው በነበራቸው ተስፋና ባሳዩት ፍቅር «እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም» ተብሎ እስኪ መሰከርላቸው ድረስ ከታመኑ፣ ይልቁንም እናንተ የምሳሌውን አ ማናዊ /አካላዊ ቃልን/ የትንቢቱን ፍጻሜ ኢየሱስ ክርስቶስን የአፉን ትምህርት የእጁን ታምራት እያያችሁ ስለ ምን አታምኑበትም፣ ስንኳን እርሱ በደቀ መዛሙርቱ ጥላና በጨርቃቸው ድውያን መፈወሳቸው ሙታን መነሣታቸው፣ በአንድ ልሳን ይናገሩ የነበሩ 120 ቤተሰቦች በ72 ልሳን መናገራቸው፣ እንድታምኑ አይበቃች ሁምን? እነርሱ ያለ ምንም የተስፋ ፍጻሜ ይህን ያህል ካመኑ እኛ የአባቶቻችን ተስፋ የእግዚአብሔር ሰው የመሆን ቀጠሮ ተፈጽሞ፣ ኃጢአት ተደምስሶ፣ ካሣ ተመልሶ፣ ነፍሳት ከሲኦል ወደ ገነት ተሻግረው ሳለ ስለ ምን አናምንም? ለማለት ለመውቀስ ለመገሰጽ የተናገረው ነው። ይኸውም «እነዚህም ሁሉ በእምነታቸው ተመሰክ ሮላቸው ሳሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል አላገኙም÷ ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና» ዕብ.11÷39-40 በማለቱ ታውቋል።

እኛም የዛሬ ክርስቲያኖች ተስፋችንን ጠንቅቀን ዐውቀን እንደ አበው ግብዝነት በሌለበት እምነት፣ በንጹሕ ኅሊናና በበጐ ፈቃድ በሚፈጸም ትእዛዝ ለእግዚአብሔርና ለሰው ያለንን ፍቅር በሥራ ልንተረጉመው ይገባል። በዚህ ሕይወት እንኳን ባንኖር ወደዚህ

በፍጹም ተስፋ ላይ በተመሠረተ የእምነትና የፍቅር ሕይወት ለማደግ ራሳችንን ማሠልጠን ይጠበቅብናል። «የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ኅሊና ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው።» 1ኛጢሞ.1÷5 በሚል ታዝዘናልና።

www.zeyeneta.com

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

ተስፋ ወንጌል–መንግሥተ ሰማያት

ቅዱስ ጳውሎስ በመልእክቱ ማጠቃለያ የሚገልጽላቸው ክርስቶስን በማመን የሚገኘውን ጥቅም ነው። የክርስትና ተስፋ ምንድን ነው? በጊዜው ዕብራውያን በሮማውያን ቅኝ ግዛት ሥር ወደቀች ብለው የሚጨነቁላት የእስራኤል ከተማ ኢየሩሳሌም ናትን? የሚጠበቀውስ ግዛትና ዘላለማዊ መንግሥት ዕብራውያን የሚያስቡት ሮማውያንን በጦር አስለቅቆ ዓለሙን ለእስራኤል የሚያስገዛ ነውን? አይሁድ ወይም ዕብራውያን ለእነዚህ ጥያቄዎች በጎሊናቸው ያስቀመጡት መልስ ምድራዊ ስለሆነ ጌታችንን መቀበል ተስኗቸዋል። ስለዚህ ተስፋ ወንጌል እነርሱ ከሚያስቧት ምድራዊት ኢየሩሳሌም ምድራዊት ጽዮን የምትበልጥ መሆን ለመናገር አምጥቶታል።

12.1. ገነት፡– ቅዱሳት መጻሕፍትን ስንመለከት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከፈጠረ በኋላ አዳምን በ40 ቀኑ ሔዋንን ደግሞ በ80 ቀኗ ወደ ገነት እንዳስገባቸው ይናገራሉ። ዘፍ.2÷8፣ ኩፋ.4÷9። አዳም ከበደለ በኋላ ደግሞ ከገነት እንደ ተባረረ እግዚአብሔር ገነትንም በምትገለባበጥ ሰይፍና በኪሩቤል እንዳስጠበቃት ተጽፎልናል። ዘፍ.3÷24። በኋላም ጌታችን በመዋዕለ ሥጋዌው ተገልጦ ካስተማረና ፍጹም ካሣ ሊያስመልስልን በተሰቀለ ጊዜ በቀኙ የተሰቀለውን ሽፍታ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» ብሎታል። ሉቃ.23÷43።

ከላይ እንደ ተመለከትነው መረጃዎቹ የሚያመለክቱት ገነት «ዓለመ ጻድቃን» መሆኗን ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ተከላት የተባለች አዳምና ሐዋን ከበደል በፊት የነበሩባት፣ ከበደል በኋላ ሊገቡ የተባረሩባት፣ በኋላም ጌታ ራሱ «ከእኔ ጋር በገነት

ትሆናለህ» በማለት እርሱ የሚኖርባት፣ እንደ ፈያታዊ ዘየማን ተነ ሣሕያን /ንስሐ የሚገቡ/ የሚኖሩባት ንስሐ የማይገቡ ፈያታዊ ዘጸጋምን የመሰሉ የማይገቡባት ናት።

ገነት ዓለመ ጻድቃን ስለ ሆነች ክርስቲያኖች ዮሴ በሞተ ሥጋ ከዚህ ዓለም በሚለዩበት ጊዜ መካነ ዕረፍታቸው ገነት ናት። ዲያብ ሎስም በጽሎም ገጹ የሰዎችን ነፍስ ከሥጋ መለየቱ፣ በኋላም ሥጋን በመቃብር ነፍስን በሲኦል መቆራኘቱ ቀርቶ እንደ ቅዱስ እስጢፋኖስ የበቁት ምሥጢረ ሰማያትን እየተመለከቱ ያልበቱትም ቢሆኑ በመኳነ ቅዱሳን ነፍሳቸው ከሥጋቸው የምትለይና ወደ ገነት የምትሄድ በመሆኑ አስፈሪነቱ ስለ ቀረ ከሥልጣኑም ስለ ተሻረ «ሞት ሆይ÷ መውጊያህ /ኃጢአት/ የት አለ? ሲኦል ሆይ÷ ድል መንሣትህ የት አለ?» የምንል ሆነናል። 1ኛቆሮ.15÷54። የሞት አስፈሪነቱም ስለ መቅረቱ ቅዱሳን ሞትን በመናፈቃቸው ይታወቃል፡ የሚሄዱት ወደ ክርስቶስና ከእርሱ ጋር ወደሚኖሩበት ማኅበረ ጻድቃን ነውና። «ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ÷ ከዙሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና» ፊል.1÷24 እንዲል። ቅዱስ ጳውሎስ በትምህርትና በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በአካለ ሥጋም ወደ ገነት ተነጥቆ ነበር። ሦስተኛው ሰማይ /ዓለመ መላእክት/ ደርሶ ሲመለስ በገነት አሳርፈውት ስለ ነበር እጅግ ናፈቃት። 2ኛቆሮ.12÷1–6።

ቅዱስ ጳውሎስም ተስፋችንን እያነሣ የሚነግረን እንደ ዕብራውያን ስለ ምድራዊ ከተማ ስንጨነቅ ሰማያዊት የተባለች ገነትን በአጸደ ነፍስ እንዳናጣት ነው። አምላካችን እግዚአብሔር «ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ አሰጠ ዋለሁ።» ራእ.2÷7 ማለቱን አስበን ለምግባረ ሃይማኖት መነሣሣት ይጠበቅብናልና።

12.2. መንግሥተ ሰማያት፡– ከሰባቱ ሰማያተ ብርሃን ውስጥ

www.zeyeneta.com

አንዷ ናት። እነዚህም ሰባቱ ሰማያት ባለማለፍ አንተው የሚኖሩ ናቸው። «ሰማይና ምድር ያልፋሉ» ያለው ጌታ በሰለተ ሰኑይ /ሰኞ/ ከእሳትና ከውኃ የተፈጠረውን፣ በነፋሳት አለማድ የቆመውንና ብጽብጽ ውኃ ሃናስ የሰፈረበት፣ ከበታቹም ግዙፉን ብርሃናት እንደ ፋናስ የተሰቀሉበትን ነው። ሰባቱ ሰማያት ግን ብርሃናውያት ስለሆኑና ግዘፍም ስለሌለባቸው ማለፍ የለባቸውም፡ መንግሥተ ሰማያትም ከእነዚህ አንዷ ናት። ቅዱስ ጳውሎስ በ2ኛቆሮ.12+2 ላይ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጥቁ ነበር ያለው ዓለመ መላእክት የሚባሉትን ኤረር፣ ራማና ኢዮርን አይቶ ስለ ተመለሰ ነው። ብዙዎች መሆናቸውን የቀደሙት ነብያትም ተመልክተዋል። ሕዝ. 1+1፣ ኢሳ.13+3። ቅዱስ ዳዊትም «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ።» መዝ.18+1፣ «እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት።» መዝ.148+1 ብሏል።

መንግሥተ ሰማያት ኢየሩሳሌም ሰማያዊትም ትባላለች። «እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳናት ናቸውና። ከደብረ ሲና የሆነችው አንዲቱ ለባርነት ልጆችን ትወልዳለች+ እርስዋም አጋር ናት፣ ይህችም አጋር በዓረብ ምድር ያለችው ደብረ ሲና ናት፣ አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌምን ትመስላለች+ ከልጆችዋ ጋር በባርነት ናትና። ላይኛዪቱ ኢየሩሳሌም ግን በነጻነት የምትኖር ናት እርስዋም እናታችን ናት።» ገላ.4+24-26 እንዲል። «ላይኛዪቱ ኢየሩሳሌም» ያላት መንግሥተ ሰማያትን ነው።

ታድያ መንግሥተ ሰማያት ተስፋ ወንጌል ናት የምትባለው እንዴት ነው? የሚል ጥያቄ ልናነሣ እንችላለን። ከላይ ገነት ዓለመ ጻድቃን እንደ ሆነች ተመልክተናል። ይሁን እንጂ ገነት በአጸደ ነፍስ የሚኖሩባት ዳግመኛም የዚህ ዓለም አካል እንደ መሆንዋ ሰማ ይና ምድር በሚያልፉበት ሰዓት የምታልፍ ናት። ስለዚህ ሌላ

"ንኑሃችን የእግዚአብሔር ከተማ ያስፈልገናል። ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ዕብ.13፡13 ላይ «እንግዲህ ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ከክፈሩ ውጭ እንውጣ በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና+ ነዝ: ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን።» ያላት መንግሥተ ሰማያትን ነው።

ጌታችንም በዘንጌል «በኢየሩሳሌም አትግቡ+ የንጉሥ ከተማ ናትና» ያላት በትኝ ግዛት ሥር የነበረችውን ምድራዊቷን ሳይሆን የተዘጋጀቺ ከተማ ከዚህ ዓለም ማለፍ በኋላ የምትሰጠን ተስፋችን ስለሆነች ነው። «ይህ ሁሉ እንዲህ የሚተተል ከሆነ+ የእግዚአ ብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያሰቸኩላችሁ+ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል፣ ነገር ግን ቃድት የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን።» 2ኛጴጥ.3+11-13።

በእርሱ ያንተሳሰቱትን ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና ተሰፋ እንደ ሌላቸው እንደ ሌሎቹ አትዘኑ በማለት የተሰሎንቄ ሰዎችንም መክሯል። 1ኛተሰ.4+14 ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ የዕብራውያን መልእ ክቱ ላይ መንግሥተ ሰማያትን ከደብረ ሲና ጋር እያነጻጸረ በሚረዳን ውበቷንና ክብሯን ሁበቷንም ይናገራል።

በዚህ በዕብ.12+18-29 የተገለጸው ይህን ምሥጢረ መንግ ሥተ ሰማያትን ማሳየት ነው። «... ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል+ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም+ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት+ በሰማያትም ወደ ተጻፉ /በልበ አምላክ ወደ ታወቁት/ ወደ በኩራት ማኅበር /በኩር በተባለ ጌታ አምነው ወደ ዝቡት ከአቤል እስከ ምጽአት ወደሚነሡት የጻድቃን ማኅበር/+ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን

www.zeyeneta.com

ወደ እግዚአብሔር÷ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች÷ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሚሆን ወደ ኢየሱስ÷ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል::» ይለናል:: ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ምድር ሰው በጌታችን አምኖ ከተጠመቀ ሥጋውን ደሙን ከተቀበለ መንግሥተ ሰማያትን እንደሚያገኛት ለመናገር ያመጣው ነው::

ከፍ ብሎ ሐዋርያው እንደ ጠቀሰው ደብረ ሲና ላይ እንኳን ሕዝበ እስራኤል አሮንና ሖርም አልወጡባትም:: ሕዝቡ እግረ ደብሩንም አልነኩም፣ የሚነካ ቢኖር ሰውም ሆነ እንስሳ ተወግሮ እንዲሞት ታዝዞ ነበርና:: ዘጸ.19÷18:: መንግሥተ ሰማያትን ግን በጌታችን ካላመኑ አሕዛብ፣ አምነውም ከካዱ ሰዎች እንዲሁም ከኃጥአን በቀር የምንዋጃት ነን:: ወደ እርስዋም ከገቡ በኋላ ፍርሃትና ድንጋጤ የለም፣ ይልቁንም አሁን ኃጢአትን ድል እንነሣት ዘንድ እግዚአ ብሔርን መፍራት ይገባናል እንጂ:: «ስለዚህ የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ:: አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት /ፈታሔ/ ነውና::» እንዲል ዕብ.12÷28-29::

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ርስታችንን ሲሰጠን የታመነ ቃሉን የማያጥፍ አምላክ ነው:: «ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ÷ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፣ የአምላኬን ስምና የአምላኬን ከተማ ስም÷ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን÷ አዲሱንም ስሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ:: መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ::» ራዕ.3÷11-14 ተብሎ ተጽፎ ልናልና::

12.3. ለተስፋችን እንድንበቃ ምን እናድርግ?

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ ለተስፋችን እንድንበቃ የመከረንም ምክር አለ፣ እንድንፈጽመው የታዘዝነው፣ እንድንጠበቅበትም የተነገረን ነገር አለና እነርሱን እንመለከታለን::

ሀ. የጸናውን ማሰብ:- አስቀድሞ በ12÷1-2 ላይ ጌታችንን አብነት አድርገን በፊታችን ያለውን ኑሯችንን በትዕግሥት እንድን ዝዝ ከመከረን በኋላ «በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ÷ ከኃጢ አተኞች በደረሰበት መቃወም የጸናውን አስቡ::» ይለናል:: አስቀድሞ በምዕራፍ 11 ላይ የጸኑትን ቅዱሳን ያነሣበት ዐቢይ ምሥጢር ለዚህ ነበር:: «እንግዲህ ምን እላለሁ? ስለ ጌዴዎንና ስለ ባርቅ ስለ ሶምሶንም ስለ ዮፍታሔም ስለ ዳዊትና ስለ ሳሙኤልም ስለ ነብያትም እንዳልተርክ ጊዜ ያጥርብኛልና:: እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ÷... ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፣ ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእሥራትና በወኅኒ ተፈተኑ፣ በድንጋይ ተወገረው ሞቱ÷ ተፈተኑ÷ በመጋዝ ተሰነጠቁ÷ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ÷ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ሄሩ፣ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ÷ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ::» ዕብ. 11÷32-38:: እነዚህን ቅዱሳን ገድላቸውንና ተአምራታቸውን ስን መለከት ተጋድሏቸውን እያሰብን በትዕግሥት መከራ እንድንቀበልና እንድንጸና ያደርገናል:: ጌታም «ድል የነሣውን» ያለው ቅዱሳንን አብነት አድርጉ ጸንቶ ታግሦ መከራ ተቀብሎ ያሸነፈውን ለማለት ነው::

ለ. ቅጣትን መቀበል:- «ኃጢአት° የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፣ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም::» 1ኛዮሐ.1÷8 እንዲል

www.zeyeneta.com

ቅዱስ ዮሐንስ በየትኛውም ደረጃ ብንሆር እግዚአብሔርን ወሙተንም ሆነ ሳናውቅ ልንበድለው እንችላለን። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ለንስሐ እንድንፋጠንና ወደ እርሱ በፍጥነት እንድንመለስ አባት ልጁን በሚቆ ነጥብት ሆኖቅር ቁንጮዬ ይቆንጥጠናል፡ ይቀጣናል። እንደ እውነቱ ከሆነ ሰው እንደ መሆናችን እንበድላለንና ቅጣት የሚያንሰን አይ ሆንም። ይህን እንጂ አንዳንዶቻችን ስለ ምን ይህ ደረሰብን የምንል ከሆነ ፈያታዊ ዘጹጋምን እንመስለዋለን፡ ይህ ደግሞ እግዚአብሔርንም እንድንዘልፍ ያበቃናል።

ነዘርስቲያን ግን የተጠራለትን ዓላማ አስተውሉ እንደ ፈያታዊ ዘየማን ቅጣቱንና ተግሣጹን ተቀብሎ «ጌታ ሆይ፡ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አስበኝ» ይላል፡ እግዚአብሔርም ያስበዋል። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ «ለመቀጣት ታገሡ፡ እግዚአብሔር እንደ ልጆች ያደርግላችኋልና፡ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው? ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኗልና ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም።...ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፡ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።» ዕብ.12÷6-11 እንዲል።

ሐ. ወንጌልን መፈጸም፡- ወንጌል ዘርፈ ብዙ ሕገ ትሩፋት፣ ሕገ ተፋቅሮ በመጨረሻም ሕገ ፍጽምት ናት። ጌታችን የሠራት ያስተማራት፣ ሐዋርያት የሰበኳት፣ ሰማዕታትና ጻድቃን በደም ያተሟት የመንግሥተ ሰማያት ዓላማ መግቢያ በር ናት። ጌታችን ራሱ ቀሮን መንገድ ጠባብ በር ብሏታል። ማቴ.7÷13። እርሷንም ያልፈጸመ ቤቱን በአሸዋ በድቡሽት ላይ የሠራ ሞኝ ሰውን ይመስላል፣ ዝናብም ጉርፍም ነፋስም ገፍተው ይጥሉታል፡ አወዳደቁም ይከፋል /ማቴ.7÷28/ በማለት በኑፋቄ፣ በክንቱ ወሬ፣ በሐሜት፣ በፈቃድ ሥጋዊና በምድራዊ ባለሥልጣን እንዳንከድ ጌታ አስቀድሞ መክሯል።

ቅዱስ ጳውሎስም ይህን አራትን ካልተቀበሉት ጋር በማነጻጸር በአጭሩ ይጽፍልናል። «ለሚናገረው /ለሙንጌል/ እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ፡ እነዚያ በምድር ላስረዳቸው /ለሙሴ/ እምቢ ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፡ ከሰማይ ከመጣው ፈቀቅ የምንል እኛስ እንዴት እናመልጣለን?» ዕብ.12÷25 በማለት እንድንፈጽም ይጋብዘናል።

መ. ከክፉ ምግባራት መጠበቅ፡-

ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ ምዕራፍ በአጽንዖት ከሚያስተምረን አንዱ ከዚህ ነገር መጠበቅ ነው። ክፉ ምግባር የክፉ ሞት ምንጭ ከእግዚአብሔርም መንግሥት የሚለይ ነው። ጌታችን በዕለተ ምጽአት ለሰይማንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ። የሚላቸው ኃጥአንን ወይም በጉውን ምግባር ያልፈጸሙትን ነው። በጉ ምግባር አለመፈጸም ይህን ለመባል የሚያበቃ ከሆነ ይልቁንም ክፉውን ምግባር ለሚሠሩ ምን ያህል ይጸናባቸው ይሆን? «አስቀድሞ በእኛ የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?» 1ኛጴጥ.4÷18 እንዲል።

ቅዱስ ጳውሎስም የተናገረው ይህ እንዳይደርስብን ነው። «የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጐድለው፡ ብዙዎቹም የሚረክሱበት እንድ መራራ ሥር ወደ ላይ በቅሎ እንዳያስጨንቅ፡ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ፡ ወይም ስለ አንድ መብል በኩርንቱን እንደ ሸጠ እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን ተጠንቀቁ። ከዚያ በኋላ እንኳ በረከቱን ሊወርስ በወደደ ጊዜ እንደ ተጣለ ታውቃላችሁና በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሐ ሥፍራ አላገኘምና።» ዕብ.12÷15-17። በዚህ መልእክት ውስጥ ልናስተ ውላቸው የሚገቡን ነጥቦች :-

- መራራ ሥር

www.zeyeneta.com

– ሴሰኝነት

– እንደ ዔሳው ለዓለም የሚመች ሰው የሚሉት ናቸው።

ሴሰኝነት እጅግ መራራ ሥር ነው። ሣንዱንም ቅርንጫፉንም እንዲመር የዛፉ ፍሬው እንዳይጣፍጥ የሚያደርግ ነውና ክፉ ሥር አለው። የኃጢአት ቀላል ባይኖረውም ሁሉንም ምግባራት የሚደመስስ ከጸጋ ሁሉ የሚያራቁት ዋናውና ክፉ ምግባር ሴሰኝነትና ዝሙት ነው። «ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል። ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።» 1ኛቆሮ.6+18–20 እንዲል።

ሌላው እንደ ዔሳው ለመብል፣ ለመጠጥ፣ ለክብር፣ ለሥልጣንና በዓለም ለሚገኘው ዝና በመጨነት የተሳጠንን ዘብቱ መንፈስ ቅዱስ ማቅለል ነው። ታሪኩ በምዕራፍ 11 እንደ ተጠቀሰው ዔሳው በወንድሙ ቀስት የሞተው መጀመሪያ በዘጌቱ መንፃው አለቦ ብኩር ናውን ራሱ አቀለለው ሽጠውም። ዘፍ.25+27–34። በኋላም ከታሪቁ በኋላ ተቆጥቶ በሥጋ መንገድ ሥራዊት ከትቶ ወንድሙን ያፅቆብን ለመግደል ሄደ፤ ነገር ግን ራሱ ሞተ ተክታዮቹም ቀሳደጹ እንጂ አሳቡ ሊፈጸም አልቻለም።

ይህንም ያመጣው በረከቱንም ድጋሚ ያዕቆብ በመሰደበት ጊዜ ምርር ብሎ ቢያለቅስም እንባው ያለ ጊዜው የተደረገ ነውና ሊመል ስለት አልቻለም። በተራበ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ማልቀሱንና ወደ አምላኩ መመልከቱን ትቶ ወደ ወንድሙ ምስር ወጥ ተመልክቷል። ሀብቱን ካጣ በኋላ ያለቀሰው ሊትሲ ዋጋ ኢላሰገኘለትም። ቅዱስ ጳውሎስም «በእንባ ተግቶ ፈንም ቢፈልገው ለንስሐ ሥፍራ አላገኘምና።» ያለው ለዚህ ነው። ሰው ንስሐው አልሠምርለት ሲል

እንደገና ፍሬም ጥፋትን ወደሚያመጣ ወደ ሲላ የሥጋ መንገድ ይንዛል። ስለዚህ ለዓለም የሚመች አሳብ ያለው ሰው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረው «መራራ ሥር» እንደ በቀለበት ተገንዝቦ ሃይማኖቱን ሳያስከዳውና ፈጽሞ ከእግዚአብሔር ጎበረት ሳይለየው በንስሐ ራሱን ማደስ ይጠበቅበታል።

አሁን አሁን አንዳንድ ሰዎች ሰውነታቸው የሚያሻውን ምኞት ሁሉ ቤተ ክርስቲያን እንድታሟላላቸው ይፈልጋሉ። ችግሩንም የቤተ ክርስቲያን አድርገው ሲናገሩና ቤተ ክርስቲያን እንድትታደስ ወይም እንድታድግ ያስፈልጋል ሲሉ ይሰማሉ። በውኑ የቤተ ክርስቲያን እድገት የሰዎችን ሥጋዊ ምኞትና ድሉት ማትረብ ነውን? በሥጋችን ውስጥ የሠለጠነውንና ቴክኖሎጂ የወለደውን ማግበስበስ ቤተ ክርስቲያንን ያሳድጋልን? በውኑ ቤተ ክርስቲያንስ መንፈሳዊት ናት እንጂ ቁሳዊ ናትን? የቴክኖሎጂ ውጤትን ሁሉ የምታግበሰብስ የተ ሠራውንም በዓይነት የምትሰበስብ ምድራዊት ቤተ መዛግብት ናትን? እነዚህን ቁሳቁስ እቹ ነን ወይስ ቤተ ክርስቲያን ናት የምትፈል ጋቸውን ራሳችንን ልንመረምር በውስጣችን ያለውን የሰውነታችንም አዲስ መሻት ልናስተካክል የበቀለውንም ክፉ ሥር ከነሰንኮፉ ነቅለን ልንጥል ያስፈልጋል። ካለበለዚያ በምንባትትበት ጊዜ ለንስሐም ሥፍራ ሳናገኝ እንችላለን፤ ንስሐም ስጦታ ነውና። «ምናልበት እግዚአብሔር እውነትን ያውቁ ዘንድ ንስሐን ይሰጣቸ ዋልና...» 2ኛጢሞ.2+26 እንዲል።

ስለዚህ ከክፉ ምግባራት መጠበቅ አለብን። ቅዱስ ጳውሎስ ባዘዘ ምልእክቱ «ስለዚህ የሳሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች አቅኑ፤ ያንከሰውም እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ+ ለእግራችሁ ቅን መንገድ አድርጉ። ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ፤ ትቀደሱም ዘንድ ፈልጉ+ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።» ዕብ.

12+12-14 እንዲል እግዚአብሔርን ማየት እንዲቻለን እንመለሱ+ ያነከሰነው እንፈወስ ዘንድ ለእግራችን ቅን መንገድ እናድርግ፣ ሰላምን እንከታተል+ ቅድስናንም ፈቃደ ነፍስን በመሥራት የጌተ ክርስቲያንን ድምፅ በመስማት እንፈልግ።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ዋኖቻችሁን አስቡ

ቅዱስ ጳውሎስ መልእክቱን የሚደመድመው ምግባራት ሠናያትን እንዲፈጽሙ በማዘዝ ነው። ከእነዚህም ውስጥ በተደጋጋሚ የሚገልጸው ለምዕራፉ መነሻ ያደረግነውን ነው። በየፈርጁ እንመልከታቸው።

ሀ. ዋኖችን መርዳት፦ ቅዱስ ጳውሎስ ዋኖች የሚላቸው ለስብከተ ወንጌል የሚፋጠኑ ሐዋርያትን+ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ በዝቶላቸው ለተልዕኮ የሚተጉትን ደቀ መዛሙርት ነው። «ምናል ባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው፤ ዋኖች ግን መስለው ለሚታዩ ለብቻቸው አስታወቅኋቸው።» ገላ.2+2 እንዲል። አፅግድም ይላቸዋል። ቲቶ2+9። የሰው ልቡና በኑፋቄ እንዳይናወጽ የሃይማኖት ቤቱን በትምህርታቸው ያጸናሉና እነዚህን ሰዎች መርዳት እንዲገባ ያስተምራል።

«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ+ የኑሯቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሏቸው።» ዕብ. 13+7፤ «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው+ ይህንኑ በደስታ እንጂ በጎዘን እንዳያደርጉት+ ይህ የማ ይጠቅማችሁ ነበርና+ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።» ዕብ.13+17 በማለት ይህን ለምን ማድረግ እንዳለብን ያስተምረናል። በዚህ አገልግሎት የተጉትም ተመስግነዋል። «ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ አምን እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ተቀበላችሁኝ። እንግዲህ ደስ ማሰኘታችሁ ወዴት አለ? ቢቻልስ ዓይኖቻችሁን አውጥታችሁ በሰጣችሁኝ ብዬ እመሰክርላችኋለሁ።» /ገላ.4+14/ እንዲል። የቅዱስ

www.zeyeneta.com

www.zeyeneta.com

ጳውሎስን ምስክርነት ማግኘት እንዲት መታደል ነው።

ኢትዮጵያውያን ምእመናንም በዚህ ሥራ የተመሰገኑ ናቸው፡ በትድስት ድንግል ማርያምና በልጇ በወዳጇ ሳይቀር ተመስግነዋል። አሁን አሁን ግን ከመጻሕፍት የተሠወረ የጠፋ ቀለም የሚገኝባቸው መምህራን ያሉብትን ቦታ ካለማወቅ ይመስላል ወንበራቸውን እያጠፉ ጉባኤያቸውን እየዘጉ ለቁመተ ሥጋ ምግብ ወደሚያገኙበት ከተማ እየተሰደዱ መሆኑን ያስተዋለው ጥቂት ሰው ብቻ ነው። አረማውያን በበዙበትና ክርስቲ ያኖችም ባኑበት ያሉ አብያተ ክርስቲያናትንና አገልጋይ ካህናትን የሚያስባቸው ስላጡ አብያተ ክርስቲያናቱን እየዘጉ መጥተዋል። ምእመናኑም ያለ ቀዳሽና ያለ አቁራቢ፣ ጠባቂ እንደ ሌለው መንጋ ተበትነዋል።

ዋኖቻችን ሊቃውንትን ካህናትን በእውነትና በትክክል ክጽንፍ እስከ ጽንፍ ማሰብ ይገባናል። በእግዚአብሔር ቃል ታዝዘናልና።

ለ. <u>ወንድምን መውደድ</u>፡-

«እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፣ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል። ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው÷ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ። እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቷልና በዚህ ፍቅርን ዐውቀናል፣ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል። ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው÷ ወንድሙም የሚያስፈልገውን አይቶ ሲያጣ ያልራራለት ማንም ቢሆን÷ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል? ልጆች ሆይ÷ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በእንደበት አንዋደድ።» 1ኛዮሐ.3÷14-18 እንዲል ፍቅር ያስፈል ጋናል። ያለ ፍቅርም በጉ ምግባር መሥራት ከከፉውም መጠበቅ ይሣነናል÷ አንችልምም። ቅዱስ ጳውሎስም የሚመክረን ይህንኑ

ነው። «የወንድማማች መዋደድ ይኑር። እንግዶችን መቀበል አት ርሱ፣ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀበለዋልና። ከእነርሱ ጋር እንደ ታሠረ ሆናችሁ እሥሮችን አስቡ፣ የተጨነ ቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።» ዕብ. 13÷1-3 ይለናልና።

ሐ. በኑሮ መቀደስ፡-

በጋብቻ የሚኖረውም በብሕትውና በምንኩስና የሚኖረውም በንጽሕና መጠበቅ ይጠበቅበታል። ከዝሙት በመጠበቅ ብቻ ገንዘብን እየወደድን ልንጠቀም አንችልም። ገንዘብንም ጠልቶ ትዳርን ዝሙት ቢያደርጉት መጠቀም አይቻልም። ለሁሉም አግባብና ሥርዓት አለውና በኑሮ መቀደስ ያስፈልጋል። «መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን። ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚ አብሔር ይፈርድባቸዋል። አካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን÷ ያላችሁ ይብቃችሁ።» በሚል ተመክረናልና። ዕብ.13÷4-5። ቅዱስ ጳውሎስም በመጨረሻ በእርሱ አንጻር የአበውን ምክር እንድንቀበል «ወንድሞች ሆይ÷ የምክርን ቃል እንድትታገሡ እመክ ራችኋለሁ÷ በጥቂት ቃል ጽፌላችኋለሁና።» ዕብ.13÷22 ይለናል። ምክሩን ሁሉ በማንበብ ከአበውም በመመከር ልንጠቀም ኑሯችንን በቅድስና ኖረን ተስፋችንን ልንወርስ ያስፈልጋል።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር አሜን ወአሜን፣ ለይኩን ለይኩን።

ቆተፈጸመ።ቆ

www.zeyeneta.com

ዋቢ መጻሕፍት

መጽሐፈ ሰንክሳር /ብራና/

መጽሐፈ ቀሌምንጦስ /ብራና/

ሦስቱ መጻሕፍተ ሥነሥላሴ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማ/ቤት፣ 1982 ዓ.ም

ብርሃኑ ጉበና፣ መራሔ ድኅነት፣ ብራና ማተሚያ ቤት፣ 1995 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ፣ ንባቡ ከነትርጓሜ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት፣ 1988 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ መጻሕፍተ ሐዲሳት ሥለስቱ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት፣ 1989 ዓ.ም

ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ መጻሕፍተ ሰሎሞን መሰረክ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988 ዓ.ም

ትንሣኤ ማኅተሚያ ድርጅት፣ መጽሐፈ ሕዝቅኤል አንድምታ ትርጓሜ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማ/ቤት 1990 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

ቶማስ /ብፁዕ አቡነ/ ፣ ፍኖተ እግዚአብሔር፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1990 ዓ.ም አዲስ አበባ

አያሌው ታምሩ /አለቃ/፣ የኢትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት፣ አርቲስቲክ ማ/ቤት፣ 1953 ዓ.ም

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት፣ 1972፣ አዲስ አበባ

ወንጌል ቅዱስ፣ ንባቡና ትርጓሜው፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1966 ዓ.ም

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ /አለቃ/፣ መጽሐፈ ስዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ፣ 1948 ፣

ዓባይነህ ካሤ /ዲያቆን/፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አንደኛ መጽሐፍ፣ ብራና ማተሚያ ቤት፣ 1993 ዓ.ም አዲስ አበባ

ገድለ አቡሃ /ብራና/

ጉርጉርዮስ /ብፁዕ አቡነ/፣ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ 1993 ዓ.ም፣ አዲስ አበባ

ፍትሐ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1962 ዓ.ም አዲስ አበባ

Aziz S.Atiya. The Coptic Encyclopedia Vol. III. Macmillan Pub. Com. 1991 New youk.

David Noel Freedman (ed) EErdmans Dictionary of the Bible, William I. Eiersdmans pub. com., 2000, Cambridge.

Peter E. Gillquist, The (Fr.) Orthodox Study Bible. Thomas Nelson pub. 1997, Tennessee.

Readers Digest. The Bible Through the Ages. 1996. New York

Shenouda III (H.H.pope) comparative Theology. Coptic Orth. Pub.Asso. 1988 Cairo.

Tadros Y. Malaty (Fr.) The School of Alexandria before Origin (book one). 1994 Jersey city.

www.zeyeneta.com

ሐመርና ስምዐ ጽድቅን

ከቤትዎ አይለዩ

ስለ ቤተ ክርስቲያን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት፣
ስለ ሃይማኖትዎ በሚገባ ለመማር፣
ቅዱሳት መካናትን ቤትዎ ሆነው ለመጐብኘት፣
ከቀደምት አበው ጋር በብዕር ለመገናኘት

ሐመርና ስምዐ ጽድቅን
ከቤትዎ አይለዩ

ሁለቱ ኪዳናት

ለነፍስዎ ሃብ ለማግኘት ያንብቡ

መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

1ኛ መጽሐፍ

2ኛ መጽሐፍ

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በዝርዝር ለመረዳት ሊያነቡት የሚገባ መጽሐፍ

አዘጋጅ:- ዲ.ዓብይነህ ካሤ

ዋጋ :- 1ኛ መጽሐፍ 15.00

2ኛ መጽሐፍ 13.00

www.zeyeneta.com

ከሰይጣን ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ

መንፈሳውያን ልቦለዶች ፣ወጌች፣ግጥሞች ወዘተ

ዋጋ፦ 11.00

ሕግጋተ እግዚአብሔር

አሠርቱ ትእዛዛትን በዝርዝር የሚያስተምር

አዘጋጅ ፦ ቀሲስ አሸቱ ታደሰ

ዋጋ፦ 13.00

www.zeyeneta.com

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለዕብራውያን የጻፈው መልእክት ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ መናፍቃን አጣምመው ሊተረጉሙት በመሞከራቸው የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትክክለኛውን ትርጓሜ እያስተማሩት፣ እየጻፉት ኖረዋል::

በዚህ ዘመንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሊናገረው ያላሰበውንና በጭራሽም ያላስተማረውን ነገር የተለያዩ አካላት እንደመሰላቸው እየተረጎሙ በጎችን ከበረታቸው ማስደንበርያ አድርገውታል:: በዚህም ምክንያት ከትክክለኛው ምንጭ የቀዱት አርቶዶክሳውያን አበው ያስተማሩትን መሠረት በማድረግ ይህ መጽሐፍ መዘጋጀቱ ለወቅቱ ጥያቄ ተገቢ መልስ ነው ብዬ አምናለሁ::

«ሁለቱ ኪዳናት» የተሰኘው ይህ መጽሐፍ በእያንዳንዱ የመልእክቱ ምዕራፍ ላይ የተቀመጡትን ዋና ዋና ነጥቦች በማንሣትና ርዕሰ ጉዳዮችን በማጠቃለል ለማቅረብ ሞክሯል:: ይህ ደግሞ አንባቢው ነጥቦችን በተሟላና በተዘረዘረ መልኩ ለማግኘት ያስችለዋል::

መጽሐፉ በጥልቅ ጥናት፣ በጥሩ አቀራረብ አንባብያን ሊረዱት በሚችሉት መልኩ የቀረበ በመሆኑ የዕብራውያንን መልእክትን አበው በተረጎሙት መልክ ለመገንዘብ ያስችላል የሚል እምነት አለኝ::

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት
የስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ
የጎተመት ዝግጅት ማስተባበሪያ ክፍል ሓላፊ

አታሚ : አፍሮ ማተሚያ ድርጅት
0114 197 446 /47

ዋጋ ብር: 55.00